# ማዕበል

## የአብዮት መባቻ

ከብሃኑ ዘርይሁን

t.me/NooksandYou

Amharic Books t.me/amharicbookss

ምዕራፍ አንድ

«.....አንዳንድ ሰዎች ለአንዳንድ ሁኔታዎች ትክክል ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ሕዝብን የሚያሸብር ሐሰተኛ ወሬ በመንዛት የከተማውን ጸጥታ እያወኩ በሕዝብ ንብረት ላይ ጥፋት አድርሰዋል። እነዚህ ሰዎች እስከ አሁን ለፈጸሙት ተግባር በምክርና በትዕግሥት ቢታለፉም ከጥፋት ስላልተለዩ ይህን ለማገድና ለመከልከል ለጸጥታ አስከባሪዎች ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቷል.....»

ከአገር ግዛት ሚኒስቴር የተሰጠ መግለጫ።

የካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም

በከፊል እንደ ተባዘተ ጥጥ በሳሳና በተበታተነ፤ በከፊል እንደ ቡትቶ ጨርቅ የተድበለበለና የጠቋቆረ ደመና በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ረብቦ ሰንብቷል። የበልግ ዝናብ እያሰለሰ፥ ከበድም ቀለልም አድርጎ ጥሏል። የጠዋቱ አየር ቀለል ያለ ነው። ማምሻውንም ቀዝቀዝ ያለ ነፋስ ከወደ እንጦጦ እየመጣ ቀን ሰፍኖ የዋለውን ሙቀትና ወበቅ ያራግበዋል። ሁለት ቀን ያህል ብቻ ጀንበርዋ በምዕራብ ስትጠልቅ፥ ዙሪያውን ሰማይ ቀን ሻሽ የተጋረደበት ስለመሰለ፥ አንዳንድ ሰዎች እንደ መጥፎ ንግርት ወስደውታል። ከዚህ በተረፈ፥ ለሠርግም ለሽርሽርም ለበልግ አዝመራም የተፈጥሮው አየር የተስማማና የሚያዝናና የካቲት ነበር።

የማኅበራዊና የአካባቢው አየር ግን ሌላ ነበር። እንደ ነበልባል የሚያቃጥል - እንደ ምጥ የሚያስጨንቅ - እንደ ትኩሣት የሚያወራጭ - ጸሐይ ጠልቃ መውጣቷ፥ መሽቶ መንጋቱ እንደማይቀር በተፈጥሮ ሕግ እየታወቀ፥ የበነጋው ውሎ ጨለማ መስሎ የሚታይበት.....

-ባለሥልጣን፥ ሹምና ከበርቴ፥ ማርቼዲሱን፥ ፔጆውን መደበቂኢያ አጥቷል።

-ፈሪው ከግድግዳው ጋር በጭንቀት ይፋጠጣል።

-ጉበዝ፥ ጀግና ነኝ ባይ ብቻውን፥ ይፎክራል። ከራሱ ጋር ይፏከራል።

-ምንም የማያጣው፥ የሚያገኘውንም የማያውቀው ለማኝ ብቻ የዕለት ተግባሩን ቀጥሏል። - ስለ ስማለማርያም! - ስለአዛኝቱ! - ስለ ፍጡነ ረድኤት፥ - ስለገብርኤል - አብዬ አትጨክንብኝ - ለምታልፍ ዓለም።

በየሰፈሩ ሲጢያጢያስ፥ በየሰፈሩ ብልጭ ድርግም ሲል፥ በየሰፈሩ በድንጋይ ውርወራና ግርግር ብቻ ተወስኖ የሰነበተው የሕዝብ ምሬትና ቁጣ አንድ ቀን የአዲስ አበባን አደባባይ በሰልፍ አጥለቀለቀው። ሰልፉ፤ የት እንደ ተጀመረ፥ እንዴት እንደ ተጀመረ ሳይታወቅ ግድቡን እንደሰበረ የውሃ ሙላት በድንገት ገንፍሎ ሲወጣ ብቻ ታየ። የአመጹ ማዕበል፥ ቅርጽም ዓላማም ያለው አይመስለኝም ነበር።

አራት ኪሎን ይዞ የዩኒቨርሲቲና የምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለማውገዝ፥ ሕዝቡ የደረሰበትን በደል በመዘርዘር መፈክሩንና መዝሙሩን ያቀልጡታል፡፡ ቀበና ወንዝ ላይ ሠልፍ፤ ሆታና ድንጋይ ውርወራ ይደባለቃል፡፡ ካዛንቺስ ይተራመሳል ይናወጣል፡፡ ገፈርሳ መንገድ፣ ሾላ ሜክሲኮ አደባባይ ጸጥታ አስከባሪና ሰልፈኛ ይተናነቃል፡፡ በቸርቸል ጐዳና ከቴዎድሮስ አደባባይ ጀምሮ እስከ ላይኛው የትራፊክ መብራት የአውቶሞቢኢል መስታወት ይደቃል፡፡ በተለይ ትልቅ ጦርነት ግን የአዲስ አበባ ከተማ ነበር፡፡ መሐል ከተማውን ለማጥለቅለቅ የተነሣ ይመስል ከእስላም መስጊድ ገንፍሎ የወረደውን ሰልፈኛ ወደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት መዝለቅ ባይችልም፥ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ላይ መሽጎ ትራፊኩንም፥ ጸጥታ አስከባሪውንም ሁለት ቀን ሙሉ ቀጥ አድርጎት ዋለ፡፡ የሥራ አጥ፥ የቦዘኔ የወመኔ፥ የጫማ ጠራጊ፥ የኪዎስክ ነጋዴ፥ የከሠረና በትርምስ የበለጠ ለመጠቀም ዕቅድ ያለው ከበርቴ፥ የእነዚህ ሁሉ ድብልቅልቅ የሆነው ሠራዊተ ሕዝብ ሆ! ብሎ እየተመመ እየተተራመሰ አልፎ አልፎም ንብ እንደገባበት በረት ፈንድቶ አካባቢውን ሁሉ እያመሰ ወደ ፊት በመግፋት ወደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት መውጫ አውራ ጐዳና ሲዘልቅ የእሳት አደጋ ውኃ፥ የጋዝ ጭስ ጥይት በአንድነት ሲወርድበት እንደ ደነበረ መንጋ ለቅጽበት ከተበጠበጠ በኋላ፥ መልሶ ስብስብ ገታ ይልና ያደፍጣል፡፡ ጥቂት አፈፍጎ እንደገና ተከማችቶና እንደ ተለኰሰ ሞተር በሁካታ ተንቀሳቅሶ አሁንም ወደ ፊት ይገፋል፡፡ አሁንም የእሳት አደጋ ውኃ፥ የጋዝ ጭስና ጥይት ይወርድበታል፡፡ እሱም እሱም በበኩሉ ዓይኑን ጨፍኖ ድንጋዩንና በእጁ ያገኘውን ሁሉ ያዘንመዋል፡፡ ሲያይልበት የሰልፈኛው ማዕበል ሻ - ብሎ ይበተናል፡፡

-የአረፋ ዳገት መስሎ የሚወጣ የባሕር ማዕበል ከመሬት ዳርቻው ወይም ከእለቱ ጋር ይጋጫል፡፡ ከፍተኛ ድምፅ ያሰማና ወደ መጣበት ይመለሳል፡፡

-አሁንም እንደገና ኃይሉን አጠራቅሞ እየጐረፈ ይመጣል፡፡ ከወደቡ ላይ ይገታል፡፡ የአቡነ ጴጥሮስ መንገድ በዚህ ማዕበል ይናወጣል፡፡

ወሬ ለመመልከትና ለማዳነቅ በእየአውራ ጐዳናው ዳርቻና በእየአደባባዩ መጋጠሚያ የሚሰበሰበው ደግሞ አንድ ድንጋይ ሲወረወር፥ አንድ ጥይት ሲተኰስ፥ አንድ የጋዝ ጭስ ሲፈነዳ መድረሻ ያጣል፡፡ የጸጥታ አስከባሪው አውቶሞቢል ራሱ የሚፈረጥጥ ይመስል ከመጠን በላይ ይከንፋል፡፡ የእሳት አደጋው መኪና የሕዝብ ቁጣ የሣር ቃጠሎ ይመስል ውኃ እየሞላ ይመላለሳል፡፡

እንዲህ እየተባለ ይዋላል፡፡ ቀን እንዲያ ድብልቅልቅ ሲል ውሎ ምሽት ላይ አካባቢው ጭር ይላል፡፡ ሰው በጊዜ ወደ ቤቱ ገብቶ በበነጋው የሚመጣውን ጉድ በስጋትና በጭንቀት ሲጠባበቅ ያድራል፡፡ አሸናፊው ሳይለይ፥ በዚዒህ አኳኋን ሁለት ቀን አለፈ፡፡ ሰው በየቤቱና በየቤተክርስቲያኑ ስለከተተ፥ ብዙም ቀን አለፈ፡፡ ሽብርና ሁከት ባልታየበት በመካከሉ በዋለው እሑድ ቀን ግን የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በዚህ ማዕበል የቆመበትን ቋጥኝ አሳየ፡፡

የጦር ኃይሎች የሬዲዮ ፕሮግራም ሠራዊቱ ለንጉሡ ያለውን ታማኝነት፥ ንጉሠ ነገሥቱ ለሠራዊቱ ያላቸውን አሳቢነት በመዘርዘር ሐተታ ካቀረበ በኋላ የደመወዝ ጭማሪ መደረጉ ተገለጸ፡፡ በመንግሥቱ ንዋይ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ፥ የወታደር ደመወዝ ጭማሪ ታውጆ ስለ ነበር ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በጊዜው ከሞላ ጐደል የደመወዝ ጫማሪ ማድረግ ግድ ሆኖበት ነበር፡፡ በተነሣው የመንግሥት ግልበጣ ምክንያት በሠራዊቱ ዘንድ የተፈጠረውን አስጊ

ሁኔታ ያረጋጉት ጀነራሎችና ከፍተኛ መኮንኖችም ከሃምሳ ሺህ እስከ መቶ ሺህ ጉርሻ ተቀብለው ነበር። ከዚያ ወዲህ በሠራዊቱ ንቅናቄ ምክንያት የደመወዝ ጭማሪ ሲደረግ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር።

ሕዝቡም በየበኩሉ ሲወያይበትና ሲተቻችበት ዋለ፦

-ኃይሌ በአቋራጭ ከዚህ ጭንቅ መውጣቱ ነው መሰለኝ።

-እስቲ እያናለን።

-ሠራዊቱ በዚኢህ ከተደለለማ ጉድ ነው።

-እሱምኮ በየበረሃውና በእየጠረፉ ሲሠቃይና ሲቸገር ኖሮአል።

-አሁን ደህና የተያያዘው እንዲከሽፍ መደረግ የለበትም። ሕግቡም አሁን እንዲህ በቀላሉ የሚመለስ አይመስለኝም።

-እሱም ነው።

ማምሻውን ደግሞ ተጨማሪ ሁኔታዎች ታዩ። ንጉሡ፥ በራዲዮና በቴሌቪዥን ንግግር አደረጉ። ቴሌቪዥን የተመለከቱ ሰዎች፥ ሥልጣናቸው የማይገሠሥ የማይደፈር ፍጥረት ከፊታቸው የሚንቀጠቀጥ ከጠላታቸው በመለኮት ኃይል የሚፈርጥ፣ እኒያ ፈላጭ ቆራጭ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን ማመን አቃታቸው። አንዳንድ የውጭ አገር ጸሐፊዎችና ጋዜጦች ያደነቁላቸው ዓይኖቻቸው እንደ ሰካራም ዓይን ቦዘዋል። ፊታቸው ከመቃብር የተመለሰ አስከሬን ያህል ጠውልጓል። ድምፃቸው ደክሟል። የሰማኒያ ሁለት ዓመት ሽማግልና በአንድ ሰሞን ድንገት የተጫናቸው ይመስላል።

«ለሚወዱት» ሕዝባቸው ንግግር እንደሚያደርጉ ሳይሆን፥ ስለ ምን ለምን እንደሚናገር የማያውቅ ሰው፥ ወይም በራሱ የሰመመን ዓለም ውስጥ እንደሚወራ የጃጀ ሽማግሌ ከፊታቸው የቀረበውን ወረቀት እየተንተባተቡ አነበቡ። በአነበቡት ጽሑፍም የተጨመረው የቤንዚን ዋጋ ከሰባ አምስት ሳንቲም ወደ ስድሳ ሳንቲም ዝቅ ማለቱን የመምህራን ደሞዝ ጉዳይ በአንድ ወር ግዜ ውስጥ ውጤት እንዲያገኝ መደረጉን የዋጋ ቁጥጥር በሥራ ላይ የሚውል መሆኑን፥ በቀኑ የጦር ኃይሎች ፕሮግራም የተገለጠው የመለዮ ለባሹ ደመወዝ ጭማሪ ከሁለት ሳምንት በኋላ በሥራ ላይ እንዲውል መወሰኑን አስታወቁ። የንግግራቸው አቀራረብ ምናልባትት ሥልጣን ከያዙ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የመማጠን ዝንባሌ ቢኖረውም የአድማጭን የማያሳምን ከታከተ አንደበት የሚወጣ ግዑዝ ቃላት ብቻ ነበር። በአጠቃላይ ያሳደረው ስሚዔት «የራሳችሁ ጉዳይ ነው። እኔን ብቻ ተውኝ አታስቸግሩኝ» የሚል ዓይነት ነበር።

የንጉሡን ንግግር በማንተራስ፤ በዚሁ ምሽት ከአገር ግዛት ሚኒስቴርና ከመከላከያ ሚኒስቴር ተጨማሪ መግለጫ ተሰጠ። የመከላከያ ሚኒስቴር መግለጫ ሠራዊቱ በተደረገለት ጭማሪ የንጉሡን ውለታ ተረድቶ ታማኝነቱን እንዲያጠናክር የሚያስገነዝብ ሲሆን የአገር ግዛት መግለጫ ደግሞ፥ ከሰሞኑ ሽብር የደረሰው ጥፋት የሚዘረዝር ነበር። በሰባ የግልና በሰባት የዲፕሎማቲክ አውቶሞቢሎች፥ በሁለት ባቡሮች በሠላሳ ስምንት ቤቶች ላይ ጉዳት ደርሶአል

ተባለ። ከዚህ ጋር አብሮ ያልተገለጸው ግን በከተማው እንደተወራው ቢያንስ - ቢያንስ አራት መቶ ሰዎች መታሠራቸውና ከአምስት በላይ መሞታቸው ነበር። አብዛኞቹ ታክሲ ነጂዎች ናቸው ይባላል።

ሰኞ ሁኔታው ትንሽ ሻል ያለው መሰለ። በጣም አስፈላጊ የሆኑ ቁልፍ ቦታዎች ከመጠበቃቸው በቀር፥ በተዘዋዋሪ የጥበቃ ጓዶች ወደ ስፍራቸው ተመለሱ። ሱቆቹ ከሞላ ጐደል ተከፈቱ። ሰይንቸንቶችና አውቶብሶች መንቀሳቀስ ጀመሩ። ወዲያውኑ የሸፈተውን የሕዝብ አእምሮ መልሶ ለመግረክ ከፍተኛ ዘመቻ ቀጠለ። የጦር ኃይሎች ተወካዮች፥ የአገር ሽማግሌዎች፥ የሕዝብ ተጠሪዎች የተባሉና ነጋዴዎች ከንጉሡ ፊኢት እየቀረቡ ምስጋናቸውንና ታማኝነታቸውን መግለጻቸው ሁለት ሙሉ ቀን ተለፈፈ። መምህራን ሥራ ማቆማቸው፥ ወጣቶች ጸጥታ ማበላሸታቸው፥ ታክሲ ነጂዎች ነገሩን ማባባሳቸው ተወገዘ። ለአጭር ጊዜ መንግሥት ፈተናውን ለመወጣት የሚችል መስሎ ታየ።

-ጉድ ነው! እንዲህ እንደ ተጨማለቁብን ሊቀሩ? ይላል አንዱ

-ምን ታደርገዋለህ? ይላል ሌላው።

-በፍጹም! አይምሰልህ፥ ለጊዜውው ድረስ ብቻ ነው፥ ይላል ሦስተኛው።

የሰዎች ሐሳብና ምኞች ሲዋልል ውሎ አደረ።

ለውጥ ፈልገው ለተጠራጠሩት፥ ለውጥ ፈርተው ሁኔታው እንደሚረጋጋ ተስፋ ላደረጉት ምሥራችና መርዶ በድንገት ዱብ አለ።

የጠቅላይ ግዛቱ የታማኝነት መልዕክት ያጎርፋል ያልተባለውን ያህል፥ የአገር ሽማግሌዎች የሕዝብ ተጠሪዎች የልዩ ልዩ ኅብረተሰብ አውራዎች የጦር ኃይሎች በተለይም የሰሜን ክፍለ ጦር ተወካዮች ከአንድ ቀን በፊት በታላቁ ቤተ መንግሥትና በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ከንጉሡ ፊት እየቀረቡ ታማኝነታቸውን ገለጹ ያልተባለውን ያህል የሰሜኑ ሁለተኛ ክፍለ ጦር ንቅናቄ አገረሸበት። እንደገና የአሥመራን ከተማና የአውሮፕላን ጣቢያውን በቁጥጥር ሥር አደረገ። የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ተላኩ። እነሱም በቁጥጥር ሥር ዋሉ።

አሁን በጦር ኃይሎች አካባቢ ሁኔታው እየተባባሰ ሄደ። የባሕር ኃይል ወታደሮች ከሁለተኛው ክፍለ ጦር ጋር መተባበራቸውን ስለአረጋገጡ የባሕር ኃይል አዛዥ የሆነው የንጉሡ የልጅ ልጅ ከምዕዋ በጀልባ አመለጠ። የሌሎች ክፍለ ጦሮች ትብብር እየተጠናከረ መጣ። መልዕክቶች በኢትዮጵያ አየር ላይ ከጦር ሠፈር ወደ ጦር ሠፈር ተሰራጩ።

ታላቁ ቤተ መንግሥትና ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት በራሳቸው ተረት ተረት ታሪክ ተሸፋፍነው ተኙ።

በበነጋው ጠዋት በርከት ያሉ የጦር ኃይልና የፖሊስ አባሎች በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ከንጉሡ ፊት ቀረቡ። መሳፍንቱ፥ መኳንንቱና ሹማምንቱ ከንጉሡ ጀርባ ዙሪያ ከበው የጦር ኃይልና የፖሊስ አባሎች ከፊት ለፊት ቆመው ተፋጠጡ። ብዛታቸው ሲታዩ በተለይም ያልታጠቁ ስለሆኑ በዚያ በነበሩት አንጋቾች በቀላሉ በቁጥጥር ሥር ሊውሉ ይችሉ ነበር። ግን

ሁሉቱም ወገኖች ገና ኃይላቸውን በመፈታተሽ ላይ ነበሩ። ከአባሎቹ አንዱ ሰላምታ ሰጥቶ አቤቱታውን ከአነበበ በኋላ ዓቃቢ ሹሙ ጠጋ ብለው ንጉሡን በጆሮአቸው አማከሯቸው። ንጉሡም ካባቸውን እንደማጣፋት አድርገው፤ «ለተወደደው» ሠራዊታቸው ደኅንነት የሚያስቡ መሆናቸውን ገልጸው፣ ነገር ግን ኢትዮጵያ አቅም ስለሌላት የበለጠ ጭማሪ መጠየቅ እንደ ማይቻል አስገነዘቡ። ንግግራቸውን ለሚያዳምጠው፥ ማጕመትመት ብቻ ነበር። ትዕዛዙንም ምክሩንም እንደ ፈለገ ያስተረጕመው ሌላ ነበር።

የጦር ኃይሎች ሌላ ጥያቄ ማቅረባቸውና በመንግሥት በኩል ተቀባይ አለማግኘቱ እንደ ተሰማ የአዲስ አበባን ከተማ አዲስ ውጥረት ለተቀቀባት። መንግሥት ግን ድክመቱን የሞት ሽረት ጭንቀቱን በተለይ ለውጨኛው ከዓለም ለማሳየት ስላልፈለገ፤ ዓለም ሰላም እንደሆነ ሁሉ ከሰዓት በኋላ ንጉሡ የአፍሪኢካ አንድነት ድርጅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችን ጉባዔ በንግግር እንዲከፍቱ ተደረገ።

-ክቡራን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች።

-ክቡራን የተባበሩት መንግሥታትና ሌሎችም ዓለም ዓቀፍ ድርጅት ወኪሎች

-ክቡራን እንግዶች፦

ጥንታዊ ታሪክ ባላት ሀገራችን፤ በዚች አገር ዋና ከተማ ስንቀበላችሁ ከፍተኛ ደስታና ክብር ይሰማናል። በጥርጣሬ የተንጠባጠበ ጭብጨባ ያስተጋባል። ንግግሩ ሲያበቃ፥ የጉባዔው ተጠሪ የመልስ ንግግር ያደርጋሉ።

-ግርማዊ ሆይ! በዚች ታሪካዊ አገር ግርማዊነትዎና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ስላደረገልን መስተንግዶ በጉባዔው አባላት ስም ምስጋናዬን እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ!

ከበፊቱ ደመቅ ያለ ጭብጨባ ያስተጋባል። በአፍሪካ አዳራሽ ወንበር ላይ የተቀመጠው አባልና ተመልካች ሁሉ እንደወትሮው የተዝናና አለነበረም። በተመለከተውና በእየኢምባሲው አካባቢ ባገኘው መረጃ መሠረት፣ ከሚፈነዳ የእሳተ ገሞራ አናት ላይ የተቀመጠ መሆኑ እየተሰማው ሐሳቡ ብቻ ሳይሆን ሰውነቱ ጭምር ይቁነጠነጣል።

የጉባዔው መክፈቻ ሥነ ሥርዓት ሲያልቅ፥ ንጉሡም መልዕክተኞቹም በእፎይታ ተለያዩ።

አብዛኛው የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ግን በኢዮቢኤልዩ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት ስለሚካሄደው ሥነ ሥርዓት ቅንጣት ደንታ አልነበረውም። በራሱ ጭንቀት፥ በራሱ ቁጣ፥ በራሱ ስጋት ተውጥሮ ነበር።

ማታውኑ ብዙ ሰው ያልጠበቀው ነገር ደረሰ።

## ፪

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ትልቁ ፎቴ ላይ በትራስ ተደጋግፈው ተጋድመው ከንፈራቸውን በጥፍራቸው እየቀነጣጠቡ አሥር ጊዜ ሰዓታቸውን ያያሉ። ማናዬ ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ቋንጃውን



Amharic Books t.me/amharicbookss

አጣጥፎ ተቀምጦ ግድግዳውና ጣሪያውን እየተመለከተ ቀኝ ቋንጃውን ይሰብቃል። ቤቱ ካለወትሮው ቅዝቅዝ - ጭር ብሏል። ሁለቱም በየእራሳቸው ዓለም ውስጥ ይዋልላሉ።

«ምን ይዘጋሃል! አትናገርም» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ደነፉ፥ ድንገት ቱግ ብለው።

«ምን ልናገር?» ሲል ማናዬ ምለሰ፥ ግራ ተጋብቶ።

«ቢያሰኝህ ግን የመገበሪያ ስንዴ እንደበላ ሌባ ያስለፈልፍህ ነበር» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በማሽንጠጥ።

ማናዬ መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ። ሐሳቡ እልሃቸውን ለማስጨረስ ነው።

በመካከላቸው ኩርፊያ ከተጀመረ ብዙ ቀኖች አልፈዋል።

ከደሴ መልስ ሾላ ላይ ተማሪዎች ባዘነቡት ድንጋይ የአውቶሞቢላቸው የፊት መስታወት ሲከሰከስ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እስከዚህም አልተጎዱም ነበር። ግንባራቸው ላይ የመስታወት ፍንጣሪ ትንሽ የፈነከታቸውን ቁስል ቁስል ዘመዳቸው ዶክተር ጐሽሜ በቴሌፎን ተጠርቶ መጥቶ ከአከመላቸው በኋላ ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለበት በመግለጽ የእንቅልፍ መርፌ ወጋቸው። ሕሊናቸውን እስከ መሳት አድርሶአቸው የነበረው ድንጋጤ በእንቅልፍ አልፎላቸው በበነጋው ሲነቁ መነጫነጭና መብሰክሰክ ጀመሩ። ድንገት አድሮባቸው የነበረው ፍርሃት «እንዴት ተደፈርኩ?» ወደሚል ቁጭት ተለወጠ። ድንጋይ የወረወሩባቸውን «ኩታራዎች» የተበቀሉ ይመስል የቤቱን ሰው ሁሉ ያመናጭቁ ገቡ። የምላሳቸውና የዓይን ግልምጫቸው ዋና ማረፊያም ማናዬ ሆነ።

«ቊጭ ብለህ በማተ አስደበደብከኝ አይደል? ምናለ!» አሉ ገና በነገር ሲጀምሩት። ከመርፌው እንቅልፍ እንደነቁ የበሽተኛ ምግብ ቀቦላቸው በመሰላቸት እኳኋን ይቀነጣጥባሉ። ማናዬ እንደ አስታማሚ ከአጠገባቸው ተቀምጦ ነበር። በርግጥም ከደሴ እንደ ተመለሰ ወደ ቤቱ ሳይሄድ በዚሁ ውሎ በማደር ባል - አከል አስታምሟቸዋል። የቤተ ሰቦቹን ደህና መሰንበት ስንኳ ቴሌፎን ደውሎ አልጠየቀም። በአንድ በኩል አዲስ አበባ መመለሱን ከአወቁ ለምን ቤቱ መጥቶ አያድርም ብለው እንደሚጠይቁት ተሰማው። የድንጋጤ በሽተኛዋን ትቶ ቤቱ ማደር ደግሞ ጥሩ መስሎ አልታየውም። የአውቶሞቢሏን የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቀስ ብሎ በስሙ የሚዛወርበት ሁናቴ እስኪፈጠር ቃል የሰጡትን አንድ ሸህ ካሬ ሜትር ቦታ ከእጁ እስኪያስገባ ማባበል ይኖርበታል። እንደዚህ ያለው ችግር ደግሞ አሳሳቢነቱና ታማኝነቱ እይሚኢፈተንበት ወቅት ነው። ማናዬ በዚህ ፈተና ሊወድቅ አልፈልገም። ነገር ግን፥ የፀጥታ እንቅላፋቸውን እንዳያውክ ከአልጋዉ ጠርዝ ተኮራምቶ አድሮ ጠዋት ብድሩ ዘለፋ ሆነ።

«ታዲያ መቼስ ምን ይደረግ ብለሽ?» ሲል ነገሩን በማቃለል መለሰላቸው።

«ምን ይደረግ?» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የማሽሟጠጥ ሳቅ ሳቁ። «እኔ በመንጋ ዱርዬ ስደበደብ ምን ይደረግ ትላለህ? ሽጉጡን እንድትይዘው የሰጠሁህ ለአይጥ ማባረሪያ መሆኑ ነው?»

ማናዬ መስል ሳይሰጥ ንዴቱን ለማብረድ ሳሎን ክፍል ሄዶ ተቀመጠ። ሳይጠይቅ፤ ሳይፈልግ፤ ቋንጣውም፤ ጭኮውም እየቀረበለት ሲያመነዥክ፤ ቆየ። ከረፋዱ ላይ አስጠሩትና ሌላ ግልምጫ አወረዱበት።

«ምን ዝም ብለህ ቁጭ ትላለህ? መኪና አታመጣም?» አነጋገራቸው ጥየቃ ሳይሆን ትዕዛዝ ነበር። «ቤተ መንግሥት፥ ቤተ ክርስቲያንም እሄዳለሁ። ዘመድም እጠይቃለሁ።»

ማናዬ መኪና በአንድ አፍታ ከየት እንደሚያመጣ ግራ ገብቶት ጥቂት አሰበ። በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ፔጆ በመተማመን የራሱን አሮጌ ኦፔል መኪና ከጥቂት ወራት በፊት ሸጦአል። የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ፔጆ የተሰበረው መስታወት ሳይለወጥ ከግቢ እንደቆመች ናት። ብትሠራም ኖሮ ለጊዜው ሊጠቀሙባት አይችሉም። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል መኪና እንዲፈልጉ ያዘዙትም ለዚሁ ነበር። በእርሱ ላይ የሚጨፍሩትን ያህል በአፋቸው የሚያቃልሏቸውን «መንጋ ዱርየዎች» አሁንም በመፍራታቸው ራሱ የተቀበላቸው ይመስል ደስ አለው። ወዲያው ግን ሐሳቡ ወደ መኪናው ጣጣ ተመለሰ። «የዘለቃ መኪናስ?» ሲል በለዘብታ ጠየቃቸው።

«ቁልፉን ይዛ ነው የሄደችው። ደግሞስ ትዳራቸውን ከያዙ በኂላ ከእነሱ ዕቃ ምን አገባን? ራስን መቻል ነው።» ቀድሞውንም መኪናውን ሲሸጥ አስቀድሞ ያላማከራቸው ስለ ነበረ አልፎ አልፎ በነገር ዳር - ዳርታ ሲነካኩት ቆይተዋል። አሁን ግን አነጋገራቸው ከሞላ ጐደል ቀጥተኛ ነበር። መኪና ከየትም ፈልገህ አምጣ ነው። የሚፈልገውን እስኪያገኝ ድረስ ምርጫ አልነበረውም። ክፉ ቃል ሳይመልስ መኪና በውሰት የሚያገኝበትን መንገድ እያሰላሰለ ጥሏቸው ወጣ።

በመጀመሪያ የጠየቀው የመሥሪያ ቤቱን የሰርቪስ ኃላፊ ነበር። «እስቲ ተቸገርልኝ!» አለው ቢሮው ድረስ አስጠርቶ።

«ምን ከፍቶኝ ታዛኝ ነኝ።»

«በል እንግዲያ ለጥቂት ቀን፤ ለአንድ ሁለት ቀን መኪና አውሰኝ።»

«አዬ! የታለ መኪና!» ሲል የሰርቪስ ክፍሉ ኃላፊ ራሱን ይነቀንቃል።»

«አዬ አቶ ማናዬ! የት ከርመው መጡ! አንዳቸውም የሉም።

«የት ሄዱ!»

«አንድዋን ክቡር አቶ ድፋባቸው አንድዋን ምክትል ሹሙ» የሰርቪስ ኃላፊው በጣቱ ይቆጥር ገባ። «አንድዋን ክቡር አቶ ድፋባቸው ባዘዙት መሠረት ለብሩ አቶ ጓንጉል አንዱዋ ፋዞ ሆና ጋራዥ ነው ያለችው።»

«የእነርሱ ማርቸዲሶች ምን ሆኑባቸውና ነው አርጌ የሽማኔ ጉድጓድ ያሰኛቸው!» ሲል ማናዬ የማያውቃት ይመስል በቀልድ መልክ ጠየቀ።

«አዬ አቶ ማናዬ? እርስዎስ ለምን ፈለጉ?» የሰርቪስ ኃላፊው ጥያቄ የቀልድ አሸሙር ነበረበት።

«እኔማ ሲያቅበጠብጠኝ መኪናዬን ሸጨ ነው።» - ታዲያ እንደሌሎቹ ፈርቼ መሰለህ? - ሲል ቃጣውና ነገሩ ከአለቆቹ ጆሮ እንዳይገባ በመጠርጠር መልሶ ተወው። «ለመሆኑ ምንም አትረዳኝም ማለት ነው?» ሲል በማቆላመጥ ጠየቀ።

«ካለ ለእርስዎ ያልሆነ ለማን ሊሆን ኖሯል?» አለ የሰርቪስ ኃላፊው በመቂ ቀበሌ አንድ ጋሻ መሬት እንዲያገኝ ረድቶት ስለ ነበር ባለውለታ መሆኑን በመግለጽ።

«ከሌለ መቼስ ምን ይደረጋል?» ሲል አስናበተውና ለጥቂት ጊዜ የብስጭት ሐሳብ ገባው። ያበሳጨው መኪና ለማግኘት አለመቻሉ ብቻ አልነበረም። የቢሮው አካባቢ ሁናቴም በጣም የተለዋወጠ ሆኖ ተሰማው። የሰርቪስ ክፍል ኃላፊው ላይ ላዩን ትህትና ያሳየ ቢሆንም፥ እንደወትሮው ከልቡ ያለ መሆኑ ያስታውቅ ነበር። ተላላኪዎቹም ቢሆኑ ለወጉ ያህል እጅ ቢነሱትና ሲጠራቸው ቢመጡም አስተያየታቸው ትኑ አልመሰለውም። ወይ ጥላቻ ወይ ንቀት የሰፈነባቸው ይመስላል። ሌሎች የበታች ሠራተኞች በየበኩላቸው ይንሾካሾካሉ። ብዙ ኃላፊዎች በሥራ ገበታቸው ላይ የሉም። እንደ ልጆች የድብብቆሽ ጨዋታ በመሥሪያ ቤቱ ግቢ ሁሉም በየበኩሉ ያደባበት አንድ ዓይነት ደፈጣ እንዳለ ተሰማው። ማናዬ ፊቱን ኰስኩሶ እንደ መወራጨት እየቃጣው ወጣና ደንበኛው ወደ ነበረው ጋራዥ ሄደ።

«አሄሄ! አቶ ማናዬ!» አለ ባለጋራዡ ጥያቄውን ካዳመጠ በኋላ «አሮጌ ቮልስዋገንማ ጨው ሆኖ የለም! ይገርምዎታል አንድ ወግ ዕቃ የተቀመጠጭ አንዲኢት የጣሊያን አርዱታ ነበረችን። በአንድ ቀን ታድሳ ትድረስልኝ ተብዬ ማመን የሚያቅትዎት ዋጋ አወጣች። እነዚህ ሁለቱ ነገ የሚወስዱ ቀብድ የተከፈለባቸው ናቸው።» ሁለት የከረከሱ ሰይቼንቶዎች አሳየው። ስንት ስንት ሽጥኒቸው ይመልዎታል? ይችን ሶስት ሺህ አምስት መቶ፥ ይችን አራት ሺህ አንድ መቶ። ትላልቅ ሰዎች ናቸው። ዓይናቸውን አላሹም! ይህን አውቄ ቢሆን ኖሮ አንድ ሰላሳ አሮጌ መኪና ሰብስቤ ይኸኔ ሚሌነር ነበርኩ። ድንገት ሆነ።»

«የአንተን ሚሌኔርነት ተወውና አሁን እኒኤ ምን ተሻለኝ?» ሲል ማናዬ ኰስተር ብሎ ጠየቀ።

«አዬ አቶ ማናዬ! አሁን ማ - ይሙት ከሆነ በእርስዎ እለግማለሁ?» ባለጋራዡ ችላ ብሎት ወደ ጥገናው ሥራ አመራ።

ማናዬ በሸቀ። አሁን እንደ አቶ ድፋባቸው ከፍተኛ ሥልጣን ቢኖረው ከየትም ወልዶ ያመጣለት ነበር።

ወደ ሌሎች ጋራዦች ሄዶ ያገኘው የማይጥም ቀልድ ነበር።

-ስም ተለውጦአል ጌታው! አሮጌ መኪና አይባልም። ሰነፍ አድን ነው የሚባሉት - ይላል አንዱ።

-እኔ የምፈራው - ይላል ሌላው - በየግቢው የተደበቀው ማርቼዲስ ይፈተሽና የተረቱ ነገር እንዳይደርስ ነው።

-የምን ተረት? - ማናዬ ሳይወድ ይጠይቃል።

-ተረቱማ እንደ አሁን የጭንቅ ጊዜ አንዱ ነፍሱን ለማዳን የሴት ቀሚስ ለብሶ አፈር ሲያቋርጥ አንድ ጎበዝ ያገኘውና አስቁሞ ይጠይቀዋል። ምንድን ነህ? ኧረ እኔ ሴት ነኝ! የተጠራጠረው ጉበዝ፤ ወስላታ! በማለት ቀሚሱን ወደ ላይ ገለብ ሲያደርግበት አንድስ የሚያክል ጉድ የቀትር እባብ መስሎ መገኘት! ይኼ ታዲያ ምንድን ነው? ብሎ ቢያፋጥጠው ካለዛሬም አላየሁትጥ አለ ይባላል።

ማናዬ የተረቱ አሽሙር እርሱም የሚጠቅስ መሆኑ እየተሰማው አቋርጦት ሄደ። የባሰውን ያበሸቁት ደግሞ ታክሲ ነጂዎች ነበሩ። አንዱ ሹፌር፥ ማናዬ በሩን ከፍቶ እንደ ተሳፈረ ያልፈለገውን ሰላምታ ያስቀድምለትና «ታዲያስ እንዴት ነው አገሩ? እኛ ይኸው እየወደቅን እየታገልን እየታሠርን ከዚህ ደርሰናል። ትናንት መሬት መርገጥ ይጠየፉ የነበሩ ቀብራሮቻችን ዛሬ ድመት እንደመጣባት አይጥ መግቢያ ቀዳዳ ጠፏቸዋል። መቆየት ደግ ነው። ነገ ደግሞ ሌላ ጉድ እናይ ይሆናል» ይላል።

ሌላው አንድ ከበርቴ ጉረቤት እንደ ዓይኑ ብሌን የሚጠነቀቅላት ማርቼድስ መስተዋቷ ተከስክሶ አጉን የእርሱ ደንበኛ ሆነው መሰንበቻቸውን ይተርካል - ይኸኔ ድንጋይ ወርዋሪው አንተ ትሆናለህ - ይላል ማናዬ በሆዱ። አንዳቸውንም ሳያነጋግርና መልስ ሳይሰጥ ስሙኒውን ከፍሎ ይወጣል።

በዚህ ዓይነት አራት ጋራዥ አዳርሶ ከአምስተኛው ላይ የመቀመጫዋ ሽቦ የወጣ ከርካሳ ሬኖ አገኘ።

«ለመግዛት ነው ኪራይ?» ባለጋራዡ ጠየቀው።

«የሁለቱንም ልስማው።»

«የሽያጩ ዋጋስ የክብድዎታል።»

«ስንት ትላታለህ?»

«ሞተሯ ጥይት ነው። ወንበሯን በሙቶ አምት ብር ባሳድሳት ሰባት ስምንት ሺህ ዓይን ሳይታሽ ታወጣለች።»

«ምን?» ማናዬ እንደ መጮህ ቃጣው።

«ጊዜው ያመጣው ነው።»

«እሺ በኪራይስ?»

ባለ ጋራዡ ጸጉሩን እያካከከ ጥቂት አሰላሰለ «በቀን ሃምሳ ብር ለአሥር ቀን አምስት መቶ ብር ይከፍላሉ። ዛሬ ጊዜ የሚሆነው አይታወቅምና ከአሥር ቀን በኋላ ሌላ ውለታ እናደርጋለን።» ከብዙ ክርክር በኋላ በ፫፻፶ ብር ተስማምተው ፔጆዋ ሰርቪስ እየተደረገችና መስታወቱ እየተጠመ ለዋስትና ከጋራዡ እንድትሰነብት ተደረገ።

በማግሥቱ ጠዋት ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤተ ክርስቲያን እንዲያደርሳቸው አዘዙት። ያችኑም ስንት ተንከራትቶ ያላገኛትን ያህል ከመኪናዋ ሲገቡ በመጠየፍ ፊታቸውን አጨፍግገው «ምኑን ጣለብኝ እባካችሁ። በእግር መሄድ በስንት ጣዕሙ!» አሉ።

በመንገድ ላይ እንዳሉ ደግሞ «የት ነው የምትነዳው ቤተ መንግሥት እኮ ነው የምሄደው» አኢሉ ደነፉ።

«ቤተ ክርስቲያን ስለ ተባልኩ ነዋ!»

«ታዲያ ቤተ መንግሥት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የለም?» በዓይናቸው ገረፉት።

ማናዬ ጥርሱን በንዴት እያፋጨ ነዳ። ውሉ ባለየለት በአሁኑ ቀውጢ ጊዜ በጠዋት ቤተ መንግሥት ሲገቡ በሰላይነት መጠርጠርን ሊያመጣ ይችላል። በመንግሥት ላይ የተነሡት ክፍሎች በየቦታው ታዛቢና ተከታታይ ሳያደርጉ ይቀራሉ? ራሳቸው ዘቦችስ ቢሆኑ መቼ ይታመኑና።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በበኩላቸው ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ቢል የማይቀብሩት ነገር ነበር። በቤተ መንግሥት የተፈሳው ሁሉ የማያመልጣቸው ወይዘሮ ሽዋዬ ማታውኑ ደውለው ንጉሡ የሚያስቀድሱት በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ በምትገኘው በደብረ መንክራት ሥዕል ቤት መሆኑን ነግረዋቸው ነበር። ያልተለመዱ በመሆኑ ነገሩ ከነከናቸው። እንደ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ፍላጎትና አስተሳሰብ ቢሆን ኖሮ ወጣ ብለው ለሕዝባቸው በታዩና በተቀባው ሰውነታቸው ባረጋጉት መልካም ነበር። ነገር ግን ከንጉሡ ልቦና የሚሠወር ነገር የለምና በሥዕል ቤት የሚያስቀድሱበት ምክንያት ሳይኖር ይቀራል? በሥፍራው ተገኝተው ማየት መስማትና ማወቅ አለባቸው። ከዚህም በተረፈ እጅ ከነሡና ፊታቸውን ካዩት ብዙ ጊዜ ሆኗል።

ነገር ግን እንዳሰቡት አልሆነላቸውም። መጀመሪያ ልዩ ፈቃድ ያስፈልጋል በማለት የእልፍኝ አስከልካዩ እንዳይገቡ አገዳቸው። «እኔ ዘርፈሽዋል ነኝ ከጌታዬ ግቢ የማልገባው? እልፍኝ ውስጥ ውስጡን ያቃጠላቸው ግን የእርሳቸው ቤተ መንግሥት ሥዕል ቢኤት አለመግባት ሳይሆን ድንገት ወይዘሮ ሽዋዬ ተፈቅዶላቸው እንደ ሆነ በማለት ነበር። በዘር ከሆነ ከማን ያንሳሉ! አዲስ የጸጥታ አጠባበቅ መመሪያ በመስጠቱ እንጂ የቤተ መንግሥት ባለሟል መሆናቸውን ወትሮውንም የሚያውቀው የእልፍኝ እስከልካዩ መልሶ በማባባል አሳለፋቸው።

ከውስጥ ንጉሡ በግል እንደሚጸልዩበትና እንደሚያስቀድሱበት ጊዜ ሳይሆን ሥዕል ቤቱ ተጣቦ ነበር። እገሌ የተባለ መኳንንትና መሳፍንት ሁሉ ተገኝቷል። አስቀድሞ የደረሰው ሁሉም በየደረጃው በመኮልኮል ሥፍራውን ይዞ ስለ ነበር ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከወደ ዳር ቦታ ተሰጣቸውና በዓይናቸው ሁሉንም ይቃኙ ጀመር። ንጉሡ የሁለት እጃቸውን አውራ ጣትና ሌባ ጣት ከእምብርታቸው ሥር እንደ ቀለበት በመሥራት ቀጥ ብለው ቁመው ማንንም የሚያዩ አይመስሉም። ዓይናቸውን ገርበብ አድርገው ፊታቸውን ብቻ ለሥዕል ቤቱ ቤተ መቅደስ ሰጥተዋል። የካህናቱን የቅዳሴ ሥርዓት አልፎ አልፎ በመመልከት ከንፈራቸውን ያንቀሳቅሳሉ። አንገታቸውንም ደፋ ያደርጋሉ። በተረፈ ግን ስንኳን ትኩረታቸው ሐሳባቸው በቦታው የለም። በመላ ሰውነታቸውም ተንቀሳቃሽ ሕይወት የለም። ከፊታቸው ጀምሮ የራሱን የተፈጥሮ አካል መሸከም አቅቶት አልፎ አልፎ ሲንቀጠቀጥ እስከሚታየው በርካቸው ድረስ ሥሩ ተነቅሎ

የጠወልገ ቅጠል ይመስላሉ። መኳንንቱ መሳፍንቶቹና፣ ሹማምንቱ ሁሉ መቋሚያቸውን ተደግፈው እንደተነፈሰ ጐማ ሙሽሽዋል። ትንሽ ደረቱን ነፋ፥ አንገቱን ቀና አድርጎ የቆመው እስከ ጥቂት ዓመታት ድረስ አገረ ገዥ ሆኖ ከቆየ በኋላ ዓቃቤ ሹም ጐንጤ ሥልጣኑን ለማደላደል በጎነጎነው ሤራ ሊቀ መኳስ የሆነው የአልጋ ወራሹ ተቀናቃኝና የመሳፍንቱ ቀንደኛ መሪ የሆነው ራስ ዝማነህ ብቻ ነበር። አልፎ አልፎ የሹማምንቱን አካባቢ በዓይኑ ይገረምማል። ዓቃቤ ሹም ጎንጤም በዚያ ጉጉት ዓይኑ እያሸለቀ ያየዋል። በሁለቱ መካከል ያለው የጥላቻ ስሜት ግልጽ ነበር።

ቀሳውስቱም እንድ ሰይቸንቶ ነጂዎች ያደሙ ይመስል ቅዳሴው ሳያምርበት ከአንድ ሁለት ሰዎች የተቆራረጠ እልልታ በስተቀር ዑደት ሳይደምቅ አለቀ። በሬ የዋጡ የሚመስሉት ሊቀ ካህናት ቡራኬ ሰጥተው ሠርሆተ ሕዝብ እንደ  ሆነ፥ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ምኑም - ምኑ ደስ ሳይላቸው ንጉሡንም በሚገባ እጅ ሳይነሡ ወጥተው ከመኪና ውስጥ ሲገቡ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ። ልቅሷቸው ግን ለተከዙት ለፈዘዙት ንጉሥ፥ መሳፍንትና መኳንንት ሳይሆን በአብዛኛው ለራሳቸው ነበር። ሆደ - ባሽነት ተሰምቷቸዋል። በተለይም ወይዘሮ ሸዋዬ ከእርሳቸው የላቀና ከፍ ያለ ቦታ በመያዛቸው። በመኪና ውስጥ ተቀምጦ ሲጠብቅ የቆየው ማናዬ ግን እንደ ወትሮው በማቆላመጥ ማጽናናቱ ቀርቶ አንድ ቃል አላናገራቸውም።

በምሳ ሰዓት ላይም የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ፥ ንጉሡ የኪዳነ ምሕረትን በዓል በደብረ መንክራቱ ሥዕል ቤት ማስቀደሳቸውንና ይህም በዓል የሚከበረው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእመቤታችን ለቅድስት ማርያም፥ በትናንቱ ዕለት ቃል ኪዳን የገባላት መሆኑን ለማስታወስ መሆኑን ሲናገር ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከንፈራቸውን እየመጠጡ፥ «ኤዲያ ዛሬ ጊዜ ምን ቃል ኪዳን አለና! ሁሉም ቃል ኪዳኑን እያፈረሰ ነው» በማለት በመካከላቸው ተዘግቶ ያደረ የዋለውን ንግግር ለመክፈት ሞከሩ። ማናዬ ግን ምንም መልስ ሳይሰጣቸው ምግቡን ቆነጣጥሮ ተነሣ። ባንድ በኩል ካፈርኩ አይመልሰኝ ዓይነት ነው። በሌላ በኩል በትእዛዙም፥ በቁጣውም እጅግ እየከፋ የሄደውን አመላቸውን ጥሎኝ ይሄዳል ብለው በመፍራት ያርሙ እንደሆን በማለት ነበር። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በበኩላቸው አራት ቀን ተኰሳትረው ከሰነበቱ በኋላ እየቀራረብም ቢሆን የኩርፊያውን መጋረጃ ለመቅደድ ተገደዱ።

«አሁን ማ - ይሙት የምትናገረው አጥተህ ነው?» አሉና አፍንጫቸውንና ዓይናቸውን በነጠላቸው እየጠራረጉ መነፋረቅ ጀመሩ።

«ምን ያለቅስሻል ታዲያ?»

«በዚህ በመከራ ጊዜ ደጃዝማች የሉ፥ ልጁ ከአጠገቤ የለች። ለነገሩማ የተማመንኩት ባንተ አልነበር?» ልቅሶው ባሰባቸው።

«ታዲያ እኔ መች ከአጠገብሽ ተለየሁ?» ማናዬ መርታቱ ተሰማውና ወደ ማቆላመጡ ቃና አዘነበለ።

«አንተማ ይኸው ለማነጋገር ስንኳ ተጀንነህብኝ! ንጉሡን አሽከሮቻቸው ሁሉ እንደ ከዱዋቸው ልትተወኝ ብታስብ ይሆናል እንጂ» ተንሰቀሰቁ።

«እኔ አንቺን ልከዳሽ? የማይመስል ለምን ታስቢያለሽ?» በእርግጥም መኪናዋን ከእጁ ሳያስገባ ቃል የገቡለትን ጋሻ መሬት ሳይረከብ ሊተዋቸው ሊከዳቸው አላሰበም። አንድ እጅ ዙሮ የማይገጥመውን ያነን ትከሻቸውን በሁለት እጁ ታቅፎ እንደ ሕፃን ልጅ እሹሩሩ እያደረገ አባበላቸው።

ወይዘሮ ሸዋዬ ድንገት ዘው ብለው የገቡት በዚህ ጊዜ ነበር። «ውይ ፊልም መስላችኋል» አሉ እንደ መንከትከት እየቃጣቸው።

«ውይ! አስደነገጽሽን እቴ! ራሴን አሞኝ ሻሽ እሰርልኝ ብዬው ነው። ድንገት ከየት ብቅ አልሽ?» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጠየቁ፤ ከወንድ ጋር ሲዳሩ በመገኘታቸው ኃፍረትም ደስታም እየተሰማቸው።

«ከሰው ቤት ቆየሁና እግረ መንገዴን ልጠይቅሽ ብዬ ነዋ! ግና አልዋሽም ወሬ እንዳለ ቤቴ እስክደርስ የቴሌቪዥኑ ሰዓት ያልፍብኛል ብዬ ነው ጉራ ያልኩት።»

«የተፈጠረ አዲስ ነገር አለ?»

«የወሬ ወሬ ነው። ካለ እንደርስበት የለ? እስቲ ክፈቱት።»

ቴሌቪዥኑ ተከፍቶ ቦግ ብሎ ሲበራ፥ የዕለቱ ፕሮግራም መግለጫ አልቆ ልክ የዕለቱ ዜና መነገር ሲጀምር ዜና አንባቢው በወረቀት ላይ ሰፍሮ የሚያየውን ማመን ያቃተው ይመስል ዓይኑን እየበለጠጠ፥ «ከቤተ መንግሥት የተሰጠ መግለጫ። ዛሬ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ.ም በዓቃቤ ሹም ጎንጤ የሚመራው የሹማምንት ሸንጎ በአንድ ድምፅ ተስማምተው ሥራቸውን ለመልቀቅ ለግርማዊነታቸው ልመና አቅርበዋል። ግርማዊነታቸውም የሹማምንቱን የሥራ መልቀቅ ልመና ተቀብለው ውሳኔ የሚሰጣቸው መሆኑን ከቤተ መንግሥት ቃል አቀባይ ተገልጡኡአል።» ሲል አስታወቀ።

«ምን ማለቱ ነው ሸዋዬ!» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጠየቁ ከተቀመጡበት ድንገት ፍርጥም እያሉ።

«እንደምትሰሚው ነዋ! ስንብት ጠየቁ ማለት ነው።»

«የምን ስንብት? ከሚስቱ አገር ለመሄድ ነው የሚሰናበተው?» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጥርሳቸውን እንደማፋጨት ቃጣቸው።

«ዘመናዊ አሠራር በፈረንጅ አገር የሚሠራበት እንደዚህ ነው» አሉ ወይዘሮ ሸዋዬ ብዙ ጊዜ ውጭ አገር ደርሰው በመመለሳቸው የዘመናዊነት ብልጫ እየተሰማቸው።

«ኤረዲያልኝ ዘመናዊነት! ንጉሡ ራሳቸው የሾሙትን ራሳቸው ነው የሚሽሩት። ሰው ራሱን ሲሽር ታይቶም ተሰምቶም አያውቅ!»

«ቴሌቪዥኑ እንዳለው ልመና አቀረቡ ነው። አንድ ሰው ደከመኝ አቃተኝ ጌታዬ ይብቃህ ይበሉኝ ቢል ነውር ያለበት አይመስለኝም።»

«አጨማልቆ አጨማልቆ አሁን የት ነው የሚሸሸው! ይወጣት እንጂ! የአንቺም ጥብቅና መቆም በዛ!» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሳያስቡት አነጋገራቸው ከረር አደረጉት።

«የአንቺስ አቃቤ ሹም ጎንጤን እንዲህ ጠምደሽ መያዝ ምን ይባላል?» ወይዘሮ ሸዋዬ በበኩላቸው ኰስተር አሉ። ሁለቱም መልስ አልተሰጣጡም። ለቅጽበት ያህ ወደየራሳቸው ውስጣዊ ሐሳብ ተመለሱ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ንጉሡ ማርቸዲሲ አዘውላቸው ፔጆ መቀበላቸውን በንዴት አስታወሱ። ወይዘሮ ሸዋዬ ደግሞ ከአቃቤ ሹም ጕንጤ ወንድም ጋር አበልጅ ከሆኑ ወዲህ የተፈጸመላቸው ብዙ ውለታ ትዝ አላቸው ከሆኑ ወዲህ የተፈጸመላቸው ብዙ ውለታ ትዝ አላቸው። ከውለታዎቹ አንዱ ከበሩ ውጭ የቆመችው ማርቸዲስ ነበረች።

አንዱ የሚያስበውን ሌላው የሚያውቅ ይመስል ለብዙ ሴኮንዶች በትዝብት ተፋጠጡ። የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቋጥኝ ደረት ከፍና ዝቅ ይላል። ስንደዶ የመሰለው የወይዘሮ ሸዋዬ አፍንጫ ተወርውሮ ሊዋጋ የሚሰበቅ ይመስላል። ሲናደዱ ይኸው ናቸው።

«አየሽ ዘርፏ የእኅትነት ምክሬን ልሰጥሽ። ሳይቸግር ወዳጅ እንጂ ጠላት አታፍሪ» አሉ ዓይናቸውን ሳይሰብሩ።

«ኧረ እኔ ካለወስፋቴ ጠላትም የለኝ!»

«እኔ አንቺን ብሆን ከወስፍቴም ጋራ ቢሆን ምን አጣላኝ። በምግብ አስታግሠዋለሁ። እና እንዳልኩሽ ዛሬ ሳይቸገር ጠላት አለማፍራት ነው። ዛሬ ቀን እያለላችሁ?» ወይዘሮ ሸዋዬ መሮ የመሰሉ ጥርሶቻቸውን ብልጭ አደረጉ።

## ፫

በአቃቤ ሹም ጎንጤ ቤት ከሹማምንት ሸንጎ አባላት መካከል በተለይ ለእርሱ ቅርብ የሆነና የአነሣሳቸውንም ሆነ የአወዳደቃቸውን ዕድል ከጎንጤ ጋር ያስተሳሰሩ አራቱ ብቻ ተሰብስበው ነበር። አንዱ የዓቃቤ ሹም «ቀኝ እጅ» እየተባለ የሚጠራው ትንሽ ወንድሙ ነበር። ሌላው የአዲስ አበባው ብጥብጥ የመለዮ ለባሹ ግፊት እየበረታ ሲመጣ በደሴ የረሃብተኞች ጉዳይ ሥራውን አቋርጦ የተመለሰው ሹም ጓንጉል ነው። የቀሩት ሸክሙ የወረደለት የመሰለው ወደ ቤት የጨነቀው አንዳኙ ወደ ሆነው ጐራው ከብስጭቱ የተነሣ ሁሉንም መርሳት የፈለገው ደግሞ ወደ ውሽማውና ወደ እነጐብልዬ ሠፈር ተበታትነዋል።

«አሎር» አለ አለቃ ሹም ጎንጤ ቴሌቪዥን ዜናውን ሲጨርስ ከግድግዳው ላይ በተሠራ ልዩ መሣሪያ እያጠፋ። ከተከፈተ ዳቦና ፎርማጆ ጋር ሦስቱ የሚያወራርዱት ዊስኪ፥ ዐቃቤ ሹሙ የሚጐነጨው ሻምፓኝ ዛሬ እንደ ወትሮው አልጣማቸውም። አላዝናናቸውም። የሚስቡት ለልማዱ ይህል ብቻ ነበር። የአቃቤ ሹሙ ስሜት ከጭንቀት ይልቅ የብስጭት ከድካሙ ይልቅ የመሰልቸት ነበር። በዚህ ባለቤት ከአጠገቡ ብትኖር ተመኘ። የበለጠ ደግሞ እርሱ ከዚያው ከባለቤቱ ጋር መሆኑን መረጠ። ሁናቴው አላምር እያለ ሲሄድ ባለቤቱን ከጥቂት ቀናት በፊት ወደ አውሮፓ ልኮ ነበር። «አሎር» አለ አቃቤ ሹም ጎንጤ ደግሞ።

«አሁን እንግዲህ ምንድነው የሚቀጥለው?» ሹም ጓንጉል ፈተናው እንደ ከበደበት ተማሪ ጠየቀ።

«ከዚህ ደርሰናል። ወደ ፊት የሚመጣውን ማየት ነው» አቃቤ ሹም ጉንጤ ሁለት መዳፉን ዘርጋ ብትን አደረገ። «መግለጫው መጥፎ አይደለም። ራስ ዝማነህ ከአናቱ ላይ የሌለ ፀጉሩን ሲነጭ ይታየኛል።» ወደፊት በገፋ አገጩ ሥር የተደበቁትን ጥርሶቹን ለማሳየት ሞከረ።

«ለምን? የፈለገውን እንደሆነ አግኝቷል። ባንድ በኩል እንዳንሠራ በልዩ ልዩ ተንኰልና የቤተ መንግሥት ሤራው ሲያደናቅፈን ኖረ። አሁን ቦታውን ለቀቅንለት። ሌላ ምን ይፈልጋል?»

«አዎ ቦታውን ለጊዜው ለቀንለታል። ግን የሚፈልገውን አላገኘም።»

«ከዚህ የበለጠ ምን ነበር የፈለገው?» ሲል ሹም ሥራህ ብዙ ጠየቀ።

«ታሪኩ ብዙ ነው። አንተ አልነበርክም እንጂ።» አቃቤ ሹሙ ሹም ሥራህ ብዙን እንደ አትክልት ከሥር ጀምሮ ኰትኵቶ ያሳደገው ስለሆነ እንደ ልጅ ነው የሚመለከተው።

«አስቀድሜ ነግሬዎታለሁኮ። የኢንተርናሲዮናል ብድሩን ንግግር ለማጠናቀቅ በጉብኝነትም በሽርሽርም ማባባል ነበረብኝ። ከስምምነት ደርሰናል። አምስት ሚሊዮን ዶላር ትንሽ አይደለም።»

«ነበር። ነገር ግን አሁን ሁናቴው እስኪለይ ድረስ በይደር ማቆየቱ ሳይሻል አይቀርም። ከማን እጅ እንደሚገባ አናውቅም። የባንኩ ሰዎችም ቢሆኑ የጸጥታ ምክንያት የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የሚኒስትሮች ጉባዔ እንዲበተን መጠየቃችንን እያየ ለጊዜው በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ግዴታ ውስጥ መግባታቸውን እጠራጠራለሁ። የሚሻለው ነገሩን እንዳለ መተው ነው። ለነገሩማ አንተ አሁን ምንም ነገር ለማድረግ ሥልታን የለህም። ግን በቅርብ ስለምታውቃቸው ወደ ሀገራቸው በቶሎ እንዲመለሱ ንገራቸው።»

«ነገር ግን በድንገት እንዲህ ምን አፈነዳው?» ሹም ሥራህ ብዙ እንግዶቹን ይዞ ሁለቱን ቀን ሳንጋኖ ሰንብቶ ስለ ነበር ሁናቴውን አልተከታተለውም ነበር።

«ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። በትክክል ይህ ነው ተብሎ የተጨበጠ ነገር ግን የለም።»

ዓቃቤ ሹም ጉንጤ ሻምፓኙን በኃይል ተጉንጭቶ በንዴት መዳፉን ቡጢ አደረገው።

«አንድ ነገር መኖር አለበት» አለ ሹም ሥራህ ብዙ፥ አለዝቦ።

«እሱ ምን ጥያቄ አለው? ግን ስናንቀላፋ የተማረክነው እኛ ነን።» ወደ ወንድሙ እያመለከተ፥ «አንተ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ የዘረጋኸው የመረጃ አውታር ነበረህ። አንተም» ወደ ሹም ኃንጉል ጣቱን እየቀሰረ «አንተም ደግሞ ጀምሬአለሁ በለኸኝ ነበር። ካላ ኢንፎርማስዮን መንግሥት ሊቆም እንደማይችል ግልጽ ነው። ግን.....» በንዴት ንግግሩን አንጠልጥሎ እንደ መተው ቃጣው። ሻምፓኙን በተጉነጨው መጠን እየሞቀውና ሰውነቱ እየተሟሟቀ ሄደ። «እውነቱን ከእናንተ መደበቅ አልፈልግም፤ በሥራና በመረጥኳቸው የሥራ ባልደረቦቼ፥ በሕይወቴ ሙሉ እንደ ዛሬ አፍሬ አላውቅም።»

ሌሎቹ ሹማምንት ሁሉ አንገታቸውን አቀረቀሩ። የአቃቤ ሹሙ ወንድም ብቻ ለማስረዳት ፈለገና መግለጫውን አጉመትምቶ ተወው።

«ማንንም ለመውቀስ አይደለም። ሁላችንም የተቻለንን ሠርተናል። ነገር ግን ልጅ ጉግሣ ከፍተኛ ጉዳይ መሆኑን እያወቀው ከጢቱ ሰብሰባችን መጠራጠር ይገባ ነበር።» አቃቤ ሹም ጉንጤ ቁልፉን ለማግኘት የዕለቱን ሁናቴ ሂደት በሐሳቡ እንደ ገና መልሶ ሄደበት....ሠራዊቱ ስላቀረበው ተጨማሪ ጥያቄ እንዲነጋገር ሹም ድፋባቸው ጢቱኡን ተልኮ ነበር። ከሰዓት ላይ የተጨበጠ መልስ ሳይዝ መጣ። ሪፖርቱን ሲያጠቃልል፣ የሚፈልጉትን የሚያቁ አልመሰለኝም ብሎ ነበር። አብዛኞቹ ሹማምንትም - ንጉሡን ጨምሮ - ማዕበሉ እየበረደ መሄዱን ገመቱ። ቀደም ብሎ በወጣው ፕሮግራም መሠረት ንጉሡ የአፍሪቃ ሚኒስትሮችን ጉባዔ እንዲከፍቱ፥ የሪሴፕሽን ግብዣውንም እንዲያስተናግዱ ተወሰነ። ከሰዓት በኋላ ግን ያልታሰበ መርዶ መጣ። ሹም ድፋባቸው ጫን ጫን እየተነፈሰ ከስብሰባው ዘው ብሎ ገባና፥ የአራተኛው ክፍለ ጦር በሙሉ ከሁለተኛው ክፍለ ጦር ጋር መተባበሩን አዲስ አበባ የሚገኙ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎችም የበላይ አለቆቻቸውን ማሠራቸውን፥ ግማሽ የሚሆነው የሀገሪቱ ሠራዊት በበታች ሹማምንት ቊጥጥር ሥር መዋሉን አስታወቀ። ንጉሡ በዚህ ጊዜ የአፍሪቃ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችን ለማስተናገድ ሄደው ነበር። ሹም ድፋባቸው አቃቤ ሹሙን ለብቻ ለየት አድርጎ በሹክሹክታ ሌላም ወሬ ነገረው - ሠራዊቱ የአቃቤ ሹም አንሥቶ የሹማምንቱን ቡድን በቊጥጥር ሥር ለማድረግ ማሰቡ ይነፍሳል - አቃቤ ሹሙ በበኩሉ ይህንን ወሬ ቀስ ብሎ ለወንድሙ ነገረው። ሁለቱ ለብቻ ተመካከሩና መላው የሹማምንት ቡድን የሥራ ስንብት እንዲጠይቅ ሐሳብ አቀረቡ። የቡድንኑ አፈ ቀላጤ ደብዳቤውን እንዲያዘጋጅ ተደረገ።

ንጉሡ ሪሴፕሽኑ ሲያበቃ ተመልሰው የአቃቤ ሹሙን ሐሳብን እንደ ሰሙ በግልጽ ባይቆጡም ሁሉንም በክፉ ዓይን ተመለከቷቸው። «ከእኛ ሐሳብና ፈቃድ ውጭ ለምንድን ነው የምትሰናበቱት? ከሠራዊታችን ዘንድ የቀረበ አዲስ ጥያቄ አለ?» ሲሉ ጠየቁ።

«እምብዛም አዲስ ነገር የለም። ግን ሁናቴውን የበለጠ ለማረጋጋት ይረዳ ይሆናል ብለን ነው» ሲል አቃቤ ሹም ጉንጤ አድበስብሶ መለሰ።

«ግርማዊ ሆይ! ይህ ፈጽሞ የማይደረግ ነገር ነው» ሲል ራስ ዥማነህ ኰስተር ብሎ ጣልቃ ገባ። «ሹማምንት በፈቃዳቸው ከሥራ ሲሰናበቱ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም። ንጉሡ እንደ ፈለገ ይሾማል፤» አለ በማሽሟጠጥ ወደ ሹሙ ዘወር ብሎ «ኢትዮጵያ ፈረንሣይ አይደለችም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሥራት ሲያቅተው ለፕሬዝዳንቱ ስንብት የሚያቀርብበት።»

አቃቤ ሹም ጉንጤ ከንዴቱ የተነሣ «ደንቆሮ ፊውዳል» ብሎ ለመሳደብ ከጀለውና መለስ አድርጎ «ነገሥታት በአሉበትም ቢሆን ይደረጋል። እንግሊዝ አገር ኑረዋል። ይህንን እንዴት ሳያውቁት ቀሩ?» ሲል እሱም በአሽሙር መልክ መለሰ። በመካከላቸው የቆየው ጥርጣሬኢ ሤራና መናናቅ አሁን ወደ ተፋጠጠ ጥላቻ ተለወጠ። ይህ የሁለቱንም ወገኖች በግልጽ ተሰማቸው። በእርጅና መጃጀት ምክንያት ይህ ግልጽ መፋጠጥ ያን ጊዜ አልታያቸው የሁለቱን ኃይልና ግጭት እያመዛዘኑ ሲጠቀሙበት የኖሩት ንጉሥ ብቻ ነበሩ።

ደህና ጕፈሬ ከሚመስል ቅንድብ ሥር ያሉት ዓይኖቻቸውን ከወዲያ ወዲህ እያንከራተቱ በታከተ አንደበት «አሁንኮ ታዲያ ምን ይሁን ነው የምትሉት?» አሉ ምናለበት ባታደክሙኝ ባታሰልቹኝ እንደ ማለት ያህል ነበር።

ሁለቱ ተቀናቃኝዎች በፖለቲካ ገመድ ጐትታ ረጅም ጊዜ የቆዩ ስለሆነ ፊት ለፊት መጋፈጡን እስከ መጨረሻው አልገፉበትም። በዚያ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ከተገኙት መካከል ብዙዎቹ የአቃቤ ሹም ወገን የሆኑት የሹማምንቱ ቡድን አባሎች ነበሩ። ግን ንጉሡ የየትኛውን ወገን ሐሳብ እንደሚቀበሉ አቃቤ ሹም ድፋባቸው ስላመጣው ወሬ ከምንጩ ድረስ የሚያውቅ ቢሆንም በሠራዊቱ፣ ውስጥ፥ ያለው ድጋፍ አሰላለፍ እንዴት እንደ ሆነ ራሱን ማጋፈጥ የማይበጅ መስሎ ተሰማው። አንዱ የሌላውን ኃይል እንደሚያውቅ የተቃራኒ ሠራዊት መሪዎች ሁለቱም ወደ ኋላ ማፈግፈጉን መረጡ።

አቃቤ ሹም ጐንጤ ተደፍቶ እጅ እየነሣ «ግርማዊ ሆይ፥ እኔና የሥራ ጓደኞቼ በታማኝነት፥ በቅንነት፥ በታዛዥነት፥ በትጋት ንጉሠ ነገሥታችንን አገልግለናል ብለን እናምናለን። አሁንም ያቀረብነው ሐሳብ፥ ሁናቴዎች ከቍጥጥራች ውጭ ቢሆኑም፥ የኛም ታማኝነትና አገልግሎት በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ዋጋ እንዳያጣ በሚል መንፈስ ብቻ ነው። ከዚህ በተረፈ ግርማዊነትዎ ለሚያደርገው ውሳኔ ሁሉ አሁንም ወደ ፊትም ምን ጊዜም ታዛዥ ባሪያዎችዎ ነን።» ደግሞ እጅ ነሣ።

ራስ ዠማነህ ወዲያው ለጠቅ አደረገና «ግርማዊ ሆይ፥ እኔም ዓቃቤ ሹም ጐንጤና የሥራ ጓደኞቹ አይደሉም፤ አላገለገሉም ማለቴ አይደለም። ቢሆን ኖሮ እኛም ዝም ብለን አንመለከትም። ከጫማዎ ሥር ከፊትዎ ተነጥፈን የምንቋቋመው ጉዳይ ነው። ግን - ግን በሀገራችን፥ በታሪካችን ያልተለመደ አሠራር የግርማዊኢ ንጉሠ ነገሥትን ክብር የሚነካ እንዳይሆን በማለት ነው። ሕዝቡ የሚያውቀው ግርማዊነትዎ ሲሾሙ ሲሽሩ ሲቀጡ ምሕረት ሲያደርጉ ነው። አዲስ ነገር ሲመጣበት መንፈሱ ሊዋልል ይችላል።»

«በሁለታችሁም የሚበች የመሰላችሁን ማሰባችሁ የሚደገፍ ነው።» አሁንም ተነጋግራችሁ የሚበጀውን ነገር አድርጉ» ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱ ትተዋቸው ወደ እልፍኝ አመሩ። ራስ ዠማነህ እጅ ነሥቶ የሚመለስ በማስመሰል ተከትሎዋቸው ሄደ። አቃቤ ሹም ከወንድሙ ጋር እንደ ገና ተመካከረና የሥራ ስንብት ደብዳቤው እንዲሻሻል ተደረገ። «ስንብት ጠይቀዋል» በሚለው ፈንታ አሁንም ታዛዥነታቸውን ለማረጋገጥ «ልመናቸውን አቅርበዋል» ተባለ። ከዚያ አራቱ ተለይተው ወደ አቃቤ ሹም ቤት መጥተው ንጉሡ ምን እንደሚወስኑና ምን ተብሎ እንደሚነገር በዊስኪና በሻምፓኝ ዙሪኢያ ይጠባበቁ ጀመር። በዚህም ጊዜ አቃቤ ሹም ሥጋቱንና ንዴቱን በሆዱ አምቆ ቆይቷል።....ይሽሩን ይሆን? ወይ ስንብታችንን ይቀበሉት ይሆን?

አቃቤ ሹም ጐንጤ የዕለቱን ውሎ በሐሳቡ ተገኮዞ ሲአይበቃ «አሎር! ይኸው ነው» አለ ሐሳቡን ያወጋቸው ይመስል ድንገት ሳይታወቀው። ወዲያው ግን ቀጠል አደረገና «የሆነ ሆኖ ያለፈው አልፏል።»

«እና፥ እኛ የማንም መጫወቻ እንድንሆን ተጣልን ማለት ነው!» ወንድምዬው ቆፍጠን ብሎ ተናገረው።

«ማለቴ አይደለም።» አቃቤ ሹም ሻምፓኙን ፉት ብሎ ዓይኖቹን ከደን በማድረግ የሚያስብ መሰለ። «ግን ትናንት ስለሆነ ነው ስለደረሰው ወደ ኋላ ተመልሰን የምንለውጠው ነገር የለም። ውኃ ከፈሰሰ አይታፈስም ተብሏል።»

«የዕድላችን ውኃ ፊስሷል ማለት ነው?» ሲል ሹም ጓንጉል በደከመ ድምፅ ጠየቀ።

«እንዲህ በቀላሉ ተስፋ መቍረጥ የለብህም። የትናንቱ ፈስሷል። የዛሬውም እንዲሁ። ግን የፖለቲካ ሰው ዛሬ በቆመበት መድረክ ብቻ መወሰን የለበትም። በልዩ ልዩ መንገድ መልሶ - መላልሶ መሞከር አለበት። ፕሬዝዳንት ደጎል የፈረንሳይ ፖለቲካ ረስቷቸዋል እርሳቸውም ፖለቲካ ረስተዋል ከተባሉና ከስንት ዓመት በኂላ ነው በሙሉ ሥልጣን መሪነት የያዙት.....ዕድላችን አልተወሰነም።»

«እንደማየው ግን ተወስኗል» ሲል ሹም ሥራ ብዙ ተናገረ።

«የለም» አቃቤ ሹም ራሱን ነቀነቀ። «ታሪክ እንደምታውቅ እርግጠኛ ነኝ። የፈረንሳይን የእንግሊዝን ከዚያም የባሰ የሩሲያን ታሪክ የተመለከትን እንደሆን በምንም ዓይነት መንገድ የእኛ ዕድል ማለፍ፥ ከእነራስ ዠማነህ ሊቀድም አይችልም። ጋሪ ከፈርሱ እንደማይቀድም ሁሉ።»

«ቢቀድምስ?» የሹም ጓንጉል አጠያየቅ አሁንም የጭንቀት ነበር።

«እሱን ነገር እናየዋለን። እንዳይቀድም ግን ለነገው መዘጋጀት ነው። እኔ በበኩሌ ሊሆን እንደማይችል እርግጠኛ ነኝ። ካሰብንበት። የእነርሱም የዕድል ውኃ በሰባራ እንስራ ውስጥ ነው። ከእኛው እንስራ የባሰ አርጅቶ የነቃ።» አቃቤ ሹሙ ተነሥቶ ወደ መኝታ ክፍሉ አመራ። እንግዶቹን የማሰናበቱ ምልክት ነበር። ሦስቱ ዊስኪያቸውን እየጨለጡ ሲወጡ ወንድምየው ብቻ ቀረ። የነገውን ቁም ነገር በምሥጢር ለመነጋገር።

«ግንኮ የሩስያን ሬቮሊሲዮን ካነሣህ ዘንዳ፥ አሪኢስቶክራሲውንም ቡርዧዋዚውንም አብሮ ባንድነት እኮ ነው ያጠፋው።» ወንድምዬው ነገሩ እንደ ከነከነው አፍንጫውን በጣቱ ቀንጠብ ቀንጠብ አደረገ።

«እሱ ሌላ ነገር ነው። የቦልሼቪክ ፓርቲ በቡርዧ ዲሞክራሲ ስለማያምን ነው። በእኛ አገር ግን ፓርቲ የለም። ስለዚህ በእኛ አገር ቢበዛ የሚኖረው አናርሺ ነው።»

«አናርሺም ቢሆን ደስ አይለኝም።»

«ኤ - ካወቅንበት ልንጠቀምበትም እንችላለን።»

በዚህ ጊዜ የሠፈሩ ኤሌክትሪክ ድንገት ተቋርጦ ጨለማ አለበሳቸው።

«ሜርድ!» እንደዚህ ያለ ቃል ከጕንጤ አፍ ሲወጣ ወንድምየው ሰምቶ አያውቅም ነበር።

## ፬

በበነጋታው ጧት የጠራች የየካቲት ፀሐይ ጨረር የኢትዮጵያን ምድር አለበሰው። በውርጭ ወርዝቶ ያደረው መሬት እየተሟሟቀ ሄደ። ፍጥረትም መንቀሳቀስ ጀመረ። ሰው ወደ ሥራው፥ ከብት ወደ መስኩ ወደ ግጦሹ ተሠማራ። ፀጥ ረጭ ብሎ ያደረው ሕይወት እንደገና አንሠራራ - የዕለት ኑሮ ፕዞውን ቀጠለ......

ማታ ዜናውን የሰሙት አንድ ሽክም የወረደላቸው መስሎ ተሰማቸው። ያልሰሙት ደግሞ የዕለት ሕይወታቸው፥ ዛሬ ደግሞ ምን ይመጣ ይሆን?» በሚል ሐሳብ ተቀበሉት። በግል ችግራቸው ተጠምደው ለሰሞኑ ሁናቴ ቅንጣት ደስታና ሐሳብ ያልነበራቸውም የተለመደውን የዕለት እንቅስቃሴያቸውን በብስጭት ተያያዙት።

በአጭር ጊዜ ውስጥ የሰማው ላልሰማው እየነገረ ወሬው እንደ ቋያ እሳት እየተቀጣጠለ ሄደ። ከቤት ቤት ከመንደር፥ መንደር ከሠፈር ሠፈር፥ ተዳረሰ።

-ምን ይመስልሃል?

-ምኑ?

-ስንብቱ?

-የምን ስንብት?

-ራዲዮ አልሰማህም?

በአሉታ ራሱን ይነቀንቃል። የነግረዋል። «አትለኝም!» ሲል እንደ መፈንደቅ እንደ መዝለል ይቃጣዋል። አንዳንዱ ደግሞ ከልደታ እንዴት እንደሚያደርስ እያሰላሰለ «መንግሥት ከሌለ ታዲያ ደሞዛችንስ?» ሲል ይጠይቃል።

ነገሩ ቅንታት ስሜት ያልሰጣቸውና የዕለት ሥራቸውን እንደ ወትሮው፥ በጧት የተያያዙት ክፍሎች ደግሞ ነበሩ። በሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያና በምኒልክ ትምህርት ቤት በትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት የመንገዱን ዳር ይዞ፥ ሻማ፥ ዕጣን፥ ጧፍ የባቄላ ንፍሮ ተዘርግቷል።

-ከዚህ የተሻለ ወፍራም ሻማ አያገኙም።
-ምርጥ ዕጣን ነው.....
-የእኔ መስፈሪያ እንደ ሌሎቹ ከቂጡ የተሰረጐደ አይምሰልዎት! —

አካለ ስንኩል፥ ዓይነ ሥውር ቆዳው፥ የተገለበጠ የሥጋ ደዌ በሽተኛ፥ ከጧፍ ከባቄላ ንፍሮ ጎን ተረፍርፏል።
-ስለ ወላዲተ አምላክ።
-ስለ አዛኝቷ።
-ስለ ጭንቅ አማላጅቷ።
-እንደኔ ከመሆን ይሠውራችሁ! በወንድ ልጅ አምላክ አትለፉኝ!

በአየሩ ላይ፥ ስብከት ጸሎት፥ ቅዳሴ፥ በድምፅ ማጉያ ያስተጋባል።

ከረፋዱ ላይ የአዲስ አበባ ባንኮች ገንዘብ ለማውጣት በሚጣደፉ ደንበኞች ተጣበበ።

ወደ ግሮሰሪና ወደ መርካቶ መሯሯጥ በረከተ። ሠራተኞች ወደ እያሻሻቸው ሲሄዱ ብዙዎቹ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሮዎች ባዶ ሆኑ። ከቀትር ላይ የታጠቁ ብዙ ወታደሮች በከተማው

ተሰማሩ። የኢትዮጵያ ራዲዮ፥ ቴሌቪዥን፥ ቴሌኮሚዩኒኬሽን፥ ባንኮችና ሌሎችም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጥበቃ ሥራ ዋሉ። የወታደሮች ተሽከርካሪዎች ጅፖች፥ ትሬኳርተሮችና ብረት ለበሶች በዋና ዋና መንገዶች በብዛት ሲንቀሳቀሱ ታዩ። ብዙ ሰዎችም የመንግሥት ግልበጣ የተካሄደ መስሏቸው ታኀሣሥን አስታውሱ። ማን ይሆን መሪው? የሚል ጥያቄ ተነሣ።

በሰዓት ላይ ካፊያ መጣል ጀመረ። ልዩ ዓይነት ካፊያ - የወረቀት ካፊያ። ከጧት ጀምሮ ከአዲስ አበባ ሰማይ ላይ የጦር ኃይሎች ሄሊኮፕተሮች ሲያንዣብቡ ውለው ነበር። ተግባራቸው በሚገባ ያልገባው ሰውም ቀና እያለ ተመልክቷቸዋል። ከዚያም ድንገት በፒያሳ፥ በአራት ኪሎ በሜክሲኮ አደባባይ በስድስት ኪሎ ላይ ወረቀቱን ያዘንቡት ጀመር። ነገሩ እንቆቅልሽ ሆኖበት የቆየው ሰው ሁሉ ተረባረበ። ወረቀቶቹ ወደ ተበተኑበት አካባቢ ሰው አንዴ ግር ብሎ ይሄድና አንዱ በአንዱ ላይ እየተነባበረ አንዱ ሌላውን እየገፈተረ ሲሻማ የተረገጠ፥ የወደቀና የተጐዳም ነበር። ብዙ ጊዜ አንዱን የተረገጠ ጊዜ ሁለት እጆች ይቀልቡትና አንዱ ለሌላው በመተው ፈንታ ለሁለት ሲቀዳድዱት ሁለቱንም ሳይጠቅም ይቀራል።

በመጀመሪያ የተበተነው እንዲህ ይላል፦

የምሥራች፦

ለምድር ጦር መኰንኖችና የበታች ሹማምንት

ለአየር ኃይል መኰንኖችና የበታች ሹማምንት

ለባሕር ኃይል መኰንኖችና የበታች ሹማምንት

ለፖሊስ ሠራዊት

ለሰላማዊ ሕዝብ

ኢትዮጵያ፦

ሰሞኑን ያደረግነውና በማድረግም ላይ ያለነው የለውጥ እንቅስቃሴ ካለ ደም መፋሰስ የምናፍናቸው ተኩላዎች በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን ለመልቀቅ ጠይቀዋል። እኛም የምንፈልገውና ለሀገራችን ይጠቅማል ብለን ያሰብነው ይህንኑ ነበር። ቢሆንም ይህ ብቻ በቂ አይደለም። አሁንም የሚቀሩን የኀብረት ሥራዎች አሉን።

በማንኛውም አገር መሪ የሚያስፈልገው በቀውጢ ቀን ነበር። የሆነ - ሆኖ የእኛ መሪዎች በሰላም ጊዜ ኖረው ለክፉ ቀን አጋልጠውን መሸሻቸው ከውጭ ጠላት ጋራ የተስማሙበት አንድ ነገር ቢኖር ነው። ምናልባትም በሕዝቡ ኀብረት ዓላማቸው ከሽፎ ሊሆን ይችላል።

አሁን በኀብረት የምንጠይቀው፦

፩. በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን ለመልቀቅ ያቀረቡት ጥያቄ እንዲፈጸምላቸው።

፪. ሥልጣን ከተገፈፉ በኂላ በነፃ ሳይለቀቁ እስከ ዛሬ ያባከኑትን የሀገሪቱን ሀብት የት እንዳደረሱ እንዲጠየቁ። ቢቻል በውጭ አገር ያስቀመጡት ንብረት እንዳለ በኢንተርናሲዮል ትብብር ተጋልጦ አስፈላጊው እንዲደረግ።

፫. በሀገር ውስጥ ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ ከደሃም ሆነ ከማንኛውም ግለሰብ የወሰዱት ሀብትና መሬት ልዩ ልዩ ንብረት እንዳለ ተጠንቶ ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን።

፬. በጠቅላላው እስከዛሬ ድረስ የነበሩትን ባለሥልጣኖች ሰብስቦ ስንዴውን ከእንክርዳዱ ለይቶ በእንክርዳዱ ላይ ውሳኔ መስጠት።

*ማሳሰቢያ*

*ይህ መግለጫ የሚመለከተው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቢሆንም እያንዳንዱም የሀገሪቱን ዕድገት እንጂ ውድቀት የሚፈልግ መሆን የለበትም። ስለዚህ፥ ሁሉም እስካሁን በአለው ይዞታው መጽናት አለበት። ይኸውም ድንበር በማከበር ላይ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ግዳጁን በተወሰነለት ቦታ ማስከበር ሲኖርበት የሚያስፈልገውም ድጋፍ ከአስፈላጊው ቦታ እንዳይጓደልበት ያሻል። በሌላውም የሥራ መስክ የተሰማራው የዕለት ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል ።*

*«የመረቁ ብዛት ለፍትፍት ያመቻል» እንደሚባለው ኅብረትን አጠናክሮ ለብሔራዊ ችግር መፍትሔ መፈለግ ነው እንጂ አልፎ አልፎ በሚደረገው ወሬ መፈታት ለጠላቶቻችን ምቹ ያደርገናል።*

*ኅብረት ኃይል ነው።*

*የተበተኑት ወረቀቶችና በወረቀቶቹም ውስጥ ያለው መልዕክት በትክክልም ሆነ ተዛብቶ በቅብብሎሽ ሩጫ ፍጥነት በራቱም ማዕዘን ተዛመተ። ወረቀቱን ያገኘው፥ በእግሩ እየተጣደፈ በአውቶሞቢልና በሰይቼንቶ እየተሳፈረ አፋጣኝ በመሰለው መንገድ ተጉዞ ለቅርብ ጓደኛው ያደርሳል። ሌላው ተውሶ አንብቦ በበኩሉ ለሌሎች ይተርክላቸዋል። ሰዎች በየቢሮው በየቡና ቤቱ ተነጋገሩበት፥ ተወያዩበት። ትናንት ፈላጭ ቆራጭ የነበሩት ሹማምንት ዛሬ ወንጀላቸው በሰማይ ከተበተነ መፍራት መሽማቀቅና ማሾክሾክ ቀርቶ ብዙው ሰው ስሜቱን አስተያየቱን በይፋና በድፍረት ይገልጽ ገባ። አንዳንዱ ማሳሰቢያውን የተመለከተው ከራሱ በደል ከዚያም፥ አልፎ ከራሱ ቂምና በቀል አንፃር ነበር። ሹመትና የደረጃ ዕድገት የዘለለው ሠራተኛ «ሕዝብ መበደል ማለት ይኸው አይደል? ሌላ ምን አለው!» ሲል በወደቀ አለቃው ላይ ጥርሱን ይነክሳል። ጣቱን ይቀስራል። አንዳንዱ ደግሞ የተበተነው ወረቀት በጠቀሰው ወንጀል አፈር ድቤ የሚያስገባቸውን ሹምና አጫፋሪውን በደፈናው ይፈልጋል - ማነው እሱ እናቱን! ዋጋውን እንዲያገኛት ነው የማደርገው! - ይላል። ዋጋውን ማግኘት ያለበት ማን እንደሆነ ግን ገና ሰው ጠይቆ የሚደርስበት ነገር ነው። እንዲህ ከሚያስበው ሰው መካከል ግማሹ በቅንነት በተበተነው መግለጫ ላይ ለተጠቀሰው አደራ ድርሻውን እያበረከተ እየመሰለው ሲሆን ግማሹ ደግሞ የአጥፊነት ባሕርይው እየገፋፋው የሚያደርገው ነገር ነበር።*

*ብዙዎቹ ደግሞ ምኞታቸውና ሐሳባቸው ከዚህ ሁሉ ወደ ላቀና ወደ ረቀቀ ደረጃ መጥቶ ከዚያ የተበተነ ወረቀት ማዶ የሚታያቸው የሚተነበዩት የነገዪቱን ኢትዮጵያ ዕድል ነበር።*

ውቢቱ፥ ለምለሚቱ ኢትዮጵያ ማርና ወተት የምታዘንቢቱ፥ ኢትዮጵያ በአራቱ ማዕዘን የሚፈስሱት.....ወንዞችሽ ከእኛ ተርፈው ለቅርብና ለሩቅ ጐረቤት ሕይወት የሚሰጡት ኢትዮጵያ ሕዝብሽ በረሃብ እንደ ቅጠል ከመርገፍ በረሃብ እንደ ቅጠል ከመርገፍ መዳኑ ይሆን? ጥንታዊ ኢትዮጵያ ዝነኛ ኢትዮጵያ ነበረች። ታሪካዊ ኢትዮጵያ ነበረች። አካባቢዋ በጨለማ ተውጦ በነበረበት ወቅት የተደነቀ ሥልጣኔ ነበራት። የተፈራች የተከበረች ሀገር ነበረች። ዳዊት በመዝሙሩ ተቀኝቶላታል። የአውሮፓ የታሪክ ጸሐፊዎች ስንኳ ጠላት ዙሪያውን ከብቦ ቢያስጨንቃትም ገናና የማትበገር ብቸኛ የአፍሪቃ የነፃነት ቋጥኝ ከየትም በኩል ጥቃት ተሰንዝሮባታል። አዎ! ቱርኮች ግብጾች፥ እንግሊዞች፥ ኢጣሊያኖች። ሁሉም የማይበገር ቋጥኟን እየተጋጩ ተመልሰዋል። ይህን ሁሉ ጸንታ አሳልፋለች። ውብ ኢትዮጵያ ገናና ጽኑ ኢትዮጵያ ነበረች። እንደ ዛሬው ወደ ኋላ ከቀሩት አገሮች አውሮፓንና ሩቅ ምሥራቅን ተብላ ሳትመደብ የሀብቷን ውጤት አውሮፓንና ሩቅ ምሥራቅን ያዳረሰ ሀብታም ነበረች። የጉም ጅብ የሆኑ ጥቂት ሰዎች አጋድመው ጥለው በላይዋ ላይ ሳይጨፍሩ ቀና ብላ የምትራመድ ኩሩ እመቤት ነበረች። እናት ኢትዮጵያ ውብ ኢትዮጵያ እንደ ገና በኩራት የምትቆምበት ጊዜ መምጣቱ ይሆን?

የኩሩዋ እናት አገር ልጆችዋ ኩሩዎች ነበሩ። ድንበርዋን የሚደፍር ክብርዋን የሚገስስ ጠላት ሲመጣ እንደ ንብ እየነደፉ ሲመልሱት ኖረዋል። ደጉአሊ - ኰአቲት - መቅደላ - አድዋ - መተማ - ማይጨው - ወልወል - የልጆችዋ ደም ወደ ምድረ ማኅፀንዋ ገብቶ እንደ ገና ሌሎች ልጆች እንድትፀንስና እንድትወልድ ያደረገበት ሥፍራ ስንቱ ተነግሮ - ስንቱ ተዘርዝሮ። ደማቸውን እያፈሰሱ ከደምዋ ሕይወት የዘሩ አጥንታቸውን እየከሰከሱ ከአካልዋ ሥጋ የወረሱ ልጆችዋ በታሪክ ዘመናት ሁሉ አንገታቸው እየከሰከሱ ከአካልዋ ሥጋ የወረሱ ልጆችዋ በታሪክ ዘመናት ሁሉ አንገታቸውን ያልሰበሩ ኩሩዎች ነበሩ። ስንኳን ተጠቅተው ሲከፉ፦

«እንደ ቆላ ጤፍ እንደ በሬሳ

ያረፈው ልቤ ደግሞ ተነሣ» የሚሉ ቁጡዎች።

አሁን ታዲያ አንገታቸውን ቀና አድርገው በኩራት የሚራመዱበት ጊዜ መምጣቴ ይሆን? ለምኞታቸው ማረጋገጫ መልስ የሚያገኙበት ይመስል ቀና ብለው የእንጦጦን ተራራ ይመለከታሉ። የእንጦጦ ተራራ በበኩሉ ከጀርባ እንደ ጒምቱ ጉብ ብሎ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚሆነውን ነገር ሁሉ በትዝብት የሚስተውል ይመስላል። ከዚያ በፊት ቁጭ ብሎ ከሥሩ እንደሚፈልቁ የቀበናና የግንፍሌ ወንዞች ታሪክ ያለማቋረጥ ሲፈስስ እንደታዘበ ሁሉ.....

የጋዝ ጢስ ሲታጠኑ በዱላ ሲቀጠቀጡ የሰነበቱት ተማሪዎች በበኩላቸው የተበተነውን ወረቀት ለተቀጣጠለው እሳት ማራገቢያ አደረጉት።

## ፫

የዩኒቨርሲቲ ካምፓሶችና የትምህርት ቤት ግቢዎች እንደ ተነቀነቀ የንብ ቀፎ ሆነዋል። በአራት ኪሎ ካምፓስ በመሐንዲስ ኮሌጅ ግቢ፥ በስድስት ኪሎ ካምፓስ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት፥ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪው በየሜዳውና በየአዳራሹ እየተሰበሰበ

በቡዱን እየተከማቸ ይመካከራል፤ ይወያያል፤ ይከራከራል፤ ይተራመሳል፡፡ ወሬ ከአንዱ ካምፓስና ትምህርት ቤት ወደ ሌላው ይቀባበላል፡፡

ዋናው ጥያቄ ምን መደረግ አለበት? እኛስ አሁን ምን እናድርግ የሚል ነበር፡፡ ግን ሁሉም የሚስማማበት አንድ ዓይነት መልስ አልተገኘም፡፡

ከፊሉ የወሎን ሕዝብ ያስጨረሱ ባለሥልጣኖች ለፍርድ እንዲቀርቡ እንጠይቅ ይላል፡፡

-ማንን ነው የምንጠይቀው? - የሚል ጥያቄ ይቀርባል፡፡

-ንጉሡን ነዋ! - የሚል የፌዝ መልስ ይሰነዘራል፡፡

-ዋናው ተከሳሽ ማን ሆነና!

በተለይ ከሥልጣን የወረደው አቃቤ ሹም በየትምህርት ቤኢቱ የተከላቸው ደጋፊ ስለነበሩት በሕዝቡ ላይ ለደረሰው ጥፋት ሁሉ ዋናው ተጠያቂ ንጉሡ መሆናቸውንና አቃቤ ሹም ንጉሡ ያዘዙትን ብቻ የሚሠራ ተላላኪ አስመስለው ለማቅረብ ይሞክሩ ነበር፡፡

አንዱ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ሳያገኝ ቢቀር ሌላ ሐሳብ ይዘነዝራል፡፡

-ለምን መሬት ላራሹ እንደገና አናነሣውም?

-አሁን መንግሥት ስለሌለ ወቅታዊ መፈክር ሊሆን አይችልም፡፡

ተማሪው በዚህ ዓይነት በዕለቱ ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያወጣ ሲያወርድ ባቆጠቆጡ ቡድኖች ተከፋፍሎ ሲፋጭ ብዙ ሰዓት በማለፉ በተለይ ታረቀኝ ብሽቅ አለ፡፡ ታረቀኝ ማርቆስና ቦጋለ የተገኙት በአራት ኪኢሎ ካምፐስ ነበር፡፡

«ይህንን ያህል የሚያጨቃጭቅና ጊዜ የሚያጠፋ አይደለም ጉዳዩ» አለ ታረቀኝ በንዴት ወደ መናገሪያው መድረክ እያመራ፡፡ ሁካታው ትንሽ ጋብ አለ፡፡ ሲያሰኘው ጥሩ ተናጋሪ መሆኑን ስለሚያውቁና በተደጋጋሚ መታሠሩም የታጋይነት ዝና ስላተረፈለት ጆሮዋቸውን አቀኑለት፡፡

«ጉንጤ ወርዶ አዝብጤ ቢተካ ምንም ዋጋ የለውም፡፡ እኛ ሥርዓቱንና የሥርዓቱን የገዢ መደብ አባላት ከቁንጮው ጀምሮ በአንድነት ነው ማየት ያለብን፡፡ ሊነጣጠሉ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ነገ ንጉሡ አዲኢስ አቃቤ ሹም እስኪሾሙ እና የተሾመው ማን እንደ ሆነ እስክናውቅ ድረስ የምንጠብቅበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ የእኛ ተግባር ይህ ይደረግ ይህ አይደረግ ብለን ለንጉሡና ለመንግሥት ጥያቄ ማቅረብ አይደለም፡፡ እኛ ከምናቀርበው ጥያቄ ይልቅ ሕዝቡ እግዚኦ! እያለ ዘወትር ሲለምን ኖሮ የለም? ልመናውን ሰሚ አላገኘም እንጂ፡፡ እኛ ማድረግ ያለብን፤ ሕዝቡ የሚፈጽምበትን በደል እንዲያውቅ መቀስቀስ ነው፡፡ የጭቆና አገዛዝ ይውደም! ስንል ሕዝቡ ምን ያህል እንደ ተጨቆነ እየተገነዘበ ይሄዳል፡፡ እኛ መሬት ላራሹ ስንል የጭሰኝነት ምሬቱ ይባባስበታል፡፡ የእኛ ተግባር መለዮ ለባሹንም ደሞዙንም አስጨምሮ መልሶ ከገዢው ወገን ጋር ተሰልፎ መሣሪያ እንዳይሆን ቁርሾውን የባሰ መቂስቀስ ነው፡፡ ወዝ አደሩም በበኩሉ እንዲነሣ መገፋፋት ነው፡፡ ይህንን ከአደረግን ይህንን መንግሥት ወጥረን እንይዘዋለን

ማለት ነው። ከናካቴው ተንኮታኩቶ የሚወድቅበት ጊዜም ይመጣል!» ታረቀኝ የአድማጮቹን ስሜት ለመገንዘብ ንግግሩን ገታ ሲያደርግ ጥያቄ ተሰነዘረ።

«ከዚያስ በኋላ?»

«ከዚያ በኋላ የሚሆነውማ ሲደርስ እንመልሰዋለን» ሲል እንደ መሳቅ ብሎ መለሰ።

«ይህ ከሆነ ትክክል አይመስለኝም። ነገ የምንፈልገውን ካላወቅን ለመበጥበጥ ብቻ ነው የምንበጠብጠው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ለትኋን ሲባል ቤትን ማቃጠል ያሰኛል» ሲል አንዱ ከመካከል ጮክ ብሎ ተናገረ።

«ሥነ ሥርዓት! መጀመሪያ እንድትናገር አልተፈቀደልህም!» አለ ታረቀኝ ንድድ ብሎ።

«ሥነ ሥርዓት!» አለ የመጀመሪያ ተናጋሪ መልሶ፥ «አንተም ቢሆን መድረክ ላይ ወጥተህ እንድትደሰኩር ፈቃድ የሰጠህ የለም። በዲሞክራሲያዊ መንገድ ከሆነ ሁላችንም የመናገር መብት አለን።»

«ለመበጥበጥና ትግላችንን ለማበላሸት ግን መብት የለህም። እናንተ የምትፈልጉትን እናውቀዋለን» ታረቀኝ ፍርጥም ብሎ ተናገረ።

«ልክ ነው!»

«ልክ አይደለም! ሥነ ሥርዓት!»

«እናንተም ሥነ ሥርዓት! አፋችሁን ዝጉ!» ሁካታና ትርምስ ሆነ።

«እናንተ ስትል ምን ማለትህ ነው? እኔ የግሌን አስተያየት ነው የሰነዘርኩት።»

«የግልህም የመሰሎችህም ጭምር ነው።» ታረቀኝ ንዴቱና ድፍረቱ እየባሰበት ሄደ። አነጋገሩን በመደገፍ የሁካታው ድምፅ አየለ።

ታረቀኝ «እናንተ» ሲል ለመጠቆም የፈለገው ነገር ነበር። ጠያቂው ቢሆን አሽሙሩ በግልጽ ገብቶታል። ከአራትና ከአምስት ዓመት ወዲህ በካምፓስ ውስጥ መከፋፈል ከዚያም አልፎ አተካራና አምባጓሮ ሲፈጠርበት የቆየ ነው። መንግሥትም ልዩነቱንና አሽሙሩን በማራገብ ሊጠቀምበት ሞክሯል። የቅጽልና የአሽሙሩ ምንጭ የፖለቲካ እንቅስቃሴአቸው ከትምህርት ደረጃቸው ጋር ካለው ግንኙነት ጋር የተያያዘ ይመስላል።

-አንደኛ ዓመቶች «ተቅለበለበች ጆሮዬ» የሚለው ዘፈን ቅጽል ወጥቶላቸዋል። ሁሉንም ነገር ለማወቅ የዩኒቨርሲቲውን አየር በሚገባ ለመላመድ ካላቸው ጉጉትና እንቅስቃሴ የተነሣ ነው።

-ሁለተኛ ዓመቶች «ያበጠው ይፈንዳ» በሚለው ዘፈን አርዕስት ይጠራሉ። በእርግጥም ደግሞ በአንደኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲውን ሕይወት ተላምደው፥ እርስ በእርስ ተዋውቀው ለዩኒቨርሲቲው ባለሥልጣኖች የነበራቸውም ፍርሐት ተወግዶ በተማሪዎች ማኅበር መሉ ተካፋይ ሆነው ከፍተኛ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያሳዩበት ወቅት ነው።

-ሦስተኛ ዓመቶች «ትዕግስቴ ገባ ወደ እናቴ» የሚባለው ዘፈን ስያሜያቸው ሆኗል። የፖለቲካ እንቅስቃሴ መሪነቱን በእነርሱ እግር ለተተኩት በአብዛኛው ትተው ወደ ጥናት ስለ የሚያዘነብሉ ነው።

-አራተኛ ዓመቶች የሚጠሩት ደግሞ «ሁሉንም ነገር አይቼዋለሁ» በሚለው ዘፈን ነው። ብዙዎቹ የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ሥራ እርግፍ አድርገው የሚታይባቸው የሚመረቁበትና ሥራ የሚይዙበት ጊዜ መሆኑን ለማመልከት ነው። ትምህርት እንዲቋረጥ ትምህርት ቤት እንዲዘጋ አይሹም።

ይህ የዓመት አደላደል ሁሉንም ተማሪዎች አይመለከትም። ከአንደኛ ዓመት ጀምሮ እያይቋረጡ እየታሠሩ ሰባት ስምንት፥ ዓመት ዩኒቨርሲቲውን የትግል መድረክ አድርገው የኖሩ አሉ። ቅጽሉ የወጣበት ጠቅላላ ዝንባሌ ግን ከሞላ ጐደል ያለ ይመስላል። መንግሥት በተለይ፥ ዓቃቤ ሹም ጐንጤ በተማሪ ስም በዩኒቨርሲቲው ማኅበረ - ሰብ መካከል በአሰማራቻው ሰላዮች አማካይነት አልፎ አልፎ የሚነሳውን ትኵሳት ለማቀዝቀዝ የሚጠቀመው በዚህ ልዩነት ነበር። አንደኛና ሁለተኛ ዓመቶች ትምህርት እናቁም ሲሉ ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ወይም ከአገር ግዛት ሚኒስቴር የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸውና አራተኛ ዓመቶች ቀስ እያሉ ክፍል መግባት ይጀምራሉ። ሌሎች እየተጠባጠቡ ይከተላሉ። እንቅስቃሴው ለጊዜው ይሚሽሻል።

ታረቀኝ እንግዲህ «እናንተ» ሲል አራተኛ ዓመቶችን ማለቱ ነበር። በተለይ ለታረቀኝ አነጋገር የተቃውሞ መልስ የሰነዘረው የአራተኛ ዓመት ተማሪ ደግሞ ቀደም ሲል «ለሽፋን» በማስታወቂያ ሚኒስቴር ይሠራ የነበር «ጸጥታ» ነው ስለሚባል ሁናቴው ልዩ መልክ ያዘ። ሌሎች የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ከእርሱ ጋር በአንድነት ተደምረው በመጠቀሳቸው ተናድደው ስብሰባውን እያቋረጡ መበተን ጀመሩ።

ነገሩ ታረቀኝን ይበልጥ አበሸቀውና «አዩዋቸው እነዚህ የዲግሪ ሱሰኞች ያገር ከዳተኞች በቀውጢ ቀን እውነተኛ መልካቸውን ሲያዩ! ዝም ብላችሁ ታያላችሁ?!» ሲል ጮኸ። በስብሰባው ላይ ተካፋይ የነበሩት ነፋስ እንደነካው ገለባ ድንገት በየአግጣጫው ተበተኑ። በመካከሉ ከየት በኩል እንደ መጣ ያልታወቀ ድምፅ «ጆሮ ጠቢው እንዳያመጥህ! ያዘው!» የሚል ጩኸት አስተጋባ። በዚህ ጊዜ የአራት ኪሎ ካምፓስ ድብልቅልቁ ወጣ። ማን እንደሚሸሽ ማን እንደሚያሳድድ ሳይታወቅ ከፊሎቹ ከአራት ኪሎ በኩል ባለው አጥር እየዘለሉ ተፈተለኩ። ግማሾቹ በጡረታ ሚኒስቴርና በምኒልክ ትምህርት ቤት ጀርባ በኩል አጥሩን እንደ ጦጣ እየቧጠጡ በመውጣት እግሬ አውጪኝ አሉ።

-ያዘው!

-አትልቀቀው!

ጫጫታው ተደበላለቀ። ትራፊክ ታወከ። ጢ ጢዝ! ጢዝ! በዚህም በዚያም የመኪና ጥሩምባ አምባረቀ። የሚሸሸው እየወደቀና እየተነሣ የሚያሳድደው እየተጨዋጨዋኸ በሩቱም ማዕዘን ሲሯሯጥ አላፊ አግዳሚው ከፊሉ በመደነቅ ይመለከታል። አንዳንዱም ተባራሪ ጥይት በመፍራት ፈጠን - ፈጠን ብሎ በመራመድ ከአካባቢው ይሸሻል።

በግቢው ውስጥ የቀሩት እነታረቀኝና ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። ያላሰቡት ሁናቴ በድንገት በመፈጠሩ በመጠኑ ተደናአግረው ክምችች ብለው ሲወያዩ ሁለት ተማሪዎች ጫን ጫን እየተነፈሱ ተመለሱና «ከባድ አደጋ ደረሰ» አሉዋቸው።

«የምን አደጋ?»

«አንድ አራተኛ ዓመት ሠገራ ጉድጓድ ውስጥ ገባ!»

«ምን ሲሆን?»

«ሲሮጥ። ጉድጓድ ግድግዳ አልነበረውምና ሳያውቅ ሲረግጠው ተደረመሰና አብሮ ይዞት ወረደ።

እየተጣደፉ ሁሉም ወደ አደጋው ሥፍራ ሄዱ። ተማሪው የሠፈሩ ሰው አላፊ አግዳሚው ሁሉ ዙሪያ ከቦ ይጯጯሃል። ግማሹ በአዘኔታ ከንፈሩን ይመጥጣል። ሌላው እንዴት ማውጣት እንደሚቻል ምክር ይሰጣል።

«አጠና ክተቱለት።»

«የለም ገመድና መንጠቆ ነው የሚሻለው።»

«ውኃ ቢሞላ ወደ ላይ ያንሳፍፈዋል።»

የመደር አሮጊቶች «እኔን አፈር ይብላኝ» እያሉ ደረታቸውን ይደልቁለታል። አንድ አምስት የሚሆኑ ተማሪዎች አፋቸውና አፍንጫቸውን በመሐረም ሸፍነው ከጉድጓድ ዙሪያ ተደፍተው በአጠና ያማስሉታል፤ ይጣራሉ። አንደኛው በስብሰባው ላይ ከታረቀኝ ጋር የተጋጨውና ጉድጓድ ውስጥ ለገባው ተማሪ ጓደኛው የሆነው ገበየሁ ነበር።

አምቡላንስ መጥራት ማስፈለጉን የተገነዘቡት አንድ አሥር ደቂቃ ከአለፈ በኋላ ነበር። አምቡላንስ እስኪደርስ ደግሞ ግማሽ ሰዓት ፈጀበት። ከጫፉ መንጠቆ ያለበት ትልቅ ሰንሰለት ከተው ሲያገላብጡት የተቀሰቀሰው ሽታ ሰውን መድረሻ አሳጣው። ብዙው ተመልካች አፍንጫውን እየያዘ ሸሸ። ከአንድ ሃያ ደቂቃ በኋላ በመንጠቆው ተጠልፎ ወጣ። አሲዱ ሰውነቱን ባንዳፍታ ገሽልጦ ማን መሆኑ አይታወቅም። ብዙ ሰውም ለማየት አልደፈረም።

አስከሬኑ ወደ ምኒልክ ሆስፒታል ሲወሰድ ገበየሁ ጥርሱን እያፋጨ፥ «አንተ ነህ ይህንን ሁሉ የሠራኸው። አትርሳ። አልረሳትም» አለው ታረቀኝን።

«ምን ለማድረግ?» ታረቀኝ በጨፈገገ ፊት ከላይ እስከ ታች ገረመመረው።

«ምን አስቸኰለህ? የሚሆነውን ሲደርስ ታውቀዋለህ።»

«አገሩን የሚገዛው ለጊዜው ኃይለ ሥላሴ ሳይሆን አሊ ፋሪስ ከሆነ....» ታረቀኝ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ።

«እንዳንተ ላለው ንጉሥ መሆን አያስፈልግም። የእንኔ አባት ደግሞ እንዳንተ ባለው መናኛ ሰው ስሙ አይጠራም።»

«እኔም አልፈልግም። አንደበቴን በመንካቱ ሊያስታውስኝ ይቃጣዋል....በአፌ ቀርቶ....»

ተፋጠጡ። «እባክህ ና ተወው!» አለና ማርቆስ ታረቀኝን በክንዱ ሳበው። ታረቀኝም በራሱ ፀፀት ተውጦ ስለ ነበር ጠቡን ሊገፋበት አልፈለገም። «ከእንደዚህ ያለው ጋር መቀራረብም አፍ መካፈትም አያስፈልግም። እኔ ገና በሩቅ ነው የሚቀፈኝ።»

«ምን አባቱ እንደማደርግ?!»

«እሱንስ አትበል!»

«ፖሀ!»

ከፊቱ ላይ ይነበብ የነበረው ጥላቻ ግን የሁለቱንም ሐሳብ በመጠኑ ሳይቆነጥጥ አልቀረም ነበር።

የካሣሁን ነገርም ለመጀመሪያ ጊዜ አበሸቃቸው።

ካሣሁን ዋሴ፥ እየተንቆራጠጠ የእነታረቀኝን መምጣት ቀኑን ሙሉ በጉጉት ሲጠባበቅ ውሏል። በትንሹ ዛኒጋባ ቤት ተማሪዎች ከሚገቡ ከሚወጡ በቀር፥ ድመት ውሻ፥ ገረድ፥ አልነበረበትም። ዛሬ ደግሞ የባሰውን ሠፈሩ በሞላ እረጭ ብሏል። የሚላላኩ ልጆች ገረዶችና፥ አሽከሮች፥ ብቻ አንዳንድ ጊዜ ይተላለፉ - ፀጥ ብለው - አንገታቸውን ደፋ አድርገው። ዛፎች ሳይቀር ፀጥ ብለው ቆመዋል። የተፈጥሮ ነፋስ ከአየር ላይ የሚንቀሳቀሱ ሳይወዛወዙ። ካሣሁን ብቻ ነበር የሚንቀሳቀሰው። እጁን እያፋተገ ጥርሱን እያፋጨ ቤት ይገባል፤ ይወጣል፤ ከቤት በራፍ ይቀመጣል፤ ተነሥቶ ይንጐራደዳል፤ መንገድ መንገዱን አሥር ጊዜ ይመለከታል፤ ይንቆራጠጣል፤ ይቅበጠበጣል፤ ስሜቱ መንታ ነበር።

በእሥር ቤት ውስጥ ተዋውቆአቸው ቁስሉን አስታመው ያዳኑት በኋላም ወደሚኖሩበት አስጠግተው እንደራሳቸው አድርገው የያዙት - በሥጋ የማይወለዳቸው ወንድሞቹ - ክፉ ነገር አጋጥሟቸው እንዳሆይን በማለት ይጨነቃል። እንደልማዳቸው ታሥረው ይሆን? አሁንስ አያስተርፏቸውም። አርፈው ቢቀመጡ ማናለ? በምን አቅማቸው እናሸንፋለን ብለው ነው? ሲል ከንፈሩን ይመጥጣል። ወዲያው መልሶ ደግሞ ስለ ራሱ ይተክዛል። ይኸኔ አደራ ያልኳቸውን ከቁም ነገር አልቆጠሩትም ይሆናል። ለነገሩማ ባዳ አይደለሁ? አይፈረድባቸውም። ጧት ማታ ሰነዘንዛቸው አሰልችቻቸው ይሆናል።

ጧት ሲወጡ «እስቲ ኧረ ባካችሁ ተቸገሩልኝ - ይላቸዋል።

-እንማከራለን - ሲሉ እንደ ዋዛ ይመልሱለታል።

ማታ ሲመለሱ ራሳቸውን በአሉታ ይነቀንቃሉ። ግን የእርሱ ጉዳይ ቀኑን ሙሉ በሐሳባቸው ውስጥ እንዳልነበር በሁናቴያቸው ያስታውቅ ነበር። የረሱትን ነገር እንዳስታወሳቸው ያህል ድንገት ድንግጥ ይላሉ።

ዛሬም ጧት ተስፋ ሳይቆርጥ ለምኖዋቸው ነበር። የተለመደውን መልስ ሰጥተውት ሂደው ነበር።

«እህስ?» ሲል ካሣሁን ጠየቀ እግራቸው ግቢውን እንደ ረገጠ። በየራሳቸው ሐሳብ እንደ ተዋጡ ዝም ብለውት ወደ ክፍላቸው አመሩ። ተከትሎዋቸው ገባና እነርሱ በታከተና በሰለቸ ስሜት ኮታቸውን እያወላለቁ እንደማረፍ ሲሉ ‹እንዳች ፍንጭ አላገኛችሁም ወይ? እኮ ነው የምለው ወንድሞቼ!»

«የምኑን?» ሲል ቦጋለ መልሶ ጠየቀ።

«የሚስቴን የዘይኔን ነዋ!» የእነርሱ ሐሳብ ግን የሚያሰላስለው ሌላው ጉዳይ ነበር። ነገር ቀብር አለ። ከዚያ በኋላ ስብሰባ ይደረግ ይሆናል።

መልስ አልሰጡትም።

«እኔማ መስሎኝ ነበር ጭንቀቴን ያዋየኋችሁ።» ካሣሁን አንገቱን ደፍቶ በስንጥር ቢጤ ጥርሱን እየነቀሰ ተከዘ። ተከፋ። «እኔማ መስሎኝ ነበር።»

«ኡፋ! ምናለ ብትታገሥ!» ታረቀኝ ድንገት ሳይታወቀው የገነፍለበት ቁጣ መልሶ ራሱን ሳይቀር አስደነገጠው። ከመጠኑ በላይ እንደ ተነፋ ላስቲክ ፊኛ ሳያስበው ነበር የፈነዳበት።

ካሣሁን ለቅጽበት ያህል ስቅጥጥ አለው። ከዚያም ምንም ሳይናገር፥ ነጠላውን አጣጥፎ ለበሰና ወደ በሩ ሲቃረብ «እናንተ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ አመስግኘ አልጨርሰውም» ሲል እንደ መሰናበት እጅ ነሣ።

«ምን እያልክ ነው!» ሦስቱም በመፈናጠር ተነሥተው ከበቡት።

«ኧረ እኔ ምንም አላልኩ!»

«ምንም አላልክ። እሺ ምን እያደረግህ ነው?»

ከበው ዓይናቸውን ተከሉበት። ተራ በተራ አያቸው። ፖሊስ ጣቢያው ታወሰው።

«መቸስ - መቸስ፤ የአርባ ቀን ዕድሌ ጥሎባችሁ፤ መቸም በጣም አስቸገርኳችሁ። እናንተስ ምን ይፈረድባችኋል? ኧረ ኧረ - ውለታችሁን ይክፈላችሁ!»

ታረቀኝ በቀልድም በቁጣም የካሣሁንን አንገት አንቆ እየወዘወዘ ማሳመን ቃጣው። በአነጋገሩ አስቀይሞታል። ካሣሁንም የእርሱ የወቅቱ ስሜት አልገባውም። ለምን አይገባውም? ግን በአነጋገሩ ማስቀየሙ ተሰማው «ካሣሁን - ካሣሁን፥ ሸህ ጊዜ ይቅርታ! ግን ሰው ሲናደድ ብዙ ይናገር የለም? አንተ ተናደህ አታውቅም?» ሁለት ክንዱን ጨብጦ ተማጠነው።

«ለሱማ ብዬ ነው። ሳታውቁኙ ሳላውቃችሁ ባጋጣሚ ድንገት ከእናንተ ላይ ጥሎኝ ብዙ አስቸገርኳችሁ። በችግሬም ስነዘንዝ አበሳጨኋችሁ፤ ስለዚህም ነው....»

«አይደለም!» ማርቆስ ቀበል አደረገ፥ «አንተኮ አላስቸገርከንም፤ አላናደድከንም:: የእኛው አዋዋል ነው ያናደደን:: ለምን አስትነግረውም ታረቀኝ?»

«ስንቱ ተብሎ ይነገራል?» ታረቀኝ ተወራጨ:: ሰመመን እንደ ያዘው ዓይኑን ከድኖ እያሰበ ለማስረዳት ሞከረ:: ካሣሁንም መከፋቱ ወደ ፀፀት ተለውጦ ዓይኑን በተራ በሦስቱም ላይ እያንዣበበ አዳመጠ:: «እና፥ አንተም እስቲ አንዳንድ ጊዜ አስብ:: ለገርዎች መሬት ቁና በሆነችበት ወቅት፤ ስንት ወራት ስለ ተለየሃት ሚስት፤ እኛም ስለአንተ ሚስት ብቻ የምንጨነቅበት ወቅት ነው ማ - ይሙት?» ታረቀኝ በቀልድ ጉሽም አደረገው::

ካሣሁን በክፍል ውስጥ ሲጋራ ሲጨስ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ ታረቀኝ ያቀጣጠልው ጢስ ወደ እርሱ እንዳይመጣ እጁን እያራገበ «እፍፍ» አለ:: በበኩሉ መዝናናት ተሰማው::

«ታዲያ ቦለቲካ ሚስት አትፈልጉ ብሏል? በእንደዚህ ያለ ጊዜ ነው እንጂ የሁነኛ ሰው መፈቃቀድ:: የሕግ ሚስቴ አንድ ሚስቴ እኮ ናት:: በዚህ ባሕር ከተማ ውስጥ በዚህ ቀውጢ ቀን አንድ ነገር ብትሆን ካለኔ ማን አላት? እኔስ ምቸም ይኸው የአምላክ ፈቃዱ ሆኖ እናንተን ጥሎልኛል:: የከተማውን መግቢያ መውጫውን አጣርቼ ባውቀው ኖሮ ራሴው እፈልጋት ነበር:: ቢጨንቀኝ እኮ ነው እናንተን የማስቸግረው::»

«ምንም ችግር የለበትም::» ታረቀኝ ደጋግሞ ሊያለሳልሰው ሞከረ:: «ግን፥ አንድም ፋታ አልነበረንም:: በሰፈር ተዘዋውረን ለመጠየቅ:: ደግሞም መኪና ውስጥ አየኋት ያልካት እሷ ላትሆን ትችላለች:: መኪና እየከነፈ እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል?»

«ዓይነ - ውኃዋ፤ ሳዱላዋ እርሷው ናት:: ደሞም ያላንዳች ምህኛት ልቤ አልደነገጠም:: ውቃቤዬ ሲነግረኝ ነው:: እናንተ ግን ነገሩ የሚያስጨንቅ መስሎ አልታያችሁም መሰለኝ፤ ይኸው ችላ ስትሉት ስንት ቀን ሆነ:: ደሞም አልፈርድባችሁም:: እኔን መሸከማችሁ አንሶ ደግሞ በስንት ሥራችሁ ላይ ሚስቴን ውለዱ ልበላችሁ?» ካሣሁን ግድግዳና ጣሪያውን በትካዜ እየተመለከተ፥ ከአፈርሳታው እልቂት በኋላ ሚስቱ ወደ አባቷ አገር ስትሰደድ፥ ቤተሰቦቿ በመላ በረሃብ ሲያልቁና ዕጣ ነፍሷን ቀርታ አውራው መንገድ ላይ ወጥታ ስትለምን፥ ከዚያም ብዙ ጊዜ የወሬ - ወሬ እንደ ሰማው አገር ቤት እየሄዱ ልጅ እግር ሴት እያባበሉ ለሽርሙጥና ወደ አዲስ አበባ የሚያመጡ ሰዎች ሲወስዱዋት በሐሳብ ታየው:: «ወይ ነዶ!» አለ ከራሱ ጋር:: ቀጠለና «አዲስ አበባ የወሎ ሠፈር የሚባል አለ አሉ:: የት እንደሆነ የሚያመላክተኝ ባገኝ እዚያ ሄጄ ልጠይቅ ይሆን?»

«አየ የዋሁ! ወሎ ሠፈር ሲባል ወሎዬ የሚኖርበት መሰለህ? ምናልባት አንድ ጊዜ የወሎ ሠራዊት ሠፍሮበት ይሆናል:: አሁን ግን ድብልቅልቅ ነው» አለው ቦጋለ::

«እና ምን ተሻለ?»

«ጥቂት ቀን ታገሠን:: አሁን ብታገኛትስ ምን ታረጋታለህ? ራስህ ማረፊያ የለህ! ሥራ የለህ:: አንተም ሥራ የምትይዝበትን መንገድ እንፈልጋለን:: እሷንም አጠያይቀን ልናገኛት እንሞክራለን:: ካቃተንም ገንዘብ እንደ ምንም ፈላልገን በራዲዮ እናስነግራለን» ብለው ታረቀኝ::

«ምን ብለን?»

«ዘይኔ ሙሔ፤ ባልሽ ካሣሁን ዋሴ ይፈልግሻል ብለን

«የዘይኔ ስም በራዲዮ ሊጠራ? ኦሆሆሆ!» ነገሩ ካሣሁንን በጣም አስገረመው፡፡

«ምን ይጐላታል፡፡ እሷም ሰው ሌላውም ሰው» አለና ማርቆስ እንደመሳቅ አለ፡፡

## ፮

ዘይኔ የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ከውሎ ችግር አልተሻላትም ነበር፡፡ በልታ ታድራለች፡፡ ግን ሕይወት ደግሞ ሆድን በእህል ከመሙላት የበለጠ ይጠይቃል፡፡ ፍቅር፥ ነፃነት፥ ሰላም፥ ሌላም ሌላም....ዘይኔ በልጅነቷ ወላጆቿ አይተው የማይጠግቡዋት እስኪመስሉ ድረስ ምላተ ፍቅር ሰጥተዋታል፡፡ በሜዳው በሸንተረሩ በጋራው ላይ እንደ ፈለገች የነፃነትን የሰላምን ሕይወት ኑራለች፡፡ በባልዋ በካሣሁን ጉያም የልብ ፍቅር አግኝታ ነበር፡፡ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በዚያ የረሃብ ግዚኤ ስንኳን በእርሷና በአባቷ መካከል ብቻ ሳይሆን በመላው ጐረቤት ዘንድ የእውነተኛ ፍቅር የመተሳሠብና የመተዛዘን ሕይወት ነበር፡፡ ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ የሆነችውም ደካማ አባቷ ከራሱ ይልቅ ስለ እርሷ ሕይወት ስለ ተጨነቀ ነበር፡፡ በአዲስ አበባ ግን ሰዎች እንደ ጭራቅ የከፋ ሆነው አገኘቻቸው፡፡ ቁታ ነው፤ ጥላቻ ነው፤ ንቀት ነው፤ ሌላም ሌላም ነው፡፡.....

ጭራቅነቱ የተገለጠላት ገና ወደ አዲስ አበባ በፖዞ ላይ እንዳለች ነበር፡፡ አውቶሞቢሉ ሲበር ሰማይና ምድሩ ዙሮባት አጥወለወላትና በባዶ ሆድዋ ሽቅብ - ሽቅብ የሚላትን አፍዋን በጨርቋ ከድና ለመግታት አቅቷት አንድ ሁለት ጊዜ ፍልቅ - ፍልቅ አደረገች፡፡

«እጭ እቴ! ምን ዕዳ ነው! አቁምላት መኪናውን አበላሸችው!» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ደነፉ፡፡ ማናዬ አውቶሞቢሉን ከፍቶ አስወርዷት ከመንገዱ ዳር ስትንጉጥ «ኧረ ኤዲያልኝ! እኔም እርም አልል፡፡ የየትም ባላገር እያግበስኩ መትገባቸው ላይቀር መጀመሪያ እንዲህ ዕቃውን ሁሉ ሲያቆሽሹና ሲያበላሹ አይጣል ነው» በማለት ምሬታቸውን ገለጡ፡፡

ዘይኔ ከአውቶሞቢሉ ወለልና ወንበር ላይ የተንጠባጠበውን በነጠላዋ እየረገጠች «ወድጄን አይደለም፡፡ ቢያመኝ እንጂ፡፡ ሲሆን ያጽናናል፤ እንዴት በሕመም ሰው ይቆጣል?» ሥትል በሆድዋ በመገረም ክፉኛ አዘነች፡፡

ጭራ ሜዳ ላይ እንደዚሁ ሌላ ትዝብት አተረፈች፡፡ ለምሣ አረፉ፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ማናዬ ማናዬ በምግብ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጠው መጀመሪያ ለጥም ማብረጃ አምቦ ውኃ ቀጥሎ ውስኪ ቀርቦላቸው ሲዝናኑ ዘይኔ የምታደርገው ጠፍቷት ከበሩ ጥግ ቁማ ቆየች፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንደ እርሳቸው ድብልብል የሆነውን ሠራተኛ «ወደዚያ በኩል አቀምጣት፤ የምትጠጣውም ውኃ ስታጥ» ብለው ያዘዙት ውስኪውን ሁለት ጊዜ ያህል ተጐንጭተው ጫን ከተነፈሱ በኂላ ነበር፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኂላ የአሞራ ነው እየተባለ የሚታማው ዝነኛው የጭራ ሜዳ የዶሮ ጥብስ ትልልቅ ጉልቻ መስሎ በሁለት ሳህን ቀረ በላቸው፡፡ ተያያዙት፡፡

-ምንችፍ፡፡

-ቁርጥም፤ ቁርጥምጥም።

-ምንችፍ።

-ቁርጥም፥ ቁርጥምጥም።

-ግልጥም - ጋጥ - ጋጥ - ቁርጥም።

-ጉንጭት።

ዘይኔ ከአለችበት አንገቷን ደፋ አድርጋ ስታይ ዓይኗ ውኃ ሞላ። ከዚያ በፊት የግርድና ኑሮ እንዴት እንደ ሆነ አይታ ስለማታውቅ አንዱ ሌላውን አስቀምጦ መብላቱ አዲስ ነገር ሆነባት። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በዘይኔ ግምት አንድ ቤተሰብ የሚሸኘውን ሙሉ ዶሮ ከአጋመሱ በኂላ «ለእርሷ የሚሆን ምግብ አለ!» ብለው ሠራተኛውን ጠየቁት።

«ክክ ወጥ ሥጋ ወጥም አለ።»

«ዋጋው እኩል ነው?»

«አይይ!»

«ታዲያ ምን ትቀላምዳለህ!» ሲሉ ተቆጡ።

ዘይኔ በክክ ወጥ የቀረበላት እንጀራ ከብዙ ወራት ወዲህ ተመግበው የማታውቅ ቢሆንም የዶሮ ጥብሱ ከሐሳቧ አልጠፋ አለ። ድምፁ በአዕምሮዋ ውስጥ እያቃጨለ አስቸገራት።

-ምንችፍ።

-ቁርጥም፤ ቁርጥምጥም።

-ቋቋቋ - ቱፍ።

«ማየት መጥፎ ነው። ዶሮም ይመረኝ!» የእነርሱን ያህል ራሷንም ታዘበችው።

ማናዬ በበኩሉ፤ ከምግብና ከመጠጥ ብዛት ፊት በወዝ ተጭረቅርቆ፥ ጥቅሻ አይሉት ማሽኮርመም ዓይኑኡን አጉረጠረጠባት።

ዘይኔ አዲስ አበባ ገብታ ከዚያ በፊት ከአደረባት ትዝብት የባሰ የሚጉፈንነውን የግርድና ሕይወት ተያያዘችው። በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጠባይ ጋር።

ከጆርባና ከጉን በኩል በሦስት ማዕዘን የተዘረጋው የወዘሮ ዘርፈሽዋል ማድቤት ክፍል ብዛት ከዋናው ቤት ይበልጣል። አንዱ ክፍል ከመሬታቸው የሚጫነው ከአሰኛቸውም ከአዲስ አበባ የሚሸመተው እህል ማስቀመጫ ነው። የሌለ የእህል ዓይነት የለም። ጆንያ ሙሉ ጅንጅብል ሳይቀር ይቀመጣል። የክፍሉን ቁልፍ ራሳቸው ብቻ ናቸው የሚይዙት። ሁለተኛው ክፍል የተሰናዳውና በየጊዜው የሚወጣው እህልና ምግብ - ቀመስ ነገር የሚቀመጥበት ነው። የጤፍ የሽሮ፥ ዱቄት በሶ፥ ብቅል የተወቀጠ ጌሾ፥ ክክ የተቀመመና የተፈጨ በርበሬ፥ የበሶ የጭኮ ዱቄት

ቅመማ ቅመም ማጠኛ ቅጠላ - ቅጠልና ሥራ ሥር ማር በአቆማዳ ቅቤ በገረወይና ሁሉም በዓይነቱ በየረድፉ ተደርድሮአል። ከእርሱ ቀጥሎ ያለው ክፍል ጠላ መጥመቂያውን ጠጅ መጣያውን ክፍል ነው። አልፎ አልፎ የማር አረቄውና የኮሶ አረቄው ይወጣበታል። ከዋናው ቤት የጋዝ ምድጃና ኩችና ቢኖርም ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ለቀቅ ያለ ቅንጦት ሲያምራቸው «ኧረ ኤዲያልያልኝ! ጋዝ ብሎ ነገር። ለችኮላ ያመቻል እንጂ ጢስ ያልሸተተው ወጥ አይጣፍጥም» ስለሚሉ አራተኛው ክፍል የእንጀራ መጋገሪያና በማገዶ የወጥ መሥሪያ ነው። ሌሎቹ ሁለት ክፍሎች የሠራተኞች መኝታ ቤት ናቸው።

የሠራተኞቹ ክፍል ድልድል ደረጃ አለው። ምግብ አቅራቢዋ የዋናው ቤት ክፍል ተላላኪዋና ጽዳት ሠራተኛዋ በዕድሜዋ ልጅ እግር በአለባበሷም ጸዳ ያለች ናት። መካከለኛ ዕድሜ ያለት ወጥ አብሳይዋ እንደዚሁ አለባበሷ ለክፉ አይሰጥም። ሁለቱ፥ ከሁለት የአጠና አልጋና የገለባ ፍራሽ ጋር አንድ ክፍል ይዘዋል። ከዕቃ ቤቱ ማዶ ጫፍ ያለው አንድ ክፍል የአገር ቤት ዘመድ ሲመጣ የሚያርፍበት የሽቦ አልጋ ተዘርግቶበት የሚቀመጥ ነው። ከሱ ጐን ያለው አንድ ክፍል ቅጥር ሠራተኛ አይሉት ቋሚ ደሞዝ የለው ዘመድ አይሉት እንደ አሽከር መታየቱ አልቀረ ከብዙ ዓመታት በፊት በአጋጣሚ ወደ ገብቶ አገር ቤት ሲወጡ አንጋች ፍርድ ቤትና መሥሪያ ቤት ሲሄዱ እንደ ጉዳይ ፈጻሚ እየሆነ ለሚያገለግላቸውና ማናዬ ገብቶ እስከ ፈነቀለው ድረስ ታማኝ አገልጋያቸው ለነበረው አሽከር በግል ፈነቀለው ድረስ ታማኝ አገልጋያቸው ለነበረው አሽከር በግል የተሰጠ ነው። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከገበታ ላይ እኩል ባያስቀምጡትም ደስ ሲላቸው «አሼ!» እያሉ በቁልምጫ ይጠሩት ነበር። የዛሬን አያርገውና እሱም ቀን ይወጣልኛል ብሎ ተስፋ ነበረው። ማናዬ፥ ልባቸውንም አልጋቸውንም ወርሶ በግቢው ፈላጭ ቆራጭ ሲሆን አሽከር መነጫነጭ ሲያመጣ ወይዘሮ ዘርፈሽውሳልም የባሰውን ችላ እያሉት ሄዱ። የቀረው አንድ ክፍል በዕድሜ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቢያንሱ እንጂ የማይበሉት የኑሮ እንግልት ግን የሰማንያ ዓመት አሮጊት ያስመስላቸው አንድ እግራቸው ከቋንጃቸው ላይ ተሰብሮ ወልከም ጐተት እያሉ፥ ጠላ የሚጠምቁት ጠጅ የሚጥሉትና እንጀራ የሚጋግሩት አጋልጋዮች መኝታ ክፍል ነው። የሚተኙት ኬሻው አልቆ ገለባው ጕዝጉዝ በሆነ ፍራሽ ከወለሉ ላይ ነው። ሠራተኞቹ «እማማ እንኮዬ» እያሉ ይጠሩዋቸዋል። የወይዘሮ ዘርፈሽዋል መጥሪያ ደግሞ «ሰው ባጣ» ዘይኔ አዲስ የገለባ ፍራሽ ተገዝቶላት ከእንኮዬ ጋር እንድትዳበል ተደረገ። አልጋ ግን አልተሰጣትም። ሥራዋም እንደርሳቸው መሆኑ ተነገራት።

ጧት ወጥ ቤትዋ ወይም አቅራቢዋ በር አንኳኰታ ታስነሣዋለች። «እሳ! ብድግ ብድግ! የይምን ተጋድሞ መዋል ነው? ቀለብተኛ መሰላችሁ!»

አስቀድመው የሚነቁት አስቀድመው እንደ ምጥ «እእእ!» እያሉ ከተጋደሙበት የሚነሡት እንኮዬ ናቸው።

«አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ!» ይሏታል ዘይኔን ከጐንዋ በርከክ ብለው በእጃቸው ነቅነቅ ነቅነቅ እያደረጉዋት።

ከዚያም በባዶ ሆዳቸው ሥራውን ይያያዙታል። አንድ ጊዜ መከካት ነው። ደግነቱ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሁለት የባሕር ድንጋይ ወፍጮ አላቸው። ሌላ ጊዜ መውቀጥ ነው። መጋገሩ ማንኮሩ ማቡካቱ ይቀጥላል። እህል መልቀሙን ማንፈሱንና መንፋቱን ስንኳ እንደ ዕረፍት

እንጂ እንደ ሥራ አይቆጥሩትም። ከሰዓት በኋላ እነ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ምሳ በልተው ቡና ጠጥተው ዕረፍት ሲያደርጉ ጥቂት ፋታ ያገኛሉ። የምሳ ጊዜያቸው ነው።

እንደ ክፍላቸው ሁሉ ምግባቸው ደረጃ አለው። አንኮዬና ዘይኔ ሦስት ዓይነት እንጀራ ይጋግራሉ። ነጭ ጤፍ ቀይ ጤፍና ሦስት እጅ በቆሎ ዋእይ ማሽላ የሆነ ጋሬ። ሽታው ግቢውን የሚያውድ ወጥም በየዓይነቱ ይሠራል። ለእንኮዬና ለዘይኒኤ ምሳና እራት የሚቀርብላቸው ጋሬና ዶኬ ነው። በራሳቸው ክፍል ወይም በዋናው ቤት ኩችና ስለሚመገቡ የሌሎቹ ሠራተኞች ምግብ የትኛው እንደሆነ እነዘይኒዬ በዓይናቸው አላዩም። የከንፈራቸው መወዛዛት ግን ከዶኬ የተለየ መሆኑን ይጠቁማል። ለእነ እንኮዬ ከእነ ዘርፈሽዋል ገበታ የተረፈውን ስንኳ አያቀምሷቸውም። እየተሰጣ ድርቆሽ ይሆናል።

አንድ ቀን ዘይኔና እንኮዬ በሥራ ቁምስቅላቸውን ሲያዩ ውለው መኝታ ክፍላቸው እንድ እገቡ እንኮዬ ከድካማቸው የተነሣ ጋሬና ዶኬያቸውን ተቀምጠው መብላት አቅቷቸው እያቃሰቱ ተጋደሙ
።

ዘይኔ በአዘኔታ እየተመለከታቸው «ለመሆኑ ሁልጊዜ እንደዚህ ነው ሥራዎ?» ስትል ጠየቀቻቸው።

«ዕድሜ ልኬን ይኸው ነው። ሥጋዬን ጨረሱት። ነብሴ ብቻ ነው የቀራቸው» በማለት አማረሩ። «ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሚሠራ ነገር ባይኖር እኔን በሥራ ለመግደል ቋጥኝ ስበሪ ይላሉ። ከድካም የተነሣ መንቀሳቀስ ሲያቅተኝ ደስ ይላቸውና ዱላቸውን አንሥተው መዓቱን ያወርዱብኛል። በያ ሰሞን ለልጃቸው ሠርግ ስንደግስ አንድ ቀን መድኃኒት ጠጥቼ መንቀሳቀስ ቢያቅተኝ በዱላ ሊጨርሱኝ በሰውዬው ገላጋይነት ተረፍኩ። ሰሞኑን ደግሞ መልስ መትራታቸው ነው መሰለኝ፤ አይጣል ነው።»

«ራትዎን ቢበሉ ይሻላል።» ዘይኔ ገበታውን ወደ ተጋደሙበት አቀረቡላቸው። «ለመሆኑ ለምን ጥለዋቸው አይሄዱም?» ስትል እንደ ዋዛ ጠየቃቸው። እሷም እንዴት እንደትኖር እያሰበች።

«የት ብዬ እሄዳለሁ ብለሽ? ካለርሳቸው ሌላ ሰው ሌላ ቤት አላውቅም። ደግሞ ይህንን ደካማ ሰውነት ይገፎ።» የተሰበረ ሰላላ እግራቸውን በአንድ እጃቸው ብድግ አድርገው አሳዩዋት። «ማነው ገረድ አድርገው አሳዩዋት። ልለምን ብለሽ? ለጠላቴም አያሳየው። እሜቴም ቢሆኑ የትም አሳድደው ነው መልሰው የሚያመጡኝ» እንደ ተጋደሙ አይናቸውን ከደን አድርገው በሰመመን ጋሬውን ያኝኩ ገቡ።

«ምን ሆነው ነው እግርዎን?»

«እሜቴ ናቸው!»

«በዱላ ሰበርዎት?»

«በጥይት!»

«ለመግደል? ምን አረጉ ብለው?»

እሳቸውማ አይደለም ነው የሚሉት። ታሪኩ ረጅም ነው ልጄ።» ንግግራቸውን አቋርጠው አሰቃቂ ትዝታ ለማየት ያልፈለጉ ይመስል፤ በእንግልት የጠወለገ ፊታቸውን ጭፍግግ በጢስ የላመ ዓይኖቻቸውን ጭፍን አደረጉት። ዘይኔ አንጀቷ እንደ መላወስ እየቃጣው ዝም ብላ ጠበቀቻቸው።

«ለመሆኑ አደጋው ከደረሰብዎት ብዙ ዘመን ነው?» ስትል ጠየቀች ታሪካቸውን ለማወቅ ያደረባት ጉጉት አላስችል ብሏል።

«ሠላሳ ዓመት ያልፈዋል።»

«ምን መጥፎ ዕድል ጣለዎች ከእሳቸው እጅ፥ እቴ።»

«እኔ ወድጄን አይደለም ከእጃቸው የወደቅሁት።»

«እህሣ?»

«አየሽ ልጄ» አሉ ድንገት አንድ ሐሳብ እንደ መጣባቸው ከአንገታቸው ቀና ብለው «እሜቴ ጌቶችን ሲዳሩ አንድ ደጃማች ዘመዳቸው እኔን ደንገጡር አድርገው ሰጡኝ። የእኔን እናት ደጃማች ጥንት የገዟት ስለ ነበር እኔም ከቤታቸው ተወልጄ ነው ያደግሁት። አሁን እኔን ስታይኝ አልመስልም እንጂ በዕድሜ የእሜቴ እኩያ ነኝ። ታዲያ በሠርጋቸው ጊዜ የደረስኩ ኰረዳ ነበርኩ። ጌቶች መጥፎ ዓመል ነበረባቸው ስለሚባል ዓይናቸውን ከኔ ላይ ባሳረፉ ቁጥር እሜቴ የውስጥ ገላዬን በአለንጋ ወደ ውጭ ይገለብጡታል። ጌቶች መልሰው ገላዬን በአመል ያገላብጡዋቸዋል። ነው እንጂ ያን ጊዜ ስንኳ ጌቶች ከኔ ጋር ምንም ነገር አላደረጉም ነበር። ያን ጊዜ ጌቶች አገረ ገዥ ነበሩና ይህንን ሁሉ ችዬ በዚያ ስንኖር፥ አንድ ጌቶች ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ተነሡ። እንኮዬን ይዤ ነው የምሄደው አሉ። በሰማይ ነብሳቸውን ይማርና፥ ጌቶች ታዲያ አዲስ አበባ ቤት ስገባ ስወጣ ማን በር ይክፈትልኝ? ማን እንጄን ያስጣጥበኝ? ብለው ተቆጡ። እሜቴ እኔ አብሬዎት ልሂድ አሉ። እንዴት ተደርጎ ቤት ንብረቱን ለማን ትተን ብለው ጌቶች እሳት ሆኑ። ሲቆጡ አይጣል ነው መቸም። ሁለቱም ያው ናቸው። በመጨረሻ ጌቶች አሽነፉና ከአንድ ሁለቱም ያው ናቸው። በመጨረሻ ጌቶች አሸነፉና ከአንድ አሽከራቸው ጋር አዲስ አበባ ይዘውኝ ወጡ። ሰነባበትን። አንድ ቀን ገላዬን ታሺኛለሽ ብለው ፍል ውኃ ይዘውኝ ገቡ።» እንኮዬ በአንድ ዓይነት ትዝታ ልም ዓይናቸውን ስልምልም ጥርሳቸውን ፈገግ አደረጉና ታሪካቸውን አቋርጠው ተውት።

«ይጨርሱት እንጂ» አለች ዘይኔ ሁናቴያቸው አስገርሟት።

«ምን የሚጨረስ ነገር አለው? ደጋግመን ፍል ውኃ እየገባን ገላቸውን አሸላቸው ጀመር።»

«የጥይቱን አደጋ ማለቴ ነው።»

«እሱማ» አሉ እንኮዬ መልሰው ፊታቸውን ጭፍግግ በማድረግ። «አዲስ አበባ ደህና ቆይተን ወደ ጌቶች ግዛት የተመለስን ለታ ነው። እሜቴ ከቤት ወጡና ጌቶች ከበቅሎ ሳይወርዱ

ጠመንጃውን ተቀበሉዋቸው፡፡ እኔ ከኂላ ነበርኩ፡፡ ወዲያው ጠመንጃውን ዞር አደረጉና አዳፈኑብኝ፡፡ ጌቶች ጀርባቸው ከእኛ በኩል ስለ ነበር እንዴት እንደሆነ አላዩም፡፡ ገደልሻት ልጅቷን! ብለው እሳት ሲሆኑ፥ እሜቴ አፈር በበላሁ፥ ባርቆብኝ ነው፡፡ ለምን አላስጠበከውም ነበር ብለው ድርቅ አሉ፡፡ እኔ ግን ማስጠበቂያውን ሲፈለቅቁት ያየሁ መስሎኛል፡፡ ከዚያ ቊስሉ ትል እያፈራ ስድስት ወር ሙሉ ተኝቼ ወይ ተቆርጦ ሳይወድቅ እንዲህ ሆኜ ቀረሁ እልሻለሁ፡፡ ያም አልበቃ ብሏቸው ይኸው እስከ መቃብሬ ድረስ ፍዳዬን ያሳዩኛል፡፡» እንኮዬ በፍዳ ያሳለፉትን ዘመን በሐሳባቸው የሚለኩ ይመስል ዓይኖቻቸውን ክድን አድርገው ዝም አሉ፡፡

የእንኮዬ ታሪክ፥ ዘይኔ በበኩልዋ በከበደ ሚስት ላይ ያደረሰውችውን አደጋ አስታውሷት የፀፀት ዕንባ ተናነቃት፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ለመድገድ ተኰሱ፡፡ ግን አካል ጐዱ እንጂ ነፍስ አላጠፉም፡፡ በእኔ ምክንያት ግን ሕይወት ጠፍቷል፤ ስትል በሕሊናዋ ራሷን ወቀሰውች፡፡ መልሳ ደግሞ ግንኮ እኔ አልደረስኩባት፡፡ እርሷ ናት ከመሬት ተነሥታ የቀናችብኝ፡፡ እሷ ናት የተቀናቀነችኝ የደበደበችኝ አስቀድማ ባገር ፊት ያዋረደችኝ፡፡ ደሞም ዘነዘናውን ስሰነዝር ለክፉ ያደርሳታል ብዬ አልነበረም - ስትል ራሷን በራሷ አስተባበለች፡፡

ዓይኖቻቸውን ገለጥ ሲያደርጉ ከሐሳቧ ጋር የምትሟገት መሆንዋን የተመለከቱት እንኮዬ «አይዞሽ አትፍሪ እስከዚህም፡፡ ዋናው ነገር መጠንቀቅ ነው» ሲሉ መከሩዋት፡፡

«ከምኑ?»

«ከማንኛውም ነገር፡፡ እሜቴ ቂመኛ በቀለኛ አጉል ቀናተኛ ናቸው፡፡ ከዚህ ግቢ እስካሉ ድረስ የወንድ ፊት ቀና ብሎ አለማየት ነው የሚሻለው፡፡»

«ወቸው ጉድ የደላው ሙቅ ያኝካል አሉ፡፡ በሬሳ ላይ ተረማምጄ የመጣሁ ሰው እንዲህ ያለውን ነገር የማስብበት አንጀትም የለኝ» ስትል በምፀት መለሰችላቸው፡፡

ሌሊቱን ግን የካሣሁን የወይዘሮ ዘርፈሽዋል የከበደ ገጽታ እየተለዋወጠና እየተዘበራረቀ በሕልሟ በመምጣት እንቅልፍዋን ሰቀቀናም አደረገባት፡፡

ብዙም ሳይቆይ እንኮዬ ያስጠነቀቁዋት ነገር ደረሰ፡፡

የዋናው ቤት ገረድ ፈቃድ ተቀብላ ሂዳለች፡፡ ወጥ ቤትዋ ገረድ በርበሬ ልታስፈጭ ሂዳ ዘግይታለች፡፡ በመከላከል እንግዶች መጡና ዘይኔ ቡና አፍልታ እንድታቀርብ ታዘዘች፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቡና የሚያስቀርቡት እምብዛም ለማይጨነቁለት እንግዳ ነው፡፡ «ሥጋና እንትትን ከበላጌ ቤት ይይረክሳል አሉ፡፡ ሁሉን እኩል ከአስተናገዱትማ ቁርጠኛው ወዳጅ በምን ይለያል?» የሚል ፈሊጥ አላቸው፡፡ ቅርብ ለሆነ እንግዳ ሥልጣን፥ ማዕረግ ክብር፥ ሀብት፥ አለው ለሚሉት ግን ጭኮው፥ ቋንጣው፥ ዳቦቆሎው፥ ጠጁ፥ ላቅ ላለውም ውስኪው ነው የሚቀርብ፡፡

ዘይኔ ቡና ማፍላቱ እምብዛም አላቃታትም፡፡ እንኮዬም እየተጐተቱ ረዱዋት፡፡ ከዚያም በዓመት በዓል ጊዜ ብቻ የምትለብሰውን የሙሽርነት ጊዜ ቀሚሷን አውጥታ ለወጠችና ሰውነቷ እየተርበተበተ ሳንቃው የሚጉዳ ይመስል ቀስ አድርጋ እየረገጠች ገብታ፥ የኩችናው ኮሪደርና የሳሎኑ ክፍል የሚጋጠምበትን ማዕዘን ተጠግታ ቆመች፡፡ እስከዚህ ድረስ ስትገባ የመጀመሪያ

ጊዜዋ ነበር። ምንጣፉ ወንበሩ፥ ጌጡ ከመጋረጃው ጀርባ በሐሳብ ብቻ የምታየውን ቤተ መቅደስ መሰላት።

እንግዶቹ ሁለት ጠና ያሉ ሴቶች ነበሩ። ሦስቱ ሴቶች የባጥ የቆጡን ሲጫዋወቱ ማናዬ ትንሽ ፈንጠር ብሎ እንደ ዋዛ ያዳምጣል። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከጭውውታቸው መለስ ብለው እንዳስተዋልዋት፦

«አታቀርቢውም? ምን ትጠብቂያለሽ ተገትረሽ!» አሉ ዓይናቸውን በቁጣ እያጉረጠረጡ። ዘይኔ መጠየቅ ፈርታ ራሳቸው አውቀው ይነግሩኛል በማለቅ ቁማ ጠበቀች።

አሁንም ከጭውውታቸው ፊታቸውን ወደ እርሷ መልሰው፥ «አቅርቢው እኮ ነው የምልሽ! ከእኛው ጋር ቁጭ ብላ ለማውራት አማራት ልበል? አሆሆ! ወይስ አልተፈላም?» አሉ።

«ፍ - ፍንጃሉ» አለች ዘይኒኤኢ ምላስዋ እየተሳሰረባት።

በቋንቋዋ ሦስቱም ሴቶች ጥቂት ተሳሳቁባት። «በዚህ አገር ሲኒ ነው የሚባለው» ሲሉ አንደኛዋ ሴት መከርዋት።

«ያው ከዚያ ውስጥ አለልሽ» ብለው ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሲኒና ብርጭቆ የተቀመጠበትን ኮሞ በእጃቸው አሳዩዋት። ሄደችና እጅዋን ዘርጋ ብታደርግ መስታወቱ አገዳት። ወደ ጐን የሚንሸራተተው መስታወት እንዴት እንደሚከፈት ግራ ገብቷት አጐንብሳ ስትጨነቅ ስትጠብብ «ማናዬ እንደ ውርደት አትቁጠረውና እስቲ አሳያት እባክህ» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል።

ዘይኔ ከኮሞ ፊት ለፊት ጐንበስ እንዳለች ማናዬ መስታወቱን ከፍቶ ሲኒውንና የስኒ ማስቀመጫውን ሲያሳያት፥ ላመል ያህል ክንዱ ትከሻዋን ነካ አደረገው። እሷ እንኳ ማስተሐቀር ቀርቶ አልታወቃትም ነበር። ትርኢቱ በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዓይን ላይ ብቻ ውልብ ብሏል።

«ከባላገር አዲስ የመጣች ናት?» ሲሉ አንደኛዋ ሴት ጠየቁ።

«አዎ!» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በማጥላላት «ከደሴ ስመለስ መንገድ ዳር ቁማ ስትለምን አገኘኋትና ትሆን እንደሆን ብዬ ነበር።»

«አዎ መቸም ከከተማዎቹ ጥቂቲ እነርሱው ይሻላሉ። አይ! አይጣል ነው።»

«ኢጭ ኧረ ወዲያ! ሁሉም ያው ናቸው። ይህችስ አሁን ሳምንት ቆይታ ቡና ቤት ነው የምቀጠረው ባትል አይደል?» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ያንን ድብልብል አንገታቸውን እንደ ማወዛወዝ እየቃጡ ከሳምንት በኋላ ዘይኔ የምታሰማውን የቅሬታ አነጋገር ለማሳየት ሞከሩ።

ዘይኔ ነገሩ ሳይገባት አንገቷን ደፍታ ቡናውን ቀዳችና በመጀመሪያ ለማን ለማን እንደሚሰጥ በዓይኗ አስተዋለች። መጀመሪያ ለወይዘሮ ዘርፈሽዋል አቀረበች። ቀጥላ በዕድሜ ይበልጣሉ ብላ እንደገመተችው ለሁለቱ ሴቶች ሰጠች። በመጨረሻ ወደ ማናዬ ስትቀርብ ከአጠገቡ የነበረው ትንሽ ጠረጴዛ ደንቀፍ አደረጋትና ትንሽ ቡና ከስኒው አፍ እንደ መፍሰስ አለ። ይቅርታ በሚለምን የአዘኔታ መልክ ቀና ብላ አየችው - ጭንቅ ብሏት - መግቢያው

ጠፍቷት። ያላየችው ግን ከከሞው ትርኢት ወዲህ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በዓይናቸ ይከታተሏት እንደ ነበር ነው።

«ዓይንሽ ከሚንከራተት የያዝሽውን ዕቃ እያየሽ አትሄጂም? ኧረ ምኗ ዓይን አውጣዋ ናት እባካችሁ!» ሲሉ ጮሁ። ዘይኔ ተሽማቀቀች። ጠብታ ቡና ማፍሰስ ከባድ ወንጀል መስሎ ተሰማት።

እንግዶቹ እንደ ሄዱና ማናዬ እንደ ወጣ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዘይኔን አስጠሩዋት። በዚህ ጊዜ ወፍጮ ቤት የሄደችው ገረድ ተመልሳ ነበር።

«አንቺ ምን አርገሽ ነው? እሜቴ እሳት - እሳት - እሳት ሆነዋል!» አለች ወጥ ቤቷ እጅዋን እያርገበገበች።

እየተንዘፈዘፈች ገባች። በአንድ በኩል መፍራት እንደ ሌለባት ይሰማት ነበር። ግን አልሆነላትም። የምትሄድበት የላትም። የምታውቀው ሰው የላት። በአራዊት እንደተከበበ ብቸኛ ሰው መድረሻ ጠፋት።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በሳሎኑ ውስጥ፥ ይንጐራደዳሉ። ይንቆራጠጣሉ። በኃይል ሲተነፍሱ ያ - ቋጥኝ የሚመስል ትከሻቸው ከፍ - ዝቅ ይላል። ሁለት እጅ የማይሞላው አንገታቸው እንደ ወናፍ እየተነፋ ጐደል ይላል። ዓይናቸው ተጉረጥርጧል።

«ሁለተኛ» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጥርሳቸውን አገጣጥመውና አንዳንድ ጊዜ ሥራ ሲፈቱ ዳንቴል የሚሠሩበትን ሽቦ ፊቷ ላይ ጠንቁለው «ሁለተኛ እንዲህ ስታረጊ ባይሽ አይማረኝ በዚህ ነው ዓይንሽን አንቍሬ የማወጣው!»

ዘይኔ እሳት ውስጥ እድነ ገባ ቋንጣ መላ ሰውነቷ ወደ ውስጥ ተኰማተ። ፊቷንና ዓይኗን በሁለት እጅዋ ሸፈነችና «እስክላመደው እኮ ነው» አለች በጣም በሰለለ ድምፅ።

«መላመድ? ደሞ ልትላመጂው ኖሯል?» ሲሉጮሁና በቃሪያ ጥፊ አናጉዋት። ሰበብ ሲፈልጉ እንጂ ስለ ቡና ማቅረብ ማለቷን አጥተውት አይደለም። ቅናታቸው ምክንያት እንደሌለው ሁሉ፥ ነገሩን ሆን ብለው ጠምዝዘው ተረጐሙት። ዘይኔ ለቅጽበት ሰማይና ምድር ዞረባት። ጭው አለባት። በጥፊ ስትመታ የመጀመሪያዋ ጊዜ ነበር። አባቷ ሙሔ ልጆቹ እንዳይበላሹበት ሲያጠፉ ከመቅጣት የማይመለስ ቢሆንም ጥፊ የሚባል ነገር ከፊታቸው ላይ እንዲያርፍ ፈጽሞ አይፈቅድም ነበር። ልጅን ድንጉጥ የሚያደርግ መጥፎ ቅጣት ነው ይላል። በደመ - ነፍስ እየተንገዳገደች ወደ ክፍሏ ሄደች።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሾላ ላይ የድንጋይ ናዳ ያወረዱባቸውን «ምናምንቴዎች» በጥርሳቸው ያገኙ ይመስል ቁጣቸው ወዲያው ጥቂት በረድ አለላቸው። እሳቸው ያን ጊዜ የደነገጡትን ያህል አሁን ደግሞ ገረዳቸውን አስደንግጠው ተወጡት።

«ምናባታቸው ካለበለዚያ አይቻሉም» አሉ ከፎቴአቸው ላይ እየተዘረፈጡ። ለቅናቱ ይሁን፥ ወይም ሾላ ላይ ሲደንግጡ ስላየቻቸው ከአሁን ልክ ለማስገባት፥ የቅጣታቸው ምክንያት ለራሳቸውም ግልጽ ሆኖ አልተሰማቸውም።

ዘይኔ ለጊዜው ሥቃዩ አልተሰማትም - ምንም ነገር አልተሰማትም፡፡ ስሜቷንም ሆነ አስተሳሰቧን ጥፊው ከሰውነቷ ላይ እፍፍ ብሎ እንዳይጠፋው ያህል ባዶ ሆነች፡፡ የማያስብ፥ የማይሰማው ቡድን....በዚህ ጊዜ ሁሉ እንኮዬ እየጠራች እየቀሰቀሰች ልታጽናናት ሞክራ ነበር፡፡ ሌላ ሰው እንዳይሰማት ቀስ ብላ.....

ቀስ በቀስ ከድንጋጤዋ እየነቃች አእምሮዋን እየገዛች አካባቢዋን በሚገባ መገንዘብ ስትችል፥ የቀኑ ብርሃን ድርሻውን ጨርሶ በቦታው ሌሊት ነግሦ ነበር፡፡ በምሥራቅ በኩል የወጣች ሙሉ ጨረቃ ምድሩን ወርቃማ ብርሃን አልብሳዋለች፡፡ ጨረቃን ያጀቡት ከዋክብት የጠራውን ሰማይ እንደ ፈርጥ አሸብርቀውታል - እየተጠቃቀሱ፡፡ ሰው ሁሉ በየቤቱ ተከትቶ ጸጥታ ሰፍኗል፡፡ አልፎ አልፎ ብቻ የውሻ ጩኸት ይሰማል፡፡ ነፃ ለሆነ ሰው ሰላም ለሆነ ሰው ውብ ምሽት ለዘይኔ ግን የሰቀቀን ምሽት ነበር፡፡

ከማድ ቤቱ ታዛ ሥር ተቀምጣ፥ ወባ እንደያዘው ሰው መላ ሰውነቷን እስኪንዘፈዘፍ ድረስ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፡፡ በዳገታማ ሚካኤልና በቆሬ፥ ስቃ የምታሳስቅ የምትመስለው ጨረቃ - ድንቡልቦቃ አሁን እንደ ዘይኔ ፊቷን ያጨፈገገች የተከዘች መሰለች፡፡

## ፯

አዲሱ አቃቤ ሹም ማን እንደሚሆን ሰው በየቤቱ ግምቱን ሲያወጣ ሲያወርድ፥ አዲስቱ አቃቤ ሹም ስለሚመርጣቸው የሥራ ባልደረቦች በመላ ምት ስም ሲጠቅስ፥ የቤተ መንግሥት አካባቢ በራሱ የውስጥ ደንብ ሹም ሽሩን ያከናውን ነበር፡፡ ንጉሡ ራስ ዠማነህን የቀድሞውን አቃቤ ሹም ጉንጤንና ጀነራል መብረቁን አስጠሩና ጄነራል መብረቁን ኮሚቴ በፍጥነት እንዲያቋቁም አዘዙት፡፡ ወዲያው የቀድሞው ኮሚቴ አባሎች ተሰበሰቡ፡፡ ጄነራል መብረቁ በወግ አጥባቂነት የታወቀ ቢሆንም በምርጫ ብዙዎቹ የተስማሙበት መሰሉ፡፡ ጉዳዩ እንዳለቀ ተቆጥሮ ጄኔራል መብረቁ የኮሚቴ አባሎችን ለመምረጥ የቀድሞ ኮሚቴ አባል አቶ አጥላው ደግሞ ንጉሥ ስለ አዲሱ ሹመት የሚሰጡትን መግለጫ ለማዘጋጀት አብረው ወደ ሸንጎ ጽሕፈት ቤት ሄዱ፡፡ አቃቤ ሹም ጉንጤና አንዳንድ የቀድሞ ኮሚቴ አባሎች ደግሞ፥ ሁለተኛ ክፍለ ጦር ላቀረበው ጥያቄ የጽሑፍ መልስ ለማርቀቅ ወደ ኮሚቴው የመሰብሰቢያ አዳራሽ አመሩ፡፡ ራስ ዠማነህ ብቻ ከንጉሡ ጋር ቀረ፡፡ ዙሪያውን ቃኝቶ ሌላ ሰው በአጠገቡ እንደሌለ ከአረጋገጠ በኋላ እጅ እንደ መንሣት ዓይነት መላጣ ጭንቅላቱን በመጠኑ ጎንበስ አድርጎ «ምክር ለማቅረብ ይፈቀድልኝ ጃንሆይ?» ሲል ጠየቀ፡፡

«ምንድን ነው?» ሲሉ በሰለቸ አንደበት መልሰው ጠየቁት፡፡

«የሕዝብ የሰለቻቸውን የሹማምንት ኮሚቴ መለዋወጡ ችግሩን የሚያቃልለው አይመስለኝም» በማለት መለሰ፡፡

«ታዲያስ?»

«አሁን በጦር ኃይሎች ውስጥ የሚታየው አመፅ ምልክቱ እንጂ በሽታው አይደለም፡፡ ሕዝቡ ሹማምንቱን አንቅሮ ተፍቷቸዋል፡፡ በሽታው ይህ ነው፡፡»

«ታዲያስ?»

«የሚሻለውም፥ ሕገ መንግሥቱን ማገድ፥ ሸንጎውን መበተንና ራስዎ አቃቤ ሹም ሆነው አዲስ ሕገ መንግሥት እንዲረቀቅ ማድረግ ነው» አለ ራስ ዠማነህ።

«ምን ትቀባዠራለህ? እንደገና ወደ ታች ወርደን የእናንተን ሥራ እንሥራ?»አነጋገራቸው ግን ፍጹም እምቢታ አልነበረም። ራስ ዠማነህ በጉዳይ ከመግፋቱ በፊት የንጉሡ ዋና አጋፋሪ እየተቻኰለ ገባ። ራስ ዠማነህ ነገሩን ሳይጨርስ ሹልክ ብሎ ወጣ። ዋናው አጋፋሪ ቀረብ አለና «ጃንሆይ ልጅ ጉግሣ ለምን ዓቃቤ ሹም አይሆንም?» ሲል እንደ መለመን ዓይነት ጠየቀ።

«ወይድ! ምን ትቀባጭራለህ? አንድ ጊዜ ወስነናል» ጆላ ጆል ቢጤ ስለሆነ የሚቆጡት እንደ ልጅ ወይም እንደ አሳደጉት ለማዳ ውሻ ነው። እሱም ቢሆን የጌታውን ጠባይ እንደሚያውቅ ለማዳ ውሻ በአቀራረቡ ጥቂት ይደፍራቸዋል። ጓደኛ ያጣ ይመስል የንጉሡ ውሻ ሉሉ የሞተች ጊዜ ዕንባ አውጥቶ አልቅሶአል ይባላል።

«ለርስዎ ብዬ ነው እንጂ እኔ ምን ተዳዬ፥ ጃንሆይ። ግና ውሳው የማይለውጥበት ምክንያት አይታየኝም።»

«ለምን ነው የሚለወጠው?»

«አንደኛ፥ በትምህርቱ የላቀ ነው። ሁለተኛ፥ የቀድሞው ኮሚቴ ውስጥ የነበረ ቢሆንም፥ ስሙ በመጥፎ የተበከለ አይደለም። አሜሪካኖችም ቢሆኑ ይወዱታል። ከዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ ወታደሩ እንደሚቀበለው መረጃ ደርሶኛል።»

«ታዲያ እስከ አሁን የት ነበርክ?»

«መረጃው ትክክለኛ እስካረጋግጥ ነበር።»

«አሁንስ?»

«መቶ በመቶ እርግጠኛ እስክሆን ጃንሆይ ጥቂት ደቂቃ ይታገሡኝ።»

ንጉሡ መስማማታቸውን በመግለጽና በማሰናበት መልክ ካባቸውን ወለብ አደረጉ።

ከሰዓት በኋላ ጄኔራል መብረቁ የኮሚቴ አባሎችን ስም ዝርዝር አውጥቶ አጥላው መግለጫውን አዘጋጅቶ ጋዜጠኞች ማስታወሻ ደብተራቸውን ቴፕ ሪከርዳቸውንና ፎቶግራፍ ማንሻቸውን ይዘው ቤተ መንግስት ሲደርሱ፥ ንጉሡ ጥቂት ድካም ተሰምቷቸው ዕረፍት በማድረግ ላይ ስለሆኑ ለሌላ ጊዜ መተላለፉን ተነገራቸው። ግቢው ትንሽ ጭር ያለ ይመስላል። ከወዲያ ወዲህ የሚያጠረጠረው የቤተ መንግሥቱ ዋና አጋፋሪ ብቻ ነበር።

ማታ ንጉሡ ልጅ ጉግሣን አቃቤ ሹም አድርገው መሾማቸውን በራዲዮና በቴሌቪዥን አስታወቁ። ጄኔራል መብረቁ ሌላ ቁልፍ ሹመት ተሰጠው።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከተቀመጡበት ፎቴ ላይ እንደ መዝለል እየቃጣቸው «እንዲያ ነው እንጂ! እንዲያ ነው እንጂ! ጃንሆይ አሁን ገና ለበሙ። ማንንም አጠራቅመው መጫወቻ

አድርገው! የጨዋ ልጅ ግን ምንጊዜም ውሉን አይስትም። የአባቱ የነበረውን ሥልጣን ነው የተረከበው። የሚገባውን!» ሲሉ ፈነደቁ።

የቀድሞው አቃቤ ሹም ጕንጤ፥ ስለ ከንፈሩን እየበላ፥ «አሃ! ለካስ ይሄ ኖሯል። ጥሩ ነው። ማን ጲላጦስ ሆኖ እንደሚያመልጥ እናያለን» ሲል ራሱን ነቀነቀ።

እነታረቀኝ «የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእንቅቡ ወደ ምጣዱ ሊገባ? አይደረግም!» ሲሉ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም፥ በሚል አርእስት በቁጣ ተነሣስተው የራሳቸውን መልስ ማዘጋጀት ጀመሩ።

ከአዲስ አበባ አራት መቶ ኪሎ ሜትር ርቆ በደሴ ሆስፒታል ከቍስሉ በማገገም ላይ የሚገኘው ማስረሻ ደግሞ የሹም ሽሩን ወሬ ሲሰማ ሐሳቡ ተማታበት። ግን ሁኔታው እሱንም እንደሚነካው በጊዜው አልገመተም ነበር።

# ምዕራፍ ሁለት

«የትምህርት ሚኒስቴር ለድርቅ ቀበሌ ደብተርና እርሳስ በነፃ ሊሰጥ ነው።»

«በወሎ፥ በትግሬ፥ በሸዋና በሐረርጌ ግዛቶች በድርቅ ምክንያት ጉዳት በደረሰባቸው አውራጃዎች በሚገኙ ት/ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ሃያ አምስት ሽህ ደብተሮችና ሃያ አምስት ሽህ የመጻፊያ እርሳሶች ገዝቶ በነፃ የሚያድል መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር.... አስታወቀ።»

አዲስ ዘመን ጥር ፲፱፻፷፮ ዓ.ም

ለማስረሻ ወሬውን የነገረው ሐኪምሙ ነበር። ምርመራውንና የቁስል ሕክምናውን ጨርሶ «አሁን በጣም ደህና ነህ» ከኋው በኋላ «ለመሆኑ ሹም ሽሩን ሰማህ?» ሲል እንደዋዛ ጠየቀው። ማስረሻ በመገረም ትክ ብሎ እየተመለከተ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ።

«የአቃቤ ሹም ጕንጤ ኮሚቴ ከሥራ ተሰናበተ። ልጅ ጉግሣ አዲስ አቃቤ ሹም ሆነ።»

«በሙሉ?»

«አዎ፥ በሙሉ የአንተ ወዳጅ ሹም ጓንጉል ሳይቀር» አለው፥ ቀድሞ በኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ጓደኛው የነበረው ኢትዮጵያዊ ሐኪም። ከውጭ ሀገር ትምህርት ከተመለሱ በኋላ ሁለቱም በየፊናቸው የሙያ መስመራቸውን ተከትለው ብዙ ጊዜ ባይገናኙም የጥንቱን እያነሡ እንደ ጥንቱ ይቀላለዳሉ። አሁን ደግሞ ማስረሻ፥ በጥይት ቁስሎ ሐኪሙም በደሴ ሆስፒታል ተመድቦ በአጋጣሚ መገናኘታቸው አቀራርቧቸው ሰንብቶ ነበር። ማስረሻን ማን እንዳቁሰለው ሐኪም ሰምቶ ነበር። እንደ ደሴ በመለስ መጠነኛ ከተማ ወሬ ተደብቆ አይሰነብትም።

«ስሙን አትጥራብኝ! ትኩሣቴ እንደገና እንዲነሣ ትፈልጋለህ?» ሲል በቀልድ ዓይነት ፊቱን አኰሳትሮ ጠየቀ።

«የለም! የለም!» አለው ሐኪሙ እንደ ነርስ አንሶላውንና ብርድ ልብሱን አመቻችቶ እየለበሰው። «ትኩሳትህ የሚነሣበት ምንም ምክንያት የለም። አደጋ የትም ቦታ ምን ጊዜም ይደርሳል። በዚች አጭር የሕክምና ሕይወቴ ተረት ወይም ልብ ወለድ የሚመስል ብዙ አደጋ አይቻለሁ። አንተ ግን ደህና ተርፈሃል። አሁን ደህና ነህ፤ ከዚህ በኂላ የሚያስፈልግህ የሐኪም አስታማሚ አይደለም።»

«እህስ?»

«ራስህ የምታውቀው ይመስለኛል» ሲል ሐኪሙ ዓይኑን ጠቀስ አድርጎ ፈገግታ እያሳየ ወጣ።

ማስረሻ ብቻውን ሲሆን የክፍሉን ጣሪያ እየቃኘ በመብራቱ አምፖል ላይ ያረፉትን ዝንቦች እየቆጠረ ያስብ ገባ የሹም ጓንጉል ውድቀት ባንድ በኩል ደስ አሰኘው - እናቱን! ሌላው ቢቀር ያልታሰረው በሥልታኑ አይደል! መልሶ ደግሞ አሁን ተነሥቼ በሕግም ሆነ ከሕግ ውጭ አንድ ነገር ባደርገው እንደ ወንድነት ሳይሆን፥ የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል እንደሚባለው ይቆጠርብኛል - ሲል አሰበ። ጉዳዩ በዚህ ብቻ አይወሰንም። አቃቤ ሹም ጉንጤ ከወደቀ ክለብ መቶ ሠላሳ ወደቀ ማለት ነው። ክለብ መቶ ሠላሳ ከወደቀ ደግሞ የጤና አዳም ከለብ አሸነፈ ማለት ነው። ታዲያ ከልዕልት ዘንድ ቀርቦ እጅ በነሣ ጊዜ ስለ ክለብ መቶ ሠላሳ አደገኛነት ተነግሮት ከዚያም ከአምስት መቶ ብር ጉርሻ ጋር የጤና አዳም መረዳጃ ማኅበር የቴሌፎን ቊጥር ተሰጥቶት ነበር። ታዲያ አሁን አሰላለፉ ከየት በኩል ሊሆን ነው?

በመሠረቱ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በጣም ቀጭን ክር ነው። ምናልባት ከአንዱ ወደ ሌላው መሽጋገር የአንድ እርምጃ ጉዳይ ነው። በሀገሪቱ ምንም ዓይነት መሠረታዊ ልዩነት አያመጣም። አንዱ በፊውዳላዊ ትምክህት ይገዛል። ሌላው ደግሞ በለዘብተኛ ብልጠት ያስተዳድር ይሆናል።

ከአሁን ቀደም ከዘለቃ ጋር ያቆራኘው የወይዘሮ ዘርፈሽዋል አጃቢ ያደረገው መጥፎ አጋጣሚ ከሁለቱ በየትኛው በኩል ይጥለው ይሆን? በዚህም ሆነ በዚያ ወደ ፊት ከዘለቃ ጋር የሚኖረው ግንኙነት የሚወሰን ሊሆን ይችላል።

«ግን የምን ግንኙነት? በቃ። አከተመ!» ሲል በሐሳቡ ከራሱ ጋር ተቆጣ።

በዚህ ጊዜ የክፍሉ በር ተንኳኳ። ማስረሻ በፍጥነት ፊቱን ወደ ግድግዳው አዙሮ ተሸፋፈነና እንቅልፍ የወሰደው መሰለ። ማን እንደሆነ ጠርጥሯል። ዘወትር እየተመላለሰች ከውጭ ሆና ደኅንነቱን ስለምትጠይቀው ሚስቱ ነርሷ ደጋግማ ነግራዋለች። «ውይ! በጣም የምታፈቅርህ ሚስት አለህ» ብላዋለች በቀልድ አሽሙር። ከቱሪንግ ሆቴል የሚመጣለት ምግብ አስተጓጉሎ አያውቅም። ከሦስት ቀን አንድ ቀን አዳዲስ የጽጌ - ረዳ አበባ ክፍሉ ውስጥ ይቀመጥበታል። ስለዚህም ጠያቂ በር በአንኳኳ ቊጥር እርሷ እየመለሰችው ፊቱን ዞሮ ይሸፋፈናል። ለጊዜው እንድታነጋግረው ወይም ሊያነጋግራት አልፈለገም። ከእርሷም ሆነ ከሹም ጓንጉል ጋር የሚፋጠጥበት ሥፍራና ጊዜ አሁን አይደለም።

በሩ ተከፍቶ ሲዘጋ የሽቶ መዓዛ የተሸፈነበትን አንሶላ ዘልቆ ሰነፈጠው። የሴት ታኮ ጫማ ኮቴና ወንበር ሲንቋቋ ሰማ። ዘለቃ ለመሆንዋ እርግጠኛ ሆነ። አድፍጦ ዝም አለ።

እርስዋም በበኩልዋ በበኩልዋ ለአጭር ጊዜ ጸጥ ብላ ተቀመጠች። ክፍሉ በጸጥታ ተዋጠ። በክፍሉ ውስጥ የሚሰማው ጢዝዝዝ የሚል የአንድ ዝንብ በረራ ብቻ ነበር።

«ለምን እንደዚህ ትሆናለህ? ነቅተህ ስትጫወት እንደ ነበር አሁን ዶክተር ነግሮኛል» አለች ዘለቃ፥ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በትንሽ ነገር የተኳረፈ ይመስል ነገሩን በማቃለል። ማስረሻ መልስ አልሰጣትም።

«እንዲህ ሆንክና ማንን ልትጎዳ ነው?» አለች ዘለቃ ትንሽ ቆየት ብላ «የምመታው ልጠይቅህ ነው። መተሳሰብ ነውር ሆነ?»

«መተሳሰብ! ልትጠይቂኝ? ጓንጉልን አስቢለት። ሂጂና ጠይቂው» ማስረሻ ድንገት ሳይታወቀው የሚያባርቅ ድምፅ ከደረቱ ፈንቅሎ ወጣ። «አዎ፥ ማሰብና ማጽናናት የሚያስፈልገው ነው። አልሰማሽ እንደሆን፥ ያ ሥልጣኑ እንደ ዶሮ ላባ ተነቃቅሎለታል። የእኛ አሳቢ!» ፊቱን ወደ እርስዋ አዙሮ አፈጠጠባት።

ዘለቃ ግን ዓይንዋንም ቅንጣት ስብር አላደረገችለትም። ራስዋን እያወዛወዘች እንዳስቸጋሪ ሕፃን በአዘኔታ አኳኋን ተመለከተችው። «ባትወራጭ ለአንተ መልካም ነው። የዳነ ቁስልህን ነው የምታፈነዳው።»

«እሰዬ ነዋ ላንቺ። ተገላገልሽ። ጓንጉል የመጀረልሽ ተጨመረልሽ ማለት ነዋ!» ማሰሻ ጥርሱን ግጥጥ አደረገባት።

«ከምኑ ነው የምገላገለው?»

«ከእኔ ነዋ!»

«አሁንስ ማን አሰረም?»

«ማን እንዳሰረሽ የራስሽን ልብ ጠይቂው። ግን አጉል ሐሜትና ግርግር ከመፍጠር በተሻለ ዘዴ ብትጠቀሚ ይሻል ነበር። ብዙ ረቂቅ መንገዶች አሉ። ከቡና ጋር ፋት የምትደረግ ጠብታ መርዝ....» ማስረሻ በመጠየፍ አኳኋን ከንፈሩን ለጥጦ ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው።

«አንተ እኮ ያደረብህ ስሜት የቅናት ሳይሆን፥ የአእምሮ ሐኪሞች እንደሚሉት ሰው ሁሉ የሚጠላና የሚያሳድድህ የሚመስልህ ስሜት ነው።»

«ፈርዶብሽ እብድ አግብተሽ ነበር።»

«ወጣኝ አሁን?»

«እኔም ወጣሽ አላልሁም።»

«ነገር ግን» ዘለቃ አነጋገርዋን ረገጥ አደረገችው፥ «ነገር ግን ስሜትህን ገልጸሃል። ግልጽ ባለ ሁኔታ። እኔም ሌላውም - ሌላውም ሊያጠፋህ እንደ ሞከረ። እኔ ደሞ የምለው አስቀድመህ በስሜት አትመራ ነው። ረጋ ብለህ ጠይቅ ረጋ ብለህ አነጋግር። ረጋ ብለህ ተመራመር። ተመራምረህ አረጋግጥ። ከዚያ በኋላ ፍረድ።»

«ከዚህ የበለተ ማረጋገጫ አለ?» ሲል ማስረሻ የደረቱን ቊስል በእጁ ዳበስ አደረገ፡፡

«በአንድ በኩል የሱ ጥፋት ብቻ አልነበረም፡፡»

«ጥብቅና መቆምሽ አያስደንቀኝም፡፡»

«እሱ ከአንተ በልጥብኝ ነው?»

«ለማበላለጥም ባይሆን ለማማረጥ በጨረታው አይገደድም ተብሏል፡፡ የሚያሳዝነኝ ለጨረታው ምርጫ የእኔ ሕይወት ዋጋ ሆኖ መቅረቡ፡፡ ለእኔው ለእራሴ ዋጋ እንደ ሌለው ሁሉ፡፡» ማስረሻ በመጸጸት አኳኋን በከባዱ ተነፈሰ፡፡

ዘለቃ ከወንበርዋ ተነሥታ ከአልጋው ላይ ዳሩን ይዛ ተቀመጠች፡፡ የተዝናንችና እንደምታሽንፈውም በራስዋ የተማመነች ትመስል ነበር፡፡ ይህም ማስረሻን አበሸቀው፡፡ በሌላ በኩል ግን፥ የሽቶዋ መዓዛ ሲያውደው ዳሌዋ ከብርድ ልብሱና ከአንሶላው ሥር ያለውን ጭኑን ሲዳስሰው ሰውነቱ ልውጥውጥ አለበት፡፡ ጀርባውን ሊያዞር ከጀለ፡፡ ፍርሃት መስሎ ተሰማው፡፡

«ለምንድ ነው እንዲህ የምትሆነው ማስረሻ?» አለች ጋር ነህ፡፡ አብሮ ለመኖርም የበለጠ አስቸጋሪ ነህ፡፡ ነገር ግን ለዚህ ስል እችለዋለሁ» አለች ሆድዋን በእጅዋ እያመለከተች፡፡

ማስረሻ በማሾፍ አኳሁን እንደመሳቅ ቃጣው፡፡ «አሃ ለልጁ ስትይ? የማን ልጅ? የእኔ? የእርሱ? ወይስ?»

«ኧረ ተው ማስረሻ እንዲህ ግፍ አትናገር፡፡» ዘለቃ ከቦርሳዋ መሐረም አውጥታ አፍንጫዋን እየጠራረገች ታለቃቅስ ገባች፡፡ የምታሸንፍበትን መንገድ አሳምራ ታውቀዋለች፡፡ አንድ ጊዜ ትኰሳተርበታለች፡፡ አራስ ነብር ትሆንበታለች፡፡ ወዲያውኑ መልሳ፥ እንደ ልበ - ንጹሕ ሕፃን፥ እንደ ተበደለ - በግፈኛ እንደ ተበደለ ሰው - ትንሰቀሰቅበታለች፡፡ ግራ ይገባዋል፡፡ አስተሳሰቡ ይረበሽበታል፡፡ ይህንን ደካማ ባሕሪውን በሚገባ ተረድተዋለች፡፡ እንዳወቀችበትም ያውቃል፡፡ በዚህም መልሶ ይበሽቃል፡፡ ግን ምንም ማድረግ አይችልም፡፡

«ታዲያ አሁን ምን የሚያስለቅስ ነገር አለ?» አለ በደከመ አነጋገር፡፡

«ለምን የደም ዕንባ አላለቅስም? አጥንት የሚሰብር ነገር ስናገር፡፡» የባሰውን ተንፈቀፈቀች፡፡ ምንስ ቢሆን በጫጉላ ቀኔ ትጠረጥረኛለህ?»

«ታዲያ ከሰው ክፍል ውስጥ ምን አመጣሽ?»

«አንተስ የጫጉላ ምሽትህን እኔን ትተህ ዙሪት ምን አስሄደህ?»

«እኔም ምክንያት ይኖረኛል፡፡ የሚሰማኝ አልተገኘም እንጂ፡፡» አሁን ልቅሶዋ ጋብ እያለ ሄደ፡፡

«እስቲ እንስማዋ!» ከቁስሉ ሰመመን እንደ ወጣና የደረሰበትን እንዳገናዘበ ከእንግዲህ በቃኝ ብሎ ያልፎከረውን ያህል፥ ልትጠይቀው እየመጣች ከውጭ መጠበቋ በተነገረው ጊዜ ፊቷን እያሳየኝ እያለ የቆረጠ ያልመሰለውን ያህል፥ አሁን እርግጠኛ አልሆነም፡፡ አስተሳሰቡ ያመነታበት

ጀመር - ከአጠገቢአ ከአልጋው ላይ የተቀመጠችው ብትወደኝ አይደል? ባትወደኝ ዛሬውኑ እንፋታ ከማለት ምን ይከለክላታል? ስለ ልጁም አስተዳደግ የተጨነቀችው የእኔ ልጅ ቢሆን ነው - እያለ ራሱን እንደሚያባብል ሕፃን በሆዱ አሰበ። ሌላ ተቃራኒ አስተሳሰብ ሲመጣበት፥ ቢሆንም ቢሆንም፣ ብትወደኝ ነው ሲል የራሱን ሐሳብ ተሚገተው።

የሐሳብ ሙግቱን የተረዳች ይመስል እንደ ገና እንደ ማልቀስ ቃጣት።

«እሺ ልስማው!» አለ በተሸነፈ አንደበት።

«ከየት ልጀምር?»

«ከፈልግሽበት።»

«እንዴት እንደምጀምር ግራ ገባኝ።» እውነትም ግራ የተጋባች መሰለች።

«ለማቃለል ያህል ከጓንጉል ጋር ግንኙነታችሁ ምን እንደሆነ። ግንኙነት ስል በመጥፎ ትርጉም በመውሰድ አይደለም።» እንደገና እንድታለቅስበት አልፈለገም።

ዘለቃ ትንሽ እንደ ማቅማማት አለች። «ጓንጉልማ የእኅቴ ወዳጅ ነው።»

«ምን? የምን እኅት!?»

«አዎ እኅት አለኝ።»

«እንዴት አላውቃትም?»

«በመልክና በስም ታውቃት ይሆናል። የእኔ እኅት መሆንዋን ግን አታውቅም። ሰው ሁሉ አያውቅም። እማማም አታውቅም። ምናልባት ብትጠራጠርም እንደማታውቀ ነው የምትመስለው። እኔ፥ እኅቴ እናቷ ምናልባትም ሚቱ አባቴና ተናዝዞም ከሆነ የንስሐ አባቱ የነበሩት ብቻ ነን የምናውቀው።»

«ምንድን ነው ምሥጢርነቱ?» ማስረሻ አሁን ነገሩ እየሳበው ሄደ።

«ከጋብቻ ውጭ ነዋ የተወለደችው! እማማ እቤት እያለች።»

«ታዲያ ምን አዲስ ነገር ሆነና ነው። መኳንንቱና መስፍንቱ ሚስቱን ከእልፍኝ አስተኝቶ፥ ከገረድ ጋር ወፍጮ ሥር ይንደፋደፋል ይባላል።»

«ስለ እኛ መልካም አስተያየትህ እግዜር ይስጥልኝ» አለች በቅሬታ አነጋገር።

«የአንችን ቤተሰብ ወይም አባትሽን ማለቴ አይደለም። በአጠቃላዩ ነው ያነሣሁት።»

«ያም ሆነ ይህ ከአቶ ጓንጉል ጋር ያለን ግንኙነት ይኸው ነው» ስትል ንግግሯን አቋረጠች።

«እኅትማማችነታችሁ እንደዚህ ባለ ከፍተኛ ምሥጢር የተጠበቀበትን ምክንያት አላስረዳሽም።»

«እሱማ አንዱ ምክንያት እማማና አባባ የተጋቡት በቍርባን ስለ ነበረ ነው» አለች እንደ ዋዛ።

«እሱስ ቢሆን! እኔ እንደማውቀው እንኳን የቍርባን ጋብቻ ቅስናም ይፈርስ የለ? እኔ አገር ቤት ከንስሐ ልጃቸው ልጅ የወለዱ አንድ መነኵሴ አውቅ ነበር። ‹አህያ መጣች ተጭና አሞሌ ቆብ ጥለው ሄዱ የኔታ ሳህሌ› እያለ እረኛ ሁሉ ይቀልድባቸው ነበር።»

አንዱ ምክንያት እሱ ከሆነ ከሱ የላቀ ሌላ አለ ማለት ነው። «ሌላው ምክንያትስ?» ማስረሻ ያነሣው ታሪክ ሁለቱንም እንደ ማሳቅ አላቸው።

«ሌላው ምክንያት ሌላው ምክንያት» ዘለቃ ለመንገር ያረፈች ይመስል ጥቂት አመነታች። «እኅቴ በእናቴ በኩል ዘመዴም ናት። እንዲያውም እማማና እናቷ የአንድ አያት ልጆች ናቸው። ስለዚህ ነው በምሥጢር የተያዘው። አባባ ለዝናው ለስሙ በጣም የሚጨነቅ ሰው ነበር። እንደምታውቃት እማማ ደግሞ በጣም ኃይለኛ ናት። ስለዚህ በጊዜው በምሥጢር ተጠበቀ። በዚያው ተደብቆ ቀረ። ለእስዋ ያለሻት አንቺው ነሽ። ለአንቺም ያለችሽ እስዋው ብቻ ናት ብቻ ምሥጢሩን የነገረችኝ እናቷ ናት። ምናልባት እማማ ትጠራጠር ይሆናል። ምክንያቱም ሁለታችን በጣም እንመሳሰላለን። ከገጠር መናፈሻ ሆቴል ከጓንጉል ጋር ስትወጪ አየሁሽ ብለህ ያን ጊዜ እንዲያ የሆንከው እስዋን አይተህ ይሆናል። እኔ ደግሞ አባትሽን ትመስያለሽ እባላለሁ። ታዲያ እስዋ ደግሞ በጋብቻ ብቻ ተስባ አባቴን ትመስላለች እንዳይባል፥ ሁለታችሁም በእናታችሁ በኩል ቅድመ አያታችሁን ትመስላላችሁ ይላል ቤተ ዘመድ። ወደድክም ጠላህም ይኸው ነው ታሪኩ።»

«አባትሽን ፍቅር አስውሮአቸው ነበር ማለት ነዋ» አለ ማስረሻ ነገሩን እንደ ቀልድ በማቃለል።

«የአንድ ቀን ስህተት ሆኖ ዕድሜ ልካቸውን የተፀፀቱበት ሊሆንም ይችላል» ስትል መለሰችለት። ቀጠል አድርጋ፥ «የዚያን ቀን ከጓንጉል ክፍል ለምን እንደ መጣሁ ልነግርህ እችላለሁ» አለችው።

-ከሞት አፋፍ የተመለስኩበት እሱ ነው ዋናው ቁም ነገር! አለና በሆዱ፥ እስክትነግረው ጠበቃት።

አሁንም ለመንገር የተጨነቀች ይመስል ቦርሳዋን ከፍታ ውስጡን እየፈታተሸች «ሲጋራ ማጤስ ይቻል የለም?» ስትል ጠየቀች።

«ጥይቱ የሳንባዬን ጫፍ ስለ ነካው ሐኪሜ ደስ ባይለውም፥ እኔም ራሴ አጨሳለሁ» አላት ማስረሻ።

አንዱን ራስዋ አቀጣጥላ ሰጠችውና ሁለተኛውን ውኃ ጠምቶት እንደ ቆየ መንገደኛ በሰፊው ሳብ አደረገችለትና ንግግሯን ቀጠለች፡፡ «እንደ ነገርኩህ ለረጅም ጊዜ ወዳጆች ሆነው ከቆዩ በኋላ በድንገት ቅሪት ሆነች፡፡»

«ሚስት ደሞ አለው መሰለኝ?» ሲል እንደ ዋዛ ጠየቀ፡፡

«ችግሩ ከሱ ላይ አይደል! ዲቃላ ወለደች መባል ስለማትፈልግና ቃል የገባችለት እጮኛም ስላላት አሁን ታዲያ ርሴን እገድላለሁ ባይ ናት፡፡»

«ምን ተሻለ?» ማስረሻ መካሪና አጽናኝ መሰለ፡፡

«ከዚህ አገር ብታስወጣው አንደኛ ሕክምናው አያስተማምንም፡፡ የፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ እንደሚያወራው ስንቶቹ ናቸው፡፡ የሚሞቱት፡፡ በዚህ ላይ ሐኪሙንም አስወራጅዋንም መክሰስ ተጀምሯል፡፡ ስለዚህ ፈረንጅ አገር ልኮ ያሳክማታ! ያን ቀን ማታ ከክፍሉ ድረስ መጥቼ ሳነጋግረው የነበረው ስለዚህ ጉዳይ ነበር፡፡»

«ምን አለ ታዲያ?»

«ገና መልስ ሳይሰጠኝ አንተ ደርሰህ ነገሩን ሁሉ አበላሸሽዋ!» አለችው በመክሰስና በመውቀስ አኳኋን፡፡

ማስረሻ ክሱን የማይቀበለው መሆኑን በመግለጽ በአፍንጫው ትንፋሽ አወጣ፡፡ ስሜቱ የነገረችውን ሁሉ ለማመን ፈለገ፡፡ የሚያስብ አእምሮው ደግሞ የመከራከሪያና የመጠራጠሪያ ጉዳዮች አነሣባት፡፡ - ተረት ነው እውነት የምትተርክልኝ? እህት ያለት መሆኑ እውነት ከሆነስ ከገጠር መናፈሻ ስትወጭ አይቼሻለሁ ብዬ ስንጣላ ለምን ፍንጭ አልሰጠችኝም ነበር? እስዋ በስህተት አረገዝኩ ብላ ከቀጠሮው ጊዜ በፊትና ፕሮግራማችን ውጭ እንድንግጋባ አደረገች፡፡ እኅት ተባይዋ ደግሞ እንደዚሁ አረገዝኩ ብላ ፈረንጅ አገር መላክ ትፈልጋለች፡፡ የሁለቱም ስህተት ያጋጣሚ ነው? ወይስ ሌላ ምሥጢር አለው? - ለጥቂት ጊዜ ፍዝዝ ብሎ አሰበና «ሁለታችሁም የከተማ ልጆች ናችሁ፡፡ ክኒን ቀለበት፥ የወር ዑደት ሌላው ሌላውም መከላከያ ሁሉ እንዴት እንዴት እንደሚሠራ አሳምራችሁ ታውቃላችሁ፡፡ አንቺ ያንን ያህል ብዙ ተመካክረን ድንገት በማርገዝሽ ፕላናችን ሁሉ ፉርሽ ሆነ፡፡ እኅትሽ ደግሞ የባሰውን ከባለሚስት ወንድ ዘንድ መቋጠር፡፡ ምን ነካችሁ?» አጠያየቁ ሆነ ብሎ እንደ ዋዛ ነበር፡፡ ምናልባት የእውነቱን ፍንጭ በዚህ ጥያቄ መልስ የሚያገኘው መሰለው፡፡

«እንኳ ያረገዝኩት በስህተት አይደለም፡፡ አውቄ ነው» ስትለው በመገረም ከተጋደመበት እንደ መነሣት ቃጣው፡፡

«ለምን?»

«ፈለኩ፡፡»

«መልስ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሠርጋችን ጊዜ እንዲዘገይ እንደ ተጋባን ውጭ አገርም እንድሄድ ፈልገሽ ነበር፡፡»

«ታዲያ አዲሱ ፍላጎት ምንድን ነው?»

«አሁንስ አበዛሽው! ከሆዴ ውስጥ ያለውን የግል ምሥጢሬን ዘክዝኬ ማውጣት አለብኝ?» ፊቷን ኮስተር አደረገች ::

-አታፈግፍግ፥ ግፋበት - ሲል በሆዱ ራሱን አደፋፈረ:: «አንዴ ከጀመርሽው ብዬ ነው:: ደግሞ ልጁ የሁለታችን ከሆነ ምክንያቱ የግልሽ ሊሆን አይችልም::»

ዘለቃ ግንባሯን በጣቶችዋ ፈታተገች:: «ማናዬ የውርስ ድርሻዬን እንዲነጥቀኝ አልፈለኩም» ድንገት ንዴት ባዘለ አንደበት::

«እንዴት?» ነገሩ ሁሉ ይበልጥ አስገራሚና እንቆቅልሽ እየሆነበት ሄደ::

«ምን አዚም እንዳዞረባት እንጃ፥ እማማ እንዴት እንደምትሆንለት የምታየው ነው:: አንዳንድ ጊዜ ከሰው ፊት ብታመናጭቀውም እውነት አይምሰልህ:: ከመዳፉ ውስጥ ነው ያስገባት:: ስለዚህ መኪናውንና መሬቱን ሁሉ ብትለቅለት አይገርመኝም:: እኔ ግን እጄን አጣጥፌ ኣላይም::»

«እና?»

«እማማ የልጅ ልጅ ለማየት በጣም እንደምትጓጓ አውቃለሁ:: ስለዚህ የልጅ ልጅ ስታገኝ፥ ፍቅርዋ አስተሳሰቧ በከፊል ወደርሱ እንደሚሳብ እርግጠኛ ነኝ:: አያት መሆንዋ ሲታወቅኮ ምናልባት ሌላአውን ነገር እርግፍ አድርጋ ትተወው ይሆናል::» እንደ መሳቅ አለች፥ «ያም ባይሆን ለልጅ ልጇ ይሄን - ይሄን ብላ መተዋ የማይቀር ነው:: እኔንማ ሥራ ይዘሻል፥ ራስሽን ችለሻል የምትለው ነገር አላት:: አባባ የረባ ነገር አልተወ:: ይኸው ነው ምክንያቱ::»

ማስረሻ የሳቅ ትንታ ያዘው::

«ምን ያስቅሃል?» ዘለቃ በበኩሏ በቀልድ ዓይነት ተቆጣች::

«ከወላጆችዋ እንደምትኮበልል ኮረዳ፥ እሜቴ በፍቅር ከንፈው የሚሠሩትን የማያውቁ መሆናቸው ነዋ!»

«ፌዙን ተወውና፥ ይልቅስ የምነግርህ አንድ ዋና ጉዳይ አል፡፦፧

«ምን የቀረ ጉዳይ ወይም ተአምር ደሞ ይኖርሽ ይሆን?»

«እማማ ቴሌፎን ደውላ ነበር::»

«እና?»

«አዲሱ አቃቤ ሹም፥ ልጅ ጉግሣ ይፈልግሀል አለች::»

«ለምን?»

«የኮሚቴ አባሎችን በመምረጥ ላይ አይደል ያለው ሊሾምህ ይሆናላ!»

«ምን?» ሲል ጮኸ፡፡

«አንተ ምን ይጐድሃል?» አለች፡፡

ግን አልሰማትም፡፡ የምትተርክለትን ሁሉ ሳያምንም ሳይክድም እንደ ዋዛ፥ እንደ ጨዋታ ሲያዳምጥ የቆየውን ያህል አሁን ሐሳቡ በአንድ ጊዜ ተኮማተረበት፡፡ እሱ ሳይፈልግ በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ውሳኔ ተዳረ፡፡ እሱ ሳይፈልግ በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ውሳኔ ሠርጉ ደሴ ከተማ ሆነ፡፡ ምናልባት ደሴ ባይመጣ ኖሮ ይህ አደጋም አይደርስበትም ነበር፡ አሁን ደግሞ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እሱን ሳይጠይቁና ሳያማክሩ ከልዕልት ዘንድ ቀርበው፥ «ከነዚያ መልቲዎች ከሥልጣን ከተባረሩ እንግዲህ እርስዎ ፊት አቅርቤ እጅ ያስነሣሁት የልጄ ባል ይሾምልኝ እንጂ፡፡ ዓዋቂ የተማረ የመራመረ ነው ብለው ሲለምኑ በሐሳቡ ታየው፡፡ ከተሾመ ደግሞ የጤና አዳም ማኅበር አባልና የመቶ ሠላሳ ክለብ ባለጋራ መሆኑ ነው፡፡ እሱ የመናጢ ደሃ ዘር ከመኳንንትና ከመሳፍንት ጋር ምን አሰለፈው? በዚህ ላይ ደግሞ «ይኸውልህ! ወይ ከደህና ተወለደ ወይ ከደህና ተጋባ እንደተባለው እኔ፥ እናትህ ለዚህ አበቃሁህ» እያልሁ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዝንተ ዓለም ሲመጻደቁበት ተሰማው፡፡

«ይኸኔ እሜቴ ይሆናሉ ይህን የሚሠሩት» አለ በምሬት አነጋገር፡፡

«በምን አወቅህ?»

«ታዲያ ከልጅ ጉግሣ ጋር እውቂያ የለኝ፡፡»

«ሌላ ሰው ስለ አንተ ነግሮት ይሆናል፡፡»

«ሹመቱን ባልቀበልስ?» ሲል በቁጣ ጠየቀ፡፡

«እሱ ያንተ ምርጫ ነው»፡፡ ዳሌዋ ታፋዋን እስኪጫነው ድረስ ሆን ብላ ተጠጋችው፡፡ ሳይፈልግ ስሜቱ ተነሣበት፡፡ እስዋም አወቀች፡፡ «ግን ሹመቱን የማትቀበልበት ምክንያት አልታየኝም፡፡ ችሎታው አለህ፡፡ ለሀገርህ መሥራት ትፈልግ ነበር፡፡ ታዲያ ከዚህ የተሻለ ዕድል የለም፡፡ ቀደም በለን እንዳሰብንበት ወደ ውጭ አገር አብረን ለመሄድ ደግሞ ቆይቶ አምባሳደር ለመሆን መጠየቅ ነው፡፡ አንተ ለዶክተርነት ታጠናለህ፡፡ እኔም እማራለሁ፡፡ ልጃችንም በሚገባ ያድጋል፡፡ ሊያመልጥ የማይገባ ዕድል ይመስለኛል፡፡ አይመስልህም?» ስት ትኩሣቱን እንደሚለካ ግንባሩን በእጅዋ እየዳበሰች በቁልምጫ ጠየቀችው፡፡

ልቡ ከሁለት ተከፈለበት፡፡ በአንድ በኩል በአሉታ ለመመለስ ፈለገ፡፡ ግን አልቻለም፡፡

በምትኩ «ምን ሹመት ሊሰጠኝ ይችላል?» ሲል ጠየቀ፡፡

«ምናልባት የጓንጉልን፡፡ ሙያህን የሚመለከት እሱው ነው፡፡ ለወሎው ችግርም ጉበዝ ሰው ሳያስፈልገው አይቀርም» ስልት መለሰችለት፡፡

«ታሪክ ማለት እንዲህ ነው! ፊልም ሊያሠራ የሚችል፡፡»

«እንዴት?»

«እኔን ሊገድል ያቆሰለኝን የአለቃዬን ቦታ መውሰዴ ነዋ!» ከሹም ጓንጉል ቢሮውንና ሌላውንም ሰነድ ሲረከብና ከዚያ ጠረጴዛ ላይ ጉብ ብሎ «በየጊዜው ብንገናኝ መልካም ነው:: ለሥራው አዲሲ ስለ ሆንኩ የርስዎን ምክር ማግኘት ይኖርብኛል:: ዓለም ተለዋዋጭ ስለሆነ በሁናቴው አለማዘን ነው» ብሎ ሲሸነግልረው በሐሳቡ ታየው:: በቀሉን የተወጣ መስሎ ተሰማው:: ሳይታወቀው ባፍንጫው በሰፊው ተነፈሰ:: ግን በዚህ ስሜት ተዝናንቶ ብዙም አልቆየ::

ነርስዋና ሐኪሙ በጥቂት ደቂቃ ልዩነት ተከታትለው ገቡ::

«የመጠየቂያው ሰዓት አልፏል» አለች ነርስዋ ኰስተር ባለ አነጋገር:: «ምነው ክፍሉንስ ቢጠስ ያፈናችሁት?» አለች ዘለቃን በዓይኗ እየገረመመችና ነፋሻ አየር ለማስገባት መስኮቱን እየከፈተች:: ዘለቃ በበኩሏ ከእግር እስከ እራስዋ ገላመጠቻት::

«ልናስቸግርህ ነው ማስረሻ» አለው ዶክተር እንደገባ::

«ምነው?»

«ፋሻውን ለልውጥልህና ሆቴልህ ተኝጠህ እየተመላለስህ ታከም:: ወይም ደግሞ» ሐኪሙ በአነጋገሩ እንደ...ማቅማማት አለ:: «ወይም ደግሞ በዚህ ክፍል ውስጥ ሌሎች በሽተኞች ማስተኛት ግድ ሊሆንብን ነው::»

«ለምን?» ስትል ዘለቃ ጣልቃ ገብታ ጠየቀች::

«ሰምተህ ይሆናል ረሃብተኛው ሕዝብ በየቀኑ በብዙ መቶ እያለቀ ነው:: ሰው ካላየ አያምንም ይባላል:: እኔ፥ መጠለያ ሄጄ በዓይኔ ያየሁትን ስንኳ ማመን ያቅተኛል:: ሕልም ነው የሚመስለኝ:: የሰው አካል እንደዚያ እንደ ጨው ሲሟሽሽ ሕይወት እንደ ቅጠል ሲረግፍ:: የሕክምና ትምህርቴ፥ ለብዙ ዓመታት በሕይወትና በሞት መካከል ያለውን ቀጭን ልዩነት ዘወትር መመልከቴ ስንኳ ይህንን ለመሰለው መዓት አላዘጋጀኝም ነበር ማለት እችላለሁ::»

ሐኪሙ ከዚህ በላይ አንገቱን ደፋ አድርጎ ጥቂት አሰበ:: «እና እኛ፥ ማለቴ ይህ ሐኪም ቤት የተቻለውን ያህል ሲያደርግ ሰንብቷል:: አዎ፥ በረሃብ ምክንያት በምግብ ብቻ ሊድኑ አይችሉም:: ስለዚህም ነው በየመጠለያይው ብዙ ሕዝብ በየቀኑ የሚያልቀው:: ሆስፒታላችን በሦስተኛና በሁለተኛ ማዕረግ መተላለፊያ እስኪተፋ ድረስ የደከሙትን ረሃብተኞች ተቀብሎ በማከም ላይ ነው:: ነገር ግን እየዳነ ቦታ ከሚለቀው በየደቂቃው የሚጎርፈው በብዙ ሽህ የሚቆጠር ሆኖአል:: በዚህም ምክንያት ከወጣቱ ከከተማው ነዋሪ ሕዝብ፥ ችግረኞችን ከሚረዱት ኢንተርናሲዮናልና መንፈሳዊኢ ድጅርቶች ዘንድ፥ በቂ የሕክምና አገልግሎት አልተሰጠም የሚለው ቅሬታ እጅግ እየበረታ ሄዶብናል:: በተለይ ወጣቶች ከአምና ጀምሮ ለችግረኞች ዕርዳታ አልተደረገም እያሉ የተቃወሙትን ያህል አሁን ደግሞ ሆስፒታሉ በቂ ሕክምና አልተሰጠም እያሉ ከፍተኛ ድምፅ በማሰማት ላይ ናቸው:: እኛ የተቻለንን ያህል መሥራታችን ይሰማናል:: የተቻለንን ያህል መሥራታችን በቂ ካሆነ ደግሞ እኔ በበኩሌ የሕክምና ግዴታህን አላሟላህም ተብዬ በቸልታ ወንጀል ለመጠየቅ አልፈልግም:: ስለዚህም» ሐኪሙ ከዚህም ላይ ንግግሩን ገታ

አድርጎ በክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ በመንጎራደድ ጥቂት አሰበ። «ስለዚህም ለአንዳንድ በሽተኛ ብቻ ተመድበው የነበሩትን አንደኛ ማዕረግ ክፍሎች፣ እንደ ሌሎች ሁሉ የተቻለውን ያህል በሽተኛ እንዲተኛባቸው ከማድረግ በቀር ምርጫ የለንም። ስለዚህ ይቅርታ አድርግልኝና ይህም ክፍል ከዚህ አስገዳጅ ሁናቴ ውጭ ሊሆን አይችልም። እንደ ምንም ተጣቦ አንድ አምስት ሰው ቢተኛበት፥ የዚያኑ ያህል ሕይወት ይተርፋል ማለት ነው። እርግጥ ለአንተ ምቹ አይሆንም። ስለዚህ ነው ሆቴል አርፈህ እየተመላለስህ ብትታከም ይሻላል ያልኩት። አይ! ግድየለም፥ ከሌሎች በሽተኞች ጋር አብሬ እሆናለሁ ካልህ ደግሞ በእኛ በኩል ችግር የለም።» ሐኪሙ ንግግሩን ሲጨርስ አንድ ትልቅ ሸክም እንደ ወረደለት ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ።

የማስረሻ - አእምሮ በውድቅት ጨለማ ድንገት እንደ ተለኰሰ ኤሌክትሪክ በቅጽበት አዲስ ጽላሎት ፈነጠቀበት። የእንጀራ አባቱ የሙሄ ምስል እንደ ፊልም እየተለያየና እየተከታተለ መጣበት። አንዳንዱ ክፍል የተዘበራረቀና የተማታ ያለፈ ትዝታ። ሌላው ያለፈውን ከወደፊቱ ጋር ያዳቀለ አስፈሪ ቅዠት። ሁሉም ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከነበረበት የተረጋጋ ሁናቴ በቅጽበት አውጥቶ ከአእምሮ የብጥብጥ አዘቅት ውስጥ የሚዘፍቅ ነበር። መጀመሪያ ሙሔ ከሠርጉ አዘቅት ውስጥ የሚዘፍቅ ነበር። መጀመሪያ ሙሔ ከሠርጉ ዳስ በር ቁሞ እጁን እያርገበገበ «እንደኔ የሰው እጅ አያሳያችሁ! እኔም እንደናንተው ሠርቼ፥ ኮርቼ የማድር ሰው ነበርኩ» ሲል ታየው። ቀጥሎ በአንድ አውድማ ዙሪያ ከመንደርተኞች ጋር ሆኖ እሸት እያማረጠና እሸት እየቃመ «በአንተ ቤት ትልቅ ሰው ሆንክና እኔ ገንዘብ ለመንኩህና ስላልወለድኩህ ንቀህ ተውከኝ! እኔስ እንደ ልጄ ነበር የማይህ፥ ልጅ ማስረሻ። አሁን እናንተ በከተማ ስትኖሩ እንደዚህ ያለ፥ አርሶ አምርቶ እሸት፥ ትኵስ እሸት የመቃም ዕድል፥ ፀጋ አግኝታችሁ ታውቃላችሁ?» እያለ ሲያፌዝበት ታየው።

የሐሳቡ መራወጥ ትኵሳቱን እየቀሰቀሰበት ሲሄድ የባሰውን ግልብጥብጡ ወጣ። አንድ የረሃብ በሽተኛ ቡትቶ ጨርቁን እንደ ለበሰ በቃሬዛ ተሸክመው ከክፍሉ ሲያስገቡት ታየው። ማን እንደ ሆነ ለማወቅ በሐሳቡ ዘወር ሲል፥ በሽተኛውን ከራሱ አልጋ ላይ ከጐኑ ተኝቶ ያገኘዋል። ሰውየው በሕይወተ ሥጋ የሚታየው ዓየንት አካል የለውም። ረቂቅ ጣዕረ ሞት ይመስላል። ቀጥሎ ወደ አጽም ተለወጠበት። ቅንጣት ሥጋ የሌለው ነጭ አጽም። ነገር ግን ሕይወት ያለው ይመስል የሚንቀሳቀስ አጽም ነው። ሰላምታ ሊሰጠው የፈለገ ይመስል አጽሙ እጁን ወደ እርሱ ይዘረጋበታል። ቀጥሎ እንደ መሳቅ እየቃጣው፥ «አታውቀኝም እንዴ?» ይለዋል። ከሌሎች አጽሞች በምን ምክንያት እንደ ለየው ሳያውቅ በጐኑ የተጋደመው አጽም የእንጀራ አባቱ የሙሔ ሆኖ ያገኘዋል።

«የለም! እኔም ከዚህ መቆየት አልፈልግም» አለ ማስረሻ ድንገት በተወራጨ ድምፅ «እንዲያውም ወደ አዲስ አበባ መሄድ አለብኝ።»

## ፱

ከሆስፒታሉ ጥቂት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ አሮጌው ሆስፒታል እየተባለ በሚጠራው መተለያ ሞትና ሕይወት በሰፊው አውዳማ ላይ ይበራያሉ። ከሁለት መቶ የማይበልጡ በሽተኞች ለመቀበል ተሠርቶ የነበረው ግቢ አሁን ሰባት ስምንት ሽህ ረሃብተኞች ታጭቀበት ይገኛል። አዲሱ ሆስፒታል ከተሠራ ወዲህ ይህ ግቢ ከአገልግሎት ውጭ ከሆነ ቆይቷል። አሠራራቸው

ወላልቆ፥ ጣሪያቸው ፈራርሶ የከብት መጠለያ ሆነው ነበር። ሰፈሩ በአጠቃላይ እንኳን በሽተኛ የሚያገግምበት ጤነኛን በሽታ ላይ የሚጥል ባድማ ሆኖ ነበር።

ችግረኞች በዚህ ግቢ እንዲያርፉ የተደረገው ምንም ተጨማሪ ዝግጅት ሳይደረግ ነው። ከሁሉም የተሻለው አንድ ቤት ለጽሕፈት ቤት፥ ለድሬሰሮችና፥ ለማኅበራዊ ኑሮ ሠራተኞች ቢሮና ለዕቃ ቤት ተመደበ። ሁለተኛው ትልቅ ቤት ደግሞ የምግብ ማብሰያና የወጥ ቤት ሠራተኞች ነበር። ቀደም ብለው ወደ መጠለያው የገቡት ችግረኞች እየተጣበቡም የተደራረቡም፥ ከቀን ሐሩርና ከሌሊት ብርድ የሚከላከሉበት ክፍል አገኙ። እያደር ግን ክፍሎቹ እስከ አፍጢማቸው ሞልተው ችግረኛው በየታዛው፥ በየዛፉና በየቁጥቋጦው ሥር ከዚያም አልፎ በሜዳው ላይ ፈሰሰ። የቆርቆሮ ዛኒጋባ፥ የሸራ ዳስ ተሠራ። አሁንም አልበቃም። በታም የደከም ሕፃን የያዙ ወላጆች በሞተ ከዳ እንደ ምንም መጠለያ ይፈለግላቸዋል። ብዙ ሰው ግን የድንጋይ ትርስ እየደለደለ በሜዳው ላይ ዓረንዛ መስሎ ተረፈረፈ።

መጠለያው እንደ ተከፈተ ቀስቃሽ እየዞረ ችግረኛው ወደ መጠለያው እንዲገባ ያልጠየቀውን ያህል፥ ብዙ ችግረኛም የሚጋዝና የሚታሠር እየመሰለው ያልተደበቀውንና ያልሸሸውን ያህል እያደር የሚጐርፈው ስደተኛ ቍጥር መጠለያው ከሚችለው በላይ መቶ እጥፍ መሆን ጀመረ። መንግሥት መጠላያ አዘጋጅቷል የሚለው ወሬ እየተዛመተ ሲሄድ፥ በየቤቱ ታዛ ወድቆ በየበረሃው፥ ተበታትኖ ሞቱን ይጠብቅ የነበረው እንደ ምንም ጣዕረ ሞቱን ወደ መጠለያው እያደረሰ ተቀበሉን አለ። ነገር ግን የችግረኛው ጐርፍ እየሞላ ሲፈስ ወደ መጠለያው መግባት ከዓለም በቃኝ እንደ ማምለጥ፥ ወይም ለአንዳንድ ተራ ሰው የኢዮቤልዩን ቤተ መንግሥት በር እንደ ማለፍ ከባድ ሆነ።

ግማሹ ከዚያ ውሎ እያደረ፥ ግማሹ በደሴኢ ከተማ ተበታትኖ ከለማመነ በኋላ ከንጋት ላይ እየተመለሰ፥ ጠዋት ሁሉም በመጠለያው ዋና በር ዙሪያ ተከማችቶ እንደ ደራ ገበያ ይሰጣል። ግማሹ በያለበት ተጋድሞ ያቃስታል። ያጣጥራል። ግምሹ ተቀምጦ ይወዛወዛል። አንዳንዱ ደግሞ ለመቅረብ ለመታየትና ለመሰማት መቆም ያቃተው አካሉን ከበትር ላይ አስደግፎ በደከመ ድምፅ አቤቱታ ያሰማል። የሰለለ እጁን እያነሣ ይጥላል። ሁሉም እንደየአቅሙ አቤቱታ የሚያሰማበት አዲስ ዓይነት ደጅ ጥናት ነው። ታቦት ያልወጣበት ድባብ ያልተዘረጋበት የጣዕረ ሞት እግዚኦታ ነው።

ከሦስት ሰዓት በኋላ የመጠለያው ኃላፊዎችና አንዳንድ ሠራተኞች ይወጣሉ። የማቃሰት የልመና ደካማ ድምፅ ተቀላቅሎ ያሰማል። አንጀት የሚበላ ሕሊና፥ የሚወጋ ድምፅ....የሚያይበሳጭ የሚያስለቅስ ድምፅ....

የመጠለያው ኃላፊዎችና ሠራተኞችና በደከመ ስሜት በተሳቀቀ መንፈስ፥ እየተዘዋወሩ ይመለከታል። መጠለያው በዕለቱ ሊቀበል የሚችለውን አስቀድመው ገምተዋል። ግን ማንን ተቀብለው ማንን እንደሚተው በሚገባ መርምረው በትክክል አጣርተው ለመወሰን ጊዜም አቅምም የላቸውም። በጣም ተዳክሞ፥ ግን ሊድን የሚችል የሚመስላቸውን ያስገቡታል። ከመጨረሻው ጣዕር ላይ የሚገኘው ሆስፒታሉ እንዲቀበለው ይመዘግቡታል። ምናልባትም ሆስፒታል አልጋ ተገኝቶለት እስኪተኛ ድረስ ሊሞት እንደሚችል ያውቃሉ። ግን ምንም ማድረግ አይቻልም።

ሌሎችን ለማትረፍ የሞት ጥላ ያንዣበበት የሚመስለው ጥርሳቸውን ነክሰው ማለፍ አለባቸው። የተለየ አስተያየት የሚደረግላቸው ሕፃናት ብቻ ናቸው። ሕፃኑ ብቻ ሳይሆን ደከም ጠውለግ ያለ ሕፃን የያዘ ወላጅ ወይም ወላጅ ነኝ ባይ አብሮ እንዲኢገባ ይፈቀድለት ነበር። ምክንያቱም ሕፃን ይዞ የሚያስታምም ሠራተኛ ስላልነበር....። ለስንቱ ሽህ ሕፃን ሞግዚት ይቀጠራል? ይህ ሁናቴ ችግረኛው ወደ መጠለያው የሚያስገባ ቀዳዳ እንዲፈልግ አስገደደው። ሕፃን የያዙ በቀላሉ እንደሚገቡ ወሬው ሲዳረስ፥ የጨነቀው መንገድ ላይ ያገኘውን ወላጅ የሞተበት ሕፃን እየያዘ ይመጣ ጀመር። ሕይወትን ማትረፍ ምን ኃጢኢአት አለበት? የእሱም የእኔም ሕይወት ይድናል - እያለ ራሱን በማጽናናት።

ቆይቶ ከዚህ እልፍ ያለ አዲስ ዘዴ ተፈጠረ። የቅርብ ዘመዶቻቸውና ወላጆቻቸው ከውጭ የቀሩባቸው ከመጠለያው ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ምሽትና ሌሊት ቀስ ብለው በፈራረሰው አጥር በኩል ልጅ አዘልለው እየሰጡ በዚህ ሰበብ እንዲገቡ አደረጉ። ሌሊት ሌሊት ልጅ መዋሱ እየተስፋፋ በአንድ ብር በሃምሳ፥ ሳንቲም ማከራየትም መጣ። እንደ ምንም ሕይወት ብቻ ይትረፍ። ትንቅንቁ ለዚህ ነበር።

መጠለያ የገባው ሁሉ ሕይወቱን አላተረፈም። እንዲያውም ብዙው ረሃብተኛ በአጣዳፊ ያጣት ነበር። አንዳንዱ የታደለውን እህል እስኪያበስል አላስችል ብሎት ጥሬውን በሚቅምበት ጊዜ ተናንቆት ዱብ ይላል። በጣም የደከሙ ናቸው የሚባሉት ደግሞ ኤስ - ኤስ የተባለው አልሚ ምግብ ተሰጥቷቸው ገና ሆዳቸውን ሲነካው ተቅማጥና ትውከት ባንድ አፍታ ያጣድፋቸውና ወዲኢያውኑ ክልብስ ይላሉ። ከሚያገግመው የሚሞተው ሲበዛ አልሚ ምግቡ ቀርቶ እንጀራና ቂጣ እየተጋገረ እንዲሰጥ ተደረገ። ይህም ሆኖ ሞት የተቀነሰው በጣም በመጠኑ ነበር።

በመጠለያው ውስጥ የሚታየው ዋና እንቅስቃሴ ሞትን የሚመለከት ነው። አንዱ ጠዋት ሲነቃ ከጐኑ ተጋድሞ የነበረውን ከዚህ ዓለም ጣጣ ተሰንዳብቶ ያገኘዋል። ሌላው ዝንብ መከላከል እስኪያቅተው ድረስ ፈዝዞ ይውል ያድርና ድንገት አእምሮውን ስቶ እንደ መቃዠት እንደ መወራጨት ከአደረገው በኋላ ከዚያው ድርቅ ይላል። ከእናቱ ጉያ የተሸጐጠው ሕፃን ልጅዋን ጡት - ያጎረሰች እናት ልጁን የሚያባብል አባት ክንድ ለክንድ የተደጋገፈ ባልና ሚስት ሳይታወቅ ለዘለዓለም ያሸልባሉ። በመጠለያው ውስጥ ሲያንስ ሠላሳና አርባ፥ ሲባዛ ከመቶ በላይ ሰው በየቅኑ ይሞታል።

ለዚህ ሁሉ ሚች ተገቢ የቀርብ ሥነ ሥርዓት ለመፈጸም ባይቻልም ለንጽሕናና ለጤንነት ሲባል - ጤንነትና ንጽሕና ያለ ይመስል - አስክሬኑን ከግቢው ማውጣ ግድ ነበር።

-ኧረ ከዚህ ሰው አርፎብናል ጃል! - ሲባል ለመጠለያው ሠራተኛ ይመለከታል።

-ታዲያ አንሡት እንጂኢ ምን ትጠብቃላችሁ! - የሚል መልስ ይስጣል።

-ኧረ ጉዴ ፈላ እናንተ፥ ልጄ ሞተ - ትላለች ለማልቀስ ቀርቶ ለመንቀሳቀስ የደከመች እናት። ከአጠገቧ የሚገኙ ሰዎች ልጅዋን ከጉያዋ አላቅቀው ሌላ ሥፍራ ያስቀምጡላታል።

-እንዴ! እንዴ! እናንተ ሬሳ ከመካከላችሁ አድርጋችሁ ስትቀመጡ አይከብዳችሁም? - ሲኢል እየተዘዋወውረ ሲጉበኝ የሞተ ሰው ያገኘው የመጠለያው ሠራተኛ ይጠይቃል።

ከዚያም «በሉ እንጂ ጉበዝ እንረዳዳ» በመባባል ሰውነቱን ማንቀሳቀስ የሚችለው የእንጨት፥ ርብራቦሽና የጨርቃ ጨርቅ ቃሬዛ እየሠራ አስከሬን ማጓጓዙን ይቀጥላል። መከፈን የለም። ቤተ ክርስቲያን ማደስም የለም። ከመጠለያ ያለ ባዶ ቦታ ሁሉ መካነ መቃብር ነው። በመጠለያው ውስጥ በርከት ያለ ዘመድና ወዳጅ ያለው ለብቻው አንድ መቃብር ይቆፈርለት ይሆናል። በየቀኑ ሃምሳ ጉድጓድ መቆፈሩ እያቃተ ሲሄድ ግን አምስት አሥሩ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ እንደ ነገሩ አፈር ማልበስ የተለመደ ሆነ።

እያንዳንዱ ሰው ደግሞ ልዩ የሆነ የግል ጣዕር፥ የሕልውና ሥቃይና ትግል አለው።

የሙሔም እንዲሁ።

## ፫

ሙሔ ወደ መጠለያው የገባው ገና ባልተጣበበት ጊዜ ስለ ነበር፥ ብዙም ችግር አላጋጠመውም። ከፈራረሱት ቢሔቶች በአንደኛ ማረፊያ ክፍል አገኘ። በመጀመሪያ ሰሞን ጥቂቶች ነበሩ። እየቆየ ግን የእግር መተላለፊያ እስኪጠፋ ድረስ ክፍሉ ጢቅ ብሎ ሞላ። በዚያው መጠን ደግሞ እንደ አሸን ፈላ። በግድግዳውና በወለሉ ላይ ትኋኑ ይርመሰመሳል። በቡቱቶው ጨርቅ ላይ ፍስስ ይላል። ቁንጫው እንደ አበባ ቆሎ በየሥፍራው ይፈናጠራል። በየጊዜው የሚረጨው ዲዲቲም የሚያረባቸው እንጂ የሚያጠፋቸው አይመስልም።

ቀን ቀን ዋናው የጊዜ መተላለፊያ ተባይ መልቀም ነው። አቅም ያለው ጨርቁን እያገላበጠ፣ ግድግዳውን እየዳበሰና እየፈተሸ ጣቱንና ጥፍሩን ደም እኪጋግርበት ድረስ ቁንጫ ሲያፍተለትል ቅማልና ትኋን፥ ጣ! ጣ! ሲያደርግ ይውላል። የተሻለው ደካማውን የሚረዳው አንዱ በዚሁ ነው። ጨርቁን ፀጉሩን ይቀምልለታል። ብዙ ሽህ ተባይ አልቆ ይውላል። ማታ መብራት ሲጠፋ ግን አንድም የቀነሰለት አይመስልም። ምድረ ቅማል፥ ምድረ ትኋን ምድሩ፥ ቁንጫ፥ ችግር ባደረቀው ገላ ላይ ዘምቶ ሲያንገበግበው የደከምና የሰለለ እጅም የደረቀ ቆዳ ሲፎክት ያድራል።

ከዚህ ጋር ወደ ጓሮ ወጣ ብሎ የተፈጥሮ ግዴታውን ለመተንፈስ አቅም ያጠረው ወይም ፋታ ያላገኘው ባለበትና በልብሱ ላይ የሚስተው ነገር ሽታና ቆሻሻ ተደምሮ መድረሻ ያሳጣል። ከዚህ ኑሮ የትም ወድቀው መቅረትን እየመረጡ፥ ዕርዳታውን አቋርጠው ከመጠለያው የወጡ አሉ። ሙሔም ሁለት ሳምንት እንደ ቆየ ብዙ ጊዜ ከጅሎት ነበር።

-ሰው ክቡር ነው ይላሉ፤ ቄሶችም ሰዎችም። ታዲያ እንዴት ሰው ከውሻ የባሰ ይዋረዳል? - ሲል ተፈጥሮውን ይታዘባል።

-ሁሉን ሸኘቼና ጨርሼ ብቻዬን እንዲሁ የቀረሁት ይህንን ሊያሳየኝ ነው? ለምን ጉድ ነው የፈጠረኝ? - በማለት ያማርራል። ግን ቊርጥ አድርጎ ሳይወስን ውሎ ያድራል። ስብእናው እንድ እተባይ አንሶ ከተባይ ጋር እየተሟሟተ።

በመካከሉ ስለ ራሱ ምሬት ብቻ እንዳይብከነከን የሚያደርጉ አንዳንድ ነገሮች አጋጠሙት።

አንድ ቀን ጠዋት፥ ሙሔ ወገቡን አሳሽቶ ሲመለስ፥ በሁለት ሰዎች ተደግፎ ጓሮ ሲወጣ ከበደን ያገኘዋል።

«አንተ ከበደ ነህ?» ሲል ጠየቀ ዓይኑን ማመን አቅቶት።

«አልመስለውም እንጂ ነኝ፥ አይዋ ሙሔ» ሲል ከበደ በለሰለሰ ድምፅ መለሰ። ያ ደንዳና ሰውነቱ ጭራሮ ሆኗል። ያ ደበልበል ያለ የነበረው ፊቱ ከስሞ ዓይኑ ተጉልጉሎ የወጣ ይመስላል። ሁለት ክንዱን ከሰዎቹ ትከሻ ላይ አስደግፎ ሁለት እግሩ መሬት መርገጥ ያቃተው ይመስል እንደ መንጠልጠል ብሏል።

«አንተ መቼ መጣህ?» አለ ሙሔ፥ ከተሳሳሙ በኋላ፥ በመገረም መዳፉን ከጭንቅላቱ ላይ አድርጎ።

«እናንት ጠዋት።።»

«ለመሆኑ ማረፊያ ክፍል አገኘህ?»

«ከታዛው ላይ ነው ያለሁት።።»

«ግዴለህም እንግዲያው ተጣበንም ቢሆን ከእኛው ጋር ይበቃናል» በማለት ሙሔ ወደ አረፈበት ክፍል ወሰደው።

«ኧረ ለመሆኑ እንዴት ከረምከው? እንዴትስ ከዚህ ደረስህ?» ሲል ሙሔ ጠየቀ።

«ክራሞትም አይባል አይዋ ሙሔ! ከቆሬ ከወጣሁ የምሄድበትንም ሳላውቀው እንዲያው ዝም ብዬ ወደ ባቲ ተጉተትኩ። ለመድረስ ቀትር የሚያህል መንገድ ሲቀረኝ ከካትራሚው መንገድ ላይ ምን አየሁ መሰለህ? አንድ ሦስት አራት የባቄላ ፍሬ። ለካንስ እህል ተተጫነ ትሬንታ ኳትሮ እየተንጠባጠበ የሚወድቅ ኖሯል። እኔም ለዚህ ያበቃኝን ወስፋቴን እየረገምኩ በሌላ በኩል መንገዱን ይገፋፋኛል በማለት ራሴን እየሸነገልኩ ካትራሚውን አንዳንድ ባቄላ ጥሬ እየለቀምኩ ተጉዤ ባቲ ስደርስ አንድ ሁለት ኩባያ ሙሉ የሚሆን አላገኙ መሰለህ? አንድ አምስት ቀን በዚኢያች ሰንበትኩ።።»

ሙሔ የራሱ ጉዞ ትዝ እያለው በአዘኔታ ከንፈሩን መጠጠ።

«ከዚያ በኋላ ባቲንም የባሰውን ሆኖ አገኘሁት። ከብቱ ያለቀበት የቆላው ሕዝብ ጭንቅ አድርጎ እግዚኦ ይላል። የከተማው ሰው የሚያደርገው ችሮታ ለስንቱ ይብቃ! ረገፈ ሰው ሁሉ። እኔም ሽቅዬ እንዳላድርም በምን አቅሜ። ከእኔም የተሻለው የሚሸቅለው አላገኘውም። በዚህ ላይ ወባና ቸነፈር ገብቶ ረሃብ ገና ያልገደለውን በተራ ረፈረፈው። እኔም ሁለት ወር ሙሉ ሜዳ ላይ ወድቄ ከሞት አፋፍ ከደረስኩ በኋላ የእሱ ነገር ምናለ - በተአምር ዳንኩ። ከዚያም የመንገዱን ዳር ይዤ እየዳሁና እየተንፏቀቅሁ አላፊ አግዳሚውን ስማጠን ለነፍስ ያለ አድን ባለ ካሚዮን አምጥቶ ከዚህ ጣለኝ።።» ከበደ ንግግሩ ያደከመው ይመስል ለአንድ አፍታ እንደማቃሰት እያለ ከተነፈሰ በኋላ «ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ሆናችሁ? ለመሆኑ በቆሬ ሰው ተርፎአል?» ሲል ሙሔን ጠየቀው።

ሙሔ የትዝታው ሰቀቀን እንደ አፍላ እያኰማተረው የደረሰበትን ሁሉ ተረከለት። «ወላጅ፥ ሕጻን ልጁን መንገድ ላይ ጥሎ እንዲሸሽ የሚያደርግ ችግር ነው በወሎ ላይ የመጣው» አለ በመጨረሻ ራሱን እየነቀነቀ።

«መቸስ ምን ይደረግ? አንተማ ሕይወቱ ቢተርፍ ብለህ ነው» ሲል ከበደ ሊያጽናናው ሞከረ። ነገር ግን ቃላት ሊያጽናኑዋቸው እንደማይችሉ ሁለቱም ይታወቃቸው ነበር። የሚነጋገሩት ጠፍቷቸው ለብዙ ደቂቃዎች ያህል ሁለቱም በጸጥታ ተውጠው ቆዩ።

ሙሔ ከበደን የአባት ያህል አስታመመው። በበሽታው ትኵሳትና የሐሩር ወበቅ ምክንያት ተሸማቅቆ የነበረውን ታፋውን ጠዋትና ማታ በሙቅ ውኃ አሸለት። ለአዋቂዎች ከሚታደለው ቂጣና እንጀራ ሌላ ለደከሙ ሕፃናት የሚሰጠውን ልዩ ምግብ ከየትም ፈላልጎ እያመጣ መገበው። ተስፋ ቆርጦ በሁናቴ ተማርሮ ሞቱን የሚመርጥ እንዳለ ሁሉ ከሞት ለመትረፍ በቶሎ ሰውነትን ለማገገም በዚያው መጠለያ ውስጥ የማይደረግ ጥረት የለም። ሕፃን የሞተ እንደ ሆነ መሞቱን ለመጠለያው ሠራተኞች ሳያስታውቁ በመቆየት ለሕፃኑ የሚሰጠውን ልዩ ምግብ እየተቀበሉ መመገብ ወይም ለባሰበት መስጠት የተለመደ ነበር። ሙሔ እየተዘዋወረ ያጠያይቅና ለምኖ ያገኘውን ያመጣለታል።

«እንደ ሕፃን ልጅ ሙቁን ሁሉ ተጋት ነው የምትለኝ አይዋ ሙሔ?» ሲል ከበደ ይግደራደራል።

«በል ፉት በለው! አንተስ ከሕፃን ምን ትሻላለህና! ያች ሚኢስትህ የመጨረሻ፥ ፍየሌንም በልታ ሳትድን ቀረች። አንተም ኵነኔ ላይ ትጥለኛለህ» ይላል ሙሔ በቀልድ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በከበደ ሰውነት እየተመለሰ ሄደ። ሙሔም፥ የሌላ ሰው ሕይወት እንዲተርፍ መርዳቱ የአልጣሽን ሞትና የልጁን ማጣት የካሰለት ይመስል፥ ሰቀቀኑ እየቀለለት ሄደ። የሰው መድኃኒቱ ሰው ነው እንዲሉ፥ መተሳሰቡ ራሱ አንድ ዓይነት የሕይወት አለኝታ ሰጠው።

ከበደ ሰውነቱ ተጠናክሮለት በመጠለያው መዘዋወር ሲጀምር የወትሮ አመሉን አመጣ።

ሕይወት እስካለ ድረስ የተፈጥሮ ፍላጎቶች የተፈጥሮ፥ ስሜቶችና ባሕርዮች፥ አሉ። የተፈጥሮ ፍላጎትና ስሜት እስካለ ድረስ ደግሞ፥ ፍቅርም ጥላቻም ጨዋታም አምባጓሮም ይኖራል። በዚያ በተጨናነቀ ሰፈር መካከል ወንድና ሴት በጋቢ ውስጥ ተሸፍነው በደከመ ሰውነት የፍቅር ስሜታቸውን ይወጣሉኡ። ሌሎች አይተው እንዳላዩ ያልፉዋቸዋል። ለደስታና ለምቾት ኑሮ ተስፋ ቆርጠው የመጨረሻ ኃይላቸውን ለወሲብ ስሜታቸው ብቻ በማዋል እንደተቃቀፉ፥ ምናልባትም ከጭንቀት የተነሣ እንደ ተጣበቁ ሞተው የሚገኙ ባልና ሚስት አሉ። ሞት በሚወስደው ሕይወት መጠን በዚያ መጠለያ ውስጥ ብዙ ሕይወት ይዘራ ነበር። እየቆዩ ብዙ ሕፃናት በመጠለያ ለመውለድ በቅተዋል። ወጣት፥ ኮረዳ፥ ጉልማሳ ባሏ የሞተባት ሴት ሚስቱ የሞተችበት ባል፥ ስንት ሽህ የግል ጭንቀትና መቅበጥበጥ ስንት ሽህ የግል ጠባይና ዝንባሌ በአንድነት በተከማቸበት ሥፍራ የዚያኑ ያህል የፍቅር ጨዋታ ዓይነት የዚያኑ ያህል ግጭት ነበር።

ከበደ ደግሞ ለዚሁ ሁናቴ የበኩሉን ድርሻ አበረከተ። መለከ - መልካም ሴት ብቻዋን ካጋጠመው ሳይጠቅስና ሳያሽኮረምም ብዙ ሴቶች በአንድነት ሆነው ካገኘ ሳይቀላለድ ማለፍ አይሆንለትም። አብዛኛውን ጊዜ ለቁም ነገር ሳይሆን የአፍ ልማድ ሆኖበት ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጠባይም ሆኖበት ነው።

አንዳንዶቹ ሴቶች «ውይ!! ኧረ ምን ያሉ ጉደኛ ሰውዬ ናቸው!» ሲሉ በማፈርና በመሽኮርመም እየተሳሳቁ ያልፉታል። ሌሎች ደግሞ ክፉኛ ይገላምጡታል። ወይም «ምን ዓይነት የሽማግሌ ወራዳ! ኧረ አፈር ብላ! ጨምላቃ!» በማለት ስድብ ያከናንቡታል። ከበደ በዚህ ዓይነቱ መልስም ቢሆን ቅንጣት ሳይሰማው ተጨማሪ ቀልዶች ይጣጥላል።

ከበደ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመጠለያው የሴቶች መንሾካሾኪያ መጠቃቀሻ የወንዶች ከንፈር መንከሻ ሆነ።

አንድ ቀን ጠዋት ጓሮ ደርሶ ሲመለስ አንዲት ልጃገረድ ሴት ግብር ውኃ ስትወጣ አገኘ። ደንገጥ ብላ ቀሚስዋን ሰብ ሰብ አደረገችና አንገቷን ደፋች።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከቅጥነቱ የተነሣ የያዘውን በትር የሚመስል አንድ ሰው እየተንቀጠቀጠና ጥርሱን እያፋጨ ከእነ ሙሔ ክፍል ገባ። «ማን አባቱ ነው ባለቤቴን የሚደፍራት?» አለ በቆረፈደ ድምፅ። ከክፍሉ ያሉት ሰዎች ሁሉ እርስ በእርሳቸው ተያዩ። «እኮ ማነው? ወንድ ከሆነ እኔ ነኝ ይበል!»

ሁሉም ዝም ሲሉ ሙሔ «የሠራኸው ነገር አለ?» ሲል ከበደን ጠየቀው።

«ምንም የሠራሁት ነገር የለም።» ከበደ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ። «ግን አሁን ወደዚህ ስመጣ አንዲት ልጅ ለቀልድ ያህል ሰላምታ ሰጥቻት ነበር።»

«ኧረ ሰላም ያሳጣህ! ሴት አውል ልክስክስ።» ሰውየው በደከመ ሰውነቱ ወደፊት እንደ መንደርደር በትሩን እንደ መስበቅ ቃጣው። «ሱሪው የታጠቅን ወንድ ከሆንክ ወደ ደጅ ውጣ። ወይስ ሱሪ የታጠቅከው ለወጉ ያህል ነው? ቱፍ!» ሰውየው በዛለ ክንዱ ዱላውን እንደ መሰንዘር ሲል ሙሔ መሐል ገባ። ለከበደ መደብደብ አዝኖ ሳይሆን ሰውየው እንዳይጐዳ በማሰብ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ከበደ ከተቀመጠበት አልተነሣም። ለመከላከልም አልከጀለም። ሰውየው በዕድሜ ከከበደ የገፋ ከመሆኑ በቀር የሚሸሸው ሰውነቱ ራሱን መሸከም ያቃተው ነው። በሌላ ሰው ላይ በትር ወይም ዱላ አሳርፎ ከመጉዳቱ ይልቅ በጣት ቢገፉት የሚወድቅ የሚመስል ነው። ልቡ ብቻ አልደከመም። ሐሞቱ ብቻ አልቀጠነም። የመጨረሻ እስትንፋሱ፥ ውርደቱንና ጥቃቱን ሊወጣበት የተዘጋጀ መሆኑን ግን በሁናቴው ያስታውቅ ነበር።

«ረጋ ይበሉ እንጂ፥ በሞት አፋፍ ላይ ሆነን፥ እንዲህ መሆን አይገባም።»

«ባለጌን ከወለደ የገደለው ጸደቀ ተብሏል። እንዲህ ያለው ሴት አውል፥ ኖረስ አልኖረስ ምን ይረባል! መዘዙ ለሌላ እንዳይተርፍ መገላገሉ ይሻላል።» ሰውየው አሁንም በትሩን እንደ ማወራጨት አለ።

ሙሔ ጠቡን ለማብረድ አንድ ሐሳብ መጣበት። «ወዶን፥ አውቆን እኮ አይደለም ታዲያ» አለ።

«እሳ! ወትሮውንስ ባለጌ ብልግናውን አውቆ ቢያርም መቼ ባለጌ ይሆን ነበር!»

«የብልግና ጉዳይ አይደለም!» ሙሔ ከበደን በአዘኔታ የተመለከተው መሰለ።

«እህስ?»

«በሽተኛ ነው።»

«እሱማ ምን ጥርጥር አለው። መድኃኒቱ በዚህ በሽታው እንዲወጣለት ማድረግ ነው።» አሁንም በትሩን ወደ ላይ ብድግ አደረገ።

«ኸረ እንደሱም አይደል በሽታው። ያገር ጠበልም አላዳነው።»

«እኔ ሌላ ምንም አላይበት። ልብሱን እንደሆነ አልጣለ።» ሰውየው ከበደን ትኵር ብሎ ተመለከተው።

«ለሚያውቀውማ ይመስላል። ታሪኩ ግን የሚያሳዝን ነው።»

ሰውየው ለማመንም ላለማመንም የተቸገረ መሰለ። «ትልቅ ሰው ነዎት። ታዲያ ለእንዲህ ያለ ሰው....» ጣቱን ወደ ከበደ በመቀሰር በጥርጣሬ ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው።

«በዚህ ዕድሜዬ ምን አስዋሸኝ!» አለ ሙሔ። «አዩ ነገሩ እንዲህ ነው። ጐልማሳ በነበረ ጊዜ ወደ በረሃው ወርዶ እንደማኮን ሆኖ ነው የተመለሰው። ከዚያ ወዲህ ሴት ሲያይ የሆነ ያልሆነ ያናግረዋል። አፉ ነው እንጂ ክፉ ነገር አያደርግም። ታዲያ ሕመሙ ይህ ከሆነ የተናገረውን ከቁም ነገር ማስገባቱ ፋይዳም የለው።

ሰውየው አሁንም በመጠራጠር አንድ ጊዜ ሙሔን ትኵር ብሎ አይቶ ሌላ ጊዜ ከበደን በዓይኑ ገርምሞ «አስኮናኝ» በማለት እየተንጠራወዘ ወጣ።

ለአንድ አፍታ በክፍሉ ያለው ሰው ሁሉ ጸጥ ብሎ እንደ ቆየ ሙሔ «ለበጎ ነገር መዋሸት ኃጢአት ነው?» አለ። መጠየቁ ሳይሆን ትክክለኛነቱን መግለጹ ነበር።

«ግን እንዴት አሳመርከው!» አለ ከበደ ሳቅ ይዞት።

«ዝም በል አንተ! የማትረባ ውሻ ነህ!» ሙሔ ተቆጣ።

«ሙት አይዋ ሙሔ ምንምኮ አላደረግሁ።

«ዝም በል አልኩህ ስንተዋወቅ አንተናነቅ!»

‹፣በእንደይህ ያለ ቦታ በእንዲህ ያለ ምህኛት አምባጓሮ ተነሥቶ ሰው ቢጎዳ አገር ምን ይላል? አንተ ግን ወደ ፊት በመጥፎ አመል ስምህ ቢነሣ ቁርጥርጣችን ነው። ከመቃብሬ እንዳትቆም»

ጉዳዩንም ሌላ ጊዜ ያነሣው የለም። የጠቡ ወሬም፥ በዚያ ጣዕረ መካከል እንደ ሞተ ሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተረሳ። ከበደም አመሉን አሳምሮ ከክፍሉ ተከትቶ ሰነበተ።

## ፬

አዲስ አበባን ያጥለቀለቀውና ያናወጠው ማዕበል ዜና ውሎ አድሮ ከመጠለያው ሠፈርም ደረሰ። ግን ማናወጥ ቀርቶ የነፋስ ሽውታ ያህል እንቅስቃሴ አልፈጠረም። ዋናው ትንቅንቅ ከሞት ጋር ነው። ሕቅታው ከጣዕር ጋር ነው። መሽነፍን ለማሽነፍ። ወይም ደግሞ ከሕልውናው የሽረሪት ክር ላይ መንጠልጠል። ከዚህ በቀር ሁናቴውን በሚገባ ለመገንዘብ አይችሉም ነበር።

-ሰምተሃል? ኧረ አገር ታውኳል አሉ! - ይላል አንዱ።

-ምነው አልጋ ፈረሰ? - ሲል ሌላው ይጠይቃል።

-የለም! ግና የንጉሡ ሹማምንት ሁሉ ከሹመታቸው ተሽረዋል ይባላል።

-ሽህ ቢታሰብ ያው በገሌ አለች ድመት! ታዲያ የነሱ መሻር መሾም ለእኛ ምን እንዲያደርግልን -

-ኧረ የአሁኑ በደግም አይደል! ንጉሡም ሹማምንቱም ተቀያይመው ነው አሉ -

ይህም ቢሆን የሚያስደነግጥ ነገር አልሆነም። ስንቱ ሹማምንት ንጉሥ ተቀይሞት ተሽሯል። ስንቱ መኳንንትና መሳፍንት ከንጉሥ ጋር ተቀያይሞ ወይም አልጋ ከጅሎ ሸፍቷል። አንዱ በሽፈተ የንጉሥ ሠራዊት በዘመተ ስንት ጦርነት ተደርጓል። ስንት ሰው አልቋል። ስንት ንብረት ጠፍቷል፣ ስንት ሰው አልቋል። ስንት ንብረት ተዘርፏል። የጦርነት መራኮቻ የሠራዊት መረማመጃ ሆኖ ለኖረው የወሎ ገበሬ፥ የአሁኑ የንጉሥና የሹማምንት ቅይይሞሽ አዲስ ነገር አልሆነበትም። ከአሁኑ የባሰ እልቂት ምን ሊመጣ!

ስለ አዲስ አበባው ዜና እንደ ዋዛ የሚደረገውን ጭውውትና ጥይይቅ «ኧረ ወዲያ ተወኝ! አሁን ማ - ይሙት ባድማ ውጦት የፍልፈል የአይጠ - ሞገጥ የፋሮ - መናኸሪያ ሆኖ ጉተራውን አይጦች ጉድጓድ አድርገውት ማሳ ጠፍ በረሃ ሆኖ እኛም ከዚህ እንደዚኢህ ጣዕረ ሞት እያማጥን ወይ አንሽር ወይ አንሞት ጥንብ አንሣ በጕጕት ሲጠባበቅ ሬሳችንን መቅበር አቅቶን ኧረ ኤዲያ ማን ተሾመ? ማን ተሻረ? አሁን ለእኛ ቅንጣት ፋይዳ አለው?» ሲል አንዱ በታከተ አነጋገር ይዘጋዋል።

ቆይቶ ግን ሁሉንም የሚያሳስብና በጕጕት የሚያወያይ ነገር ከጣቢያው ድረስ መጣ።

ከዚያ በፊት በመጠለያው ታይተው የማያውቁ ሰዎች መጡና ጠረጴዛ ዘርግተው ችግረኛውን ተራ በተራ እየተየቁ ይመዘግቡ ጀመር። ከየት አውራጃ? ከየት ወረዳ? ከየት ቀበሌ? ነው የመጣኸው? ጭቃ ሹምህ ማነው? ስንት ቤተሰብ ነበረህ? አሁንስ? ስንት ከብቶች ነበሩህ? እነዚህ ሰዎች ከየት እንደመጡ ለምን እንደሚጠይቁ ችግረኛው ወዲያውኑ አላወቀም ነበር። ከመንግሥት የተላኩ ይሆናሉ የሚል ግምት አደረበት። መንግሥትስ ለምን ማወቅ ፈለገ? አንዳንዱ ጥርጣሬ ገባው። የተወዘፈ ግብር ለማስከፈል ይሆን? ወይስ አዲስ ቀላድ ለመጣል?

ንጉሡ ከሠራዊታቸው ጋር አልተጣጣም እየተባለ የሚወራው እውነት ከሆነ፥ ከመካከላችሁ መልምላችሁ የሚዘምት ሰው ስጡ ለማለት ይሆን? የመንግሥትን ሐሳብ ማን አውቆ ይደርስበታል?

ታዲያ ሳይወድ በግድ ንብረቱን ጕልበቱን ከዚያም አልፎ ሕይወቱን ለመንግሥትና ለሹማምንት ሲገብር የኖረው ብኩን ገበሬም ቢሆን በቀላሉ ልቡን አይሰጥም። ብዙዎቹ ለቀረበላቸው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ በመስጠት ፈንታ የማሳቸውን የአለቀባቸውን ከብትና የቤተሰባቸውን መጠን በግማሽ እየቀነሱ ይናገራሉ። አንዳንዶቹ ማሳም ከብትም ቤተሰብም ያልነበራቸው ሌጣ - ሞላጫ መሆናቸውን አስታወቁ።

ሰዎቹ ምዝገባቸውን ጨርሰው ከሄዱ ከጥቂት ቀናት በኋላ የመጡበት ምክንያት በመጠኑ እየታወቀ ሄደ። ለችግረኞቹ በሬ ወይም የበሬ መግዣና የዘር እህል የሚታደል መሆኑ በመጠለያው ተወራ። ቀንሰው ያስመዘገቡት አንዳንዶቹ ተቆጩ። ብዙዎቹ ግን ለደግ ነገር ከመሆኑ እፎይ አሉ።

መዝጋቢዎቹ ከመምጣታቸው በፊት ሙሔ ሰውነቱ ጠንከር እንዳለለት ከመጠለያው ለመውጣት ሐሳብ ነበረው። ወደ ቆሬ ተመልሶ እንደ ገና መቋቋም እንደማይችል ያውቀዋል። ምኑን ከምን አያይዞት? በዶማስ ስንኳ ቆፍሬ ልዝራ ቢል የዘር እህል መካረሚያ ስንቅ ያስፈልገዋል። በዶማ ተቆፍሮ የተመረተውን እፍኝ እህል ለመካፈል እኒያ ወይዘሮ መምጣታቸው ደግሞ አይቀር ይሆናል። እንደ ገና ራስን ለመቻል ምኑ ከምን ተያይዞ? ነገር ግን በዚህ መጠለያ ውስት ነዳይ ሆኖ ነጋ ጠባ ቊራሽ እየተመጸወተ ነጋ ጠባ በጣዕርና በሞት ጥላ ተከቦ ባለቤት እንዳጣ በረት በቆሻሻና በጠረን ተውጦ ከመኖር የማይሻል ነገር የሌላ መስሎ ተሰማው። ሌላው ቢቀር ነፋሻ አየር ንጹህ የአፈር የሣርና፥ የቅጠል ሽታ ምን ያህል ትልቅ ነገር ነው። ሲሶ አራሽነት አድሮ የልጆቹን መጨረሻ ለማጠያየቅ አሰበ።

ሰዎች ችግረኞችን የመዘገቡት ምክንያት ከተጣራ በኋላ ግን እንደ ሌሎቹ ስደተኞች ሁሉ ሙሔም ከመጠለያው ጋር በቀጭን የተስፋ ክር ታሠረ - ይህንን ቀን አልፈን ሰው እንሆን ይሆን? ብቻውን ብዙ ከሰላሰለ በኋላ ለከበደ አማከረው። ለነገሩማ መጀመሪያውንም ቢሆን ከመጠለያው መውጣት የፈለገበትን አንዱ ምህኛት ሌላው አጠያፊ ነገርና የሰው ሥቃይ አንሶ ከበደ በዚያ አመሉ ችግር ፈጥሮ ችግር ሲደርስበት ላለማየት ነው። በጣቢያው እስከ ቆየ ድረስ አያስችለውም። እንደ አባት እንደ እረኛ መጠበቅ አለበት። ካለበለዚያም እርግፍ አድርጎ መተው አለበት። ሁለቱም ያቅተዋል።

አንድ ቀን ምሳቸውን፥ ታድለው ከክፍላቸው ትንፋግ ለመሸሽ በታዛው ሥር ተቀምጠው ሲበሉ «ከበደ እንዲያው ምን ይመስልሃል ነገሩ?» ሲል ሙሔ ጠየቀ።

«ምኑ?»

«ይኸ የምንሰውማው ነገር።»

«እኔ ምን አውቃለሁ በለኸኝ አይዋ፥ ሙሔ። የሚሆነውን ማየት ነው እንጂ።»

«እኔማ ከዚህ ክርፋታም ሥፍራ ከመቀመጥ የትም ቀልጬ መቅረቱን መርጬ ነበር። አሁን ደሞ ነገሩን ሳየው፥ መቸም ሰው ሲባል ተስፋ ቆርጦ አይቀርምና እንደገና ሆዴ አቅማማ። »

«ምነዋ?»

«የተባለው ነገር የሚሰጥ ከሆነ እኔ የተመዘገብኩት ከዚህ ነው። ሁላችንም በዚህ ብንወጣ አሁን ማ ይሙት እከሌ የሚባለው የት ነው እያሉ ድፍን የወሎን ችግረኛ ይፈልጋሉ ማለት ዘበት ነው። እኔም የምደርስበትንና ለማን አቤት እንደ ምል አላውቅ ብዬ ነው! ምን ትመክረኛለህ? ስለ ራስህስ ምን እያሰብክ ነው?» ሲል ሙሔ ጠየቀ።

ከበደ ጥቂት አሰበ። «መቸም ለነገሩማ ላም አለኝ በሰማይ ነው። ሰጭው ማን እንደሆነኮ አላውቅነውም። አንዱ የውጭ አገር ሰዎች ናቸው ይላል። መንግሥት ነውም ይባላል። የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ደግሞ እንኳን ችግር ዞር ብሎ ሊያይ ይኸው እየተተራመሰ ነው አሉኡ። ለሁሉም ግን ምክር ስጠኝ ካልከኝ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ማየቱ አይከፋም ባይ ነኝ። ተሂዶስ ምን ይገኛል? ከዚህ ቆይቶስ ምን ይቀራል? እኔ በበኩሌ ስለ ራሴ ምንም የማስበው ነገር የለኝም። የማደርገው ሁሉ ጠፍቶኝ ቀኔን መግፋት ብቻ ነው። ከባለመሬት እንዳላድር እንደምታውቀው አመሌ ከሰው አይስማማ። ከተማ ገብቼ ውኃ ቀጂ ዕቃ ተሸካሚ፥ እንደሁ አልሆንም።» ከብደ ራሱን በቅሬታ ነቀነቀ።

እንደ እነ ሙሔ ሁሉ ሌላውም ችግረኛ የመቋቋሚዒያ ዕርዳታውን መምታት በጉጉት ጠበቀ። ከዕርዳታው በፊት ግን የበልጉ ዝናም መጣ።

በደሴ ከተማ ላይ ጥቁር ደመና ሲያንዣብብ ከክፍል ያለው ሳይቀር ተጠራርቶ እየወጣ አንጋጦ ተመለከተ። ደጋዋ የደሴ ከተማ ባለፉት ሁለት ዓመታት እምብዛም ዝናም ያልተለያት ቢሆንም ከድርቅ ቀበሌ ለመጡት ችግረኞች ጠል የቋጠረው ደመና ብርቅና ድንቅ ሆነባቸው። እንደ አስደናቂ ሥዕል እንደ ልዩ ትርኢት እርስ በእርስቸው በአርምሞ፥ በተደምሞ አስተዋሉት። እንደ ትንግርት ተወያዩበት።

-ታየዋለ እንዴት እንደተቆረዘዘ?

-ኤዲያ! አምና የት ነበር!

-ካልክስ አምናም እንዲሁ እያሳየ ነበር የነሳን!

-ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ አሉ። ከአለቅን በኋላ አሁን ቸርኩ ማለቱ ነው ፈጣሪ? —

-ተው በእሱ ላይ ክፉ አትናገር! - ሲል አንዱ ኰስተር ብሎ ይገስጻል።

-ኧረ ኤዲያልኝ! ሰማይ ቤቱን እንደሆነ ባሻው ይቀርቅርብን! ለምድሩ እንደሆነ ይኸው የምናየው ነው። -

-ከዚህ የሚብስ አለ? ወይ ያድናሉ የምባል በሽተኞች አይደለንም - የቁም ሙቶች እንጂ!

በዚህ ዓይነት ጭውውት መካከል ደምናው እየተሰበሰበ እንደ ተቆጣ ሰው፥ መልክ ገጽታውን እያጠቆረ፥ እየቋጠረ፥ የነጐድጓድ ቁጣ እያሰማ የመብረቅ ጅራፍ እያወናጨፈ ጥቂት ቆይቶ ሽክሙን ማራገፍ ጀመረ። ለመጠለል ወደ ክፍሉና ወደ ታዛው የሄደው ከፊሉ ነበር። የቀረው ግን እገላው ላይ አዝመራ ያበቅልበት ይመስል በሰባዔና በምሕላ መልክ አንገቱን ቀና አድርጎ የበልጉን ጠል እንደ ጠበል በጕጕትና በደስታ ተቀበለው።

አንዱ ሙሔ ነበር።

ሙሔ፥ እንደ በረዶ ናዳ የሚያደባው የበልግ ዝናም በፊቱ ተንዥርግጎ በመውረድ አንገቱ ሥር እየዘለቀ ጨርቁን እያራሰ መላ ሰውነቱን ሲያጠምቀው - እ - እ - እ - ት - ት - ት እያለ ደስታ አይሉት ምሬት ተስፋ አይሉት ፀፀት አንድ ዓይነት ሲቃ ተናነቀው። እንደ ሐውልት ተገትሮ ጥርሱን እያፋጨ ለረጅም ጊዜ ቆየ።

«ምን እያልክ ነው አይዋ ሙሔ! ሰው ሁሉ የሆዱ ችጋር አይምሮውን ነካው መሰለኝ!» ሲል ከበደ ክንዱን ይዞ እየሳበ ወደ ክፍላቸው አስገባው።

-የበልጉ አዝመራ አለፈ። ለመከሩስ እንደርስ ይሆን ችግረኛው በአዲስ ተስፋ ጠበቀ።

## ፳

ሰውነቱ መለስ ያለለት እንዲወጣ ሲደረግ ከፊሉ ሲሞት በሥፍራ አዳዲስ ችግረኛ ሲተካ አንድ አባትና ልጅ ከእነ ሙሔ ክፍል እንዲገቡ ተደረገ።

አባትዬው በችግር ሰውነታቸው ክፉኛ የደከመና በዕድሜ የገፉ ከመሆናቸው ሌላ፥ ዓይናቸውን ጋርዶዋቸዋል። ሲነሳባቸው የሚያንፈራፍር ብርቱ ሳል አለባቸው። ልጂቱ ገና ሳዱላዋን ያልደፈነች ናት። ሰውነቷ በጣም የተጐዳ አይመስልም። ወደ መጠለያው እንድትገባ የተፈቀደላትም አባቷን እንድትመራና እንድታስታምም ተብሎ ነው። ልጅቷ ግን ማስታመም ብቻ ሳይሆን ራሷ የመታመም ያህል ትጨነቅላቸዋለች። በተቀሳቀሱ ቊጥር መደጋገፍ ነው። ባሳላቸው ቊጥር ፊቷ ተለዋውጦ ሰውነቷ አብሮ ይንዘፈዘፋል። «ኧረ ሄደብኝ? ምን ተሻለኝ እናንተዬ!» ስትል እነ ሙሔን በጭንቀት ትጠይቃለች።

«ኡህ - ኡህ - ኡህ - ኡህ - ደህና ነኝ ያይኔ አበባ» ሰውየው መልሰው እርሷን ሊያጽናኑ ይሞክራሉ። «ለመሆኑ እህል ቀመስሽ አንቺ?» ስትመገብ አይተውም ቢሆን መጠየቃቸው አይቀርም።

እነ ሙሔ፣ ሲያጽናኑዋቸው ሽማግሌውን ለማገለባበጥና ለመደገፍ ሲረዱዋቸው ሽማግሌው ነጋ ጠባ «ይችም አንዲት ልጄን እንግዴህ ምን ላድርጋት?» እያሉ ሲማጠኑና ምክር ሲጠይቁ፥ ልጅቷ ያይኔ አበባ ለትንሹም ለትልቁም ስትላላካቸው በጥቂት ቀኖች ውስጥ እንደ አንድ ቤተሰብ ቅርብ ሆኑ። አብረው ይበላሉ። ሽማግሌው ሳሉ ተግ ሲልላቸው አብረው ይጫዋወታሉ። ልጅቷም እንደ ሕፃን ከአባቷ አጠገብ ኵርምት ብላ ተቀምጣ ታዳምጣቸዋለች። በማፈር አንገቷን ደፋ አድርጋ። የከበደ ዓይንም ከአቀረቀረው ፊቷ ላይ ተተክሎ ይውላል። ሙሔ በዓይኑ ሲገረምመረው መለስ ያደርጋል። አስተያየቱ ግን እንደ ወትሮው የማዳራት ሳይሆን የአዘኔታና የማሰብ ዓይነት ነበር።

አንድ ቀን ውኃ ለብ አድርጋ አባትዋ እንደ ተጋደሙ ጭቅቅት የተጋገረበት ቋንጃቸውንና እግራቸውን አጥባ ስትጨርስ የተረፈውን ውኃ እያቀረበች «እርስዎንም ልለቅልቅዎት አለችው ሙሔን።

«ተዪው ግድ የለም አትቸገሪ የኔ ልጅ» አለ ሙሔ እግሩን እየሰበሰበ።

«ኧረ ያምጡት!» መልሳ ጠየቀችው።

«ነውርም አይደል? ከበሬታ ነው እንዳትል የእኔም ልጅ ብትሆን በዕድሜ ያንተስ ልጅ ሳትሆን ትቀራለች?» ሲሉ ሽማግሌው በደከመው ድምጽ ተናገሩ።

«ለሱ ሳይሆን ዛሬ ነው የታጠብኩት ብዬ ነው።»

«ለምርቃቱስ ቢሆን» ብለው ሽማግሌው ዓይናቸውን መልሰው ሸለብ አደረጉት።

ሙሔ እግሩን እየታጠበ ያይኔ አበባን ሲያስተውላት ልጁን ዘይኔን አስታውሰችው። - እንደ እኚህ ሽማግሌ ይዟት መጥቶ ቢሆን ይሻል ነበር? አሁን የት ደርሳ ይሆን? ሌሎቹ ልጆቹስ? ስንት ቤተሰብ ስንት ዘር የነበር እንዴት ነጠላውን ይቀራል? እነዚህስ እንደሱው አይደሉም? አዬ እሎ፥ ዘር አይውጣልህ የተባለ አይምሰልም? ከሐሳቡ የነቃው አጥባ ጨርሳ ለመሳም ሳብ አድርጋ ጉንበስ ስትል ነበር። «ተዪው! ተዪው!» ሲል እግሩን ከከንፈሯ ሳይደርስ ነጠቃት። ከበደ ደግሞ ውኃውን ይዞ ገና ወደ እርሱ ሳትዞር ፈጠን ብሎ ወጣ። ሙሔ በዓይኑ ተከተለውና «ኧረ ያዝልቅልህ!» አለ በሆዱ።

ሽማግሌው ፀሐይ እንደ ነካው በረዶ ቀን ተቀን እየሟሙ ሂደው መንቀሳቀስ እስኪያቅታቸው ተዳከሙ። አንድ ቀን እንደ ምንም ከአንገታቸው ቀና ብለው «አይዋ ሙሔ፥ አንድ የማስቸግርህ ነገር አለ» አሉ እብሳል መካከል ንግግራቸውን እያቋረጡ። አሁን መሳል ስንኳ እያቃታቸው ከትናጋቸው ሥር ትክ - ትክ እያለ ተውጦ ይቀር ነበር። «ያይኔ አበባ! ይችን ጨር ለቅልቂልኝ እስቲ» በለው እንድትወጣ ሲያደርጉ ጉዳዩ ልጃቸውን የሚመለከት መሆኑ ሙሔ ገባው።

«አየህ! አንድ ልጄ ናት። እናት የላት ወንድም፥ የላት እኅት የላት። ዕጣ ነፍሷን።»

«መችም የዘንድሮው መዓት በሁሉም ላይ ነው የደረሰው» አለ ሙሔ በማጽናናት ዓይነት።

«እሱማ ነው።» ሽማግሌው መናገር ስንኳ እየደከማቸው በማቃሰት ይተነፍሳሉ። «ግን፥ የእሷ ቆይቷል። ታሪኩ ረጅም ነው።»

ሙሔ ታሪካቸውን እንዲጨርሱ ዝም ብሎ ጠበቃቸው።

«ሁነኛ ጠባቂ ያስፈልጋታል» አሉና አሁንም ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ። ሙሔ ግራ ገባው። - አእምሮአቸውን አመማቸው ይሆን? በማለት አሰበ።

«ታሪኩ እንዴት ነው ብለህ አትጠይቀኝም?» በጣም በተዳከመ አንደበት እንደ መገሰጽ አሉት።

«ሊነግሩኝ ነው ብዬ ነዋ!»

«ልነግርህማ ነው።» ዓይኖቻቸውን ከድነው ለጥቂት ጊዜ ሰመመን ውስጥ ገቡ። «አየህ እናቷ በሽታ ነበረባትና አራት ጊዜ አከታትሎ ከሆድዋ ውስጥ ጠፋባት። በአምስተኛው እርግዝና ዘጠኝ ወር ሙሉ ከአልጋ እንዳትወርድ አድርገን በስንት መከራ ያይኔ አበባን እንደ ምንም ተገላገለች። ግን ዕድሜ ልኳን የናፈቀችውን የልጅዋን ፊት ስንኳ ለማየት አልበቃችም። አራስ ትታልኝ መቃብር ወረደች። እኔም ወተት እየጋትሁ ጣቴን እያጠባሁ አባትም እናትም ሆኜ አሳደግኋት። ስለዚህ ነው ሁነኛ ጠባቂ ያስፈልጋታል የምለው።»

ሙሔ የነገሩ አዝማሚያ አሁንም ስላልገባው «ባል አልዳሯትም ነበር?» ሲል ጠየቀ።

«ያውም አሳምሬ እንጂ!» ሽማግሌው ያለ የሌለ ኃይላቸውን አሟጥጠው በማዳነቅ ተናገሩ። «ላንድ ልጄ ያልሆነ ብዬ ያለ የሌለኝን ደግሼ። ያን ጊዜኳ ደህና ነበርኩ። ፓሶ ሚሌ ላይ ጥሩ መሬት ነበረችኝ። ያለ ማቋረጥ ውኃ የሚፈስባት በመሃሏ። ዓመት ከዓመት ለቃሪያም ለጐመንም ለአትክልትም የምትሆን። በኋላ የራስ አሊ ወሌ ልጆች ባለሟል ለኔ ተሰጥቷል ብሎ ነጥቆ አስነሣኝ እንጂ። እሷም መልካም ባል አግብታ ነበር። ታዲያ ያንቺ ይሁን ያላላት ኖሮ አንድ ጊዜ በትልቁ ካሚዎን ተጭኖ ሲሄድ ተገብልጦ ሞተ። እንጃት የመሰለ ልጅ። እንደገና ከኔ ዘንዳ ተመልሳ የበሬ ግንባር የማታህል የተባለች ማሳ ላይ እንደ ምንም ተቻጋግረን ስንኖር ይኸው መዓት ደሞ መጣና እንዲህ አደረገን። ታዲያ አሁን ዕጣ ነፍሷን ናትና ሁነኛ ሰው ያስፈልጋታል።»

«ከዚህ ከደረሰች ምንም አትሆንም። እርስዎም አሉላት። የተበታተነው ዘመድም እንግዲህ መሰባሰቡ አይቀር። እንደሚወራው ስንቅም ከብትም ቢጤ የሚሰጥ ከሆነ» ሲል ሙሔ አሁንም ሊያጽናናቸው ሞከረ።

«የተረፈም ዘመድ የለኝ። ግማሹ ቀደም ብሎ ግማሹ አሁን ሁሉም አልቋል። የእኔም ነገር እንደሆነ አብቅቷል። ቀኔ ተቃርቧል።»

«ኧረ እንዲህ አይበሉ። የልጅነቱም ሆድ ያባቡታል። ስንቱ የደከመ ድኖ ወጥቶ የለ?»

«እሷንስ አልነገርኳትም።» እንደማረፍ ዓይነት ንግግራቸውን ላንዳፍታ አቆሙ። «የእኔን ግን አውቀዋለሁ። ጣት አይሞላም ቀኔ።»

«ኧረ ደግ አይደለም እንዲህ አይበሉ!»

«እኔ እንኳ ግድ የለኝም። የኖርኩት ዕድሜ ይበቃኛል። የምታሳዝነኝ ዕታ ነፍሷ የሆነችዋ ናት።»

ሙሔ የሚመልሰው ጠፍቶት ዝም አለ።

ቆይተው - ቆይተው «መቸም ክፉ ቀን ነው ያስተዋወቀን። ስለዚህ ነው የማስቸግርህ» አሉት።

-አግባት ሊሉኝ ይሆን? - የሚል ስጋት በሐሳቡ መጣበት።

«የሚቻለኝ ነገር ከሆነ ምን ቸግሮኝ!› አለ ቅዝዝ ባለ አነጋገር።

«ምንም ችግር የለበትም። ጡት እንድታጠባት ነው የምለምንህ» አሉት።

«አሄሄ! ለዚሁ ነው እንዲህ የተጨነቁት? ግና ምን ልጠቅማት? እኔም እንደሚያዩኝ የሰው እጅ የማይ ሆኜአለሁ።»

«ምንስ ባታረግላት። እንድታሾማት፥ እንድታሽልማት አይደለም። የእኛ ቢጤው አበልጅ የሚኳኳነው ጡት የሚጣባው ጥቅም አይቶ አይደለም። ዝምድና ፍለጋ እንጂ። ያይኔ አበባም ዕጣ ነፍሷን ስለሆነች እንደ አባት ዓይንህ እንዲያርፍባት ብዬ ነው ያስቸገርኩህ» አሉ ሽማግሌው።

«ኧረ ምንም ችግር የለበትም» ሲል ሙሔ በድጋሚ አረጋገጠላቸው።

በበነጋው ለመድኃኒት ነው ተብሎ ጠብታ ማር ተፈልጎ በመጠለያው ውስጥ ያሉ አንድ ካህን ተጠርተው ሥርዓቱ ተካሄደ። በመጀመሪያ ሙሔ እጁን ታጥቦ እንደ ተቀመጠ ካህኑ አቡነ ዘበሰማያት ደግመው በትሸን ቢልቃጥ ውስጥ ያለውን ማር ቱፍ ቱፍ አሉበትና ለሙሔ ሰጡት። ሙሔም የግራ እጁን አወጣና ለያይኔ አበባ ዘረጋላት። የያይኔ አበባ በማፈር አንገቷን ሰበር አድርጋ የሙሔን ጣት ጉረሰችና መጠጥ አደረገችው። ሽማግሌው አባት ልጃቸውን በስስት ዓይን እየተመለከቱ በእርካታ ተነፈሱ። ሙሔ ግን አንድ ዓይነት ሰቀቀን መላ ሰውነቱን ሰበቀው። ኀዘን አይሉት ፀፀት ጉሮሮውን የሚተናነቅ ስሜት፤ የራሴን ልጅ እንደገና አቅቶኝ መንገድ ዳር ጥዬ መጥቼ አሁን ለሰው ልጅ እንደገና አባት ልሁን? - ጣቱን ከአፍዋ አውጥቶ እንደተነገራት ጉልበቱን ስትስመው ቀና አድርጎ ጉንጭዋን አገላብጦ ሳማትና «ከአብራኬ ከወጡት ልጆቼ ብለይሽ እሱ ነፍሴን ከሥጋዬ ይለያት» ብሎ ቃል ኪዳኑን ፈጸመ። ለዕለቱ የታደላቸው ምግብ ቀርቦ እንደ ጠበል ጠዲቅ ተቃመሱት።

ሽማግሌው ሁለቱን ቀን በዓለም ላይ የሚመኙት ዓላማ የተሳካላቸው ይመስል የመርካት መንፈስ ሰፍኖባቸው ሰነበቱ። ላሉም በመጠኑ ቀለል አለላቸው። በሦስተኛው ቀን ግን እንደገና ብሶባቸው ሳንባቸው የሚፈነዳ እስኪመስል ድረስ ሌሊቱን ሙሉ ሲስሉ አድረው ከንጋቱ ላይ ድምፃቸው ረጭ አለ።

ጧት ያይኔ አበባ አስተዳደራቸውን ለማወቅ ቀረብ ብላ ተመለከተችና «ውይ! አባብዬ! ውኃ በላኝ!» ስትል እሪታዋን አደባለቀችው። ሙሔና ከበደ ደጋግፈው ከክፍሉ አወጧትና ሌላ ክፍል ውስጥ እንድትቆይ አደረጉ። ከዚያም ሬሳውን አጥበው በአሮጌ ጨርቅና በቱቻ ገመድ ከፈኑት። አስከሬኑ ለመሸከም የሚረዳዱ ሰባት ስምንት ፈቃደኞችም ተገኙ። ለአውሬ መከላከያ ያህል ቆፍረው ከቀበሩት በኋላ ሌሎቹ ሰዎች ወደ መጠለያው ሲመለሱ ሙሔ ባለቤቱ አልጣሽ የሞተች ጊዜ አንዳደረገው ከመቃብሩ አጠገብ ቁጭ ብሎ ተከዘ። ከበደ ከአጠገቡ ቆሞ ጠበቀ።

«ምን እያሰብክ ነው?» ሲል ጠየቀ።

«ደሞ ምን የሚታሰብ ነገር አለ? ስም ብሎ መደንዘዝ ነው እንጂ። ሕይወታችን እንዲህ ቀብር ብቻ ሆኖ ቀረ? መኖር ስያቅተን መቅበር አይታክተን። ምን ይሉታል ይህንን ሕይወት?

ሰውየው ግን ጻድቅ ነበሩ። ቀናቸው መድረሱ አስቀድሞ የታያቸው። አሁን ምን አባቴን ላረጋት ነው?» አለ ሙሔ በአብዛኛው ከራሱ ጋር በመነጋገር።

«ማንን?»

«ልጅቷን ነዋ! እኔ ራሴ ነገ የምወድቅበትን የማላውቅ ተመጽዋች። በዚህ ላይ ደግሞ ዕድሜ ከሰጠኝ የጠፉትን ልጆቼን ፍለጋ ለመሄድ አሳብ አለኝ። እሷን ይዤ ልንከራተት ታዲያ? ይህማ እሷኑ ማሰቃየት ለርሷ ሸክም መሆኑ ነው። ልጄን ዘይኔንስ አዲስ አበባ ሂጅ ያልኳት ይኸንኑ ፍራቻ አይደል? የራሴን ሕጣን መንገድ ላይ ትቼ ሌላ ልጅ መያዝ። እንዲህ አርጎም ሁነኛ መሆን የለ! ታዲያ ምን አባቴ ላረጋት ነው?» አሁንም ሙሔ ከሐሳቡ ጋር የሚነጋገር ይመስል ነበር።

«- እ - » ከበደ መናገር ፈርቶ አቅማማ። በእግሩ አውራ ጣት አፈር እየጫረ፥ «እ - እ - እ - አትቆጣ እንደሆነ እኔ የምጠይቅህ አንድ ሐሳብ ነበረኝ።»

«ምን ያስቆጣኛል። ተቆጥቸስ ምን እንዳላደርግህ ብለህ?»

«እ - እ - እኔማ አንተ ልጆችህን ፍለጋ የምትሄድ ከሆነ ልጅቷን እኔ ልጠብቃት ልያዛት ለማለት ነበር።» አንድ ትልቅ ሸክም እንደ ወረደለት ያህል ቀለለው።

«በምን አኳኋን?» ሙሔ በጥርጣሬ ዓይን እየተመለከተ ጠየቀው።

«የእኔማ ሐሳብ እንዳገባት ነበር።»

«ምን?» ሙሔ ፊቱን አኰሳትሮ ተቆጣ።

«ምን ነውር አለበት? ሚስቴም እንደሆነች ከሞተች መንፈቅዋ አልፏል።»

«ከትኵስ መቃብር ላይ ቆመህ ይህንን ስትናገር ጥቂትም አታርፍ? አሁን የቀበርነውኮ ወላጅ አባቷን ነው!» አለ ሙሔ በአፈጠጠ ዓይኑ መቃብሩን እያመለከተ።

«አሁንኮ ይሁን አላልኩም። አውቀኸው እንድትቆይ ነው እንጂ ነገሩን ያነሣሁት። ማለቴ እሷም ቢሆን አባቴ ሞተ ብላ መንኵሳ አትቀር። ውላ አድራ የምታገባው ከሆነ። እኔም ቢሆን መቸም እንደገና ጐጆ የቀረቀርኩ እንደሆነ የሴቱንም የወንዱንም ሥራ ብቻዬን አይሆንልኝ። ብቻዬንስ ብባክን ሟችቷን ምን ልጠቅማት? ሲሆን - ሲሆን ዘር ለማፍራት እበቃ ይሆናል። ማን ያውቃል? ዕውቂያና ዘር አንድ ቀን ነው ተብሏል። ልጅቷም ጠባየ መልካም ዓይነ አፋር ትመስላለች። ለዚህ ብዬ ነው፥ ሐሳቤን በክፉ አተርጕምብኝ አይዋ ሙሔ። ያ - አመሉ ነው ብለህ አትገምተኝ። ሰው መቸስ አዙሮ የሚያይ አንገት ካለው ራሱን እየታዘበ መሄዱ ይቀራል? እኔም አመሌን መታዘብ እየጀመርኩ ነው።» ከበደ ንግግሩን ሲጨርስ እንደ ማፈር ዓይነት ፊቱን መለስ አደረገ።

ሙሔ አቀርቅሮ ጥቂት አሰበ። «ነገር ግን ጊዜውን ገምቼ እኔው ሳልፈቅድ አንድ ነገር አደርጋለሁ ብትል ወዬው አንተን አያርገኝ! በእጄ ነፍስ እንዳታስጠፋ!» ሲል ኵስተር ብሎ አስጠነቀቀ። ልብ የማይሞት ሆኖ ነው እንጂ በጕልበት ከሆነ ከበደ ከመቅጽበት አፈር

እንደሚያስበላው ያውቃል። የደከመ ሰውነታቸውን እየጐተቱ ያለ አንዳች ንግግር ወደ መጠለያቸው ሲመለሱ ሙሔ በሐሳብ ተውጦ ነበር። ሕይወት ምን ዓይነት እንቆቅልሽ ነው? ምን ያህል አስቸጋሪና አስጨናቂ ነው? ኑሮ ኑሮ ወደ መሬት ዙሮ ዙሮ ወደ ቤት ይባል ነበር። ዛሬ ግን ሰው የሚሞተው ኑሮውን በመጨረስ አይደለም እየኖረ ይሞታል፣ እየሞተ ይኖራል። ዙሮ ቤቱ አይመለስም ተበትኖ ይቀራል። ይህም ሁሉ ሆኖ ሕይወት ውድ ናትና አምሳያውን አፈር እያለበሰ ስለ ራሱ ትዳርና ደስታ ያስባል። የሞትና የሕይወት ልዩነት ምንድን ነው? ሰው ሞተ የሚባለው ምን ሲሆን ነው? በሌሎች ዘንድ ሕልውናው ሲረሳ ነው? በሰዎች ሕሊና ውስጥ የሚታወስ ከሆነ እንዴት ሞተ ሊባል ይችላል? ሰው ሲሞት ምን ይሰማው ይሆን? ሰውየው የሚሞቱ መሆናቸው አስቀድሞ በሐሳባቸው ታይቷቸው ነበር። በሞቱበት ቅጽበትስ ምን ተሰምቷቸው ይሆን? ሞት ጥቁር አካል ለብሶ ዓይኑን አፍጥጦ ጥርሱን አግጥጦ የሚመጣ ነው? ወይስ ነፍስ እንደዚሁ ብን ብላ ትጠፋለች? የሕይወትን ትርጉም ለማወቅ የሞትን ምሥጢር ማወቅ ሳያስፈልግ ይቀራል?

ከወደ መሐል ከተማ ተደጋግሞ የተተኰሰ ጥይት ሙሔን ከሐሳብ ቀሰቀሰው። አሁንም መልሶ ጧ! ጧ! ጧ! አለ።

ሙሔ የጥይት ድምፅ ወደመጣበት አግጣጫ ጆሮውን ቀና አድርጎ «አዲስ አበባ ተፈጠረ የተባለው ሁከት ከዚህም መድረሱ ነው መሰል ጃል!» አለው። ወደ አዲስ አበባ የሰደዳት ልጁ ዕድል አእምሮውን አስጨነቀው።

አዲስ አበባ ደፍርሶ ከሆነማ ዘይኤን ምን በጃት?

## ምዕራፍ ሦስት

ከተሾመበት ቀን አንሥቶ «ፋታ ስጡት» እየተባለ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ቢለፈፍለትም ልጅ ጉግሣ አፈቀላጤዎቹ ያዳነቁትን የመሪነት ችሎታውን ለማስመስከር በቂ ድጋፍም ሆነ በቂ ጊዜ አላገኘም። ተራው ሰው እስከዚህ እንደ ትልቅ ነገር አልቆጠረውም። የሚወያይበትም በማቃለል እንደ ዘበት ሆነ።

-ታዲያስ አዲስ ነገር የሚያመጣ ይመስልሃል?

-እኔ ምን አውቃለሁ። የጉልቻ መለዋወጥ ብቻ እንዳይሆን!

-ምናልባት አገሩ ትንሽ ረጋ ይል እንደሆነ።

-ለሰዓት እላፊው እንደ ሆነ እንጂ የሚሰበር አውቶሞቢል የለኝ አልጨነቅ።

-አገሪቱስ ዕድል ቢሆን።

-እሱስ ነው። ግን የባሰ እንደሆነስ? አናውቀው።

ጭውውቱስ በዚህ ዓይነት ተንጠልጥሎ ይቀራል።

በሁለተኛው ቀን ከአራት ኪሎ የተነሣ የተቃውሞ ሰልፍ «ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም!» «ቀዳዳ ሱሪ ገልብጠው ቢታጠቁት ያው ቀዳዳ ነው!» «ጐንጤ ይሰቀል!» «ጉግሣ ይውረድ!» የሚል ሰሌዳ ይዞ መሐል ከተማውን አጥለቀለቀው። ሰልፉ በራስ መኰንን ድልድይ አድርጎ ወደ ፒያሳ እስኪዘልቅ ሌሎች በብዛት እየተቀላቀሉበት ቴዎድሮስ አደባባይ ሲገባ የሚተም ማዕበል ሆነ።

በዚህ ጊዜ አዲሱ አቃቤ ሹም ጉግሣ «ሁናቴው በቊጥር ሥር ስለ መዋሉ ራሱም የሕዝብን ተቀባይነት ስለ ማግኘቱ» በቢሮው ውስጥ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጋዜጠኞች መግለጫ ይሰጥ ነበር። ተዝናንቶ ፈገግ እያለ፤ ፈረንጅ ቀመስ ቀልዶችም በመልሱ መሐል ጣል ጣል ያደርጋል። በዚያ የነበሩ አንዳንድ ጋዜጠኞች «ይህንን ፈተና በእርግጥ ያልፈዋል?» የሚል ግምት ሳያድርባቸው አልቀረም። በራሱ የሚተማመን ይመስል ነበርና....።

ነገር ግን በመካከሉ ሰልፈኛው ከቢሮው ባሻገር ሲደርስ ጩኸት ከክፍሉ ገብቶ አስተጋባ። ውግዘቱ «አትነሣም ወይ፤ አትነሣም ወይ፤ የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ» የሚለው መዝሙር በመስኮቱ በኩል አልፎ የአቃቤ ሹሙን መግለጫ የሚያስተባብል መሰሰ። በተለይ የውጭ አገር ጋዜጠኞች ጆሮአቸውን ወደ መስኮቱ በማቅናት በአስተያየታቸው ላቀረቡት የጥርጣሬ ጥያቄ «መቸም እንደምታውቁት በእንደዚህ ያለ የሽግግር ጊዜ፥ እንደዚህ ያለ ሁናቴ መድረሱ የሚጠበቅ ነው። ብዙም አያስጨንቀኝም። ምክንያቱም ከአቀድኩት ፕሮግራም አንዱ የሕዝብ መብትን ማክብር ስለሚሆን አልቃወመውም። ግዴላችሁም እስኪሰክን ድረስ ለጥቂት ጊዜ ነው» ሲል እየመለሰ፥ ቅንጣት ያህል አለመጨነቁን በሚገልጽ ፈገግታ ዙሪያውን ቃኘ።

ፈገግታውን ግን አልጨረሰውም። ወዲያው ተኵስ ተንጣጣ። ጩኸትና ኡኡታ ተደባለቀ። ከቢሮው መለኮት ባሻገር ሰው ሲበረግግና ሲሯሯጥ ታየ። ፈገግታው ከዚያ ለስላሳ ፊቱ ላይ ደርቆ ቀረ። የደም ሥሮቹ ከግንባሩ ላይ ግትር ብለው ወጡ። «ይቅርታ አድርጉልኝ ለዛሬው ይኸው ነው። ነገም ከነገ ወዲያም በሩ ለእናንተ ክፍት ነው። እንደዚህ ያለው ነገር የሚሰክን ግርግር ስለሆነ እነደኔ በሕዝብ መገናኛ የሚገለጽ አይደለም።»

በሚቀጥሉት ቀኖችም ሆነ ሳምንቶች አንዱም ነገር አልሰከነም።

ከብዙ አግጣጫ የሚመጣው እንቅስቅሴ ግፊት፥ በዋከብ ፋታ ከመጠየቅ አልፎ «ውኃ ውኃ» የሚያሰኝ ሆነ።

በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር ባለ አሥራ ስድስት ነጥብ ጥያቄዎች አቅርቦ ብዙ ንግግር ተደርጎ ሌሎች ታክልውበት ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ በመላ ኢትዮጵያ ተደረገ። ከዳቦ መጋገሪያ እስከ ከፍተኛ እንዱስትሪ ድረስ የሠራተኛ እጅና መሣሪያ ቀጥ ብለው ስነበቱ። እርግጥ የአዲስ አበባ ሕይወት በሙሉ ቀጥ አላለም። ግን የልብ ሕመም እንዳለበት በሽተኛ የእንቅስቃሴ ትርታዋ ተዳክሞ ጭር ብላ ሰነበተች።

አጠቃላይ የሥራ ማቆም አዳማ ሲያበቃ የተናጠሉ በየሥፍራው ቀጠለ። የሲቪል አቪየሽን የትምባሆ፥ ሞኖፖል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፥ የአሰብ ወደብ ሌሎችም ሠራተኞች የየበኩላቸውን ጥያቄ እያቀረቡ ሥራ አቆሙ። ለአዲስ አበባ ኗሪ ሕዝብ ምናልባት ከሁሉም ጐልቶ የተሰማው የማዘጋጃ ቤት ጽዳት ሠራተኞች አድማ ነበር። የአዲስ አበባ መንገድና

መንደር በቆሻሻ ሽታ መተላለፊያ አሳጣ። በየሥፍራው የሚፈነዳውን እምቢታ በቂስ ውግዘት ስንኳ ለማገድ አላመቻም።

ከዚህ ሁሉ ያላነሰ ለአዲሱ አቃቤ ሹም ፋታ የማይሰጠው መስክ ደግሞ በዜና ማሰራጫዎችና በሚበተኑ ወረቀቶች የሚሰማው እሮሮ ሆነ። በሽተኛና የሚመረምር ሐኪም «ተንፍስ! ተንፍስ!» አለ ሲል አንድ ጋዜጠኛ በጊዜው እንደ ጠቀሰ ከሕዝብ ዘንድ የሚጕርፈውን ብሶት ውንጀላ፥ ጥቆማ ለመግለጽ ጋዜጦች ዓምድ አልበቃቸው አለ።

-የቀድሞው አቃቤ ሹም ወገን በመሆን ያለ ችሎታው የተሾመው አቶ እገሌ ሠራተኛን የበደሉ፥ ዘመዶቹን የቀጠረ በደመወዝ ያሳደገ፥ የመንግሥት ገንዘብ የሠረቀ ወንጀለኛ ስለሆነ ከሕግ ፊት እንዲቀርብ እንጠይቃለን።

-የጕንጤ ወንድም የጡት ልጅ የሆነው አቶ እገሌ የፈጸመው ወንጀል የሚከተለው ነው....ስለዚህም እኛ....መሥሪያ ቤት ሠራተኞች እንፋረደዋለን።

-ብ....መሥሪያ ቤት በሹሙ በአቶ እገሌ የተፈጸመውን ግፍና በደል መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀው ይሆን.....?

ከፍተኛ የሃይማኖት ማዕርግ ያላቸው አንድ የቤተ ክህነት ሰው ሳይቀሩ የአቶ እገሌን ሚስትና ወይዘሮ እገሊትን ለማማገጣቸው ማስረጃ ተጠቅሶ ክስ ተጽፎባቸው ነበር።

በጋዜጣ የማይታተሙት እየተባዙ በየአደባባዩ፥ በየመኪናው፥ በየመሥሪያ ቤቱ፥ ይታደላሉ። በአዲስ አበባ ወረቀት ያልተበተነበት የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ድርጅት ቢኖር ብርቅ ነበር። ለአላፊ አግዳሚዊ የሚታድሉት የውንጀላ ወረቀትቶች ከግርጌያቸው «.....የእገሌ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች በሙሉ» የሚል ጽሑፍ ይኑራቸው እንጂ አንዳንዶቹ ከግል ሰዎች የመነጩ ነበሩ። ለግል ቂም በቀል የተጻፉም ነበሩ።

ይህም ሆኖ በየመሥሪያ ቤቱ አለቃና ምንዝርን የሚያገናኘው እትብት መበጠስ አዲሱ አቃቤ ሹም እንደሚፈልገው የመንግሥቱን ሥራ የሚያንቀሳቅሰው ሆነ። አለቃ ከፍርሃቱ የተነሣ ቢሮውን ከውስጥ ቆልፎ በመቀመጥ ወይም ዘግቶ በመውጣቱ አንድም ነገር ሳይሠራ ይውላል።

አቃቢኤ ሹም ጉግሣ አዲስ ዕቅድ ማውጣት ቀርቶ ያለ ማቋረጥ የሚያደርሱትን የችግር ጥሪዎች በቅደም ተከተሉ እንዴት እንደሚያስተናግዳቸው ግራ ገባው።

በዚህ ሁሉ ላይ አቃቤ ሹም ጉግሣ ከስድስተኛ ፎቅ ቢሮው ሆኖ ከታች ከዚህም -ከዚያም የሚያጣድፈውን የተራው ሕዝብ መቶና ሽህ ጥያቄ በአንድ አንጕል በአሥር ጣት ለማስተካከል በሚጥርበት ጊዜ በእርሱ ደረጃና ከእርሱ በላይ በቤተ መንግሥት አካባቢ ሦስት ፊት የፖለቲካ ጭዋታ ይካሄድ ነበር። አቃቤ ሹም ጉግሣም ይህንን ጨዋታ ከመጀመሪያው አንሥቶ አሳምሮ ያውቀዋል። ከጨዋታው ውስጥም አለበት።

ነገሩ ቆይቷል። የአድዋ ድል በዓል ቀን ንጉሡ በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሲያስቀድሱ፥ የቀድሞው አቃቢዔ ሹም ጕንጤ ከአጠገባቸው ቁም መታየቱ ሕዝቡን አስገረመው እንጂ፥ ልጅ ጕንጤ እጅግም አላስጨነቀውም ነበር። ነገር ግን እያደር ጕንጤ ውሎ ቤተ መንግሥት ሆነ።

ሌላው ቀርቶ ልጅ ጉግሣ ንጉሡን ለብቻ ማነጋገር አልቻለም። ጉንጤ ሁልጊዜ ከአጠገባቸው ይገኝ ነበር። ልጅ ጉግሣ ለሚያቀርበው ሐሳብ አስተያየት ይሰጣል። ምክር ይሰነዝራል። ልጅ ጉግሣም በቢሮው ውስጥ ከጠረጴዛው ፊት ለፊት ከግድግዳው ላይ የተለጠፈውን የኢትዮጵያ ካርታ እየተመለከተ «አገሪቱን የሚያስተዳድር እኔ ነኝ እርሱ? ምን ማድረግ ነው የሚፈልገው? ራሱ እንደ ወደቀ እኔንም አብሮ ለመጣል? እያለና!» ይላል ብቻውን።

ንጉሡም በምርጫው ሐሳባቸውን ለውጠው ፊት የነሡት ስለመሰለው ስጋቱ እየተጠናከረ ሄደ። ዡማነህ ሳይቀር እንደ ቀድሞው ሆኖ አልታየውም።

የሥራ ማቆም አድማው፥ በየመሥሪያ ቤቱ አለቀና የመክሰስ ንቅናቄው፥ ወረቀት መበተኑ ሰልፍ ማድረጉ በጠቅላላው ቀውሱ፥ በመብረድ ፈንታ እየተባባሰ ሄደ። ልጅ ጉግሣ የጠየቀውን ፋታ ሳያገኝ መጋቢትን ጨርሶ ሚያዝያ ገባ። በዚህ ዓይነት ሊቀጥል እንደማይችል ታወቀው። አንድ ቀን የስንብት መጠየቂያ ደብዳቤ ለንጉሡ ለማቅረብ በሚያሰላስልበት ጊዜ እንደ ሻንጣ ውጭ አገር አብሮት ይዞር የነበረው ታማኝ ልዩ ጸሐፊው አዲስ የተበተነ ወረቀት አምጥቶ ሰጠው። ከጦር ኃይሎች ኮሚቴ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተላለፈ መልዕክት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያ የደረሰባቸውን በደል ይዘረዝርና በአዲሱ አቃቤ ሹም አመራርም ቢሆን ጥርጣሬ ያደረበት መሆኑን ያመለክታል።

«ነው?» አለ ከንፈሩን እንደ መንከስ እየቃጣው። ፊቱ ልውጥውጥ አለ። «እንግዲያ እንተያያለን!» አለ፥ እልህ በመጋባት የስንብት ጥያቄ ሐሳቡን ቀይሮ። ቴሌፎኑን አነሳና ደወለ። «ከእናንተ በኩል እንዴት ናችሁ? አዎ አሁን ደረሰኝ። አሁንም የደወልኩት ስለዚህ ነው። ሰዎችህ በሚገባ ተእጋጅተው ይጠብቁ። አዎ! በፍጹም። ከአንገቴ ደርሷል። አልችልም። አዎ! ማታ ዘግየት ብለህ ናና ሁሉንም እንነጋገርበታለን። ሦስት ሰዓት ተኩል ገደማ» አለና ዘጋ።

ማታ ከፓራ ኮማንዶ የደንብ ልብሱ ላይ የሲቪል ካፖርት የለበሰ ሰው ከልጅ ጉግሣ ቤት ድረስ መጣ። «የመርካቶ ነጋዴ አልመሰልኩም?» ሽበት ጣል - ጣል ያደረገበት ፀጉሩ በአጭሩ የተከረከመ፥ ከትከሻው ሰፋ ከወገቡ ሸንቀጥ ያለ ጥሩ ቁመና አለው። የፊቱ መጠውለግና የጡንቻው መጠማዘዝ ችግር ሳይሆን ብዙ ጦር ሜዳ ያየ ጥሩ ወታደር ያስመስለዋል። ማዕርጉ ኰሎኔል ነበር። በር ለመክፈት ከቆየው አሽከር በቀር በቤቱ ውስጥ ሌላ ሰው አልነበረም። እንግዶች በጊዜ ተሸኝተዋል። ሴቶችና ልጆችም ወደየክፍላቸው እንዲሄዱ ተነግሯቸዋል። ሁለቱ ብቻ ተያይዘው ወደ ልጅ ጉግሣ ቢሮ ገቡ። በሩ ተዘጋ። ከትንሽ ጠረጴዛ ላይ ውስኪና አምቦ ውኃ ከብርጭቆ ጋር ተዘጋጅቶ ተቀምቆ ነበር። ልጅ ጉግሣ ኰሎኔል ራሱን እንዲጋብዝ በእጁ አመለከተው።

መረጃዎች ከተለዋወጡ በሁኔታው ላይ ከተወያዩ በኋላ ልጅ ጉግሣ ከስሕፈት ጠረጴዛው ላይ ቁጢጥ ብሎ እንደ ተቀመጠ ማጠቃለያ ሐሳቡን ነገረው። «የምንክበው እየተናደ የምንቋጥረው እየተተረተረ እኛው ራሳችን አብረን በዚህ የብጥብጥ ጎርፍ እስክንወስድ በታጋሽነት ስም ዝም ብለን ማየት አንችልም። አንድ ወጥ የሆነ አመራር የግድ አስፈላጊ ነው። ጠንካራ እርምጃዎች ካልተወሰዱ ተንኮለኞች ከሚፈጥሩት ከሚያባብሱት ከዚህ ወደ ጥፋት ከሚያመራ ትርምስ መውጣት እንደማይቻል ተገንዝቤአለሁ። አስረድቻችሁማልሁ። አሁን እንደማየው የጦር ኃይሉ ፈጽሞ መዋጋት የማይችል ነው። ተከፋፍሏል። ዲስፕሊን የለውም። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ጠላት ብዙ ነው። ታዲያ በዚህ ሁናቴ ጦር ኃይሉ እንዴት ነው

የሚቋቋመው? በፍጹም፡፡ ከዚህስ ቢሆን የትም ቦታ ሥራ አልተሠራም፡፡ ሥራ ማቆም ነው፡፡ ሰልፍ ነው፡፡ ማኅበር እናቋቁም ነው፡፡ አለቃችን ይነሣልን ነው፡፡ የዚህን ሁሉ ብጥብጥ ምንጭ ከሞላ ጐደል እናውቀዋለን፡፡ በጦር ኃይሉ ውስጥ ዋና ነቀርሳ የሆኑት ኮሚቴ የሚባሉት ነገሮች ናቸው፡፡ በእነሱ ምክንያት የትዕዛዝ ተዋረድ ፈጽሞ ቀርቷል፡፡ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችም እንደዚሁ ነው፡፡ የሠራተኛ ማኅበራት እናቋቁም የሚሉት ክፍሎች ደግሞ አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የተንኮልና የብጥብጥ ምድጃዎች መፈራረስ አለባቸው፡፡ ምድጃቸውን ማን እንደሚቆሰቁሰው ደግሞ ማወቅና እጁን መቁረጥ አለብን፡፡ ኮሚኒስቶችም ሥራ ያጡ ተማሪዎችም፥ እነ ጐንጤም ሌሎችም ሌሎችም ሥራ አይፈቱም፡፡ እንግዴህ አስቸኳይ ሥራችን ይህ ነው፡፡»

«መሆንም አለበት» ሲል ኰሎኔል መለሰ፡፡

«ዋናው ጉዳይ እርምጃ ለመውሰድ አለማወላወል ነው፡፡ አሁን ባለንበት ደረጃ፥ ይህ ቢሆን ይሻ ነው ብለን ስለሞራል የምንፈላሰፍ ከሆነ በቃን፡፡ የጐንጤም መንግሥት የወደቀው ሲያወላውልና ይህንንም ያንንም ማባባል ሲሞክር ነው፡፡ እኛ ያንን ስህተት አንደግመውም፡፡ ስለዚህ የምታደርገውን ታውቀዋለህ፡፡»

«ግዴለም፡፡ ለሱ አጨነቅ» አለ ኮሎኔል፡፡

«አውቃለሁ፥ ስለዚህ ኮ ነው የተማመንኩብህ» አለና ልጅ ጉግሣ ግንባሩን እያሻሸ ጥቂት አሰበና «ነገር ግን ዓለም ዘጠኝ ናት እንደሚባለው ከአሥርዋ አንድዋ ብትጐድልብን በአገር ቤት ደህና ከለላ እናገኛለን? እርግጥ አገሬ ነው፡፡ ግን ሰውንም አገሩንም አላውቀውም፡፡ በዝና በስም ብቻ ነው፡፡»

«ግዴለም ለእሱ አታስብ ለወገኑ አጋም አጥር ነው፡፡ እነዳጃዝማች ዘለቀን በዚያ መዓት አምስት ዓመት ሙሉ ጋርዶ ደብቆ የኖረ፡፡ ግዴለህም ቤቴ ነው፡፡ ጓዳህ ነው፡፡» ሲል በሙሉ ልብ ተናገረ፡፡

«የአገሬን ሰው እንግዳ ተቀባይነት አውቀዋለሁ፡፡ ግን አሁን ከማስጠጋት አልፎ የዘመቻ መንቀሳቀሻ መሆን አለበት፡፡»

ኮሎኔል ውስኪውን እየተጐነጨ የማረጋገጥ ፈገግታ አሳየ፡፡

በበነጋው ከአቃቤ ሹም ጀምሮ የቀድሞዎቹ ሹማምንትና ከፍተኛ የጦር መኰንኖች ከየአሉበት እየተለቀሙ ጐፋ ሠፈር ካምፕ ተወሰዱ፡፡ በየሥፍራው የሚፈነዳውን እንቅስቃሴ የሚያዳፍን ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን በዚያ ቀን ተቋቋመ፡፡ አመፁን ተብትቦ ያሥራል ተብሎ የተገመተው አውታር ተዘረጋ፡፡

ነገር ግን የቊጥጥር አውታሩ እሳት እንዳሸተተው የሸረሪት ድር በአጭር ጊዜ ይበጣጠ ገባ፡፡

ማስረሻ የሚገኝበት የልጅ ጉግሣ ኮሚቴም ሳይገነባ መናድ ጀመረ፡፡

፫

ማስረሻ ነገሩ ሁሉ እንዳሰበው አለመሆኑ እየታወቀው የሄደው በአዲሱ አቃቤ ዙም ዘመን ገና የወር ደመወዙን ሳይበላ ነው። ከመጋቢት ወር አጋማሽ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ሲጀምሩ ማታውኑ ሐኪሞቹ ነርሶቹ የወሎ ጠቅላይ ግዛት ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖችና የቅርብ ዕውቂያዎች የታደሙበት የመሰነባበቻና የምሥጋና ግብዣ ዘለቃ በቱሪንግ ሆቴል የምግብ አዳራሽ አዘጋጅታ ውስኪ እንደ ውኃ ሲፈስስ አመሸ። ማስረሻ ከምግብ አዳራሹ አናት ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ የሁሉም ዓይን የሚያርፍበት በመሆኑ የክብር እንግዳ ይመስል ነበር። ዘለቃ ደግሞ ቅርጽዋን የተደፋ የኮካኮላ ጠርሙስ የሚያስመስል የኮክቴል ልብስ ለብሳ ወደ ወጥ ቤቱ እየተመላለሰች ቦዮቹን እየመራች፥ በጠረጴዛው እየተዘዋወረች «ምነው? ተጋበዙ ይላል ኮ ማስረሻ» እያለች ወት ስታወጣ፥ መተጥ ስትቀዳ ስታጫውት ስታቆላምጥ አስተናጋጁን ማሥረሻ አድርጋ ነበር።

ምግቡ እያረካ መጠጡ፥ ከራስ እየወጣ ሲሄድ አብዛኛው ተጋባዥ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በቱሪንግ ሆቴል የደረሰውንና በዚሁም ሳቢያ የተነሣውን ሐሜት ረስቶ እርስ በእርሱ በሐሳቡ አስደናቂ ፍቅራቸውንና ትዳራቸውን መመረቅ ያዘ። የምትገላምጣትና በአሽሙር የምትነካካት የነበረችው ነርስ ስንኳ ብዙም ባልተላመደችው አልኮል ቡዝዝ ያለ ዓይኗን ብልጥጥ አድርጋ የዘለቃን ክንድ ጨምድዳ በመያዝ «አስቀይሜሽ እንደሆነ ይቅርታ አድርጊልኝ ማስረሻ ያለ ምክንያት አላገባሽም። ነፍስ ነሽ። ያዝልቅልሽ!» አለቻት።

ዘለቃ በበኩላ የትንሽ እኅት ማባበያ የመሰለ ፈገግታ እየሳየች፥ «አመሰግናለሁ። በእናንተው እርዳታ ነው የተረፈው» አለች። በአቀራረቧ በቁንጅናዋ የምሽቱ ኮከብ ነበረች። ወንዶች እንደዚች ያለች ሚስት ባገኘን ብለው ቀኑ። ሴቶችም ምነው እንደ እርስዋ በሆንን ብለው ተመኙ። በዚህ ላይ፥ ማስረሻ በአዲሱ አቃቤ ሹም ወደ አዲስ አበባ የመጠራቱ ወሬ ውስጥ ውስጡን ተዛምቶ ስለ ነበር የአድናቆቱ ሹክሹክታ ግብዣቸውን ተጨማሪ ድምቀት ሰጠው።

የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ከማስረሻ አጠገብ ቆሞ አጨበጨበና ጉሮሮውን በድምፁ ጠራርጎ «አሁን ደግሞ አቶ ማስረሻ ለዶክተር ምን ተስኖት አንዲት ትንሽ ስጦታ ያበረክታሉ። መታሰቢያነቱ ግን ለሆስትፒታሉ ሠራተኞች በሙሉ ነው» በማለት የስጦታውን ዕቃ ለማስረሻ አቀረበለት።

ያልተዘጋጁበት ነገር ሆኖ ሰጭም ተቀባይም ላንድ አፍታ ከተደናገሩ በኋል፥ ዶክተር ምን ተስኖት «ያላሰብኩት ነገር ስለሆነ ለመናገር አልተዘጋጀሁም። ከዚህም በቀር እኔ ሰው መቅደድና መስፋት እንጂ መናገር አልችልም። እኔ ተግባሬን ነው ያከናወንኩት። አቶ ማስረሻም እንደሰማነው መልካም ዜና - ከሆነ በተግባራቸው፥ የደሴ ሕዝብ የወሎ ሕዝብ፥ የደረሰበትን ችግር በአጭር ጊዜ እንደሚያቃልሉት ተስፋ እናደርጋለን። ስለ ስጦታው በጣም አመሰግናለሁ» አለ። ተደጋግሞ ተጨበጨበ። ስጦታው ከወርቅ የተሠራ የሸሚዝ እጅጌ መቆለፊያና የከራባራት መያዣ ነበር።

«ምንድን ነው የሠራሽው ዘለቃ?» ሲል ማሰረሻ ጠየቃት ተጋባዦቹን ሸኝተው ከክፍላቸው ገብተው እንዳረፉ። አጠያየቁ የቁጣ ሳይሆን የመገረምም፥ የአድናቆትም ቅልቅል ነበር።

«አንዳንድ ጊዜ ያስፈልጋል። እማማ ባትኖር እኔው ራሴ ራሴን መልስ አልጠራም?» አለች ዘለቃ በቀልድ። ሌሊቱን ከዚያ በፊት አይቶት የማያውቀው የፍቅር ደስታ ስታኰመኵመው አደረች።

የፍቅር ማቆላመጫ ጭውውቷ ከዚያ በፊት ስሙቶ የማያውቀው ረቂቅ ውብ ሙዚቃ ሆነበት። የእጅዋ ዳሰሳ ከንድፍ ጥጥ ለሰለሰበት። አስተያየቷ፥ ፈገግታዋ እንደ ሙሉ ጨረቃ ፈካበት። እንቅልፍ ሳይወስደው ሰመመን ውስጥ ገባ። ካልጋው ሳይነሣ ሰማየ - ሰማያት ወጣ።

ጠዋት እንደዚሁ ለጉዞው ምቾት የተደረገው ዝግጅት ያላሰበው ነበር። ዘለቃ ሰሞኑን እየተዋሰች ስትዘዋወር የነበረችው የደጃዝማች አሊ ዘገዬን ማርቼዲስ ይዛ ማስረሻ ከጉኗ ተቀምጦ በሸዋ በር በኩል ወጥተው የሐረጎን ቁልቁለት ሲያያዙት «እንዴት ነው የሰው መኪና ይዘን የምንሄደው?» ሲል ጠየቃት።

«ምን አለበት? መኪና ማዋስ በእርሳቸው አልተጀመረ። ለዚህ ጊዜ ያልሆነ ዘመድ ለመቸ ሊሆን ነው?» አለች።

«በኋላ እንዴት ትመለሳለች?»

«እሱ የእማማ ፕሮብሌም ነው።»

«ምን ማለትሽ ነው? እሳቸው እየነዱ ሲመለሱልሽ ኖሯል? ጥሩ አልሠራሽም» በቀልድ ፊቱን ኮስተር አድርጎ ተመለከታት።

በአንድ እጅዋ መሪውን እንደ ያዘች በአንድ እጅዋ መዳፍ ጭኑን ጠብ ጠብ እያደረገች «ግዴለህም አታስብ። እኔ ልጠይቃቸ ነው እኔ አዲስ አበባ መምጣቴ አይቀርምና አውቶሞቢሏን ይዛችሁ ሂዱ፤ እኔ በዚህ በላንድሮቨሯ እመጣለሁ ያሉት። ኮሚቴው ከተለወጠ መሻሬ አይቀርም ብለው ሰግተዋል መሰለኝ። ግዴለህም ያንተንም ወሬ ሳይሰሙ አልቀሩም። ከመኪናዋ ኋላ ውስኪም አምቦ ውኃም ቢራም፥ የአገልግል እንጀራም አብሮ ነው የተላከው። የእማማ ዘመድ ቢሆኑም እስከዚህ አይጨነቁላትም ነበር። ሹመትም ከዝምድና የሚበልጥበት ጊዜ አለ ማለት ነው» አለችና ከፈገግታ ጋር የጐሪጥ አየችው። ማሰረሻ ኰራት ቢጤ ተሰማው። «ኰራት ኰራት አይልሽም ወይ?» እየተባለ የተዘፈነላት የእርስዋን የመኳንንት ዘመዶች ስም በመዘርዘር ነበር። የሠርጓ ዕለት። አሁን ደግሞ «ኰራት ኰራት አይሽልም ወይ፥ የማስረሻ አይደለሽም ወይ?» መባሉ ነው የሚሉ ሐሳቡ መጣበት።

በአውቶሞቢሉ የካሴት ሙዚቃ ማጫወቻ አንድ ጊዜ የካሣን ክራር ሌላ ጊዜ የባሕሩን ማሲንቆ እነጥላሁንን፣ እነማሕሙድን፥ እነአያሌውን፥ እያዘፈኑ ሲያሰኛቸው ፈረንጂኛ እየለዋወጡ ቢ. ቢ. ቢ. ቮይስ ኦፍ አሜሪካ ራዲዮ እየከፈቱ ሲደክማቸው አቋመው ወርደው ቢራ በመጠጣት ውስኪ በመጐንጨት እየተዝናኑ በማርቸዲስ ወደ አዲስ አበባ ሲፈስሱ ማስረሻ እንደ ሌሊቱ ሁሉ ሌላ ዓለም ውስጥ ገብቶ ዋለ።

የማትነቀንቀው የማትጐረብጠ ማርቸዲስ እንደ ቋያ እሳት መንገዱን ስትበላው የኮምቦልቻ የሮንቲኒና የጨፋ፥ የእለዲ፥ የአልቡሶ፥ የከሚሲ፥ የሮቢ፥ ከተሞች ከወደኋልቸው ቀሩ። ከፊት ለፊታቸው የሚንጣለለው ሜዳው ሸንተረሩ ዳገቱ ዛፉ፥ ሣሩ፥ እንደ መጋረጃ ወደ ኋላቸው እየታጠፈ ሲሄድ ማስረሻ መንገዱን አይሳት እንጂ በሐሳቡ የሚታየው ሌላ ሌላ ትርኢት ነበር። አንድ ጊዜ ከሹም ጓንጉል ጋር የሚያደርገው የሥራ ርክክብ ይታየዋል። ሹም ጓንጉል ከቢሮው በራፍ ላይ ይቀበለውና እየመራ አስገብቶት ከወንበሩ ላይ እንዲቀመጥ ይጋብዘዋል። ሹም ጓንጉል በበኩሉ አንድ ጊዜ ማስረሻ ስራስ ሹክክ ብሎ ይቀመጥበት ከነበረው ከጠረጴዛው ፊት ከሚገኘው የእንግዳ ወንበር ላይ ይቀመጣል። ሹም ጓንጉል የሚናገረው ጠፍቶት መዳፉን እያፋተገ ሲያቅማማ፥ ማስረሻ «ምንም አይደለም። የዓለም ነገር እንደዚህ ነው። እኔ መቼም ስለ ስራው በየጊዜው ምክር እንደሚሰጡኝ ተስፋ አደርጋለሁ» ሲል ያጽናናዋል።

የሐሳቡ ትርኢት ወዲያው ይለወጣል፡፡….የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞቹ ገንዘብ አዋጥተው የመቀበያና የመሸኛ ግብዣ ያደርጋሉ፡፡ በግብዣው ላይ አንዱ በሥራ ጓደኞቹ ስም ስለ ማስረሻ ችሎታ፥ ታታሪነት፥ ከሰው ጋር ስላለው መግባባት በመዘርዘር ምስጋናውን ያኸርጉደጉደዋል፡፡ እርሱም በበኩሉ ትሕትና የተሞላበት መልስ ይሰጣል፡፡ ጭብጨባው የንጉዳል፡፡ ጓንጉል ግን ለስሙ ያህል ይገኝ እንጂ እስከነመኖሩም ይረሳል፡፡

ሌላ የሐሳብ መጋረጃ ይገለጣል፡፡….በአዲሱ አቃቤ ሹም ሊቀ መንበርነት የሚመራው የሹማምንት ኮሚቴ ጉባዔ አጀንዳ - አገሪቷን የገጠሟትን ችግሮች እንዴት ነው የምንፈታው? አንዳንዱ ሹም የመሰለውን ሐሳብ ይሰነዝራል፡፡ ማስረሻ ተራው ሲደርስ ሁናቴውን በልዩ ልዩ አግጣጫ በማሳየት ነገሮችን በማያያዝና በማቀነባበር ረጋ ባለ አንደበት አስተያየቱን ያቀርባል፡፡ ጸጥ ብለው ያዳምጡታል፡፡ ሲጨርስ ልጅ ጉግሣ «በጣም ግሩም ሐሳብ ነው እንዳንተ ያሉ አዋቂዎች በመካከላችን እስካሉ ድረስ ችግራችን ሁሉ ቀላል እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ« ሲል ያደንቀዋል፡፡

ቦታ ለመቀያየር ወይም ለማረፍ በቆሙ ቍጥር የሚጉነጨት ውስኪ ወደ ጭንቅላቱ እየወጣ ሲሄድ የሐሳቡ ትርኢት ይበልጥ እየተዘበራረቀና እያሸበረቀ ሄደ፡፡ በደሴና በአዲስ አበባ መካከል እንዳለው ርቀት ማስረሻ፥ ከአካባቢው እውነታ ራቀ፤ መጠቀ፡፡ ሌላው ቀርቶ የቆሬን መንደር ስያልፍ እንኳ ሙሔ የፃፈለት ደብዳቤ ትዝ አላለውም፡፡

ደብረ ሲናን አልፈው የጣርማ በርን ዳገት ሲያያዙት ከሞቅታቸው የተነሣ ሁለቱም ከቴፑ ጋር መዝፈን ጀምረው ነበር፡፡ «ውይ! ማስረሻዬ» ስትል በውሸት ፍርሃት ተጠግታው እንደ መተቃቀፍ ብለው ዋሻውን ወጡና ከደጋው አናት ላይ ሲዘልቁ ያ የታወቀው የተጉለት ቆፈን ተቀበላቸው፡፡ ድንገት ማቀዝቀዣ ውስጥ እንደ ተከተቱ ያህል አጥንት ሰርስሮ የሚገባ ውርጭ….በአልኮል ምድጃ ከውስጥ ሰውነታቸው የሚፈላው ሙቀት በውጭ ከሚገርፋቸው ብርድ ጋር ሲጋጭ አንድ ልዩ ዓይነት ስሜት ሰጣቸው፡፡ የሚያንከተክትም የሚያቅበጠብጥም፡፡….

ጥቂት እንደ ተጓዙ ከሰላ ድንጋይ አለፍ ብለው አመቺ ቦታ መረጡና መኪናዋን ከወደ ዳር አቁመው፥ ሹራብና ኮት ደርበው ወጡ፡፡ ከዚያም የመኪናዋን ፓራውልት ተደግፈው የቀረውን ውስኪ እየተጉነጩ አካባቢውን ቃኙት፡፡ ከምሥራቅ በኩል አዘቅዝቆ የይፋት፥ ሸንተረር እንደ ሕልም አገር ጭጋግ ለብሶ በሩቅ ይታያል፡፡ ከእርሱ በስተደቡብ ሲል በምኒልክ መስኮት በኩል ተደርምሶ የገባ በሚመስለው ገደል ባሻገር ተጉለት ቆላው አገር ባሕር መስሎ ዓይንን ያጥበረብራል፡፡ በሰሜን አልፎ አልፎ በጉብታና በባሕር ዛፍ ከመደናቀፉ በቀር ለጥ ያለው መሐል ሜዳ ተንጣልሏል፡፡ በምዕራብ የተጉለትና ቡልጋ ደጋ አገር ደረቱኡን የገለበጠ መስሎ ተዘርግቷል፡፡ የማታ ጀንበር በጭጋግ ተጋርዳ ግራጫ መስላለች፡፡ አልፎ አልፎ ከሚታየው የበልግ ቡቃያ በስተቀር መሬቱንም ግራጫ መልክ ሰጥታዋለች፡፡ ባሻገር - በዝንጀሮ ወንዝ ገደል አፋፍ ላይ - የዝንጀሮ መንጋ ይንጎማለላል፡፡ ከቋጥኝ ቋጥኝ ይዘላል፡፡ ክምችት ብሎ በመቀመጥ በትዝብት ዙሪያውን ይመለከታል፡፡ በደበሎና በባና የተሸፈኑ እረኞች በየዳገቱና በየቋጥኙ ጥግ ጉች ጉች ብለዋል፡፡ ተኰማትረው - ጉቶ መስለው፡፡

«ታውቂያለሽ?» አለ ማስረሻ በተሳሰረ አንደበት የተጨለጠውን የውስኪ ጠርሙስ በቁልቁለት እየወረወረ ፣«ይህ ምድር መስሎ አይታየኝም፡፡ ከከፍታው የተነሣ አንጉሌ አየር ስላነሰው ሊሆን ይችላል - ብቻ በምድርና በሰማይ መካከል የተንሳፈፍኩ ይመስለኛል፡፡ ልክ እንደ ሕልም አለም እያስደሰተኝ የማየው እውነት እየመሰለኝ እወደዋለሁ፥ እፈራዋለሁ፡፡ ይገባሻል? አዞረኝ!» እየተንገዳገደ በመሪው በኩል የመኪናውን በር ከፈተ፡

«ተው እኔ ልንዳ» አለችው ዘለቃ።

«ምክንያት?»

«ይደክምሃል።»

«በጨዋ አነጋገር ሰክረሃል ማለትሽ ነው? አብረን ነው የጠጣነው አንቺ የአህያ ውኃ ጠጭ የሆንሽ እንደሆነ። ከዚህም በቀር፥ ተሽክመው ቢያስገቡሽ ስንኳ መኪናዬን ጭረት እንደማላስነካት ታውቂያለሽ። በእንቅልፍ ልባቸው መኪና መንዳት ከሚችሉት አንዱ ሳልሆን እቀራለሁ?» ሲል ሳቀ።

ጥቂት እንደ ተጓዙ በጋ ከክረምት የማይለየው የቡልጋ ጉም አገር ምድሩን እየሸፈነው መጣ። ሜዳውን ዳገቱን ሁሉ እንደ ንድፍ ጥጥ አለበሰው። መብራቱ አብርቶ ስንኳ ከጥቂት ሜትሮች ርቀት በላይ ማየት አይቻልም። በአልኮል ፈረስ የሚጋልበው ማስረሻ ግን ፍጥነቱን እስከዚህም አልቀነሰም ነበር።

ከአንድ መጠምዘዣ መንገድ ላይ መሪውን ወደ ግራው ሲጠመጥምና ከአሥር ሜትር ባልበለጠ ርቀት አንድ ሌዎንችን ከፊት ለፊቱ ሲመጣበት አንድ ሆነ። በአለ በሌለ ኃይሉ መሪውን ወደ ቀኝ ሲዘውረው አውቶሞቢሏ፥ ከአንድ ነገር ጋር ጓ ብላ ወደ ላይ ነጠረች። ወዲያው ከሰማይ ምድሩ ተገለባበጠባቸው። ከድንገተኛነቱም ከመጠጡም የተነሣ ምን እንደደረሰ በትክክል አላወቁም። የሚታወቃቸው ከእርስ በርሳቸው ላይ መገለባበጣቸው ከወዲያ ወዲህ ከሆነ ነገር ጋር መላተማቸው ብቻ ነው። ዘለቃ ስትጮህ ማስረሻ እንደ ሕልም በሩቅ ተሰምቶታል። ለሁለቱ ዕድሜ ልክ ከመሰለ አንዳፍታ በኋላ የሚያናውጥ ግጭትና ጓ! የሚል ከፍተኛ ድምፅ ተሰምቶ እንቅስቃሴው ቀጥ አለ። ከመኪናው የውስጥ ጣሪያ ላይ ወድቀው ራሳቸውን አገኙት። ተቀምጠውበት የነበረው ወንበር ከላያቸው ላይ ተንጠልጥሏል።

«ደህና ነሽ?» ሲል ጠየቃት።

«እኔ እንጃ!» አለች።

እረኞችና መንገደኞች ወዲያው ደረሱላቸውና ከፍተው አስወጡአቸው። ዓይናቸውን ማመን አቅቷቸው ዙሪያውን ተመለከቱ። መኪናዋ ከመጠምዘዣው ላይ ከአንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ ወጥታ ከተገለበጠችና አንድ ሃያ ሜትር ከተንከባለለች በኋላ አንድ ዛፍ ተደግፋ በአናቷ ቆማለች። ዛፉን ግማሽ ሜትር ብትስት ኖሮ ወንዝ ገብታ መከስከስዋ የማይቀር ነበር።

-ተአምር ነው።

-ወይ ትረፍ ያለው ሕይወት - አሉ ሰዎች ሁሉ። ከጥቃቅን ጭረት በቀር ሁለቱም ጉዳት አልደረሰባቸውም ነበር።፡

ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ ባለ መኪና ከቤታቸው አደረሳቸው። ይደነግጣሉ በማለት ስለ አደጋው ሳያነሡ መድረሳቸውን ብቻ ለወይዘሮ ዘርፈሽዋል በቴሌፎን አስታውቀው ጥቂት እንደ ቆዩ ዘለቃ ወገቤን ከረታተፈኝ ቆረጠኝ አቃጠለኝ ብላ ታቃስት ገባች። ወዲያው ደም ይፈሳት ጀመር። ጋንዲ ሆስፒታል ወሰዳት።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ነርሷ ከሕክምና ክፍሉ ወጥታ ዘለቃ «ተጠርጋ» አሁን ደህና መሆኗን ጉልት ቀን ግን መተኛት እንደሚያስፈልጋት ነገረችው።

«ምኑ ነው የሚጠረገው?» ሲል ጠየቀ ግራ ገብቶት።

«ፅንሱ ወጥቷል ማለት ነው።»

ሞቅታው አሁን የበረደለት ይሁን እንጂ በመርዶው ድንጋጤም ሆነ ኀዘን አልተሰማውም። ምንም ነገር አልተሰማውም። ዘለቃ በበኩሏ ወደ ምኝጣ ክፍል ለመዛወር በተሽከርካሪው ቃሬዛ ላይ ተጋድማ ስትወጣ ኮሶ እነ ሻረ ሰው ፍቷ ፈገግታ ይታይበት ነበር።

ተጠርጎ ስለ ወጣው ልጃቸው አንድም ጊዜ አንሥተው አልተነጋገሩበትም። የሁለቱም ሐሳብ ያተኮረው ስለ ራሳቸው የወደፊት ሕይወት ነበር። ግን የራሳቸውም ሕይወት እንዳሰቡት አልሆነም። ማስረሻ ከደሴ ሲመጣ ሁኔታውን ካለመው ፈጽሞ የተለየ ሆኖ አገኘው።

## ፫

ማስረሻ አስቀድሞ ከልዩ ጸሐፊው ቀጠሮ ተብሎት ከልጅ ጉግሣ ጋር ሲገናኝ የተደረገለት አቀባበል በጣም የቀዘቀዘ ነበር። ልጅ ጉግሣ የታከተውና የሰለቸው በሚመስል እንቅስቃሴ ከወንበሩ ተነሥቶ የእጅ ሰላምታ ከሰጠው በኋላ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ልዕልት መጀመሪያ እንዳደረጉት ከእግር እስከ ራሱ ገመገመው። በአካለ ገጽታ ከሆነ ሚዛን የሚያነሣ መሆኑን ያውቀዋል። በተለይ ከልጅ ጉግሣ ጋር ሲነፃፀር። ስድስት ጫማ የሚሆነው የልጅ ጉግሣ ረጅም ቁመትና ከላይ እስከ ታች ሙሉና እንደ ናሙና ተስተካክሎ የተቀረፀ ነው። ትከሻው ታች ደረቱ ደልዳላ ሆዱ ስብስብ ያለ ነው። መልከ - መልካም ፊት በጥንቃቄ ተይዞ ያወለወለ ነው። ጸጉሩን በጣም አሳጥሮ እየተከረከመው ከበድ ብሎ የሚታየው ጭንቅላቱ ሴታ - ሴት ከመምሰል አድኖታል። አለባበሱ እንደዚሁ ሌላ ነገር ነው። እንግሊዝ አገር ካለው ደንበኛው የሚመጡ ናቸው። የሚባሉት ልብሶች ከከራባት መያዣው እስከ እግር ሹራቡ ድረስ አንዱም ሳይቀር እንደ ሞዴል በየቀኑ ተስተካክለው መቀናጀት አለባቸው። ከቁመናው ጋር አብሮ የሚሄደው ድምፁ ብቻ ነበር። ትንሽ ቀጠን ይላል።

«ከአሁን ቀደም የተገናኘን አይመስለኝም» ሲል ልጅ ጉግሣ በብዕሩ ጠረጴዛውን እየቆረቆረ ንግግሩን ጀመረ። «ግን ሰዎች ስለ አንተ ችሎታና ታታሪነት ነግረውኛል» ድምፁ የማድነቅ ቃና አልነበረበትም። ለመደለል ሲባል በተለምዶ የሚነገር የሰለቸ ቃል መሆኑ ያስታውቅበት ነበር። የማኅበራዊ ሥራ ባለሙያ የሆነው ማሰሻ ይህንን ለመገንዘብ አላቃተውም።

«ልዕልት፥ ወይም ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንደ ነገሩኡኝ ብትል አይሻልም?» ሲል ማስረሻ በሆዱ አሰበና የግንኙነታቸውን ርቀት ለማቀራረብ ያህል «ምናልባት እርስዎ አያስታውሱኝም ይሆናል እንጂ፥ እንግሊዝ አገር አምባሳደር በነበሩበት ጊዜኤ እኔ ለማስትሬት ትምህርቴን ስከታተል ኤምባሲ እየመጣሁ ብዙ ጊዜ ረድተውኛል» አለ።

«አዎ! ብዙዎቹ ነበሩ እየመጡ ዕርዳታ የሚጠይቁን» አለ ልጅ ጉግሣ። ይህንን ሲናገር ሐሳቡ ሌላ አጣዳፊ ጉዳይ ዘንድ መሆኑ በግልጽ ያስታውቅ ነበር። መሰላቸቱን የዲፕሎማቲሲ ልማዱ ስንኳ ሊሸፍንለት አልቻለም። «እና፥ መልካም ነው። በዚህ የፈተና ወቅት በችሎታህ በሙያህ እንድትረዳኝ ነው የፈለግሁት። ምናልባት ሰምተህ ይሆናል፥ መሠሪያ ቤታችሁ ባዶ ነው። ባለ ሥልጣን የለበትም። ሹሙ

ያው ከኮሚቴው ጋር ከሥራው ተሰናብቷል። ምክትል ሹሑንም የጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ማድረግ ተገድጃለሁ።»

የሹመቱን ፍሬ ነገር ለመስማት ማስረሻ ጆሮውን አቆበቆበ።

«ለጊዜው የምፈልገው የምክትል ሹሙን ቦታ እንድትይዝልኝ ነው - ለጊዜው።»

«ምክንያቱም» ሲል ልጅ ጉግሣ አሁንም ጠረጴዛውን በብዕሩ እየቆረቆረ ወደ ሌላ ሐሳብ የተወሰደ መስሎ ንግግሩን ቀጠለ። «ምክንያቱም አሁን ሁሉም ከፍተኛ ነገር የተነሣበት የድርቁን ጉዳይ ነው። ግልጽ ሳድርገውና በተሰናበተው ኮሚቴ ላይ አሁንም የሚሰነዘረው ከፍተኛ ክስ ሕዝብ ዝም ብለው አስጨረሱ የሚል ነው። አንተ ቀደም በለህ ጉዳዩን ሰለምታውቀው የሚያዋጣ መፍትሔ እንደምትሰጠው እተማመናለሁ። ከውጭ በመምጣት ላይ ያለ ዕርዳታ አለ። በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል እንደ አቅማችን አስፈላጊው በጀት ይመደባል።

አሁን የእናንተ ዋና ተግባር ዕቅድህን አውጥተህ ለማወቅ ያህል እቅዱን እንዳየው እፈልጋለሁ። ምክንያቱም ነገ እጠየቅበታለሁና። ከዚያ በኋላ በተቻለ ፍጥነት በሥራ ላይ ማዋል ነው። እንደኔ ግምት ግን ብዙ የውጭ ዕርዳታ በየዓይነቱ እየጐረፈ ስለሆነ ዋናው ተግባር እሱን ማቀነባበር ይመስለኛል።»

በመሥሪያ ቤቱ ያጋጠመው ሁናቴውም በጉዞ፥ ላይ ሆኖ እንዳለውመው አልሆነለትም። ጓንጉል ሊያረካክበው በሥፍራው አልተገኘም። ፋይሉም የቢሮ ዕቃውንም ቀደም ሲል ለመሥሪያ ቤቱ የንብረት ኃላፊ አስረክቦ ቀርቷል። ምክትል ሹም የነበረው አዲሱን ሥራውን ለመጀመር ወደ ጠቅላይ ግዛት ሄዶአል። ስንኳን በሰልፍ ወጥቶ መቀበል ቀርቶ ሥራዬ ብላ «እንኳን ደህና መጣህ!» ያለችው የቀድሞ ጸሐፊው ብቻ ነበረች። ያውም ከቀድሞ ቢሮው ውስጥ መግባት ስለ ነበረበት እንደ ግዳጅ ዓይነት ፈራ ተባ እያለች።

-ሹመቱ እንደ ሌሎቹ በጋዜጣ ስላልወጣ ወይም ደብዳቤው ስላልደረሰ ባይሰሙ ይሆናል - ሲል ራሱን አባበለ። ወሬው ግን ተሰምቶ ነበር። የልጅ ጉግሣ ልዩ ረዳት ለመሥሪያ ቤቱ ሹም ልዩ ጸሐፊ ቴሌፎን ደውሎ ማዘዣው ተጽፎ እስኪላክ ስራውን መጀመር እንዲችል አስፈላጊውን መመሪያ ሰጥቶ ነበር። ልዩ ጸሐፊውም በተሰጠው መመሪያ መሠረት የምክትል ሹሙን ቢሮ አዘጋጅቶ ጠብቋል።

ማስረሻ ቢሮው መግባቱን እንደ ሰማ ልዩ ጸሐፊው የተቻኰለ በሚመስል አረማመድ መጥቶ «እንዴ! አቶ ማስረሻ እንግዲህ እኮ ይህ ቢሮዎ አይደለም። ሌላ ቢሮ ተዘጋጅቶልዎታል።» አለው የሽሙጥ አይሉት የሳቅ ከንፈሩን ወደ ጎን ጠመም አድርጎ ጥርሱን እያሳየ።

«የሚያስፈልገግ ሌላም ነገር ካለ ታዛዥ ነኝ» አለው ጸሐፊው አዲሱን ቢሮ ከፍቶ ከአስገባው በኋላ። «አመሰግናለሁ፥ ለቦታው አዲስ በመሆኔ ዕርዳታ ሳያስፈልገኝ አይቀርም። ለማንኛውም የሚያስፈልገኝ ነገር ሲኖር አስታውቅሃለሁ» አለ ማስረሻ ከኋላ የገፉት ይመስል ወደ ፊት ደፋ ደፋ በማለት ወደ ተሰናዳለት መቀመጫ እያመራ።

ማስረሻ በዚያ ሰፊ ክፍል ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ በሐሳብ ሲተክዝ ከጥቂት ቀናት በፊት የነበረው የተስፋ ስሜቱ ሁሉ ፀሐይ እንደ ነካው ቅቤ እየቀለጠ ሄደበት። ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ዘለቃ የነገሩት ሁሉም ነገር እንዳማረ፥ እንደ ሠመረ፥ አዲስ ብሩህ ዘመን እንደ መጣለት አድርገው ነበር።

የልጅ ጉግሣ አቀባበል ሲገርመው የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ሁናቴ ደግሞ የባሰ ሆነበትና አንጐሉን በጠበጠው።

እስከዚህ የተጠላሁ ነበርኩ እንዴ? ወይስ ሠርግ ሳልጠራኋቸው ሁሉ ተቀይመውኝ ነው» ማንም ቢሆን ለሠርጉ የአንድ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ በሙሉ ሊጠራ አይችልም። አምስት ስድስት መቶ ሠራተኛ እንኳን እኔ ራሶችም አይችሉት። እኔ ደግሞ ከነአካቴው ያልጠራሁበት ምክንያት አለኝ። ቢሆንስ ከሥራዬ ግር ምን አገናኘው? - እያለ ራሱን በጥያቄ አስጨነቀው። ግን መልስ አላገኘም።

ቀኑን ሙሉ የእርሱን ውሳኔ አስተያእይት ወይም ፊርማ የሚጠይቅ አንዳችም ፋይል ሳይቀርብለት ዋለ። ሁለት ዝቅተኛ ሠራተኞች ብቻ ባለፈው ሹምና በእሱ ባለሟሎች የተበደሉ መሆናቸውን በመግለጽ የአቤቱታ ደብዳቤ ይዘው ቀረቡ። እዚያው ሊወስነው የማይችል ስለሆነ አስቀመጠው። እንደዚሁም ሠራተኛ እምብዛም የማይወዳቸው ሁለት የይክፍል ኃላፊዎች ሹልክ እያሉ መጥተው ግንባራቸው አስወጉ። ወደ ቢሮ ሲገባና ሲወጣ ስንኳ በፊት እንደ ጓደኛ ይቆጥራቸው የነበሩት ሆን ብለው የሚሸሹት መሰለው። እንዳላዩ ፊታቸውን ዘወር አርገው ያልፋሉ። ቢሮአቸው ድረስ ሄዶ እንዳያነጋግራቸው ይሉኝታ አሸነፈው።

ማሰሻ ለጊዜው ያላወቀው፥ ግን በመሥሪኢያ ቤቱ ውስጥ አንድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚሄድ መሆኑን ነው። እንደ ቴሌ፥ መብራት ኃይል፣ የውኃና ፍሳሽ የመሳሰሉት መንግሥታዊ ድርጅት ሠራተኞች ትንቅንቅ እንደ ገጠሙበት ሁሉ፥ የኢትዮጵያ መንግሥት ሠራተኞች - ማለት የመንግሥት ሠራተኛ ማስተዳደሪያ ደንብ የሚመለከታቸው - አጠቃላይ ማኅበር ለማቋቋም ሙከራ ተቃጥቶ ነበር። የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ተረቅቆ በየመሥሪያ ቤቱ ተሰራጭቷል። የጊዜያዊ ኮሚቴ መሪዎች ከጥቂት ወራት በፊት በማስረሻ መሥሪያ ቤት እንደ ረዳት ከማኅበራዊ ኑሮ ሠራተኞች የተቀጠሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ናቸው።

ልጅ ጉግሣ በየሥፍራው እየፈነዳ ያስቸገረውን እሳት ለማጥፋት ባስወሰደው እርምጃ ሰሞኑን ሦስቱ ታሥረዋል። አንድ ሁለት አምልጠው በልጅ ጉግሣ ኮሚቴ ላይ ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ በማካሄድ ላይ ናቸው። አብዛኛው ሠራተኛ ተንዷል። በሽቋል። ተበሳጭቷል። በየክፍሉ በየኮሪደሩ በየጓሮው፥ ሴራው ይጐነጐናል። ዓመፅ የጠነሰሳል። ማስረሻን ዓይነ - ምድር እንደ ነካው ጨርቅ የሸሹት ፊታቸውን ያዞሩበት በግል ሰውነቱ ሳይሆን የልጅ ጉግሣ ቡድን አባሪ ተባባሪ በመሆኑ ብቻ ነው። በዚህ ላይ የመኳንንቱ ቤተሰብ ጋብቻውንም ወሬ ተዛምቶ ስለ ነበር ከመሳንፍቱ ቡድን ጋር ያለውን ቁርኝነት አጠናከረበት። ስለዚህ ግላዊ እሱናቱን ከሥልጣኑ፥ የትናንቱን ማስረሻ ከዛሬው በአካል ለይተው መቀበል ስላልቻሉ ጓደኞቹ ሳይቀር ራቁት።

ማስረሻ ሁለቱን ቀን ቢሮውን ዘግቶ ስለ ወሎ ድርቅ የተቀነባበረውን ፋይል በማጥናናትና ለፕዘው ስለሚያስፈልገው ዝግጅት መመሪያ በመስጠት ብስጭቱንና ባይተዋርነቱን ከሞላ ጐደል ዋጠው። በምሳ ሰዓትና ማታ የተወዘፈውን ለመጨረስና በየመስኮቱ የሚያጨልጉበትን ሠራተኝኖች ለማሳየት ክንድ የሚዘነጥል መዓት ሰነድ እየያዘ ወደ ቤቱ ይሄዳል።

በመሥሪያ ቤቶች መካከል ከተደረገው ደብዳቤ ልውውጥ በስተቀር፥ ከጠቅላይ ግዛት መሥሪያ ቤቶች የቀረቡት አብዛኞቹ ደብዳቤዎች የግብር ምሕረት እንዲደረግ የሚጠይቁ ነበር። ስለ ችግሩ ከልዩ ልዩ ክፍሎች የቀረቡት የጥናት መዝገቦች በእርግጥ ውስብስብና ጭንቅላት የሚወጥሩ ነበር። ስለሚያስፈልገው እህል ብዛት ከአንድ አጥኚ ክፍል፥ ጉዳት ስለ ደረሰባቸው ሕፃናትና ስለ አያያዛቸው

ከሌላ፥ ስለ መጓጓዝ ከሦስተኛ ስለ ውጭ ዕርዳታና ስለ ሀገር ውስጥ መዋጮ ስለ ጸጥታ ስለ ጐተራ ስለ መጠለያ ጥበት፥ ስለ ከብት እልቂት መልሶ ስለ ማቋቋም ስለ መማሪያ ደብተርና እርሳስ ሁሉም በየበኩሉ ወፍራም ወፍራም ጥራዝ አቅርቧል።

ዝርዝሩ ለጊዜው ማቀነባበር የማይቻል ውስብስብ ቢሆንበትም በጠቅላይ ግዛቱ የችግረኛው ሕዝብ ብዛት ከሰባት መቶ ሽህ መብለጡን እንደ ዋና ነጥብ ያዘ። ለዚሁ አርባ ሁለት ሽህ ኩንታል እህል ያስፈልጋል። አሥራ ሰባት የእህል ማደያ ጣቢያዎችና ሃያ መጠለያዎች መቋቋማቸውና ከክኒን አንሥቶ እስከ ጥሬ ገንዘብ ድረስ ከውጭ አገሮች የቀረበው ዕርዳታ ተዘርዝሯል። ማስረሻ ከዚህ ሁሉ የሚፈልገውን ጨምቆ አውትጦ በማስታወሻ በመያዝ፥ ስለሚያከናውነው ተግባር በልዩ ጸሐፊው በኩል ሪፖርቱን ለልጅ ጉግሣ አቅርቦ ወደ ስሜን ጐዞው ተነሣ።

ጐዞው ለሥራ ይሁን እንጂ የተጣደፈው በራሱ ምክንያት ነበር። ሲወጣ ሲገባ የሠራተኛው ሁሉ ዓይን የሚገርፈው በሚመስልበት መሥሪያ ቤት መቆየት ክፉኛ አስጠላው። በቤትም ቢሆን ከወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ከዘለቃ ጋር የሚያደርገው ጭውውት ወደ ንትርክ እየተለወጠ መሄድ ይዞአል። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ለሹመት ያበቁት እርሳቸው መሆናቸውን በነገር ዳር - ዳርታ እያስገነዘቡ ሥራውን እንዴት እንደሚያካሂድ ዘወትር መመሪያ ሊሰጡት ይፈልጋሉ።

ዘለቃ ስለ ተገለጠችው መኪና ማሠሪያ ገንዘብ በመጨቅጨቅ ገና የወር ደሞዙን ሳይቀበል ተበድሮ እንዲከፍል ጠይቃዋለች።

ከዚህ ሁሉ ለመሸሽ ነበር።

ግን ደብረ ብርሃንን እንዳለፈ ሌላ ሰቀቀን ከፊት ለፊቱ ተጋረጠበት።

## ፬

ማሳረሻ፥ በእርሱ ላይ ባንዳ አግብታ እንደ ኰበለለችው የቀድሞ ሚስቱ ልጅ ሳይሆን እንደ ወላጅ አባት ሳይተርፈው የጥቅምት ጥብቆ ይገዛላት የነበረው ሙሔ በነፍሴ ድረስልኝ ብሎ የጻፈለት ዳብዳቤ አልፎ - አልፎ በአጋጣሚ ትዝ ሲለው ሕሊናው መቧጠጡ አልቀረም። ግን፥ ጊዜ ያለፈ የጎዘንና የሰቀቀን ቍስል ያሽራል እንደሚባለ እያደር የሚያስታውስበት ጊዜ እየረዘመ ሄዶ ነበር። አሁንም ለጐዞ ሲነሣ የሙሔ ዕድል አውሶት ነበር። ግን የሞት መኖር የሚያስጨንቀው በጠና ታሞ ከጣዕር ጋር ሲፋጠጡ ነውና፥ የዕዳም ነገር የቀጠሮው ቀን እስኪደርስ ከብዶ አይሰማምና የመንገዱ ርቀት ማስረሻንም ስለ ሙሔ ከሚሰማው ጭንቀት አዘነጋው።

ሰውነቱ መሸማቀቅ የጀመረው የቦርከናን ወንዝ ሲሻገር ነበር። ወሎ ግዛት ውስጥ መግባቱ አየር እንደ ሌለው ክፍል አስጨነቀው።

ከብዙ ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ደህና የጣለው የበልግ ዝናም መሬቱን ከሞላ ጐደል አረንጓዴ መልክ ሰጥቶታል። ሣሩ ለምልሟል። ዛፎች ቅጠል አቆጥቁጠዋል። ከበልግ የተረፉ ቁርጥራጭ ደመናዎች በሰማያዊ ሰማይ ላይ ተንጠባጥበዋል። ማስረሻ ግን ይህ የተፈጥሮ ውብ ገጽታ የሚያስደስት ሳይሆን የሚያስፈራ ጭንቅ ትርኢት ሆነበት። በዚህ መካከል ለማየት የሚፈራው ነገር ነበር - የሙሔ ዓይን። በተሁለደሬ ባላባት በወይዘሮ ምንትዋብ ግቢ በእሱ ሠርግ ቀን፥ ከዚያ መዓት ረሃብተኛ ጋር ተሰልፎ ሲለምን ያየውን የዚያን አንድ ጊዜ አፍቃሪ አባት የነበረ አሳዛኝ መልክ።

እንዳለፈው ጊዜ አሁን በመንገድ ላይ ብዙ ችግረኛ ተኰልኵሎ አይታይም። ያለቀው አልቆ የተረፈው ተበትኗል። አሁን ሦስትም አራትም እየሆኑ አንዳንድ ጊዜም በርከት ብለው በአውራ ጐዳናው ላይ ሲጓዙ የሚታዩት ከዘመድ ጋር ተጠግተው ከርመው ወይም በመጠለያ ቆይተው ወደ ቀድሞው መንደራቸው የሚመለሱና ዕርዳታ ጥየቃ ወደ እህል ማደያዎች ጣቢያ የሚሄዱ ናቸው። መኪና ሲመጣ፥ ያንን ጭራሮ የሆነ አካላታቸውን ነፋስ እንዳይጥለው የሰጉ ይመስል በበትራቸው ያስደግፉና ከአውራ ጐዳናው ዳር ቆመው እስኪያልፍ ያስተውሉታል። ትዝብታቸው አጥንት ሰርስሮ ይገባል። እነርሱ ከመቃብር ወጥትተው ሥጋ የለበሰ ጭራቅ ድንገት እንዳዩ ያህል በመገረም። በዚህ ጊዜ ማስረሻ ከመኪናው ውስጥ ይኰማተራል። የሁሉም ዓይን - የሙሔ ዓይን - የሙሔ ዓይን - የሁሉም ትዝብት - የሙሔ ትዝብት እየመሰለው ድድቅ ጨለማ ቢውጠው ይመኛል።

ቆሬን ሲቃረብ በድፍን ወሎ ሲዘዋወር ከማይለየው ሰቀቀኑን ለመላቀቅ አንድ ሐሳብ መጣበት። የአውራ ጐዳናውን ዳርና ዳር ይዛ ከተቆረቆረችው መንደር ሲደርስ ሹፌሩን አስቆመና ወረደ። ግራና ቀኝ የተሠሩት ቤቶች ከሣያ አይበልጡም። አንድ አምስቱ በሳር የተከደኑ ናቸው። በርከት ያሉት የጠላ ቤት መሆናቸውን ከየበራፋቸው ተደፍቶ በእንጨት ላይ የተሰቀለው፥ ድንጋይ ላይ የተቀመጠው ጣሳ ያበሥራል። በራፉ በሱቲ ጨርቅ የተጋረደ አንድ ጠጅ ቤት አለ።

ከእርሱ ጐን አንዲት ትንሽ መደብር አለች። ከርስዋ ጐን አንድ ልብስ ሰፊ ከበሩ አጠገብ ተቀምጦ ልብስ ይጠቅማል። ከሁሉም ጐልቶ የሚታየው ቤት «ቆሬ ሆቴል - መኝታ አለ» የሚለው ነው። ትልቅም ይሁን ትንሽ አብዛኞቹ ቤቶች የብሔራዊ ሎተሪና የወንጂ ስኳር ማስታወቂያ ተለጥፎባቸዋል። ቀይ ዝሆን ወረቀት የነከሰች ነጭ የባሕር አሞራ።

መኪናው ሲቆም ሴቶች እጃቸውን እየጠራረጉ ወንዶች ልብሳቸውን እያስተካከሉ ብዙ ሰዎች፥ ከየቤታቸው እየወጡ ከበራፋቸው ላይ ቆሙ። አዲስ ገበያተኛ ለማግኘት ወሬ ለመስማት የመንግሥት አቶሞቢል ከመንደራቸው የቆመችበትን ምክንያት ለማወቅ ሁሉም በየፊናው። ከመንደሩ የቀን ሠራተኞችና ልጅ ቢጤ ተላላኪዎች በቀር፥ በየቤቱ ታዛ ሥር ከወሎ እልቂት የተረሱ የሚመስሉ ጥቂት ሕያው አጽሞች እዚህም እዚያም ወዳድቀዋል። ማስረሻ ከመንደሩ መሐል ቆሞ ይህንን ሁሉ ለቅጽበት ከተመለከተ በኋላ አሁንም የሙሔ ዓይን የወጋው መሰለውና መልሶ ወደ አውቶሞቢሉ መሸሽ ቃጣው። አሁን ካልተወጣው በየደረሰበት እንዲህ እንደሚሆን ደግሞ ተሰማውና ጥርሱን ነክሶ ወደ ሆቴሉ ሄደ። ከደረቡት ነጠላና ከራሳቸው ላይ ሸብ ካደረጉት ነጭ ሻሽ መካከል ንቅሳታቸው እስከ አገጫቸው ሥር ደምቆ የሚታይ ደልዳላ ሴቶች ከባንኮው ጀርባ ተቀበሉት። ጭንቅላታቸውን በማወዛወዝ ሰላምታ ተለዋወቱ።

«ምን ልታዘዝ?»

«ምን አለ?» አለ ማስረሻ ፈገግ፥ በማለት የወየቡ ጥርሶቹን ለሴትየዋ እያሳየ።

«ቢራም፥ አረኢም፥ ቢኖም -» ሌላ ያልጠቀሱት እንዳለ ለማረጋገጥ መደርደሪያውን ተመለከቱ።

«ሰው ብጠይቅዎት ያውቃሉ? እሜቴ?» ማስረሻ አረቂውን እየተጐነጨ ጠየቀ።

«ከዚች ከተማ?»

«አይ! ወደዚያ ወደ ዳገቱ ካሉት መንደሮች ይመስለኛል።»

«አገር ቤቱንስ አላውቀውም። ባዳ ነኝ። ከአምባሰል ነው የመጣሁት።»

«በዚህ አካባቢ ችግሩ ለመሆኑ ከባድ ነበር?»

«ኧረ ኤዲያልኝ ምኑ፥ ተነግሮ!»

«ብዙ ሰው ሞተ?»

«የተረፈውስ ያለቀውስ ምኑ ይታወቃል? ቤቱ ይቁጠረው እንጂ። የዛሬ አራትና አምስት ወር ይሄ ሜዳው ሁሉ አይታይም ነበር። ሰው እንደ አረንዛ ተረፍርፎበት።»

«አንድ ሰው ይሙትም ይዳን፥ እንዴት እንደሆነ ማወቅ እፈልግ ነበር። ማን ሊነግረኝ ይችላል?»

«እንዳልኩዎት እኔ አገሩን ብዙም አላውቀውም። ከዚህም በተረፈ ከባላገሮቹ ጋር ብዙም አንገናኝም። አንዳንዴ ነው ብቅ የሚሉት።» ሴትዮዋ ጥቂት አሰቡ «አንተ ማነህ እስቲ ሾፌሩ ጠጅ ቤት እንዳለ ጥራው» ሲሉ ተጣሉ። «ከዚያ መንደር አጠገብ በመኪና የሚያደርስ ልጅ ነው፤ ምናልባት እርሱ ያውቃቸው ይሆናል።»

ማስረሻ ላቀረበለት ጥያቄ፥ «አዎ! ከብዙዎቹ ጋር ብዙ ጊዜ እንገናኝ ነበር» ሲል ሹፌሩ መለሰ።

«አሁን በመንደሩ ሰው አለ?»

«ማንም የለም። እኔ ሰሞኑን እርሻ ስወጣ ማንንም አላየሁም። አንዲት አሮጊት ብቻ ነበሩ። እሳቸውም ሰሞኑን ጠፍተዋል።»

«አቶ ሙሔ የሚባሉትን ታውቃቸዋለህ?»

ሹፌሩ ጥቂት አሰበ። «ቀጠን ረዘም ያሉ ጠይም?»

ማስረሻ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ። «በሕይወት አሉ ለመሆኑ?»

«እኔ ምን አውቄ።» አጉል ጥያቄ የቀረበለት ይመስል ሹፌሩ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ።

«በቅርብ አላየሃቸውም?»

«ወደ ታኅሣሥና ጥር ገደማ ነበሩ። ብዙው ሰው ከሞተና ከተሰደደ በኋላ እሳቸውና አንዲት ልጃቸው አለች መሰለኝ እነሱና አንድ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበር የቀሩት።»

«አሁን የት እንደ ደረሱ አታውቅም?»

ሹፌሩ በአሉታ ትከሻውን ነቀነቀ። «ምኑ ይታወቃል ጌታዬ!» ሹፌሩ እንዳልተጋበዘ ሲያይ ወደ ጠጅ ቤቱ ተመለሰ።

ማስረሻ ያሰበው ሙሔ በሕይወት መኖሩን ካወቀ ራሱ ፊቱን ለማየት ስለማይደፍር በላንድሮቨሮ ሹፌር መቶ ብር ሊልክለትና ከሕሊና ፀፀቱ ለመገላገል ነበር፡፡ ወይም መሞቱን ቢያረጋግጥ የወሎ ረሃብተኛ ባጋጠመው ቊጥር ሙሔ እየመሰለው አይሸማቀቅም ነበር፡፡ ግን ሁለቱም አልሆነለትም፡፡

## ፫

በባቲ፥ በመርሣ፥ በሙርጌሣ፥ በኰረም፥ በጕብዬ፥ በደዊያ፥ በአላማጣ፥ በሐይቅ፥ በወልዲያ፥ በአሳይታ፥ በሰርዶ፥ በሎጊያ፥ በጨፋ፥ በሮቢት፥ በከሚሴ፥ በቆቦና፥ በደሴ፥ የተቋቋሙት የመጠለያ ጣቢያዎች የተላያዩም ናቸው፥ ተመሣሣይም ናቸው፡፡ አንዳንዱ ስሙ መጠለያ ይባል እንጂ ከጐኑ ግድግዳ ቀርቶ፣ ከላዩ ለፀሐይና ለዝናም ሽፋን የሌለው የተከለለ ገላጣ ሥፍራ ብቻ ነው፡፡ ሰው ከሜዳ ላይ ፈስሶ የቀን ሐሩር የሌሊት ቊር ይፈራረቅበታል፡፡ ታዲያ ለስሞታና ለአቤቱታ እንዳይመች የከተማውና የአካባቢው ሕዝብ በመረዳዳት በአስቸኳይ የሠራው የሣርና የቅጠላ ቅጠል ዳስ አለ፡፡ ለፀሐይ ይረዳል፡፡ ከዝናምና ከብርድ ግን ምንም ያህል አያድንም፡፡ እንዲያውም ዝናም ከአቧራ በኋላ፥ ከሣርና ቅጠሉ የሚወርደው ጠፈጠፍ የበለጠ ያሠቃያል፡፡

እንደ ደሴ፥ እንደ ባቲ፥ እንደ አላማጣ ያሉት ጥቂት መጠለያዎች ደግሞ ለእህል መጋዘንና ለሌላም ተግባር የተሠሩ፥ ወይም ተጀምረው በውዝፍ የቀሩና ያረጁ የቆርቆሮ ዛኒጋባዎች ናቸው፡፡ ከአንድ ቦታ በኢጣሊያ ጊዜ የወታደር ሠፈር የነበረ አንድ የአዳራሽ ፍርስራሽ ደህና መጠለያ ወጥቶታል ፡

የሥፍራው አየር ሁኔታ የመጠለያው ዓይነት ይለያይ እንጂ፥ የችግረኛው ገጽታ ተመሳሳይ ነው፡፡ በእሳት እንደተለበለበ እንጨት የከሰመ ቁመና ውኃ እንደ ሸረሸረው አፈር ፍርግርጉ የወጣ ቆዳ፥ የተሰረጐደ ጉንች የታጠፈ አንጀት፥ ያገጠጠ ጥርስ የፈዘዙ ዓይኖች ሆዱ፥ በሁለት እንጨት ላይ የተንጠለጠለ ቅንብቻ የሚመስል ሕፃን የተንጨፈረረ ፀጕር ለቆለኛውም ለደገኛውም የረሃብ መልኩ አንድ ዓይነት ነው፡፡ አካልን ብቻ ሳይሆን ቅስምን አብሮ የሚሰብር እንደ ሆድ አንጀት መንፈስን ጭምር የሚሰንግ.....

አዛውንቶቹ ችግረኞች ቆመውም ሆነ ተቀምጠው፥ አብዛኛውን ጊዜ ዓይናቸው ሰማዩንና አድማሱን ይማትራል፡፡ አንጋጠው ሰማዩን የሚያማርሩ ይመስላል፡፡ ልጆቹ ደግሞ አንገታቸውን ደፍተው ዓይኖቻቸውን ሸለብ ማድረግ ያዘወትራሉ፡፡ ቀና ብለው ዓይናቸውን የሚያሳርፉበት አስደሳች ዓለም ስለማይታያቸው ጭንቀት ውስት ይሸፈናሉ፡፡ ያደፍጣሉ፡፡ እናቶች ደግሞ ነጋ ጠባ ልጆቻቸውን በጉያቸው ውስጥ አድርገው ይውላሉ፡፡ ከረሃብ ከሞት ከበሽታ፥ ደብቀው ያድኗቸው ይመስል፡፡

ማስረሻ በየደረሰበት የመጠለያ ጣቢያ የሚያጋጥመው ትርኢት ይህንን የመሰለ ነገር፡፡ ተመሣሣይ አቀባበልም ይደረግለታል፡፡

ማን መሆኑን ለመደበቅ የተቻለውን ያህል ቢሞክርም ከአንድ መጠለያ ደርሶ ትንሽ እንደ ቆየ አዛውንቶች ከፊት ቀድመው ችግረኛው በዙሪያው ይሰበሰብና ይፋጠጠዋል፡፡ ወጥመድ ውስት እንደ ገባች አይጥ ይቅበዘበዛል፡፡ ይቊለጨልጫል፡፡

-ምን ሆናችሁ? - ሲል ይጠይቃል በጭንቀት በርበሬ በመሰለ ዓይኑ ዙሪያውን እየማተረ፡፡

-አዬ ጌታው አሁን ምን ሆናችሁ ተብሎ ይጠየቃል? ምን ያልሆነ ነገር አለና ነው እሱማ፡፡ ግና፥ ኸረ እንዲያው ለመሆኑ መጨረሻችን ምንድን ነው? ሲሉ መልሰው ይጠይቁታል፡፡

-ትንሽ ስትበረቱ ወደየመጣችሁበት ትመለሳላችሁ:: አርሳችሁ መብላት ነው ከዚያ በኋላ - ይላል ማስረሻ አዲስ ምሥጢር እንደ ገለጠላቸው ያህል::

-እሱንማ መች አጣነው ጌታው:: መመለሻው ጠፋን እንጂ!

-መቼም እንደ ተቻለ ያህል መካረሚያ ስንቅና የዘር እህል ይሰጣችኋል:: ምናልባት አንዳንዶቻችሁም የበሬ መግዣ ታገኙ ይሆናል::

ከአንድ የውጭ ድርጅት የተገኘው ዕርዳታ ለአሥር ሽህ በሬ መግዣ ብቻ መሆኑን ማስረሻ ያውቅ ነበር:: በእያንዳንዱ መጠለያ ያለው ችግረኛ ደግሞ በብዙ ሽህ ቤት የሚቈጠር ነው:: ግን የጭንቀት ጥያቄአቸው ሳያፋጥጠው የመጣለትን የተስፋ ቃል መስጠት ነበረበት:: ችግሩ፥ የወሎ ገበሬ፥ የመንግሥት ሹም ቃል ምን እንደሆነ አሳምሮ ያውቀዋል::

-ኧረ ወዲያ! ወሬውን ስንሰማ ዘመንም የለው:: እኛን እንደ ከብት በበረት ከመታጐር አልገላገለንም እንጂ::

-ያው እንደ ልማዳቸው ሹማምንቱ በልተውታል ግድ የላችሁም:: እኔን የሚገርመኝ ሹሞች ስንት ስንት ሆድ ቢኖራቸው ነው የማይጠግቡት? ሲል ሌላው ቀበል ያደርጋል::

-እስከ አሁን ከቆያችሁ አይቀር ትንሽ መታገሥ ነው - ይላል ማስረሻ በከበው ሕዝብ መሐል ተሽሎክሉኮ የሚወጣበትን መንገድ በስላች ቅድ ዓይኖቹ እየፈለገ::

-ግን እህሉም የበሬ መግዣውም ቢገኝ ያው የመንግሥት ግብር ይወሰደው የለ? - የሚል ሌላ ጥያቄ ይቀርባል::

-ግብርማ ምሕረት ተደርጓል:: አዋጁን አልሰማችሁም?

-አሄሄ! ጌታው አምናም እንደይሁ ተነግሮ ነበር:: ታድያ ምስለኔና ጭቃ ሹም አፍንጫችንን ሰንጎ አላስከፈለንም? - ተናጋሪው ምስክር የሚቈጥር ይመስል ከወዲያ ወዲህ በዓይኑ ይቃኛል:: የአዎንታ ድምፅ ያስተጋባል::

-ስለ አምናው የማውቀው ነገር የለኝም:: ቢሉ ደህና ሁኒ አይዞአችሁ - ማስረሻ ዞር ብሎ ሳይመለከት በክብና ጉባጣ ትከሻው የከበበውን ስደተኛ ጣጥሶ ይወጣል :

-አሄሄ! አሁን ማ - ይሙት አምና የደረሰብንን ሳያውቁት ወደ ፊት የሚሆነውን ትንቢት ይነግሩናል? - የሚል የሕሊና ጥያቄና የትዝብት ዓይን ይከተለዋል::

ነገር ግን ከጥያቄዎቹም ይልቅ ከአንድ መጠለያ በደረሰ ቊጥር የሚያስጨንቀው እንደ ጥላ ከሐሳቡ አልላቀቅ ያለበት የሙሔ ፊት ነበር:: ሹፌሩን ግራ የሚያጋባ የጉብኝት መሥመር ያወጣውም በዚሁ ምክንያት ነበር::

መጀመሪያ ሌሎችን መጠለያዎችን ሁሉ እያለፈ በቀጥታ ኮረም ሄደ:: ከዚያ ሲመለስ የአላማጣን የቆቦን የጉብዬን፥ የዳዊን፥ የወልድያን፥ መጠለያዎች ጐብኝቶ የደሴና የሐይቅን በመዝለል ወደ አሳይታ አመራ:: በዚህኛው መሥመር ሠርዶን ሎጊያን፥ ባቲን፥ አዳረሰ:: አሁንም ጨፋንና ከሚሴን አልፎ አልፎ ሮቢን ከጐበኘ በኋላ ወደ ሐይቅ የሚመለሱ መሆናቸውን ለሹፌሩ ነገረው::

«በአንድ አግጣጫ እያዳረስናቸው ልንሄድ እንችል ነበር እኮ። በከንቱ ነው ነዳጅ ያቃጠልነው» አለ ነገሩ ያልገባው ሹፌሩ ጉዞአቸው እንደ እብድ ሩጫ ከወዲያ ወዲህ ሆኖበት።

«ዋናው ቁም ነገር የነዳጁ አይደለም። ቅድሚያ የሚሰጣቸው አሉ» ሲል ማስረሻ በመኰሳተር መለሰለት።

«ለችግሩ እንደሆነ ሁሉም አንድ ዓይነት ናቸው» አለ ሹፌሩ በማቅማማት።

«አይደለም!» ማስረሻ ሳይታወቀው ጮኸ።

በእርግት ለእርሱ አልነበረም። ሙሔ ቆሬ አለመኖሩን እንዳረጋገጠ ማስረሻ ሦስት ዓይነት ግምት መጣበት። አንድ ምናልባት ሞቶ ይሆናል የሚል ነው። በደብዳቤ እንደ ለመነው በሕይወት ሊደርስለት አለምቻሉ ቢያሳዝነውም ፊት ለፊት፥ የመገናኘቱ ጭንቀት እልባት ይሰጠዋል። ከሁሉም የፈራው ይህንን ነበር። ሁለተኛው እደ ዳገታማ ወጥቶ ወይም ከአንድ ዘመድ ዘንድ ተጠግቶ ይሆናል የሚል ነው። ሕይወቱ ተርፎ ቤቱ ለመመለስ ያብቃው እንጂ በተመቸው ጊዜ ርዳታ ይልክለታል። ግን ይህ ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ በአንደኛው መጠለያ ውስጥ እንዳለስ? ከመቃብር የወጣ ዐጽም የሚመስለው አካሉ እየተውተረተረ ጣቱን ቀስሮ «አንተ የኄው ልጅ ማስረሻ አይደለህም? ወይስ ስላልወለድኩህ ነው? ለመሆኑ ሰው ነህ አውሬ?»እያለ ሲመጣበት ታየው። ምስቅልቅል የጕብኝት መንገድ የቀየሰው የዚህን ግጥጥሞሽ ጊዜ በተቻለ መጠን ለማዘ�ት ነበር። መጠለያ የሚገባ ከሆነ በጣም ርቆ የሚጓዝበት ምክንያት የለም። ሌላው ቢቀር መቸም ኮረም ድረስ አይሄድም። ምን ሊሠራ? ከዚያም የመጠለያ ጣቢያዎቹ ከቆሬ ያላቸውን ርቀት በማነፃፀር እየቀረበ መጣ።

አሁን ከሚሴ ጨፋና ደሴ ብቻ ቀሩት። የትኛውን እንደሚያስቀድም ተቸገረ። ለቆሬ ከሦስቱም የሚቀርበው ከሚሴ ነው። ነገር ግን ብዙ ሰዎች በሚያውቃቸው አካባቢ መካከል ተመጽዋች ሆነው መታየት አይፈልጉም። አገር ጥለው የሚሰደዱትም ለዚህ ነው። ሙሔም አርሶ፥ አምርቶ፥ ይኖርበት የነበረውን መጠለያ አልፎ ራቅ ብሎ ቢሄድ አያስደንቅም። እርግጠኛ አልሆነም እንጂ የሠርጉ ዕለት ደሴ ከተማ በወይዘሮ ምንትዋብ ግቢ ቆሞ የድግስ ትራፊ ሲለምን ያየው መስሎት አልነበር? ማስረሻ እንደ አዲስ ነገር ሰቀጠጠው። መጫወቻ እንደ ጠፋበት ልጅ ከመዳፉ ላይ ምራቁን ትፍ ብሎ በማፈናጠቅ አግጣጫ መምረጥ እስከሚቃጣው ድረስ ካመነታና ከተጨነቀ በኋላ፥ «የማይቀር ከሆነ ብወጣው ይሻላል» ሲል መደዳውን ለመጨረስ ወሰነ።

ከሚሴን በደህና ወጣ። ጨፋና ደሴ ቀሩ። እያላበው ዓይኑ እየተቅበዘበዘ የጨፋውን ጕብኝት ሲጨርስ እፎይ አለ። አሁን ቊርጡን የሚለየው አንድ ብቻ ነው። የደሴው። ስሜቱ እንደ ምጥ ድርብ ሆነበት። በአንድ በኩል ስንት ወራት ጭንቅ አርግዞ በመጨረሻ የመገላገል ተስፋ ይታየዋል። በሌላ በኩል ሕያውም በድንም መገላገል ስላለ የመጨረሻው ቅጽበት ሥጋት ቀስፎ ያዘው።

የሐረጎን ተራራ ወጥቶ በሸዋ በር በኩል የደሴ ከተማ ከፊቱ ሲንጣለል፥ በእግሩ ተጕዞ የወጣ ያህል ሰውነቱን ላብ አጥምቆት ነበር። መንፈሱ ሲታወክ የሚነሣበት ራስ ምታት አናቱን ይፈልጠው ጀመር።

በአረብ ገንዳ መንገድ ጦሳ መድኃኒት ቤት ቫይናክ ገዝቶ ሲመለስ፣ ከመደዳው ቤት ግድግዳ ተጠግቶ ምጽዋት ከሚጠይቅ ችግረኛ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጠሙ። በመካከላቸው አንድ ሠላሳ ሜትር ያህል ርቀር አለ። ነገር ግን የፀሐይ ጨረር ያረፈበት የሰውየው ፊት በሚገባ ይለያል። በሠርጉ ቀን

ያየው የሙሔ ፊት ነው? ወይስ አይደለም? እርግጠኛ መሆን አልቻለም። ዕድሜና ችግር እንደ ውኃ ሸርሽረው ቅርጹን ወዙን ለወጠውታል። ዝናም ጐርፍ፥ ነፋስ፥ ሐሩር በዘመናት ብዛት የቆየውን መልክና ወዝ እየበላ እንደሚጨርሰው ሁሉ የሰውየውም ወዘና ሽንተረርና ድርቀት ተተክቶበታል። ግን እንደውም ወዝና ቁመናው ገጽታው ያስታውቃል። ቀስ ብሎ ለማረጋገጥ ዘወር አለ። ችግረኛው አሁንም ዓይኑን አፍጥጦበታል። ቅንድቡ ሳይሰበር አሁንም እንዳፈጠጠበት ነው። እነዚያ ሁለት ዓይኖቹ እንደ ጦር ተቀስረው በእርሱ ላይ የተነጣጠሩ መሰለው። ሆነ ብሎ ነው የሚከታተለኝ? ወይስ የራሴው ሕሊና ነው በእርሱ ተመስሎ የሚያሳድደኝ? ሂዶ ለማረጋገጥ ከጀለ። ግን ያችን ሠላሳ እርምጃ የሚያቋርጥ ድፍረት ከመላ ሰውነቱ ተጨምቆ አልወጣ አለ።

«ሂድና፥ የዚያን ሰውዬ ስም ጠይቀህልናኝ ና!» አለው ሹፌሩን አሁንም ያፈጠጡበትን ዓይኖች ሰረቅ አድርጎ እየተመለከተ።

«ሙሔ ይባላል» አለ ሹፌሩ ሲመለስ።

«እህ?» ማሰሻ ድምጹ ድንገት ከዳው። ከቦርሳው ገንዘብ አወጣ። «ሂድና ይህንን ስጠው» አለ።

ሹፌሩ ገንዘብ ጨብጦ እንደ ጉድ ተመለከተው።

«ምነው?»

«ባለ ሃምሳ ብር ነው እኮ!»

«አውቄአለሁ!»

እንግዲህ የደሴ መጠለያ ጉብኝት አያስጨንቀውም።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማስረሻ ገንዘብ የሰጠው ችግረኛ ከተቀመጠበት ተነሥቶ በበትሩ መሬቱን እየዳሰሰ «እንደኔ ካለው የቀን ጨለማ ያድናችሁ» እያለ ልመናውን ለመቀጠል ወደ ሌላ ሠፈር አመራ።

## ፮

ሲታመስና ሲበጠበጥ በሰነበተው በደሴ መጠለያ ማስረሻ የተደረገለት አቀባበል ከሌሎች የተለየ ነበር። ስለ ጉብኝቱ አስቀድመው የሰሙት የመጠለያው ኃላፊዎች ከአንድ ቀን በፊት ጀምሮ በተቻለ መጠን ተዘጋጅተዋል። በግልጽና ፊት ለፊት ጐልተው የሚታዩ የጽዳት ጉድለቶች እንዲሻሻሉ ተደርጓል። ውኃ በገፍ ተለቆ ብዙዎቹ ችግረኞች ልብሳቸውን እንዲለቀልቁ ገላባቸውንም እንዲታጠቡ ተነግሯቸዋል። ምግቡም ከወትሮው ጥቂት ሻል ብሎ ተሠርቷል። ችግረኛው ግን በበኩሉ ወሬውን እንደ ሰማ በዚህ እንደ አንድ ቀን ግብር ሳይደለል ስለ ራሱ ችግርና ጭንቀት ነበር ሲያወያይና ሲመካከር የቆየው። ለዚሁም እሱን መስለው እሱን ሆነው ጉዳዩን የሚያስረዱት ሽማግሌዎች መርጦ መድቧል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የደሴ መጠለያ ችግረኛ ከራሱ የረሃብ ብሶት፥ ከፈራረሰ ቤቱ፥ ከአለቀ ቤተሰቡ ኃዘን በሌላ ተጨማሪ ንዴትና ቁጣ ሲብገነገን ሰንብቶ ነበር። ምክንያት ነበረው።

አስቀድሞ እንደ ሠጋው፥ ዕርዳታው በተለይም የበሬ መግዣው ገንዘብ በትክክል የማይዳረሰው ሆነ። እያንዳንዱም ችግረኛ የበሬ መግዣ ከመቀበሉ በፊት ከብቶቹ ያለቁበት ለመሆኑ ምስክር ማቅረብ ነበረበት።

መስካሪው ጭቃ ሹምና ምስለኔ ነው። መስክሮ ለማሰጠት ከአንድ በሬ መግዣ ቢያንስ - ቢያንስ ሠላሳ አርባ ብር ይወስዳል። አንዳንዱ ችግረኛ ገንዘቡን ከእጁ ካስገባ በኋላ አፍንጫህን ላስ ብሎ ይፈተለካል። ግን የት ሊገባ? ነገርም ከርሞም ምስለኔና ጭቃ ሹም እጥፍ ድርብ እንደሚያስተፋው ያውቃል። ይህም ባይሆን አብዛኛው የወሎ ባተሌ ገበሬ የገባውን ቃል ማጠፍ አልለመደበትም።

በዚያ ላይ ደግሞ ከዋግ ከወረይሉ፥ ከዋድላ ደላንታ ከባቲ፥ ከአምባሰል ከየጁ ድረስ የመጣ ችግረኛ አለ። ታዲያ ምስክር ከየት ሊወለድ ነው? በመካከሉ የራስ አሊ ወሴና የአልጋ ወራሽ ቤተሰብ አሽከሮች በሚያውቁበት እርስ በእርስ ምስክርነት እየተጠራሩ የዕርዳታውን ገንዘብ ይሻሙት ገቡ። ደሃው ገበሬ የአንድ ጥማድ መግዣ ሳይደርሰው እነርሱ በሽህ ብር ቤት አጋበሱ። ችግረኛው በዚህ ከንፈሩን እየነከሰ ሲያርር ማኒንጃይትስ በሽታ ገብቶ ያንን ከንፈሩን ቃቂ የሞት ሸለቆ አልፎ የመትረፍረፍ ቅንጣት ተስፋ እያደረበትን እያጣደፈር ያግዘው ጀመር። ትኵሳት ከንዳድና ከተስቦ የባሰ ሲኦል ቃጠሎ ነው። ከውስጥ ደግሞ አንጐል ያሳብጣል አሉ። ከዚያ አንገት ድርቅ ብሎ መቅረት ነው።

ማስረሻ የሙሔን ነገር የተገላገለ መስሎት ሕሊኢናው ትንሽ ቀለል ብሎለት ወደ ደሴው መጠለያ የመጣው ይህንን የመሰለ ሁናቴ በሰፈነበት ወቅት ነበር።

ከዚያም ከመጠለያው እንደ ደረሰ እንደ ጨፈቃ የተገጠገጠው ችግረኛ አቤቱታውን አደባለቀ።

-አቤት አቤት! አቤት አለቅን አለቅን! አለቅን!

-አቤት አቤት! አቤት! የመንግሥት ያለህ! የንጉሥ ያለህ!

የችግረኛው ጩኸት ከግቢው አልፎ በአየር ሠረገላ ላይ በመስፈን በዘመናት ሁሉ በወሎ ሕዝብ ላይ የደረሰውን ሁሉ ሲታዘቡ ለኖሩት የጦስና የአዘዋል ገደል ተራሮች የደረሰ መሰለ። በሰማዩ ላይ ወደ ተንጠባጠበው የበልግ ትራፊ ደመና፥ ከርሱ ስር እየደረበ ቁልቁል ወደሚመለከቱት አዕዋፍ ዘለቀ።

«ምን ሆነዋል?» ሲል ማስረሻ ጆሮውን በመዳፉ መድፈን እየቃጣው የጣቢያውን ኃላፊ ጠየቀ።

«እኛ መቸም የቻልነውን ያህል እያደረግን ነው። የገውንም በሽታ በቁጥጥር ሥር ለማዋል ተቃርበናል። እነሱ ግን በትንሹም በትልቁም ሆድ ይብሳቸዋል። በልሆነ ነገር እየሞሉ የሚጠመዝዟቸው አይጠፉም ይመስለናል። ተማሪዎቹ የማይገቡበት ነገር የለም። ለችግረኞች ነፃ አገልግሎት እንሰጣለን ይላሉ። ሲከለክሏቸው ደግሞ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋሉ» ሲል የመጠለያው ኃልፊ መለሰ።

-አቤት አቤት እግዚኦ እግዚኦ! የመንግሥት ያለህ! ጩኸት በመከታተል አስተጋባ።

«ምን ሆናችሁ! እስቲ ረጋ በሉ። እንዲሁ በጩኸት ይሆናል እንዴ? ችግራችሁን በጥሞና ተናገሩ።»

-ምን በበደልን ነው እንዲህ ያለ ግፍ የሚፈጸምብን?

-ኸረ ሰውን ባይሆን ጡር ይፍራ!

-ሥቃያችን ከሚበዛ ሞታችን ከሚከፋ ምናለ እንደ ሚሆን ጨርሳችሁ ብትገላግሉን።

-ወሎ መሬቱ እንጂ ሰውስ የተፈለገውም አልመሰለን! - ችግረኛው ማታውኑ የተማረከውን ትቶ ሁሉም በየበኩሉ እንዳመጣለት ይናገር ጀመር። መደማመጥ ቀረ።

«አሁንምኮ ልክ አይደላችሁም።» ማስረሻ በጭንቀት እጁን አወዛወዘ። «ይሄ - ደርሶብናል። ይሄ ቢሆን ይሄ ነው! ብሎ በፈርጅ በፈርጁ ማስረዳት እንጂ እንደ እብድ ገበያ ሁሉም እንዳሻው ቢጯጯህ ምንም ፋይዳ የለውም።»

«እውነታቸውን ነው ጃል» አለ ከወደፊት በኩል የቆመ አንዱ። «ሰዎቻችን ያስረዱ። ወዲህ ቅረብ እንጂ! አይዋ አሊ ጋዝ፥ አይዋ ፊጠነ፥ አይዋ ሙሔ!» ብሎ ሰውየው ሲጠራ ማስረሻ ክው አለ። ሰውነቱን ነዘረው።

«ሙሔ የሚባል አለ ከዚህ መጠለያ?» ሲል ማስረሻ አዲስ ድንጋጤ ባፈነው ድምፅ የመጠለያ ኃላፊውን ጠየቀ።

«የወሎ ስም ሣር ቅጠሉ ሙሔ ብቻ ነው። ከዚህ ስንኳ ብዙ ናቸው ያሉት።»

-አረብ ገንዳ ያየሁትም እንደዚሁ ሞክሼ ይሆን? - የሚል ሐሳብ አደረበት።

## ፯

ሙሔ አቤቱታ ለማሰማት ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የተገኘው ስሙ ከመጠራቱ በፊት ነበር። ዓይኑ በማስረሻ ላይ ሲያርፍ ሰውነቱ ስንጥቅ አለበት። ከኋላ በኩል ስለ ነበር ራቅ ብሏል። በመጀመሪያ ጥርጣሬ ብቻ ነበር። - እሱ ነው? አይደለም? ምን ጊዜ እንደዚህ አረጀ? የትናንቱ ጮርቃ ልጅ? ወላጆች ቤተሰቦች ቤተዘመዶች በዕድሜ ከእነርሱ በታች የሆነውን ሁሉ ልክ እንደ ተለዩበት ጊዜ ሳይለወጥ የሚያገኙት ይመስላቸዋል። ወይም ሳይለወጥ ዘወትር እንዲያገኙት ይፈርልጋሉ። እንደ ትናንቱ እንደ አምናው ዛሬም ለማቄላመጥ ጆሮውን እየቈነጠጡ ለመጫወት። ሙሔም፥ በዓይነ ሥጋ ከተገናኙ አሥር ዓመት ማለፉ፥ አሥር ዓመትም ረጅም ጊዜ መሆኑ አልታሰበውም። - ታዲያ ምነው እንዲህ ገረጀፈ? እንደኔው አብቅቶ የለ? ኧረ ማስረሻ አይደለም! እሱ እንዲህ ያረጀ እኔም ምን ሆኛለሁ ማለት ነው? አንገቱን ሰገግ አድርጎ በመንጠራራት እስከ ደረቱ ድረስ አየው። ማስረሻን ለመምሰሉ ጥርጥር የለውም። ከግንባሩ እስከ አገጩ፥ ከዓይኑ ቅድ እስከ ከንፈሩ ትከሻው መጉብጡ አገጩ ሾጠጥ ማለቱ የእሱው ነው። እንዲያው ከማርጀቱ በስተቀር። ከዚያም የሙሔ ዓይን ወደሚያስታውሰው ምልክት አተኰረ። አዎ! ያች የማርያም ስሞሽ ምልክት በቀኝ አገጩ ላይ አሁንም በሩቅ ጠቁራ ታስታውቃለች። ከተለምደው የማርያም ስሞች የተለየች ነበረች።

ጣቢያው በዝርዝር የሚጕበኝ እንደሆነ በየሥራ ቦታቸው ላይ እንዲገኙ ተብሎ የምግብ ቤት ሠራተኞች ወደ ፊት ቀርበው ማስረሻን ለመቀበል ስላልተፈቀደላቸው፥ በየአቅራቢያቸው ከችግረኛው ጀርባ እየተሰባሰቡ ቆመው ነበር።

«ለመሆኑ እኚህ ሰው ማናቸው?» ሲል ሙሔ በአጠገቡ የነበረው የአንድ ክፍል የምግብ ሥራ ኃላፊ ጠየቀ።

«አዲሱ ሹም ናቸው። እነዚያኞቹ ከተሻሩ በኋላ የተሾሙት።»

«እሱንማ መቼ አጣሁት። ግና ማን ይባላሉ ማለቴ እንጂ።» ሙሔ ጥርጣሬውን የሚያስተባብል መልስ ጠብቋል።

የአንደኛው ምግብ ማብሰያ ቤት ኃላፊ አካከከ። «እምም አሥራ? አስረስ?? መሸሻ? ወደዚህ ገደማ ነው ስማቸው።»

«ማስረሻ ነው?» ሙሔ ያሉታ መልስ እየጠበቀ ጠየቀ።

«እ? ነው? ማስረሻ? ነው መሰለኝ።»

ሙሔ «ወቸው ጉድ! እያለ ተነጥሎ ወደ ጓሮ በኩል ሄደ። የፀሐይ ጨረር ከዓይኑ ላይ እንዳረፈ ያህል ከማስረሻ ጋር ፊት ለፊት መተያየት አልተቻለውም። ሐሳቡ ተከፈለበት። ዋለለበት። ከመጠለያው ጉሮ አጥር ጥግ ከድንጋይ ላይ ተቀምጦ በስንጥር መሬቱን እየቻረ እጅግ በመረረ የትካዜ ሐሳብ ውስጥ ሰመጠ።

-ደብዳቤው ደርሶት ይሆን ወይስ ሳይደርሰው ነው? ደርሶት ከሆነ አውቆ የተወኝን ምን አድርግ ብዬ ነው በሕዝብ ፊት እንዲሳቀቅ እንዲበሳጭ የማደርገው? አሳደግሁት እንጂ አልወለድኩት። እኔም እራሴ ለወለድኳቸው ልጆቼ አልኮንኩ። በየሜዳው በትኛቸው አይደል ከዚህ የደረስኩት። ኦሆሆ! ታዲያ ምን አድርግ ብዬ ነው የማስቸግረው? ቁመናው ይኑር እንጂ እንዳሻው ይሁን። የልጆን ዕድል ለልጆቹ ምን አድርግ ብዬ?! ደብዳቤው አልደረሰውም እንደሆንም እሱ ባይልልኝ ነው። ታዲያ ጣረ ሞት መስዬ በድፍን የወሎ ችግረኛ ፊት የማደነግጠው የማሳፍረው ምን ምህኛት አለ? ከሆነ ቀስ ብዬ ለብቻው ብገናኘው ስንኳ ይሻላል እንጂ! ለማንኛውም እንዳሻው። ክፉ አይንካው ብቻ።

ሙሔ ካቀረቀረበት ቀና ሲል ሁለት ወፎች ሣር እያመላለሱ በግራር ዛፍ ላይ ጐጆ ሲሠሩ አየ። በመገረም ራሱን ነቀንቀ። «ሰው ከወፍ አንሶ ጐጆ አልባ ይሁን!?»

ሙሔ፥ የታጠፈ አንጀቱ በሰቀቀን እየተኰማተረ ለረጅም ጊዜ ብቻውን ተቀምጦ ቆየ። ማስረሻን ለብቻው ለመገናኘት ግን ዕድል አላጋጠመው።

ማስረሻ ከመጨነቁ የተነሣ ነጭ ላብ ወደ ግራ ባጋደለው ጆሮ ግንዱ ኩልል ብሎ እየወረደ ዓይኑ እየተቅበዘበዘ፥ ችግረኞቹ ለሚናገሩት ሁሉ፥ «ግድ የለም በእኔ ይሁንባችሁ» የሚል ቃል በጥድፊያ ደጋግሞ ከደረደረ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተፈተለከ።

ሕሊናውን እንደ ጦር ከሚወጋው ከሙሔ ዓይን ያመለጠ መሰሎት።

## ምዕራፍ አራት

«የቀድሞ ባለሥልጣኖች በፈቃዳቸው እጃቸውን ሰጡ።

«በትናንቱ ዕለት ቀደም ሲል ከጦር ኃይሎች ከፖሊስ ሠራዊትና ከብሔራዊ ጦር ማስተባበሪያ ኮሚቴ በታወጀው መሠረት ተፈላጊዎች ናቸ በመባል ስማቸው ከተገለጠው ባለሥልጣኖች

መካከል....በፈቃዳቸው እጃቸውን ለደርጉ የሰጡ መሆናቸውን የደርጉ ቃል አቀባይ ትናንት አስታውቋል.....»

አዲስ ዘመን ጋዜጣ

ሐምሌ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም

ማስረሻ ከወሎ ሸሽቶ የመጣበት አዲስ አበባ የሚያጽናና ምሽግ ሆኖ አላገኘውም። ገና በሚገባ ያልተገነባው የልጅ ጉግሣ ኮሚቴ በመፈራረስ ላይ ነበር። ከውጭ አገር ተጠርቶ የመጣው ሹም ደመቀ፥ ሥራውን ለቅቆ እንደ ገና ወደ ዋሽንግተን ተመልሷል። እርሱን የተካው ሹም ኃይለ ማርያም በማዕበሉ ውስጥ ለመግባት ፈራ ተባ የሚል በአሜሪካ የሚያደርገውን ጉብኝት አራዝሟል። በቀድሞው ኮሚቴ ውስጥ የነበረውና በአዲሱ አቃቤ ሹም እንደገና የተመረጠው ሹም ጥዱ ከናካቴው ሥራውን አልጀመረም። የልማት ሹም የሆነው አቶ አምኅ የስንብት ደብዳቤ አቅርቧል። አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይህ ነው ተብሎ ወደ ማይለይ ሹመት የተዛወረው ልጅ ወልደ ገብርኤል ቤተሰቡን ለማምጣት ወደ አውሮፓ ከሄደ ረጅም ጊዜ ሆነው። እንደዚሁም እንደ ተሾመ በጋዜጣ ላይ ውርጅብኝ የወረደበት የኮሚቴው አፈቀላጤ አቶ ሠመረ ኀዙን ለማምጣት ለጥቂት ቀኖች ወደ ጐረቤት አገር ሄደ።

ጥቂት ቀኖች ብዙ ወራት ሆኑ። ከመጀመሪያው አንሥቶ ነገሩ ሁሉ ያላማረው በንጉሡ ትዕዛዝ የቀድሞ ሥራውን እንዲቀጥል የተደረገው ዶክተር ዮናስ ከመጋቢት ወር አንሥቶ ስያንገራግር ከቆየ በኋላ በመጨረሻ በሰኔ ወር ሥራውን ለቀቀ። ችግሩ በስንብት ብቻ አላበቃም። በመጀመሪያው የሰሜኑ ክፍለ ጦር ንቅናቄ ወደ አሥመራ ከተላኩት መልእክተኞች አንዱ የነበረው የአዲሱ ኮሚቴ አባል ሹም ጄኔራል ገረመው የአሥመራ ወታደሮችን ሊያሳፍን ነበር የሚል ክስ ቀርቦበት በጦር ኃይሎች ታሠረ። በያዙት ቁልፍ - ቁልፍ ቦታ ልጅ ጉግሣ ይተማመንባቸው የነበሩ ብዙ ከፍተኛ መኮንኖችም ጐፋ ሠፈርና አራተኛ ክፍለ ጦር ገቡ። ልጅ ጉግሣ ከጸጥታ እስከ በአሪ ቡድኑ ጋር ብቻ የቀረ መሰለ። ሥልጣን የት ነው ያለው? የሚያውቅ ጠፋ። ልጅ ጉግሣና መለዮ ለባሾች የተፋጠጡ መሆናቸው ግን ያስታውቅ ነበር።

ማስረሻ የተሾመበት አዲሱ ኮሚቴና የአዲስ አበባ ሁናቴ የሚገኘው በዚህ ዓይነት ነበር። ማስረሻ ለኮሚቴ ስብሳባ አልተጠራም። ዋና ሹም ስላልሆነ ለኮሚቴ ስብሰባ እንደማይጠራ ያውቀዋል። ቦታው አሁንም ሰው አልተሾመበትም ስለዚህ መመሪያ የሚኢሰጠው ሰው በአቃቢያው የለም። ለዕርዳታው ተባባሪና አስፈላጊ የሆኑት መሥሪያ ቤቶች ብዙ ናቸው። ካለነርሱ ምንም መሥራት አይችልም። ግን አንዳንዶቹ ኃልፊ የላቸውም። ቢኖራቸውም ከምክትል ሹም ጋር ግዴታ ለመግባት የሚፈሩ ይመስል ጥያቄውን አድበስብሰው ይመልሱለታል። የአቃቤ ሹም ዕርዳታ የግድ የሚያስፈልገው ሆነ። አስፈላጊውን ትዕዛዝ ለየመሥሪያ ቤቱ በሚያስተላልፍለት ነገሩ መልክ ይይዛል። ወይም ደግሞ ምን ማድረግ እንደሚገባው መመሪያ ይሰጠዋል። ግን ሁለቱንም አላገኘም።

ለልጅ ጉግሣ ልዩ ፀሐፊ ብዙ ጊዜ እየደወለ ቀጠሮ ጠየቀ። በቴሌፎን ለማነጋገር ስንኳ። አንድ ጊዜ ስብሰባ ላይ ናቸው። በቴሌፎን ማነጋገር አይችሉም። ሌላ ጊዜ የሉም። የት ሄዱ? ቤተ መንግሥት። ወይም አስቸኳይ ጉዳይ አጋጥሞአቸው ወጣ ብለዋል። መቸ ይመለሳሉ? አይታወቅም። ምን ተሻለ? እስቲ እንግዲህ ከሰሞኑ መጠየቅ ነው።

ማስረሻ ጠበቀ። የሠራተኛው ሥውር ዓይን እየገረፈውና እየገላመጠው ቢሮ ገብቶ ከግድግዳ ጋር ተፋጥጦ ይውላል። የሚቀርብለት ብዙ ሥራ የለም። በቀን አንድ ሦስት የሚፈረሙ ወረቀቶች

ቢመጡለት ነው። የቴሌፎን ደወል ስንኳ ብርቅ ሆነበት። የካርታና የአረቄ ጓደኞቹ ሆነ ብለው የሸሹት ይመስል አይደውሉለትም። ወይስ አዲሱን ቍጥር ሳያውቁት ቀርተው ይሆን? አንድ ሁለቱን ደወለና ሊያነጋግራቸው ሞከረ። በአጭር ሰላምታ ዘጉት። ቢቸግረው ልብ ወለድ መጽሐፍ ይዞ እየገባ ሲያነብ መዋል ጀመረ።

አንድ ቀን በመሥሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ ከወትሮው የተለየ እንቅስቃሴ ታየ። ሠራተኛው ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ይመላለሳሉ። በየመተላለፊያው ይንሾካሾካሉ። ብዙ ሰዎች ከውጭ ይመጣሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከውጭም የሚመጡትም በየቢሮአቸው የነበሩትም ሜዳው ላይ መሰብሰብ ጀመሩ። ማስረሻ ይህንን ሁሉ በመስኮት በኩል ከተመለከተ በኋላ ተላላኪውን በደወል ጠርቶ ጠየቀው።

«ምንድን ነው እሱ?»

«ምኑ ጌታዬ?»

«ግርግሩ።»

«ኧረ ሰላም ነው ጌታዬ።»

«ታዲያ ሠራተኛው ሁሉ ከቢሮው እየወጣ እልምን ሜዳ ላይ ይሰበሰባል? ከውጭስ የሚጕርፈው ሰው ምንድን ነው?»

ተላላኪው ጥቂት አቅማማ። «እሱማ ለመመካከር ነው» ሲል መለሰለት።

«የምን ምክር?» - ማስረሻ ይነሣልን ሲሉ ነው? — የሚል ሐሳብ መጣበት።

«እሱንማ ምኑን አውቃለሁ ጌታዬ?»

«ለመሆኑ ማን ነው ይህንን ሁሉ የሚሠራ?»

«ምኑን ጌታዬ?»

«የሚሰበስብና የሚመክር።»

«ሠራተኛው በሙሉ ነው። ኧረ እንዲያውም ከጐናችን ያሉት የሁለት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ጭምር ናቸው።»

«ቢሆንም። ሁሉም ሠራተኛ እንደ አንድ ልብ አስቦ በአንድ ጊዜ አይነሣም። የሚያስተባብረው ሰው መኖር አለበት። እነማን ናቸው እነሱ ነው ጥያቄዬ?»

ተላላኪው መልስ ሳይሰት ለመውጣት ፊቱን ወደ በሩ መለሰ።

«ቆይ! ንገረኝ እንጂ!» ማስረሻ አነጋገር ትዕዛዝ - ቀመስ ነበር።

«ምኑን ልንገርዎት ጌታዬ?» የተላላኪው ጭንቀት ከፊቱ ላይ የነበባል።

«አይዞህ ለክፋት አይደለም። ብንማከርበት እኔም ጠቃሚ አስተያየት ልሰጣቸው እችላለሁ»

ተላላኪው አንገቱን አቀርቅሮ ዝም አለ። ማስረሻ በማስጠንቀቅም፥ በማባበልም ብዙ ከወተወተ በኋላ «እንዳልኩዎት ሁሉም ሠራተኛ ነው። ግና - » ተላላኪው ፊቱን እየጨፈገገ የሦስት ሠራተኞች ስም ነገረው።

«እስቲ ጥራቸው» አለ ማስረሻ ትንሽ በመኰሳተር።

አሁን በግቢው የተሰበሰበው ሰው ብዛት መጠነኛ ገበያ አክሏል። ሁካታው በዚያው ልክ ደርቷል። ተላላኪው ወዲያውኑ ተመልሰና «ስብሰባ ላይ ነን አሉ ጌታዬ» አለው።

«አንመጣም እምቢ ነው የሚሉት?»

«ስብሰባ ጀምረናል ነው ያሉት ጌታዬ።»

«ወቸው ጉድ! ባጭሩ ትዕዛዝህን አንቀበልም ማለታቸው ነው!» ሲል ማስረሻ ጮኸ። የተጠራቀመ ብስጭትና ሰቀቀኑ በንዴት ስሜት ገነፈለ። ራሱ ሂዶ ልክ ልካቸውን ሊነግቸውና ስብሰባውንም ሊበትን ከጀለው። ግን የባሰውን ውርደት ቢያከውናትስ? ግን እንዲሁ ከተዋቸው ድግሞ ነገ አንድም ሠራተኛ አይታዘዘውም። ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ ደግሞ ከወንበሩ ላይ ምን አስቀመጠው? በትሾመበት መሥሪያ ቤት መንግሥትን የሚቃወም ስብሰባ ሲደረግ አድማ ሲካሄድ ዝም ብሎ ከተመለከተ ራሱን አያስጠይቀውም? ሁለት ጊዜ እጁን ወደ ቴሌፎኑ እየዘረጋ መለሰ። በየሥፍራው የሚፈነዳውን እንቅስቃሴ ለመግታት የልጅ ጉግሣ የጸጥታ አስከባሪ ቡድን እርምጃ ከመውሰድ አይመለስም። የኮሚቴው ብዙዎቹ አባሎችና የተሰናበቱትም ቡድኑ በሚፈጽመው ተግባር ባለመስማማት ነበር። ሕዝብን የበለተ ያስቆጣል የሚል አስተያየት ነበራቸው። ማስረሻ ለጥቂት ጊዜ ተቸገረና ግንባሩን በመዳፉ እየፈተገ ቴሌፎኑን አንሥቶ ደወለ። ለልጅ ጉግሣ ጸሐፊ ነበር። «ምንም አይደል አትሥጋ። ብቻ ቢሮህ ውስጥ እንደሆንክ ራስህን ጠብቅ» ተባለ። ምን ማለቱ ነው? እኔን እንዳይገድሉኝ ማለቱ ነው? ተላላኪው ወደ ስብሰባው ሂዶ ስለ ነበር የቢሮውን በር ከውስጥ ቆለፈ። መስኮቱንም ለመዝጋት ሄዶ ከስብሰባው ፊት ለፊት ስለሆነበት በፍርሃቱ እንዳይዛበቱበት በማለት ተወው። የስብሰባው ንግግር በሩቅ ይሰማዋል። ጭብጨባው ጉልቶ ያስተጋባል። ነገሩን መስማት ፈለገ። መስማትም አልፈለገም። በእርሱ ላይ የሚዛበቱ እንደሆነስ? - የተማረ ቅጥረኛ ለሀብት ሲል የመኳንንቱ ልጅ ያገባ፥ የአዲሱ የመሳፍንት መንግሥት ባለሟል - እያሉ ሲያብጠልጥሉት ዝም ብሎ ሊያዳምጥ ነው? «ሁሉም ነገር እናቱን!» ሲል በቡጢ ጠረጴዛውን መታና የእንግሊዝኛ ልብ ወለድ መጽሐፉን አውጥቶ መንበብ ጀመረ።

አሥር ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ማስረሻ እንደ ገመተው የከባድ መኪኢና ድምፅ ተሰማ። የልጅ ጉግሣ የጸጥታ አስከባሪ ቡድኖች ግቢውን አለበሱት። ላንዳፍታ ግቢው ጸጥ አለ። ማስረሻም ከመስኮቱ በኩል ተጠግቶ አዳመጠ። አንድ ሰው ተናገረ። የጸጥታ አስከባሪዎች መሪ መሆን አለበት። እንደ ንብ የሚተም ድምጽ አስተጋባ። ቀጥሎ ሌላ ሰው ተናገረ። አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮችና ሐሳቦች ተቀነጫጭበው ተሰሙት - ማኅበር ለማቋቋም እንጂ ጸጥታ አላደፈረስም....እንደ ድሮው መቀለድ ቀርቷል....መብት የላችሁም ከተባልን፥ እኛው መብታችንን እናስከብራለን....ጭብጨባ ቀጠለ።

የሌላ ተናጋሪ ድምፅ ሲሰማ፥ ውው! ውው! የሚል የፌዝ ጩኸት አተመመ። ቀጥሎ እንደ ደፈረሰ ገበያ፥ ሁካታ ጩኸት፥ የሰው ኮቴ በአንድነት ተደባልቆ አስተጋባ። ይህ ሁሉ ሲሆን ማስረሻ ከግድግዳው ጋር ተለጥፎ ያዳምጣል። ልቡ ደረቱን ተርትሮ የሚወጣ እስኪመስል ድረስ እንደ ታምቡር ይመታል። ወዲያውኑ አንድ ጥይት ተተኰሰ። ጩኸትና ትርምስ ፈነዳ! ማስረሻ ክው አለ። ተከታትሎ

መዓት ተኩስ ተንጣጣ። ጧ! ጧ! ጧ! ጧጧ! ትርርም! ዷ! ዷ! ማስረሻ ጆሮውን በመዳፉ ሸፈነ። ተኩስ መልሶ ቀጥ አለ። አልፎ አልፎ ኡኡታ ብቻ ይሰማል ፡

ማስረሻ አንገቱን ሰገግ አድርጎ በመስኮቱ በኩል ወደ ውጭ ተመለከተ። የሞተውና ቊስለኛው በወሳንሳ እየተያዘ ከካሚዎኑ ላይ ይጫናል። የቀረው ማጅራቱን እየታነቀ ከካሚዎችኑ ላይ እንደሚወጣ ይደረጋል። አንዳንዱ በአጥር ዘልየ አመልጣለሁ ሲል እየጐተተ ይወድቃል። መዝለል የቻለው ተኩስ ይከተለዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ነገር ተፈጸመ።

ጸጥታ አስከባሪዎቹ የያዙትን ይዘው ሄዱ። ሌላው ድራሹ ጠፋ። ግቢው ጭር አለ። ጊዜው አሥራ አንድ ሰዓት ይሆናል። ማስረሻ በአስፋልቱ ላይ የፈሰሰውንና የተንጣለለውን ደም ፊቱን ጨፍግጎ እየተመለከተ ወጣና ሄደ። ከውጭ ሰዎች ስብስብ - ስብስብ ብለው ስለ ድርጊቱ ይጠያየቃሉ። ያወራሉ። ፊታቸው በኀዘንና በንዴት ተኰማትሯል።

፳

«ይቅርታ ያድርጉልኝና እርስዎ ነዎት ከዚህ ሁሉ ያደረሱኝ!» አለ ማስረሻ፥ አንገቱን ደፋ አድርጎ እየተከዘ፥ ውስጥ - ውስጡን የጋብቻው፣ የሹመቱ፥ የሙሔና የወሎ ሰቀቀን በአንድነት ተደባልቆ፥ ስሜቱን እያመሰው። ያልተጣራ የወሬ - ወሬ ሰምተው እንዳይደነግጡ በማለት ማምሻውን ማስረሻና ዘለቃ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት መጥተው በመሥሪያ በኢቱ የሆነውን ሁሉ እንደ መሰለው ተርኮላቸዋል። ቅሬታውን የገለጸው ከትረካው በኂላ ነበር። የአቃቤ ሹም ጕንጤ ኮሚቴ ጕፋ ሠፈር ከገባ በኂላ የመዝናናት ስሜት ያደረባቸው ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ያዳምጡትም ረጋ ብለው ነበር። እንደ ወትሮው አላመናጨቁትም። ፊታቸውን አላኰሳተሩትም።

«እኔ ምን አጠፋሁ ደግሞ ነው የምትለኝ?» ሲሉ ጠየቁት ፊት፥ ለፊታቸው የተቀመጠውን ማናዬን በፈገግታ እየተመለከቱ።

«ከዚህ ጣጣ ውስጥ ባያስገቡኝ ኖሮ። ለምንስ ከመጀመሪያው እኔ ፈቀደኛ መሆኔንና አለመሆኔን ቢያማክሩኝ ምን ነበረበት?» ማስረሻ ብዙ መናገር ከጅሎት አቋርጦ ተወው።

«ለሹመቱ? ኦሆሆሆ! ለምሳሌ እናንተ ስትተጫጩ ሰው አማከራችሁ? ከአሁን ቀደምም ነግሬሃለሁ። እናንተው አስቀድማችሁ ጨርሳችሁ እንጋባለን አላችህ። ያመጣችሁትን ተቀበልን። እናንተው እንድመትደብቁት መንግሥት ፀሐዩ መንግሥታችን፥ ፀሐዩ ንጉሣችን እንደ መሰለው ይሾማል ይሽራል። እኮ አሁን ምን ሆነ ነው የምትለው? ለምን ተሾምኩ? ለምን አደግሁ? ምነው ሸዋ!»

«ግንኮ በሠራተኞቹ ላይ የተወሰደው እርምጃ ልክ አልነበረም» አለ ማስረሻ። «ያ ሁሉ ተኩስ ያ ሁሉ ግድያ ምን ያስፈልጋል? ከዚህ የሚያደርስ አልነበረም። ያንን ሁሉ ሬሣና ደም ሳይ በጣም ነው የሰቀጠጠኝ።» ማስረሻ የሐሳብ ደጋፊ ለማግኘት ወደ ዘለቃና ወደ ማናዬ ተመለከተ። ግን አንዳቸውም ፊት አልሰጡትም። ዘለቃ አቀርቅራ የእጅ ጥፍርዋን ትለቅማለች። እንዳልሰማች መስላ። ይነሣልን ተብሎ በመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ወረቀት የተበተነበት ማናዬም የእጅ ጣቶቹን እያቁላለፈና እያፍታታ ጣሪያ ጣሪያውን ይመለከታል።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ብቻ ከትከት ብለው ሳቁ። «አዛኝ ቅቤ አንጓች የሆነችው ሴት ታሪክ ሆንክብኝ። ዶሮ ሲታረድ ታለቅሳለች፥ ውጡ ሲቀርብ ብልት አይቅረኝ ትላለች ይባላል። እና አሁንም

አገር ላስተዳድር ብሎ ላመጻኛ ራርቶና አዝኖ ይዘለቃል? ነፍሳቸውን ይማርና ደጃዝማች ባልሆኑ ኖሮ ወላሞን ማን ይችለው ነበር? ነጋ ጠባ ማደም ነው። ነጋ ጠባ ማመፅ ነው። ታዲያ እያጋደሙ ጀርባውን ሲገለብጡት ልክ ገባ! ጸጥ ለበጥ ብሎ ተገዝ። ወትሮውንስ ሥልጣኔ ተብሎ ወይም ወለም ዘለም ባይባል ኖሮ ከዚህ ሁሉ መቸ እንደርስ ነበር? ስለዚህ ወንድ ልጅ ሆኖ አለመርበትበት ነው። ምነው ሸዋ!»

«የመርበትበት ጉዳይ አይደለም!» አለ ማስረሻ በተለመደ አሽሙራቸው ስለነኩት የተሰማውን ንዴት ዋጥ እያደረገ። «ከመሬት ተነሥቶ ሰው መግደል ትክክል አይመስለኝ። ሕይወት እኮ ውድ ናት!»

«እንደ ዓይነቱ ነው! ሰው የተባለው ሁሉ አንድ አይደለም። እንደ ዘሩ እንደ ዓይነቱ ነው» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተኰፍሰው።

«አይ መቸም ቢሆን ሕይወት ለዚያ ለባለቤቱ ውድ ነው። እንደ ሌላው አመለካከት ሳይሆን እንደየራሱ።» ማስረሻ አሁንም ደጋፊ ለማግኘት ወደ ዘለቃና ወደ ማናዬ ተመለከተ። አላገኘውም።

«ሌላው ቢቀር እኒህ አምስት ጣቶቻችን እኩል አለመሆናቸውን አጥተኸው ነው?»

«በቁመት ነው የሚለያዩት እንጂ ያው - የአንድ ሰው አካል ናቸው።»

«በሥራቸው የለያያሉ።»

«እንዴት?»

«ለምሳሌ ይኸ የጌጥ ነው። ይኸ ደግሞ አይደለም።» አውራ ጣታቸውን አሳዩት።

«ግን አንደኛው ጣትዎ ቢቆረጥ ደስ ይልዎታል!»

«በምን ምህኛት?»

«ውድ የሆነው የሰውን ሕይወት ማጥፋትም እንደዚሁ ነው!» ማስረሻ በመርታት አኳኋን ጮክ ብሎ ተናገረ።

«ርካሽ ሰው ሕይወቱን ራሱ ነው የሚያረክሰው» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተኰሳተረው።

«እማዬ ለመሆኑ አዲሲቷ ገረድሽ እንዴት ናት? የኔን ላባርራት ነው» ስትል ዘለቃ ጠየቀች፥ የጨዋታውን አዝማሚያ ለመለወጥ።

«ቂን - ቂን ማለት ጀምራለች። ወትሮውንስ ወሎ መቼ ጥጋብ ይችላልና።»

«እርስዎ ወሎ ይወለዱ የለ?» አለ ማስረሻ ነገር ለመለኰስ ሞቅታው እየገፋፋው።

«ኸረግ አብ ሲነካ ወልድ ይከፋ እንዲሉ ለካ፥ አንተም ከዚያው ነህና! ጥብቅና መቆምህ ነው? ስለኔ ትውልድ ግን፥ ዝግባና ብሳና ለእየቅል ተብሏል።»

«እና፥ እኛዎቹ ብሳና!»

«ምነው ሸዋ! ጤናም አልያዘው!» ያ -ደንደሳቸው በቁጣ ይነፉ ጀመር።

«እውነትዎን ነው፤ ጤናማማ ብሆን ኖሮ.....» ማስረሽ ነገሩን አንጠልጥሎ እንደ ተወው የነገሩ አዝማሚያ ያላማራት ዘለቃ ቦርሳዋን ይዛ ብድግ አለች፡፡

«ኧረ በጊዜ እንግባ ቤታችን ማስረሻ! ነገ ሥራ እኮ ነው፡፡»

«ነገ? ስለ ነገ ምን እናውቃለን?» የዘመመ ትከሻውን እየነቀነቀ ተነሣ፡፡

## ፫

ማስረሻ እንደገና ወደ ቢሮ ለመሄድ በቂ ድፍረት አላገኘም፡፡ በወሬ እንደሰማው አራት ሰራተኞች ሞተዋል፤ ሰባት ያህል በጠና ቈስለዋል፤ ወደ አምሳ የሚደርሱ ታስረዋል፡፡ የቀረው ሠራተኛ በንዴት ተቃጥሏል፡፡ ቁምትጣውም ያተኰረው በእርሱ ላይ ነው፡፡ ለጠፋው የንጹሐን ደም ተጠያቂ መሆኑንና ወትሮውንም ለሹማምንትና ለሀብት ሲል ከመኳንንት ቤት አሽከርነት መግባቱን የሚገልጽ ወረቀት ተበትኖበታል፡፡ በገመድ እንደ ተንጠለጠለ የሚያሳይ ሥዕል ከመሥሪያ ቤቱ በር ላይ ተለጥፎ አላፊ አግዳሚው ይመለከተዋል፡፡ በቴሌፎን ጠይቋት እያቅማማች ይህንን የነገረችው የቀድሞ ጸሐፊው ናት፡፡

ስንብት ሳይጠይቅ፥ ወይም ሳያስታውቅ ከሥራ ቀርቶም ሰላም ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ከሥራ በመቅረቱ ዘለቃ ትነዘንዘው ገባች፡፡ መጀመሪያ መገፋፋትና ማደፋፈር ነበር፥ «ምን እንዳያደርጉህ ነው? የአንድ ሁለት ቀን አሉባልታ ነው፡፡  እስካሁን አልፏል፥ ተረስቷል» ትለዋለች፡፡

እያደር ወደ ማመናጨቅ ተለወጠ፥ «አታፍርም እንዴ! አንድ ወንድ ባለሥልጣን የበታች ሠራተኞቹን ፈርቶ ቤት ሲውል?»

«ፈርቼ አይደለም፡፡ ነገሩ አስጠልቶኝ ነው» ሲል ይጮሃል፡፡

«የሚፈራ ይጠላል - የሚጠላም ይፈራል፡፡ ልዩነት የለውም» ስትል በምፀት ትመልስለታለች፡፡ በመጨረሻ ፊት ነሣችው፡፡ ማነጋገርም ተወችው፡፡ ብዙውን ቀን በምሳ ሰዓት ቤት አትመጣም፡፡ ብትመጣም ምግብ በሰሐን አስቋጥራ ወዲያው ተመልሳ ትሄዳለች፡፡ ማታ የምትገባው አምሽታ ነው፡፡ የመቅበጥበጥ ሁናቴዋ ብሶባታል፡፡

አንድ ቀን እንደ ተለመደው ሰሐን በፕላስቲክ ቅርጫት ይዛ ስትወጣ እንደ ዋዛ ጠየቃት፡፡ «ለመሆኑ የምን ምግብ ነው የምታስላልሺው?»

«ሰው አይጠየቅም ነው?» ስትል ፊቷን ኮሶ አስመስላ መለሰችለት፡፡ የምትሄድበትን ግን ጠርጥሯል፡፡ አንድ ቀን በምሳ ሰዓት ወደዚያው ሄደ፡፡ በእርግጥ የዘለቃን አውቶሞቢል ቁማ አገኛት፡፡ የቀድሞዎቹ ሹማምንት በታሠሩበት በኀፋ ሠፈር ነበር፡፡ ከንንጉል ሌላ የምትጠይቀው ሊኖር አይችልም፡፡ እሱ እስከሚያውቀው ድረስ ከቀድሞዎቹ ሹማምንት እስከዚህም የቅርብ ዘመድ የላትም፡፡ የነገረችውን ታሪክ ለማመን ከጅሎት የነበረው ሁሉ አሁን እንደ ገና ተበጠበጠበት፡፡ ግን እንደ ገና ሰሞኑ ሁናቴዋም ከምታስረዳውና ምክንያት ከምትሰጠው ይልቅ ታሸፍበት ይሆናል፡፡

ወደ ተለመደው መደበቂያው ወደ አረቂ ጠርሙስ ውስጥ ገባ፡፡ በከተማው ዳርቻና በሠዋራ ቦታዎች በሚገኙ ሆቴሎች አረቂውን ተጋትሮ ይውላል፡፡ ሲያሰኘው ክፍል ተከርይቶ ያርፋል፡፡ ሰዓት እላፊ ሊደርስ አቅራቢያ ቤት ገብቶ የስካር እንቅልፉን ይለጥጣል፡፡

አብረው በአንድ ጣሪያ ሥር ይኑሩ እንጂ እያንዳንዳቸው የግላቸውን ኑሮ መምራት ያዙ፡፡ አሁንም ባልና ሚስት ናቸው፡፡ ግን በመካከላቸው አንዳችም ዓይነት የመተሳሰብና የመሳሳብ ስሜት ያለ አይመስለኝም፡፡ ባሕር ውስጥ እንደ ተጣለ ቡሽ በየአግጣጫው ይንሳፈፋሉ፡፡ በተለይ ማስረሻ የወትሮው የለየለት ንዴቱ፥ የሚያቃጥል ቅናቱ በልቡ ውስጥ እየደበዘዘ ሄደ፡፡ ሌላው ቀርቶ የሚያፈቅራት ወይም የሚጠላት መሆኑ አልሰማው አለ፡፡ የእህል ዘር አፈር ውስጥ ወድቆ፥ ሌላ ቡቃያ ሆኖ እስኪወጣ ድረስ እንደማይለይ ሁሉ፡፡ መሰላቸት ራስንም ሌላውንም መሰልቸትና መጠየፍ ነበር፡፡ የአእምሮ መደንዘዝ የሕሊና መደንዘዝ እንቅልፍ፥ የተፈጥሮ ሳይሆን የሕሊና እንቅልፍ፥ የግል ሳይሆን የማኅበረሰባዊ እንቅልፍ.....አንዳንድ ዓይነት ትሎች ለተወሰነ ወራት በድን ሆነው እንደሚከርሙት ሁሉ፡፡....

ይህ እንቅልፍ ግን እስከ ዘልቄታው ጭልጥ ያለ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ መባነን አለ፡፡ መወራጨት አለ፡፡ ትላትሉም ዘራ ዘሩም ከብድንነቱ ከብስብስበቱ ፈንቅሎ ለመውጣት የሚቀጠቀጥበት ጊዜ አለ.....

ማስረሻም እንደዚሁ ከእንቅልፍ ላይ የሚባንንበት ጊዜ ነበር - ይህንን ችጋር እኔ አላመጣሁት፡፡ ሙሔን እኔ ረሃብ ላይ አልጣልኩት! እንኳ የተፈጥሮን አዛለሁ እንዴ? ምንድን ነው ይህ ሁሉ ጭንቀት?! ምንድን ነው ሰቀቀኑ! - ይልና መለኪያውን ይከለብሰዋል፡፡

ሌላ ጊዜ - ጓንጉልም ጉግሣም ዘለቃም ዘርፈሽዋልም እናታችሁን እናታችሁን! ገደል ግቡ እናታችሁን! - የሚጠጣበትን ጠረጴዛ በአረቄ ብርጭቆው ዷ! ዷ! ያደርገዋል፡፡

-ሠራተኛው ሁሉ እናቱን! እኔ ምን ወንጀል ሠራሁና ነው? ማንንም አልፈራም! - ሲል ጠረጴዛውን ደግሞ ይወቅጠዋል፡፡

-ምን ልታዘዝ ጌቶች? - የሆቴሉ ሠራተኛ ትጠይቃለች፡፡

-አልጠራሁሽም ነበር! ግን ከመጣሽ ጨምሪልኝ! አንድ ቀን ግን የማስረሻ መባነን፥ ከቅዠት ከመወራጨት ከለየለት የስካር መቃዠት በመለስ መጠነኛ ሞቅታ ታጥቆ ከዘለቃ ጋር በድፍረት ተፋጠጠ፡፡

«ከዚህ ሁሉ ጠቅልለሽ ብትገቢ አይሻልም?» አላት፡፡ ካለወትሮው ሁለቱም እንደ አጋጣሚ በጊዜ ገብተው ቴሌቪዥን ፕሮግራሙን ጨርሶ በትልቁ፥ አልጋ ላይ ተራርቀው ጀርባ ለጀርባ ተኝተዋል፡፡ በመካከላቸው ለአንድ ሰው የሚበቃ ቦታ አለ፡፡

«የት?» ስትል ኰስተር ብላ ጠየቀችው ፊቷን ሳትመልስ፡፡

«ጎፋ ሠፈር ወይም ቤቱ፡፡»

«እንደ ጭራ መከተሉን አሁንም አልተወክም?»

«ምኑ ምሥጢር ሆኖ ነው ተከታታይ የሚያስፈልገው? ለመሆኑ ሚስቱ ቀለብ አትወስድለትም? ወይስ የባልና ፉክክር ገጥሚችኋል ማለት ነው?» አነጋገሩን የፌዝ ቅላጼ ሰጠው፡፡

«የቀለብ ወጪ አስቸገርኩህ እንዴ? ድንቄም!» አለች ዘለቃ አሁንም ጀርባ ለጀርባ እንደ ተጋደሙ፡፡ የማፌዝ ቃናዋ የሰላ ምላጭ ነበር፡፡

«እህህ! ቀለብ ያስቸገርኩትማ እኔ መሆን አለብኝ!» አሽሙርዋ ለለገባው ማስረሻ ብሽቅ አለ፡፡ ደሞዙን አላመጣም ነበር፡፡ ለአረቄውም፥ ለቤንዚኑም የግል ወጪውን ችሎለት የቆየው የውሎ ሥራው የውሎ አበልና መጠባበቂያ ወጭ ነው፡፡ እሱም እየመነመነ በመሄድ ላይ ነው፡፡

«ያስቸገርኩሽማ እኔ ልሆን እችላለሁ፡፡ ግን የቤት ኪራዩ እንደሆነ የእኔው ዕዳ ነው፡፡ አንቺማ የምትሄጂበት እልፍኝ ካዳራሽ አለሽ፡፡ ከሥራ የወጣ ባልሽን አንድ ወር ቀለብ አልችልም ካልሽ ደግሞ መቼስ ማል ጎደኒ ይሏል፡፡»

«አሁን እኔ ስለ ወጪ መጓደል ወጣኝ? ለምን ነገር ትጠመዝዛለህ?»

«ሕይወትም ጠምዛዛ ነው፡፡ በተለይ፥ ጋራ ሸለቆ፥ ሸንተረር ዳገት በሚበዛትበት በኢትዮጵያ ምድር፡፡ ነገር ግን መፈላሰፉንም የሕይወት ምርምሩንም እንተወውና ለመሆኑ፥ የሚጠጣ ነገር ካለ ወጭህን አልሸፈንክም ካልተባልኩ አልተላም ነበር፡፡»

ከንፈርዋን መጥጣ በመነሣት ዊስኪ በገፍ ቀድታ አመጣችለት፡፡ አመሉን አሳምራ ታውቀዋለች፡፡ ሳይጠጣ አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ መጠነኛ ሞቅታ ሲሰማው ግን አይጣል ነው ንግግሩ ክርክሩ ምርምሩ፥ አሽሙሩ፥ እንደ ምላጭ ስሎ ይወጣል፡፡ እንቅልፉ አይመጣም፡፡ ለነገሩማ በጥሩ ስሜት ጊዜው ደህና አፍቃሪ ለመሆን የሚሞክረው በዚህ ደረጃ ነው፡፡ አሁን ግን አይደለም፡፡ አንድያውን ድብን ብሎ ሲሰክር እንቅልፍ ይወስደዋል፡፡ ይባይወስደውም ፈዛዛ፥ ደንባዛ፥ ገራም ይሆናል፡፡

«እግዚአብሔር ይስጥልኝ» አለ ብርጭቆውን በአንድ ጕርጕጭታ አጋምሶ፡፡

«ዚስ ኢስ ጉድ!» አለ ብርጭቆውን ሲጨልጥ፥ «ፎር ጌት ኤቭሪሲንግ - ኑሮንም ሕይወትንም፥ እንርሳው!» ዓይኖቹ እየፈዘዙ ሄዱ፡፡

ሌላ ጊዜ ብንን ብሎ ከሕይወት አለመጣጣም ጋር እስኪፋጠጥ ድረስ ወደ መታከት እንቅልፉ ገባ፡፡

## ፬

ማስረሻ ቀስ በቀስ ከቀን ወደ ቀን በጠርሙስ ውስጥ እየሰመጠ መሄዱን ቀጠለ፡፡ ጥንብዝ ብሎ ቢሰክርም ራሱን አይስትም፤ ግን አንድም ቀን ደግሞ አእምሮው ሙሉ ጤናማ ሆኖ አያውቅም፡፡ በየቀኑ በየሰዓቱ ይጠጣል፡፡ በየሰዓቱ መለኪያ፡፡ በየደቂቃው ሲጋራ፡፡ ዓይኑ የባሰውን ግሽርጥ መሰለ፡፡ ለመጠጡ እንጂ ሆዱ ለምግብ ስለ ተዘጋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ኪሎ ቀንሶ ወትሮውንም ልብስ ሰፊ በማያስመካ ሰውነቱ ላይ ኮትና ሱሪው ሳይለካ የተገዛው እይም የተመጸወተው የውራጅ ውራጅ መሰለበት፡፡

ቀደም ሲል ጓደኞቹን ለመገናኘት ያልፈልገውን ያህል አሁንም ደግሞ የሚያውቀው ሰው እንዳያየው ይሸሽ ጀመር፡፡ እየተገላመጠ ሹክክ እያለ ከአንዲት አነስተኛ ግሮሰሪ ይገባና ጥግ ይዞ መለኪያውን ብቻውን ይጋተረዋል፡፡ አንድ ሁለት መለኪያ ጠጥቶ ይወጣና ወደ ቤቱ ይሄዳል፡፡ ወይም ከመኪናው ውስጥ ተቀምጦ ያንጕላጃል፡፡ ከጥቂት ሰዓት በኋላ እንደ ገና ሌላ ግሮሰሪ ይገባና ይጠጣል፡፡ እንደሚዘዋወረው ደሙ የሚጕነጨውም አልኰል የማያቋርጥ ዑደት ነበር፡፡ አእምሮውም ያለ ማቋረጥ

ደነዘ። የስሜት ሕዋሱ እንደ ሞተበት የሥጋ ደዌ ገላ የማሰሻ ሐሳብም በሀገሪቱ የተፈጠረው እንቅስቃሴ የማይሰማው ቡድን ሆነ። በዘፈቀደ ይንቀሳቀሳል። በቡዙም ይኖራል።

በእንቅልፍና በንቃት፥ በቅዠትና በውን መካከል አንዳንድ ጊዜ ብቻ አንድ ነገር በሚገባ ያስታውሳል። በቦርሳው ውስጥ ያእልውን የገንዘብ መጠን በየጊዜው እያወጣ በደነዘ አስተሳሰብ ይቁጥረዋል። እየሳሳ በሄደ ቍጥር ከውስኪው ወደ ኮኛክ፥ ወደ ቀጠና አራት ተሻገረው። ግን ባለሰሌን ቪኖ የሚያሞቅ በጕሮሮ ሲወርድ የሚያቃጥል ሆኖ ስላገኘው አላረካውም። ሌላ አማራጭ ፈለገ።

ማስረሻ አንድ ቀን በቦዘ አእምሮ ቦርሳውን እየፈተሸ ከቴዎድሮስ አደባባይ ወደ ተረት ሠፈር በሚወስደው አስፋልት መንገድ ሲያልፍ በከሰል ሱቅና በአሮጌ የሸንት ቤት ዕቃ መሸጫ መካከል ተጣብቃ፥ ከቦርሳዋ ላይ «ጥሩ ጠላ አለ» የሚል የካርቶን ሰሌዳ የተለጠፈባት ጣሳ ቤት አገኘ። «የአገር አረቂ አለ?» ሲል ጠይቆ ገባና የዘወትር ደንበኛ ሆነ።

አንድዋ ክፍል ቤት መካከል ላይ በጨርቅ መጋረጃ ተከፍላለች። ከመጋረጃው ጀርባ፥ የሸቦ አልጋ የተዘረጋበትና ሌላውም የመኝታና የምግብ ቁሳቁስ ያለበት ነው። ከኋለኛው ግድግዳ ወደ ጕሮ የሚያስወጣ በር አለ። ከመጋረጃው ወዲህ ሲገቡ በስተግራ ግድግዳውን ተጠግቶ ባለው የጣውላ ጠረጴዛ ላይ ባዶ ጠላና አረቂ የተሞሉ ጠርሙሶች፥ የተደፉ ብርጭቆዎችና መለኪያዎች ተደርድረውበታል። በጠረጴዛውና መጋረጃው ገለጥ ብሎ በሚከፈትበት በአልጋው ራስጌ መካከል ባለቤቷ የሚቀመጡበት የሳንቃ ሳጥን አለ። መቆርቆሩ ሲበረታባቸው አሮጌ ትራስ ጣል ያደርጉበታል። ከቀኝ በኩል የደንበኞች ማስተናገጃ አንድ አግዳሚ ሳንቃ አንድ ያዘመመ ታጣፊ የእንጨት ወንበር፥ አንድ በጨርቅና በድብዳብ የተሞላ ካርቶን ይገኛል።

ማስረሻ ገብቶ በካሮትንዋ ላይ በተቀመጠ ቍጥር ባለቤቷ ከበሬታ የሰጡት እየመሰላቸው «ኧረ ወንበርዋ ትሻልዎታለች» ይሉታል። እሱ ግን ዘርፈጥ ብሎ ሲቀመጥ ስለሚመቸው ከአላፊ አግዳሚው ከለ ያለ ቦታ ስለሆነ ካርቶኑን ይመርጣል።

ከሰዓት በፊት ከእንቅልፉ እንደ ተነሣ በመሄድ ብዙ ጊዜ ገበያውን ገድ የሚልላቸው ማስረሻ ሆነ። አንዳንድ ጊዜ ከማስረሻ የሚቀድመው ገና ሳይገባ «ወይዘሮ ፋንቱ አንድ ድርብ ቡልኮ» ሲል የሚታራው ገብሬ የሚባለው የመንገዱ ልብስ አጣቢ ነው።

«የሩቁን አቅርበው የቅርቡን ሳበው፥ አንተ ታውቃለህ» ብለው በመጸለይ ቀድተው ይሰጡትና «ዛሬ ገበያዬ ደርቶ ነው የሚውለው» ይሉታል። በደንበኝነቱ እየተለማመዱ ከሄዱ በኋላ።

«ገድ ነኝ ማለት ነው?»

«ምን አንድና ሁለት አለው። ሎተሪ ነዎት እንጂ።»

«አዬ ሎተሪማ ከስንቱ ሽህ ለአንዱ ብቻ ነው የሚደርሰው።»

«የሚደርሰው ማለቴ ነው።»

«ለእኔ ግን ደርሶኝ አያውቅም።» አረቄውን በሰፊው ይጕነጭለታል ፡

«እሱ አንድዬ እንደ መደበለት ነው። አንዱ ለሌላው ገስ እንው። አንዳንዱ ደግሞ ለራሱ የታደለ ነው።» ጭውውታቸው ግን ከዚህ ብዙም አይገፋም። ማስረሻ የሚፈልገው ዝም ብሎ በመጠኑ ለማተኮር ነው። ወዲያውም፥ ከባለቤትዋ ጋር ይበልጥ የሚተዋወቁት የረጅም ጊዜ ደንበኞች ግንበኞች አናጢዎች የቀን ሙያተኞች ደላሎች ይመጡና ጭውውቱ በእነርሱው መካከል ብቻ ይወሰናል።

ከብር ባነሰ ወጪ አንድ ሦስቱን መለኪያ አጋብቶ አልኮሉ በመላ ደም ሥሩ ተሰራጭቶ ሞቅ ፍዝዝ ሲያደርገው አእምሮውን ሲያቦዘው ይወጣና ቸርችል ጐዳና ወይም ከሚጠጣበት ሠፈር ቤንዚን ማደያ ከሚያቆማት መኪናው ውስጥ ገብቶ ይቀመጣል። ሲጋራውን እየማገና በሲጋራ ጢስ እየታፈነ፥ ወይም እየተወላገደ በሰፈሩ በእግሩ ሲንከራተት ይቆያል። ከሁለት ሦስት ሰዓት በኋላ በደም ሥሩ ያለው አልኮል ከሚፈልገው መጠን ሲቀንስ የጥሪ ደወል በሰውነቱ ውስት ያቃጨለ ይመስል እግሩ ወደ ጣሳዋ ቤት ይስበዋል። አሁንም ሁለት ሦስቱን ይቀነድበዋል። ቤንዚኑ እንደሚያልቅ ተሽከርካሪ የማስረሻ ገላ ያለማቋረጥ መሞላት ነበረበት።

ለሠፈሩ አዲስ ከመሆኑ ጋር በቀን ሦስት አራት ጊዜ መመላለሱ ለሌሎች ደንበኞች ትንሽ እንቆቅልሽ ሳይሆንባቸው አልቀረም። ወጣ ሲል ይጠያየቁበታል።

ይህ ሰው አንቺን ሊነጥቀኝ ይሆን ወይዘሮ ፋንቱ? - ሲል ገብሬ ይቀልዳል።

-ኧረ ሞት ይንጠቅህ! - ሲሉ ወይዘሮ ፋንቱ በቀልድ ይቆጣሉ።

-ታዲያ ምን ያመላልሰዋል? —

-ሊጠጣ - ሊጠጣ ነዋ!

-ማ - ይሙት ከድፍን አዲስ አበባ የፋንቱ አረቄ በልጦ ነው? እኛ እንደሆነ መቼም ስለ ለመድነው ባጣ ቆየን አድርገነዋል።

-አትሄድም የተሻለ ካለበት! ማን ከለከለህ? እኔ ፋንቱ እንደሁ እጄን ስሞ የሚጠጣልኝ ያጣሁ መሰለህ?

-እኔ ደግሞ ጉንጭሽን ስሜ ነዋ!

-ኧረ ይድፋህ!

-ካላችሁስ አውቶሞቢል አለ። ከጣሳ ቤት ምን አስገባው? - ሲል ሌላው ለጠቅ ያደርጋል።

የተለያዩ መልሶች ይቀርባሉ።

-ሲ. አይ. ዲ. እንደሆነ። ከዚህ ሠፈር የሚፈልገው ሰው ይኖራል።

-እንዲህ እየጠጣ ምኑን ፈልገው።

-እኔ ገብሬ እንደ ሆንኩ በዚህ እጄ ሠርቼ የማድር ነጣ ነኝ። ምን አስፈራኝ!

-ወይም ራሱ በመንግሥት የሚፈለግ ይሆናል። ይኸውና የነበረው ሁሉ እየተለቀመ እየገባ አይደል? በሱ

ቤት ከእኛ ቢጤዎች ተቀላቅሎ መደበቁ እንደ ሆነስ??

-ነግሬሻለሁ ፋንቱ፤ ተጠንቀቂ አብረሽ እንዳትለቀሚ!

-ኧረ? - ሲሉ ወይዘሮ ፋንቱ ደንገጥ ይላሉ።

-ቢሆንስ ምን አገባን? አያቀን። አናውቀው። መጣ። ጠጣ። የራሱ ጉዳይ ነው። ወይም የከሰረ ነጋዴ ይሆናል። እየተበሳጨ የሚጠጣ። ታዲያ ምን አገባን - በማለት ሌላው ያጽናናቸዋል።

ማስረሻ እንደገና ነዳጅ ለመሙላት ተመልሶ ሲጠጣ፥ «ኖር» ሲሉ የአክብሮት አቀባበል አድርገውለት ጨዋታቸውን ይቀይራሉ።

ነገር ግን በጉሪጥ ማየትና መተያየት ቀርቶ እየሰማ በይፋ ቢያሙትም ደንታ አልነበረውም። እንደ ግዑዝ ተሽከርካሪ ነዳጅ እየሞላ ቀኑን ለመግፋት ነው የሚፈልገው። ከዚያ ለተረፈው አለኝታ ሞቷል።

ለቤቱ ሕይወትም እንደዚሁ የሞተ ነው። ውድቀት ላይ ቤቱ የሚገባው ጥቂት ጀርባውን ለማሳረፍ ብቻ ነው። በአልኮል ሲዘፈቅ የዋለው ሰውነቱ እንቅልፍ ሲያሰኘው....መቆም ሲደክመው መቀመጥ ሲታክተው እየተንገላወደ ገብቶ ከአልጋው ላይ ይዘረጋል። ዘለቃም የት ዋልክ የት አመሸህ ብላ አትጠይቀውም። መነጋገር ትተዋል። እንዲያውም የሚተያዩት እንደ አጋጣሚ ከስንት አንድ ቀን ነው። መኝታዋን ወደ ሌላ ክፍል አዛውራለች።

በየዕለቱ ገብታ ትደርም አትደርም አረጋግጦ አያውቅም። በቦዘ ሐሳቡም አልመጣም። ገረዲቱ ሳትቀር አትታይም። በሩ ይከፈትለታል። አልፎ አልፎ ከጠረጴዛው ላይ ወይም ከአልጋው ኮሞ ላይ ምግብ ተከድኖ ያገኛል። የሰው እንቅስቃሴ ግን የለም። ቤተሰቡ በየፊናው የተበተነበት በየጉራው፥ የተሰማራበት ቤት ነበር። ማስረሻ ግን ደንታ አልነበረውም።

አንዳንድ ቀን ጧት ሲነቃ ከኮሞው ላይ ብሮች ተቀምጠውለት ያገኛል። አልኮል ባደነዘዘው አእምሮው - አንድ ጊዜ ከተኛ ጅብ ተሸክሞት ቢሄድ አይሰማምና - ማን እንደሚያስቀምጥለት አያይም። ግን ዝለቃ እጅግ ሌላ ሊሆን አይችልም - ሲጋራ መግዣ እንዳይቸግረው ብላ ነው? ወይም መጠጣቱን እንዲቀጥልበት ማደፋፈርዋ ነው? አሃ! ፉዞ እንድሆንላት ትፈልጋለች? - አለ ከራሱ ጋር የመጀመሪያው ቀን። ግን አልተከፋም። ዓላማው ምንም ይሁን ቦርሳው እየሳሳ ሲሄድ ብር ተገኝቶ ነው?? እንዲያውም ከጊዜ በኋላ ጧት ከኮሞው ላይ ብር ሲያጣ ቅር መሰኘት ጀመረ።

በዚህ ዓይነት ጥቂት ሳምታት አሳለፈ። አንድ ቀን ረፋድ ላይ ከእንቅልፍ ሲነቃ የመኝታ ክፍሉ ለወጥወጥ ብሎበት አገኘ። የሚያየው ነገር በሕልሙ መሆኑንና አለመሆኑን ለማጣርት ይመስል ዓይኑን ጨፈን ገለጥ አደረገ። የዞረ ድምር ጭንቅላቱን ቢከብደውም ፍጹም ነቅቶ ነበር።

በእግጥም ለሠርጋቸው በስጦታ የተቀበሉት የፋርስ ምንጣፍ ከወለሉ ላይ ተነሥቶ ወንደላጤ ሳለ ይጠቀምበት የነበረው ብጣሽ አሮጌ ምንጣፍ ከአልጋው አጠገብ ተነጥፏል። ከሞዝቮልድ የተገዛው አዲሱ ቁምሳንጥና የእርሱ ቅንጅት የሆነው የውስጥ ልብስ ማስቀመጫ ኮሞ የለም። ዓይኑን ማመን እያቃተው

ወደ ሳሎን አመራ። ማድቤት ተቀምጠው የነበሩት የእርሱ አሮጌ ፎቴዎች ተተክተውበታል። ወይዝሮ ሸዋዬ ያበረከቱዋቸው እስቴርዮ ካሴት ቴፕሪከርደርና እንደዚሁም ሌላው በስጦታ ያገኙት ባለ ሦስት እግር የሳሎን መብራት የለም። ቴሌቪዥኑ ብቻ አለ። ማስረሻ አሁንም ለማረጋገጥ ዓይኑን በጣቱ አሻሽቶ በመበልጠጥ ተመለከተ። የጐደለውን የቤት ዕቃ በዝርዝር ሊያውቀው አይችልም። ከድሴ ከተመለሰ ወዲህ የቤቱን ሁናቴ በሚገባ አስተውሎት አያውቅም ነበርና ግን፥ አሁን ሲያየው ወና መሰለው። መቼ ነው ይህ ሁሉ የሆነው? ሌሊት ነው? ወይስ ማታ ስገባ አላየሁትም ማለት ነው? ሌባ ነው? ሌባ ቴሌቭዥን ትቶ አይሄድም። ዘልቃ የምተኛበትን ክፍል ከፈት አድርጎ አየ። ሰውም አልጋም የለበትም። «አሃ! ነው!» አለ ራሱን እየነቀነቀ፡

ከአልጋው ኮሞ ላይ የተለመዱት ብሮች ተትተው እንደ ሆነ በማለት ለትዝብት ያህል ሲመለከት የተጣጠፈ ወረቀት የሲጋራ መተርኮሻው ተጭኖበት አገኘ።

ወረቀቱን የያዘበት እጁ እየተንቀጠቀጠ ያነብ ጀመር.....

«....ይህንን ደብዳቤ ስታነብ ምን እንደምትል ይገባኛል። እኔን ለመስደብና ለማውገዝ የአማርኛ ቃላት አልበቃህ ሲሉ ይሰማኛል። ግን ለምን? ብዬ እኔ ጥያቄውን ላቅርብልህና ፈረንጅ አገር ተምሬአለሁ ካልህ ትንሽ ተመራመርበት። ባትመራመርም ግዴለኝም። ምክንያቱም እንደ ሰሞኑ አኳኋንህ መመራመር የምትችል አልመሰለኝም። ግን አንተ ባትችል እኔ በበኩሌ ያለኝን አስተሳሰብ ልንገርህ።

«መቼም እንደምታውቀው በዚህ ዓለም ሁላችን የምንኖረው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አንድ ግዚኤ ብቻ ከኖርን ምን ማለት ነው? አንድ ሕይወት ብቻ አለን ማለት ነው። ሌላው እንደ ፈለገ ስለ ሞራል፥ ስለ ግብረገብነት፥ ስለ ጽድቅ ሊያወራ ይችላል። እኔ ግን ይችን አንድ ብቻ የሆነች ሕይወቴን በደስታና በምቾት ሳሳልፋት እፈልጋለሁ። በዚህ ዓላማዬ ማንም ሊያግደኝ አይችልም። ትዳርም ቢሆን አንዱ ለሌላው ደስታና ምቾት ሰጥቶ እንደዚሁ ምቾትና ደስታ የሚቀበልበት መሆን አለበት። ካለበለዚያ እንደ እሥር ቤት እቁጥረዋለሁ። እሥር ቤት ደግሞ አልፈልግም። ከልጅነቴ አንሥቶ እንዳሻኝ መሆን፥ የፈለግሁትን ማድረግ የምወድ ነኝ። ፍቅርንም በሚመለከት ረገድ ቢሆን.....

«ምክንያቱም አንድ ጊዜ በፊልም እንዳየሁት አንድ ሰው ብዙ ሰዎችን ሊያፈቅር ይችላል። አንዱን በፈገግታው አንዱን በመልኩ፥ አንዱን በጠጉሩ አንዱን፥ በአነጋገሩ አንዱን በአደናነሱ፥ አንዱን በችሎታው.....ስለዚህ በየመልኩ ደስታ ይገኛል ማለት ነው። ታዲያ ይህ ከሆነ ትዳር መያዝ ለምን ፈለግሽ? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። ትዳር መያዝ የፈለግሁት ለትዳር ለራሱ ስል አይደለም። አንተን ያገባሁት ግን ምክንያት ነበረኝ። ከፍ ብዬ እንዳልኩት ከአንተም የምወደው ነገር ሊኖር ይችላል። ብቻ አሁን ይህ ነው ብዬ መጥቀስ አልፈልግም። ሌላው ምክንያቴ ግን እውነቱን ልንገርህ ትምህርትም ችሎታም ስላለህ የምትሾም መስሎኝ ነው። በሹመት በዕድገት ምቾት ይገኛል። እንደ እኔ እምነት ዋና ደስታ የሚገኘው በምቾት ነው። ይህ ዕድል ተሰጥቶህ ነበር። ግን ልስፍስፍነትህ የትም እንደማያደርስህ አየሁት። ልፍስፍስ ጠባይ ያስጠላል። ወንድ ልጅ ሆኖ መልፈስፈስ.....

«የራስክን ደካማነት ሳታውቅ ሰሞኑን ሲያብከነክንህ የነበረው የእኔው ሰው ጥየቃ ጎፋ ሠፈር መመላለስ። እናንተ የሞራል ሕግ የምትሉት ነገር ነው እንጂ ከመሠረቱ ምን የሚያገባህ ነገር ነበር? አንተን ጐዳሁህ? የአንተን ጥቅም ነካሁ? በራሴ ስሜት በራሴው ሰውነት የፈለግሁትን ብሠራ ሌላውን

እስከ አልጉዳሁ ድረስ የራሴው ጉዳይ ነው። እንደኔ ቅናት ሌላው፥ የእኔ ብቻ ይሁን ማለት ነው። ይህ ደግሞ የሌላውን ጥቅም መንካት ነው።

«ቅናት የምትለው ከአንጎልህ ጨርሶ እንዲወጣልህ፥ ጎፋ ሠፈር ማንን ልጠይቅ እንደምሄድ ልንገርህ? ጓንጉልን ነው። አሁንም ትዕግሥት ይኑርህና ሆቴሉ ውስጥ የነገርኩህ ሁሉ ውሸት ነው። እኅት የለኝም። ከጓንጉል አር ግን ከአንተ በፊት እንተዋወቃለን። መኪናዬን የገዛልኝ እሱ ነው። ሥራ ያስያዘኝ እሱ ነው። ሌላም ብዙ ነገር አድርጎልኛል። አሁንም ኢ.ሲ.ኤ ደህና ቦታ ሊያስቀጥረኝ ነበር። የሠርጋችን ቀን ግን ከእርሱ ጋር ምንም አላደረግንም። እንዲሁ ለመጫወት ነበር የሄድኩት። አንተ ግን እንደዚያ ሆንክ። ምንስ ባደርግ ኖሮ? እናንተ በጋብቻ ላይ ማመንዘር የምትሉት ሕግ አለ እንጂ (እኔ አላምንበትም) በእኔ ሰውነትና ስሜት ላይ ማንም ሞኖፖል ሊኖረው አይገባም።

«ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንምና ነገር አላበዛም። ግን አሁንም ደግሞ አንድ ነገር ላስታውቅህ እፈልጋለሁ። እኒኤ ሕይወቴን የምመራበት ዓላማ አለኝ። የአንተ ሁናቴ ግን ለዚህ የሕይወት ዓላማዬ የሚስማማ ሆኖ አላገኘሁትም። ስለዚህም ካለ አንድ ጊዜ በስተቀር ድጋሚ የማላገኛትን ሕይወቴን እንዳስፈለገኝ እመራታለሁ። አንተም እንደ መሰለህ ሕይወትህን ምራት። ሕይወቴ የራሴ ናት። ሕይወትህ የራስህ ናት። በመካከላችን ጠብ የለም!

ደህና ሁን

ያንተው ዘለቃ።»

«ያንተው» የሚለው ቃል ብቻ እንደ እብድ አሳቀው። «ቀልደኛ ሽርሙጣ!» አለ።

## ፳

«አንቱ! አንቱ!» አሉት የታሳ ቤቷ ባለቤት ማስረሻን ትከሻውን ነቀነቀው ለማንቃት ፈርተው በጣታቸው ነካ እያደረጉ።

«እህ!» አለ ማስረሻ የተደፋ ጭንቅላቱን ለማቅናት እየተንገዳገደ። «መሽቶብዎታል በጊዜ ይሂዱ?» አሉ ባለቤቷ።

«ምምን?» አለ ማስረሻ በሚያንኳርፍ ድምፅ። «ስ - ስ - ሰዓት ስንት ነው?» እየተጨናበሰ ሰዓቱን ለማየት ሞከረ። በቀኝ እጁ ግራውን ደግፎ ያነበበ እየመሰለ፥ «ስንት ሰዓት ነው? ገና ሁለት ሦስት አራት።» ማንበብ ሲያቅተው ዓይኑን ጨፈን ገለጥ እያደረገ፥ «ቢ - ቢሆንም ሰዓት ዕላፊ ገና ነው።»

«እሱማ ገና ነው። ግና ወደ ቤትዎ ለመሄድ ይመሽብዎታል። በአሁኑ ጊዜ ከመሽ በኋላ መዘዋወር ጥሩ አይደለም» ሲሉ ወይዘሮ ፋንቱ እጃቸውን አጣምረው ቍልቍል ተመለከቱት። ምሽቱ እስከዚህም አለመግፋቱን አላጡትም። ተመለከቱት። ምሽቱ እስከዚህም አለመግፋቱን አላጡትም። ግን ሁናቴው አላማራቸውም ነበር። እንደ ወትሮው ወጣ ብሎ ቆይቶ በመመለስ ፈንታ ቀኑን ሙሉ መጠጡን ፋታ ሳይሰጥ ነው ሲጋተው የዋለው። ሁለት ጊዜ ያህል የወጣው ፊኛውን ለማስተንፈስ ብቻ ነበር። ባፉ እህል አልዞረም። ወደ ማምሻው ሰውነቱ ዝሎና ተዝለፍልፎ አንገቱን ይደፋ ጀመር። ከተቀመጠበት እንደ መንገዳገድም ይላል። እያንጐላቸ ብንን እንደሚል ሰው አንገቱን እንደ ምንም ቀና

አድርጎ በተሳሰረ ምላሱ፥ «አ! እስቲ ይ - ይቸምሩልኝ» ሲል በከንፈሩ ዳርና ዳር ላሃጭ ይፈልቃል ። በተረፈ አረቄውን ለመጉንጨት ስንኳ የሚሞክረው ዝናም እንደ መታት ዶሮ አንገቱን ደፍቶ እንደ ተስለመለመ ነበር። ግማሹ ከጠረጴዛው ላይ ግማሹ ከልብሱ ላይ ይፈስሳል። ሌሎች ደንበኝኖች፥ እነገብሬ ሳይቀሩ ሳይቀሩ እጅግ በመገረም ራሳቸውን ሲነቀንቁና ከንፈራቸውን ሲመጡለት ውለዋል።

ማስረሻ ጠጥቶ በሰላም እንደሚሄድላቸው እርግጠኛ ቢሆኑ ኖሮ እስኪ ዘጉ ድረስ ሲጠጣ ቢቆይ ወይዘሮ ፋንቱ ግዴላቸውም ነበር። ጣሳ ቤት የከፍቱት በተቻለ መጠን ሸጠው ለማትረፍ እንጂ ደንበኛቸው በመጠኑ እንዲጠጣ ለምክር አይለም። ስለ ራሳቸው ኑሮ ማን አሰበላቸውና? ስለ ሌላውስ ሕይወት ምን ዶላቸው? የስካር ጠባዩን የማያውቁት አዲስ ደንበኛ ግን ያሳስባቸዋል። ከመሬት ተነሥቶ አምባ ጓሮ የሚያነሣ ሊሆን ይችላል። ዕቃ የሚሰባብርም አለ። ጸያፍ ብልግናው አውሬ የሚያስመስለው ሞልቷል። ማስረሻን ከዚያ በፊት ሲጠጣ መጥፎ ጠባይ ባያዩትም እንደ ዛሬው ጠጥቶ እንደ ዛሬው ሆኖ ደግሞ አላዩትም። በዚህ ላይ በአስቸኳይ እጃቸውን እንዲሰጡ የተሻሩት ባለሥልጣኖች ስም እየተደጋገመ በራዲዮ መነገሩ በመንደሩ ሲወራ ውሏል። ማስረሻ ስንኳ ባለሥልጣን የነበረ መሎ አይታያቸውም። ግን ማን ያውቃል? ከነገሩ ጦም እደሩ ተብሏል።

«ይበሉ ይነሡ እንጂ!» ሲሉ ወይዘሮ ፋንቱ እንደገና ጠየቁት። «በር ልዘጋ ነው።»

«ይዝጉታ!» ሲል መለሰ ማስረሻ ከተቀመጠበት መውደቅ እየቃጣው።

አሁን ከአሁን ይነሣል ብለው ጥቂት ጠበቁት። «ይበሉ እንጂ!»

«በሩን እ - እንደሆን ይከንቸሩት። እኔ ከዚህ ነው የማድረው!»

«ኧረ እቴ፥ ምን ነካዎት ዛሬ?» ወይዘሮ ፋንቱ እንደ መቆጣትም እንደ መገረምም አሉ።

«ምን አለበት? ተቾንከር መግባት በኔ አልተጀመረ። ወይስ ከኔ በፊት ተቾንከር የገባ አለ? ካስፈለገም እኸይዳለሁ!» ንግግሩ ትከሻውን የከበደው ይመስል ማስረሻ ከወዲያ ወዲህ ተንገዳገደ።

ማስረሻ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ፥ ጥልቅ ጉድጓድ በመሰለ የአእምሮ ጨለማ ውስጥ፥ ከዱርየዎች ከቦዘኔዎች ከለማኞች የባሰ ምን ያህል ከኅብረተሰቡ አቂልቁሎ እንደ ወደቀ፥ ራሱን ምን ያህል ከሰው በታች እንደ ጣለ እንደ ሕልም ደብዘዝ ብሎ እንደ ቅዠት ተዘበራርቆ በስመመን ይታየው ነበር። ግን ከአዘቀጠበት ለመውጣት ብርታትም ፍላጐትም አላገኘም። በደብዛዛው ሩቅ አእምሮ ፖህ! ዘለቃም ሽርሙጣ ይህችም ሽርሙጣ ያችም ሴት ይህችም ሴት ሲል ራሱን በማባበል አዳልጦት እንደ ወደቀ ልጅ በጭቃው ውስጥ መንከባለሉን መረጠ። «አ - አልወጣም ብልስ!» አለ።

ወይዘሮ ፋንቱ በአዘኔታም በንዴትም አስተዋሉት። «እንደ ፈረደብኝ ፖሊስ መጥራት ነዋ!»

«ፖ - ሊ - ሽስ - ፖሊሽስ? ከረብሻ እንጂ ምን ቸገረኝ - ሺተውት ይከራል ያለከለት ፍክር።» ተነሥቼ እቆማለሁ ሲል አውሎ ነፋስ እንደ ነካው ዛፍ ተጥመለመለና ወደቀ። ብርጭቆ ተሰበረ።

«ውይ!» ወይዘሮ ፋንቱ የሚዝለፈለፍ ሰውነቱን እንደ ምንም አንሥተው ከካርቶኑ ላይ አስቀመጡት።

«አዝናለሁ!» አለ እንደገና ለመውደቅ ወደ ጐኑ አጋድሎ።

ወይዘሮ ፋንቱ የወዳደቀውን ዕቃ አነሣስተው በአንድ ልባቸው ለዚህ ዕድል የዳረጋቸውን እያማረሩ አሰቡ። አዘኑ። ስለ ራሳቸው ሕይወት ማን አሰበ? ማን አዘነ? ማን ነበረ? ማንም። ለማያውቁት ደንበኛ ለማስረሻ ከንፈራቸውን እየመጠጡለት ለራሳቸው ሕይወት የሚበጀውን መወሰን ግድ ሆነባቸው።

ማስረሻ የሁካታ ብዛት ትንሽ ነቃ አድርጎት ቀና ሲል አሁንም ዝብርቅርቁ በወጣ ደብዛዛ ምስል ብዙ ሰዎች ከበውት አየ። የሚጠማዘዙ የሚያጥሩ የሚረዝሙ፥ የሚጣመሙ ምስሎች።

«ምን ወንጀል ሰራሁ?» በማለት ጠየቀ፥ ለመንቃት ራሱን እየነቀነቀና ዓይኑን ከደን ከፈት እያደረገ። መስከሩ አሳምሮ ይታወቀዋል። እንዲያውም እራሱን የሚያየው ከራሱ ውስጥና ከራሱ ውጭ ነው። ሲዘቅጥ ሲሰምጥ ይሰማዋል። ውኃ ውስጥ እንደ ሰመጠ ያህል። ወደ ላይ ለመውጣትና አየር ለማግኘት ይፍጨረጨራል። ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ዓይነት። በሌላ በኩል ከአዳራሽ ውስጥ ተቀምጦ ሌላው ራሱን በመድረክ ላይ ያየዋል። የአሁኑ ብቻ ሳይሆን ያለፈው ሁሉ ተጠቃልሎ እንደሚተረተር ፊልም ይመጣበታል። ሠርጉ፥ የጫጉላ ቤቱ ድርጊት ሹመቱ፥ የመጠለያ ጣቢያው ጉብኝት መሥሪያ ቤቱ ስብሰባና ተኩስ የጣሳ ቤት ደንበኛነቱ ይህ ሁሉ ድብልቅልቁ ወጥቶ በደበዘዘ አእምሮው ውስጥ አለፈ።

ማስረሻ አሁንም በስንት ጭንቅ ተነሣና ለመራመድ ሲሞክር ሊወድቅ ተንገዳገደ። «ከመኪናዬ መድረስ ብቻ ነው የምፈልገው» አለ። ወይዘሮ ፋንቱ ከፊት ለፊቱ እየመሩ፥ ሁለት ጐረቤቶች ግራና ቀኝ ደግፈው ከመኪናው አደረሱት። በአንድ እጁ መኪናዋን ተደግፎ እንደ ምንም ከፍቶ ገባ። ሞተር ከማስነሣቱ በፊት ለጥቂት ጊዜ ያህል ሽልብታ ይዞት ቆየ።

፮

ማስረሻ የቸርችልን ጐዳና የወረደው በደብዛዛ የእንቅልፍ ልብ ዓይነት አነዳድ ነው። ሌላው ቀርቶ

የመንገድ ዳር መብራቶች በሚገባ አይታዩትም ነበር። ዓይኑን አሥር ጊዜ ቢጨምቅም አገር ምድሩ ዳመና የለበሰ ሆነበት። የትራፊክ መብራቶች አልጠበቀም። ጨርሶ አልታሰበውም። ሐራምቤ ሆቴል ከመስቀለኛው መንገድ ላይ ቀኙን ትቶ በግራው መንገድ ውስጥ ገባና ወደ ካዛንቺስ አመራ። ከፊት ለፊቱ የሚመጡት አውቶሞቢሎች፥ መብራት እየለዋወጡ ጥሩምባ እየነፉ ሕይወታቸውን ለማዳን ከመንገዱ እየወጡና እየጮሁበት ሲያልፉ መንገድ መሳቱ ጥቂት ታወቀውና ፍል ውኃ ላይ አግጣጫውን ያዘ። መብራቶች እየደበዘዙበት መንገዱ እየጨለመበት በደመ ነፍስ እጁ መሪ ጨብጦ ቀኝ እግሩ የቤንዚን መስጫውን ረግጦ፥ ድሮ ደንበኛው የነበረውን የኖቸን ቤት እልፍኝ እንዳለ፥ እንደ ፈነዳ ቦምብ በሚመስል ከፍተኛ ድምፅ ከአንድ ነገር ጋር ሲላተም ተሰማው። አንድ ግዙፍ ነገር ከአውቶሞቢሉ ኮፈን ላይ ነጥሮ ሲወድቅና የፊቱ መስታወት እንክሽክሽ ሲል አንድ ሆነ። አውቶሞቢሏ ለአንድ አፍታ ተንቀጠቀጠች። ማስረሻም ድንገት በጥፊ እንደ ተመታ ከደብዛዛ የሰመመን ዓለሙ በመጠኑ ብንን ብሎ ወጣ። የደረሰው አደጋ ምን እንደሆነ አላወቀም። ለማወቅም ደግሞ አልቆመም። በዚህ ሠፈር አይጠፉም የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ድንጋይ ወርውረውብኝ ይሆን? ወይስ ግጭት ነው? ግጭትም ከሆነ ውሻ ወይም ሌላ እንስሳ መሆን አለበት። ሰው ዓይኑ እያየ መኪና ጉማ ሥር አይገባም - ሲል ራሱን እያጽናና ጉዞውን ሲቀጥል ከወደኋላው የኡኡታ ድምፅ የሰማ መሰለው። ሰውነቱ እንደ መንቀጥቀጥ እየቃጣው ፍጠንት ጨመረ።

## ፯

ማስረሻ በአስተሳሰብ ጨለማ ውስጥ ተዘፍቆ በሚዳክርበት ወቅት የተገታ መስሎ የቆየው የዓመፅ ማዕበል እንደገና ተጥለቀለቀ። ትናንት የማይነኩ የማይደፈሩ ይመስሉ የነበሩት መኳንንትና መሳፍንት በር እየሰበረ ገባ። ውስጥ ውስጡን ሲታመስ የቆየ ቢሆንም ከላይ እንደ ክብሪት ተመስሎ የለኮሰው የአንድ የፓርላማ እንደራሴ አድራጐት ነበር። በወደቀው ኮሚቴ ዘመነ መንግሥት ለሕዝብ የቆመ ነው ተብሎ የሚነገርለት ሻለቃ ቢልልኝ የተባለ እንደራሴ ስምንት እንደራሴዎች የሚገኙበት የልዑካን ቡድን እየመራ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር በመሄድ በሽህ ለሚቆጠሩ ወታደሮች ንግግር አደረገ። ንግግሩ በአቃቤ ሹም ጉንጤ ላይ ያመፀውን ወታደር ቀርቶ ማንንም አድማጭ የሚያስቆጣ ነበር። ተወክሎ የተላከ ይመስል በመላው የመምሪያው ምክር ቤት ስም፥ አቃቢዔ ሹም ጎንጤን ጨምሮ የታሠሩት ሹማምንትና የመንግሥታዊ ድርጅት ኃላፊዎች እንዲፈቱ ጠየቀ።

ወሬው ሲሰማ ፓርላማው ታመሰ። ማን ላከው? ምን አገባው? በበነጋው በአጀንዳ ቀርቦ የነበረው ጉዳይ ሁሉ ቀጥ ብሎ ፓርላማው ቀኑን ሙሉ በሻለቃ ቢልልኝ አድራጐት ውግዘት ተሰነዘረ። ከብዙ ሁካታ በኋላ ቢልልኝና ጓደኞቹ ለአንድ ሣምንት ከፓርላማ ወንበራቸው ታገዱ።

በመለዮ ለባሹ ሠፈር ግን ጉዳዩ በቃላት ውግዘት ተወስኖ አልቀረም። የትዕግሥት ቀጭን ክር መበጠሻ ሆነ። በኮሎኔል አለማየሁ ይመራ የነበረውና የልጅ ጉግሣ ቀኝ እጅ የነበረው የጦር ኃይሎች ኮሚቴ ድንገት ሳይታሰብ በመሠረታዊ ለውጥ ፈላጊዎች ቁጥጥር ሥር ገባ። በዚህ ኮሚቴ ትዕዛዝ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ የኢትዮጵያ፥ ቴሌቪዥን የብሥረተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያና ሌሎችም የሕዝብ መገናኛ ድርጅቶች በወታደራዊ ጥበቃ ሥር ዋሉ። ሌሎች ወታደሮች ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች ያዙ። የስም ዝርዝር የተሰጣቸው ደግሞ ወደሚፈልጉ ሰዎች ቤት ተሠማሩ።

«ምን አዲስ ነገር መጣ?» ሲል ልጅ ጉግሣ ጠየቀው።

«ለጊዜው ስብሰባውን ብናቋርጠው ይሻላል።» ጄኔራል መብረቁ ሁሉም እንዲሰሙ አልፈለገም። አንደኛ፥ የተፈጠረው አዲስ ሁናቴ በትክክል ምን እንደሆነ አላረጋገጠም። ሁለተኛ፥ አንዳንዶቹ የኮሚቴ አባላት ደንግጠው በመበርገግ ነገር ሊያበላሹ ይችላሉ። ልጅ ጉግሣን በዓይኑ አመለከተው።

«ይቅርታ ሌላ ጊዜ እንሰበስባለን እንግዲያው» ልጅ ጉግሣ ስብሰባው ማብቃቱን ለመግለጽ ከሊቀ መንበር መቀመጫው ብድግ ብሎ ቆመ።

«ወታደሮች እንደገና አገርሽቶባቸው አምፀዋል» አለ ጄኔራል መብረቁ ከራስ ዠማነህ ጋር ሦስቱ ከቀሩ በኋላ በሌባ ጣቱ ጠረጴዛውን እየቆረቆረ።

«ምን ጠየቁ ደሞ አሁን?»

«መጠየቅማ የወግ ነው። በከተማው ተሰማርተው ሰውን ሁሉ እየያዙ በማሠር ላይ ናቸው። ከእነ ጉንጤ ጭፍሮች እስከ አሁን ሳይያዙ የቀሩትን ብቻ ሳይሆን የእኛ ወገን የሆኑትን ጭምር። እኛም ሳያሠጋን አይቀርም።»

«ምን?» የራስ ዠማነህ አነጋገር ጥያቄ ሳይሆን የንቀት አንክሮ ነበር።

«ሐሳባቸው ምን እንደሆነ ገና አላወቅሁም። ስለዚህ መጠንቀቅ አይከፋም።»

«ኰሎኔል ዓለማየሁ የት ሄደ?» ሲል ልጅ ጉግሣ ጠየቀ።

«እሱማ አባይን ተሻግሯል። ጉሐ ፅዮን ሲደርስ ለባለቤቱ በቴሌፎን ነግሯት እስዋ ናት አሁን የደወለችልኝ። ምንም ማድረግ አልቻለም። የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ የሚባል አዲስ ቡድን ስለ ተነሣባት እጁን መስጠት አልፈለገም።»

«ምን ያህል ኃይል አለው ይህ ኮሚቴ?»

«አሁንም እርግጠኛ አይደለሁም። ምናልባት ስልሳ ሰባ ይሆናሉ ይባላል» በማለት ጀኔራል መብረቁ መለሰ። «እና፥ አራተኛ ክፍለ ጦር ነው ተሰብስበው ያሉት።»

«በአንድ ሻለቃ ጦር መያዝ ነዋ! ኮሚሽኑ ሊሠራው ይችላል» አለ ራስ ዠማነህ ፍርጥም ባለ አድነበት።

«ቀላል አይይመስለኝም።»

«ታዲያ ምን ተሻለ?» አለ ልጅ ጉግሣ በአብዛኛው ከራሱ ጋር። በየራሳቸው ሐሳብ ተውጠው ለጥቂት ጊዜ ያህል ሦስቱም ዝም አሉ። ከዚያም የልጅ ጉግሣ ዓይን፥ ከጠረጴዛው ከአንድ ጉን በኩል ከተቀመጠ ፋይል ላይ ሲያርፍ ሐሳቡ ብልጭ አለ። «ግዴላችሁም መንገድ አናጣም።»

ፋይሉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመደበልን የጦር ሜዳ አበል ቀርቶብናል ብለው አቤቱታ ያቀረቡት የኮንጎ ዘማች ወታደሮች ጉዳይ ነበር። እርግጥ የሚያስከትለው ወጭ በጣም ከፍተኛ ነው። ግን ቢሆንስ? በሙሉ ልብ የተሰለፈ ሁለት ሽህ ወታደር ቀላል ኃይል አይሆንም። ብዙ ነገር ይመልሳል። እንደ ገባቸው ሁሉ የሁለቱም ዓይን በፋይሉ ላይ አረፈና መልሰው ተያዩ።

፳

አረንጓዴዋ የፖሊስ መኪና በኮረኮንቹ መንገድ ሁለት ሦስት ጊዜ ስትመላለስ እነ ታረቀኝ በሚኖሩበት ግቢ ውስጥ ከአሥር የሚበልጡ ተማሪዎች ተሰብስበው መለዮ ለባሾች ስለ ጀመሩት አዲስ ንቅናቄ በመወያየት ላይ ነበሩ። ሁሉም በተማሪው ንቅናቄ ተደማጭነት ያላቸው ናቸው። ለክትትል ሠወር ያለ ስለሆነ ብዙ ጊዜ በእነ ታረቀኝ መኖሪያ ቤት በር ዘግተው ይሰበሰባሉ። የመለዮ ለባሾች አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥልጣን ከሁለት ከተከፈለ ወዲህ ግን ተዳፍረው የተሰበሰቡት ከውጭ ከባሕር ዛፍ ጥላ ሥር ነበር።

«መለዮ ለባሹ ምን ማድረግ ነው ያሰበው?»

«ማሠር ነዋ! ሌላ ምን ያደርጋል?» ሲል ቦጋለ ቀበል አድርጎ መለሰ።

«አንተ ደግሞ ማውራት የያዝከው ስለ መታሠር ሆኗል። እነ ጉንጤ ታሠሩና እኛን ምን አገባን? ይሰቀሉ እያልን ሰላማዊ ሰልፍ ያደረግንባቸው አይደሉም?»

«ሆነ አልሆነ ወደ ፊት የምናየው ነው።»

ቦጋለ የጕንጤ፥ ኮሚቴ አባላትና ጭፍሮች በቁጥጥር ሥር ከዋሉ ወዲህ ጉዳዩን ደጋግሞ እንደዋዛ አንሥቶታል። አልፎ አልፎም ቅሬታና ሐሳብ የገባው ሲመስል አይተውታል። ግን ሆነ ብለው ምክንያቱን ለመጠየቅ ጭንቀቱ ወይም የጠባዩ መለወጥ እስከዝህም ጉልህ ሆኖ አላገኙትም። ጕንፋን ሲይዝ ሆድ ሲታወክ ሊፈጠር የሚችል ያህል ብቻ ነበር። እሱም ራሱ አልነገራቸውም።

ባልንጀሮቹም በጥያቄው ሳይገፉበት ወደ ዋናው ጉዳይ ተመለሱ።

«እሺ እንግዲያውስ እኛ ምን ማድረግ አለብን?»

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ልጅ ጉግሣ በአፀፋው ምን እርምጃ ይውሰድ ይሆን?»

ውይይታቸው በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ይሁን እንጂ በተለይ የሦስቱ ባልንጀራሞች አእምሮ የሚያሰላስለው ወጥቶ ሳይመለስ ስለ ቀረው ስለ ካሣሁን ነበር። አርፎ ቤት እንዲውል አጥብቀው መክረውት ነበ። «አይ! እናንተ የሀገር ጉዳይ ፋታ ባይሰጣችሁ እኔ ዘይኔን ካላገኘሁ ምንም ልቤ አይረጋም» ብሎ አውቶቡስ ፌርማታ ቁጥርና የሠፈሩን ስም አጥንቶ ጠዋት እየወጣ ሲንከራተት ይውላል። እንደ ሞኝ አላፊኢ አግዳሚውን ይጠይቃል። በየግቢው በር እየተገተረ በዓይኑ ይፈልጋል። ቢጨንቃቸው የረዱት መስሎአቸው አንድ ቀን ማርካቶ አብረውት ሄዱና የእነ ጋሜን የነቢሻውን የገረድ ደላሎች ቢሮ በተራ አዳረሱት። በተርታ ተኰልኵለው ተቀምጠው ሴቶች «ይህች በቅርብ ጊዜ ባሏ የፈታት ባለሙያ ናት። እንዲያውም ይህችኛዋ ከፈረንጅ ቤት የኖረች ናት። የወንደ ላጤ ቤት ከሆነ በደሞዝዋ አትጣሉም። አሁን ማ ይሙት ይችን የመሰለች ልጅ ለሚስትነት እንጂ ለግርድና የምትገባ ነበረች?» እያለ የሚቀባጥረውን ደላላ፥ ከብት እንደሚገዛ ሰው በንቀት ዓይን ሁሉንም የሚገመግመውን ቀጣሪ፥ ካሣሁን ሲመለከት ባሰበት። «እኔ በሕይወት ቁሜ እየሄድኩ እንዲህ አትሆንም ዘይኔ!» በማለት ቆረጠ። ለምሳ ስንኳ መመለስ የተወው ከዚህ በኋላ ነበር።

ትናንትናውኑ ሲያምሽ፥ ካሁን አሁን ይመጣ ይሆናል እያሉ ሲያቅማሙ ፖሊስ ጣቢያም፥ ሆስፒታልም፥ ሦስተኛም ተዟዙሮ ለመጠየቅ ሰዓቱ አለፈ። ዛሬውኑ ደግሞ አዲስ የተፈጠረው ሁናቴ ፋታ የሚሰጥ ባይሆንም ስለ እርሱ ማሰባቸውና መጨነቃቸው ደግሞ አልቀረም ነበር። በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ ሲካፈሉ የዋሉት ከሁለት በተከፈለ ልብ ነበር።

የፖሊስዋ ቮልስዋገን በአጠና አጥሩ መካከል ከቆርቆሮው በር ፊት ለፊት ስትቆም ተማሪዎቹ ከመቅጽበት ተበታትነው ተሠወሩ።

አንደኛው ፖሊስ የቆርቆሮውን በር ሲደበድበው ቦጋለ ወጥቶ ጠየቀ። «ምን ነበር?»

«ካሣሁን የሚባል ሰው ከዚህ ይኖር ነበር?»

ቦጋለ በአወንታ ለመመለስ ቃጣውና መልሶ ተጠራጠረ። ጥያቄው ለምን እንደሆነ ማን ያውቃል? በአንድ ምክንያት ይዘውት - እነሱን ጨምሮ ከፖሊኢስ ጣቢያ ያመለጠ ስለሆነ ለመያዝ በቂ ምክንያት አላቸው - አሰለፍልፈውት እንደሆነስ? ያልጠረጠረ ተመነጠረ ነው። «እኔ ጓደኞቼን ለመጐብኘት የመጣሁ እንግዳ ነኝ። ልጠይቅላችሁ» አለና ወደ ቤት ገባ።

«ካሣሁን የሚባል ሰው ከዚህ የለም» ሲል ታረቀኝ ለፖሊሱ መለሰለት ተመካክረው ከወጡ በኋላ።

«አሁንማ እንደሌለ አውቃለሁ።»

«አለመኖሩን ካወቁ ታዲያ ለምን ይጠይቁናል።»

ፖሊሱ በአኳኋናቸውና በአነጋገራቸው ጥርጣሬ እንዳደረባቸው ገባው።

«ለክፉ ነገር አይደለም። እሱ ራሱ ንገርልኝ ስላለን ነው» አለ ፖሊሱ። ተማሪዎቹ መልስ ለመስጠት አሁንም በማቅማማት ዝም አሉ። ፖሊሱ አሁን እርግጠኛ ሆነ። «አደጋ ደርሶበት ሐኪም ቤት ነው። ምኒልክ ሆስፒታል ነው ያለው» ሲል አረዳቸው።

ተማሪዎቹ አሁንም ዝም አሉ። ፖሊሱም መኪናውን አስነሥቶ ወደ መጣበት አመራ።

በምኒልክ ሆስፒታል በሦስተኛ ማዕረግ የተኛው ካሣሁን ጭንቅላቱን እስከ ማጅራቱ አንድ እግሩንና አንድ እጁን በጀሶ ተጠቅልሏል። ጓደኞቹን ሲያይ ፈገግታ ለማለት ሞከረ። ግን ከነጩ ጀሶ ጋር ፈገግታው አስፈሪ ገጽታ ሰጠው።

«ምን አገኘህ?» ሲሉ ጠየቁት ዙሪያውን ከበው።

ዘይኔን ፍለጋ ከየት በየት ሲንከራተት እንደዋለና መሽትሽት ሲልበት ወደ ቤታቸው ጉዞ እንደ ጀመረ ተረከላቸውና «ከዚያም አንድ ነገር ወደ ሰማይ አጐነኝ። ነፍሴን ያወቅሁት በዚህ ሆኘ ነው» አለ በመጨረሻ።

የቀረውን አጠገቡ የተኛው ሕመምተኛ አከለበት። «መኪና ነው የገጨው። ትራፊክ ፖሊሱ እንዳለው ከሆነ ከባድ ጉዳት ነበር የደረሰበት። ግን እንደምታዩት ከሞት ተርፎአል።»

«ገጪውስ?»

«ለጊዜው አልተገኘም። በአካባቢው የነበሩና አደጋውን ያዩ ሰዎች ናቸው በአጣዳፊ ለፖሊስ አስታውቀው ሆስፒታል እንዲገባ ያደረጉት። እንደኔ ግምት ስንኳ ጥፋቱ የእርሱ ሊሆን ይችላል። ከጭቃ ሸሽሁ ብሎ ወደ አስፋልቱ ሳይገባ አልቀረ ይሆናል። ቢሆንም ገጭቶ መሸሽ ራሱ ከባድ ፋት ስለሆነ፥ ታርጋውን ይዞ እንደሆነ በማለት አእምሮውን በሚገባ ሲያውቅ ትራፊክ ፖሊሱ ሊጠይቀው ሲመጣ ለእናንተ እንዲነግርለት አድራሻ ያለበት ቁራጭ ወረቀት ሰጥቶ ልኮት ነበር።»

«እኛ አላመነውም እንጂ ፖሊሱስ መጥቶ ሁኔታውን ነግሮናል። ለመሆኑ ታርጋው ተይዞአል?»

ሕመምተኛው በአሉታ ራሱን ነቀነቀ።

«ገድሎትም ቢሆን ኖሮ አምልጦ መቅረቱ ነበር ማለት ነው!»

«ሊያዝ ይችላል። መኪናዋ ቮልስዋገን መሆኗ ታውቋል። ከሱ ሰውነቱ ላይም የመስታወት ስብርባሪ ምልክት ስለ ተገኘ የፊት መታወቷ ተሰብሯል ማለት ነው። ኮፈኗና ፓራፋንጎዋም ሳይሰረጉድ አይቀርም። መኪናዋ በየጋራዡ እየተፈለገች ነው» ሲል ሕመምተኛው መለሰ። ሕመምተኛው ስለ መኪናዋ መፈለግ የነገራቸው ሌላም ነገር ነበር። ይኸውም ገጭቶ የሸሸው ሰው፥ እጃቸውን እንዲሰጡ ከሚፈለጉት ሰዎች አንዱ ሳይሆን አይቀርም የሚል ጥርጣሬ በፖሊሶች ዘንድ እንዳለ ነበር «ብዙዎቹ አሮጌ መኪና እየቀየሩ በጨለማ ለማምለጥ እንደሚሞክሩ ተደርሶበታል። እስቲ ከቻላችሁ እናንተም

በበኩላችሁ ተከታተሉ» አላቸው ሕመምተኛው፡፡ የፊት መስታወቷ የተሰበረ ቮልስዋገን በየጋራዡና በየሰፈሩ መፈለግ በኑልቱም ወገን ቀጠለ፡፡

የአስተባባሪ ኮሚቴ አግጣቻና ዓላማ ተለይቶ እስኪታወቅ ድረስም ቢሆን ለጊዜው የፖለቲካ ሥራቸውን አቋርጠው የካሣሁንን ገጪ ለሚፈልጉት ለእነታረቀኝ በየጋራዡ መጠያየቅ ችግር አልሆነባቸውም፡፡ መኪና ለማሠራት ወይም የሚሸጥ መኪና እንዳለ ብለው ይገቡና የፊት መስታወቷ የወለቀ፥ ኮፈንዋ የተጠረመሰ ቮልስዋገን ካዩ አንዱን ሠራተኛ እንደ ዋዛ ይጠይቁታል፡፡ ይህች የዘመዳችን መኪና ናት? መቼ ነው ጋራዥ የገባችው? አደጋ ደርሶባቸው ነው? ሌላም ሌላም ቀላል ጥያቄ፡፡ መላው አዲሲ አበባን ማዳረስ ስለማይችሉ ይህንኑም አደጋው ከደረሰበት ቦታ ቅርበት ባለው ክልል ወሰኑት፡፡ አልቀናቸውም፡፡

ቀጥሎ በየሰው ግቢ ውስጥ መፈለግ ግን አስቸጋሪ ሆነባቸው፡፡ እርግጥ የድፍን አዲስ አበባን ግቢ ሁሉ ማዳረስ እንደሌለባቸው ያውቁታል፡፡ ካሣሁንን ገጭቶ ያመለጠው አስተባባሪ ኮሚቴ ከሚፈልጋቸው ወይም ገና ለገና መያዛችን አይቀርም ብለው ከሚሽሎከለኩት ባለሥልጣኖችና መኳንንት አንዱ ከሆነ የሚኖረው በጥሩ ቪላ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ የአስተባባሪው ኮሚቴ መግለጫ፥ ካለአግባብ የበለጸጉና በሥልጣናቸው የባለጉ ብሎ የለ? በአብዛኛው የሚኖሩበት አካባቢ ደግሞ ከሞላ ጐደል ይታወቃል፡፡ ካዛንቺስ፥ አሥመራ መንገድ፥ የዱሮ አውሮፕላን ማረፊያ፥ ቦሌ ሁለቱም ሾላ፥ ሜክሲኮ አደባባይ ነው፡፡

ፍለጋውን ከየት አካባቢ መጀመር እንደሚሻል መምረጡ ቀላል ነበር፡፡ አደጋው በደረሰበት አቅራቢያና አካባቢ፡፡ ግን ከማይተዋወቁት ሰው ግብቢ እንዴት ዘው ብሎ መግባት ይቻላል? በተላይ በግርግሩ ሌባና አጭበርባሪ በዝቷል ተብሎ ሰው ጠንቀቅ ማለት አምጥቷል፡፡ ነገሩን አውጥተው አውርደው ተስፋ ቁርጠው ለመተው በተቃረቡበት ወቀት ቦጋለ አንድ ዘዴ ብልጭ አለበት፡፡

ከንጉሡ ጀምሮ የቀንደኞች መሣፍንቶችና መኳንንቶች የልጅ ጐንጤ ኮሚቴ አባሎችን፥ የአሁንም አቃቤ የልጅ ጉግሣን ከፍተኛ የጦር መኰንኖችን ወንጀል በመዘርዘር በመተንተን ከተበተኑት ብዙ ዓይነት ወረቀቶች ሌላ፥ የሰሞኑ ትልቅ መቃለጃ ወሬ ንጉሡ አውቶሞቢል የሰጡአቸው ወይዛዝርት ስም የሰፈረበቱ ነበር፡፡ «በሕዝብ ሀብት ከንጉሡ አውቶሞቢል የተሸለሙ» በሚል አርእስት ምንም ሐተታ ሳይጨምር ከማርቸዲስ አንሥት እስከ ቮልስዋገን - ቮልስዋገን የተሰጣት አንዲት ሴት ብቻ ናት - የተቀበሉ የሰላሳ ሶስት ወይዛዝርት ስም በሁለት ረድፍ የተጻፈበት ወረቀት ከተማውን አዳርሶታል፡፡ ከፔጆዋቸው ጋር የወይዝሮ ዘርፈሽዋል ስምም አለበት፡፡ ከየት እንደ መነጨ አይታወቅም፡፡ ግን፥ አብዛኞቹ አውቶሞቢሎች ስሌዳ ቊጥራቸው ሳይቀር መጠቀሱ፥ ብዙዎቹ ወይዛዝርት በቤተ መንግሥት አካባቢ በነበራቸው ግንኙነት ቀደም ሲል የተወራላቸውና ሐሜትም የፈጠሩ መሆናቸው የጽሑፉ ምንጭ ውስጥ አዋቂ ሳይሆን እንደማይቀር ይጠቁማል፡፡

ወረቀቱን ያገኘ ወይም የወሬ - ወሬ የሰማ ሁሉ እየተሰበሰበ ተዳነቀበት፡፡

-ሴቱን ሁሉ በአውቶሞቢል አፍነሸንሸውት የለ? በሰማኒያ ሁለት ዓመታቸው? ለጉድ ነው!

-ሽሜው አንድ ነገር ቢኖረው ነው! ከጐረምሳ ይበረታል ይላሉ! ሲል ተሜው ያፌዛል፡፡

-ይህችኛዋ ደግሞ ማናት?

-እስዋማ የደጃዝማች እገሌ ሚስት ነበረች አሉ። አሁን ትልቅ የመሶብ ቤት አላት። ቆንጆ ናት አሉ።

-እንዴ ይህች የአቶ እገሌ ሚስት አይደለችም? ባልዋ ምን ይላል?

-ሳይስምደው ይቀራል? ሹመውታልኮ!

ከሁሉም የአድናቆት መጫወቻ የሆነችው ሁለት ማርቸዲስ የተቀበለችው ወይዘሮ መሶብ ወርቅ ነበረች።

-ፖህ! ይህች ደግሞ ልዩ መሆን አለባት

-አዎ! አረግራጊው ዳሌዋ በእቅፍ አይደረስበትም አሉ - ሲል ስለ ሴትዮዋ ወሬ የሰማው ይመልሳል።

እነ ታረቀኝ በዕለቱ ያገኙዋቸውን ብትን ወረቀቶች ከተወያዩባቸው በኋላ የሴቶቹን ስም እያነበቡ ሲሳሳቁ፥ «ለምን ይህንን ወረቀት አንጠቀምበትም?» ሲል ቦጋለ አልፎ አልፎ ከማፌዝ ሐዛቡ ተመልሶ ጠየቀ።

«ለምኑ?»

«ሰውየውን ለመፈለግ ነዋ!»

«እንዴት?»

አስረዳቸው። «ይህን ወረቀት ይዘን በሕዝብ ሀብት ከንጉሡ የተሰጡትን አውቶሞቢሎች መዝግቡ ተብለን የተደበቀ እንዳለ እንፈልጋለን እንላለን። ሰሞኑን የተበተነው ወረቀት ያገባኛል የሚለው ሁሉ ደግሞ በመርበድበድ ላይ ነውና የሚከለክል አይኖርም። ማለቴ፥ ብዙ ባለሥልጣኖች እጃቸውን እየሰጡ ናቸው። ማለቴ፥ ብዙ ባለሥጣኖች እጃቸውን እየሰጡ ናቸው። ስለዚህ የአውቶሞቢል ስጦታ ዝርዝር የወጣባቸው ሰዎች ከተያዙትና ከሚፈልጉት ምናልባት በሀብትም በሥልጣንም አይበልጡም። በመሆኑም አውቶሞቢላቸውን አስረክበው በነፃ ማምለጥ ስለሚፈልጉ አናሳይም ብለው አስተባባሪውን ኮሚቴ መጋፋት አይከጅሉም ባይ ነኝ። ሌላ ሥጋት ያለባቸው ወገኖች ከሆኑ ደግሞ በአውቶሞቢል ምክንያት በወታደር ኃይል ተይዘው ከመሄድ አውቶሞቢሎቻቸውን ደርድረው ማሳየትን ይመርጣሉ ባይ ነኝ። አደጋ ካደረሰው ሰው ግቢ እስክንደርስ ድረስ በእነዚህ ሁለት ተጠራጣሪ ወገኖች መካከል መጫወት እንችላለን ማለት ነው። እርግጥ ለማስመሰል ያህል የወታደር ጃኬት መልበስ ያስፈልገን ይሆናል። የሚያውሱን ግን የምናጣ አይመስለኝም።»

በየሰው ግቢ ያጋጠማቸው ሁናቴ ራሱን የቻለ ትንግርት ነበር።

«ንጉሡ ያለ አግባብ ለግለሰቦች የሰጡአቸው አውቶሞቢሎች ታርጋ እንድንመዘግብና አውቶሞቢሎቹ የሚገኙበትንም ሁናቴ እንድንመረምር ከጦር ኃይሎች፥ ከፖሊስ ሠራዊትና ከብሔራዊ ጦር አስተባባሪኢ ኮሚቴ የተላክን ነን» ሲሉት አንዳንዱ ያልተጠየቀውን ይዘላብዳል።

«ኦሆሆ! እኔን ደግሞ ከዚኢያ ደረጃ ምን አደረሰኝ? ግቢውንም ረግጨው አላውቅ። ሚስቴ? እኔም ሚስቴም እየጣርን እየጋርን ነው ከዚህ የደረስነው። እኔ በመሥሪያ ቤቴ  እስዋ በቤት። ቤቱም

የተሠራው መኪናም የገዛን በባንክ ብድር ነው። በየወሩ ምን ያህል ዕዳ እንደምንገፈግፍ ብነግራችሁ ትደነቃላችሁ። ደሞዝኮ እንዳለ ጭልጥ ብሎ ነው የሚሄደው። ሸሮውንም ቆሎውንም እየበሉ መቻል ነው። ያም ሆኖ አይገፋ። ወለዱ እየተቆለለበት ባለህበት ሂድ ነው። አታምኑኝም ይኸው አምስት ዓመት ሙሉ ስከፍል ዕዳው ንቅንቅ አላለም። ይህችን አውቶሞቢል ስታይዋት ምናልባት አዲስ ትመስላችኋለች። በሩም ኮፈኑም ይከፈታል። የቆየች ነች እኮ! ግን የደሃ መኪና ስለሆነች በደንብ እይዛታለሁ። አልሰክር። አልጋጭ። ለመጠጫ ገንዘቡስ ከየት እይዛታለሁ። አልሰክር። አልጋጭ። ለመጠጫ ገንዘቡስ ከየት ይመጣና። ባንክ ነው የሚወስደው» ይላል መኪናዋን እንደሚባርክ እጁን ዘርግቶ። «ደግሞም ከዚህ የምታዩት ይሄ ሁሉ አትክልት ራሴ ቆፍሬ ተክዬ፥ ኮትኩቼ ያሳደኩት ነው። ቤትም ስሠራ እንደዚሁ። አታምኑኝም ስሚንቶ ራሴው አንጒቼ እስቱኮ፥ የቀለም ስንቱ ጣጣው እንደ ኩሊ ሆኜ ነው የተሠራው። ታዲያ የደሃ ቤት ስለሆነ በደንብ እይዘዋለሁ።»

የኑሮ ችግሩን በዚህ ዓይነት ያነበነበላቸው ሰው ሲደክሙ መዋላቸውን ገልጾ ሻይ እንዲጠጡ ይጋብዛቸዋል። ግን ለመረማመድና ለመቀመጥ በሚያስፈራ ሳሎን ውስጥ ሺቫዝ ውስኪና ኩርባይዘር ያቀርብላቸዋል።

የፈረንሣይ ቡርዧ ባሕል ነኩ ደግሞ እየተቆጣ እያፌዘ ይቀበላቸዋል። «ፐሀ! እዩ! ግን ይኸ አናርሺ ነው? ማለት ሕግ አለ። የሴትየዋ መብት አለ። መንግሥት አለ። ምንድን ነው ይሄ? አናርሺ! እኔ ግን ግድ የለኝም። እርግጥ ባለሥላን ነኝ። ታዲያስ? እኔ በበኩሌ እኔ ብቻ ሳልሆን አባቴ ጭምር በሊቤርቴ፥ በፍራቴርኒቴኢ። በኤጋሊቴ የምናምን ስለሆነ ከጃንሆይ ጋር አንስማማም ነበር። የአባቴን ታሪክ ብነግራችሁ ብዙ ነው። እንኤን ግን የሾሙን ሳይወዱኝ ነው። ችሎታ አለኝ! አሎር! ግን ጃንሆይ በፊውዳሎች ተጠምጥመው ላዬሞክራሲ መሆን አለበት ስንላቸው አልፈልጉም። አሎር! አሁን ይሄ ነገር መጣ። የፈረንሣይ ሪቮሊሲዮን ዓይነት። እኔ መጋደልን አልወድም እንጂ እቀበለዋለሁ። ክሚቴያችሁ ይህንን እንደሚያስብበት ተስፋ አደርጋለሁ። እኔን በሚመለከት ግን ንጉሡ ምንም ነገር አድርገውልኝ አያውቁም። ሀብትም ቢኖረኝ ከአባቴ ከእኔ ብቻ የተገኘ ነው። ሌላው ቀርቶ ይህንን ለውጥ የሚቃወም አንዳንድ ሰዎች በእኔ መሥሪያ ቤት ቢኖሡ እንኳ አብዛኛው ሠራተኛ እኔ ስለ መከርኩት የእናንተን ተግባር ደግፎአል። ለሊቤርቴ መቆማችሁን» እያለ ሁለት ሦስት መኪኖቹን አሳይቶ ይሸኛቸዋል።

ሌሎች ዓይነቶች ደግሞ ነበሩ። የኑሮ ትርጒም ያልገባት የባልና ሚስት ፍቅርም ነገሩ ያላረካት ብዙም ብዙ ወሬ የምትሰማ፥ ሐሳብ መበተኛ ጒልበት ማባከኛ የሌላት ባልዋ በዚህም በዚያም ብሎ በሚያመጣው ሀብት አንቀባሮ የያዛት ወይዘሮ በፍንደቃ ተቀበለቻቸው። «ውይ! ውይ! ጃንሆይ መኪና ሸልመውኝ? በማን ዕድሌ! ለነገሩማ ሀብትም አላጣንም። መኪናዎችም አሉን። ባሌ ጥሩ ነጋዴ ነው። እንግዲህ ማወቅ ከፈለጋችሁ ባሌ ማርቸዲስዋን ይዞ ሄዶአል። ይች የምታዩዋት ፔጆ እኔ ሲያስፈልገኝ የምዘዋወርባት ናት። እውነቱን ልንገራችሁ? አልወዳትም። ባለቤቴ ግን ለውጥልኝ ስለው ገንዘቡ ከየት ይመጣል ይለኛል። ችግር ነው ኑሮ። ብቻ አላማርረውም» ስትል ጒርምስናቸውን በዓይኗ ትቀላውጣለች።

የስበከት - መንግሥት ምክትል ባለሥልጣን ሳይጠይቁት ረጅም ዜና ተረከላቸው። «አዎ! ያችን ፔጆ ሳልወድ በግድ ተቀብያለሁ። መስታንን ግን ራሴው የገዛኋት ናት። እኔ ብቻ አይደለሁም። ሌሎች ብዙዎች የመሥሪያ ቤቱ ባልደረቦች እንዲሁ በግድ ውሰዱ ተብለዋል። እንዴት መሰላችሁ ነገሩ? እንደምታውቁት የሥራው ጠባይ በግድ መኪና ያስፈልገዋል። ካለበለዚያ ምንም ማድረግ አይቻልም። ስለዚህ በሙያው የተሰማሩት ኃላፊዎችና የሙያ ምርጥ ሰዎች እንደዚሁም በሥራቸው ጠባይ ዓይነት

መኪና የሚያስፈልጋቸው ኃላፊዎች የመንግሥት መኪና ይዘው እንዲገለገሉ ከተደረገ ቆይቷል። ማለቴ እንደ መብራት ኃይል፥ እንደ ቴሌኮሙኒኬሽንና እንደ ሌላው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሁሉ እነዚህ መኪኖች ሲበላሹ ሲገጩ፥ የሚሠሩት በየጊዜው ሰርቪስ የሚደረጉት በመንግሥት ወጪ ነው። መቼም የመንግሥትን መኪና በራስህ ገንዘብ አሳድስ ሰርቪስ አስደርግ ማለት አይቻልም። በዚህም ምክንያት ሚኒስቴሩ ለእነዚህ መኪኖች ማሠሪያና ማሳደሻ ለሰርቪስ በዓመት ከመቶ ሺህ ብር በላይ ያወጣ ነበር። ከዚህ በፊት የነበሩት ሹም ይህንን የመንግሥት ገንዘብ ለመቆጠብ አንድ ዘዴ መቱ መሰለኝ። አንድ ቀን ጠዋት ቤተ መንግሥት ድረስ ትፈለጋላችሁ ተባልን። በእሳቸው አቅራቢነት ከጃንሆይ ፊት እንደ ቀረብን የሠራችሁት ሁሉ ጥሩ አቅራቢነት ከጃንሆይ ፊት እንደ ቀረብን የሥራሁት ሁሉ ጥሩ ነውና የያዛችኋቸው መኪኖች የራሳችሁ እንዲሆኑ ተሰጥተዋቸዋል፤ ለወደፊቱም በርቱ ተብለን ወጣን። የመንግሥት መኪና ሳይዙ በስሕተት ቀርበው እጅ ነሥተው የተመለሱም ነበሩ። ጫማችን ተመረቀልን ብለው ቀለዱ። አንዱም የራሱ መኪና ተበላሽታ እስክትሠራ ከመሥሪያ ቤቱ አዲስ አውቶሞቢል ተውሶ በዚያው ጸደቀለት። ወዲያው ሰሞኑን ኦርማ ጋራዥ በገመተው መሠረት አሹራውን እየከፈልን ስም እንድናዛውር ታርጋ እንድናስለውጥ ማዘዣ ተጻፈልን። እሳቸውም አንድ አውቶሞቢል ወሰዱ። መጉዳታችን የተሰማን እየቆየ ነው። ሲበላሹ ራሳችን ማሠራት ስንጀምር። በእርግጥም ዋናው ሹም አሳምረው ነው የሠሩልን።

«ቅድም እንዳልኩት ለመኪኖቹ ሰርቪስና ማሠሪያ በዓመት ወጪ የሚሆነው ከመቶ ሺህ ብር በላይ ነበር። መኪኖቹ በሙሉ የተገመቱበት ድምር ደግሞ ከአርባ ሺህ ብር አልበለጡም። ታዲያ መልሱልን ብለን የንጉሥ ትዕዛዝ መጋፋት አንችል! የሰጡንን፥ የጣሉብንን መቀበል ነው። ግን አሁን እንደዚህ ያለ ጥያቄ ከተነሣ፥ በእኔ በኩል ሊብሬውም ታርጋውም ዛሬ እንዲለወጥ ፈቃደኛ ነኝ። ምን ይጐዳኛል? ወጪ እንጂ። ከሥራ ውጭ ለሆነው ነገር ይኸው እንደምታዩት የራሴ መኪና አለኝ። እና ከሆነ አሁኑኑ ብትረከቡኝ በጣም ነበር ደስ የሚለኝ። እና ለሥራዬ መኪና ይሰጠኝ። ለሌላው ጊዜ ግን መኪና አለኝ። እና፥ እውነቱን ለመናገር እስቲ ይህን ነገር ጨርስሩልኝ» እያለ እራሱንም፥ የተሰጠውንም መኪናዎች አስጐበኘ።

ኰስተር ባለ አነጋገር አፋጣጭ ጥያቄ ያቀረበላቸው አንድ ሰው ብቻ ነበር። «አህያም የለኝ ከጅብ አልታላ እንደሚባለው እኔ የምሠጋበት ነገር ስለሌለኝ ማየት ትችላላችሁ። ግን አሠራራችሁ ልክ አልመሰለኝም። በየቤቱ እየሄዳችሁ ሰውን ከማስቸገርና ከማስደንገጥ ይልቅ ለእናንተም ቀላሉ የሚሆነው ስቸገርና ከማስደንገጥ ይልቅ ለእናንተም ቀላሉ የሚሆነው ማዘጋጃ ቤት ተሽከርካሪ ክፍል በታርጋና በሊብሬ ብታጣሩ ነበር» አላቸው። ደግነቱ ሌሎች ሰዎች ከመደናገጥ በተቀር ይህንን የመሰለ አፋጣጭ የምርምር ጥያቄ ስላልሰነዘሩ እነታረቀኝ ከፈለጉበት ግቢ ለመግባት ችግር አልገጠማቸውም ነበር።

የካዛንቺስን አካባቢ እንዳጋመሱ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ደረሱ።

## ፱

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ የሚሆኑትንና የሚሠሩትን አሳጥቶአቸው ያልሰነበቱትን ያህል ከደጃዝማች አደፍርሰው ልቅሶ ከተመለሱ በኋላ ደግሞ በአጠገባቸው ያለ ሰው ሁሉ አይትረፈኝ አሉ።

«ቀሚስ ያጠለቀው ሁሉ ቁሞ፥ ሱሪኢ የታጠቀው መሞት አለበት!»

«ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከደጃዝማች አደፍርስ ቀብር እንደ ተመለሱ፥ ከጥቁር ካፖርታቸው ሥር ያገለደሙትን ጥቁር ሐር ነጠላቸውን ሳይፈቱ እጃቸውን የኋሊት አጣምረው በቤቱ በረንዳ ላይ ፈንደር ፈንደር እያሉ ይንጎራደዳሉ። እርር ድብን ያደረጋቸው ኀዘኑ ሳይሆን፥ ሰሞኑን ይፎክሩበት የነበረው ተስፋ በመቀጨቱ ነበር። ራሱ ደጃዝማቹ፥ ፊታውራሪው ጄኔራሉ በጀግንነቱም በቤተ መንግሥት ቀራቢነቱም ካለ እኔ ማን አለ የሚለውና መሬት የጠበበው የመሰለው ሁሉ ቤት ንብረቱህ ሊወረስ ነው እየተባለ ስሙ በራዲዮ ሲጠራ ጌታው ቤት እንደሚገባ ለማዳ እንስሳ ሱክ - ሱክ እያለ ለአራተኛ ክፍለ ጦር እጁን ሲሰጥ ራሳቸውን ይዘው «ኡ! ኡ!» እያሉ ተገርመዋል። በተለይም በንጉሡ ልዩ ፈቃድ የጄነራልነትና የማርሻልነት ማዕረግ ደርበው የያዙት ራስ ማን አለብህ መቶ፣ ሽህ ሠራዊት አሰልፈው በአስተባባሪው ኮሚቴ ላይ ተነሥተዋል ብሎ የቢ.ቢ.ሲ. ሬዲዮ ከአወጀላቸው በኋላ የከተማ ቪላዎቻቸውንና ጥቂት ጋሻ መሬት ነው ሲሉ በጋዜጣ የጠቀሱትን የገጠር መሬታቸውን ለማዳን በፈቃዳቸው አራተኛ ክፍለ ጦር ገቡ ማለትን ሲሰሙ፣ ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ወንድነት እርማቸውን ሊያወጡ ተቃርበው ነበር። «ወየው! ወየው! በቃን ይኸው ነው ፍጻሜው?» ሲሉ የሌለ እንባቸውን መጠራረግ ከቃጣቸው በኋላ፥ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የማናዬን ወንድነት ተጠራጥረው ለማብሸቅ የፈለጉ ይመስል «እንኳን ደጃማች ገሠሠ ይህንን ውርደት አላዩት» በማለት ሚች ባላቸውን በማስታወስ፥ ዓይናቸውን አጕረጠረጡበት።

ያ ሁሉ መኳንንትና የጦር አለቃ ያለ አንዳች ማንገራገር በራዲዮ በተነገረው ቀንና ሰዓት እጁን ሲሰጥ የደጃዝማች አደርፍርስ ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር መሸፈት በወቅቱ እንደ ትንግርት ተቈጥሮ ሰንብቶ ነበር። በያለበት ሰው አቅርፎአቸዋል እየተባለ በየቤቱ በየቡና ቤቱ ሁሉ መወያያና መጠያየቂያ ሆኖ ነበር። አስተባባሪው ኮሚቴ ሊወድቅ ይሆን? ደጃማች አደፍርስ አሸንፈው ከመጡማ «ለውጥ - ለውጥ እያለ የቀበጠው ሁሉ የቀበጠው ሁሉ ይብላኝለት! እሱን አያርገኝ።»

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የደጃዝማች አደፍርስን ሱሪ ራሳቸው የታጠቁት ይመስል ማናዬን ከማጨናነቅ አንሥቶ ባገኙት ሁሉ ላይ ሲፎክሩ ሰንብተው ነበር። «የአገሬ ጨዋ የአገሬ መኳንንት ሁሉ ሱሪውን አልፈታም። ኦሆሆ! ገና ምኑ ታይቶ! ምድረ ምናምንቴ እንዲሁ እንደ ፎለለ ይቀር መስሏችሁ! ገና ምኑ ታይቶ! እንደ አይጥ መደበቂኢያው ነው የሚጠፋው! ምን አቀበጠኝ ብሎ የተወለደበትን ቀን ነው የሚረግመው» እያሉ ደንፍተዋል።

ግን ይህ ተስፋና ዛቻ ብዙም ጊዜ አልቆየ። ደጃዝማች አደፍርስ አስቀድሞ እንደ ተወራው አዲስ አበባን ይዘው መኳንንቱን መሳፍንቱን፥ ከታሠረበት አስፈትተው አሳሪዎቹን በማሠር ፈንታ ወበሬ ሥላሴ ድብር ከአንድ ገበሬ ቤት ከጥቂት አበሮቻቸው ጋር መገደላቸው ሲሰማ፥ የእነ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና የመሰሎቻቸው ሐሞት እንደ ተነፈሰ ጕማ ሙ[illegible] አለ።

የባሰው ነውጥ የደረሰባቸው ግን በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ ነበር። ቤተሰቦቹ ኀዘናቸውን እንዲያወጡ ተፈቅዶላው ልቅሶው ሲሚሚቅ ከአልቃሹ ከአስለቃሹ ከጥቁር ለባሹ፥ ከልቅሶ ደራሽ ሊኤላ ተማሪው ቦዘኔው ዋናውን መንገድ ይዞ ይሰበሰብ ጀመር። ማርቸዲሱ፥ ፔጆው ከአውራ ጐዳናው ዳርና ቀደም ሲል ዝናው ከተነገረለት ግቢ በራፍ እየቆመ ተሳፋሪዎቹ ሲወርዱ፥ ፉጨቱ ከያለበት አስተጋባ። ነገር ግን እንደ የካቲት መኪና ሰበራ ጊዜ መደናገጥና መረበሽ አልነበረም። አልፎ አልፎ የመለዮ ለባሽ ጸጥታ አስከባሪዎች ስለ ነበሩ፥ ወይዛዝርቱም፥ መኳንንቱም አንዳንዱ አንገቱን ደፋ አድርጎ ሌላውም እየገላመጠ ወደ ዳሱና ወደ አዳራሹ ገባ። ከሁለቱም በኩል ሰው እየበረከተ ሲሄድ መፋጠጡ በዚያው ልክ እየበረታ መታ። ከኀዘንተኛው በኩል ልቅሶው በሦስት ተከፈለ፥ በእያንዳንዱ ቡድን ከአንድ የበለጠ

አስለቃሽ ቁሞ ግጥም ይወርዳል። ደረት ይደለቃል። ከሴቱም መካከል አልፎ አልፎ ለስሙ ያህል የቀሚሱን የደረስት ክፈፍ በሁለት ጣቱ ነካ ነካ ያደርጋል።

ዋይ - ዋይ! የት ትሄዳለህ?

ዋይ - ዋይ! የት ትሄዳለህ?

አፈር ሊበላው ነው ወይ?

አፈር ሊበላው ነው ወይ?

ያገሩን ዋርካ ያገርን ዝግባ?

አፈር ሊበላው ነው ወይ?

አፈር ሊበላው ነው ወይ?

ያንን ቁመና ያንን አንገር፥

ያንን ጀግንነት ያንን ወንድነት፥

አፈር ሊበላው ነው ወይ?

በዚህ መካከል የፌዝ፥ ሁካታና የፌዝ ጭብጨባው አብሮ እያጀበ እንደ ቆየ፥ ጓዳ ውስጥ ጠርሙስ አረቂ ተቀምጦላት እየገባች ካልተጐነጨች ከዱዳ የማትሻል መሆንዋ የሚነገርላት ስመ ጥሩዋ የኮርያ ሠፈር አልቃሽ፥ በአዲስ የአልኮል ፈረስ እንባዋን እየረጨች ድምፅዋን ከፍ አድርጋ - ሆድ ያባውን በብቅል ኃይል አፈረጠችው።

ዋይ፣ ዋይ የት ትሄዳለህ?

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ?

ከቡልጋ አሥር አልጋ

ዋይ፥ ዋይ የት ትሄዳለህ?

ከመንዝ አሥር አልጋ

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ?

ከዲስጌ አሥር አልጋ፥

ዋይ ዋይ፥ የት ትሄዳለህ?

ከአስኳል አሥር አልጋ

ዋይ ዋይ፥ የት ትሄዳለህ?

ከግሼ አሥር አልጋ

ዋይ ዋይ፥ የት ትሄዳለህ?

ከተጉለት ዘጠኝ፥

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ?

አንተን የሚተካ

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ።

ውይ ዋይ ዋይ ዋይ፥ ዋይ ዋይ፥ ዋይ!

በዚህ ጊዜ ዙሪያውን ቆሞ ያፌዝና ስድብ ያሰማ የነበረው ተቃዋሚ የልቅሶውን ክብ ጥሶ ገባ።

-አልጋው ሊቃጠል ነው!

-አሁንም በዘር ማምለክ አይበቃችሁም?

-የናንተ አልጋ የትኋን መሰብሰቢያ ነው። ይወድማል!

በትርምሱና በግርግሩ መካከል ግማሹ ኀዘንተኛ ወደ ዋናው ቤት አዳራሽ ገባ። ሌላው እየተንጫጫና እየተወራጨ ወደ አውቶሞቢሉ ሄደ። እንደ ወይዘሮ ዘርፌሽዋል ያሉት ደግሞ አንፈራጠው በመቆም ተጋፈጡ። በአለባበሱ የቀን ሠራተኛ የሚመስል አንድ ጉረምሳ ድንገት ከአጠገባቸው ደርሶ በመቃ እንደ ተነፋ ያበጠ ቁመናቸውን ከታች እስከ ላይ ተመለከተና የፌዝ ሳቅ በወጠረው አንደበት፥ «ይችስ እንዴት ብትበላ ነው እንዲህ የተነፋችው፥ ባካችሁ! እኛን እየጋጡ ነው!» አላቸው።

ወይዘሮ ዘርፌሽዋል፥ መጮህና በጥርሳቸው መቦጫጨቅ ቢያቅታቸውም ምናልባት ውርደቱን ፈርተው እንደ ምንም ቻሉትና፥ «ቢያድለኝ ነው! እንደናንተ የተረገምኩ ቆርማዳ መሰልኳችሁ?» ሲሉ መለሱ።

ሁኔታውን የተመለከቱ የጸጥታ አስከባሪዎች ወዲያውኑ ጸጥታውን አስከበሩት። ወይዘሮ ዘርፌሽዋል ግን ከደሴ ሲመለሱ ካጋጠማቸው ከሾላው የድንጋይ ናዳ አደጋ የባሰ እርር ድብን ብለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

«ወይ ነዶ፥ አሁን ስንቱ ቀሚስ የለበሰ እያለ?» አሉና አሁንም ዓይናቸውን በማናዬ ላይ አጉረጠረጡ።

«መቼም ላንዱ ያለው ለሌላው አይሆን» ሲል ማናዬ በማመንታት ለማብረድ ሞከረ። አሽሙሩ በእርሱም ላይ የተሰነዘረ መሆኑ ስለ ታወቀው ባንድ በኩል መከላከያ ማቅረቡም ነበር።

«ምኑ?» የወይዘሮ ዘርፌሽዋል አነጋገር ጥያቄ ሳይሆን የባረቀ ቁጣ ነበር።

«ማለቴ ማለቴ፥ በአደጋም ይሙት በሕመም እገሌ በሕይወት እያለ እገሌ ለምን ሞተ ምን አሰኘን?»

«አንተ ዝም በል! ስለ ሕይወትም ስለ ሞትም አታውራ። የት ታውቀውና!»

«እንዴ! ሳልሞት ስለ ሞት እንዴት ማወቅ እችላለሁ? እንቅልፍሽ አጥተሽ መሰንበትሽ ነው መሰለኝ እንዲህ ያብስከሰክሽ።» ማናዬ አንደበቱን ለማለስለስ ሞከረ፡

«ኤጭ! ስለኔ እንቅልፍ ማጣትስ ቢሆን ምን ያገባህና! የሰው ስሜት የሚገባው ነው፥ ወንድነት የሚኢሰማው ነው ስለ እንቅልፍ ማጣትም የሚያውቅ። ሌላውማ ከተ ጋደመ ይበቃዋል።»

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የነገሩን አዝማሚያ የጠመዘዙት ሲበሽቁ የሰነበቱበት ሁናቴ ስለ ገነፈለባቸው ነበር። ሰው ሁሉ የተለያየ ስሜት አለው። አንዳንዱ ሰው፥ የፍቅር ጨወታ የሚያምረው ሲዝናና ደስ ሲለው ነው። ሌላው ሞቅታ ሲሰማው ነው። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ደግሞ ከዘውትር ፍላጐታቸው ሌላ፥ ሲናደዱ፥ ሲጨነቁ ስሜታቸው ይቅበጠበጣል። በገረድና በአሽከር ላይ የዱላ ናዳ እንደሚያወርዱት ሁሉ፥ የወንድ ክንድ፥ ጭንቅ፥ ፍጥርቅ እንዲያደርጋቸው ይፈልጋሉ። ከውስጥ ስሜታቸውን አንጠፍጥፎ ያወጣላቸው ይመስል.....

አስተባባሪው ኮሚቴ ተቋቁሞ ሰዎች መታሰር ከጀመሩ ወዲህም ይህ ስሜት ሰፍኖባቸዋል። ማናዬ ደግሞ በር በተንኳኳ ቍጥር የሚፈልጉ ሰዎች ስም ዝርዝር ራዲዮ በተራ ቍጥር የራሱ ተራ እየመሰለው ሲሸማቀቅ የወሲብ ስሜቱ በድን ሆኖበታል። ዕቃው - እሳት ላይ እንደ ተጣለ ቋንጣ - ወደ ውስጥ ተኰማትሮ ገብቷል።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አንዳንድ ጊዜ ስሜታቸውን መቆጣጠር ሲያቅታቸው በውድቀት ሌሊት «ማናዬ! አንተ ማናዬ! ተኝተሃል እንዴ?» እያሉ በመጣራት ጠጋ ይላሉ። ማናዬ ግን ዓይኑን ከድኖ ጀርባውን አሹሎ እያዳመጠም ቢሆን፥ በዕንቅልፍ ልቡ ይመስል እያጕመተመተና እየተወራጨ ጀርባውን ይሰጣል። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በንዴት ከንፈራቸውን እየነከሱ ከጨለማው ጋር ተፋጠው ያድራሉ።

ይህ ሁሉ በሐሳባቸው ሲመጣ፥ የደጃዝማች አደፍርስን ሞት ወደ ጐን ትተው «ስለዚህ ለእኔ እንቅልፍ ማጣት አንተ አይደለህም ምስክር የምትሆነው» ብለው ንግግራቸውን ሳይጨርሱ የግቢው በር ተንኳኳ። የማናዬ ልብም አብሮ ዳንኪራ መታ።

«በሆነ ባልሆነው ስታማርሪ እረፊው!» አለ ማናዬ ወኔ በከዳው አንደበት። በር ከፍቶ የጠየቀው አሽከር ከአስተባባሪ ኮሚቴ የተላኩ ሰዎች መሆናቸውን አስታወቀ።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በግልቢያ እንደ ደከመ ፈረስ፥ የፉጨትና የኩርፊያ ቅልቅል በመሰለ ድምፅ በፍንጫቸው ተነፈሱ።

## ፲

ሁለቱም ወገኖች ለረጅም ጊዜ ተፋጥጠው ቆሙ። እነታረቀኝ ከበረንዳው ፊት ለፊት በተርታ ቆመው መልስ ይጠብቃሉ - ከንጉሡ የተሰጠ አውቶሞቢል አለ በዚህ ግቢ? ግን ለዚህ ቀላል ጥያቄ ወዲያውኑ መልስ የሚሰጥ አልተገኘም። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሰሙም የሚያዩም አይመስሉም።

ዓይናቸው ፈጥጦ ከአድማስ ባሻገር አንድ የተደበቀ ነገር የሚፈግ ይመስላል፡፡ የማናዬ ዓይን ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ላይ ተተክሏል፡፡

ከላይ ዝናም የቋጠረ ዳመና እየተሰበሰበ ሰማዩን በመሸፈን ላይ ይገኛል፡፡ ጆንበሯ በዳመናው ተጋርዳ ደብዛዛ ጥላ ሰፍኗል፡፡ በመብረቅ የታጀበ ነጐድጓድ ማስተጋባት ጀመረ፡፡ ሁለቱ ሰዎች ግን ሰማይና ምድር የሚያደባልቀውንም ጩኸት የሚሰሙ አይመስሉም፡፡ ዝም፥ ጸጥ፡፡ ደንቆሮዎች ይሆኑ ይሆን? ሁለቱ ተጠያቂዎች ግን ልብ ካልሰማ ጆሮ አይሰማም እንደሚባለው ሆነው ነበር፡፡

በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዓይነ - ሕሊና ፊት እንደ ገሃድ ትርኢት የተጋረጠው ከስንት ዓመታት በፊት የደረሰባቸው ነገር ነበር፡፡ ገና ዘለቃ ሳትወለድ ደጃማች ገሠሰን ባገቡ በሦስተኛው ዓመት ገደማ ነው፡፡ ሎሚኢ ይወራወሩት የነበረውን የልጅነት ከፍነር ወዳጃቸውን ምኞት ለመፈጸም መኝታ ቤት አስገብተውት እንዳለ ደጃዝማች ገሠሠ ከአደን ድንገት ከተፍ ይላሉ፡፡ ሁለት ስንኳ ገና ምንም አላደረጉም ነበር፡፡ ግን ባልየው በበር ሲገቡ ጐረምሳው በአጥር ዘሎ ሲወጣ መታየት አልቀረም፡፡ ደጃዝማች ምንም እንዳላዩና እንዳልሰሙ ረጋ ብለው መኝታ ቤት ከገቡ በኋላ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልን የፊጥኝ አስረው ጀርባቸው እስኪገለበጥ በጉማሬ አለንጋ ተለተሏቸው፡፡ መንቀሳቀስ ሲችሉ ከእቴጌ ዘንድ ሄደው ገላቸውን አሳዩ፡፡ እቴጌም ስንኳን ያላደረገችውን ብታደርገውም፥ ከልጅነት የከንፈር ወዳጅ ጋር አንድ ቀን መጫወት ነውር አልነበረበትምና እኅቴን ደፍሮ ከገረፈ እሱም ተጥሎ ይገረፍልኝ ብለው ንጉሡን ጠየቁ፡፡ ነገር ግን የንጉሥ ደጃዝማች በቤተሰብ ጉዳይ እንዴት በአደባባይ ይገረፋል ተብሎ፥ ሁለተኛ እንዳይደግማቸው ዋስ እንዲጠሩ ተደረገ፡፡ የዚያ ግርፋት ጠባሳ አሁንም አልፎ አልፎ ከጀርባቸው ላይ ያስታውቃል፡፡ ብድር ለመመለስ ወይም በቀል ለመወጣት ይመስል፥ በሥውር ሕሊናቸው እየተገፋፉ የእሳቸውን ወንድ ቀና ብላ ያየች ሴት ሁሉ አትትረፈኝ ማለት ያመጡትም ከዚያ በኋላ ነው፡፡

አሁን ደግሞ የመንግሥት አውቶሞቢል ሰርቀሻል ተብለው በምድረ ጐረምሳ ሊገረፉ፡፡

ማናዬ ደግሞ በበኩሉ አውቶሞቢሏን እየነዳ አራተኛ ክፍለ ጦር እንዲያደርስ ሲታዘዝ፥ ከዚያም ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው ቃሉን ሲሰጥ፥ የት እንደሚሠራ ተጠይቆ የመሬት ይዞታ ኃላፊ መሆኑ ሲታወቅ ሕዝብ መበደሉና አለመበደሉ እስኪጣራ በቁጥጥር ሥር እንዲቆይ ሲደረግ ታየው፡፡ ምናልባት ከዚህ ግቢ ባይገኝ ኖሮ ይህንን ክፉ ቀን እንደ ምንም ያልፈው ነበር፡፡ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጋር የተገናኘበትን ቀን በሆዱ ይረግም ጀመር፡፡

ሦስቱ ወጣቶች በመገረም ከጠበቋቸው በኋላ «ከዚህ ግቢ ከንጉሡ በስጦታ መኪና የተቀብለ ሰው አለ? መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆናችሁ ነገሩ ቀላል ነው!» ሲል ታረቀኝ በማስጠንቀቅ አኳኋን አንደበቱን ከፍ አድርጎ ተናገረ፡፡

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ድንገት ከእንቅልፍ እንደ ባነነ ሰው ዞር ብለው ማናዬን በመማጠን ተመለከቱት፡፡

«ከዚያ የቆመች አንድ ፔጆ አለች፡፡» ማናዬ የመኪናዋን ቊልፍ ከኪሱ አውጥቶ እጁን ዘረጋ፡፡

እነታረቀኝ አውቶሞቢሏን ተመልክተው ከተመለሱ በኋላ ቁልፉን መልሰው ሲሰጡት ማናዬ የባሰ ግራ ገባው፡፡ «ምን ሳርገው?» ሲል ጠየቀ፡፡

«ከእናንተው ጋር ይቆይ፡፡ አሁን ለመመዝገብ ነው እንጂ ለመውሰድ አይመጣንም፡፡»

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ትንሽ ነፍሳቸው ተመለሰ። «ኧረ የኔውስ ስንኳን ስጦታ አይባልም! ባለቤቴ ባርበኝነት ላፈሰሱት ደም እንደ ውለታ ተቈጥሮ የተሰጠኝ ነው እንጂ!» የባላቸውን ደጃዝማችነት ሳይጠቅሱ ያለፉት አውቀው ነበር።

ወጣቶቹ ከግቢው ሲወጡ ዳመናው የቋጠረውን ሽክም ይዘረግፈው ገባ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዱላ ፍለጋ እየተንደረደሩ ወደ ቤት ውስጥ ገቡ። የሚበርድላቸው የሚወጣላቸው በእሱው ነው። በማድ ቤት ውስጥ ክክ በመልቀም ላይ የነበረችውን የዘይኔን ወጣትነትና ወዘና ሲመለከቱ ደግሞ ግፊት አየለባቸው። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ማናዬ ፊቱን እየዞረ የሚተኛባቸው መች ያለ ምክንያት ይሆናል? የሚል ጥርጣሬ ውልብ አለባቸው። ከገረድ ላይ መለክስከስን ከደጃዝማች ገሠሠ ጠባይ ያውቁታልና።

የዱላው ጫፍ የማድቤቱን ጣሪያ እስኪነካ ድረስ ወደ ላይ ሊያነሡትና ዘይኔ በድንጋጤ ቀና ስትል አንድ ሆነ።

## ፲፭

እነታረቀኝ ዝናሙ እስቲያባራ ድረስ ከአንድ ሱቅ ውስጥ ተጠልለው በመጨረሻ ስለ ገቡበት ቤት ሁናቴ በመገረምና በመሳሳቅ እየተጨዋወቱ ሲጋራ ያጨሳሉ። ጥቂት ቀደም ሲል፥ በነጐድጓድ በዶፍና በጣሪያው ቆርቆሮ ድምፅ መካከል የኡኡታ ድምጽ የሰሙ መስሏቸው ነበር። እምብዛም አልታሰባቸውም። ከሚወርድባት ዝናም እኩል ዕንባዋ የሚወርደው ዘይኔ መጥታ ከቤቱ ታዛ ስትጠጋ እንደ ዋዛ ዓይተው ጨዋታቸውን እንደ ቀጠሉ ከዝናሙ አለመዳኗ ተመለከቱና፥ «ወደ ውስጥ ብትገቢ አይሻልም? የዚህ የዚህ ገላጣው ሜዳ ምን አለሽ?» አሏት። ሷቋ ታዛ ስላልነበራት ከካፊያው የምታስጠልል አልነበረችም። አንገቷን ደፍታ እየተንሰቀሰቀች ገብታ ከመደብሩ ጥግ ቆመች። ጨርቅ ቢጤ በጉያዋ ሸጉጣ እንዳይታወቅባት አቀርቅራ እችለው ስትል ከንፈሯን ነክሳ ሕቅታው ገንፍሎ ሲወጣባት ሰውነቷ የሚተረተር ይመስላል። ከእጆዋና ከአገጭዋ ላይ የፍንክታና የቡጭራት ምልክት አለ።

«ምን ሆነሽ ነው?»

መልስ የለም። ደጋግመው ጠየቋት። ከመንሰቅሰቅ በቀር - ምንም።

«የዚህ ሠፈር ሰው ናት?» ሲሉ ባለሱቁን ጠየቁት ከባሏ ጋር የተጣላች መስሏቸው።

«ከዚያ ግቢ የምትሠራ ናት መሰለኝ» ሲል ባለ ሱቁ በጭንቅላቱ እያመለከተ መለሰ።

«የማን ግቢ ነው?»

«የወይዘሮ ዘርፈሽዋል።»

«ማናቸው እሳቸው?»

«ደጃዝማች ባል ነበራቸው ሞተዋል አሉ። ሴትዮዋ የቤተ መንግሥት ሰው ናቸው ይላሉ። ገረድ አይቀመጥላቸውም።»

«ታዲያ ከሥራ ወጣሁ ብለሽ ነው እንዲህ የምትሆኚውን? አይዞሽ አዲስ አበባ እንደሆነ ሌላው ቢቀር ግርድና አይጠፋም»

«ከዚህ ሁሉ መከራ ምነው እንደ ዘመዶቼ እዚያው ወሎ አፈር በበላኝ!» መንሰቅሰቁ ባሰባት:: በስንት ውትወታ ልቅሶው በረድ ብሎላት ያደረጓትን ሁሉ ነገረቻቸው:: «አገሩን አላውቀው:: አሁን የት አባቴ ልገባ ነው?» ዘይኔን መሪር የኀዘን ትዝታ አኰማተራትና እንደመንቀጥቀጥ ቃጣት::

«እንዴት መጣሽ ከወሎ?

«እሳቸው ናቸው ከደሴ ያመጡኝ::»

ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ የቆመችው ፔጆና ሾላ ላይ ካሣሁን ተከትሏት የሮጠው ፔጆ ድንገት ተገናዘበባቸው::

«ስንት ግዜሽ ይሆናል ከመጣሽ!»

ጥቂት አሰበች:: «አሁንማ መንፈቅ መሆኑ ነው::»

እነታረቀኝ በመግባባት እርስ በርሳቸው ተያዩ:: «ስምሽ ማነው?» ዘይኔ እንደ ቆቅ በጥርጣሬ ነቃች:: እሷ የምታውቀው ምስለኔ ጭቃ፥ ሹም ስም ጠይቆ ግብር ሲያስከፍል እህል ሲያስጭን ነው:: የአገር ቤት ሰው ሁሉ ይህንን አሳምሮ ስለሚያውቀው ስሙንም መንደሩንም በቀላሉ አይገልጽም::

መልስ ሳትሰጥ ኰስተር ብላ አቀረቀረች::

«አትናገሪም? ስም የለሽም እንዴ?»

«ወንጀል የለብኝም::»

«ስም የሚጠይቀው ለወንጀል ብቻ ነው እንዴ?»

መልስ አልሰጣቸውም:: መደበቋ ግን ያስታውቅ ነበር::

«አንች ዘይኔ አይደለሽም?» ሲል ቦጋለ በድንገት ጠየቃት:: ከአንድ የስለላ መስሐፍ እንዳነበበው በማስደንገጥ ለማስወጣት::

«ኧረ አይደለሁም!» ብላ ከመመለሷ በፊትም ሳታስበው መደንገጥዋ ያለ ጥርጥር ግልጽ ሆኖ ታየባት::

ሦስቱም በመግባባት ተያዩና በመንሾካሾክ ተመካከሩ:: ከዚያም ታረቀኝ የባሰውን አስደንጋጭ ጥያቄ ተኰሰባት::

«ዘይኔ ሙሔ ከሆንሽ፥ ካሣሁን.....»

«ም - ም - ም?» የቆመችበት ቋንጃዋ ከሥር የከዳት ይመስል ተዝለፈለፈች::

«አይዞሽ ደህና ነው:: እናገናኝሻለን::»

ዙሪያውን ከበቧት፡፡

«አራት ኮካኮላ! ዝናም ቢሆንም ሞቆናል!»

የደስታና የቀልድ ሳቅ በትንሽዋ ሱቅ ውስጥ አስተጋባ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

ኃይለ ሥላሴ በቮልስዋገን ተጭነው ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር በመወሰድ ላይ እንዳሉ፣ በመገዱ ዳር የቆመውና የሚተላለፈው ሰው፣ «ሌባ! ሌባ!» እያለ ይጮሃል፡፡ «ምንድነው የሚሉት?» ሲሉ ከሹፌሩ ጐን የተቀመጠውን መለዮ ለባሽ ጠየቁት፡፡ «ሌባ ሌባ! ይላሉ» ብሎ ሲመልስላቸው «ታዲያ ምን ያርግ ሕዝቡ፤ በጠራራ ፀሐይ ንጉሡን ስትሰርቁበት» አሉ ይባላል፡፡

መስከረም ፳፯ ዓ.ም ቀልድ፡፡

ኃይለ ሥላሴ ያላንዳች ግርግር ከዙፋን ቢወርዱም፥ ሥልሳ ሰባት መስከረም ይዞ፥ ጥቅምትን፥ ኅዳርን ታኅሣሥን፥ ይዞ የፖለቲካው ነውጥ በመብረድ ፋንታ እየባሰበት ሄደ፡፡ መለዮ ለባሹ ለደመውዝ ጭማሪው ብቻ ተነሣ እንዳይባል ለጊዜው አንገራግሮ ወደ ሠፈሩ፥ ንጉሡም ወደ ሙሉ እምኩልሄ ሥልጣናቸው ይመለሳሉ፥ ብሎ በተስፋ ሲጠባበቁ የቆየው ወገን ሁሉ አሁን በየጐራው እያደፈጠ ጥርሱን ያፋጭ ገባ፡፡ ምን - ምን ይተካ? የሚለው ጥያቄ ኃይለ ሥላሴ ይውረድ ይል የነበረውን ሠፈር ከሁለት ከፍሎ አፋጠጠው፤ አተራመሰው፤ አፋጨው፡፡

ከሁሉ በፊት ኢ.ሠ.አ.ማ በመስከረም መጀመሪያ ላይ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ እስከ መስከረም ሁለት የተወሰዱትን እርምጃዎች ከደገፈ በኋላ የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር ያወጣውን የጊዜያው ወታደራዊ አስተዳደር አዋጅ በመቃወም ውሳኔ አስተላለፈ፡፡ በወሰደው አቋም ለሚፈጠረው ችግር ከዳር - ዳር በጠንቀቅ ተዘጋጅቶ በመጠባበቅ ላይ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተለይ በተማሪውና በመምህራኑ አካባቢ ከፍተኛ የመከፋፈል ሁናቴ የፈጠረው የዕድገት በሕብረት ዘመቻ ነበር፡፡ በነሐሴ ወር የዘመቻው ሐሳብ ሲጠነሰስ ብበዙ ሰዎች ዘንድ አንድ ሰሞን ተራግቦ በወሬ ብቻ እንደሚቀየር ተገምቶ ነበር፡፡ በኋላ መምሪያ ሲቋቋምለትና መዝመትም ግዴታ ሆኖ ፕሮግራም ሲወጣለት፥ የተጧጧፈ ክርክርና አስላለፍ አስከተለ፡፡

በወታደሩም አካባቢ ቢሆን አንዳንድ ሁኔታዎች ተፈጠሩ፡፡

የአዲስ አበባ ሕይወት እንደ ክራር ጅማት ተወጠረ፡፡ ዛሬ ምን ይመጣ ይሆን? ነገር ምን ይፈጠር ይሆን? ደርግ ለመውደቅ ስንት ቀን ቀረው? ሁሉም እንደ ዝንባሌው በተስፋ ጠበቀ ወይም ተጨነቀ፡፡ ነገር ግን የሚያደበላልቅ ሁናቴ ሳይፈጠር ሳምንታት አለፉ፡፡ በመሐንዲስ ሠፈር የተነሣው ሁከት ወደ ሌላ ሳይዛመት በዚያው ተገታ፡፡ የዘመቻው ጉዳይ በተማሪ አካባቢ ብቻ ሲጢያጢያስ ቆየ፡፡ እሱም ቢሆን ግዴታውን ያላሟላ ዘማች የትምህርትና የሥራ ማግኘት መብቱን እንደሚነፈግ ሲገልጽ፥ ከፊሉ ሲያጉረመርም አብዛኛው ተማሪ ግን ለመዝመት ይዘጋጅ ጀመር፡፡

ከዚያም በኅዳር ወር ውጥረቱን የሚበጥስ ባለተስፋውና የሚያስደነግጥ ባለጭንቀቱን የሚያስተነፍስ የዜና መብረቅ ወረደ፡፡

በዚህ ቀን ቦጋለ፥ ሾላ የሚኖሩ አክስቱን ለመጠየቅ በጧት ከቤት ውጥቶ ነበር። ታረቀኝና ማርቆስ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ መግለጫውን በሬዲዮ ሲሰሙ ለቅጽበት ብቻ በመገረም ራሳቸውን ቢይዙበትም ሳይዝኑም፥ ሳይደሰቱም ነገሩ ወዲያው ከአእምሮአቸው አስወጡት።

«በሰፈሩበት ቁና መሰፈር አይቀር» ሲል አስተያየት የሰጠበት ካሣሁን ብቻ ነበር።

ካሣሁን ሰሞኑን ከሆስፒታል ወጥቶ ከቤት በማገገም ላይ ነበር። ዘይኔም ምግብ በማብሰልና ቤት በማጽዳት እየረዳቻቸው አብራ ተቀምጣለች።

ዛሬ እንደ ዋዛ መቃለጃ ሊያደርጉት ካሣሁንና ዘይኔ፥ ሲገናኙ ትንግርት ነበር የታየው። ዘይኔ ከሆስፒታል ክፍል እስክትገባ እውነት አልመሰላትም ነበር። ከትራሱ ላይ ቀና ብሎ እንዳየችው በሽተኛው ሁሉ እስኪደናገጥና ነርስ እስኪ መጣ ድረስ እልልታዋን አደባለቀችው። ካሣሁንም ቢሆን ዓይኑን ማመን አቃተው። «ዘይኔ! ዘይኔ! ዘይኔ!» አለ እየደጋገመ የሚናገረው ጠፍቶት። እንደ አሁኑ ጊዜ በሾላ መንገድ ሲነግሯት እንባዋ ተንዠረዠረ። በኋላም በእርስዋና በቤተ ሰቦቻቸው ላይ ሁሉ የደረውሰውን ስትነግረው ደስታው ወደ ኀዘን ተለወጠ። ወደ ሀገሩ ለመመለስም ልቡ ተነሣ። ጤንነቱ ለጉዞ እስኪያበቃ ግን፥ ከነታረቀኝ ጋር ተጣብበው መቆየት ግድ ሆነባቸው። መጣበባቸውን ትንሽ ለማቃለል አባተ ወደ ሌሎች ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ።

ቦጋለ ዓይኑ በርበሬ መስሎ፥ ፊቱ እንደ ማባበጥ ብሎ ከቀጥር ላይ ተለመለሰና የቤቱን ዕቃ ያተረማምሰው ገባ። ከግድግዳው ላይ በሚስማር ተንጠልጥለው የነበሩትን ልብሶቹን ደብተሮቹንና መጻሕፍቱን በሻንጣው ውስጥ ይጒስጒሳል። ከእርሱው ጋር ተቀላቅለው የነበሩትን የጓደኞቹን ንብረት ከወዲያ ወዲህ ወለሉ ላይ ይጥላል።

ታረቀኝ ከሚያነበው መጽሐፍ ማርቆስ ሥራ ላለመፍታት ከሚጫጭረው ሥዕል እንደ ዋዛ ቀና እያሉ ሲመለከቱት ቆዩና፥ ኮዳ የጨበጠውን እጁን ዘርግቶ «ይህንን የሚፈልግ ካለ ይውሰድ» ሲላቸው የያዙትን ሥራ ቁመው በመገረም አስተዋሉት።

«ለምን?»

«እኔ አልፈገውማ!» አለ ቦጋልከ በሸካራ ድምፅ።

«ለምን?»

«አልዘምትማ።»

«አክስቴን እጠይቃለሁ ብለህ ከእነገበየሁ ጋር ዋልክ እንዴ?» የታረቀኝ ጥያቄ የፌዝ ቃና ነበረበት።

«አልዋልኩም እንጂ ብውልም ወንጀል አይደለም። ከአንተ ጋር ስለ ተጣላ እኔ ጓደኝነቱን የምሰርዝበት ምንም ምክንያት የለም።»

ቦጋለ ያመጣው አዲስ ጠባይ ካሣሁንን ሳይቀር አስገረመው።

«እሱን ማለቴ እንዳልሆነ ታውቀዋለህ። ታዲያ አልዘምትምን ምን አመጣው?» ሲል ታረቀኝ አነጋገሩኡን መለስ አድርጎ ጠየቀ። ገበየሁ ጓደኛው ከመጸዳጃ ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ከሞት ጊዜ አንሥቶ፥

መንገድና ሰበብ ባጋጠማቸው ቍጥር ታረቀኝን በአስተያየቱ «ጠብቅ! አትርሳ!» እያለ የሚዝትበት ከመሆኑም ሌላ የራሱን የፖለቲካ ክልል ፈጥሮ እያሰፋ በመሄድ ላይ ነው። ታረቀኝ ዘመቻውን በመደገፍ እንደ ተነሣ ሲረዳ እሱ ደግሞ ዘመቻውን ለሚቃወሙ ክፍሎች እንደ መሪም እንደ ቃል አቀባይም መሆን ያዘ።

«የዘመቻ ትጥቅህን ካዘጋጀህ በኋላ?» ማርቆስ ለጠቅ አደረገ።

«ሰው ሐሳቡን ሊቀይር አይችልም? የተሳሳተ አይታረምም? ያላወቀ አይረዳም?» ቦጋለ በአነጋገሩ እንደ ጨኸት ቃጣው።

«እርግጥ! እርግጥ ልክ ነህ። በዚህ ነጥብ ግን ትክክል ስለ መሆኑና አለ መሆኑ ብዙ ሳምንታት ተወያይተንበት፥ ተከራክረንበት ከስምምነት የደረስን ይመስለኛል። አሁን በጥቂት ሰዓት ውስጥ ሐሳብ የሚያስቀይር በቂ ምክንያት ልኖርህ ይገባል»። ታረቀኝ ፍርጥም አርጎ ተናገረ።

ካሣሁን በመሐሉ ለጠቀ። «ዘመቻው ለማይምና መከረኛ ለሆነው ያገሬ ሰው የሚበጅ ለመሆኑ እሱስ አንድና ሁለት የለውም። እኔ ስንኳ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አወቅሁ። ወዳጄንም ጠላቴንም። እናንተም እንደምትሉት ውጤትንም - ምህኛትንም።

ቦጋለ አገጩን በሁለት መዳፉ ደግፎ ከፕላስቲክ ሻንጣው ላይ ተቀመጠ። «ዘመቻው ሕዝቡን ይጠቅመው ይሆናል ግን……» በማለት ሐሳቡን ገታው።

«ታዲያ እኛ ምን ቸገረን ዘመቻው ሕዝቡን ከጠቀመው፥ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው፥ እንደሚባለውም ከስንት ዓመት በፊት አንሥቶ የትጥቅ ትግል እያልን በአራት ኪሎ አካባቢ የምንከራከርበት በዚህ መልሱን የሚያገኝ ይመስለኛል። የትጥቅ ትግሉን የሚያካሄደው ሕዝቡ ራሱ ሲያውቅ ነው።»

ቦጋለ ራሱን ነቀነቀ። «የለም እንዳናስቸግራቸው ከሆነ ዓላማው ልክ አይደለም። እኛም ሰላም አንሰጣቸውም።» መሐረሙን አውጥቶ አፍንጫውንም ዓይኑንም እንደ መጥረግ አለ።

«ለምን?» አስተሳሰባቸው የተጋጠመ ይመስል፥ ታረቀኝም ማርቆስም ባንድ ጊዜ ተናገሩ።

«ልክ አይደለማ?» ቦጋለ መልሱን ለማረጋገጥ ተወራጨ።

«ምኑ ልክ አይደለም?» ጥያቄው በተረጋጋ ሁናቴ ቀረበለት።

«ልክ - አይደለም! ልክ አይደለም!» ቦጋለ ትከሻውን ነቀነቀ።

«ለትምህርት ፈተና እንደዚህ ያለ መልስ ትሰጣለህ?» ሁለቱም የትምህርት ቤት ባልንጀሮቹ አፍጥጠው ተመለከቱትና። «እንደዚህ ብትመልስስ ልክ ነው?»

«አሁን ስለ ትምህርት ፈተና አይደለም የምናገረው።»

«እህስ?» የባልጀሮቹ ዓይኖች አነጣጠሩበት። «ዘመቻችንም ከሕይወት ጋር የተያያዘ ነው። ከገጠሬ ሕይወት ጋር።»

ቦጋለ ወጥመድ ውስጥ እንደ ገባ አውሬ ዓይኑን በሦስቱም ላይ አቁለጨለጨና ጫን ተነፈሰ። «ሌላም ሕይወት፥ የሌላም ሕይወት አለ። ዛሬ የሆነውን አልሰማችሁም ማለት ነው?»

«ምኑን?»

«ፈጁዋችው» አለ ረገጥ አድርጎ።

«የቀድሞ ባለሥልጣኖችን ማለትህ ነው? እና?»

«ምን እንደ ቀላል ነገር እና? ያሰኛል። ትክክል አይደለማ!»

«እሱ ሌላ ጉዳይ ነው» ማርቆስ ረጋ ብሎ ተናገረ። «ትክክል መሆኑና አለመሆኑን ለመፍረድ አስቀድሞ የክሱን ዓይነት፥ የተከሳሹን መከላከያ የዳኞቹን ትችት ማወቅ ይኖርብናል። ዛሬ የሰማነው ግን በአጠቃላይ የአስተዳደር በደል ያደረሱ የፍርድ መጓደል የፈጸሙ የቀድሞ ባለሥልጣኖች፥ የሕዝቡንና የወታደሩን ንቅናቄ ለማደናቀፍ የሞከሩ ሥልሳ ሰዎች በከፍተኛ የፖለቲካ ውሳኔ የሞት ቅጣት የተፈጸመባቸው መሆኑን ነው። እኛ ራሳችንም ቢሆን እነዚኢሁ ባለሥልጣኖች ለፍርድ ይቅረቡ ይቀጡ እያልን ሰላማዊ ሰልፍ ስናደርግ ነበር። አሁንም የሆነው ይኸው ነው።»

«እኛስ በየመንደሩ እየጨፈርን አልነበር?» አለ ካሣሁን ቀበል አድርጎ።

ቦጋለ ዓይኑን በልጥጦ አንገቱን ሰገግ አደረገና፥ «ልክ አልነበረም ያልነዋ ነዋ! ይኸኛውም ልክ አይደለም።»

«በመግለጫው እንደተነገረው ለፍርድ ቀርበው ነው የተቀጡት። ግን እሰጥ አገባ ላይኖረው ይችላል። ማለቴ ተስማማንበትም አልተስማማንበትም ወታደሮቹ ንቅናቄ የሚሉት ይዘቱ አብዮት ከሆነ፥ ሙግትን ምን ያመጣዋል? ማን ተሟጋች ማን አሟጋች ማን ጠበቃ ማን ምስክር ሊሆን? በእንደዚህ ያለ ጊዜ ፖለቲካዊ እርምጃ ፖለቲካዊ ፍርድ መሆኑን ከብዙ አብዮቶች ታሪክ ተነሥተን የተነጋገርንበት ይመስለኛል። ቁም ነገሩ ንጹሐን ከወንጀለኛው ከመለየቱ ላይ ነው። እንዲያውም ድሮም ሲታረድ፥ ዝንብም ሲጨፈለቅ ሆደ ቡቡ መሆን አያስፈልግም።» ታረቀኝ ከተቀመጠበት ተነሣና ለማጽናናት ያህል የቦጋለን ትከሻ በእጁ ጭፍልቅ ጭፍልቅ እያደረገ፥ «መበረታታት ነው እንጂ! መበርታት ነው እንጂ» አለ።

ቦጋለ ኮረንቲ እንደ ያዘው ሰውነቱ እንደ መኰማተር እንደ መንቀጥቀጥ አለ። ተወራጭቶ ተነሣ። ከዚያም ፊቱን በሁለት እጁ ሸፍኖ ከራስ እስከ እግሩ ቀላል ነፋስ እንደ ነካው ሰንበሌጥ በቀስታ ግራና ቀኝ እያዘመመ «አንደኛው እኮ አባቴ ነው» አለ። ታረቀኝ የራሱ ጀርባና ቋንጃ ከቆመበት እየከዳው እንደ ምንም ደግፎ ከሻንጣው ላይ አስቀመጠው። ክፍሉ ጸጥ እርጭ አለ። የትንኞቹ በረራ ድምፅ እንኳ ድንገት የቆመ መሰለ። ካሣሁን አንገቱን ቀና እንዳደረገ ዘይኔ ከክፍሉ አንድ ጥግ ተሸጉጣ የካሣሁንን ሱሪ ለመጥቀም መርፌውን እንደ ሰካች፥ ሁሉም በያለበት ደረቀ። «አዎ! አዎ!» አለ ቦጋለ በሰመመን ድምፅ፥ «ከተገደሉት ባለሥልጣኖች አንዱ የኔ አባት ነበር።»

«ማን?» የሚል የለሆሳስ ድምፅ ተሰማ።

ስሙን ተናገረ።

«ግን የምትጠራበት የአባትህ ስም ሌላ ነው፡፡»

«አዎ! የምታውቁት አይደል የሀገራችንን አንዳንድ ብስብስ ባሕል፡፡ ጌታ ባል ከገረዱ እመቤት፥ ሚስት ከሎሌል ሲል ቦጋለ ጀመረ፡፡ «አባቴ በጽሕፈት ሚኒስቴር ሥራ እንደ ጀመረ መልከ ቀና ነውና የመሳፍንት ዝርያ የሆኑት የአሁኑ ሚስቱ ዓይናቸውን ይጥሉበታል - እምቢልታ መለከት የሚሰማው የት ነው፥ አንድም በስርቆሽ በር አንድም በግቢ ነው - እንደ ተባለው ከእርሱ በኩል፥ እምቢ ማለቱን ፈርቶ ወይም ለዕድገት ለሹመት ለሽልማት ይጠቅመኛል ብሎ ይሆናል እንጂ የፍቅር ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሴትዮዋ ሁለት ጊዜ አግብተው የፈቱ በዕድሜ ከእርሱ በጣም የጠኑ ነበሩ፡፡ ያም ሆነ ይህ፥ ተጋብተው ሲኖሩ እናቴ ከቤታቸው ግርድና ትቀጠራለች፡፡ እመቤቲቱ እንዳይሰሙና እንዳያውቁ ከቤት እንድትወጣ ያደርጋል፡፡ እኔ ስወለድም ሌላ የአባት ስም ይሰጠኛል፡፡»

ቦጋለ ከሰውነቱ ውስጥ የወጠረው ነገር ድንገት የተነፈሰለት ይመስል ሲቃውና መወራጨቱ ጋብ ብሎለት ታሪኩን ያወጋቸው ረጋ ባለ ሁኔታ ነበር፡፡ የአባቱን ሞት የተረዳ ኀዘንተኛ ሳይሆን የድሮ ትዝታ እንደሚተርክ፡፡ «እና፥ ከተገደሉት መካከል አንዱ የእኔ አባት ነው» አለ፥ ታሪኩን ሲጨርስ፥ የረሳውን ቁም ነገር ድንገት ያስታወሰ ይመስል፡፡

ሲጋራ የያዘ ሰው እንዳለ ጠየቀ፡፡

«ኤዲያ!» አለ ካሣሁን ፈቀቅ ብሎ ከተጋደመበት «ልጅን የሚኢክድ የልጁን እናት የትም የሚጥል እነኢ አባት ነው አልለውም፡፡»

«የትም እኮ አልጣላትም፡፡» ቦጋለ ሲጋራ ሲያቀጣጥል እጁ እንደ መንቀጥቀጥ አለ፡፡ «ይረዳት ነበር፡፡ ይህንን ቦታ ገዝቶ ይህንን ቤት አሠርቶ የሰጣትም እሱው ነው፡፡ እሷ ከሞተች በኋላ ግን ብቻዬን መኖር ስለማልችል ዩኒቨርሲቲ እስክገባ አክስቴ ወስዳ አሳደገችኝ፡፡»

«ግን አትተዋወቁም ነበር?» ሲል ታረቀኝ ጠየቀው፡፡

«ለምን አንተዋወቅም? የሚያስፈልገኝን ሁሉ በድብቅ ይሰጠኝ ነበር፡፡»

ለሁለት ጓደኞቹ አሁን አንዳንድ ነገሮች ግልጽ እየሆኑላቸው ሄዱ - አክስቴ ጠላ እየሸጠች ያሳደገችኝ ደሃ ነኝ ይላቸዋል - ግን ገንዘብ ከኪሱ አይጠፋም ነበር፡፡ አንዳንድ ልብሶቹም ምርጥ ነበሩ፡፡

«ያም ሆኖ በእርሱ የአባትነት ስም እንድጠራ ፈቃደኛ አልነበረም» አለው ማርቆስ ትኩር ብሎ እየተመለከተው፡፡

«የአባትነት ስሙን ብቻ ሳይሆን ሀብቱንም ጭምር ሊያወርሰኝ ነበር፡፡»

ቦጋለ ሲጋራውን በኃይል እየሳበ መወራጨቱ ተነሣበት፡፡ «አንድ ልጁ እኔ ብቻ ነኝ፡፡ ሴትዮዋ የማኅፀን ካንሰር ስለነበረባቸው አልወለዱም፡፡ ግን በጣም ይፈራቸው ነበር፡፡ እሳቸውንም ብቻ ሳይሆን ዘመዳቸው ናቸው የሚባሉትን ንጉሡን፡፡ ሴትዮዋ አሁን ዕድሜያቸው ገፍቷል፡፡ እስኪሞቱ ነበር የሚጠብቀው፡፡»

«ግን የታሰበው ሳይሆን ቀረና ውርስ ከእጅህ አመለጠ፡፡» ታረቀኝ በሚገባ አውቀዋለሁ ይል የነበረውን የረጅም ጊዜ ጓደኛውን ይዘንለት - ወይም ይጠየፈው ግራ ገባው፡፡

«አይደለም!» አለ ቦጋለ በጩኸት፡፡ ተነሥቶ ተንቆራጠጠ፡፡ «አባቴ ነው፡፡ ሥጋውና ደሙ ነኝ፡፡»

«አባትህ ሥልጣን የያዘበትን መንግሥት ለምን ስትቃወም ቆየህ?» ማርቆስ እንደ ዋዛ ጠየቀ፡፡

ቦጋለ አዲስ ምሥጢር በድንገት የተገለጠለት ይመስል በመገረም ዓይኑን ብልጥጥ አደረገ፡፡ «እውነቱን ለመናገር አላውቅም፡፡ ምናልባት የእኔን ሕይወት የእኔን ሥጋና ደም በቀጥታ የማይነካ መስሎ ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ሳይታወቀኝ በሥውር ሕሊናዬ ከሥልጣን መውረድ አባቴን ከሚስቱ ፍራቻ ነፃ የሚያወጣው መስሎኝ ሊሆን ይችላል፡፡»

እውነቱ በመናገሩ ሁሉም በአዘኔታ ራሳቸውን ነቀነቁለት፡፡

«ታዲያ አሁን ሻንታ መጠቅለልህ ለምንድ ነው? ዘመቻውንስ እሺ ተወው፡፡»

«አብረን መኖር አንችልም፡፡ በአንድ ጣሪያ ሥር አብረን ከኖርን መከራከራችን ስለማይቀር መጨቃጨቃችን ከተጨቃጨቅን ደግሞ መጋጨታችን ስለማይቀር ከክፉ ነገር እንዳረሳለን፡፡» የሻንጣውን መሸርገጊያ ገጠመና ተነሣ፡፡

«ከሆነም አንተ የምትሄድበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ የራስህ ቤት ስለሆነ እኛው መሂድ ይኖርብናል» ሲል ታረቀኝ አስታወቀ፡፡

«የለም፡፡ የለም፡፡ መስመራችን ተለያየ እንጂ እኛኮ አሁን ተጣልተናል ማለት አይደለም፡፡ ጓደኞሞች ሆነን ኖረናል፡፡ እነ ካሣሁንም የሚያርፉበት የላቸውም፡፡ ዘመቻ እስክትሄዱ ቆዩበት፡፡ እኔ ካክስቴ ዘንድ ማረፍ እችላለሁ፡፡ እንዲያውም ብቸኝነት እየተሰማት ስለ ሄደ ደስ ይላታል፡፡»

የእጅ ሰላምታ እየተለዋወጡ ሲሰናበታቸው ቦጋለ ዕንባው በዓይኑ ላይ ተንቁረዘዘ፡፡

«ወይ እንገናኝ ይሆናል፡፡ ወይም አንገናኝም» አላቸው፡፡

የአጥሩን በር ሲወጣ ሁሉ ዞር ብሎ አልተመለከተም፡፡

ለረጅም ጊዜ ሁሉም በዝምታ ተውጠው ከቆዩ በኋላ፥ «ማርቆስ ነገሮቹ እየተባባሱ ሳይሄዱ እኛም እንንቀሳቀስ እንጂ» ሲል ታረቀኝ ጓደኛውን ከሐሳቡ ሰመመን አነቃው፡፡ በአፋጣኝ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ሳይነጋገሩ ሁለቱም ተሰምቶአቸዋል፡፡

ቦጋለ ከዘመቻው ደጋፊዎች አንዱና ዋናው ነበር፡፡ በማወላወል ላይ የነበሩ ብዙ ተማሪዎችንም አግባብቶ አሳምኗል፡፡ የእርሱ አቋም መቀየር ብዙ ተማሪዎችን ከዘመቻ ድጋፍ ሊያስበረግግ ይችላል፡፡ ገበየሁ ደግሞ አሳምሮ ሊጠቀምበት ይሞክራል፡፡ እየተዘዋወሩ መመካከርና ማስረዳት አለባቸው፡፡ ምናልባትም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የቦጋለን ትክክለኛ ምክንያት ማጋለጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ዓለማ ለጓደኝነት አይሠዋም! ጓደኝነት ለዓላማ እንጂ፡፡

«ማታ ያልተመለስን እንደሆን ለእኛ አታስቡ» በማለት ካሣሁንና ዘይኔን ለብቻቸው ትተዋቸው ሄዱ፡፡

፪

ታረቀኝና ማርቆስ ማምሻውን ሳይመጡ ቀሩ። ካሣሁንና ዘይኔ በዚያች ቤት ውስጥ ሁለቱ ብቻቸውን ሲያድሩ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ዘይኔ ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ ደስ ደስ አላት። ልቧ ካሣሁንን ይፈልገዋል። የፍቅር ስሜት፥ የተፈጥሮ ስሜት። ግን በሆስፒታሉም ሆነ በዚህች ቤት ለብቻቸው የሚዝናኑበት አጋጣሚ ከቶ አላገኙም ነበር። ካሣሁን ገመምተኛ በመሆኑ ለብቻው አንድ አልጋ ተሰጥቶት ይተኛል። እርስዋ ደግሞ የምትተኛው ወደ ትንሿ ማድ ቤት የሚያስተላልፈውን ግድግዳ ጥግ ይዛ ከመሬት ላይ ነበር - በቤቱ ውስጥ የተገኘውን ደባደቦ ቢጤ አንጥፋ። አንድ ቀን ቦጋለ «ለምን ከባልሽ ጋር አትተኚም» አላት እንደ ዋዛ። ግን ያ - ሁሉ ሰው ብ አለበት ፍፍል እንዴት በአንድ አልጋ ላይ ከባልዋ ጋር ልትተኛ ትችላለች? መብራቱ እየበራ ልብስዋን አውልቃ? በዚህ ላይ ደግሞ ካሣሁን «ነይ ይበቃናል» ብሎ አላደፋፈራትም። ሌሎችም አስተያየት አልሰጡም። «አይ! እኔ በዚህ ነው የሚመቸኝ፥ ከበሽተኛ ጋር ምን አጋፋኝ» ስትል የተለመደ የመኝታ ቦታዋን ያዘች። ቀንም ቢሆን ያው ነው። ጓደኞቻቸው ያለማቋረጥ ይመጣሉ። ያለ ማቋረጥ ሻይ እየተፈላ ሲነታረኩ ይውላሉ። ናፍቃው መክረሟን ስታስብ ልብዋ ታምቡር ይመታ ጀመር። ናፍቆት ስሜት፥ ከወዲያ ወዲህ በደስታ አንጐራደዳት። ካሣሁን ግን የጓደኞቹን እንዲህ መሆን አስገርሞት የሐሳብ ሰመመን ይዞታል። አንዳንድ ጊዜ ነገራቸው ይገባዋል። ሌላ ጊዜ አይገባውም። «አሁን የዛሬውን ምን ይሉታል? ያንን ሁሉ ሥቃይ አብረው ሲቀበሉኡ ኖሩ። አሁን ታዲያ እንዲህ መሆናቸው ምን ይባላል!» ካሣሁን ከሰውነቱ ድካም ጋር እንደ እንቅልፍም እንደ ቅዠትም ሳብ አድርጎ ወሰደው።

ዘይኔ በፍቅርም በኀዘኔታም ጐንበስ ብላ ተመለከተችውና ወደ ጓዳ ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች። ለምሳ የተሠራውን ሽሮ ትንሽ ቅባት አክላ አፍላላችው። እንደ ሽሮ እያዘገመ ትክ - ትክ በማለት ፈንታ በፍጥነት ቱስ - ቱስ - ቱስ ጨ - ጨ - ጨ - አለ። ቅባቱ ከላይ ተንቸረፈፈ። ካሣሁን ወደ ተጋደመበት አልጋ እየተመለከተች መዳፍዋን በማፋተግ አሁንም አሰበች። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አብዛኛውን ደሞዝዋን አስቀርተውባታል። ረጋ ብሎ መተሳሰብ ቀርቶ ነፍስዋን አድና መውጣቷ ተአምር ነበር። ግን በየወራቱ እየቁረጡ ከሚሰጥዋት ያጠራቀመችው ከአሥር ብር በላይ አላት። ሰዓት ዕላፊው እየተቃረበ ነው። «ፎሊስ ይይዘኝ ይሆን? ባወጣ ያውጣው» አለች ካራሷ ጋር። ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ተብሏል። ፎሊስም አንድ ቀን ጣቢያ ቢያሳድራት ገንዘቡም ቢጠፋ ካሣሁንን ይህንን ያህል ወራት በናፍቆት ከጠበቀች አይብስም። ትንሿን ሽቶ፥ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት እንዳየችው «ያ ስንጥር የሚመስለው ሽቶ» ብላ በአሥር ሣንቲም ሰንደል ከአቅራቢያው ገዝታ ተመለሰች።

ሁሉን ነገር ከአሰናዳች በኋላ «ካሣሁን ተነሥ እንጂ እራትህን ብላ!» አለችው በቁልምጫ፥ አንደበት። የቡናውም የእጣኑም፥ የሰንደሉም መዓዛ ሲያውደው «ምን እያረግሽ ነው ዘይኔ?» አለ ካሣሁን በፈገግታ የበዓል ቀን የጐጆው ትዝታ እየመጣበት።

«ምን አረግሁ?»

«ጥገኛ እኮ ነን። በሰው ቤት ሁሉ?» መልሶ ቅሬታ ተሰማው።

«እነሱም እኮ ደስ ነው የሚላቸው።»

«እኔ እንጃ እንዲህ ሲሆኑ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። ነገራቸው ብዙም አይገባኝም።»

ነገሩን በማቃለል «የሥጋ ትል የቤተ ዘመድ ጥል ይባላል። ስለይህም እንደ ቤት ጥል እንየው» አለችና ራት ማቅረብ ጀመረች።

ራት በልተው ጠጥተው ከጨረሱ በኋላ ካሣሁን ከአልጋው ላይ ተጋደመ - አሁንም ስለ ተማሪ ጓደኞቹና ስለ ዘይኔ እያሰበ:: ዘይኔ እቃውን ሁሉ ከከወነች በኋላ የግድግዳውን ጥግ ይዛ በመቆም ለረጅም ጊዜ አስተዋለችው:: አብረው እንደዚህ በሆኑ ዓመት ገዳማ አለፈ:: ካለ እርሱ ሌላ ወንድ አታውቅም:: የሌላ ወንድ ጠረን አልተላመደችም:: ግን የእርሱ ጠረን ምን ዓይነት ነበር? አልታወሳት አለ:: የምታስታውሰው ግን የሚያስደስት ጠረን እንደ ነበረው ነው::

-ካሣሁን! ከስንት ጊዜ በኋላ ተገናኘን? - አለች በሐሳቧ:: ወደ ጓሮ ወጣ ብላ ተመለሰች:: ወደ ማድ ቤቱ ክፍል ገባ ብላ ሽቶዋን በሰውነቷ ላይ አርከፈከፈች:: የክፍሉን መብራት አጠፋችው:: ባልተዘጋው መስኮት በኩል የጨረቃ ጨረር በክፍሉ ውስጥ ተሰራጭቷል:: ከፊሉም ከካሣሁን አልጋ ላይ አርፎ ስብጥርጥር ያለ ልዩ ትርኢት ዘርግቷል::

ልብዋ እንደ ታንቡር ይመታ ጀመር:: ዓይኗን ጭፍን፥ ጥርሷን ንክስ አድርጋው ወደ አልጋው ሄደች:: ሰውነቷ እየተቃጠለ ልቧ እየቦረቀ.....::

ጠረኑ ምን ዓይነት ነበር? አልታወሳት አለ:: «እስቲ ጠጋ በል:: አይበቃንም?» አለችው ብርድ ልብሱን እየገለጠች:: ፈራ ተባ እያለ ክንዱን ዘርግቶ ተቀበላት:: ከዓመት በላይ ናፍቃው የቆየችው ገላው መካከል ሽጉጥ አለች:: የተንጨፈረረ ጸጕርዋን በእጁ እየዳሰሰ፥ መላ አካላቷን እየዳበሰ ዓይኑን ክድን አድርጎ በከንፈሩ ጉንጭዋን ግንባርዋን ከንፈርዋን፥ አንገቷን አሰሰ:: በአንድ በኩል ገላዋን በመታቀፉ ብቻ አንድ ዓይነት ደስታ ሲሰማው በሌላ በኩል ሐሳቡ እየተጨነቀ ሄደ:: እስከ አሁን ድረስ በጥርጣሬና በተስፋ መካከል ሲወዛወዝ ቆይቶ ነበር:: ጕረምሳ ሆኖ - ወሎ ሳለ - ወር እስከ ወር እንደዚህ ሆኖ አያውቅም ነበር:: ሽንት እንኳ ይወጥራል:: ግን ካገባ ጀምሮ ካለ ዘይኔ ሌላ ሴት አያውቅም:: ሌላ ሴትም መንፈሱ አልከጀለም ነበር:: ስለዚህ ይሆናል እንዲህ የሆንኩት እያለ በተስፋ ሲጽናና ቆይቶ ነበር:: አሁን ከገላው ተጣብቃ ምንም ነገር አልሆነም:: ዘይኔ ደግሞ መላ አካላቷ እየተቃጠለ ትጠብቃለች:: ከበደም የወይዘሮ ዘርፈሽዋል አሽከሮችም የጕረቤት ጕረምሳም በዓይኑ እየቀላወጠ በእጁ እየጐነተለ ሲያስቸግራት ሁሉ ስንት ወራት ስሜቷን ለጉማ ጠብቃዋለች - እንደዚህ ላለችው ቀን ስትል:: «ካሤ ስንት ቀን ሆነን? እንደኔ አልናፈቅሽኝም?» አለች ጭንቅላቷን ከአንገቱ ሥር ሽጉጣ ትንፋሿ ቍርጥ ቍርጥ እያለ:: ምንም:: በመጀመሪያ ግራ ገባት:: እየቆእይች ግን ነገር ብልጭ አለባት:: የጋለሞታ ፍቅር የለመዱ ወንዶች ከሚስቶቻቸው ጋር እምብዛም እንደሚሆኑ ሰምታለች:: ልባቸው ከጋለሞታዋ ጋር ስለሚቀር አካላቸውም በድን ይሆናል:: አዎ! ካሣሁንም አገር ምድሩ በጋለሞታ ከተሞላው የአዲስ አበባ ከተማ ከገባ ብዙ ጊዜም ነው:: አንድዋ ነድፋዋለች ማለት ነው:: እስዋ ስለርሱ ስትጨነቅና ስሜቷን አመንዥሳ ስትጠብቀው እሱ ከጋለሞታ ጋር ዓለሙን እያየ ኑሮአል:: ጠረኑ ለመለወጥ እርግጠኛ ባትሆንም ገላው፥ ባንዴ ቀፈፋት:: ከአልጋው ተፈናጥራ ወረደችና «ውሻ! ውሻ! ልክስክስ ውሻ» ብላ ጮኸች:: ካሣሁም ከንፈሩን እየነከሰ ከአልጋው ወረደና ግድግዳውን ዳበስ ዳበስ አድርጎ የኤሌክትሪኩን መብራት ለኰሰው::

ሁለቱም እርቃናቸውን ነበሩ:: ተፋጠጡ::

ካሣሁን አንገቱን ደፋ አድርጎ ወደ ጭኑ ተመለከተና «ግናስ ለምን ትሳደቢያለሽ?» ሲል በታከተ ድምፅ ጠየቀ::

«አዎ ውሻ! ውሻ! ነህ! ልክስክስ! ለምን ከጋለሞታህ ጋር አትቀመጥም? በድን!» አለች ዘይኔ፥ እርቃን በሆነው ደረቷ ላይ ክንድዋን አጣፍታና ጥርሷን ነክሳ::

ካሣሁን በእንቅልፍ ልቡ እንደሚራመድ ሰው እየተንገዳገደ ከአልጋው ላይ ዘፍ አለ፡፡ «ሌላው ሁሉ ይቅርና በድን ማለትሽ ግን እውነት ነው፡፡ በድን ነኝ፡፡»

«ያዲሳባ ጋለሞታ ልብህን ስትሰርቀው ስትሰልበው ለምን በድን አትሆን!» አለች ዘይኔ በፈረጠመ አነጋገር፡፡

ካሣሁን ከጉሮሮው ላይ አንድ ነገር ተናነቀው፡፡ ኅዘን አይሉት ንዴት ልቅሶ አይሉት ፉከራ ከተቀመጠበት አልጋ ላይ ኩርምት ዝርግት አደረገው፡፡ «ጽድቁስ ቀርቶ በውል በኰነነኝ ይላል ያገሬ ሰው» አለ የተመጠመጠ አንጀቱን ስቦ የሚያወጣ ይመስል በረጅሙ ተንፍሶ፡፡ «እንደ ወንዶቹ ማመንዘሩ ቀርቶ እንደ ሰው በሆንኩ፡፡» አሁንም ጭኑን እንደ ማየት አለና ተወራጭቶ ገላውን በብርድ ልብሱ ሸፈነ፡፡ «አዎ! እንዳልሽው በድን ነኝ፡፡ ቅጥቅጥ ሙክት፡፡ አዎ! አኰላሽተውኛል፡፡ እንድነቴን ገድለውታል፡፡ ዘይኔ ከእኔ ወንድነት የለም፡፡ ገድለውታል፡፡ እርምሽን አውጪ፡፡ ወይም ወንድሺን ፈልጊ!»

አገጩን በመዳፉ ደግፎ ወባ የተነሳበት ይመስል ከእግር እስከ ራሱ ተንዘፈዘፈ፡፡ የይምሰል ሳይሆን ሰቀቀኑ ከልቡ መሆን ግልጽ ነበር፡፡ ዘይኔ አሁንም እርቃኑዋን እንደ ሆነች ከአልጋው ጠርዝ ተቀምጣ በሁለት እጅዋ ትከሻውን ጭምቅ አደረገችው፡፡

«ካሤ ምን ነካህ?» አደጋው ነው?»

«እ - እህ! እእህ!» ትዝታውን ከአእምሮው ውስጥ ለማጥፋት የሚሞክር ይመስል ዓይኖቹን ጭፍን አደረገ፡፡ «አደጋማ ቢዒሆን ለወሬ ይመቻል፡፡ ማንስ ቢሆን በአደን በጦርነት በጉግስ ሊደርስበት ይችል የለ? ሴት ያደረጉኝ እነዚያ አረመኔዎች ናቸው እንጂ?!»

ዘይኔ ከአንገቱ ላይ ተጠምጥማ ከአጽናናችውና ከወተወተችው በኂላ በፖሊስ ጣቢያ ምርመራ የደረሰበትን ሁሉ ነገራት፡፡ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፡፡ በአንድ በኩል የራሱንም ሰቀቀን ለመወጣት ዘይኔን እያባበለ አብሮ አለቀሰ፡፡ ለረጅም ጊዜ በተጋጠመው ፊታቸው መካከል ዕንባቸው ተቀላቅሎ ወረደ፡፡

«የወደፊት የራስሽ ምርጫ ነው፡፡ ለዘለቄታው የማይሻለኝ ከሆነ ወንድ ባል ልሆንልሽ እንደማልችል የታወቀ ነው፡፡» አለ አንገቱን ቀና እያደረገ፡፡

«እስቲ አሁን ዕረፍና ተኛ» አለች ዝይኔ ከአልጋው ላይ እያጋደመችውና ሰውነቷ ብቻ ሳይሆን መንፈሷ ሁሉ ጥምጥም አድርጎ እያቀፈው፡፡ «ግን ሰው እንዴት ጨካኝ ነው! ብቆይ ኖሮ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የኔንም ቢሆን በእሳት ጉርማጅ ያቃጥሉት ነበር፡፡ ሰንካላ ሆና እንደ ቀረችው እንኮዬ፡፡»

«አዎ! አንቺምኮ ተሠቃይተሻል እንዴ፡፡ እኚህ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሚባሉት ግን ምን ዓይነት ሴትዮ እንደ ሆኑ ማወቅ እፈልግ ነበር፡፡»

«አርፈህ ተቀመጥ!» በቁልምጫ ደረቱን ቆነጠጠችው፥ «እንዳንተ ያለውን ወንድ አይፈልጉም፡፡ ያስቀመጡት ወንድ አላቸው፡፡»

«አሮጊት አይደሉም እንዴ?»

«ስለ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አሁን ምን አስጨነቀህ?»

ሐሳቧ ግን ሳትወድ ቁምስቅል ያየችበትን ያንን ግቢ አመጣባት፡፡

## ፫

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አዲሱን የጭንቀት ሕይወት እያደር እየተላመዱት ሄደዋል። የመጨረሻው ከፍተኛ ድንጋጤ የተሰማቸው ንጉሡ ከሥልጣን የወረዱ ጊዜ ነበር። «አብደዋል? ሰው ሁሉ አበደ?» አሉ ደግመው ደጋግመው፥ ጆሮአቸውን ማመን አቅቷቸው። አንድ ሁለት ቀን ያህልም እንደ ገና በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው ድምፃቸውን በራዲዮ የሚያሰሙ እየመሰላቸው «እስቲ ራዲዮኑን ክፈቱት!» ማለታቸው አልቀረም። ተስፋው እየሟሸሸ ሐቁን መቀበል ግድ ሲሆንባቸው ግን፥ ምንም ነገር ቢደርስ መገረማቸውን ተውት። «ምን ያስገርማል? ወትሮውንስ ንጉሥ በሌለበት አገር» የሚል ፍልስፍና አመጡ። «ሰማይ ተደፋ» ቢሏቸው ስንኳ፥ «ታዲያ ንጉሥ ከሌለ ምን ያስደንቃል?» የሚል መልስ መስጠታቸው አይቀርም ነበር። የሥልሳዎቹ ሰዎች በሞት መቀጣት ስንኳ እስከዚህም አላስደነገጣቸውም ነበር። ያደረባቸው ስሜት ቅልቅል ነበር። በቅርብ ለሚያውቋቸው መኳንንትና መሳፍንት አዘኑ። በሌላ በኩል ደግሞ - የደጃዝማች አደፍርስ አሟሟት በስንት ጣሙ። እንደ በግ እየተነዱ እጃቸውን ማን ስጡ አላቸው - በማለት አስቀድመው የተነበዩት በመድረሱ ተኵራሩበት። «የሚሰማኝ አጣሁ እንጂ እኔ ቀድሞውኑም ተናግሬአለሁ። አስጠንቂአለሁ» እያሉ በየደረሱበት ልቅሶ ቤት ሁሉ ከንፈራቸውን መጠጡበት። ከቀድሞው አቃቤ ሹም ጕንጤና ከወንድሙ ልቅሶ ብቻ አልደረሱም። «ከእኛው ይቅር ምናለበት» ቢላቸው ማናዬ የሰጡት መስል «ንጉሡን ከዚህ ሁሉ ያደረሰ ማን ሆነና!» የሚል ነበር።

የየቤቱ የጎዘን ሥነ ሥርዓት የራሱ አስገራሚ መልክም ነበረው።

-ያች ደግሞ ማናት? - በጣት ቊጥጥር አድርጎ ይጠየቃል።

-ኸረ እኔ አላውቃትም።

-ታዲያ እንዲህ የምትሆነው ቤተ ሰብ ነች እንጼ?

-ብትሆን ነዋ! - በአሽሙር ከንፈር ይጣመማል።

ከሌላ የተወለዱ ልጆችም አሏቸው ማለት ነው? ወቸው ጉድ። ከንፈር ይመጠጣል።

-ይኸ ደርግ ጕባኑን ሁሉ በአንድነት አዋለው አይደል?

-የአርባው ለት ነው ጣጣው እንግዲህ።

በኀዘን አንድ ጊዜ ከንፈር ተመጥጦ እንደሆነ ሦስት ጊዜ በሐሜት መንሾካሾክ፣ ዕንባ ለመጥረግ አንድ ጊዜ መሐረም ከዓይን ላይ አርፎ እንደሆነ ሦስት ጊዜ መጠቃቀስና መሽኰርመም ዓይነተኛ መልክ ነበር።

ዘለቃ፥ የሚስ ወገኖች ያለ ማቋረጥ እየገረመሙዋት፥ እየተጕናተሉባት፥ ዓይንዋን በጨው አጥባ አንድ ቀን በጓንጉል ቤት ኀዘን ተቀምጣ ዋለች። በሦስተኛው ቀን ጥቁር ቀሚሷን እንደ ለበሰች ከአዲሱ ወዳጅዋ ጋር ሽርሽር ወጣች።

ዘለቀ ከአዲሱ ወዳጅዋ ጋር አዘውትራ መውጣት ከጀመረች ገና ጥቂት ሳምንትዋ ነው። ከዚያ በፊት፥ ግን ከማስረሻ ጋር ከተለያየች በኋላ ወንድ የምትቀያይረው እንደ ሸሚዝ ነበር። ይህ ነው የማይባል የመቅበጥበጥ ስሜት ሰፍኖባት እንደ ጕረምሳ ነበር ከተማውን በአውቶሞቢል ስታስስ

የምትውለው። ግዮን፥ ራስ፥ ኢትዮጵያ ሆቴል ብቻዋን ገብታ ዓይን አውጥታ በአስተያየቷ በመጋበዝ አንዱን ወንድ ይዛ ትወጣለች። ደስ የሚላት ወጣት በእግሩ ሲሄድ ከአገኘች አውቶሞቢሏን አቁማ ግባ ብላ ትወስደዋለች። አንዳንድ ተደናግጦና ግራ ገብቶት የማይሆንለት አለ። ብቻ ብዙዎቹን ድጋሚ ዕድል አትሰጣቸውም። ያደረባት ስሜት እንደ ወጥ ቀማሽ ማዳረስ ዓይነት ነበር። ግን በመካከሉ በጥንቃቄ መያዝ ያለበት አዲስ ዓይነት ወዳጅ አጋጠማት።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ለዚሁ ስምሪት ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ ስትጓዝ ቅድስት ማርያም ላይ የትራፊክ መብራት አስቆማት። በሹፌር የሚነዳ አንድ ፔጆ ከጐንዋ ቆመ። ሆነ ብላ እንደ ዋዛ ዘወር ስትል ከሹፌሩ ጐን ከተቀመጠው ሰውዬ ጋር ዓይን ለዓይን ታጋጠሙ። መኰንን ይሁን ባለ ሌላ ማዕረግ በጃኬቱ ላይ ምልክት የለውም። ግን ተራ ተሳፋሪ አለመሆኑ ወዲያው ገባት። ቅብርር ያለ ነበር። የትራፊኩን መብራት ቀና ብላ ተመልክታ አሁንም ዘወር ስትል ዓይኑ ከርሷ ላይ እንደ ተተከለ ነበር። ቀጭን ፈገግታ አሳየችው።

እንደሚከተላት በኋሊት መስታወት እያረጋገጠች ወደ ራስ ሆቴል ገባች።

«ይቻላል?» ሲል ጠየቃት፥ ተከታትሎ ገብቶ ከተቀመጠችበት ጠረጴዛ ለመቀመጥ ወንበር እየሳበ።

«የኔ ንብረት አይደለም!» አለች በቀልድ። ሹፌሩ ፓኮ ዊንስተን ሲጋራና ሮንሰን ማቀጣጠያ አምጥጦ ከፊቱ አስቀመጠለት። ቦዩ ተጣድፎ መጥቶ ትዕዛዝ ጠየቀ። ዘለቃ ቢራ አዘዘች።

«ሌላ ነገር ይሻልላ - ቢራ ሆድ ይነፋል። ራት አያስበላም። ዊስኪ አምጣልን።»

«ምን ዓይነት?»

ግንባሩን ኰስተር አድርጎ ጥቂት አሰበ። «ቤስቱን።»

«ሽቫዝ? ዲምፐል?»

«ያው ነው ሁለቱም።»

አንዳንድ መለኪያ ጨርሰው ድጋሚ እንዳዘዙ በሚገባ፥ አልተዋወቅንምኮ። ማን ልበል?» ስትል ዘለቃ ጠየቀችው።

«አንቺስ?»

ነገረችው።

«እኔ ደግሞ» ጠጋ ብሎ በጆሮዋ ሹክ አላት። «ሥራዬን ደግሞ ማወቅ ትፈልጊያለሽ?»

በኵራት መንፈስ ወደ ኋላው ልጥጥ ብሎ ከጃኬቱ ኪስ የመታወቂያ ካርድ አወጣና አሳያት። በመደነቅ ዓይንዋን ብልጥጥ አድርጋ እንደ ማፏጨት ቃጣት። «ትልቁ ዓሣ ተጠመደ» አለች በልብዋ።

«ክብር ይሰማኛል።» በአክብሮት ሰላምታ አንገቷን ደፋ አደረገች። በሆድዋ ደግሞ «ዛሬ ትልቁ ዓሣ ተጠመደ» አለች።

በእርግጥም ተጠመደ፡፡ ጠባዩን ለማወቅ ረጅም ግዚኤ አልወሰደባትም፡፡ መከበር፥ ማዘዝ፥ ሥልጣን ማሳየት ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ትንሽ ይበቃዋል፡፡ ቦዩን ሲቆጣ አብራ በዓይኗ ከገላመጠችለት ከርሱ ጋር ናት፡፡ ከቢሮዋ ቴሌፎን ደውሎ፥ «አሁን እፈልግሻለሁ» ሲላት፥ «ውይ አሁን ስላንተ ሳስብ ደወልክ» ካለችው መምጣት ስላለመቻሏ ማንኛውንም ምክንያት ብትሰጠው ይቀባላል፡፡ ብቻ «አለቃዬ አይፈቅድልኝም» አትበለው፡፡ «ምናባቱ ቁርጦት» ሲል ይደነፋል፡፡ መጀመሪያ ላይ ያስጠላት የሹፌሩ ጉዳይ ነበር፡፡ መኝታ ሲገቡ ከውጭ ይጠብቃል፡፡ በሬስቶራንትና በባር ሲቀመጡ አንድ ጥግ ይዞ ይቆያል፡፡ ከአጠገባቸው የማይለይ ጥላ ነበር፡፡ በኋላ ለብቻቸው እንደ ልባቸው እንዲሆኑ ምንም አግባብታው ሹፌሩን ከአንድ ቦታ እየተው ፔጆዋን ራስዋ እየነዳች መዘዋወር ያዙ፡፡

የአዲስ አበባ ታላላቅ ሆቴሎችና የከተማ ዳርቻ መናፈሻዎችን እንደ ፈለጉ አዳረሱት፡፡ ገንዘብ ሲያወጣ ዓይኑን አያሽም፡፡ ውስኪ ጠርሙስ አስከፍቶ የተረፈውን ጥሎ መሄድ ነው፡፡ ሆን ብላ በአድናቆት ስትመለከተው፥ «እኛ ለገንዘብ አንስገበገብም፡፡ ተካፍለን ነው የምንኖረው፡፡ ለውጡ የመጣው ሁሉም እንዲተቀምበት ነው» ይላታል በኩራት፡፡

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ስለ ዘለቃ አዲስ ወዳጅ ማንነት ቆይተው ወሬ - ወሬ ሰሙ፡፡ አንድ ቀን ወይዘሮ ሽዋዬ፥ «አንቺ ዘርፉ፥ ስለ ዘለቃ የሰማው ወሬ ምንድን ነው?» ሲሉ እንደ ዋዛ ጠየቁ፡፡

«ምን ሰማሽ ደግሞ?»

«ውሎዋ ከአሁኖቹ ጋር ነው አሉ፡፡»

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ላመል ያህል ስቅጥጥ አሉ፡፡ «ኤጭ! ሰው ፈጥሮ አውሪ ሆኗል፡፡ እኔ በበኩሌ የማውቀው ነገር የለኝም፡፡»

ማታ ዘለቃን ጠየቋት፡፡ ዓይኗን አላሸችበትም፡፡ «ያጣ ወሬ ነው፡፡» የሴቶችም ስም እየጠራች፥ «አልሆነላቸው ብሎ ነው እንጂ ሒልተን ሆቴል ሲያንዣብቡ ይውሉ የለ» አለች፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አልተቆጡም፡፡ እንዲያውም በልጃቸው ቅልጥፍና እንደ መደሰት አሉ፡፡ ወንድ ነኝ ባዩ ሁሉ ካላንበረከከች የሴት ቁንጅና ዋጋው የት ላይ ነው? እርግጥ ወሬው እየተዛመተ ሲሄድ አንዳንድ ጓደኞቻቸው ይሸሹዋቸው ጀመር፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግን በቅናት ተረጐሙት፡፡

አንድ ቀን እቤት አመጣችው፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጊዜ፥ ለማሳለፊያ ያህል ዳቦ ቆሎ ይቁርጡ ነበር፡፡ ግቢው ጭር ብሏል፡፡ አሽከራቸው ከፍና ዝቅ አድርጎ ተናግሯቸው ከሄደ ሰንብቷል፡፡ ማንዬም ጧት እንደ ወጣ አልተመለሰም፡፡ በግቢው ውጥ እንኮዬና አንዲት ገረድ ብቻ ነበሩ፡፡ የመኪና ጡሩምባ ሲሰሙ ጆሮዋቸውን ቀና አድርገው «ማን ይሆን?» አሉ በሐሳባቸው፡፡ የፔጆዋቸውም የዘልቃም ቶዮታም ጡሩምባ ድምፅ አይደለም፡፡ በደወል ገረድዋን ጠሩና «አትከፍችም በር!» ሲሉ ተነጫነጩ፡፡

«ተዋወቁ! እናቴ ናት፡፡» ዘለቃ እጅዋን ወደ ሁለቱም በኩል አመለከተች፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግን ካሉበት ፈዝዘው ቀሩ፡፡ እነዚህ ናቸው ሰማይና ምድሩን የሚያደበላልቁት? ደርግ ሲባል በሐሳባቸው የሚታያቸው ሌላ ሥዕል ነበር፡፡ ጥቁር መነፅር አድርጎ ከአጠገባቸው የቆመ ሰው ግን መንገድ ላይ ከሚያዩት ወታደር የተለየ አይደለም፡፡ ያም ሆኖ መኰሳተሩ ትንሽ አደናገጣቸው፡፡ የእጅ ሰላምታ ለመስጠት እጁን ሲዘረጋ የዳቦ ቆሎ ሊጥ ሲያፍተለትሉበት የነበረውን እጃቸውን በመገረም እየተመለከቱ «ኧረ እጄ ቆሻሻ ነው» በማለት ወደ መጸዳጃ ቤት አመሩ፡፡

ጭውውታቸው እየተዝናና የሄደው ሰውዬው ሦስት መለኪያ፥ እሳቸውና ዘለቃ ሁለት መለኪያ ውስኪ ካጋቡ በኋላ ነበር። «መቼም ሥራ ይበዛባችኋል። አገር ማስተዳደር ከባድ ነው። ብዙ ጣጣ አለበት» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ ለመክፈቻ ያህል። ብቻ! እስከዚህ ድረስ ነው እንጂ!» በማለት እጁን ካራ «ማስመሰል አፍንጫው አካባቢ አሳረፈ።

«መቼም የእኛ ሰው ነገር ይወዳል። ታዲያ የሰው ነገር ሁሉ አለመስማት ነው። የሥራ ጊዜ ያጠፋል» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል መከሩ፤ ባንድ በኩል ሰየውን ያባበሉ፥ በሌላ በኩል «አሳስርሻለ አንቺ አቆርቋዥ» እያሉ የሚፎክሩትን ገረዶቻቸውን ዕድል የዘጉ መስሎአቸው።

«ነገር ወደደ አልወደደ የት እንዳይደርስ። በእነዚያ ደደብ ባለሥልጣኖች ዝም ብሎ ሲገዛ ኑሮ፥ ተባዮችን ከላዩ ላይ ስናነሣለት አሁን ምን ልሁን ነው የሚለው?»

«ቅብጠት - ቅብጠት» በማለት ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አደነቁለት።

«እኛ ለሕዝቡ ብለን ነው እንጂ ጠላት ማፍራት ወደን ነው? እንደ ሰው የሰላም ዕንቅልፍ ተኝተን ማደር ጠልተን ነው?»

«ሰው የሚበጀውን የት ያውቃል?» አሉ። ቢያውቅማ ኖሮ ጃንሆይ ከዙፋን ሲወርዱ ዝም ብሎ መች ያይ ነበር - አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በሆዳቸው።

«በግዱ እንዲያውቅ ይደረጋል። እኛ ለሕዝቡ ብለን ነው እንጂ ሥልጣን ጠምቶት አይደለም።»

«ምናምንቴው ሰው ነው ነገር የሚያበላሽ።»

«ማንም አይፈቀድለትም። የኢትዮጵያ ትቅደም ዓይን እንኳን የተሠራው በሆድ ውስጥ የተደበቀውን ሁሉ ያያል።»

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ራሳቸውም በሆዳቸው የያዙት ነገር የሚታይባቸው ይመስል ላንዳፍታ እንደ መደንገጥ አሉ።

«ግን እኛ የምንፈልገው ሁሉም በሰላም ተደስቶ እንዲኖር ነው።»

«ነው፥ ነው አንጂ።»

«ከፊቲአችን የሚጋረጠው ግን ወዮለት።»

«ቅብጠት ቅብጠት» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንድገና።

«ለመሆኑ ቴሌፎን አለ?» ሲል ጠየቀ።

ዘለቃ አሳየችው። ደውሎ በሹክሹክታ ተነጋገረና ወደ ፎቴው ተመለሰ። ውስኪውን እየተጉነጨ ቀለበት ለማበጀት የሲጋራውን ጢስ ወደ ጣሪያው ቡልቅ ቡልቅ፥ አደረገ። አቃተውና ተወው። በጥቁር መነጽሩ በኩል ዓይኑን ከዘለቃ ላይ ተክሎ ካለርሱ መመሪያ የመንግሥት ሥራ ምንም መንቀሳቀስ እንደማይችል አድርጎ፥ ስለ ሥራው ብዛት ሲያወጋ ዘለቃ ውስኪውን በላይ በላዩ እየቀዳች በአድናቆትና በፍቅር እንደ ተመሰጠችለት ሆና ታስተውለው ነበር።

«ለመሆኑ መኪና ልትወስዱ ነው የሚባለው እውነት ነው?» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ፈራ ተባ እያሉ እንደ ዋዛ ጠየቁ። ብዙ ጊዜ በሐሳባቸው ሲጉላላ የቆየው ዋና ጉዳይ ይህ ነበር። መኪናቸው ከተወሰደች ማናዬም ጠቅልሎ ወደ ሚስቱ ይመስል ይሆናል። የሠራተኛው ሁካታና ግልምጫ በርዶ ሥራውን ከቀጠለ ወዲህ ቀለል ብሎት ደህና ሲያጫውታት ሰንብቶ ነበር።

«የምን መኪና?» ሲል ጠየቀ።

«ንጉሡ ለሰው የሰጡት መኪና ሁሉ ይመስላል ብለው የእናንተው ሰዎች እየዞሩ ሲመዘግቡ ነበር።»

እንደሚያውቅና ትዕዛዙንም ራሱ እንዳስተላለፈው ሁሉ ራሱን አወዛወዘ። «አዎ! ያለ አግባብ የተሰጣቸው ካሉ ይመለሳል። እርስዎን ግን የሚያሳስብዎት ነገር የለም። መመሪያ እሰጣቸዋለሁ። መጥተው ካስቸገሩም ዘለቃ ትንገረኝ፥ አስፈላጊውን እርምጃ እወስዳለሁ።» የኩራት ፈገግታ አሳየ።

«ኧረ እኔ ብትወስድም ግድ የለኝም። እንዲያው ነገሩን አነሣሁት እንጂ» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ መለስ አድርገው።

«ለምን ተብሎ! ማንም አይነካብዎትም።»

የሸሹዋቸው ጓደኞቻቸው መኪኖች ተወስደውባቸው ሰይቸንቶ ሲጠብቁ፥ እሳቸው በፔጆዋቸው እየተንፈላሰሱ ሲያልፉዋቸው ታያቸው። ልባቸው ረካ።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ ለመሄድ ሲነሣ መቆም አቅቶት ተንገዳገደ። ዘለቃ ግን የምትሸኘው መስላ ደገፍ አደረገችው።

«ራት በልተው አይሄዱም?» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል «አንቱ» ማለቱ አፋቸውን ከበደው።

«ገገና - ሥ ሥራ እገባለሁ» ምላሱን ያዘው።

ዘለቃ አድርሳው የራስዋን መኪና ይዛ ተመለሰች። «ግዴለሽም ብዙ ሊረዳን የሚችል ሰው ነው» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ በውስኪው ሰውነታቸው ግሎ።

«እሱማ ስለ ጋብቻም ያወራል። እኔ ፊት አልሰጠሁትም እንጂ።»

«ኧረ? ዘሩስ እንዴት ነው?»

«አዬ እማማ፥ ዛሬ ደግሞ ስለ ዘር ይጠየቃል?»

«እሱስ እውነትሽን ነው። ማዕረጉስ ምንድን ነው?»

«እንጃ። ግን ምን ይመስልሻል?»

«ምኑ?»

«ጋብቻው።»

«ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጥቂት አሰቡ። «መጀመሪያ ከማስረሻ ጋር ያለውን የጋብቻ ወረቀት ሳታስቀድሺ?»

«ምን ያደርጋል ብለሽ?»

«ሰውየው ግን ብዙ ሊረዳን የሚችል ይመስለኛል» አሉ።

## ፬

ማስረሻ ለመሟገት ሆነ የጋብቻ ወረቀት ለመቅደድ በማይችልበት ሁናቴ ላይ ይገኝ ነበር። ከመኪናው አደጋ ምሽት አንሥቶ በራሱ ልዩ ዓለም ውስጥ ሰምጦ ነበር። የቅዠት የሰመመን ዓለም.....

ለማስረሻ ቀኑም ሌሊቱም አንድ ሆነበት። እንቅልፍ ሳይወስደውም በደበዘዘ ዓይኑ ላይ የሌለ ነገር ይታየዋል። ሽልብ ሲያደርገውም አስደንጋጭና አስፈሪ ቅዠት ቁም ስቅሉን ያሳየዋል። ደግማ፥ ደጋግማ፥ የምትመጣበት መልክዋ ዘለቃን የመሰለ፥ ውፍረቷ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልን የምታህል ሴት ናት። አንድ ጊዜ እንደ ብረት በጠነከረ እጅዋ አንገቱን ፍጥርቅ አድርጋ ስታንቀው፥ «ኣ!» ይልና ተወራጭቶ ብንን ይላል። እውነት ይመስል አንገቱን እየዳበሰ ይቃስታል። ሌላ ጊዜ እንደ ወረቀት ጭብጥብጥ አድርጋ ሙቀጫ ውስጥ ትጨምረውና አንድስ የሚኢያክለውን ዘነዘና ጭንቅላቱ ላይ ልታሳርፍበት ስትል ሌላ ክፍል ያለችው ገረድ እስክትሰማ ድረስ ጩኸቱን ያደባልቀዋል። ተደናግታ መጥታ ስትጠይቀው «ምንም! ምንም! ደህና ነኝ» ይላል ሰውነቱ በላብ ተዘፍቆ።

አልፎ አልፎ ሙሔም፥ በልዩ ልዩ ቅርጽና አቀራረብ እየመጣ ያስጨንቀዋል። ብዙ ጊዜ የሚመጣበት ጣዕረ ሞት ሆኖ ነው።

ከዚህ በተረፈ፥ ክረምት አልፎ በጋ መምጣቱ፥ የተፈጠረው ሁናቴ፥ ሌላው ቀርቶ - ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን መውረድ አይታወቀውም። አይሰማውም ነበር። ከእውነተኛው ዓለም፥ ከእውነተኛው ሕይወት ተለይቷል። ያልተለየው ነገር ቢኖር አረቄው ብቻ ነው። መለኪያው ከኮሞዲኖው ላይ ተነሥቶ አያውቅም። አሁንም ፉት አሁንም ቅዠት፥ አሁንም መወራጨት። አንድ ጉርሻ እህል ከአፉ ሲገባ ግን መዋጥ ያቅተዋል። አሁንም ፉት አሁንም ቅዠት አሁንም መወራጨት አየተንገዳገደ መጸዳጃ ክፍል ደርሶ መመለስ....

ከኪሱ የነበረው ገንዘብ እስኪያልቅ ድረስ፥ ገረዱ ከመንደር ካቲካላ እየገዛች ስታመጣለት ቆየች። ከጊዜ በኋላ ገንዘቡም የተገዛው አረቂም አልቆ እንደ ሕፃን እየተወራጨ ቢያለቅስባት ድሮ ከራስዋ ደሞዝ ከአጠራቀመችው ገንዘብ እየገዛች ታመጣለት ጀመር። ብዙ ጊዜ ትታው ለመሄድ ከጅሏት ነበር። ደግሞ አዘነችለት። - ያች ርጉም ሚስታቸው አንድ ነገር ብታቀምሳቸው ነው እንጂ ደህና ነበሩ። ሁነኛ ሰው ቢያገኙ ይድናሉ - ስትል ውለትዋ እንደሚከፈላት በመተማመን አብራ መቸገሩን መረጠች። ግን እሷም ያጠራቀመችው ገንዘብ ተሟጥጦ ሲያልቅ «ኧረ ምን ተሻለ? በቤቱኮ ምንም ነገር የለም» አለችው፥ የጭንቀት ዕንባ እየተናነቃት።

«የሚጠጣ ምንም ነገር የለም?»

«ምንም!»

«ግቢያ!»

«በምኔ የራሴውኑ ገንዘብ እንኳ ጨርሻለሁ። ከዚህ በኂላ መቼስ የምሆነው ነገር የለኝም። ቤቱን ይረከቡኝ።

በተደናበረ አዕምሮ ለማሰብ ሞከረ። ዓይኑን ገለጥ አድርጎ የቤቱን ዕቃ ቃኘ። ጨለማው ትንሽ ገለጥ አለለት። «ቴሌቪዥኑን ሽጪው!» ትልቅ ዘዴ የፈጠረ መስሎ ተሰማው። ያም ሲያልቅ ሌላ የቤት ዕቃ አለ። መኪናው አለች።

በዚህ ጊዜ በሩቁና በደብዛዛው ሐሳቡ አንድ ነገር ትዝ አለው። መኪናዋ ለካ መስተዋቷ ተሰብሯል። ምን ሆና ነው የተሰበረው? ለማስታወስ ዓይኑን ጭፍን አደረገ። ግጭት። የምን ግጭት? ሁሉም እናቱን! ፖሊስ የለም። ፍርድ ቤት የለም። ራስን መስቀልም የለም። ለምን ተብሎ! ከአልጋው ሳይነሣ ሁሉንም ነገር ይወጣዋል። «ቴሌቪዥኑን ሺጪው!» አለ በስንት ሳምንቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እርግጠኛ በመሰለ አድነበት።

«እኔ የትብዬ ነው የምሸጠው?» ለነገሩ ግን ትንሽ ቀለል ከዚያ አልፎ እንደ መደሰት ብሏታል። አውጥተው አውርደው ይህንን ሐሳብ ከወሰኑ የሚሰሩትን ያውቃሉኡ ማለት ነው። የሚሠሩትንም ካወቁ ተሽሏቸዋል ማለት ነው - ለእርሷ አጭር ትርጓሜ ነበር። ምናልባትም ይህ የጊዜው ግርግር አስመርሮአቸው ይሆናል - ከሚስታቸው ጠባይ ጭምር። እና፥ የቤት ዕቃው መኪናው፥ ሌላውም ትርፍ ነገር ሁሉ ቢሸጥ ምንም ችግር አይኖርም። ይህ የግርግርና የብስጭት ጊዜ እስኪያልፍ መሸታም እየሸጠች ትኖራለች። ከዚያም ርሳቸው ሲሻላቸውና ሥራቸው ሲመለስ ውለታዋን አይረሱትም - ሌላም - ሌላም ሐሳብ እየተውለበለበባት የውለታው ዓይነት ተቀላቀለባት። «እና፥ ማን ያውቃል?» አለችና በሐሳቧ «እንዴት አርጌ ነው የምሸጠው?» ስትል ጠየቀች።

ለህልውናው የሚታገል ይመስል በዚያ ጨለማ ዓለም ውስጥ አዕምሮው ራሱ አውቆ ይሠራ ጀመር። «ቀላል ነው አታስቢ» ሲል ዘዴውን አስረዳት። ከአቅራቢያቸው ያለው ባለ ሱቅ የሚገዛ ከሆነ በመጀመሪያ እሱን ትጠይቂዋች። ካልሆነ ከእሱ ገንዘብ ትበደርና ብሔራዊ ቲአትር ፊት ለፊት ወደሚገኘው ላየን ባር ወይም ፒያሳ ራስ መኰንን ቡና ቤት ትሄዳለች። ከዚያ ብዙ ደላሎች አሉ። የቤት ዕቃ፥ የአራጣ፥ ገረድ ምን እንደምትፈልግ ይጠይቋታል። ትነግራቸዋለች። ከዚያም ቤት መጥተው ዕቃውን ያያሉ። ቀላል ነው።

እርግጥ አነጋገሩ የተዘበራረቀና የተምታታ ስለሆነ በቀላሉ አላስረዳትም። ግን በንግግሩ መካከል ላይ ደጋግማ እየጠየቀች እንደ ምንም ገባት። በሦስት ሰዓት ውስጥ ገገር ይዛ ተመሰለች። ገገር አራት መቶ ብር። ሻጭ ስምንት መቶ ብር። ዓመት ያልሞላው ባለ ሃያ አራት ኢንች ቴሌቪዥን በስድትስ መቶ ብር ሄደ።

የተላከባቸው ይመስል ያለ ወትሮአቸው ወደ ማታ ገደማ የቤቱ ባለቤት መጡ። ለካንስ ባለቤቱ ተከራይ ኪራዩን አጠናቅቆ ሳይከፍል ዕቃውን ጭኖ እንዳይጠፋ ቤት ባላቸው ሰፈር ሁሉ አንድ ቋሚ ኑሮአቸዋል። እምብዛም አይፈረድባቸውም። ልጅ ሲልኩ ራሳቸው ሲመላለሱ የፈረደባት ገረድ፥ «በጣም አሟቸዋልኮ! ያቺ ሚስታቸው ናት ከዚህ መከራ የጣለቻቸው ምናለ ጥቂት ቀን ቢታገሡአቸው» እያለች ስትማጠናቸው ሦስት ወር አሳልፈዋል። ይህንን ያህል ጊዜ የታገሡበትም አንዱ ምክንያት በሥልጣን እያደገ የሚሄድ የልጅ ጉግሣ አዲስ ሹም ስለሆነ፥ ወደ ፊት በብዙ ነገር እንደሚረዳኝ በመገመት ነበር።

አሁን እነ ልጅ ጉግሣ አራተኛ ክፍለ ጦር ከገቡ በኋላ ቴሌቪዥን ከቤት መውጣቱን ሲሰሙ ግን ሊታገሱ አልቻሉም።

ገረድ እየተርገበገበች ለመነች። «ሲበዛም ማር ይመራል» አሉ። «ኧረ ለመሆኑ አንቺ ምን ቤት ነሽ? ባለቤቱ ራሱ ጉዳዩን አይጨርስም?» ሲሉ ተኰሳተሩ። ማስረሻ ግን ጉዳዩን መጨረስ ወይም ስለ ጉዳዩ መነጋገር ቀርቶ ቅንጣት ደንታ አልነበረውም። ገረዱ ያሻትን እንድታደርግ የዛለ እጁን በማወዛወዝ አሰናበታት። በስንት ልመና፥ የሁለቱን ወር ኪራይ ሦስት መቶ ብር ተቀብለው ሄዱ።

አሁንም እንደ ገና ከአንድ ወር በላይ ከታገሡ በኋላ «ቤቴን ልቀቅልኝ» ብለው ማስረሻን ራሳቸው ለማነጋገር ገረድዋን ወደ ጎን ገፍተር አድርገው መኝታ ክፍል ገቡ። «ዝም ብለሽ ታያለሽ?» አሉ አገጫቸውን በመዳፋቸው አቅፈው ቁልቁል እየተመለከቱት። ከሰውነት ውጭ ሆኗል። ከስቷል ማለት በቂ አገላለጽ አይደለም። መንምኗል። ሰሏል። ቆዳው ገርጥቷል። ጸጉሩ ተንጨፍርሮአል። በማበጠሪያ ነክቶት የሚያውቅ አይመስልም። ጉንጮቹ ወደ ውስጥ ተሰርጉደው ዙሪያውን ሊጥ የተንጠባጠበባቸው የሚመስሉት የቀሉ ዓይኖቹ ከጣሪያው ላይ ተተክለዋል። «አቶ ማስረሻ - አቶ ማስረሻ» ሲሉ ተጣሩ። ለመናገር እንደ ፈለገ ዓይነት ከፍነሮቹን እንደ ማንቀሳቀስ አደረገ። ድምፅ ግን አልወጣውም። እንደ መወራጨት ብሎ በጐኑ ተኛ። ያወቃቸው አልመሰለም። ብርድ ልብሱና አንሶላው በከፊሉ ወለሉ ላይ ወድቋል። «እንዲህ እስኪሆን ምን ትጠብቂያለሽ?» አሏት ገረድዋን በግሣጼ መልክ።

«ምናባቴን ላርግ?»

«ዘመዶቹን አታስጠሪም?»

«አዲስ አበባ ዘመድ ይኑራቸው አይኑራቸው እኔ አላውቅም።»

«ጓደኞችም የሉትም?»

«በፊት ብዙ ጊዜ ከቤት የሚመጡ ነበሩ። ለውጥ ከመጣ ወዲህ ግን ቀርተዋል።»

«ስማቸውንም አድራሻቸውንም አታውቂም?»

በአሉታ ራስዋን ነቀነቀች።

ባለቤቱ ጥቂቲ አሰቡ። ይሙትም ይዳን የሚሻለው ጓደኞቹ ሆስፒታል እንዲያስገቡት ማድረግ ነው። ድኖ ሥራውን ከቀጠለ ኪራያቸውን ይከፍላቸዋል። ካለበለዚያም ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ለማድረግ ያለው ዘዴ ይኸው ነው። በጊዜው የፈረንሣይ ተማሪ ነበሩና ኮቱን አስመጥተው ኪሱን ሲፈትሹ ስምና የቴሌፎን ቁጥር የተደረደረበት ትንሽ ማስታወሻ ደብተር አገኙ። ወደ ቴሌፎኑ ሄዱና ጭንቅላቱን አንሥተው ወደ ጆሮ ግንዳቸው እንዳስጠጉት «ኬዝርስዊ ቤት» ሲሉ መልሰው አስቀመጡት። ይህንን ያህል ወራት የቤት ኪራይ ሳይከፈል፥ ቴሌፎኑ እንደ ሚቁረጥ እንዴት ሳያስቡ ቀሩ? በቤታቸው ቴሌፎን መደወል ሊኖርባቸው ነው። ተጨማሪ ወጪ።

## ፭

ሁለቱ የማስረሻ የአምና ጓደኞቹ አውቶሞቢላቸውን ራቅ አድርገው አቁመው ተላላፊ መንገደኛ በመምሰል እንደ ዋዛ ወደ ቤቱ ቀረቡ። አሁንም፥ አሁንም ጥርጣሬው አልወጣላቸውም። የማስረሻ ቤት

ጌታ ለአንደኛው ደውለው ሲጠይቁት ጓደኛ መሆኑን አላመነላቸውም ነበር። ዛሬ ግዜ ማን - ምንስ ይታመናል? ግማሹ ይታሰራል። ግማሹ ይሞታል። ግማሹ ይጠፋል። አንዱ በሌላው ላይ ይጠቁማል። ማስረሻ፥ በልጅ ጉግሣ እንደ ተሾመ የመሳፍንት አቀንቃኝ ብለው ከሽሹት ወድህ አይተውት አያውቁም። ፀጥታ አስከባሪዎች አስጠርቶ ሠራተኞች እንዳስገደለ፥ ከዚያም ሥራ መሄዱን እንደ ተወ ተሰምቶአል። የት እንደ ደረሰ፥ ምን እንደሚሠራ ግን አላረጋገጡም። ደንታም አልነበራቸውም። ታዲያ ጠፍቶ እየተፈለገ እንደሆንስ? ተይዞ ሲቸበቸብ የቀድሞ ጓደኞቹን ስም እየጠራ ዘባርቆ እንደ ሆንስ? ወይም በመሾሙ ስለ ሽሹት ሊበቀል ሲል በሐሰት ወንጅሏቸው እንደሆንስ? ማን ያውቃል? በስመ ጓደኝንትም መመርመር ይኖር ይሆናል። «የማስረሻ ጓደኛም አይደለህ?» በማለት ሰውየው አንደኛውን በቴሌፎን ሲጠይቁት በሐሳቡ የመጣበት ሥጋትና ጥርጣሬ ይህን የመሰለ፥ ነበር። «ማስረሻ? ማስረሻ?» ለማስታወስ የሚሞክር መሰለ። «የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ጊዜ ከሆነ ብዙዎቹን ረስቻቸዋለሁ» ብሏቸው ነበር።

«ኧረ አሁን እስከ ጥቂት ወራት ድረስ?»

«እንደርሱ የሚባል ጓደኛም የለኝ» ብሎ ሊዘጋ ሲል፥

«ስምና ቁጥርህ ግን ከማስታወሻ ደብተሩ ውስጥ ሰፍሯል» ቢሉት የባሰውን ሠጋ። «ከቴሌፎን ማውጫ ላይ ወስዶት ይሆናል» አለ፥ እንዳይታወቅበት በማቃለል አነጋገር። ሰውየው ግን አጥብቀው ያዙን «የጠየቅኋቸው ሌሎችም እንደዚሁ አናውቀውም ነው ያሉት። ኧረ እንዲያ ጉደኝነት ለመቼ ነው?»

«ያልሆንኩትን? የማላውቀውን?» ተገዶ ፖሊስ ጣቢያ ከሄደ በኋላ ቃሉን ይሰጣል እንጂ በቴሌፎን አይለፈልፍላቸውም።

«ለነገሩማ እኔ ምንቸገረኝ። ግን ተቀያይማችሁማ ቢሆን ይቅር ለእግዚአብሔር ብላችሁ ብትጠይቁት አይከፋም። በጠና ታሟል» ብለው ዘጉ።

ከሁለተኛው ጓደኛው ጋር ከተመካከሩበት በኋላ አሁን አመጣጣቸው ለመሰለል ያህል ነበር። ግን በሰፈሩ ምንም ግርግር የለም። ሁሉም እንደዘወትሩ ወደየጉዳዩ ያመራል። አንድ ነገር ቢኖር ኖሮ ወሬ አዳናቂው ይሰበሰብ ነበር። የፖሊስ ቮልስዋገን ወይም የወታደር ጅፕ ይኖር ነበር። ቢሆንም ማረጋገጡ አይከፋም። በሩን ከማንኳኳታቸው በፊት በበሩ ቆርቆሮ ቀዳዳ አጮልገው ተመለከቱ። ግቢውም ጭር ብሏል። ሕይወት ያለበትም አይመስል።

ማስረሻ ከአልጋው ላይ ተዘርግቶ ሲያዩት ከጥቂት ወራት በፊት ስለ እርሱ አድሮባቸው የነበረውን ጥያፌና ንቀት ሁሉ ረሱት። ጣዕረ ሞት እንዳፈራገጠው ሁሉ፥ ሁለት እጁ ተመሰቃቅሎ አንድ እግሩ ከአንድ ጫፍ በኩል ተንጠልጥሎ በጀርባው ተዘርሯል። ውኃ ካልነካው ልብስና ገላ እየወጣ የረጋው የላብ፥ የጉሬዛ ሲጋራና የካቲካላ ጠረን አፍንጫ ይቆርጣል። የአዲስ ከተማ በረንዳን ያስታውሳል። ከቆዳው ጋር በተጣበቀው ፒጃማ ውስጥ ያለው ገላ ያለቀ፥ የሚሸሽ አስከሬን ነው። ግን ያልሞተ መሆኑን ለመገንዘብ ረጅም ጊዜ አልወሰደባቸውም። ትንፋሹ እየተንቄራጠጠ ይወጣ ነበር። «ትንሽ ሽልብ አድርጓችዋል» አለች ገረዲቱ በሹክሹክታ።

ምንም ሳይነጋገሩ በመገረም እየተያዩ ቆዩ። ሰው እንዴት ባንድ ጊዜ እንዲህ ይወድቃል? አምና ይህን ጊዜ ከዚያች እጮኛው ጋር ዓለምን የቀጨ መስሎ ነበር። ከጥቂት ወራት በፊት በሹመት አንዴ

ተተኰሰ፡፡ አሁን ደግሞ እንዳወጣጡ ከበረንዳ አዳሪዎች በታች ወደቀ፡፡ በሁለቱ ሕይወቶች መካከል ያለው መስመር ምን ያህል ከሸረሪት ድር የቀጠነ ቢሆን ነው?

ሹክክ እያሉ ወደ ሳሎን ክፍል ሄደው በራሱ እስኪነቃ ጠበቁት፡፡ ገረዲቱም ግድግዳ ተጠግታ ጥፍሯን እየቆረጠመች የምታውቀውን ያህል ስለ ሁናቴው ነገረቻቸው፡፡

ድንገት የሚያንቧርቅ ጩኸት ተሰማ፡፡ ተሯሩጠው ሲገቡ ማስረሻ ሁለት እግሩ ከአልጋው ዳር ወርዶ፥ መቀመጥ አቅቶት ግራና ቀኝ ፊትና ኋላ እየተወዛወዘ፥ በሁለት እጁ ፊቱን ሸፍኖ ሳቅ አይሉት ልቅሶ ሲንፈቀፈቅ አገኙት፡፡

«ማስረሻ! ማስረሻ! ምን - ነካህ?»

«ብዙ ጊዜ ነው እንዲዒህ የሚያደርጋቸው፡፡ የለከፋቸውን እንጃ አለች ገረድ፡፡!»

እጁን ከፊቱ ላይ አንሥቶ ዓይኑን አጕረጠረጠባቸው፡፡ ዓይኑን ይበልጥጥ እንጂ የሚያያቸው አይመስልም፡፡ ቢያያቸውም እነማን መሆናቸውን መገንዘቡ አያስታውቅም፡፡ ከዚያም ጥርሱን እያፋጨ ጠላት እንደሚፈልግ ዓይኑን እያንከራተተ ይቀባጥር ገባ፡፡

«ገደልኳት - ፖህ! ገደልኳት!»

«ማንን?» አለ አንደኛው ጥያቄው አስፈላጊ አለመሆኑ ወዲያው እየታወቀው፡፡

«ዝንቧን ነዋ! ከእኔ አሥር እጅ ብትበልጥም አላሸነፈችኝም - የእስዋ ጡንቻ ለእኔ ምን ነው - እስዋ መጥለፊያ ገመድ ይዛ ብትመጣ ለእኔ ምኔ ነው - በጣጠስኩታ! እፎይ - እፎይ! ቁም ስቅል አሳይታኝ - በየሄድኩበት መከተል ኦሆሆ! እናቷን - ደሟ ደሞ ምን ያህል ይበዛል - ባካችሁ - ሽማዬንኮ አጨማለቀው - የት እንደ ተጋጠምን ታውቃላችሁ?»

«የት ነው?» ማረጋጋት ያህል ጥያቄውን ማርካት አስፈላጊ ሆኖ አገኙት፡፡

«ሕዋአው - ሕዋው ውስጥ ነዋ! እኔ ስበርር እስዋ ስትከተለኝ - ለኔ - ለኔ - ምኔ ነው ያበጠው ይፈንዳ አልኩዋ! ደም - በደም - ለኔ ምኔ ነው - .....»

ንግግሩን አቋርጦ ትኵር ብሎ ሲመለከታቸው አእምሮው የተገነዘባቸው መሰላቸውና፥ «እኛ ማነን? አታውቀንም?» ሲሉ ጠየቁት፡፡

ከት ከት ብሎ ሳቀ፡፡ «እውቂያ በሽ በሽ ነው!» ወዲያው ድንገት ትውስ እንዳለው ዓይነት አንገቱን ሰገግ አደረገ፡፡ «ኤ - ኤ ! ኮተቤ! ተሼ - ተስፍሽ! የት አገር ትኖራላችሁ! አንተ የሚስተር እስፒዲ አቃጣሪ» አለ በቀልድ ስድብ፡፡ ስለ ኮተቤ ሕይወታቸው ብዙ ለፈለፈ፡፡

«ቲያትር ይመስል ከዚህ ተቀምጠን ብናየው ዋጋ የለውም» አለ አንደኛው ጓደኛ፡፡ እንዳይሰማቸው ሌላ ክፍል ሄዱና ተማከሩ ፡

«ሊሞትኮ ተቃርቧል፡፡ ደንበኛ ሕክምና ያስፈልገዋል፡፡ ያውስ ቢተርፍ አይደል? ስለዚህ የሚሻለው ሆስፒታል መውሰዱ ነው፡፡ መቶ ብር ነው አስይዙ ቢሉን፡፡»

«ግን እንደዚህ የሆነ ሰው እሽ ብለው የሚያስተኙልን ይመስልሃል?»

«እህሳ!»

«ወደድንም ጠላንም እውነቱን መዋጥ አለብን። ምርጫ የለንም።

«ተነሣ እንሂድ» አሉት ወደ መኝታ ክፍሉ ሲመለሱ።

«ሰዓ እላፊ አልደረሰም?» በተረጋጋ መገረም ጠየቃቸው።

«ገና ነው። የሰዓት እላፊ ፈቃድ ደግሞ አለን።»

ልብሱን በማልበስ ከረዱት በኋላ መኪና ውስጥ ደግፈው ስያስገቡት «ተስፍሽ ጥሩ አውቶሞቢል ሽምተሻል» ሲል አደነቀ። ከዚያ በፊት ብዙ ጊዜ አብረው ሽርሽር የወጡባት ዳትሰን ነበረች።

«ግንኮ የቆየበት ይመስለኛል። ትዝ ይልሃል አምና በሰርጉ ሰሞን፥ ሙሔ የሚባለው ሰው አባቴ ነው፥ አባቴም አይደለም እያለ ሲቀባዥር?» ሲል መሪ የጨበጠው ከጐኑ የተቀመጠውን ጓደኛውን ጠየቀው። ከኋላቸው የተቀመጠው ማስረሻ የሚሰማ መሆኑን ዘንግቶት ነበር። ማስረሻ ግን ቢሰማም ስለ ራሱ መሆኑ በተማታ አእምሮው ውስጥ ፈጽሞ አልገባም።

ወደ መርካቶ አግጣጫ አመሩ።

# ፮

«ያመጣል መግነድ ይወስዳል መንገድ፥

ማስተናበሩ ለእርሱ እንደሁ አይገድ።»

እንዲሉ በየመጠለያው፥ በየዘመዱም፥ በየከተማውም የባሰበትም በየፈፋው ከርሞ የተረፈው ችግረኛ፥ ግንቦትና ስኔን ይዞ ወደ ቀየው፥ ወደ መንደሩ ወደ ጐጆው መመለስ ጀመረ። አብዛኛው አቅፎ ስሞ፥ እንኳን ደህና መጣህ ብሎ የሚቀበለው እህል አቅርቦ የሚያስተናግደው አልነበረም። ሕይወት የተለየው የእሳት ሙቀት የሌለው በሩ ገርበብ ያለ ግድግዳው፥ የዘመመ፥ የሳር ክዳኑ የተበሳሳ ወና ጐጆ ይጠብቀዋል። ሠፈሩን ለብቻው ይዘውት የከረሙት አይጦችና አይጠ - መጎጦች የሰው ኮቴ ሲሰሙ እየተሽሎከሎኦኩ ወደየጉድጓዳቸው ይገባሉ። አንዳንዶቹም ብዙ ወራት የሰፈነውን ጸጥታ ያሰፈረባቸውን ነገር ለማወቅ የሚፈልጉ ይመስል በመደነቅ ዓይነት ያስተውሉና ፈትለክ ይላሉ። በተረፈ ሁሉም ነገር ጭር ያለ ነው።

አምስት ራሱን ወጥቶ ሦስት ራሱን የተመለሰ ቤተሰብ ዕድለኛ ነው። አብዛኛው በአምባሰል፥ በቃሉ፥ በወረይሉ፥ በወረሂመኑ፥ በራያና ቆቦ፥ በአውሳ ሸንተረር ጋራና በረሃ ቀልጦ ቀርቷል። እንደገና ሥጋ ለብሶ ሕይወት ገዝቶ የሚበቅል ይመስል በየፈፋው በየጠፉ ማሳ ተዘርቷል። ከአራዊትና ከአሞራ የተረፈው የከብት አጥንትና ቀንድ በየሥፍራው ተበትኗል። የሰው ገላ ከመሬት ሥር ሲበሰብስና ሲፈርስ አሞሮች ከላይ ያንዣብባሉ። ጥርኝ አፈር የመልበስ ወግ ያገኙት መቃብሮች አሁን የበልግ አረም በቅሎባቸዋል። ነፋስ እየተንሾካሾከ በላያቸው ላይ ያልፋል። አይሰሙትም።

አብረው ወጥተው ብቻዋን የተመለሰች ሚስት፥ ምን ያህል ደጅ ደጁን ብትመለከት ምን ያህል መዳፍዋን ከዓይኗ ላይ ጋርዳ ማዶ ማዶውን ብታንጋጥጥ የምትወደው ባሏ እርፍ ተሸክሞ በሬ እየነዳ ሲመጣ አታየውም። ላይመለስ ሄዶአል። ላይገናኙ ተለያይተዋል። ግን ልማድ ሆኖ ዓይኗ መቃኘቱን አይተውም። ከተረፉ ልጆችዋ ጋር ተመልሳ እንደሆነ ራሳቸውን እየደባበሰች ዓይኗ በአካባቢው ይንከራተታል። አባት የሌላቸው ልጆች ምን ይሆናሉ? ጸጉርን እየነጩ፥ ልብን በሰቀቀን እየፋቁ ማሰብ ነው።

ወንዱም ከቤተሰቡ፥ መቅበር የቻለውን ቀብሮ ያልቻለውን የትም ጥሎ የተረፈውን ይዞ እንደ ምንም ቤቱ ይደርሳል። ግን ምን ያህል ጆሮውን ቢያቀና እህል እየፈጨች ስታንጐራጕር የሚስቱኡን ድምፅ አይሰማም። ምን ያህል ቢጠብቅ ምግብ ቋጥራ ከማሳው ድረስ አትመጣለትም።

ከደከሙና ከሞጨሞጨ ዓይኖች ምን ያህል ዕንባ ቢፈስስ የፊትን ቆዳ ይሸረሽራል እንጂ ኀዘንን አያጥብም። የልቅሶ ድምስጽ በየፈፋው ከወደቀው ሬሳ ጆሮ አይደርስም።

የተረፉት ሕፃናት ልጆችዋን ይዛ የተመለሰች እናት ደግሞ በተለይ ሰቀቀኗ እጥፍ ድርብ ነው።

በእንግልት የሳሳ ጸጉሯን ትነጫለች። ደም እስኪ ቋጥር ድረስ ከንፈሯን ትነክሳለች። በሥራና በችግር የተፍረገረገ እጅዋን ታፋትጋለች። ከመደቡ ላይ ተደፍታ ትንሰቀሰቃለች። ባሏን - የቤቷን ጌታ - ለዘለዓለሙ አጥታለችና። ልጆችዋ አባት አልባ ቀርተዋል። ልጆችዋን በፍቅር የሚዳብስና የሚያጫውት አባት እንግዲህ የለም። ቀኑን ሙሉ በሥራ ስትባክን ውላ ማታ ደክሟት ከመደብ ላይ ስትጋደም ክንዱን አንተርሶ «አይዞሽ የኔዋ! አትጨነቂ። እሱ ያውቃል» እያለ የሚያጽናናት እና ሲበርዳት የሚያሞቃት የትዳር ጓደኛ እንግዲህ አይኖርም። እንግዲህ ሌላ ባል አታገኝም። ሥራ፥ እንግልት ችግር፥ ወሊድ፥ የሴትነት ውበቷትና ወዝዋን ጨርሶታልና። የተጨማተረ፥ ያለቀ ገላ ማን ፈላጊ አለው? ልጆችዋ «አባባ!» ብለው የሚጠሩት የእንጀራ አባት ስንኳ ላይኖራቸው ነው።

ሳርና አረም በሟቾች መቃብር ላይ እያደገ ሲሄድ የኀዘን ሥቃይንም ጊዜ እያደበዘዘው ይሄዳል። የሟቾቹ ገላ ወደ አፈርነት እየተለወጠ በሄደ መጠን የቋሚዎቹ ሰቀቀን እየቀዘቀዘ ይሄዳል። ትዝታም እንደ ሩቅ አድማስ ጭጋግ እየለበሰ ይሄዳል።

ወደ ሰፈራቸው ከተመለሱት ከፊሎቹ የበሬ መግዣና እህል አግኝተዋል። ሌሎች ግማሽዋ የምትቀመስ ግማሽዋ ለመሬት በአደራ የምትሰጥ ትንሽ ትንሽ እህል ቋጥረዋል። ብዙዎቹ ይዘውት የወጡትን ወይም በከተማ የተለቀቁትን ማረሻ፥ ዶማ፥ ምሳር ይዘዋል። ነገር ግን ባላቸውና በሌላቸው መካከል እስከዚህም ልዩነት አይኖርም። በአንድ በሬ ብቻ አይታረስምና ከሌላ ጋር ማቀናጀት አለ። በአንድ መንደር የማን ማሳ ታርሶ የማን ይቀራል? በሬ አውሱኝ ዘር ስጡኝ፥ በጉልበት እርዱኝ ብሎ ጐረቤት ሲጠይቅ ማን እምቢ ይላል? ማን በልቶ ማን ጦሙን ያድራል? አምና ካቻምና ተካፍለው የጭንቁን ቀን ለማለፍ እንደ ሞከሩ ጣእራቸውን እንደ ተጋሩ ሙታኖቻቸውን አብረው እንደ ቀበሩ ሁሉ አሁንም ደግሞ ተፈጥሮ ፊቷን ከመለሰች የተስፋ እንጕቻቸውን አብረው መጋገራቸው የማይቀር ነው። የሰው ሕይወቱ ከሰው ጋር ነው። ሌጣ ነፍሱን ከሆነማ መኖሩንስ ማን ያውቅለታል!

ሙሔ ከበደና፥ የሙሔ የአደራ ልጅ ያይኔ አበባ ክረምቱ ሊጋመስ ሲቃረብ ከደሴው መጠለያ ተሰናብተው ወጡ። ከበደ ሐይቅ ከተማ ተመላልሶ የአንድ በሬ መግዣ መቶ ሃምሳ ብርና ሃያ አምስት ኪሎ እህል አግኝቷል። ለመስከረለት የወርጠያ ምስለኔ ሃያ ብር ከፍሎ መቶ ሠላሳው ተርፎታል።

ሙሔ በበኩሉ ይህንን ያህል አልቀናውም ነበር። መጀመሪያ «የወርጠያ ነዋሪ ነኝ ብየ በሐሰት አስመክሬ ገንዘብ አልወስድም፥ ለሐሰት ምስክሬ ምስለኔም ጉቦ አልሰጥም» እያለ ሲያቅማማ ቆይቶ ከበደ ብር ቋጥሮ ሲመጣ ቆጨውና እያዘገመ ቢሄድ ለበሬ፥ መግዣ የተመደበው ገንዘብ አልቆ አገኘ።

«ለጥቂት፥ ከሁለት ቀን በፊት ቢመጡ ኖሮ» አለችው የዕርዳታ ሰጪው ድርጅት ሠራተኛ።

«አዬ፥ መቼም እሱ ለእኔ ባይለው ነው» በማለት አንገቱን ደፍቶ ሲመለስ አሳዘናትና በበቆሎ ፈንታ በተላይ ከተቀመጠው ስንዴ ሠላሳ አምስት ኪሎ ያህል ሰጠችው።

የእህሉን ሸክም ለሦስት ተካፍሎ በአረብ ገንዳ በኩል አድርገው በሸዋ በር ሲዳፉ፥ ከመጠለያው ለቁርስ የተሰጣቸውን ቂኢጣ ቀማመሱና ባዶ በሆነ ልብ፥ ባልተቻኮለ እርምጃ የሐረጎን ቁልቁለት ተያያዙት። ምን ያቻኩላል? የት ለመድረስ? ምንስ ለማግኘት? ሙሔ ባዶ እጁንና ሦስት እራሱን ከቤቱ ወጣ። ከዘይኔ ጋር ወደ ደሴ የዘለቁት በዚህ ዳገት በኩል ነበር። አሁን ደግሞ ከጥቂት፥ እህል በቀር ባዶ እጁንና ብቻውን እየተመለሰ ነው። ታዲያ ምን የሚያቻኩል ነገር አለ?

ሆኖም የኮምቦልቻን መዳረሻ ሲቃረቡ ሙሔ፥ ከእግሩ ፈጠን ፈጠን አለ። በዚያ በደከመ ሰውነቱ እንደ መሮጥም ቃጣው። ልቡ በኃይል ይመታ፥ ስሜቱ ይቅበጠበጥ ጀመር። ከሁለት ተከፍሎበት....

«ኧረ ቀስ፥ ልባችን ይፈርሳል!» አለ ምክንያቱን ያላወቀው ከበደ፥ ከኋላ እየተከተለ። ሕፃን ልጁን ከሰው ዘንድ እንደ ተወው ሙሔ የነገረው ቢሆንም የት ቦታና በምን ዓይነት ውለታ እንደተወው ግን አያውቅም ነበር።

ሙሔን እንደ መሮጥ የሚያደርገው የልቡ ከሁለት መከፈል ነበር። ባንድ በኩል ልጁን የማየት የመሳም፥ ለሀጨን በከንፈሩ እየዳሰሰ የመጥረግ የአባት ጉጉት እንደ ብርቱ መግነጢስ ይስበዋል። በሌላ በኩል፥ እንግዲህ አባት ላትሆነው ላታሳድገው አባቱ መሆንክን ስንኳ ላትነግረው የምን ጭንቀት ማብዛት ነው? የሚል ደወል በአእምሮው ውስጥ እያቃጨለ፥ ሳያይ ሳይገላመጥ ያንን ቤት በሩጫ ለማለፍ ይከጅላል። ከቤቱ ፊት ለፊት ሲደርስ ግን ሳይታወቅ ከመሬቱ ጋር እንደ ተቸከለ ቀጥ ብሎ ቆመ።

«ምን ነካህ አይዋ ሙሔ?» ከበደ ከአጠገቡ ቆሞ በመገረም አስተዋለው። የሙሔ ዓይን ደግሞ የተተከለው ከመንገድ ዳር ባለችው ቤት የተዘጋ በር ላይ ነበር። - ልጁን የትወሰዱት? እነሱስ የት ሄዱ!? መሸታ ቤት በቀን አይዘጋም - ጥሎላቸው ከመሄዱ በፊት አድሮበት የነበረው ጥርጣሬና ሥጋት ዓይኑ በእንባ ሲጋረድ ቤት ደብዘዝ አለበት። እንዳይታወቅበት ፊቱን መለስ አድርጎ ሽንጉን እንደሚከፍል ከአውራ መንገዱ እየወጣ «እኔ ከዚህ የምጠይቀው ሰው ስላለኝ እቢያሳው ጠብቁ» አለ፥ በተሰባበረ ድምፅ።

«ከዚሁ የማንቆይህና አብረን የማንሄድ?»

«ግዴለም ቀስ እያላቹ አዝግሙ። እደርስባችኋለሁ።»

ግን አልደረሰባቸውም። አንድ ሰዓት፥ ሁለት ሰዓት፥ ሦስት ሰዓት ጠብቀው ወደ ተውበት ቦታ ቢኢመለሱ ከድንጋይ ላይ ተቀምጦ ሲያለቅስ አገኙት። ጨኸት በሌለበት አንጀት በሚያኰማትር ጥልቅ ኀዘን ተጨምድዶ ዕንባው ብቻ ይረግፋል።

«ልጄን የት እንዳደረሱት አላውቅም» አለ ቀና ብሎ በመማጠን።

«እነማን?»

«የዚያ ቤት ሰዎች። ለእነርሱ ነበር የሰጠኋቸው።» ቤቱን ለማየት የፈራ ይመስል ወደ ሌላ በኩል ዘወር እንዳለ አንድ እጁን ዘርግቶ አመለከተ።

«ጠይቃቸዋ!» አለው ከበደ። ሙሔ ያላየው ነገር አንገቱን ደፍቶ ሲያለቅስ ሴትዮዋ ከሄዱበት ተመልሰው የቤቱ በር የተከፈተ መሆኑን ነበር።

ሴትዮዋ ሲያዩት ተርገበገቡ። የሚሆኑት ጠፋቸው። ቅራሪም፥ ምግብም በአንድ ጊዜ ለማቅረብ እየተንደፋደፉ «ወይ የእግዜር ነገር? እንደገና በሕይወት ለመተያየት አበቃን? ለመሆኑ እንዴት ዘለቁት? መቼም ሳያስችል አይሰጠው ይባላል። ሴት ልጅዎስ ደህና ናት? ይሄ ችግር ስንቱን አለ ያየው?» ሙሔ ግን ሰላምታቸውንም ሆነ ጥያቄያቸውን አያዳምጥም ነበር። ሐሳቡ ያለው ከራሱ ጥያቄ ላይ ነው። ከመጋረጃው ጀርባ አልጋውን በበሩ በኩል ውጭ ውጭውን በዓይኑ ማተረ። የለም። ጆሮውን አንቅቶ አዳመጠ። የልጅ ድምፅ አይሰማም።

እህል ከመቅመሱ በፊኢት አላስችለው አለና አፉ፥ ስቶ፥ «ልጇሳ?» እንደ ማለት ቃጣውና፥ መለስ አድርጎ «ልጁሳ» ሲል ጠየቀ።

«ተንዳሆ ሄዶአል - ከእናቱ ጋር።» በሥጋት ተመለከቱት።

«ምነው በደህና?»

«በደህናም ነው በደህናም አይደለም።» ሙሔ ደንገጥ ማለቱን ተገነዘቡና መለስ አድርገው «እናትና ልጁስ ደህና ናቸው» አሉ።

«እህስ?»

«የልጇ ባል አርፎአል።»

«ሙሔ ከንፈሩን በመምጠጥ ኀዘኑን ገለጠ። በሆዱ ግን አንድ ዓይነት የተስፋ ደስታ ተሰማው። ከመሠረቱ ልጃችው አድርገው ከናካቴው ለመውሰድ የፈለጉት የልጃቸው ትዳር እንዲጠና ነበር። አንዲት ልጃቸው ፀንሳ እያስወረዳትና ልጅ እየሞተባት ስላስቸገራት፥ የሙሔ ልጅ ወስዳ ባሏን ልጅ ወለድኩልህ ማለት ማጭበርበር መሆኑ ያን ጊዜ ቢሰማውም ምርጫ አልነበረውም። ልጁ በረሃብና በእንግልት ከሞት አፋፍ ደርሶ ነበር። የልጃቸውን ጋብቻ የሚያጸና የልጁም ሕይወት የሚተርፍ ከሆነ መቼስ ምን ይደረግ አለ በልቡ። አሁን የተታለለው ባል ከሞተ ልጁን መልሶ መውሰድ ይችላል። እርግጥ ሕፃን ልጅ ማሳደግ ቀርቶ የራስንም ሕይወት ማቆየት አሁንም ችግር ነው። ግን ክረምቱን እንደ ምንም ከዘለቁ ምንም አይሉ። ያይኔ አበባም እንደ እኅቱ ሆና መያዝዋ አይቀርም።

«ብዙ ጊዜ ሆነው ከአረፈ?» ሲል ጠየቀ ለተስፋው ተጨማሪ ፍንጭ የሚያገኝ መስሎት።

«አርባው አለፈ።»

«ምን ሆኖ ሞተ?»

«በአደጋ በፋፍሪካ አደጋ።»

«እነሱ ታዲያ ብቻቸውን ከዚያ ምን እያደረጉ ነው? ሐሩሩኮ አይቻልም» አለ ሙሔ፥ የልጁ በሐሩር መሠቃየት በሐሳቡ እየታየው።

«የአባትየውን ገንዘብ ለማስወጣት ነዋ» ሲሉ መለሱለት።

«የምን ገንዘብ?» እንቆቅልሽ ሆነበት። በነገር ተመስጠው ከውጭ የሚጠብቁትን እነከበደን እረስቷቸዋል። ምግቡንም ገና አልቀመሰም።

ዘርዝረው አስረዱት። «ልጅዎ ባለገድ ሆኖ፥ ልክ እናንተ እንደ መጣችሁ ሰሞን፥ የልጇ ባል ቋሚ ሆኖ በጥጥ መዳመጫው ፋብሪካ ውስጥ ተቀጠረ። መቼም እንዲህ አይምሰልዎት ባለሙያ ነበር። ሥራ መፍታት ቢጠላ ነው እንጂ ጦር ሠራዊት ያገለገለበት ጡረታ አለው። የሻምበል ባሻ። ኮርያ ዘምቶ ቆስሎ ነው የወጣው። በሐኪም ትዕዛዝ። ታዲያ ማማረር አይሁንብኝ እንጂ፥ እሱስ ነገር ሁሉንም አሟልቶ አያድልምና ኑሮአቸው ደህና መደላደል ሲጀምር መልሶ ጉድ አረገን።» ሴትዮዋ ንግግራቸውን ከመቀጠላቸው በፊት ሁለት ሦስት ጊዜ ከንፈራቸውን በአዘኔታ መጠጡ። «አደጋው የደረሰው የመዳመጫው ፋፍሪካ ኮረንቲ ተበላሽቶ ነው አሉ። ፋፍሪካው ተበላሽቶ በሚያደርስ አደጋ ሠራተኛ ሲጐዳና ሲሞት ደሞ ፋፍሪካው ካሣ ይከፍላል። ካሣውም ጠቀም ያለ ነው የሚሉት። ይኸውልዎት ለጋብቻቸው የወረቀት ፊርማ ባይኖርም የወለደችለት ሚስቱ መሆንዋን ልጁም ልጁ እንደሆነ መቀበሉን አስመስክራ እስኪበየንላት ከዚያው ሆና በመጠባባቅ ላይ ናት። ከጡረታውም ከካሣውም የራስዋንም የልጁንም ድርሻ ማግኘቷ አይቀርም። አሁን አስተባባሪ ኮሚቴ የሚባእልው ከመጣ ወዲህ ደግሞ ሰው ሁሉ እየፈራ ነው። ዳኛው ቶሎ ይፈርዳል የፋፍሪካው አለቃም በተለይ ጦር ሠራዊት ነበር ከተባለ ለመክፈል አያንገርግርም ነው የሚሉት ሰዎች። ይኸው ሆኖ ነው ነገሩ እንደ አጋጣሚ በሌሉበት የመጡት።»

«እና እና» ሙሔ መላሱ ተሳሰረበት። «እና፥ ልጄ፥ ማለቴ ልጁ፥ የሰውየውን ካሣም፥ ጡረታም እየበላ ሊያድግ ነው ማለት ነው?»

«እህሳ! ለእኛም ሁሉ ተረፈን እንጂ።» ሴትዮዋ የሙሔን ሁናቴ ሲመለከቱ ትንሽ ስቅቅ አሉ። «ወይስ ሐሳብዎን የመቀየር ፍላጐት አለዎ? መቼስ ልጄን ስጡኝ ካሉ በግድ አናስቀረው። መቼም በዕድላችን ማዘን ነው እንጂ። የሌላ ሰው ልጅ መሆኑን ካወቁ....» ሴትዮዋ ለመጨረስ የይፈሩ ይመስል ንግግራቸውን አንጠልጥለው ተውት።

ሙሔ ስሜቱ ተወራጨ። ተበሰጫጨ። ምን ዓይነት የሕይወት ዕድል ነው? እሱ ራሱ የሚያቀምሰው አጥቶ አሳልፎ ለሌላ የሰጠው ልጅ የእንጀራ ማስገኛ ሆነ። «ኤዲያ! አንዴ ቃል ገብቼ። የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ ተብሏል» በማለት ሙሔ ሐሳቡ እንዳይወላውልበት በመጣደፍ ተነሥቶ ወጣ። እህሉንም ሳይቀምስ። የመንፈስ ባዶነት የመንፍስ ጭርታ ተሰማው።

የቆሬ ቀዬም ጭር ብሎ እንደ ሸኛቸው ጭር ብሎ ተቀበላቸው።

## ፯

ከስደት ተመልሶ፥ሀ ብሎ እንደ ገና ለመቆርቆር መሞከር ስደት ከመሄድ ያላነሰ ጽልመተ ሕይወት ነው። ከየት፥ በምን እንደሚጀምር ምኑ ከምን፥ እንደሚያያዝ ውሉ ይጠፋል። ሙሔና ከበደም ምን እንደሚያደርጉ ግራ ገብቷቸው ሁለት ቀን ያህል ዝም ብለው ከቀዬው ጋር ተፋጠጡ። መሬቱ አለ።

ዝናሙ ደህና ይጥላል። ግን በምን ይታረሳል? እርግጥ በምኑም በምኑም መሬት ተጭሮ ለመስከረም መዝለቂያ ጐመን ማግኘት ይቻላል። ነገር ግን በተጋመሰ ክረምት በዶማ ታርሶ የዓመት ቀለብ አመርታለሁ ማለት ዘበት ነው። በሰፈሩ ደግሞ አንድም የቀንድ ከብት አይታይም። ከእነርሱ ሌላ ጢስ የሚጤስባቸው ሌሎች ሁለት ቤቶች ብቻ ናቸው። ከአንዲቷ ጐጆ አንዲት በዕርዳታ ያገኝዋትን እህል እየቀማመሱ አንዲት አሮጊት ብቻቸውን ይኖራሉ። ሌላው ጐጆ እንደ ሙሔ ብዙ ሆኖ ወጥቶ አንድ ራሱን የተመለሰው የቢልልኝ ነው። በተአምር አንድ አህያ ተርፎታል።

ከበደ ለረጅም ጊዜ ካወጣ ካወረደ በኋላ «ለምን ፈረስ አንገዛም?» ሲል ሙሔን አማከረው።

«ምን ልንሠራበት?»

«ልናርስበት ነዋ!»

«በፈረስ?» ሙሔ ሳቅ ቃጣው።

«አዎ! አንዴ ጐዛም የሄድሁ ጊዜ አቸፈር በፈረስ ሲያርሱ አይቻለሁ። ታዲያ መቶ ሠላሳ ብር አንድ በሬ ስንኳ አይገዛ።»

«ታዲያ በአንድ ፈረስስ ልታርስ ኖሯል?» ሲል ሙሔ ቀለደበት። «ደግሞ በዚህ ቆላ ፈረስ አንድ ቀንም አያድር። ባንዳፍታ ንድፍት ነው የሚከነብለው።»

ከበደ አሁንም ጥቂት አሰበ። «ለምን ከአያ ቢልልኝ አህያ ጋር አንጠምደውም?»

ሙሔ ሳይወድ ነገሩ በግድ አሳቀው። አህያና ፈረስ ባንድ ተጠምደው ሊያርሱ? ጉድ ነው! ተረት - ተረት ነው - «ኦሆሆ! ኦሆሆ! የፈረሱ ሲገርመኝ አህያ አከልክበት! አታመጣው የለህ!»

«እንዲያውስ ሳይስማሙ ይቀራሉ? የበቅሎ ወላጆች ባልና ሚስት ናቸው» አለ ከበደ በበኩሉ በመቀለድ።

ነገር ግን ጭንቀት ጉምን ያስቧጥጣልና ሊሞክሩት ተስማሙ። ቦናው የወጣ አንድ አጋሰስ በሰማኒያ ብር ተገኘ። በሃያ ስምንት ብር አንዲት ሽል የያዘችና አንዲት ጠቦት ፍየሎች ተገዙ። የተረፈው ብር ለመጠባበቂያ ተቀመጠ።

ፈረስና አህያ ማጣመዱ ራሱን የቻለ አንድ ትንግርት ነበር። አህያ ቁሞ ልራገጥ ስል ፈረስ አግድም ልሽመጥጥ ይላል። አንዱ ወደ ቀኝ ሲስብ አንዱ ወደ ግራ ይዞራል። አህያል ለምለም ሳር ካገኘ አቀርቅሮ ወይ ፍንክች ይላል። በዚህ ላይ የአህያና የፈረስ ቁመት አልመጣጠን ብሎ ቀንበር ወደ አህያ ትከሻ ላይ ሲያደላ ማረሻው ስያፍ ይንሻፍፋል። ግን ሁለቱም እንስሶች ገራም ኖረው በጥቂት ቀናት ውስጥ አለማምደው፥ ሦስቱም እየተጋገዙ ትልም ማውጣት ቻሉ። ክረምቱ ገፍቶ መሬቱ ርሶ ስለ ነበር ለማረሻ እምብዛም አላስቸገረም። ብዙ ጊዜ አንዱ እርፍ ሲይዝ ሌላ ሰው፥ ከፊት ሆኖ አህያውን ወይም ፈረሱን መሳብ ነበረበት። አሮጊቷ ሳይቀሩ በአገኙት መሣሪያ ይቆፍራሉ። በዚህ ዓይነት የአራቱም ማሳ ዘር ቀመሰ።

መስከረም ላይ ጐመን ደረሰላቸው። ከአንዳንዱ ጓሮም ከስንት ዓመት በፊት ከወዳደቀ ፍሬ ዱባ አፍሮት ተገኘ። ጠል ካገኘ መሬት የሰጧትን አታስቀር! ምነው ጭቃ፥ ሹሙን፥ ምስለኔውን ገዢውን፥ ጉልተኛውን እንደ ተባረከከችው መሬት ቢያደርጋቸው?

በዚህ ጊዜ ሁሉ እንደ ድፍን ኢትዮጵያ እንደ ድፍን ወሎ፥ የአልጋ መናጋር ወሬ በተለያየና በተዘበራረቀ መልክ በቆሬ ቀበሌም ተዳርሶ ነበር። ግን እስከዚህም የተጨነቀበት አልነበረም። ወሬው የሚነሣው እንደ ዋዛ ነበር።

-ኸረ እናንተ የራስ አሊ ወሴ ቅምጥሎች እኮ ታሰሩ አሉ።

-ይበቃቸዋል በልተዋል።

-አዲሳባ ምድረ መኳንንት አልተረፈም አሉ፥ ከርቸሌ ገባ።

-እ ዛዲያ ምን አሳሰበህ?

ምን አዲስ ነገር ሆነና? እንደነሙሔ እንደነከበደ እንደነ ቢልልኝ የመሳሰሉትን ባተሌዎች ለጊዜው የሚያሳስባቸው፥ የሚያስጨንቃቸው ለሕልውና ብቻ የሚያደርጉት ትግል ነበር።

በሕልውናቸው፥ በኑሮዋቸው ላይ ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣ ማዕበል የተነሣ መሆኑን ግን አላወቁትም።

## ፳

ፀደይ ገብቶ ሰማዩ ከዳር እስከ ዳር ገለጠ። ቀዝቀዝ ያለ የመስከረም፥ የጥቅምት አየር ነፈሰ። እሸት ተቀምሶ የገበሬ ዓይን በተስፋ የሚያየው አዝመራ ሁሉ ጐመራ። ደፍርሰው ሲያጓሩ የከረሙት ወንዞች ኵል እየመሰሉ በእርጋታ በሹክሹክታ፥ መፍሰስ ጀመሩ። አገር ምድሩ በአዝመራ መዓዛ ታጠነ። ያለቀው አልቆ፥ የተረፈው እንደ ምንም አዲስ ኑሮ አቀጠቀጠ። የመስቀል ወፍ ስትሄድ የሚመጣው፥ ጉልተኛ ምስለኔ ባላባት ዘንድሮስ ያሰልስ ይሆን? የሚል ሥጋትም አብሮ በቀለ።

ደርጎች የሚባሉ እንግዳ ነገር እየሰበኩ፥ አዲስ ዜና እያበሠሩ ወደ ገጠሩ መዝለቅ ጀመሩ። ሙሔ ከበደና ቢልልኝም ንጉሥ ያወረዱትን ደርጎች ለማየትና ሲናገር ለመስማት ከሚሴ ከተማ ወጡ። የከተማው ሰውና የአካባቢው ገበሬ ሁሉ ከገበያው ላይ ተሰበሰበ።

እንደ አውቲስታ እንደ አውታንቲ፥ ካቶሞቢል ጣሪያ ላይ ወጥተው ብዙ ይናገራሉ። ብዙ ሰው ግን የሚናገሩትን ከማዳመጥ ይልቅ በመገረም ይመለከታቸዋል። ስንኳ ንጉሥ የጣሉ የአንድ ፊታውራሪ ጦር ድል ያደረጉም አይመስሉ። የሚናገሩት ሁሉ ባይገባቸው አልፎ አልፎ፥ የሚያዝላቸው የባተሌ ልብ የመከረኛን አንጀት የንካል።

-ከእንግዲህ ወዲያ ማንም ሰው የአስተዳደር በደል አይፈጸምበትም፤ የፍርድ መጓደል አይደርስበትም።

የአድናቆት ድምስጽ ያተማል።

-ከእንግዲህ ወዲህ፥ ኢትዮጵያ አገራችን የመላ ሕዝቦቿ ስለሆነች፥ ተባብረን፥ ተሳስበን፥ እናሳድጋታለን። ኢትዮጵያ ትቅደም!

አሁንም የደስታ ሁካታ ያስተጋባል።

-በኢትዮጵያ ትቅደም ፍልስፍና መሠረት፥ የወሎ ረሃብ፥ የወሎ እልቂት ወደ ፊኢት እንዳይደገም እንጥራለን።

ከሴቱ ወገን ዕልልታ ይቀልጣል።

ከፊሉም የሞተበን እያስታወሰ ዕንባ ያቀራል።

-ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ዛሬም ነገርም የቆመው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም ኑሮ ስለሆነ፥ ጥቂቱ በቁንጣን ሲወጠር ብዙኃኑ በረሃብ የሚሠቃይ መሆኑ ይወገዳል።

ጭብጨባና ሹክሹክታ ይደባለቃል።

ጥያቄዎች ይቀርባሉ።

-ምስለኔዎችንና ጭቃ ሹሞችን ምን ልታደርጓቸው ነው?

-ይታገሡን አስፈላጊውን መንገድ እንፈልግላቸዋለን።

-ይልቅስ ጐተራ የሚያሟጥጥብንን ይህንን ባለባት አንድ በሉን።

-ለሁሉም ታገሡን።

-ታግሠን ታግሠን አጥንታችን ወጣ!

የቅሬታ ማጉረምረም ይሰማል።

በተለይ ብዙ ሰው በቀላሉ ሊገባው ያልቻለው የዘማቾች መምጣት ጉዳይ ነበር። የምን ቸማች? እንደ ቀድሞው በየጢሲ እየተተከለ፥ መሶብ የሚገለጥ፥ ድስት የሚደፋ የመሰላቸው ብዙዎች ነበሩ።

-ምን ሊያረግ ነው ዘማች የሚመጣብን?

-ሊያስተምራችሁ፥ ሊረዳችሁ።

-ምን ሊያስተምረን?

-የሚበጃችሁን ማንኛውንም ነገር፥ ማንበብም መጻፍም።

-እንግዲህ እኛ ተምረን? ይልቅስ ለልጆቻችን ትምህርት ቤት ሥሩልን።

-ልጆቻችሁንም ያስተምሩላችኋል።

-እሱ መልካም።

ዘማቾች የሚያርፉበትን ቤት ለመሥራት ፈቃደኛ መሆኑን በመስማማት እያውካካ ወደየሰፈሩ ተበተኑ።

ሲመለሱ ከበደ ሲከነክነው የቆየውን ጉዳይ ለመጠየቅ ሰበብ አገኘ።

«ይኸው እስከ ዛሬ ቃሌን ጠብቄ ታግሼ ቆይቻለሁ። አሁን ግን ልጅቷን ስጠኝ» አለው ሙሔን።

«ቆይ ምን አስቸኰለህ! ባይሆን መጀመሪያ የበልግ መከር ይለፍ» ሲል ሙሒሀ መለሰለት።

«ይኸው እንደ ሰማነው ዘማቾች የሚመጡ ከሆነ ሴት ልጅ ብቻዋን ናት መባሉ ደግ አይመስለኝም። የከተማው እንድ ብዙ የለመደ ነው።»

«ቁሜ እየሄድኩ?» ሲል ሙሔ እንደ መፈከር ቃጣው።

«ቢሆን። ከነገሩ ጦም እደሩ እንደሚባለው ቀላሉ መንገድ እያለ? ባለባል ናት ከተባለ ወንድ ይታቀባል።»

«ሁሉ እንዳንተ ልክስክስ ይመስልሃል?» አለ ሙሔ፥ በቀልድ ግሣዌ። በሐሳቡ ግን የማይከፋ ጥንቃቄ መሆኑን አመነ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ከከበደ ቤት አንዷት ዶሮ ታርዳ ያይኔ አበባ ጨርቆቿን ይዛ ገባች።

ሙሔ ቤቱ የባሰውን ጭር ሲልበት ኀዘንና ትካዜ ክፉኛ ተጫነው። የሞቱትስ ቊርጣቸው ታውቋል። የተፉትና የተበተኑት ልጆቹስ? አዲሱ መንግስት የሕዝብ አለኝታ ነኝ ካለ በዚህ መከራ የተበተኑት ቤተሰቦች የሚሰበሰቡት ዘዴ ቢፈርልግ መልካም ነበር የሚል ሐሳብ መጣበት።

## ፱

ከሰኔ ጀምሮ እስከ ጥቅምት ድረስ ገንፍሎ የተነሣው እንቅስቃሴ እንደ አፍለኛ ሙላት፥ ፍንፍል መለስ በማለቱ የውጭ አገር ጋዜጦች «አዝጋሚው የመንግሥት ግልበጣ» የሚል ቅጽል ያልሰጡትን ያህል አሁን ከዳር ዳር የሚያደርግ የሚተራምስ የሚጠያይቅ ፍጥነት ያዘ።

-ኢትዮጵያ ወደ ፊት የምትመርበት ፖሊሲ፥ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብአዊ ወይንም ሶሻሊዝም ነው።

-የኢትዮጵያ ኅብረተሰበአዊነት፥ መረዳዳት መተጋገዝ፥ ከሆነ አዲስ ነገር አይደለም። ወትሮም የሚፈልገው ይኸው ነበር። ግን ሶሻሊዝምን ምን አመጣው? በየቡና ቤቱ፥ በየቤቱ በየአካባቢው መከራከር መጨቃጨቅ.....

-በሃይማኖቶች መካከል ልዩነት ስለማይኖር፥ የክርስቲያኖችም፥ የእስላሞችም በዓላት እኩል ይከበራሉ።

-እንዴት ተደርጎ! ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት! እስላም አይሠለጥንባትም። በየቤቱ፥ በየቤተ ክርስቲያኑ፥ በየአደባባዩ ዱላ ቀረሽ ግጭት....

-ከዛሬ ጀርሞ የኢትዮጵያ ራዲዮ ጣቢያ በኦሮምኛ ፕሮግራም መጀመሩን በደስታ ያስታውቃል።

-ምን? ኦሮምኛ? የምን በስም መሽፋፈን! ጋልኛም በመንግሥት ራዲዮ ሊነገር! በየመንደሩ የጦፈ ጠብ…..

-ከዛሬ ጀምሮ የንግድ ባንኮች፥ የገንዘብ ድርጅቶችና የኢንሹራንስ ኩባንይያዎች በሕዝብ ይዞታና በመንግሥት ቊጥጥር ሥር ተደርገዋል።

-ምን ማለት ነው? መውረስ ማለት ነው? ሶሻሊዝም የግል ሀብትን ይወርሳል ይባላል። ግን ልክ ነው የሰውን ንብረት መውረስ? ክርክር፥ ምክር ጥያቄና ጥርጣሬ በየቀየው….

ይህ ሁሉ ውጥንቅጥ ስሜትና አስተያየት እንደ አዙሪት እየተሽከረከረ የሚከማቸው በዘማቾችና በዘመቻው ላይ ነበር። በብዙ ትግልና ተቃውሞ መካከል የዕድገት በኅብረት የዘመቻ የክተት በዓል ታይቶ በማያውቅ ሁናቴ በአዲስ አበባ ተከበረ።

የዘመቻው የደንብ ልብስ የሆነው ካኪ ቀብ፥ ሸሚዝና ሱሪ ለዘማቹ ልዩ ውበትና ግርማ ሞገስ ሰጥቶት ግማሹ ኮዳ አንግቶ ሌላው፥ አካፋ፥ ዶማ፥ ማጭድ ይዞ ከዘመቻ መምሪያ ጽሕፈት ቤት በመነሣት በድል ሐውልት በታላቁ ቤተ መንግሥት በኩል ሲያልፍ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ተሰናበተው። መዝሙሩ፥ ዘፈኑ፥ ጭብጨባው ዕልልታው፥ ቀለጠ። ብዙ ሰው የደስታና የኵራት ሕቅታ ተናነቀው። ብዙ የደስታ እንባ ፈፍሰሰ። የኃይለ ሥላሴ መንግሥት እያወገዙ፥ ከፀጥታ አስከባሪዎች ጋር እየተጋጩ ባለፉበት አደባባይ «መሄዴ ነው ዘመቻ፥ መሄዴ ነው ገጠር» እያሉ በመዘመር እጃቸውን በኵራት ሲያውለበልቡ ማየት የደስታ ሲቃ የሚያሲዝ ነበር።

በዚህ ስሜት ሥር ግን ሌሎች ስሜቶች ወዲያውኑ ሥር መስደድ ጀመሩ። አንዳንድ ዘመናይ ወላጅ ልጁ፥ ከአዲስ አበባ አካባቢ እንዳይርቅበት ይፈልጋል። አንዳንድ ዘመናይ ቡና ቤት ከሌለበት ገጠር ለመሄድ ይፈልጋል። የዘመቻው ድልድል ልክ አይደለም - አድልዎ አለበት የሚለው ሐሜት በዚያ ልክ ይናፈሳል። በዚህ መካከል በደርግ፥ ላይ ቂም፥ - በቀል የያዙ በደርግ ላይ የተነሡ ሥራ አልፈቱም ነበር። መዝመት ግዳጅ ከሆነ ወደደም ጠላም አብዛኛው መዝመት ቢኖርበትም በነገር የተበከለው በተንኰል የተመረዘው ጥቂት አልነበረም።

ለምን እንደሚዘምቱ፥ ለማን እንደሚዘምቱ የሚያቁት እንደነታረቀኝ ያሉት ደግሞ፥ የትግልና የመሥዋዕትነት ዓርማቸውን ተሸክመው ተነሡ።

ከአዲስ አበባ ለመነሣት አንድ ቀን ሲቀራቸው ቦጋለ ድንገት ከተፍ አለ። በኅዳር ወር ከተለያቸው አንሥቶ አይተውትም ተገናኝተውትም አያውቁም። አውቆ እንደ ሸሻቸው ግልጽ ነበር። የተቀመጡት በእርሱ ቤት ቢሆንም፥ ከስንት ወራት በኋላ አሁን መምጣቱ አስገረማቸው።

ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ «ኧረ ለመሆኑ ምን እግር ጣለህ ዛሬ? እኛማኮ የቤቱን ቁልፍ ለማን እንደምንሰጥ ግራ ገብቶን ነበር» አለው ታረቀኝ።

«ልጠይቃችሁ ልሰናበታችሁ ብመታ ነውር አለበት እንዴ? ስለዚህ አመጣጤ ቤት ለመረከብ አይደለም። እነርሱው ሊቆዩበት ይችላሉ።» ካሣሁንና ዘይኔን ማለቱ ነበር።

«እነርሱም እኮ ሂያጆች ናቸው።»

«ከእናንተው ጋር? ዘማች ሆኑ እንዳትሉ?» አለ ቦጋለ በፌዝ።

«እውነቱን ለመናገር እኛስ ስንኳ የዘማች ልስብ አልብሰን በማሳፈር ለማጭበርበር አስበን ነበር። ስንሳፈር ዝርዝር ስም ስለሚጠራ መልሰን ተውነው።»

«የት ነው እነርሱ የሚሄዱት?» ቦጋለ ግራ የተጋባ መስሎ ጠየቀ።

ወደ ውሎ ነዋ! በጀም ከፋም እዚያው ገብተው ከአፍር ጋር እየታገሉ መኖር ይፈልጋሉ። ባንድ በኩል አይፈረድባቸውም። አዲስ አበባ ምን አላቸው? አረረም መረረም ያው የለመዱት ኑሮ ይሻላቸዋል። ግን አንተስ አሳብክን አላሻሻልክም?» ሲል ማርቆስ ጠየቀው።

«ማሻሻል የሚለውን ቃል አውቀህ ያመጣኸው ከሆነ ያከራክራል። የማንኛችን ሐሳብ የተሻለ ሆነና ነው? ሐሳብክን አልቀርክም? ማለትህ ከሆነ መልሱ አሉታ ነው። ለመሆኑ አንተም ታረቀኝም ወሎ ነው የምትዘምቱት ማለት ነው?» የማርቆስ ንግግር ደህና መንገድ ስለ ከፈተለት የቦጋለ አጠያየቅ እንደ ዋዛ ነበር።

«ደቡብ መዝመት ከሚፈሉት ልጆች ጋር ተለዋውጠን፥ እንደ አጋጣሚ ከሚሴ፥ ከሚባል ከተማ ወጣ ብሎ በዚያው በቆሬ አቅራቢያ ነው የዘመቻ ጣቢያችን። ካሣሁንና ዘይኔ ፈንድቀው መሞታቸው ነው።» ታረቀኝ ተሽቀዳድሞ መልስ የሰጠው ሳይታወቀው ነበር።

ተሰናብቷቸው ከሄደ በኋላ ማርቆስ በታረቀኝ ላይ አፈጠጠበት፥ «ምን ማለትህ ነው?»

«ምኑ?»

«የዘመቻ ጣቢያችንን መንገርህ?»

«ምናለበት?»

ማርቆስ በአፍንጫው ተነፈሰ። «ምን አለበት በል! እንዴት ምንም የለበትም? ገበየሁ ምን በመሥራት ላይ እንዳለ ታውቃለህ? ታጥቆ ተነሥቶብናል። በተለይ ያ ኀደኛው ሽንት ቤት ገብቶ ከሞተ ወዲህ አንተን ሳያጠፋ እንደ ማይጠፋ አየዞረ በግልጽ ነው የሚያወራው።»

«እና?» የታረቀኝ አነጋገር የረጋ ነበር።

«የወሎ ባላባት የሆነው አባቱ ፊታውራሪ ፋሪስ ደግሞ ኃይለ ሥላሲዔ ከሥልጣን ከወረደ ጊዜ አንሥቶ ተሠውሯል አሉ። እንዲያውም ሽፍቷል ነው የሚባለው።»

«እና?»

«እንደሚሰማው ጭምጭምታው የመሬት ይዞታን የሚያሻሽል አዋጅ ከወጣ ደግሞ፥ እኛ የምንጋፈጠው እንደ ፋሪስ ከመሰሉት ባላባቶች ጋር ይሆናል።»

«እና?»

«ምን እና? እና? ትላለህ!» ማርቆስ በሸቀ። «አንድና አንድ ሁለት ብለህ መደመር ያቅትሃል?»

«እስቲ መጀመሪያ መሬት ላራሹ ይሁን፡፡ ስለኛ በኋላ እንጨነቃለን፡፡» ታረቀኝ ነገሩን በማቃለል ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ፡፡ ነገር ግን ቦጋለ ከዘመቻ ከቀረና ከእነርሱ ጋር ከተለያየ አንሥቶ የገበየሁ ዋና ደቀመዝሙር መሆኑን ሰምተው ስለ ነበር ጥቂት ሐሳብ ገባው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

«.....አብዮቱን የምመራው አቋም መጠናከርና መሪዎችም በአብዮታዊ ሥነ ምግባር የተገነቡ መሆን ስለሚገባቸው ከአብዮቱ መሥመር የሚወጡትና በአሳፋሪ ተግባር የሚገኙ የደርግ አባሎች በማንኛውም ጊዜ ለሕዝብ ተጋልጠው አስፈላጊው አብዮታዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ስድስት የደርግ አባሎች ከአብዮታዊ ሥነ ምግባር ውጭ የሆነ ተግባር በመፈጸማቸው በከባድ ማስጠንቀቂያ በእሥራት ቅጣትና ስድስቱም ከደርግ አባልነት እንዲሰረዙ ተወስኖባቸዋል.....»

ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

የተሠጠ መግለጫ

እንደሚሉት፥ ዲስኩርና ስብከት ከማብዛቱ በስተቀር ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እያደር «የደርጉ መንግሥት» እስከዚህም የሚስመምርር ሆኖ አላገኙትም፡፡ የመጀመሪኢያው ድንጋጤ ሲያልፍ ኀዘኑም፥ ሲረሳሳ የዘለቃ ወዳጅም ቤተኛ ሲሆን እየተላመዱት ሄዱ፡፡ ባንክና ኢንሹራንስ ቢወረስ ደንታ አልነበራቸውም፡፡ ፋብሪካ ቢወረስ እሳቸው የላቸው! እንዲያውም የጓደኞቻቸው አውቶሞቢሎች ሁሉ ተወርሰው በሃራጅ ሲሸጡ የእርሳቸው ፔጆ ብቻ ሳትነካ ስትቀር፥ የዘለቀአ ወዳጅ ለገና ስጦታ ማዳም ሮሽ ሽቶ ሲያመጣላቸው በታም ተደስተው ነበር፡፡

የማናዬ በጡረታ መገለል ስንኳ አላስከፋቸውም፡፡ በለውጥ ሐዋርያ ትዕዛዝ ከእርሱ ጋር ዘጠኝ የመሥሪያ ቤቱ ሰዎች ጡረታ እንዲወጡ በመደረጉ «ገናኮ አሥር ዓመት ይቀረኛል፡፡ በችሎታም እንደሆነ ከማንም አላንስም» እያለ ማናዬ ሲናደድ «ወቸው ጉድ! እንግዲህ ቀንድ ልታወጣ ኖሯል? ባንተ ቤት ጒረምሳ ነኝ ማለት? ድንቄም! ይልቅስ ዝም ብለህ እየነገድህ አትኖርም?» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ነገሩን አቃለሉበት፡፡ ውስጡን በሆዳቸው ግን ጡረታ መውጣቱ በዕድሜ ከእርሳቸው የሚያስበልጠው ሆኖ ተሰማቸው፡፡ የጡረታ አበሉም እምብዛም ስለማያወላዳ የበለጠ በእርሳቸው መተማመን ግድ እንደሚሆንበት ተስፋ አደረጉ፡፡ ዘለቃ ወዳጅዋን እንድትለምንለት በጠየቃት ጊዜ «በንትሽ በትልቁ የምን ማስቸገር ነው፡፡ ውለታን ቆጠብ አድርጎ መያዝ ነው እንጂ እንደ ሞኝ እንትን በሆነ ባልሆነ መጣል ምን ይባላል?» በማለት የተቃወሙትም ስለዚህ ነበር፡፡

«እየነገድህ አርፈህ ተቀመጥ አሉት፡፡»

«ንግድኮ ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃል፡፡»

«ይፈለጋል፡፡»

የገንዘቡ ጉዳይ ግን ራሳቸውንም ቢሆን በመጠኑ እያሳሰባቸው ነው፡፡ ለማይሆን ጋብቻ ለዘለቃና ለማስረሻ ሠርግ ብዙ ገንዘብ አፍስሰዋል፡፡ በዚህ ላይ ድርቅ ገብቷል፥ ሕዝብ ተሰዶአል ተብሎ ከቆሬ መሬታቸው ዓመት ሙሉ ቁና እህል አላገኙም፡፡ ከቀለብ አቅም እየሸመቱ ነበር የከረሙት፡፡ የረዳቸው የሠንጋ ተራ መሬታቸው መሸጣቸው ነበር፡፡ አንድ ደህና ቪላ የማታሠራ አራት መቶ ሃምሳ ካሬ ሜትር

ከመሆኗ በቀር ወሽመጥ ቅድ ሸጣጣ ስለሆነች ዋጋ አጥታ ስትኖር ገንዘቡን መበተን ያማረው አንድ የመርካቶ ነጋዴ ሜቱን በሰማኒያ ብር ሒሳብ ገዛቸው። ዋናውን መንገድ ይዞ ሠፈሩ በካሬ ሚዬትር መቶ ሰባ አምስት ብር ደርሶአል። ሁለት መቶ መድፈኑ ይቀራል? ለዘንድሮ ነው እንጂ ከርሞ ስንኳ ብዙ ዕቅድ አላቸው። ለዘንድሮውም ቢሆን ወሎ እንደገና ታርሶ ተዘርቶ ከርሚል። ሌላው ቢቀር ለፋሲካ ዓመት በዓል መዋያ የሚሆን ለማምጣት ቅበላውን ውለው ወደ ወሎ ለመሄድ ማሰባቸውን ለዘለቃ ወዳጅ አንድ ቀን በጨወታ ጨወታ ነገሩት።

«እንደኔ - እንደኔ መሸጡ ነው የሚሻለው። ብዙ መሬት ምን ያደርጋል?» ሲል አማከራቸው።

«ምን አለው ብለህ? ትንሽ እኮ ነው። አምስት ጋሻ ስንኳ አይሞላም።»

«ቢሆንም ይሸጡት።»

«ለምን ተብሎ? የታሰበ ነገር አለ?» ሲሉ ጠየቁ።

ለወትሮው እንደ ጨርቅ የሚተረተረውን ጉራውን እንደ ምንም ገትቶ «ቢሸጡት ነው የሚሻለው ካልኩ አይበቃም?» በማለት ዘጋ።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሲነከክናቸው ሰነበተ። ሐሳባቸው ከሁለት ተከፈለ። ባንድ በኩል ከርሞ ከልማት ባንክ የፈልጉትን ያህል ብር አግኝተው፥ ትራክተር ገዝተው፥ ጭሰኞቻቸውን አሥነሥተው ግቢያቸው የማይበቃው፥ ገበያ የሚያጣብብ እህል በስንት መዓት ትሬንታ ኳትሮ እየተጫነ ሲመጣ ይታያቸዋል። ማናዬ ጡረታ ከወጣ የእርሻውን አስተዳደር ሙሉ ኃላፊ ሆኖ ቀጥ አድርጎ ይሠራዋል። የሚሰጠውን ሰጥቶ ከዚህያች ሚስቱ ጋር ማለያየት ብቻ ነው። የሰው ልጅ ልቡ ከሁለት ቤት ከተከፈለ አይረባም። አባካኝ ብስክስክ ነው የሚሆነው።

ሌላው ጥርጣሬ ደግሞ አለ። - ወዳጃችን ለምን ሸጪው ሲል መከረኝ? ነገር ቢኖር ነው። ግን ምን ነገር ሊኖር ይችላል? እንኳን እኔ ሽህ ጋሻ ያላቸውም አልተጨነቁ። የወይዘሮ ሸዋዬ የአዳው አሥራ አምስት ጋሻ መሬት አለ አይደል? አምስት ጋሻ መሬት ምንድን ናት? ግናስ ቢሸጥ፥ ቢሸጥ ለምን ይሻላል አለ? እኒህ ደርጎች እኮ ጉደኞች ናቸው። ብዙ ሰዓት ለብቻቸው ከሐሳባቸው ጋር ሲወያዩበት ሰነበቱ። ጥርጣሬያቸው ሲበረታ የሚኢገዛም አጠያየቁ። ግን አንድ ሁለት ሰዎች ለመግዛት ፈቃደኛ ቢሆኑም ዋጋ በጣም ሰበሩባቸው።

«እንደነወይዘሮ ሸዋዬ የአድአ መሬት ስልሣ ሰባት ሽህ ብር ባልለመንበት፥ ጋሻ መሬት በአንድ ሁለት ሽህ ብርስ አልሸጥም። እንዲሁ በነፃ አልሰጠውም?» ሲሉ ተቆጡ።

በዚህ አኳኋን የወሎ መንገዳቸው እየተላለፈ ቆይቶ የካቲት መጨረሻ ሳምንት ላይ ሰማይና ምድሩን ያደባለቀው ዱብ - ዕዳ ወረደ። የገጠር መሬት አዋጅ....

ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ሌሎችም ብዙ ሰዎች በመጀመሪያ ራዲዮው እንደ መርዶ ተናጋሪ በጠዋት እየደጋገመ የሚለፈልፈውን ማመን አቃታቸው። እንገሩም አልገባቸው አለ። ከዛሬ ጀምሮ የሕዝብ ሆኗል ማለት ምን ማለት ነው? ካልተሸጠ ካልተለወጠ ምኑን የሕዝብ ሆነው? አሥር ሄክታር ያህል መሆኑ ነው? ሩብ ጋሻ? እንደ መቃብር ቦታ ሦስት ሦስት ክንድ ቢያደርጉት አይሻልም?

በበነጋው የአዲስ አበባ አደባባዮችና መንገዶች በሰልፈኛ ተጥለቀለቁ። ጭፋሮው ሆታው፥ መዝሙሩ ቀለጠ።

ዋይ ዋይ ባላባት፥

ዋይ ዋይ ባላባት፥

እንግዲህ ቀረ ሳይሠሩ መብላት።

ዋይ ዋይ መኳንንት፥

ዋይ ዋይ መሳፍንት፥

እንግዲህ ቀረ የአገልግል ፍትፍት።

ዋይ ዋይ ባላባት፥

እንግዲህ ቀረ ሙክት ማስጐተት።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የባሰ ያበሸቃቸው የሕዝቡ እንዲህ መሆን ነው። አደባባይ ወጥተው አላዩትም።

ራዲዮው የሰልፉን ወሬ ከጭፋሮው ጋር ሲያስተላልፍ። «ስድቡን ደግሞ እስቲ ም ን አመጣው? እሱ ቆሎ ያረረበት እንደሆን የሰው ልጅ ለምን ፍትፍት በላ ብሎ ስድብ አለ? ዝጉልኝ እሱን ራዲዮ አታደንቁሩኝ» ሲሉ ጦፉ።

ይህም ሆኖ ጨርሰው ተስፋ አልቆረጡም ነበር። የዘለቀአ ወዳጅ አውቶሞቢላቸው እንዳስቀረላቸው፥ «ቢሸጡ ይሻላል» ሲል እንደ መከራቸው አሁንም አንድ ዘዴ ይፈልግላቸዋል። እሳቸውም በበኩላቸው ሕዝብ የሚያበጣብጥ እንደዚያ ያለ ስሕተት ወደ ፊት ደርጎች እንዳይደግሙ አንዳንድ ምክር ይሰጡታል።

ሰውየው ግን ለዘለቃ ቴሌፎን ስንኳ ሳይደውልላት ብዙ ሳምንታት አለፉ። በመጀመሪያ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል «ዓይናችንን ማየት ቢያፍር ነው። ንዴታችን እስኪበርድ ድረስ በማለት ይሆናል» የሚል ግምት አደረባቸው። ከሳምንት በኋላ ትክክለኛውን ምክንያት ተረዱ። «ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተሰጠ መግለጫ!» የአድማጭ ሁሉ ጆሮ ወደ ራዲዮ አቆበቆበ። ደግሞ ምን አዲስ ነገር ሊመጣ ይሆን? መግለጫው የደርግ አባሎች «የኢትዮያ ትቅደምን ዓርማ ይዘው ሲነሡ የገቡትን ቃል ኪዳንና የፈጸሙትን መሐላ ከአተተ በኋላ አንዳንድ የደርግ አባሎች ግን ይህንን ቃል ኪዳናቸውን ዘንግተው ወራዳና ልክስክስ ጠባይ ማሳየታቸውን ዘርዝሮ ከፍተኛ የእርማት ቅጣት እንዲሰጣቸው መወሰኑን አስታወቀ።ከተጠራው አንዱ የዘለእቃ ወዳጅ ነበር።

የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተስፋ ድንገት እንደ ተንሰራራ ድንገት መልሶ ሚሸሸ። የተገላቢጦሽ ዘልቃ አጽናኝ ሆነች። «እኔኮ ለሰውየው እስከዚኢህም ፍቅር አልነበረኝም» አለቻቸው በማቃለል።

«ቢሆንስ ልጄ፥ በዚህ ክፉ ቀን አንድ ሁነኛ ሰው መያዙ መጥፎ አልነበረም።»

«ታዲያ ሌላ መፈለግ ነዋ!» ወዲያው ከሐሳቢ እያወጣችው፡፡

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የፈሩት አልቀረም፡፡ ማናዬ አንድ ቀን መኪናዋን ይዞ ወጥቶ በእግሩ ተመለሰ፡፡

«ወሰዱዋት» አለ ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠና ግንባሩ ላብ ችፍፍ ብሎበት፡፡

«ምኗን?»

«መኪናዋን?»

«ማን?» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጣሪያ በሚሰነጥቅ ጩኸት ጠየቁ፡፡

«ወታደሮች፡፡»

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዓይናቸውን አፈጠጡበት፡፡

«መብራት ላይ ትራፊክ ቁም አለኝና ሊብሬ ጠየቀኝ፡፡» ማናዬ ከንፈሩን በላ፡፡ «አውጥቼ አሳየሁት፡፡ ከዚያም ከማስታወሻ ደብተሩ ጋር አመሳከረና የመንግሥት ንብረት ስለሆነች ገቢ ትሆናለች ሲል ፖሊስ ጣቢያ በር ቊልፉን ተቀበለኝ፡፡

«እና መኪናዬን አስክበህ መጣህ?» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሲንቆራጠጡ ክፍሉ የጠበባቸው መሰሉ፡፡

«እኔ ምን አስረክባቸዋለሁ፡፡ እነርሱው ወሰዱዋት እንጂ፡፡»

«እና፥ ዝም ብለህ ሰጥተሃቸው መጣህ?»

«ታዲያ ምን ማድረግ እችላለሁ?»

«አዎ! እውነትክን ነው፡፡ ምን ማድረግ ትችላለህ? ወኔ ያለው ወንድ ያለመኖሩ ዘንግቼው ነው፡፡»

«ከዚያ ቀን ጀምሮ ንዝንዙን ተያያዙት፡፡ «አንተ ምን ገዶህ! መሬት አልተወሰደብህ፥ መኪና አልተነጠቅህ?» አሉ ነጋ ጠባ መብሰክሰክ ሆነ፡፡

ማናዬ ከእርሳቸው መሬትና መኪና የበለጠ ዕድል ያመለጠው መሆኑን አያውቁም፡፡ ውስጥ ውስጡን እያረረ ለማንም ያልገለጸው ምሥጢር ነበር፡፡

ማናዬ ከመገብ ቤት ተራ ጸሐፊነት አንሥቶ እስከ ዲሬክተርነት ድረስ በአገር አስተዳደር የርስት ክፍል ከሥራ አምስት ዓመት በላይ ሲሠራ፥ የማን መሬት የት እንደሆነ ጥሩ መሬት የት የት እንደሚገኝ በደን የተሸፈነው፥ ጠፉ ለም ጠፉ ለሙ የትኛው እንደሆነ ከመዝገበ ቃላት ያላነሰ ዕውቀት አከማችቶ ነበር፡፡ አምና የካቲት ከመንፈንዳቱ በፊቲ፥ የስም ሞክሼው የሆኑት የቀድሞ ባለሥልጣን ሦስት ጋሻ መሬት ከንጉሡ አስፈቅደው ከርስት ክፍል ማዘዣውን በማስወጣት ላይ ነበሩ፡፡ በአስቦት ወረዳ የተጠቀሰው መሬት የደን መሬት መሆኑን ማናዬ ያውቅ ነበር፡፡ ብዙዎቹ ባለሥልጣኖች የሚያደርጉት ነው፡፡ የእርሻ መሬት ነው ብለው የደን መሬት ይቀበሉና ደኑን በመቶ ሽህ ብር ይቸበችቡታል፡፡ በመሠረቱ የደን መሬት ልዩ ፈቃድ ያስፈልገዋል፡፡ ግን ከባለሥልጣኑን ጋር ምን አጋጨኝ? ነገሩን በሆዱ ያዘና ማዘዣው እንዲጻፍላቸው አደረገ፡፡ ማዘዣው በመዝገብ ቤት በኩል ወጭ

ሆኖ ከመውሰዳቸው በፊት የካቲት ፈነዱ፥ ቆይተው በቁጥጥር ሥር ዋሉ። እንደገና ወደ ሥራ ሲመለስ፥ ለሞክሼው የፈረመው የመሬት ማስረከቢያ ማዘዣ ከእነ ፋይሉ ከጠረጴዛው ላይ እንደ ተቀመጠ አገኘው። ከዚያም ሰውየው የቅጣት ውሳኔ ተፈጽሞባቸው ወሳጅ ያጣውን ማዘዣ በገባ በወጣ ቍጥር ሲመለከተው አንድ ሐሳብ መጣበት።

-ማዘዣው ከእጃቸው እስካልገባ ድረስ ቤተሰቦቻቸው የሚያውቁበት ምንም መንገድ የለም። እስከአሳወቁ ድረስ ደግሞ ውርስ መጠየቅ አይችሉም። ማን ያውቃል? እርግጥ የአባታቸው ስም ይላያያል። ግን እሱም መንገድ አለው። በፍርድ ቤት ስም መለወጥ ይቻላል። የምጠራው በአሳደጉኝ አያቴ ስም ነበር። ከዛሬ ጀምሮ ግን በወላጅ አባቴ ስም እንድጠራ ይፈቀድልኝ ብሎ ደብዳቤ ያስገባል። ተቃዋሚ ቢኖር ተብሎ ማስታወቂያ ይወጣል። የሟቹ ባለሥልጣን ቤተሰቦች አይቃወሙትም። ሚስጥሩን የት አውቀውት? እስከ አባት ድረስ የስም ሞክሼ እንደሆነ ሞልቷል። ከዚያ አረሳስቶ ቆይቶ በአዲሱ የአባቱ ስም የደን መሪቱን ይረከባል። መቶ - መቶ ሃምሳ ሽህ ብር በጠዋት ከኪስ....

ዘዴውን ብዙ ጊዜ ካወጣና ካወረደ በኋላ፥ የመዝገብ ቤቱ ሠራተኛ መድኃኒት ጠጥቶ በቀረበት ቀን «ኧረ ደርጎቹ ሥራ አትጎትቱ ብለዋል!» በማለት ፋይል ይዞ መዝገብ ቤት ጉድ ጉድ ሲል ቆየ። ተላላኪው ዘወር ሲልለት በፈራ ተባ ልቡ ታንቡር እየመታ ያልፈውን ዓመት የመመዝገቢያ ደብተር አወጣና የአለፈውን ዓመት ቍጥር አሲዞ ማዘዣውን ከሲሱ ከተተ። ቀሪውን ፋይል ከአልፈው ዓመት መዛግብት መካከል ቀላቀለው። ያለፈውን ዓመት ፋይል ተመልሶ ማን ያጣራል? እንዲሁ የሚያየውም አምና ወጭ ይሆነ ሕጋዊ ይመስላል። በታም ቀላል ሆኖ አገኘው። በሥራው ላይ እስከቆየ ድረስ መሬቱን ለመረከብ የዚያኑ ያህል ቀላል በሆነለት ነበር። እርግጥ ድንገት ሳያስበው ጡረታ በሥልጣኑ እንደ ልቡ እንዳይጠቀም ሊያደርገው ቢችልም መረከብ ችግር አይሆንበትም ነበር። ቢያስፈልግ ትንሽ «በእጅ» ማለት ነው።

ታዲያ የመቶና የመቶ ሃምሳ ሽህ ብር ዕድል በአንዲት መግለጫ በአንዲት ውሳኔ በአዲት አዋጅ ገደል ገባ። ማናዬ ይህንን ብሽቀቱን በሆዱ ቀብሮ ለማንም አላዋየውም። ግን ደሞ የሚያስቀምጥ አልሰር እስኪነሣበት ድረስ ውስጥ ውስጡን እያሳረረው ነው። በዚህ ላይ ደግሞ የወሎ መሬትና አንድ መኪና አጣሁ ብለው የወይዘሮ ዘርፈሽዋል መብሰክሰክና መነዛነዝ ተጨምሮ የሚሆነውን አሳጣው።

-ቋሚ የጋላ መሬት - ተነቃይ የጋላ መሬት - የየጁ ትክል - የአሊ ዘማች መሬት - ጋነ ገብ ያለንጋ መሬት - የሻለቃ ሁዳድ። የወሎ ባተሌ ገበሬ የሚያውቀው የመሬቱ ሥሪት ታሪኢክ ይህ ነበር።

-ባንድ ገባር አራት ዳውላ ማር - ጣሳ ቅቤ - ጉንዶ ማር - ጨው ግብር - የሻማ - ለፋሲካ የዓመት በዓል በጢስ - የጢፍ - የበግ ምልምል - እርቦ - ቤት ሥራ - አጥር አጠራ- እንጨት ሠበራ - ሁዳድ እርሻ። የወሎ ባተሌ ገበሬ ከአያት ቅድመ አያቱ አንሥቶ የሚያውቀው ሸክም ይህ ነበር።

አሁን ይህ ሁሉ ቀረ፥ ተፋቀ ማለት ነው? ብዙው ገበሬ የገጠሩን መሬት አዋጅ መረዳትና ማመን አቃተው። በተለይ የወሬ - ወሬ የሚዳረሰው ግራ የሚያጋባና የተማታ ሆነበት።

የእነ አልጋወራሽ ቤቶች - የራስ አሊ ወሌ ዘሮች - የእነ ራስ ይመር - የነ ራስ ያዘው ወገኖች - ከደሴ ከሐይቅ ከወልድያ፥ ወሬውን እያጣመሙ ነዙት።

-ምን መሰላችሁ? እኛ ብቻ አይደለምንም ከርስታችን ከጉልታችን ተነቀልነው። ማንም መሬት አይኖረውም። መሬቱን በሞላ ደርግ ወሰደው። እኛስ ከዚሁ ከእናንተው ጋር ተካፍለን ነበር የምንኖረው። አሁን ግን አዲሳባ ድረስ ልትጭኑ ነው።

-ታውቃላችሁ? የመቃብር መሬት ስንኳ አይፈቀድም። መጀመሪያ ለደርግ ኪራይ ከፍላችሁ ነው ሙታናችሁን የምትቀብሩት።

-ይኸማ ትሻልን ፊትቼ ትብስን አገባሁ መሆኑ ነው።

-ምን ጥርጥር አለው!

ይህንን አሉባልታ ለመቋቋም ዘማቾች የበኩላቸውን ብስራት ይዘው በየገጠሩ ተሰማሩ።

በከሚሴ ወረዳ የሚገኘው የእነታረቀኝ ዘመቻ ጣቢያ ኑሮ ባለፉት ሁለት ሳምንታት የመሰላቸትና የመቀዝቀዝ ስሜት ታይቶበት ነበር። ከአዲስ አበባ በዕልልታ የመሸኘቱ ሞቃት ስሜት እያደረ ሲበርድ የገጠሩ ኑሮ እስከዚህም አስደሳች አልሆነም። አንደኛ፥ ዝግጅቱ ያልተሟላ ስለ ነበር አንድ ሁለት ሳምንት ያህል ምንም የሚሠራ ነገር አልነበረም። ፊደል ማስቁጠሩን ስለ ጤንነት ማስረዳቱን አንዳንዶቹ በቂ ሆኖ አላገኙትም። ሆዶ ባዶ የሆነ ችግረኛ ገበሬ ፊደል ቊጠር ብሉት የት ያዳምጥና? የሚል ጥያቄ ተነሣ። በዚህ ላይ ከአርባና ከሃምሳ የተለያዩ ቤተሰብ ከተለያየ አስተዳደግ ከተለያየ የኑሮ ጣዕም የመጣ ወጣት በአንድ ጣሪያ ውስጥ ሲከማች በትንሽ በትልቁ አለመግባባት አለ። ታጥበውበት የተረሣ ሳሙና፥ መተላለፊያ ላይ የተቀመጠ ሳህን ወይም ኩባያ የጽዳት ተረኞች ያከናወኑት ተግባር ቡጢ፥ ቀረሽ ሊያጣላ ይችላል። ከናታቸው ጉያ ወጥተው የማያውቁት ልጅ ቢጤዎች ደግሞ ባስነጠሳቸው ቊጥር ዕንባ ይተናነቃቸዋል። ሻይው ሱካር አነሰው፥ ሾርባው ጨው በዛበት እንሽላሊት በግድግዳው ጠብቂያ ታየች ብለው ልቅሶአቸው ያቀልጡታል። ይህ ሁሉ የታረቀኝና የማርቆስን ስሜትም መንካቱ አልቀረም። እነርሱም እንደ ሌሎቹ ብስጭትን ንጭንጭ ይላሉ። ይህንን ሁሉ ለማስታገሥ፥ ይህንን ሁሉ ለማባበል፥ ይህንን ሁሉ አንድ ሥርዓት ለማስያዝ ለሚጥረው የዘመቻ ኃላፊ ብቻ የሚያዝንለት የለም።

ታረቀኝና ማርቆስ ብቻ አልፎ አልፎ ውጥረት ሲበረታባቸው ከዚህ አምልጠው የሚረጋጉበት ሥፍራ ነበራቸው። ቆሬ የእነሙሔ መንደር። ከዚያ አንድ ዓይነት የመንፈስ ደስታ ያገኛሉ። ከእነ ሙሔ ጋር እየተጫዋወቱም ሆነ በአንዳንድ ሥራ እየረዱ ቀኑ ሳይታወቅ ያልፍላቸዋል። ብዙ ጊዜም ውለው ያድራሉ። ከተገናኙ ዕለት አንሥቶ የማይለያዩ ቤተ ሰቦች ሆነዋል። የተገናኙበትን ዕለትም ከቶ አይረሷትም።

ጣቢያ በደረሱ በማሥቱ ነበር እስካሁን በዘማቾች የዕርዳታ ገንዘብ መዋጮ ከአዲስ አበባ የተነሡት። ከእነታረቀኝ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ቢሆንም «አባታችንን የምናገኘው አብረን ባንድነት ነው። እስካሁን ከርመን አንድ ሁለት ቀን መቻል ያቅተናል? የለም እናንተም የልጆቹን ሕይወት ያተረፋችሁለት ልጆቹ ማለት ናችሁና ደስታው የበለጠ እጥፍ ድርብ ይሆናል። በሕይወት ካላገኘውም ብቻችንን ከምንኰራመት ታጥኑናላችሁ» በማለት ከሚሴ ላይ ጠበቋቸው። ከዚያም አራቱ አውራ ጐዳንውን ይዘው አልፊ መኪና እየለመኑ የቀረውን በእግራቸው የፓዘው ቆሬ ከእነ ሙሔ መንደር ሲደርሱ ጊዜው ለዓይን ያዝ አድርጎ ነበር። በግድግዳው ቀዳዳዎች በኩል የእሳት ጭላንጭል ይታያል።

«ኧረ ሰው አለ?» አለች ዘይኒኤ እየተፋጠነች በመራመድ።

«እህህህ!» ካሣሁን በመሳል ጕሮሮውን እንደ መጠራረግ አደረገ። «ከዚህ ቤት! ከዚህ ቤት ሰው የለም?»

«ማነው?» የሚል መልስ ከማስማቱ ወዲያው በሩን ከፍቶ ሙሔ ብቅ አለ። የእሳቱ ውጋጋን ፊት - ለፊት በቆመችው ዘይኔ ላይ አርፎ ቀይ ብርሃን አለበሳት። ድንገት ምትሐት እየዳየ ሙሔ ደርቆ ቆመ። «አባዬ! አባዬ!» ተጠመጠመችበት።

ሙሔ ለብዙ ደቂቃዎች ፈዝዞ ከቆየ በኋላ ሁለት ክድንዋን በእጁ ጨብጦ፥ «ዘይኔ! ዘይኔ!» ሲል በለሰለሰ ድምፅ ተጣራ። ከዚያም አንድ ጊዜ ዘይኔን አንድ ጊዜ ካሣሁንን ሌላ ጊዜ እነታረቀኝ እያፈራረቀ ተመለከታቸው። «በውኔ ነው በሕልሜ? ወይም የአምላክ ነገር! እሱ ምን ይሳነዋል። ግና ሰው ወና ቤት ውስጥ ሲሆን ሌላ ሥራ የለውምና ከመምጣታችሁ በፊት ጥቂት ዕንቅልፍ ሸለብ አድርጎሽ ስለነበር አሁንም ጧት ስነቃ የማላገኘው ቅዠት ይመስለኛል።»

ሁሉም በየተራ የደረሰባቸውን ታሪክ ሲያወጉ አነጉ። ጧት ከበደ ለደስ ደስ አንድዋ ፍየል ካልታረደች በማለት ድርቅ አለ። «አይሆንም አትበልኝ አይዋ ሙሔ! የኔም ደስታ ነው። እናንተ ግን ለዛሬ እንግዶች ናችሁ። አርፋችሁ ተቀመጡ። ከልካይ አዛዥ ማን አረጋችሁና! ደሞስ እኛ እርጉም ሴትዮ መምጣታቸው አይቀርምና ከሚወስዱት እኛው ብናስብበት አይሻልም? በይህ ላይ ሰሞኑን ቅበላ ነው» ሲል ለገላጋይ አቃተ።

ታረቀኝና ማርቆስ ወደ ጣቢአይቸው ለመመለስ ሲነሡ። የእነርሱም ፍላጐት ካልተፈጸመ ሁለተኛ እግራቸው የቆሬን መንደር እንደማይረግጥ በመዛት፥ ለስንቅ ከቋጠሩዋት አሥር ብር ተኩ። የገጠርን በተለይ ሞት ተፍቶት የተመለሰውን የወሎ ባተሌ ኑሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በዕርቃኑ ተመለከቱት። ችግር እርስ በርሱ እንዲተሳሰብ ጭንቅ እንዲተሳሰር ያደርገውን የጭንቁን የገበሬ ቤተሰብና መንደርተኛ ፍቅር ለመጀመሪያ ጊዜ ቀመሱት። ደስታ ከልብ፥ ፍቅር ከልብ፥ አዘኔታ ከልብ፥ ተንኰል ስግብግብነት ግብዝነት ያላቆሸሸው ጥሩ የሕይወት ምንጭ ምን ያህል ውብ ነው? ማረካቸው። በሥውር እጁ አቅፎ ያዛቸው። ከተማ እየገቡ በካቲካላ ይሰክራሉ፥ ውሽሞች አብጅተዋል። ብለው አንዳንድ ዘማቾች ሐሜት እስኪፈጥሩባቸው ድረስ የጣቢያው ስሜት ሲቀፋቸውና አጋጣሚ ሲያገኙ የሚኰበልሉት ወደ ቆሬ ሆነ። ከካሣሁንና ከዘይኔ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ታሪክ አስቀድመው የነገሩት የጣቢያው ኃላፊም እምብዛም አይቃወማቸውም። ሥነ ሥርዓትን በሚመለከትና የታዘዙትን በመፈጸም ረገድ ከአብዛኞቹ ዘማቾች የተሻሉ እንደሆኑ ተገንዝቦ ነበር።

ማክሰኞ ቀን ጧት የገጠሩ መሬት አዋጅ የከሚሴን ወረዳ ዘመቻ ጣቢያ ያተራመሰው፥ የዕለቱን እንቅስቃሴ ሳይጀመር ነበር። ግማሹ ከተሸፈነበት ብርድ ልርድ ልብስ አልወጣም። ትጉህ ቢጤው ፊቱን ተጣጥቦ ጨርሶ መኝታውን ያሰናዳል። ሌላው ከውጭ ገና ያልሞቀች ፀሐይ ይሞቃል። እንደ ተጋደመ ካርታ የሚጫወትም አለ ፡

በዚህ ሁሉ መካከል ሰዓት፥ እንደ ዋዛ ይታይና ራዲዮ ይከፈታል። እንደ ቀድሞው ነጋሪት የተቁጠረው «ማርሽ›. ሲሰማ ሁሉም ጆሮውን ቀና ቀና ያደርጋል። ድንጋጤ አይሉት ደስታ፥ ለቅጽበት ክው! ማለት። ከዚያም አዋጁ ተነግሮ ሳያልቅ ትርምሱ ወጣ።

ከመሠረቱ የመሬትም ሆነ ሌላ ከፍተኛ አዋጅ በሚወጣበት ጊዜ የጣቢያው ኃላፊ በሚያወጣው ድልድል የገጠሬውን ሕዝብ ለማስረዳት መሠማራት እንዳለባቸው ተነግሮአቸው ነበር። አሁን ግን ስለ

መመሪያ ደንታ አልነበራቸውም። ስሜታቸው የመመሪያውን ልጓም የበጠሰ ነበር። አብዛኞቹ ሜዳ አልበቃ እንዳለው ወይፈን ወዲኢህ እየዘለሉ መጨፈር ያዙ። የስሜት ግጥም ወዲያው ተዘረፈ።

ወይ ጉልተኛ ጉድ ፈላባችሁ፥

መሬት ላራሹ፥ ታወጀባቸው።

ማረሻህን አንሣ ያገሬ ገበሬ፣

ያንተው ሆኖልሃል የድካምህ ፍሬ።

ለጋራው፥ ለሽንተረሩ፥ ለዛፍ፥ ቅጠሉ ነገሩት። ከፊሎቹ እየጨፈሩ ወደ ከሚሴ አመሩ። ይህንን ትልቅ የገበሬ በዓል በከተማ ለማክበር መሄዳቸው ነበር። የአስተዳደግ ዝንባሌ በአንድ ቀን አይለወጥ። ዘወር ብለው እንባቸውን የዋጡ አንዳንዶችም ነበሩ። እንደ ሌሎቹ «መሬት ላራሹ» እያሉ ሲያስተጋቡ እንደዚህ በአንድ አፍታ ወና የሚያስቀር አልመሰላቸውም ነበር። አንዱ የታወቀ ጋዜጠኛ «ለአንድ ሰው አምስት ስድስት ጋሻ ይበቃዋል። ስለዚህ….» ሲል በሄራልድ ጋዜጣ ላይ የጻፈውን ዓይነት ተጠባብቀው ነበር። - አባባ እማማ፥ ወይስ እኔ ገጠር ገብተን በበሬ አሥር ሄክታር መረኢት አርሰን ልንኖር ነው? አዋጁንም አዋጁን ያወጣውንም ረገሙ።

በዚህ መካከል ታረቀኝና ማርቆስ ልብ ለልብ የተመካከሩ ይመስል፥ «እንሂድ እንጂ? ምን እንጠብቃለን» ተባብለው ወደ ቆሬ አቀኑ።

«አብዬ ሙሒሀ ወሬውን ሰማችሁ?» እንደ አባት ያዩት እንደ አጐት ይጠሩት ጀምረው ነበር።

«የምን ወሬ? እናንተ ልጆች ደግሞ ነገር አያልቅባችሁ። ደሞ ምንድን ነው? ይልቅስ አረፍ በሉ። በበጋ ጠሐይ ነው የመጣችሁት።»

«እንግዲያውስ ለብቻዎ አንነግርዎትም።»

«የምታረዱኝ ነገር ካለ፥ ከዚህ ለተረፉልኝ በስተቀር ለቀረው እርሜን አውጥቻለሁ። አታስቡ።» ሙሔ ፊቱን በመዳፉ ዳሰሰ። «እንዲያው ለነገራችሁ እናንተ የከተማ ልጆች ያገር ወግ አታውቁም። ባሁኑ ሰዓት ይረዳል አሏችሁ?» የትካዜ ፈገግታ አሳየ።

«መርዶ አይደለም። የደስ ደስ ወሬ ነው።»

«ታዲያ ንገሩኛ!»

«እነካሣሁንስ? ደስታችንን ለብቻቸው አናደርገውም። ደስታ የሚያምረው ባንድነት ሲጋሩት ነው ብለው እኛን ሳይዙ ብቻችንን አንመጣም እንዳሉት ሁሉ፥ እኛም የደስ ደሱን ለብቻዎ አንነግርዎትም።» ታረቀኝ የቀልድ መኰሳተር አሳየ።

«ማር በአፋችሁ የሚንጠባጠብ ልጆች ጀሃነምስ ውረድ ብትሉ እናንተን ማን እምቢ ይላል።»

ከበደ፥ ቢልልኝ፥ ያይኔ አበባ አሮጊቷ ሳይቀሩ ከያሉበት እየተጠሩ ከግራሩ ዛፍ ሥር ተሰበሰቡ።

«አሁን በጠራራ ፀሐይ የመጣነው፥ ደስታችሁን ከእናንተ ጋር ለመካፈል፥ ደስታውን ሳትሰሙት እንዳታድሩ ብለን፥ ከአሁን ቀደም ሰምታችሁት የምታውቁት ትልቅ የምሥራቅ ልንነግራችሁ ነው።» ታረቀኝ ሁሉም ቀና ብለው በጕጕት ሲመለከቱት ጕሮሮውን አንድ ነገር ዓጕጠው።

«ካሁን ቀደም ከሰማነውማ ምኑን ምሥራች ይሆን ነበር?» ከበደ ቀልድ ጣል አደረገ።

«መሬት ላራሹ ታውጆአል!»

«ምን?» ሲል ካሣሁን እንደ መዝለል ቃጣው። አዲስ አበባ ብዙ ጊዜ ስለ ተነጋገሩበት በመጠኑ ገብቶታል። ሌሎቹ ግን ሳንዳፍታ ያህል በሚገባ አልተከሰተላቸውም ነበር።

«አዎ! ይህ የምታርሱት መሬት የራሳችሁ ነው። የማንም ጉልተኛና ባላባት አይደለም። አርሳችሁ የምታመርቱት አርብታችሁ የምታደልቡት የድካማችሁ ፍሬ ሁሉ የእናንተው ነው። የደንቡን ግብር ብቻ ለመንግሥት ትከፍላላችሁ። ስለዚህ ዛሬ ትልቅ አዋጅ ተነግሯል። ካሣሁን ነግሮአሁ እንደሆነ፥ እኛ «መሬት ላራሹ» እያልን በየአደባባዩ እየተደበደብን እየተጨፈጨፍን እየታሰርን ስንታገልበት የነበረው ለዚሁ ነበር። ደስ እንደሚላችሁ ደስ ብሎናል። ደስ እንዳለን ደስ ይበላችሁ። ወደ ፊት የአዋጁ ዝርዝር በጽሑፍ ሲደርሰን ደግሞ በሰፊው እንነጋገርበታለን።»

ለጥቂት ጊዜ በየግል ሐሳባቸው አበላሉት።

«እናሳ ምንም አይገኝበትም እንጂ ያች ጠብደል ወይዘሮ ጕተራ ጉስጉሻ፥ ላራግፍ አትልም ማለት ነው?»

«ማንም አይልም።»

«መጥታ ውለዱ ብላ ብታዳፋንስ? አሽከርም መሳሪያም፥ አላት። በምን አቅማችን ነው በጭራሮ የምንመክታት?» ከሕይወትና ከኑሮ ግንዛቤ ከበደ ያነሣው ይህ ጥያቄ እነታረቀኝ በሐሳብ ደረጃ ቀደም ሲል የተወያዩበት ነበር።

«ደፍረው አያደርጉትም እንጂ። ቢሞክሩትማ አዲሱ መንግሥት አለ። እኛም ዘማቾች በቅርብ አለን።» ሥጋት ላይ እንዳይጥላቸው በማለት ታረቀኝ ነገሩን አቃለለው።

የኑሮ ምሬት የሚያውቁት ገበሬዎች ግን አቃልለው አልተመለከቱትም። «እንደይህ እንኳ ማለት የዋህነት ነው። ይኸ ሁሉ የመኳንንት ዘር፥ ይኸ ሁሉ ባላባትና ጉልተኛ፥ ጉልት ርስቱን ተነጥቆ ዝም ብሎ ያያል ማለት ዘበት ነው። አንድ የተበተ ሽፍታ ስንኳ መንግሥት ባለበት አገር ስንት ጥፋት ያደርሳል።»

እነታረቀኝ መመለስ አልቻሉም።

-የከተማ ሰዎች ምን ይፈረድባቸዋል? አንደኛ አላዩት! - በሚል ግምት እነሙሔ በተራቸው ነገሩን ያቃለሉት መሰሉ። «ግዴለም ለሁሉም ሲደርስ እንደርስበታለን።»

«ለመሆኑ የእናንተን ማሰሮ ሲደፉ የነበሩት ወይዘሮ ማን ይባላሉ?» ሲል ማርቆስ ጨወታውን ለመለወጥ ያህል ጠየቀ።

«እረግ ማን ነበር ስማቸው እባክህ? ሽምግልናውም የኑሮ ውጣ ውረዱም ነገር እያስረሳኝ ጠፋኝ ዘ - ዘ - ዘር» ሙሔ ወደ ከበደ ተመለከተ፡፡ «ዘርፉ ነው?»

«ዘርፈሽዋል የአባታቸው ስም ግን እኔም አላስታውሰውም፡፡ ግን እውነተኛ ዘራፊ ናቸው፡፡» ከበደ በጥርሱ ያገኛቸው ይመስል ከንፈሩን ነከሰ፡፡

አእምሮው ፈጣን የሆነው ማርቆስ ድንገት ሐሳብ መጣበት፡፡

«ወፍራም ናቸው?»

«የእኔ ክድን የማይሞላቸው ዝርጥጥ እንጂ!» ከበደ ልኩን ለማሳየት እጁን ዘረጋ፡፡ ታረቀኝና ማርቆስ እርስ በርሳቸው ተያዩ፡፡

«ታዲያ አንቺ የነበርሽባቸው ሴቶዮ አይደሉም? እንዴት አላወቅሻቸውም?» ዘይኔ ተጠየቀች፡፡ በምን አባቷ ታውቃለች? ከመንደር ገብተው መልካቸውን አላየች፡፡

«ወቸው ጉድ! የሱ ነገር መምጫው መሄጃው አይታወቅ፡፡ ደሞ አዙሮ አዙሮ ከሳቸው ቤት ጣለሽ? ወቸው ጉድ! ብቻ ለሁሉም ፊቱን መመለሱ»፡፡ ሙሔ አማተበ፡፡ «በይህ ላይ ይሄ መሬት የኛው የራሳችን ከሆነም ምስጋና ሲያንሰው ነው፡፡» ተነሥቶ መሬቱን ሳመ፡፡ ከበደ፥ ቢልልኝ ተከተሉት፡፡

«የእኛው መሬት!»

«ለዚህም ካበቃን!»

ታረቀኝና ማርቆስ ወደ ከሚሴ ተመልሰው ዘመቻ ጣቢያ ከመግባታቸው በፊት ኮካ ለመጉንጨት ወደ ቡና ቤት ጐራ አሉ፡፡ «እኛን ምሰሉ» በሚል ፌዝ የተቀበላቸው ገበየሁ ነበር፡፡ ከእርሱ ጋር በአንዱ ጠረጴዛ ዙሪያ አራት ዘማቾች ተቀምጠዋል፡፡ የቢራ ጠርሙስ ተደርድሯል፡፡ በሞቅታ የተሟሟቀ ወሬ ይዘው ነበር፡፡

«ምን እግር ጣለህ? ከጓደኛህ ከቦጋለ ጋር እንዳትዘምቱ ስትል ሰንብተህ አሁን ሐሳብህን ቀይረህ መዝመት ነው?» ሲል ማርቆስ በአጸፋ ፌዝ ጠየቀው፡፡ ለብቻቸው ከሌላ ጠረጴዛ ተቀመጡ፡፡

«ልጉበኛችሁ ብመጣ ምን ነውር አለበት?» ገበየሁ ጥርሱን የተገሸለጠ በቆሎ አስመሰለው፡፡

«ጧት አዋጅ ሰምተህ፥ የአባትክን መሬት ላለማስነካት ከሰዓት በኋላ ከተፍ አልካታ! ለመሆኑ ስንት ጋሻ ነው?» ታረቀኝ በበኩሉ ጥርሱን አገጠጠበት፡፡

«እናንተን ምንም የሚያገባችሁ የለም፡፡»

«አንተም ሆንክ አባትህ አርፋችሁ እስከ ተቀመጣችሁ ድረስ አዎ!....ግን» ታረቀኝ በማስጠንቀቅ ጣቱን ቀሰረ፡፡

«ማነህና ነው አንተ ማስጠንቀቂያ ሰጪ የሆንከው? ቆርማዳ ችጋራም፡፡» ገበየሁ ከወንበሩ ለመነሳት ቃጣው፡፡

«በክት - አፍክን ዝጋ!» ታረቀኝ ከተቀመጠበት ተፈናጥሮ ቆመ፡፡

«እኔ ነኝ በክት?» በማለት ገበየሁም አፈፍ ብሎ ተነሣ።

አንዱ በሌላው ላይ ቡጢ ከማሳረፉ በፊት ለያዩዋቸው።

ሲወጡ «ዋጋህን ታገኛለህ!» ሲል ታረቀኝ ዞር ብሎ ሌባ ጣቱ አወዛወዘ።

«ዋአውን ማን እንደሚያገኝ ትደርስበታለህ» የሚል መልስ ተከተለው።

## ፲

«የመሬት ላራሹ ተቃዋሚዎች አጸፋ መልስ እንደ አዋጁ በድንገት ባንዳፍታ፥ አልፈነዳም። መጀመሪያ በአሉባልታ ወሬ ማወናበድ ነበር። ይህ በዘማቾች ጥረትና ከመላ ጐደል ትክክለኛው ዜና እየተዳረሰ በመሄዱ ሲከሽፍ፥ ዛቻና ማስፈራራት ተከተለ። «የጥንቱን የጧቱን ደንብ መፈጸም ነው የሚሻለው። የማንን መሬት ማን ይነጥቃል! ለአራሽ የሚበጀው አዋጅ የሚባለውን ነገር ረስቶ ከባላባት፥ ጋር ውስጥ ውስጡን መስማማት ነው። በየጠጅ ቤቱ በየቡና ቤቱ፥ በየአደባባዩ፥ በየሠፈሩ፥ እንደ ዋዛ ጣል እየተደረገ እየተቀባበለ፥ ከከተማ ወደ ገጠር ዘለቀ። የስልሳዎቹ የሞት ቅጣት ሲረሣሳ፥ በአዋጁ ድንገተኛነት የተፈጠረው ድንጋጤ ሲያልፍ የበልግ አዝመራ፥ ስያስጐመጅ አብዛኛው አስገባሪ ደረቱን ነፍቶ ይደነፋ ጀመር። «የማናባቱ ወንድ ነው! እስቲ እንተያያለን!» ብዙ ያየው የወሎ ገበሬ እሺም እምቢም ሳይል ነገሩን በሆዱ አምቆ ጠበቀ። በመጨረሻም አንዳንዱ ቀንደኛ ፊውዳል ጥቂት ራሱን እየሆነ ጫካ ገባ።

-እናንተ ደጃማች እገሌ እኮ ሸፈተ አሉ!

-ብዙ ሰው አለው?

-መዓት ነው እንጂ። ሠራዊቱ የያዘው መሣሪያ መሳሪያ መሰላችሁ።

ግልገሉ ፊውዳል እየተደፋፈረና ወይም ከማን አንሼ እያለ ተከተለ። የቀንደኛው ፊውዳል አጀብ እየበረከተ ሄደ። ልቡ ሲርበተበትና ኃይል ሲሰማው ከአንድ ሰዋራ ሥፍራ ሆኖ የቀድሞ ገባሮቹ እንደ ጥንቱ፥ እንደ ጧቱ እህልና ከብት ይዘው እንዲመጡለት ሰው ከመላክ አልፎ፥ በየገጠሩ መንደር እየዞረ ያስገድድና ይዘርፍ ገባ። እምቢ ያለው እየተጣለ ተገረፈ። የገበሬ ማኅበራት መሪ የተፈለገ ተገደለ። እየታሠረ ተወሰደ።

ለዚህ መከላከያ ተብሎ በአዋጁ መሠረት የዘማቾች አንዱ ተግባር ገበሬዎችን በማኅበር ማደራጀት ነበር። ነገር ግን ፊውዳሎቹ መሣሪያ አንሥተው መሸፈት በጀመሩበት ወቅት የገበሬ ማኅበራት የተጠናከሩ አልነበሩም። በዚህ ላይ መሣሪያ የላቸውም። በአንዳንድ ሥፍራ በገጠር የሚገኙትን የመሬት ከበርቴዎች መሣሪያ እየነጠቁ ገበሬዎችን ለማስታጠቅ ሙከራ ቢደረግም በቂ አልነበረም። የተደበቀው፥ የተቀበረው ሁሉ የት ተገኝቶ? በብዙ ሥፍራዎች ይህ ስንኳ እንዳይደረግ ተከለከለ። በዚህ ሁሉ መካከል በመፍራት በመታለል፥ ብዙ ገበሬ፥ ፊውዳሎቹን በመከተል ሽፍትነት ገባ።

አዲስ አበባ መሽጎ የነበረው የመሬት ከበርቴ ይህ ሁሉ ወሬ የተጋነነ ሲደርስ ልቡ አበጠ። «የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ፥ ልቡ ያበጠበት፥ እንዋጋ ብሎ አንበሳን ላከበት» የሚለው ቀረርቶ አንድ

ጊዜ ክፉኛ ያስደነግጠው የነበረውን ያህል አሁን ይንቀው ገባ። በየቪላው፥ በየእልፍኙ ዱለታውን ተያያዘው።

አንዱ ዋና የመዶለቻ ሥፍራ ወይዘሮ ሸዋዬ ግቢ ነበር። በዛፍ ጥቅጥቅ ብሎ የተጋረደው የግቢው ስፋት ጥይት ቢተኰስ ከውጭ አያሰማም። ቤቱ ብቻውን በሁለት መቶ ሃምሳ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ነው። ቀንም ሆነ ማታ ሹክል ብሎ ለመግባትና ለመውጣት ሠፈሩ ሠዋራ ነው።

ወይዘሮ ሸዋዬ ጉዳዩን ሥራዬ ብለው የያዙት ንጉሡ፣ የሰጡዋቸው ማርቸዲስ አውቶሞቢል ከመውሰድዋ በፊት፤ አድአ አሥራ ስድስት ጋሻ የጤፍ መሬት፥ ሲዳሞ አሥር ጋሻ የቡና መሬት፥ ሐረር ሃያ ጋሻ የጫትና ጭሰኛ የሰፈረበት መሬት ከማጣቸው በፊት የቀድሞዎቹ ባለሥልጣኖች በሞት በተቀጡ ማግሥት ነበር።

ወይዘሮ ሸዋዬ ለውጡ የጣላቸውን መሠሎቻቸውን ሲያነሡ፥ እንደ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በማመናጨቅ አይደለም። በዘዴ በፕሮግራም ነው። ብዙ ሰው ያውቃሉ። ብሱ ሰው ያውቃቸዋል። በየቀኑ የተወሰኑ ሰዎች በቴሌፎን ወይም ቤታቸው ድረስ በመሄድ ያነጋገራሉ። «በዚህ ክፉ ቀን መቼም እንጠያይቅ እንጂ። ተጠፋፋንኮ» በማለት እቤታቸው መጥተው እንዲያጫውቷቸው ይጠይቃሉ። «እሺ መቼ? ዛሬ? ነገ? አደራ እጠብቃችኂለሁ» ይላሉ። ቤታቸው ምንጊዜም ሙሉ ነውና የሚመጡትን ሰዎች የማያቋርጥ ድግስ ይጠብቃቸዋል። ሁልጊዜ ዶሮና ሙክት ማረድ፥ ብልት ማቅረብ ውስኪ፥ መክፈት ጠጅ ማንቆርቆር ነው። ከድግሱ ጋር የሚቀርብ ሌላም ነገር አለ።

ቀይ ወጥ - አልጫ፥ - ክትፎ - ጮማ - ፍትፍት - ጥብስ - «ስሞት ስቀበርላችሁ» እየተባለ፥ በውስኪና በጠጅ ለሚፈልግም በማር፥ በኮሶ፥ በቡና፥ በወተት አረቄ እየተወራረደ ሆድ ከበድ ጭንቅላት ቀለል ሲል አዝማሪ አደግድጎ፥ እጅ ነሥቶ ይቆማል - ማሲንቆውን እየቃኘ። ከዚያም ድምፅና ማሲንቆ ሰምና ወርቅ ሆነው ይንቆረቆራሉ።

በዘለሰኛ ቅኝት።

የጌታ ልጅ ተዋርዶ፥

የጨዋ ልጅ ተዋርዶ፥

እንጨት ሰበራ ቆላ ወርዶ፥

ይገፋዋል ቀኑን፥

ጊዜ ያመጣውን።

የጌታ ልጅ ተዋርዶ፥

የጨዋ ልጅ ተዋርዶ፥

መች ይቀራል እንዲህ ሆኖ፥

ከተነሣ ጨክኖ።

በባቲ ቅኝት፡፡

የጐበዙትማ የቆረጡትማ፥

ዓባይን አለፉ፥ ተከዜን አለፉ፥

መረብን አለፉ፥ ጓንግን ተሻገሩ፥

መሬት አይነካም፥

ክብሬ አይደፈርም፥

ሲሉ እየፎከሩ፡፡

አስታማሚ አጥቼ፥

አንድ እግሬን አሞኝ፥

አዋቂ ብጠይቅ እንዲያማክረኝ፥

ፍቱን መድኃኒቱ መሄድን ነው አለኝ፡፡

በአንቺ ሆዬ ምነው ቅኝት፦

እኛው ነን እኛው ነን፥

አሁምን እኛው ነን፥

ጨዋዎች አንወድቅም እናቸንፋለን፡፡

ሆድ ከብዶ ጭንቅላት ሲቀልል ያ ሁሉ መሬት ያ ሁሉ ሥልጣንና ክብር ገሃድ ሆኖ ከፊት ላይ ይደቀናል፡፡ ይህንን መሳይ ምግብና መጠጥስ እያደር ሊቀር አይደል? ስሜት ይቀሰቅሳል፡፡ ለአዝማሪው ግጥም መንገር ይጀመራል፡፡

የአንበሳ ልጅ ታሞ፥

የአንበሳ ልጅ ታሞ፥

ፍየል ጐበኘችው፥

ፍየል ጐበኘችው፥

ምነው የኋላውን አዙራ ባየችው፥ በልልኝ እባክህ፡፡

ምነው የኋላውን አዙራ ባየችው፡፡

አንዳንዱን ቁጭት ያወራጨዋል፡፡ ሌላው ፉከራ ይቃጣዋል፡፡ ተፈላጊው ስሜት መፈጠሩን ወይዘሮ ሸዋዬ ሲገነዘቡ፥ ዋናውን ድግስ ያቀርባሉ፡፡

«እህ? ምን እያላችሁ ነው? ደርግ ተብዬው የሚፈነጭበትን አደባባይ እናንተ የምትገዙት አትመስሉም? ሌላ ክፍል ግቡና አረፍ በሉ» ይሉና እየመሩ ይወስዷቸዋል። ከዚያም የጥሞና ምክክሩ ይቀጥላል።

«እውነትምኮ ሞተናል ወይዘሮ ሸዋዬ! በቁማችን ሞተናል። ምን ቀረን?» በንዴት ራስ ይነቀነቃል።

ወይዘሮ ሸዋዬ ረጋ ብለው ይመግባሉ። «ታዲያ ከተማ ሆኖ ወይኔ! ማለቱ፥ ከተማ ሆኖ መደንፋቱ ፋይዳ የለው!»

«የት እንድረስ?»

«ምነው ሸዋ! አገራችን ኢትዮጵያ ሰፊ ናት። ጫካውን ሸንተረሩን ጋራውን፥ መቶ ሃያ ደርግ አልያዘው። ምነው ብርሃነ መስቀል በላስታ፥ እነመነሻ፥ እነነጋ፥ በአርማጭሆና በወልቃይት፥ ጠገዴ፥ እነ ፊታውራሪ በላይ ዘለሰው በአምባሰል፤ በወረሂመኑን፥ እነስሜነህ በጐጃም አገሩን ቀጥ አርገው ይዘው የለም? በውጭ አገርም ልዑል ጌታዬና ሌሎችም ነገሩን ያስተባብራሉ። ሂዶ የሚጠጋቸውንም በሚገባ ይቀበላሉ። ያንን ያህል ሠራዊት ይዞ የመጣው ጣሊያንን ስንኳ ጃንሆይ ከአምስት ዓመት ስደት በኋላ በድል አድራጊነት ተመልሰውበት የለም? ቁም እንገሩ ልባም ከመሆን ላይ ነው።»

በመስማማት ጭንቅላት ይወዛወዛል። ከዚያም ዕቅድ ማውጣት ይቀጥላል።

መሣሪያ ለሚያስፈልገው መሣሪያ፥ መጓጓዣ፥ ማን የት እንደሚገኝ ከሚፈልጉበት ሥፍራ እንዴት እንደሚደርሱ ወይዘሮ ሸዋዬ አብዛኛውን ዝግጅት ያጠናቅቁላቸዋል።

አንድ ቀን ለወይዘሮ ዘርፈሽዋልም ተመሳሳይ ጥሪ አደረጉላቸው። ከዚያ በፊት አውቶሞቢላቸው ከተወሰደች በኋላ የዘለቃ ወዳጅም ከሥራ መባረሩ የወሬ ወሬ ከተሰማ በኋላ ሁለት ሦስት ጊዜ ያህል ሰላምታ ለመለዋወጥ ያህል ቴሌፎን ደውለውላቸው ነበር። እምብዛም ሆድ ለሆድ አልተግባቡም። «ኧረ እንዲያው አንቺ ቤቴ ምነው እንዲህ አስጠላሽ? ኧረ ዙሮ ዙሮ ከወገን ነው» አሉ ወይዘሮ ሸዋዬ ስልክ ደውለው።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አሽሙር ቢጤ መሆኑ ተሰማቸው። ትንሽ እንደ መብሸቅ አሉ።

«ጊዜው አላደርስኝ፥ አላመቸኝ እያለ እኮ ነው።»

«እሱስ ነው፥ እሱስ ነው፤ ግና ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም ተብሎ የለ? በሞቴ፥ እንደ ምንም ብለሽ ሰሞኑን ነዪ እስቲ። ብዙ የማጫውትሽ አለ።»

«እስቲ ሲያመቸኝ ሰሞኑን ብቅ ብዬ እጠይቅሻለሁ።»

«መቼ? ዛሬ? ከነገ ወዲያ? ቍርጥ አርገሽ ተናገሪ። ያያሌው አጥንት ዛሬስ አለቅሽም።»

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተጨንቀው ጥቂት አሰቡ። «ዘለቃ ነች እንግዲህ መኪና የያዘች። እንደ ሆነላት እንጂ፥ እኔማ - እኔማ....» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሳያስቡ የጀመሩትን ንግግር አቋርጠው ተውት።

«እሱማ በሁላችን ነው የደረሰው፡፡ ታዲያ ይህ ያቀራርበን እንጂ ያራርቀን? ያንቺው የእኔ ነው፤ የእኔውም የአንቺው ነው፤ መኪና እልክልሻለሁ፡፡ ነገ ማታ ሰውዬሽንም ይዘሽው ብትመጪ መልካም ነው፡፡ ከሰው ጋር ይተዋወቃል፡፡ በዪ ደህና ዋዪልኝ!» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እሺም፥ እምቢም ለማለት ሐሳባቸው ሲዋልል ወይዘሮ ሽዋዬ ተሰናብተው ቴሌፎኑ ተዘጋ፡፡

## ፬

ማናዬ አንድ ምሽት ከወይዘሮ ሽዋዬ ቤት ማምሽቱ ብቻ ለመሸፈት አበቃው፡፡ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሐረግ የሚመዙትን ያንን የሚያክሉ ቅምጥል ወይዘሮ «አፈር ስበላ» እያሉ በአክብሮት ሲጋብዝዙት፥ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት እየተቁጠበ የሄደውን ውስኪ እየተለመነ ሲከነብለው የተሸማቀቀ ሰውነቱ የተፍታታ መስሎ ተሰማው፡፡ ገበታ ተነሥቶ ሁሉም ከፎቴ ላይ ወደ ኋላ ተለጥጦ የተወጠረ ሆዱን በእጁ እየዳበሰ በመጠጥ መዝናናት ሲጀምር አዝማሪው ያለፉ ሰዎች ስም እያነሣ፥ እየጠራ፥ ትዝታና ስሜት መቀስቀሱን ቀጠለ፡፡ እንደ ሌሎቹ በተራው «ማናዬ ይሉታል ማናየው ልቡን፥ እንደ ከሰል ወተት የሸፈተውን» ተብሎ ሲገጠምለት ተጀነነ፡፡ ተኵራራ፡፡ ወይዘሮ ሽዋዬን ቤት ለምን ብዙ ሰው እንደሚያዘወትረው ቀደም ሲል በጭምጭምታ ሰምተው አሁን ያረጋገጡት ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሰው አያያዝ ምሳሌያቸው ወዲያው እየገባቸው ሄደ፡፡ «ሰውን ይልቅ ማባበል በአሞሌ መወዳጀት ከማስቆጣት ከማስበርገግ ይልቅ ማባበል በአሞሌ ጨው እንደሚሳብ በሬ» ብለዋቸው ነበር፡፡ ይህንን በሥራ ላይ ውሎ ሲያዩት ምሳሌው ወዲያው በመከተል በአድናቆትና በቁልምጫ ተመለከቱት፡፡ በአስተያየታቸው እንደ አበባ የሚረግፍባቸው አስመስሎት - ቱፍ! ቱፍ! ከዓይን ያውጣህ - ማለት ነበር የቀራቸው፡፡ ከሞቅታው ጋር የበለጠ ተደፋፍሮ ያለማፈር በዓይኑ ጠቀሳቸው፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በአዲስ ሁናቴው ሳቃቸውን ሊለቁት ምንም አልቀራቸው ነበር፡፡ እንደ ሌሎቹ የራሱንም ግጥም ለአዝማሪው ነገረ፡፡ «የማናዬ ልቡ ቅቤ ያሸፈተው ከቶ እንዲህ አይቀርም ወጥቶ ካልተቀባው» ሲል ተጨበጨበለት፡፡

ወይዘሮ ሽዋዬ፥ «ኦሆሆ እናንተ ጉደኞች ናችሁ!» እያሉ በማዳነቅ ሰዎቹን ወደ ሌላው ክፍል ሲወስዷቸው «እኔም ልምጣ?» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጠየቁ፥ በማመንታት፡፡

«እስቲ ቆዪ አንቺ፡፡ መጀመሪያ ወንዶቹ እርስ በርሳቸው ይጨዋወቱ፡፡»

ከሰዓቱ ዕላፊ በፊት ቤት እንደ ገቡ፥ ማናዬ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊልም እንዳየ ልጅ ተንጰረጰረ፡፡ «ይህ ሁሉ ነገር መኖሩንኮ እኔ አላውቅም ነበር፡፡ እንዲሁ በከንቱ እኮ ነው አንገታችንን አቀርቅረን ያለነው፡፡»

«አሁን እረፍ እስቲ የኔ ጉበዝ» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፤ እንደ ዓመት በዓል ልብስ በቁጠባ በተያዘው በማዳም ሮሽ ሽቶ የታወደ ገላቸውን እያስጠጉ፡፡

በሕልሙም በውኑም ገሎ ሲገባ፥ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ሲገባ፥ የደን መሬቱን ተለምኖ በሩብ ሚሊዮን ብር ሲሸጥ ከወይዘሮ ሽዋዬ አሥር ዕጥፍ የበለጠ እየደገሰ ሲጋበዝ «ማናየው ልቡን ያሸፈተውን» እየተባለ በየጠጅ ቤቱ ሲዘፈንለት እያየ ነጋ፡፡

በሁለተኛው ጊዜ የሄደው ብቻውን ነበር፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የመኪና ችግር ቢያነሡ ለመምጣት ጕጕት ያደረባቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ የፈለጉ ይመስል፥ ወይዘሮ ሽዋዬ «የኔዋ ጋራዥ

ገብታለች። አንዳንድ ጊዜ ያችን ዘዋሪ ልጅሽን እዘዣት እንጂ! መውለድ ለመቼ ነው» አሏቸው። ዘለቃ ደግሞ ስንኳ ቅዳሜና እሑድ በአዘቦቱም ከምሽቱ ከአራት ከአምስት ሰዓት በፊት አትገባም።

«እንግዲያው አንተው ሂድ መኪና ተከራይተህ» አሉት ማናዬን ሰይቸንቶ ብለው መጥራቱን ጠልተውት።

«ለምን አብረን አንሄድም? ስንለመስ መኪና አናጣም።»

«እኔ ምን እሠራለሁ? ጭውውቱ የወንዶች ነው» ሲሉ መለሱ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል። «የወንዶች» የሚለው ቃል «ጀግኖች» የሚለውን ቅላጼ እየሰጡ።

ሲመለስ አሁንም በማዳም ሮሽ ሽቶ ተቀበሉት። «ምን ይመስልሻል?» ሲል ጠየቃቸው። ልብሱን ሲያወላልቅ በሰፊው እያገሳ።

«ምኑ?» እንደማያውቁ መሰሉ።

«ልቤ ተነሥቷል። እንደ ሌሎቹ ለመውጣት አስቤአለሁ።» የድል አጥቢያ አርበኛ መባሉ ለከፍተኛ ሥልጣንና ማዕረግ እንደማይበጅ ተሰምቶታል።

«እኔስ? እኔ ከዚህ ብቻዬን ልቀር ወትሮስ ሴት ልጅ አብራ ትዘምት የለ?» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በማልቀስ ዓይነት ድምፃቸውን አስረቀረቁት። አዎ! ወይዘሮ ሸዋዬ እንደሚያደርጉት ወንድን ልጅ ማባበልና ማበረታታት ነው የሚያስፈልገው። በፍቅር አስመስሎ ሲያለቅሱለትም የበለጠ ብርታት ይሰማዋል። ወይዘሮ ሸዋዬ ያ - ሁሉ ጉረምሳ ሲንበረከክላቸው የኖረው ያለ ምክንያት አይደለም።

«አንቺ አርፈሽ ተቀመጪ፤ ይህንን ሰውነት ይዘሽ ጫካ ለጫካ ልትንከራች? አትችዪውም። ደሞ ለአጭር ጊዜ ነው፥ እንመጣበት የለ? ደግሞም ከአወቅሽበት እንደ ወይዘሮ ሸዋዬ ከዚህ ሆነሽ ብዙ መሥራት ትችያለሽ። አሁን እርሱን እንርሳውና እኔን ያሳሰበኝ....»

«ምን የሚያሳስብ ነገር አጋጠመህ?» አቋርጠው ጠየቁት።

«ከእነማን ጋር መቀላቀል እንደሚሻለኝ አላወቅሁትም። መቼም እጣ ነፍሴን ጫካ ለጫካ አልነራተትም። ወይዘሮ ሸዋዬ የሚዘረዝሯቸውን ሰዎች አንዳቸውንም አላውቃቸውም። ከደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ጋር ስንኳ በመልክ እንተዋወቃለን። ስለ ሰበታው መሬታቸው መሥሪያ ቤት ሲመላለሱ። ግን እንደ ዕድል ሆኖ ሳንጣጣም ነበር የተለያየነው። እርግጥ ወይዘሮ ሸዋዬ የመተዋወቅያና የአደራ ደብዳቤ እንደሚልኩ ተረድቻለሁ። ግን ቢሆንም....» ማናዬ አንጠልጥሎ ተወው።

«እሱስ እውነትህን ነው። ሰው ባገሩ ሰው በሚያውቀው ወገኑ፥ በዘመድ አዝማዱ መሃል መሆኑ ነው የሚበጀው።»

«እኔ ታዲያ ተወልጄ ያደግሁት ከዚሁ ከአዲስ አበባ ኡራኤል። ገጠር የማውቀው የምጠይቀው ዘመድ የለኝ።»

ከትራሱ ላይ በክንዳቸው ተጋድመው ፒጃማውን ሲለብሱ እየተመለከቱት ጥቂቷ ያሰቡ መሰሉ። «የለም ከፊታውራሪ በላይ ዘለለው ዘንድ አትሄድም? ከእኔ ጋር የአንድ አያት ልጆች ነን። እንደ ወንድሙ ይይዝሃል።»

«ወሎ?»

«ከሁሉም እሱው ነው የሚሻልህ። እንዲህ አይምሰልህ የወጣለት ጉበዝ ነው። መሬታችን እንዴት እንደሆነ በዚያው ትጉበኘዋለህ። እነዚያን መናጢ ገበሬዎች ሁሉ ከአሁኑ አንነሣልኝ!»

«እና፣ ወደ ወሎ ልሂድ?» ያመናታ ይመስል የማረጋገጫ መስል ፈለገ።

እኔ ደብዳቤ እጥፍለታለሁ። ወንድምህ ነውና እንደኔው ተንከባክበህ ያዝልኝ ብዬ።» ብርድ ልብሱን ገለጡለት።

«መብራቱን አጥፋው እስቲ?»

«ይኸ ሽቶሽ - ይኸ ሽቶሽ!»

የጉዞው ዝግጅት በጥቂት ቀናት ውስጥ ተጠናቀቀ። ብዙም የሚያዝ ነገር አልነበረም። «ዱሩ ቤቴ ያለ ወንድ ልጅ ሽክም ማብዛት የለበትም» ብለዋል ወይዘሮ ሽዋዬ። አንድ የሚነፋ ፍራሽ ከነከረጢቱ ብርድ ልብስ አንድ የበረት ኮዳ፥ አንድ ግልገል ሁለት ሙሉ ካኪ ልብስ ሁለት ጫማ፥ አንድ ባርኔታ፥ ከሩቅ የሚያሳይ መነጽር በቂ ነው ተባለ። በተነፈሰ መጠባበቂያ ጉማ ውስጥ ተደብቀው የሚሄድ አንድ ኮልት ሽጉጥ ወይዘሮ ሽዋዬ ሰጡ። የቀርውን ትልቅ መሣሪያ እዚያው እንደሚያገኝ ተነገረው። «ለዘርፈሽዋል እንደሆን እኔ እያለሁ አታስብ» አሉት ወይዘሮ ሽዋዬ በመጨረሻ ቀን።

እስከ ካራ ቆሬ ድረስ በወይዘሮ ሽዋዬ ቶዮታ ክሩዘር ሄደ። ከእርሱ ጋር ከእነ፥ አሊፋሪስ ጋር የሚቀላቀል ሲሣይ የተባለ ሌላ ሰው ነበር። ከካራ ቆሬ ከተማ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ ብለው ነፋስ እንደሚቀበል ሰው እየተንሸራሸሩና ከባለቤቶች የተነጠቀውን ያንን የተንጣለለ የጤፍ ማሳ መስክ እየተመለከቱ አንድ እኩል ሰዓት እንደ ጠበቁ፥ ከደሴ በኩል የመጣ ሌላ ላንድሮቨር ከአጠገባቸው ቆመ። ተለዋውጠው ተነጋገሩ። ከዚያም የላንድሮቨሩ ነጂ ሰላምታ ተለዋውጠው ተነጋገሩ። ከዚያም በአቅራቢያ የሚያስተውል ሰው አለመኖሩን አረጋግጠው ጓዙ በጥድፊያ ላንድሮቨሩ ተዛወረ። ትቶዮታዋ ወደ አዲስ አበባ ላንድሮቨሩ ወደ ደሴ ፊታቸውን አዞሩ።

ሲሣይ የሆቴል ክፍል ተይዞለት ኮምቦልቻ ሲቀር ማናዬ ወደ ወልድያ ተወስዶ ከወይዘሮ ዘውዲቱ ጠጅ ቤት ማረፊያ ተሰጠው። ባለቤቲቱ በግልስ ባይናገሩትም ምሥጢሩን የሚያውቁ ይመስላሉ። እንደርሱ ያለ እንግዳ ሲቀበሉ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አለመሆኑን በግልጽ ያስታውቃሉ። የሚከራይ ክፍል የላቸውም። እንዲያርፍ የተደረገው ከጠጅ ቤቱ አዳራሽ ጀርባ የራሳቸው መኖሪያ ቤት ከሆነው ቤት በአበባ ምንጣፍ በሐርና በዳንቴል በተሽቆጠቆጠ ክፍል ውስጥ ነበር። ሳይጠይቅ ሳይከፍል ወይዘሮ ዘውዲቱ ራሳቸው ምግቡንም መጠጡንም እያቀረቡለት አድሮ ዋለ። ወጣ ብሎ ከተማውን ለማየት ከጀለና ስለ ጥንቃቄ ወይዘሮ ሽዋዬ የመከሩት ትዝ ብሎት መልሶ ተወው።

ከሰዓት በኋላ ሌላ ባለ ሸራ ላንድሮቨር ግቢው ውስጥ ገብቶ ቆመ። ነጂው ከወይዘሮ ዘውዲቱ መኝታ ክፍል ገብቶ ጥቂት ከቆየ በኋላ ማናዬ ወደ አለበት ክፍል መጣ።

«ጤና ይስጥልኝ!»

«ጤና ይስጥልኝ!»

«ማን ልበል?»

«ማናዬ::›

«ይመር እባላለሁ::» እጁን ዘረጋለት::

ወደ ጠጅ አዳራሽ የሚያስተላልፈው የኋላ በር ተዘግቶ የማናዬ ጓዝ ተጫነ:: ወይዘሮ ዘውዲቱ እንደማያይ፥ እንደማይሰማ የመኝታ ቤታቸውን ገርበብ አድርገው ከቆዩ በኋላ፥ ሞተር ሲነሣ አንገታቸውን ብቅ አድርገው «መሄዳችሁ ነው እንዴ? መቼ ትመለሳላችሁ?» አሉ::

«እሱ እንዳለ!» ሲል ነጂው በፈገግታ መለሰላቸው::

«ኧረ ቶሎ ተመለሱ! እስቲ እሱው ከናንተው ጋር ይሁን::»

እንደገና ወደ ደሴ አግጣጫ ተጕዘው ፓሶ - ማሌ ከመድረሳቸው በፊት ለድርቅ ኮሚሽን የዕርዳታ ማድረሻ እንደ ነገሩ በተደለደለ መንገድ ወደ ቀኝ ታጠፉ:: ማናዬ አንጓው የወላለቀ እስኪመስለው ድረስ ከረጅም ገው - ገርገጭ ገው - ገው - ገርገጭ - ገርገጭ - ገርገጭ በኋላ አንድ የተጫነ ፈረስና አንድ አህያ የያዙ ሰዎች ከተቀመጡበት ደረሱ:: አንደኛው ሰውዬ ጠመንጃ አንግቷል::

«እኔ እስከዚህ ነው የምሸኝዎት:: እነርሱ ደግሞ ከዋናው ሠፈር ያደርሱዎታል» አለ ነጂው፥ ጓዙን እየወረደ በአህያው ላይ ሲጫን::

ከፈረሱ ላይ ወጣ:: ላንድሮቨሩ ተጠመዘዘ:: ሁሉም ነገር እንደ አውቶማቲክ ሰዓት በትክክል መካሄዱ አስገረመው:: ምን ዓይነት መገናኛ ዘዴ ቢኖራቸው ነው? በቴሌፎን? በቴሌግራም ወይስ በደብዳቤ? ጥሩ ዝግጅት ነው:: ግን አዲስ አበባ እየራቀው በሄደ ቍጥር የመጀመሪያ ስሜቱና ድፍረቱም እየራቀው ሄደ:: ይህ ደግሞ ከከተማ ሕይወት ጋር ላለው ግንኙነት የመጨረሻ መናኸሪያው ነው:: ዞር ብሎ ተመለከተ:: ላንድሮቨሩ እየራቀ ይሄዳል:: ፊት ለፊቱ ጀንበር የጠለቀችበት ተራራ እየራቀ ይሄዳል:: ፊት ለፊቱ ጀንበር የተለቀችበት ተራራ አናቱ በጨረር ቀልቶ፥ ወገቡ በጥላ ተጋርዶ በሚያስፈራ ግርማ ሞገስ ቁልቁል የሚመለከት በስተምሥራቅ የሚሌ አፍሳሽ በረሃ ጭጋግ ለብሶ የሚውጥ ጨለማ ይመስላል:: መንፈሱ ተጨነቀ:: የለም:: ይህ ወጣት ሆኖ ያየው የቴክሳስ ፊልም ዓይነት አይደለም:: ሆኖ አልተሰማውም:: እየተጣራ ወደ ላንድሮቨሩ ለመጋለብ ቃጣው:: እንደገና ተመልሶ የዘርፈሽዋልንና የወይዘሮ ሽዋዬን ፊት እንዴት ያየዋል? ሽፍትነት መውጣቱን ሌሎችስ ሰምተው እንደሆነስ? ፈርቶ ተመለሰ ሊባል? ሙከራውን ደርግ ቢሰማስ? - የለም! የለም! ባወጣ ያውጣ! ዓይኑን ከደን አድርጎ የሚውጥ ወደሚመስለው አድማስ ተጓዘ::

**፳**

ከሞት የተረፈው የወሎ ባተሌ፥ የኰሰመነው ገላው ትንሽ ሳያገግም፥ ያዘመመው ጐጆው ሳይቃና፥ የአንድ ዓመት እሸት በልቶ፥ ሳያበቃ፥ የፊውዳል ሽፍታ መንጋ ከድርቅ ያላነሰ ጥፋት አደረሰበት:: የፊውዳሉ ሽፍታ መንጋ እንደ አበደ ውሻ እየተቅነዘነዘ ከአንድ የገበሬ መንደር ሲደርስ ቀንደኛውና ግልገሎቹ ከዛፍ ጥላ ሥር፥ ወይም ተስማሚ ሥፍራ ያርፋሉ:: ጀሌው አስሳና ዝርፊያ ይገባል:: የተጠመደ በሬ፥ የታገተች ጥገት ተጥለው ይታረዳሉ:: ድስት ይደፋል:: መሶብና ጉስጉሽ ይገለጣል:: ጓዳ ይበረበራል:: ሃምቻና ያንን መከራ አልፎ ከዚህ የደረሰው ቤተሰብ፥ እንደ ጭራሮ ደርቆ አንደጀቱ አርሮ፥

ቆሽቱ በግኖ በዝምታ ይመለከታል። አብዛኛው እንባ አይወጣውም። ገላው ገና እንባ አላመነጨም። ደረቅ ነው። ከዚያም ወንድ ወንዱ ተነሣ ይባላል። ቀደም ብሎ ወደ ዱሩ በመሠወር ያመለጠው ቤቱ ከነንብረቱ በእሳት ይለኮስበታል። ሁሉም ነገር አመድ እስኪሆን ድረስ። የቀረ እንስሳ ቢኖር ይነዳል። አሁንም እናትና ልጆች እንባ አይፈሳቸውም። ምሬታቸው ከዕንባ በላይ ነው። እምቢ ያለው የፍጢኝ ተቀፍድዶ እየተዳፋ ይወሰዳል። ወይም አለፍ ብሎ ካለው ፈፋ ይደፋል።

በየመንገዱ፥ በየቤቱ የጸጥታ አስከባሪ አልቆመም። በቀበሌዎች ሁሉ ቀርቶ፥ በብዙ የወሎ አውራጃዎች ዘማች አልተሠማራም። ገበሬም በማኅበር አልተደራጀም። የፊውዳል ሽፍታ መንጋ ወሎን ፎለለበት። ንብረ ተዘረፈ።

ይህንን ሁሉ ሁናቴና ዜና ዘማቾች በተቻላቸው መጠን ይከታተሉ ነበር። ግን በዘማቾችም መካከል አዲስ ሁናቴ ተፈጥሮ ነበር። ስለ ዘማቾች ዝግጅት አለመሟላት ስለ ገጠር መሬት አዋጅ ትክክለኛ አለመሆን ስለ ሌሎች ጣቢያቸውን፥ እየዘጉ ወደ አዲስ አበባ ወይም ወደ አቅራቢያቸው ትልቅ ከተማ እንዲመለሱ የሚቀሰቅሱበትን ወረቀቶች ማሰራጨት ከጀመሩ ቆይተዋል። ክርክር ይደረግበታል። ግን ከመረታታት ሳይደርስ ስሜት ምክንያት ይጫናል። በጠብ፥ በግጭት ያበቃል። ብትን ወረቀቶቹ በሚጠቅሱዋቸው ምክንያቶች የሚያምኑበትም፥ የገጠር ኑሮ የሰለቻቸውም፥ የእየቀኑ አራት አምስት ወጣቶች ከጣቢያው ይጉድላሉ። ከዚያም የፊውዳሉ ሽፍታ መንጋ እየተጠናከረ ሲመጣና ዘማችን ማሳደድ ሲይዝ ለሕይወቱ እየፈራ የሚሸሸው ዘማች በዝቶ፥ አንዳንዱ ጣቢዒያ አባ -- ሰንጋ በሽታ የገባበት በረት ይመስል ተራቆተ። በእነታረቀኝ ጣብያ ከግማሽ ያነሱ ቀርተው፥ ይህ ጣቢያ ተቃጠለ፥ ያ ጣቢያ ሽፍታ ስለሚያሠጋው ተበተነ፥ የሚለውን ወሬ እየሰሙ በሕይወታቸው ቁርጠው ተግባራቸውን ቀጠሉ። ገበሬው ግን ማኅበር ማቋቋም በሽፍቶች እንደሚያስወርር ስለ ሰማ ለመሰብሰብ ስንኳ አገረገረ።

ቢቸግረው ሕዝቡ ተሰብስቦ በሚገኝበት ለማስረዳት አንድ እሑድ ቀን ጠዋት ታረቀኝና ማርቆስ አሥር እራሳቸውን ያህል ሆነው ከጣቢያው ራቅ ብላ ወደምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ቅዳሴ ከአበቃ በኋላ አንድ ጊዜ አረፍ ብሎ እንዲያዳምጣቸው ሕዝቡን ጠየቁ። ፈራ ተባ እያለ ምነው ባያስቸግሩን በማለት እያጉመተመተ ለእርሱ ጠቀሜታ መሆኑን ደግሞ ልቡ እያወቀ ግማሹ፥ በትሩን እየተደገፈ ቆመ። ከፊሉ ድንጋይ እየፈለገ ተቀመጠ።

«.....ምን ያህል የመከራና የሥቃይ ኑሮ ስትገፉ እንደ ኖራችሁ ከመሠረቱ እኛ ለእናንተ መንገር ስንኳ አስፈላጊ አልነበረም። እናንተው ራሳችሁ በእንጕርጕሮአችሁ እንዳላችሁት ለጭቃ ሹሙ ወጠጤ ለምስለኔው ሙክት ለገዥው ሰንጋ እያቀረባችሁ እናንተ ግን ቆሎ፥ ያርባችሁ ነበር። እናንተ ጥራችሁ ግራችሁ ባፈራችሁት ባላባትና ጉልተኛ ጐተራችሁን ሲያሟጥጥ ስልቻችሁን፥ ሲያራግፍ ልጆቻችሁ ለእፍኝ ጥሬ ዓይናቸው ሲቁለጨለጭ በአዘኔታ ከንፈራችሁን ከመምጠጥ በቀር ለምን እንዲህ እንደረጋለን ብትሉ መልሱ ምን ነበር? መታሠር መጨፍጨፍ ከዚያችው ከገባር መሬት ላይም መነቀል ነበር። ወንዱ ከርታታ ለማኝ፥ ሴቷ ገረድ ወይም ሴተኛ አዳሪ....ወሎ ይህንንና ከዚህም የከፋ ተሸክሞ ኖረ። ታዲያ እንደዚህ ያደለባችኋቸው የተሸከማችኋቸው ባላባትና ገዥዎች የዛሬ ሁለትና ሦስት ዓመት ያ ሁሉ ሕዝብ በረሃብ ሲያልቅ አሰቡላችሁ?» ታረቀኝ ራሱን አወዛወዘ። «ወሎ መሰደድ ልማድ ነው» ተባላችሁ። ወሎ ቡና ሲያንቃርር የዝናሙ ወራት ቢያልፍ እኛ አርሰን አናበላው ተባላችሁ። ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል እንደሚባለው ይህ አልነበረም ኑሮአችሁ?»

የከንፈር መምጠጥና የመስማማት ሁካታ ተሰማ።

«አሁን እንደ ሰማችሁትና እንደምታውቁት ተገቢውን የመንግሥት ግብር ብቻ እየከፈላችሁ መሬት ለእናንተ ለአራሾቹ እንዲሆን ስለ ተደረገ ያ ሁሉ የቀረባቸው የቀን ጅቦች መሣሪያ አንሥተው ጫካ ገብተው ለለውጡ መንግሥት አትመኑ እያሉ ሊያታልሏችሁ በመሞከር ላይ ይገኛሉ። የተታለሉላቸውም ይኖራሉ። ግን አረመኔ ማለትስ ከተራብ አፍ ነጥቀው ወደ ጠገበ ሆዳቸው የሚጕስጕሱት እነርሱ ናቸው። በለውጡ መንግሥት ወንድ ልጅ እኅቱን ማግባት ይችላል፥ ይሏችኋል ወሎ ክርስቲያኑም እስላሙም በፍቅር ተስማምቶ የሚኖርበት አገር ነው። አሁንም ይህን የበለጠ ለማጠናከር ሃይማኖቶች በእኩልነት እንዲከበሩ በሕግ ተደንግጓል። እዚህ ያላችሁት ሁላችሁም ክርስቲያኖች ልትሆኑ ትችላላችሁ መሆንም አለባችሁ። ካለበለዚያ ቤተ ክርስቲያን ልትሳለሙ አትመጡም ነበር። ጕረቤታችሁ፥ እነ አቶ መሐመድ አሊ እነ አቶ ይማም ሁሴን ከእናንተ እኩል ቢሆኑ ትጠላላችሁ? አይመስለንም? ባጭሩ እነዚህ የመሬት ከበርቴዎች የሚፈልጉት በውሸትና በሐሰት አወናብደው እናንተን እንደ ቀድሞው እንድትገብሩላቸው ለማድረግ ብቻ ነው። እንደ ዱሮው ለመሆን ትፈልጋላችሁ?»

«ኧረ አያምጣው!»

-ያረስነውን ያፈራነውን እኛው ከበላነው፤ ዓለም ነው እንጂ። ሌላ ምን ፈልግን?

«እናንተን አንከተልም፤ አርሰን በሰላም መኖር ነው የምንፈልገው የሚሏቸውን ምን ዓይነት ሥቃይ እንደሚያደርሱባቸው ሰምታችኋል። ወይም አይታችኋል። የእነሱም አደጋ ለመመከት እንግዲህ አንደ ዘዴ አለ። ይኸውም በየቀበሌያችን የገበሬ ማኅበር አቋቁማችሁ ኅብረት ስትፈጥሩ ነው። ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር የሚለው የሀገራችንን ምሳሌ ሁላችሁም ታውቁታላችሁ።»

አንዱ ገበሬ፥ ግንባሩን በእጁ ጋርዶ፥ «ለነገሩ እሱም መልካም መሆኑን መች አጣነውና። ወትሮውንስ መጫወቻ ሆነን የኖርነው የረባ ኅብረት ብናጣ አይደል? ግና ኅብረቱን ለመፍጠር ገና ምክክር ሲደረግ እየደረሱ ነው በሰው በክብትም በንብረትም ከባድ ጉዳት የሚያደርሱት ያለ። በዚህ ላይ እኛ ድሃ ገበሬዎች መሣሪያ የሚባል ነገር.....» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ጩኸት አስተጋባ።

«እጅ ወደ ላይ! ከያለህበት እንዳትንቀሳቀስ!»

እጃቸውን ወደ ላይ ያነሡት ዘማቾች ብቻ ነበሩ። ገበሬው ግን የቆመው እንደ ቆመ የተቀመጠው እንደ ተቀመጠ ባለበት ደርቆ ቀረ። ከሠላሳ የሚበልጥ አብዛኛው የታጠቀ ሽፍታ ባንድ ጊዜ ፈሰሰባቸው። ዘማቾችና አድማጮች ገበሬዎች ሁሉም እንደ ልቡ ዓይኑ ተመስጦ ቀርበው ሲከቡ ማንም አላያቸውም ነበር። «ተነሥ በክት! እንዳንተ ያለውን ሎሌ ከዚህ መድፋት ነበር! የእርኩስ አማኝ - እርኩስ!» ገበሬውን በሰደፍ አዳፉት። አውሬ እንደ ገባበት በረት አተራመሱት።

-ኧረ ኛ ምን አጠፋን?

-ድራሽህ ይጥፋና! ከዚህ ጥፋ!

ሰደፍ - እርግጫ - ቡጢ - ጥፊ - ዱላ - እርግጫ - ማጅራት አንቆ ውርወራ።

በኋላ እየታደነ ሲነዳ፥ ገበሬው ከተሰበሰበበት ብትንትን ሲል፥ ዘማቾች ብቻ እጃቸውን እንዳነሡ ክምችች ብለው ቀሩ። ብዙዎች ጥፊና ጕሽም ቀምሰዋል።

«እህህ የእኛ ለውጥ ፈላጊ! የደርግ ወኪል! እኛ ምን እንደምንለው ታውቃለህ? አቦጊዳ!» ገበየሁ አሊ. ድንገት ከታረቀኝ ፊት ተደነቀረ። ካኪ ሸሚዝና ሱሪ ለብሶ የሽራ ዝናር ታጥቆ ከፊት ቦት ጫማ አጥልቆ በአንገቱ ላይ ያነገተው ኡዚ ከደረቱ ላይ ተንጠልጥሎ እየተወዛወዘ በቀኝ እጁ ኮልት ሽጉጥ ደግኗል።

«እጅ ወደ ላይ? አዎ በፊልም እንዳየኸው አንተ መሆን አለብህ እንጂ ደንቆሮ ፊውዳል አባትህማ መጀመሪያ ተኩሶ መትቶ ነው በኋላ የሚያናግረው። ግን እጅ ወደ ላይ የሚያውቀውን ምስኪን ገበሬ ለምን ታደናግረዋለህ?» ሲል ታረቀኝ ገጥሞ ባገጠጠ ጥርሱን በኩል ንግግሩን ፈነጠቀ።

«ፊልም አሁንም አሳይሃለሁ!» ገበየሁ በሽጉጡ ሰደፍ የታረቀኝን አገጭ አላጋው። ደሙ ሲንዠረዠር ላለማየት ሌሎች ዘማቾች አንገታቸውን ደፉ። በያንኪ ፊልም ያዩት በራሳቸው ላይ እንዲፈጸም አልፈለጉም።

«ምን ትጠብቃላችሁ? ቀፍድዱት» ወዲያው የታረቀኝ ሁለት እጅ የኂሊት ተጠምዝዞ ተወነቸረ።

ማርቆስ በሰቀቀን ዓይኑን ጭፍን አድርጎ ከቆየ በኋላ፥ ገበየሁን ከእግር እስከ ራሱ አስተዋለው። የጓደኛውን የታረቀኝን ፊትና በደም የተነከረውን ልብሱን ተመለከተ። ለነገሩ ሁሉም በኮሌጅ ጓደኛሞች ነበሩ። አሁን ግን ገበየሁ ተቃራኒያቸው ብቻ ሳይሆን አውሬ ነው የሚመስለው። የተገታተረ ደም ሥሩ፥ በርበሬ የመሰለ ዓይኑ የሚቁነጠነጥ ሰውነቱ፥ የሚቅበዘበዝ መንፈሱ ምን ተብሎ ይተረጐማል? ያበደ ውሻ? ግን ምን ያሳብደዋል? ሠርቶ መኖር ይችላል። አባቱም ከአውራጃ አስተዳዳሪ ሹመት ተሻረ እንጂ ጡረታ ነበረው። ታዲያ ምንድን ነው እንዲህ የሚያደርጋቸው? ድንገት በአእምሮው የመጡበት ጥያቄዎች የሚናገረውን አጠፉበት ወይም ሊናገር ያላሰበውን አናገሩት። «እንደምትከታተለን የጠረጠርነው ቦጋለ የት እንደምንዘት ከጠየቀን ጊዜ አንሥቶ ነበር። ከዚያም ሌላ ጊዜ ተገናኘን። ፎንታናና ላይ። በኋላም ከአባትህ ጋር መሽፈትህን ሰምተናል። ግን ምን እንዲህ አደረገህ? - ምን?»

«ዝም በል!» ማርቆስ በሽጉጥ ጥፊ ተላጠ። «አንተም እርሱም አንድ ናችሁ!» ገበየሁ በፊቱ ንቅናቄ ምልክት ሲያሳይ ማርቆስ እንደ ጓደኛው የፌጥኝ ተቀፈደደ።

ጥምጥማቸውና ሪዛቸው ከገበሬው እንግልት ያተረፉቸው የቤተ ክርስቲያን ካህን፥ ከዛፍ ሥር ቁመው በመሳቀቅ እያማተቡ ይህ ሁሉ ሲሆን ይመለከቱ ነበር። አላስችላቸው አለና፥ ከአደጋ የሚከላከሉበት ይመስል የእጅ መስቀላቸውን ወደ ፊት አስቀድመው በመቅረብ «ጌታጌ! ወንድሞቼ ልጆቼ መቼም መቼም፥ የልጅ ነገር ይሆናል እንጂ ለክፉ ብለው የሠሩት ጥፋት....» እንዳሉ ገበየሁ አፈሙዙን ወደ እሳቸው አዙሮ ሲጮህባቸው ወደ ቤተልሔሙ ተፈተለኩ።

ገበየሁ ኡዚውን ከደረቱ ላይ እስክስታ እያስወረደ ከሌሎቹ ዘማቾች ፊት ቆመ። «ይቅርታ አድርጉልኝና እናንተን ብዙዎቻችሁን አላውቃችሁም። እናንተም አታውቁኝም» ትንሽ የተረጋጋ መሰለ። «ከእነዚህ ከሁለቱ ጋር ግን በቅርብ ልብ - ለልብ እንተዋወቃለን። እነሱ የደርግ ወኪሎች ናቸው። ብዙዎቹ ዘማቾች ይህንን እየተገነዘቡ ነው ጣቢያቸውን እየተው የተመለሱት። አዲስ አበባ ብዙ የሚሠራ ነገር እንዳለ በማወቅ። እና፥ እነዚህ አሳስተዋችሁ ከሆነ እንደ ከባድ ኃጢአት አንቆጥርባችሁም። ቁም ነገር» ደረቱን ነፋ። «ቁም ነገሩ ስሕተትን ከማረም ምክርን ከመስማት ላይ ነው። እና - እና ከዛሬ ጀምሮ ዘመቻ ጣቢያ መኖራችሁን እንዳልሰማ!» ሲል ዶሮ፥ ኩት እንደሚል በእጁ፥ ውዝዋዜ አስበረገጋቸው።

«ከእነዚህ ከሁለቱ ጋር ግን የቁም ነገር ጉዳይ አለን» አለ፡፡

፯

«ብመለስም ባለመለስም በሉ እንዲህ ደህና ሁኑ» አላቸው ሙሔ መጥረቢያውን ከትከሻው ላይ አድርጎ፡፡ ካሣሁን ዘይኔ፥ ከበደ ያይኔ አበባ ለመጨረሻ ጊዜ ለምነው ሊያስቀሩት ወይም ሊሸኙት ከጐጆው በር ላይ ከበውታል፡፡ በረባዳው አድማስ ገና ብቅ ያለችው ጀንበር ሌሎች ጀርባቸውን ሰጥተዋት እርሱ ፊት ለፊት ስለ መታችው ግንባሩን አኰማትሮ የሚጓዝበት መንገድ የት እንደሚያደርሰው የሚፈልግ ይመስል አሻገሩን ይመለከታል፡፡

«አባዬ ምናለበት ቢቀርብህ? በዚህ በደከመ ሰውነትህ ባዶ እጅህን፡፡ ኧረ ባክህ ይቅርብህ!» አለች ዘይኔ ሁለቱን ቀን ያቀረበችውን ልመና እንደ ገና በመድገም፡፡

«ሰው መንገድ ሲወጣ ይቅርብህ አይባልም፡፡ ነውር ነው፡፡ እናትሽ ገና ሳንጋባ እሷ፥ እየተንከባከበችኝ ከአባቷ ቤት ሳገግም፡፡ ቆይቼ እንደገና አርበኝነት ለመግባት ስነሣ፥ ጋሼ ሙሔ ይቅናህ ነበር ያይለችኝ፡፡ እንዲያ ነው የሚባለው ልጄ፡፡ እንደናትሽ ሁኚ፡፡ በሉ ደህና ሰንብቱ፡፡»

«እኛ እንሻላለን እኮ ነው የምልህ፡፡ ካለበለዚያ ደሞ አብረን እንሂድ፡፡» ሙሔ ጕዞውን ሊቀጥል ሲል ካሣሁን መንገዱን ጋረደበት፡፡

«ወቸው ጉድ! እናንተ ስዎች ጤናም አልያዛችሁ? እናንተ ገና ወደ ፊት መሬቷን አርሳችሁ የምታፈሩ ልጆች ወልዳችሁ የምትተከሉ ናችሁ፡፡ አዎ፥ ያለ ዘር አልፌ እንዳልረሳ ስሜን የሚያስጠሩ....» ወደ ዘይኔና ወደ ያይኔ አበባ እያመለከተ «እነርሱ ቢሆኑ? እንግዲህ ሌላ ሰው የላቸው ካለ እናንተ በስተቀር፡፡ ስለዚህ ለጊዜው አርፋችሁ ተቀመጡ፡፡ ለነገሩ ከዚሁ ድረስ መምጣታቸው ስለማይቀር ያን ጊዜ የናንተ ሥራ ደሞ አለ፡፡ ይህ ግን የራሴ የግሌ ግጥሚያ ነው፡፡ ስንት ጊዜ ልንገራችሁ?» ካሣሁንና ከበደ ስለዚሁ ጉዳይ ደግመው ደጋግመው አነጋግረውት አስረድቶአቸው ነበር፡፡

በእነታረቀኝ ላይ የተፈጸመው አሠቃቂ ድርጊት ሁሉ፥ ከባድ ኀዘን ቢጥልባቸውም በተለይ ሙሔ ያንንሁሉ የረሃብ እልቂት እንዳላየ ሁሉ፥ ሚስቱን ልጆቹን እንዳልቀረበ ሁሉ ሁለት ቀን ሙሉ በኀዘን ኵምትር ብሎ ሰነበተ፡፡ «የልጆቼ ወንድሞች ናቸውና ራሴ በወለድኳቸው ልጆች ላይ እንደ ተደረገ አድርጌ ነው የምቁጥረው፡፡ ቁሜ እየሄድኩ ዝም ብዬ አላይም!» ብሎ ተነሣ፡፡

«ምን ልታደርግ?»

«ከገቡት ገብቼ በሠፈሩት ቁና እሠፍራቸዋለሁ!»

«እነሱ የታጠቁ ብዙ ሠራዊት ያላቸው፡፡ ማ - ይሙት አሁን አንተ ብቻህን?» እነካሣሁን የሙሔ ሐሳብ አጕል የሽማግሌ እልህ መስሎ ታያቸው፡፡ «ደግሞ የት ብለህ ታገኛቸዋለህ?»

ሙሔ ግን አልተበገረም፡፡ «መንግሥትም ቢሆን ዝም ብሎ አያይም፡፡ እንዲህ አገር ሲጠፋ ወታደር ማዝመቱ ይቀራል? አብሬ እዘምታለሁ፡፡ ደሴ ወጥቼ መንግሥትን መሣሪያ እጠይቃለሁ፡፡»

«እባክህ ተወው፡፡ በድፍን ወሎ በድፍን ዘማች የመጣ ነው፡፡ አንተ ብቻህን....»

«አንተ ብቻህን ብሎ ነገር የለም» ሲል በመጮህ ንግግራቸው አቋረጣቸው። «እኔም ለልጆቼ ወንድሞች እንደ ተሰማኝ የብቻዬን የድርሻዬን እወጣለሁ! ደግሞስ እያንዳንዳችን ብቻዬን ምን ማድረግ እችላለሁ? እያልን እጁን የሚያነሣባቸው ስለ ጠፋ አይደል እንዲህ የፎለሉት። የለም በምወዳት በአልጣሽ አጥንት ምያለሁ። ሁለተኛ አታንሡብኝ« ሲል ከአንድ ቀን በፊት የመጨረሻ ውሳኔ አስታውቋቸው ነበር።

ካሣሁንና ሙሔ ትንሽ ተፋጥጠው ከቆሙ በኋላ ከመንገዱ ዘወር አለለት። «አ - አይሆንም ካልክ - መቼስ....መቼስ አባዬ - እስ - ስ በቸር ይመ - ይመልስህ....» ዘይኔ እየተንሰቀሰቀች መናገር አቃታት። ቁልቁለቱን ሲወርድ እንባ ባቁረዘዘ ዓይን ተከተሉት።

ሙሔ ከዋናው አውራ ጐዳና መዳረሻ ፈፋ ላይ ሲደርስ አዲስ ንዴት፥ አዲስ ኀዘን አዲስ ሰቀቀን፥ እንደ ኮረንቲ መላ ሰውነቱን ድንገት አኰማተረው። ሥፍራውን ለማየት የተጠየፈ ይመስል ፊቱን ዘወር አድርጎ በጥድፊያ እየተራመደ «ግዴለም! እኔ ቁሜ እየሄድኩ ደምህ ደመክልብ ሆኖ አይቀርም» ሲል ከንፈሩን ነከሰ።

የዋናው አውራ ጐዳና መዳረሻ ፈፋ ታረቀኝና ማርቆስ ታሥረው ከተወሰዱ ከሁለት ቀን በኋላ በስለት የተተለተለው የታረቀኝ አስክሬን ተጥሎ የተገኘበት ሥፍራ ነበር።

«አንደኛውንስ የት አድርሰውት ይሆን?» አለ ሙሔ፥ ማርቆስ እያሰበ።

## ፯

ደሴ ከተማ ነዋሪ፥ ሕዝብ የሚታመስበት ትኩስ ምጣድ ሆናለች። እንደ ሃቻምናው የስደት ጊዜ ሁሉ በደቡብ ከገራዶ፥ በሰኞ ገበያ በሰሜን፥ በምዕራብ ከቦሩ ሜዳ በቅዳሜ ገበያ በኩል በሐይቅ በአሥመራ በር በኩል ጓዝ የያዘ ብዙ ሰው ይገባል። በሸዋ በር በኩል ደግሞ እንደዚሁ ጓዝ የያዘ ብዙ ሰው የመጣል። አንዳንዱ የሚያሳድደው ያለ ይመስል እየተገላመጠና እየፈጠነ በየሠፈሩ፥ በየመንገዱ ብዙ ሰው ውር ውር ይላል። አንዳንዱ ደግሞ ከመንገድ ዳር ወይም ከቤቱ በራፍ አንገቱን አስግጎ ፈዞ በመቆም ከጠሳ ባሻገር በሩቅ ድምፅ የሚያዳምጥ ይመስላል።

በዚህ መካከል ሙሔ ደሴ ገብቶ ወደ ጠቅላይ ግዛቱ ጽሕፈት ቤት ቢሄድ የባሰ ትርምስ ሆኖ አገኘው። ወታደር መኪና ላይ እየተጫነ ወደ ቦሩ ሜዳ አግጣጫ ይጐርፋል። ጠመንጃ ያነገተው ጀሌውም እጅግ ብዙ፥ ሰው እንደ ደፈረሰ ገበያ ከወዲያ ወዲህ ይሯሯጣል። ይጨዋጨዋሃል። ይጠራራል። ብዙ ጊዜ ከመኪና ላይ ይራገፋል። መኪና ላይም ይጫናል። የግቢው በር በዘበኞች ይጠበቃል።

ሙሔ ነጠላውን አጣፍቶ የግቢውን በር ለማለፍ ሲል «ተመለስ ሰውዬ!» አለው ዘቡ፥ ወደ ቁጣ በተቃረበ ኮስታራ አነጋገር።

«የምጠይቀው ጉዳይ ነበረኝ።»

«ተመለስ ብያለሁ ፈቃድ የሌለው ሰው አይገባም!»

የዘቡ አመለካከት አላማረውምና ወደ ቱሪንግ ሆቴል በሚወስደው መንገድ ራቅ ብሎ ቆሞ ያስተውል ጀመር።

«ጌታው፥ ጌታው ስሙኝ ጌታው» አለ ሙሔ ደሴ ከተማ ደርሶ የጠቅላይ ግዛቱ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ የሚመስል አንድ ሰው ፋይል ይዞ ሲገባ ሲል እየተከተለ።

«ባለ ጉዳይ የምንቀበልበት ጊዜ አይደለም!» ሲል ጮኸበት።

«አንተ ሰውዬ ከዚህ አትሄድም!» ዘቡ ጠመንጃውን እንደ ማንሣት አደረገ።

ሙሔ ግራ ገብቶት እየተገረመ ወደ አረብ ገንዳ ሠፈር ሲያመራ ከመንገድ ላይ ሰዎች ጠየቀ።

«ምንድን ነው ምህኛቱ?» ውር ውር የሚለውን ሰው በዓይኑ እያመለከተ።

አንደኛው ጥያቄ እንደ ጅል ተመልክቶት መንገዱን ቀጠለ።

ሁለተኛ ተጠያቂ ከእግር እስከ ራሱ በጥርጣሬ አስተዋለውና «ቱሪስት ብላ» የሚል የከፍነር ሽርደዳ አሳይቶት አለፈ።

አንድ ነገር እንደ ተፈጠረ ሙሔ ተሰምቶታል። ምን ሊሆን ይችላል? ሰው ሞተ? አንድ መጥፎ ነገር ደርሶ ይሆን? ይህማ ከሆነ እነዚኢያ ጅቦች እየቦጫጨቁ ነው የሚበሉን አለ በሆዱ። ካሣሁን ከገጠር መንደሮች ወደ ከሚሴ እየተመላለሰ ዶሮ መነገድ ጀምሮ ነበርና ስንቅ እንዲሆነው ለሙሔ ጥቂት ብሮች አስቋጥሮታል። ሙሔ ለገበያ ከተማ ሲገባ እንደሚያውቀው መሸታ ቤት ወሬ አይጠፋም በማለት እሱም ውኃ ጠምቶት ስለ ነበር፥ አንዲት ስርጉድ ጣሳ ተበራሩ ድንጋይ ላይ ተደፍታ ወደ ተቀመጠችበት ጉጆ ጎራ አለ።

«ጠላ አለ?»

«አለ።»

«ስንት ነው?»

«ሃያ አምስት ሳንቲም ጠርሙሱ።»

መሸተኛዋ ጠላውን በጥድፊያ አቀረቡለትና የራሳቸውን አጣዳፊ ሥራ ቀጠሉ። የቤቱን ዕቃ ያተራምሱታል። በቤቱ ውስጥ ያለውን ጨርቃ ጨርቅ በሙሉ በብርድ ልብስ ጠቅልለው ገመድ አሠሩት። ጠርሙሶችን፥ ቆርቆሮዎችን፥ ሌሎችም የማድ ቤት ዕቃዎችን እያወጡ ወደ ጓሮ ወሰዱዋቸው። ሙሔ በበሩ በኩል ስመለከት ፊት ለፊት ካለው ቤትም ተመሳሳይ ተግባር ይከናወናል።

«ምነው ደሴ የእብድ ከተማ መሰለ?» ሲል ሙሔ ጠየቃቸው።

«ለምን አይበድ? ማበድም ሲያንሰው ነው!» አሉ ሴትዮዋ እቃ በዓይናቸው እየቃኙ።

«ምን ነገር ተፈጥሮ ነው?»

መሸተኛዋ በመገረም አስተዋሉት። «አልሰሙም እንዴ? ከየት መጥተው ነው?»

«ከቆሬ። እኔማ ትርምሱን አይቼ መንገድ ላይ ሰው ብጠይቅም የሚነግረኝ አጣሁ።»

«ይኸው ደሴን ሊይዙ መጥተዋል።» መሸተኛዋ በመትታከት ተነፈሱ።

«እነማን?»

«ሽፍቶች ናቸው! ለድሃ ለምን ቀን ወጣለት ብለው!»

«አሊ ፋሪስ?»

«ምን እሱ ብቻ። ብዙ ናቸው። አሁን በሃያ አንድ ግሸን ማርያም ተገናኝተው አሊፋሪስ ወረይመኑን ይዞ፥ በጋራዶ እነ በላይ ዘለለውና አስፋ ታረቀኝ ደላንታንና ወረይሉን ይዘው በአርበሮ ጉራ በር እነፍስሐ እንግዳና እነመኰንን መላኩ በክፊል አምባሰልን ይዘው፥ በሐይቅ ለመግባት በመስቀል ተማምለው ተለያይተዋል ይባላል። አሁን በእነበላይ ዘለለው ጦር በኩታ በር ዘልቋል። እንደሚያዩት የከተማውም ሰው ዕቃውን እያሸሸ ነው።»

«ደሴን ለመያዝ? ኦሆሆ! እውነትም ልባቸው አብጧል። ኧረ ምን ሆንን ብለው ነው?»

«እህ! ወሎን አንቀጥቅጠው ይገዙ አልነበር? ለምን ተሻርን ብለዋ ነዋ! በዚህ ላይ የተወሰደባቸው መሬት ምን ስፍር ቊጥር አለው» ሲሉ መለሱ፥ ዕቃ ማከናወናቸውን ሳያቋርጡ።

«እንደገና አንቀጥቅጦ ለመግዛት? እንደገና ለማስገበር? እህል ለማስጫን? የወሎ ገበሬ ይህንን ከተቀበለማ ቁሞ እየሄደ በድን ሆኗል ማለት ነው!» ንዴቱን አብሮ የሚውጥ ይመስል ጠላውን ከለበሰው።

«ከዚህ ያሉት ታጁሮችም ይኸው ያስራሩናል። የለውጡን መንግሥት ያመናችሁ ሁሉ መግቢያችሁ የት ነው እያሉ። መቼ አንድ ጥይት ከተተኰሰ እነሱ ናቸው ከዚህ የሚፈጁን። የኔ ቢጤው መድረሻ አጥቷል። ዕቃውን ወደ ገጠር እንዳያሸሽ የገጠሩም ዕቃውን እያሸሸ ወደዚህ እያመጣ ነው። ከዚህ እንዳያስቀምጠው በሽፍታው በቱጃሩም በወሮበላውም፥ መዘረፉ ላይቀር ነው። በይም ምክንያት ነው ሲተራመስ የሚያዩት።

«ልብ እንቅር ይመኛል አሉ!» ሙሔ ብቻውን የሚመልሳቸው ይመስል ጠላውን ጨልጦ ወጣ። - ልቤን ያነሳሳው እግሬን ወደ ደሴ የመራው ለዚህ ኖሯል? አለ በሆዱ። ደሴ እንደዚህ ባለ አደጋ ላይ የምትገኝ ከሆነ መንግሥት በለውጡ የሚያምነውን ገበሬ አስታጥቆ ከወታደሩ ጋር ማዝመቱ የማይቀር ነው። ማንስ መሬት የታወጀለት ገበሬ ነው ይህንን ጉድ ዝም ብሎ የሚያይ? ማ - ይሙት ያ ሥቃይና መከራ ተመልሶ ሊመጣ? አይደረግም! በኢጣሊያን ወረራ ጊዜ ማይጨው ላይ በኋላም አምስት ዓመት ሙሉ በአርበኝነት እንዳደረገው ሁሉ ምን በመሰለ ምኒሽር እየቀነደበ ሲጥላቸው ታየው.....

«አንተ ሰውዬ! አሁንም.....» ሲል ጠመንጃ የያዘው ተረኛ ዘብ ሲጮህ ከአጠገቡ የተቀመጠ ሌላ ወታደር «ካላንድ ነገር እንዲህ አልሆነም። የሚሰልለው ቢኖር ነው። ልከውት ሊሆን ይችላል። ፖሊስ ጣቢያ ወስዶ መጠየቁ አይከፋም» ብሎ መጣበት።

ሙሔ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሲወሰድ ስለ ምርመራ ካሣሁን የነገረው ሁሉ በሐሳቡ መጣበት። «እኔኮ በለውጡ ያመንኩ ነኝ። ከለውጡ መንግሥት ጋር ሆኜ ወንበዴዎችን እንድወጋ ለመጠየቅ ነበር የመጣሁት።»

«ቃልክን ስትመረመር ከዚያው ከፖሊስ ጣቢያ ትሰጣለህ።

መርማሪው ፖሊስ ብዙ የተወናበደና የተታለለ ገበሬ ፊውዳሎቹን የተከተለ መሆኑን ቢያውቅም፥ እንደዚህ ያለ ረብሻ «አሃ! እኔስ ነገሩ ድብብቆሽ የአልጋ ሽርክና ያለፈ አልመሰለኝም ነበር። እስከዚህም ተዳርሰናል!» በማለት ቡጢውን ወደ እርሱ አዞረበት። አለቅየው በከፍተኛ ንቃት ጥቂት ከተከላከለ በኋላ «ምን ይጨማለቃል ይህ ወፈፌ» አለና፥ አንዴ አጣደፈው። በምቾት የተጠበቀው ሰውነቱ ጠንካራና ግዙፍ ስለነእብረ ማስረሻ ሊቋቋመው አልቻለም። ስንኳን ከፊቱ ላይ ከደረቱ ላይ የሚያርፈው ቡጢ ትንፋሹን አቋረጠበት። እንደ ምንም ጥርሱን ነክሶ እንደ መፎከር እየቃጣውና እየተወራጨ ጡጫውን ደጋግሞ ሲሰነዝር አለቅየው ከአገጩ ሥር ያላተመበት ቡጢ አንገዳግዶ አንበረከከው። ሰማይና ምድር ለቅጽበት ዞረበት። መልስ ሲልለት በጉልበቱ እንደተንበረከከ በግራ፥ እጁ ወለሉን ተደግፎ በቀኝ እጁ አፉን ደባበሰና፥ ተመለከተ። ጥርሱ የረገፈ መስሎ ነበር። እንዲያውም አልደማም «ሚስቴን አልጋ ላይ ጣላት። እኒኤን ደግሞ ወለል ላይ ይዘርጋኝ? ወይኔ!» ሲል አዲስ ውርደት ተሰማው። ፊቱን ቀና ሲያደርግ ዓይኑ ከፍራፍሬው ቅርጫት ላይ ካለው ቢላዋ ላይ አረፈ። በዚህ ጊዜ አለቅየው ፈቀቅ ብሎ በአልጋው ራስጌ አጠገብ በመቆም እንደ ጉድ ይመለከተዋል።

ማስረሻ ለአንድ አፍታ ከሕሊናው ጋር ተሟገተ። ግን ከዚህ የባሰ ምን ይደርስበታል? እንግዲህ ከጓደኞቹ ጋር በባንኮኒ ላይ መጫወት የማይችል መሳቂያ ሆኗል። ቢበዛ ዓለም በቃኝ ነው። በአንድነት ፊት ይሻላል። እንደ መቶ ሜትር ሯጭ ከተንበረከከበት ተፈናጥሮ ቢላዎውን ጨበጠና ቀስር ሲሄድ በዓይኑ ይከታተለው የነበረው አለቃው ከእርሱ ባላነሰ ፍጥነት ከትራሱ ሥር ሽጉጥ መዝዞ ሲደቅንበት አንድ ሆነ። ልክ በምዕራባውያን ፊልም እንደ ተመለከተው የሽጉጡ አፈሙዝ የመድፍ ያክል አፉን ከፍቶ ታየው። ግን አልፈራም። ከፊት ለፊት የቀሰረው ቢላዋም፥ ጉራዴ አክሎ በኤሌክትሪክ መብራት ያብለጨልጭለት ነበር። ወደ ፊት ተመዘዘ። ወዲያውም በተኩስ ድምፅ ክፍሉ ሲነቃነቅ፤ አንድ ዓይነት ጢስ ሲያፍነው የኂሊት ተገፍትሮ ሲነቃነቅ፥ አንድ ዓይነት ጢስ ሲያፍነው የኂሊት ተገፍትሮ ወደቀ። በብብቱ ሥር ቅዝቃዜ ተሰማው። ሕሊናውን ከመሳቱ በፊት እንደ ሕልም ዓለም በሩቅ የሰማው ድምፅ «ፍቅሬ ምን ማለትህ ነው? ጥሩም አልሠራህ። የማማን ቁጣ አሁን ማን ሊችለው ነው?» የሚል ነበር።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የተነገራቸው ቊስለኛው ሆስፒታል ገብቶ የሆቴሉ ትርምስ ከተረጋጋ በኋላ በበነጋው ጧት ነበር።

«ታዲያስ?»

«እኔ ምህኛት አለኝ። ልጆቼን ገድለውብኛል»

«የወለዱዋቸውን ልጆችዎን?»

«የልጆቼ ወንድሞች ናቸው።»

«የልጆችዎ ወንድሞች ከሆኑ፥ ልጆችዎ ወይም የእንጀራ ልጆችዎ ናቸው ማለት ነው።»

ሙሔ፥ ከዳገታማ ቀበሌ አንሥቶ እስከነታረቀኝ መገደል ድረስ፥ በእርሱና በቤተሰቡ ላይ የደረሰውን ሁሉ ሲተርክ መርማሪው ፖሊስ በጥሞና አዳመጠው። በእነታረቀኝ ላይ ስለ ተፈጸመው አሰቃቂ ወንጀል ራሱን አስቀድሞ ያውቅ ስለ ነበር የታሪኩን እውነተኛነት አልተጠራጠረም።

«ታዲያ እርስዎ መበቀል የሚፈሉትን አሊ ፋሪስንና ልጁን። በሦስት ማዕዘን ደሴን ለመያዝ አስቀድመው የተስማሙ ቢሆንም አሊ ፋሪስ ባልታወቀ ምክንያት ሐሳቡን ቀይሮ ወደ ተንታ ተመልሷል ይባላል። አሁን ደሴ ለመግባት በኩታ በር በኩል የዘለቁት እነበላይ ዘለለውና እነ አሰፋ ታረቀኝ ናቸው። ስለዚህ እርስዎ መንግሥት ወደ ዘመቻ እስኪጠራዎ ድረስ አገርዎ ይመለሱ።»

«ማን? እኔው? እነ እንደሆንኩ አንዴ ምዬ ወጥቻለሁ። አንድ ነገር ሳላደርግ ቤቱ አልመለስም። አሊ ፋሪስን ባላገኝ እኔ ምን ተዳዬ? መሬት አገኛችሁ በተባልነው በእኛ ላይ በዘማች ላይ ተስማምተው ተማምለው ካበሩ ለኔ አንድ ናቸው። ዘልዝዬ ብጠብሳቸው የምወድ ጠላቶቼ! በዚህኛው በኩልም ቢሆን እዘምታለሁ አዝምቱኝ!»

ሙሔ እንደ መፎከር ቃጣው።

«እየነገርኩዎት! አሁን ለጊዜው የገበሬ ዘማች አልተፈለገም። ለጊዜው ከመለዮ ለባሹ ጐን የተሰለፉት የኩታ በር አካባቢ ገበሬዎች ብቻ ናቸው።»

«ኩታ በር አገሬ ነው! እወለድበታለሁ!» ሙሔ ኰስተር ብሎ ተናገረ።

«በመወለድ አይደለም። የኩታ በሮችም ከመንግሥት ጋር የሚተባበሩት በገበሬ ማኅበሮቻቸው በኩል ነው። ገባዎት?» መርማሪ ፖሊስ እንደ መሰልቸት አለ። «ቃልዎን በማመን የቀረበብዎት ክስ ተሰርዞ በነፃ ተለቀዋል። ስለዚህ ወደሚሄዱበት ይሂዱ። ወደ ጠቅላይ ግዛቱ ጽሕፈት ቤት ግን ድጋሚ ዝር አይበሉ። ጊዜ እናጥፋ።» በማሰናበት እጁን አወናጨፈ።

«ስለ ወንድ ልጅ ብለህ ተማጥኜሃለሁ።» በጠረጴዛው ጐን አልፎ ከጉልበቱ ላይ ለመውደቅ አመላቸው ብሎት ተንደፋደፈ።

«ሰውዬ ምን ነካዎት! ጤናም አይደሉ?» መርማሪው ፖሊስ በመበሳጨት ሙሔን እንደ መገፍተር አደረገው። «የሚናገሩት ነገር ካለ ረጋ ብለው በደንብ ይናገሩ። እንዲህ መሆን አያስፈልግም። የለውጡ ዓላማ፥ ጫማ መሳም ጉልበት ላይ መደፋት እንዲቀር አይደለም?»

«እሱስ ነው። ቢጨንቀኝ ነው እንጂ!» ሙሔ የነጠላውን መጣፊያ እያስተካከለ ቀጥ ብሎ ቆመ። «አየህ አንተ ወንድ ልጅ ስለሆንክ የወንድ ልጅ ስሜት የወንድ ልጅ ንዴት ይገባሃል። ነገሬን ረጋ ብለህ ያዳመጥኸኝ አንተው ብቻ ነህ። አየህ እኔ፥ ሚስቴን ብቻዬን ስቀብር፥ ሁለት ልጆቼ ከፊቴ ድፍት ሲሉ፥ እጣን ልጄን ከመንገድ ዳር ጥዬ ስሰደድ ሞት ረስቶኝ መቃብር ተፍቶኝ እንዲህ ቁሜ ለመታየት የበቃሁ ሰው ነኝ። እና፥ በደህና እንደ ሎሜ ሲመጡን፥ ሲመጠምጡን ኖረው ያ ሁሉ መከራ ሲወርድብን፥ የት መኖራችንን የረሱ ቅምጥሎች አሁን ሲያሩብን ምን ማራት ብቻ ሲቀዝኑብን ዝም ብለን እንያቸው? አንተስ ያስችልሃል?» ሙሔ እንደ ተሚጋች ሌባ ጣቱን በመርማሪው ፖሊስ ላይ ቀሰረበት። «ቁመህ እየሄድህ ያስችልሃል? እኔ.....እኔ እንደምታየኝ ዕድሜዬ እንግዲህ በቍጥር ነው። ሰው በሾህስ ይሞት የለ? እና፥ ለጀግና አሟሟት አብቃኝ - ቀኔ ደርሶ ከሆነ።»

መርማሪው ፖሊስ በሙሔ ንግግር እንደ ድንገተኛ ኢንፍሉዌንዛ መላ ሰውነቱን ትኵሳት ለቀቀበት። የሚያስደስትም የሚያበሳጭም ትኵሳት። ለምን አይገባውም? ይገባዋል። በእልቂቱ ጊዜ በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ስለ ነበር አይቶታል። እርግጥ እርሱም ቢሆን ንጹሕ አልነበረም። ለጠላ ለአረቄ፥ ከባለ ጉዳይ አንድ ብር - ሁለት ብር ተቀብሏል። እልቂቱን ከአየ በኋላ ግን የወትሮው ሰው አልሆነም።

ከባድ የሕሊና ሰቀቀን አደረበት። በየፊናው፥ በየመስኩ በየመንገዱ ቁሞ፥ እየሄደ፥ ዓዕረሞት የሚመስለው ሙቶ የተትረፈረፈው ሕዝብ ትርኢት ከዓይነ - ሕሊናው አልጠፋ አለበት። በሰፊው ተነፈሰ። «እኔ ዘመቻው በቀጥታ አይመለከተኝም። ግን የምረዳዎት ነገር እንዳለ ወደ ኩታ በር ይወስድዎት እንደ ሆነ የማውቃቸውን ሰዎች እጠይቅልዎታለሁ። ከሥራ ስወጣ እግረ - መንገዴን። እስከዚያው ግን ሥራ ስላለብኝ ውጭ ይጠብቁኝ።» በእጁ ውዝዋዜ ሙሒሀን አሰናበተው።

«ይባርክህ! ይባርክህ ልጄ! ኧረ እስከ ነገም እጠብቃለሁ!»

ሲወጣ በመደነቅ ራሱን ነቀነቀ። አንዳንዱ ዝሙት ሲሉት ይሸሻል። እንደዚህ ያለው ሰው ደግሞ ሞቴን አሳምርልኝ ብሎ ለመዝመት ለመዋጋት ለመሞት፥ እንደ ወገሽ በሬ ግን ባሩን አግጥጦ ይመጣል። እነዚያ ደግሞ፥ መሞታቸው ሳይቀር ለመሞት ተቅለብልበው መጥተዋል። እንግዲያውስ ማ - ይሙት የደላንታ ገበሬ ነው ይህንን መንግሥት የሚገለብጠው?

የሰው ስሜት፥ የሰው አስተሳሰብ አስገርሞት፥ ደግሞ ደጋግሞ ራሱን ነቀነቀ። - ይህ ለውጥ ስንቱን ያሳየን ይሆን? አለ በልቡ....

# ምዕራፍ ሰባት

«.....በባሕላዊው ወይም በልማዳዊው ሁናቴ መሠረት ከታህሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በፊት የተደረጉት የቤት ባለቤትነት ሥጦታዎች በቀበሌው የፍርድ ሸንጎ ወይም የሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት ተስማሚ መስሎት በሚያቋቁመው ሥነ ሥርዓት የሚረጋገጥ መሆኑን የሥራና ቤት ሚኒስቴር አስታውሶ ስለዚህ ጉዳይ ወደፊት መግለጫ በሚሰጥ ጊዜ ባለጉዳይ ሁሉ እንዲረጋገጥለት የሚፈልገው ንብረት ወደሚገኝበት ቀበሌ እየሄደ እንዲያስመክርና እንዲያጣራ የሚደረግ መሆኑን አመልክቷል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት።

አልፎ አልፎ ከተንጠባጠበው የደመና ባዘቶ በቀር በጠራው የመስከረም ሰማይ ላይ የተሠየመችው ፀሐይ በአገር ምድሩ ላይ ብሩሕ ጨረሯን ፈንጥቃበታለች። እንደ በቅሎ ሰማይ መንካት የከጀለው የመሆነኛ ተራራ በመስከረም ልምላሜው ላይ፥ እንደ አዛውንት ሽበት የአደይ አበባ ፈንጠቅ ፈንጠቅ አድርጎበት በግርማ ሞገስ ተገሽሮ አካባቢውን በትዝብት ቁልቁል የሚመለከት ይመስላል። ወይብማ መሆን በጀመረው በአላንሻ ሜዳ ላይ በሽህ የሚቆጠሩ የቤት እንስሶች እንደ ጠጠር ፈስሰው ሰፊ ድግስ ይዘዋል። ከወደ ሰሜን ጉዳቸው በኩል የሰገራት ተራራ ግራጫማ ባና የለበሰ እረኛ መስሎ ቁልቁል ያያቸዋል። የቀትር በኋላ ጀንበር ባዘነበለችበት በኩል የመስቀላ አምባ ከረጅም ጉዞ እንደ ተመለሰ መንገደኛ ጫማ ሥሩን በለከስ ወንዝ እያቀዘቀዘ፥ እየተለቃለቀ ጣመኑን እየተወጣ ከሰማዩ ጋር ተሳስሞ ይታያል - ከንፈር ለከንፈር ገጥሞ....

ውብ ተፈጥሮ የተፈጥሮ ውበት በወሎ የሰፈነበት ጊዜ ነው። ወሎዬ ፍቅር የሚቀጭበት፥ ወሎዬ የሚደሰትበት ሎሚ የሚወራወርበት ወሎዬ ክራሩን የሚቃኝበት ወሎዬ፥ ስለ ፍቅር ስለ ደስታ ብቻ የሚያስብበት ወራት ነበር። ተፈጥሮ ይህን አቅርባለች - አሳምራ።

በዚህ ሁሉ መካከል እንደ ብብት ጸጉር ተጣብቃ የበቀለችው የኩታ - በር ከተማ ሕይወታዊ እንቅስቃሴ ችጋግ ጥሎበታል። በየሰው ፊት ፈገግታ የለም። በየቤቱ ሳቅና ጨወታ የለም። በየመጠጥና ጠጅ ቤቱ፥ ክራር ማሲንቆ ዘፈን አውራጅ፥ ተቀባይ የለም.....

ሙሔ ከፈጥኖ ደራሾች ጋር በማርቸዲስ ካሚዮን ተሳፍሮ ሊደርስ በኩታ - በር ብዙም ወንድ አልነበረም። የአካባቢው ገበሬና የከተማውም ብዙ ሠርቶ አደር ወንድ የእነበላይ ዘለለውን ጦር ለማገድ ወደ መስቀላ አምባ ዘምቶ ነበር። የቀረው፥ አንድ በኩል እነመኰንን መላኩ ሐሳባቸውን ቀይረው ይመጡበታል ወደ ተባለው ወደ ሰገራት ተራራ ጆሮውን አቁሞ ዓይኑን ወደ መስቀላ አምባ ያማትራል። እንደ ደሴ የተከፋፈለ ልብ የተዘበራረቀ ስሜት የተለያየ አስተያየት ከዚህ የለም። ለውጡ የነካቸው አንድ ሁለት ሰዎች ቀደም ብለው ወጥተው ከቡድናቸው ዘንድ ተቀላቅለዋል። የቀረው ሁሉ ሰላም ለማንሣት ንብረት፥ ለመዝረፍ በመጣው ሽፍታ ላይ፥ አንድ ስሜት በአድን ልብ ጥርሱን የነከሰ ነበር። ጥርሱን ነክሶ ልቡን ነክሶ አንጀቱን ነክሶ የቁረጠ፥ የጨከነ ነበር።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ከደሴ ተጨማሪ ኃይል በመምጣት ላይ ነበር። ፈጥኖ ደራሹ፥ አየር ወለድ የታጠቀው የገበሬ ማኅበር አባል፥ ከካሚዎን እየወረደ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በየቦታው ይሰማራል። ከፊሉ ከቦሩ ሜዳ ላይ ታጥፎ የሚቀረው ሰገራት ተራራ ላይ ነበር። የዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ መድረክ ደግሞ የመሆነኛ ተራራ እንደ አገጭ ከወደላይ የተደፋበት የሰገራት ተራራ ከወደኋላው እንደ ትክሻ ያዘነበለበት ኩታ በር ከተማ እንደ ብብት የተሸጐጠበት እንደ ደረት፥ ደረቱን የሰጠው የወረዳው ግዛት ጽሕፈት ቤት ነበር።

ሙሔ፥ እንደ ሌሎች አሁንም አሁንም ወደ መስቀላ አምባ በማንጋጠጥ እንደ ተመኘው ከግንባር ውጊያው ውስጥ ወዲያውኑ ባለመግባቱ ባንድ በኩል ቢበሽቅም፥ ከወረዳው ግዛት ግቢ የሚወርደውን ጓዝ በማራገፍ መርዳቱ፥ መጠነኛ ድርሻውን እንዳበረከተ እየተሰማው በመጽናናት አመሸ።

ጀንበር በመስቀላ አምባ ጠልቃ አገር ምድሩን የጨለማ ጥላ እያለበሰው ሲሄድ ከሻሽ በር ግራና ቀኝ በሩቅ ሲመለከትዋቸው የተጫረ ክብሪት የሚያካክሉ ሁለት የእሳት ብልጭታዎች ታዩ። አራት - አምስት - አሥር....

በኩታ - በርና በአካባቢው የቀረው ሰው በሩቅ እንደ ክብሪት ጭረት እየተራቡ፥ እየተባዙ እየቆየም እንደ ከዋክብት እየበዙ የሚሄዱትን ብልጭታዎች ለመረዳት ጊዜ አልወሰደበትም። በመስቀል አምባ አንገት ላይ ተጠምጥሞ የሚኖረው ገበሬ ቤት በእሳት እየተለኰሰ ነው። ቀደም ብሎ ደርሶ የተከመረ እህል፥ ከአምና የተረፈ ጐተራና ጉሽጉሽ እህል እየተቃጠለ እየነደደ ነው። ኩታ - በር ሆኖ በአሻገር የሚመለከተው ሁሉ ጉጆ እንደ ተቃጠለ አህሉ እንዳረረ አንጀትና ልቡ አረረ።

ምሽቱ ከገፋ በኋላ ትክክለኛው ዜና ደረሰ።

ቀደም ብሎ የዘመተው ገበሬ፥ መስቀላ አምባ ሻሻ - በር ላይ አላሳፍም ብሎ ሽፍቶቹን አገደ። ሽፍቶቹ ባንድ በኩል ጉልበት ለመቁጥጠብ በሌላ በኩል ተጨማሪ ኃይል እስኪሰበሰብ ጊዜ ለማግኘት ላይ ላዩን በመሆነኛ በኩል የሚያልፉና የኩታ - በር ከተማ የማይነኩ የባላገር ንብረት የማይዘርፉ ሳይወድ በግዱ ለለውጡ መንግሥት ያመነውን ሁሉ የማይቀበሉ መሆናቸውን በመግለጽ በአቢ.ጋር ለመኑ። ገበሬ አሻፈረኝ አለና የሻሻን - በር ጠቅጥቆ ዘጋ። ጥይት እንደ ማሽላ ቆሎ እየተንጣጣ፥ በመስቀላ አምባ ተረተር ላይ ሕይወት እንደ አገዳ ተቀንጥሶ እየወደቀ ብዙ ሰዓት የፈጀ ውጊያ ተደረገ በኋላ ገበሬ ማፈግፈግ ግድ ሆነበት። መንግሥት የመነውን ሕዝብ ሀብትና ንብረት ትዘርፋለህ ተብሎ የመጣው የሽፍታ መንጋ ግድቡን እንደ ሰበረ ሙላት የማይታገድ ሆነ። ኩታ - በር ከተማ መግቢያ ላይ ሁለተኛ መከላከያ ለማበጀት ገበሬው ወደ ኋላ ተመለሰ።

የመጀመሪያው ግጥሚያ ውጤት እንደ ታወቀ፥ በኩታ - በር ከተማ መጠነኛ መደናገጥ ተፈጠረ። ሰዎች ዕቃዎቻቸውን ከቤት እያወጡ በመሆነኛ ተራራ ጥግ በየዛፉና በየቋጥቋጦው ሥር መደበቅ ጀመሩ። አንዳንዶቹም በከብትና በትከሻቸው የቻሉትን ያህል ዕቃቸውን እየያዙ ወደ ደሴ አቀኑ። በረሃብ ስደት፥ በሽፍታ ስደት ዕድላቸውን እያማረሩ። ሌሊቱን ሁሉም በየቤቱ ጆሮውን አቅንቶ፥ ኮቴና ጩኸት ሲያዳምጥ አደረ። ዕንቅልፍ ያሸለባቸው በጣም ጥቂቶች ነበሩ።

ሙሔ፥ በመሆነኛ በመስቀላ አምባ፥ በሰገራት በኩታ - በር ላይ እንደ ተነጠፈው ጨለማ ልቡ ጨልሞ በዓይናቸው ዕንቅልፍ ዝር ሳይል ካደሩት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር።

በወረዳው ግዛት መሥሪያ ቤት ፈጥኖ ደራሾች ሠፍረው ስለ ነበር፥ ከእነርሱ ጋር መጠለያ እንዲይዝ ቢለምኑት እምቢ ብሎ በወረዳው ግዛት ጽሕፈት ቤት ታዛ ላይ ግድግዳውን ተደግፎ ተቀመጠ። በሩቅ የመስቀላ ተራራን ከሰማዩ ጋር የሚያጋጥመው መስመር በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንደ ተሰመረ ደብዛዛ ጠመኔ ደብዘዝ ብሎ እየታየው፥ ከፊት ለፊቱ የመሆነኛ ተራራ በሚያስፈራ ጽልመት ተፋጥጦት፥ ከሥር የኩታ - በር ከተማ በባሰ የጨለማ አዘቅት ተውጦ ዓይኑ ይህንን ሁሉ እየቃኘ የሕይወቱ ሰቀቀን ሁሉ መጣበት።

-ማይጨው ዘምቶ መመለስ። የሕግ ሚስቱን በባንዳ መነጠቅ። አምስት ዓመት በአርበኝነት ተንገላቶ በመሬቱ ላይ ጉልተኛ መተከል። አዲስ መሬት ለማቅናት ቆላ መውረድ። ከዚያም አስገባሪ፥ ማድ ቤት በርባሪ መምታት። የዳገታማው አፈርሳታ እልቂት የቆሬው የረሃብ እልቂት። ቅበር - መጣል - መሸኘት - መሰደድ። አቤት ወሎ ስንቱን ቻለው? ታዲያ ይህ ሁሉ አልፎ ለማንም ጉልተኛ መገበር ቀርቶ ፊቱን መልሶ ሰው እፎይ ማለት ሲጀምር ስልቻ ሲገለበጥ ጉስጉሻ ሲደፋ የነበር ቅምጥል ሁሉ አሁን ወደዚያ የሥቃይ ኑሮ ለመመለስ አሰፍስፎ ተነሣ። ታዲያ ባተሌ ገበሬው ከእነርሱ ጋር ምን አቀላቀለው?

ሙሔ ይህንን ጥያቄ በትክክል ሊመልስ አልቻለም። መጠነኛ ዕውቀት እንዳገኘው እንደ ካሣሁን በየጊዜው እየመጡ ያወያዩት ይከራከሩት እንደ ነበሩት እንደ ታረቀኝና ማርቆስ የመሰሉ ዘማቾች ወረኢሉ ወረኢመኑ፥ ዋድላ ደላንታ፥ አለመዝለቃቸውን አያውቅም ነበር። ስለዚህም እንደርሱ ምስኪን የሆነው የደላንታ ገበሬ በለውጡ ላይ ሸፍቶ እንደርሱ ያሉትን ባተሌ ገበሬዎች ለመግደል ለመዝረፍ ለምን እንደ መጣ ፈጽሞ ሊገባው አልቻለም። በሬ ከአራጁ ጋር ይውላል እንደሚባለው ሆነበት።

ገባርና አስገባሪ እንደገና በአንድነት ሊኖሩ? እርያ ብቻ ነው ወደ ትፋቱ የሚመለሰው። የወሎ ባተሌ ከዚያ ሁሉ በኋላ ገባርነት አንቅሮ አልተፋውም? ሙሔ፥ በጨላማ ተጠቅልሎ ፊት ለፊት ከተጋረጠበት የመሆነኛ ተራራ ጋር ተፋጥጦ ቆሽቱ እየደበነ፥ በንዴቱ ጥርሱን ሲያፋጭ አንጀቱን እያኘከ በዓይኑ እንቅልፍ ሳይዞር ነጋ።

በበነጋው ቀን ብዙ እንቅስቃሴ ስለ ነበር እንደ ሆነለት ዕቃ በማውረድ መርዳቱ፥ ከላበለዚያም እንቅስቃሴውን በአድናቆት መመልከቱ አንጀቱን የሚያኝክበት ሐሳቡን ከፈለለት። ተጨማሪ ፈጥኖ ደራሾችና ፓራኮማንዶች መጡ። በወረዳው ግዛት ጽሕፈት ቤት ግቢ ከባድ መሣሪያ ተተከለ። ክትር ተሠራ። ከሥር የኩታ - በር ከተማ ነዋሪና አፈግፍጎ የመጣው ገበሬ ይሯሯጣል። ይዘጋጃል። እንደ ደሴው በሽፍቶች መምጣት ተደስቶ የሚያሾፍ መልክ አይታይም። እንደርሱ ሁሉም ጥርሱን ነክሶ ግንባሩን ያጨፈገገ ነበር። በዚኢህ ሙሔ መንፈሱን ቀለለው። ከቁረጡ አይቀር መቍረጥ ነው። የምን ማወላወል?

«ጀምበር በመስቀላ አምባ ጀርባ ማዘቅዘቅ ስትይዝ በመሆነኛ ተራራ ላይ አልፎ - አልፎ ጢስ መታየት ጀመረ። ጢሱ እየተበረከተ ሄደ። የሽፍታው መንጋ ከሸለቆው መተላለፊያ ላይ ከባድ መከላከል እንደሚጠብቀው በመገመት ዋናውን መንገድ ይዞ በኩታ - በር ከተማ በኩል ማለፉን ትቶታል ማለት ነው። አካሄዱ ላዩን በመሆነኛ ተራራ ላይ በኩል አድርጎ አበርብሮ ጐራ በር በመዝለቅ በጦሳ ተራራ ጥግ ጥጉን ደሴ ለመግባት ነበር። የፊውዳል ሽፍታ አእምሮ ያልተገነዘበው እስከ መሆነኛ ተራራ የሚዘልቅ መሣሪያ በሩቅ ተጠምዶ የሚጠብቀው መሆኑን ነበር።

በወረዳው ግዛት ጽሕፈት ቤት ክልልና በሰገራት አምባ ላይ የተጠመዱት ከባድ መሣሪያዎች በመሆነኛ ተራራ ላይ የቁጣ የመዓት፥ የእሳት ላንቃቸውን ከፈቱ። የሰማንያ ሚሊ ሜትር ድምፅ ከገደል ማሚቶው ጋር እየተቀባበለ ከመስቀላ አምባ እስከ ሰገራት አስተጋባ። የጆሮ ታምቡር የሚበሳ የይሚመስል፥ ልብ የሚያሸብር ድብልቅልቅ ጩኸት። በእያንዳንዱ ተኩስ ከመሆነኛ ተራራ ላይ የሚነሣው ጢስ እንደ ጃንጥላ በመክፈት ሰማዩን እያጠቆረው ሄደ። ኩታ በር - ከጭንቋ ለመገላገል ምጥ ያዛት።

የከባድ መሣሪያው ተኩስ ጥቂት ሰዓት እንደ ቆየ እግረኛው ጥቂት ጦር ከምዕራብ በኩል፥ ፈጥኖ ደራሽ፥ ፓራኮማንዶ ሽፋን ሰጭ ሆኖ ከምሥራቅ በኩል፥ መካከል ገበሬው በአብዛኛው መጥረቢያ ጦር፥ ዱላ፥ ይዞ፥ የመሆነኛን ዳገር ተያያዘው። እንደ ጉንዳን እየተርመሰመሰ፥ እንደ ፋሮ፥ ቋጥኙን፥ ቁጥቋጦውን እየቧጠጠ.....

መጥረቢያውን እንደ ያዘ ከገበሬው ተዋጊ ጋር ተቀላቅሎ የነበረው ሙሔ፥ አከላቱ ከስሜቱ እኩል ሊራመድ አለመቻሉን ለመገንዘብ ረጅም ጊዜ አልወሰደበትም። ቁጣው ተራራውን ዘልቆ ከመንጋ ሽፍታ ጋር ተናንቋል። ዕድሜ የቦረቦረው ችግርና እንግልት የጨረሰው አካሉ ግን በለስላሳ ስሚንቶ ላይ እንደሚሳብ እባብ እየተሸመደመደና እየተልፈሰፈሰ አስቸገረ። ሐሳቡ በንዴት ሠረገላ ተንሳፍፎ ጠላቶቹን ቁልቁል ይቃኛል። እጅና እግሩ ግን እንደ ደረቀ ቆዳ ለልቡ ፈቃድ አልታዘዝ አሉ።

ዘማቹ ገበሬ ከመሆነኛ ተራራ አንገት ላይ ሲዘልቅ፥ ሙሔ ገና ከወገቡ ላይ ይካክር ነበር። ጨለማ ለዓይን ሲይዝ ከባድ ዝናም ይጥል ጀመር። የከባድ መሣሪያው ተኩስ አቁሞ በቦታው የነጐድጓድ ድምፅ ተተካበት። ከተራራው አናት ላይ የጠመንጃ ተኩስ፥ የቆርቆሮ ጣሪያ እንደሚደበድብ በረዶ በሩቅ ይንኳኳል። በተራራው አናት ጥግ የአፈሙዝ ላንቃ ብልጭ ድርግም፥ ብልጭ ድርግም ይላል። አንዳንዱ እንደ በራሪ ኮከብ በሰማዩ ላይ ይወረወራል። ይህንን ሁሉ ለማብረድ ገስግሦ የመጣ ይመስል ዝናሙ ዝም ብሎ ይወርዳል።

ሙሔ፥ ብልጭታ ከሚታይበት ኳኳቴው ከሚሰማበት ለመድረስ ሲያንሸራትተው ሣቅ ቅጠል፥ ቧጥጦ ከመንከባለል እየዳነ ሁለት እርምጃ ሂዶ እንደሆነ አንድ እርምጃ ወደ ኋላ እየተመለሰ ሦስት አራት እርምጃ ሂዶ እየተጋደመ አሁንም እየተንፏቀቀ እንደ ትል እየተጐተተ ጥርሱን ነክሶ ይዳክራል። ከላይ ዝናሙ ይወርድበታል። ጭቃው ያድጠዋል። እጁ የሚጨብጠውን ነገር ይቧጥጣል። ከላይ ዝናሙ ይውርዳል - ያርሰዋል - ያበሰብሰዋል። እትትትት.... ሰውነቱ እንደ መንዘፍዘፍ ይቃጣዋል። ውስተ - ሰውነቱ ግን በእልህ ይቃጠላል። ከላይ ውኃ ከውስጥ እሳት፥ ከላይ ቅዝቃዜ፥ ከውስጡ ሙቀት....

ሙቀቱ እየቆየ ወደ ትኩሳት ተሸጋገረ። እንደ ጨቅጫቃ ሚስት የማያባራ ዝናም እየወረደበእት እያበሰበሰው ከግንባሩ፥ ላይና ከብብቱ ሥር ላብ ችፍፍ ሲል ተሰማው። ለምን እንደሆነ ወዲያውኑ አወቀ።

«እንኳን ንዳድ መድፍም አይመልሰኝም» ሲል መንገጫገጭ የጀመረው ጥርሱን ነክሶ እየጧጠጠ መሳቡን ቀጠለ። ቆሬ ከወረደ በኋላ ያተረፈው አንድ ነገር ወባ ነበር። ካፊያ ሲጥል አልፎ አልፎ ትነሣበታለች። ደግነቱ በጥቂት ሰዓት ውስጥ የምትበርድ ዓይነት ናት። እስከዚያው ግን ድብን ታደርጋለች። አሁን ደግሞ በአጉል ጊዜ ተነሥታ ከፍተኛ ተልዕኮው ልታሰናክለው? «ስንኳ ንዳድ መድፍም አያስቀረኝ!» አለ በገጠመው ጥርሱ መካከል - አሁንም እንደ ገና።

ሙሔ የመሆነኛን ዳገት ይቧጥጣል። በትኩሳት፥ በወባ ቅዠት። በደመ - ነፍስ ጊዜው ሳይታወቀው ከተራራው አናት ሲደርስ ውድቀተ ሌሊ ሆኖ ነበር። የደልዳላው አናት ቅዝቃዜ ገረፈው። ላቡ ባንዴ ደረቀ። አሁን ዝናሙ አባርቷል። የዕለቱ ውጊያ አብቅቶ ሁሉም ሥፍራውን ይዞ አድፍጧል። ከጥቂት ሰዓታት በፊት ጥይት ሲንጣጣበት፥ ጥሪ ጩኸት፥ ፉከራ፥ ሲያስተጋባበት የነበረው የመሆነኛ ደልዳላ አናት ከሩቅ መንደር ከሚጮህ ውሻና ከሚያቃስት ቊስለኛ በስተቀር ጸጥታ ሰፍኖበታል። እየገለበጠ በሄደው ሰማይ ላይ ከዋክብት መቁለጭለጭ፥ መጠቃቀስ ጀምረዋል። በሙሔ ዓይን ላይ ግን የእሳት ፍንጣሪዎች ይጨፍሩ ነበር። ቀስ በቀስ ትኵሳቱ እየበረደ ሲሄድ ሰመመን እየተተካበት በመጨረሻ ሳይታወቀው ችልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደው። በዝናም የራሰው ልብሱ ቅዝቃዜ አልተሰማውም።

ሙሔ በተደበላለቀ ጩኸት ባኖ ነቃ። ገና የፈነጠቀች ዠምበት የመሆነኛን አናት በብርማ ብርሃንዋ አጕናጽፋዋለች። የገብስና የስንዴ አዝመራ በጧት ነፋስ ይዘናፈላል፤ የሸበሸባል። ያልፈረገ ጤዛ እንደ ተበተነ የብር አሸዋ እያብለጨለጨ የተቀበለውን የፀሐይ ጮራ መልሶ ይፈነጥቃል።

ነገር ግን በመሆነኛ አናት ላይ የፈሰሰውን ይህንን የተፈጥሮ ውበት የሚያደንቅ ማንም ፍጡር አልነበረም። ሙሔ ከተጋደመበት በስተምዕራብ ወደ ፍላጎ መዳረሻ ሲል፥ መሬት ቁና ሆናለች። ዓይኑን ማመን አቃተው። ይህ መጨራረስ መፋጀት፥ መተላለቅ እንጂ ውጊያ አይባልም፥ አለ በልቡ። ከአንድ በኩል ለተዘረፈ ከብት መሣሪያና ለብር መያዛ ይዞታ የመጣውን ገመድና አቆማዳ እየጣለ የሚሸሸው ደሌ ሽፍታ፥ ያመረረው የጨከነው የቈረጠው፥ የኵታ - በር አካባቢ እያሳደደ በመጥረቢያ ይፈልጠዋል፤ በጦር ይሰቀስቀዋል፤ በጐራዴ ይቀነጥበዋል። ከሌላ በኩል ከአንድ መጠነኛ ማሳ በማይበልጥ ርቀት መለዮ ለባሹና የታጠቀው ሽፍታ ይጠዛጠዛል። አንዳንዱ ከተጋደመበትና ከተንበረከከበት ዘሎ እየተነሣ ተወርውሮ እየፎከረ ከተላቱ መሃል ይገባል። ከዚያም አፈሙዙን ከጠላቱ ግንባር ላይ ደቅኖ ይደፋል። ሌላ ሥፍራ ላይ እንደ ደፈረ ሳይደርስ መሃል መንገድ ላይ ይደፋል። ሌላ ሥፍራ ላይ እንደ ደፈረሰ ገበያ ጩከትና ትርምሱ እየቀጠለ ዱላ፥ ከዱላ ይከታከታል። በመጥረቢያ ከመጥረቢያ ይፋጫል። ጋሻ ከጋሻ ይፋተጋል። ጦር ከጦር ይላላሳል። አንዳንዱ በግንባሩ ይደፋል። ሌላው በጀርባው ይፈነገላል አንዱ ወደ ሰማይ ጉኖ ይፈጠፈጣል። ሰውነት ትንሽ እንደ መንዘፍዘፍ እንደ መንቀጥቀጥ ይልና እንደ ገና ሳይንቀሳቀስ ባለበት ይረጋል። በመሆነኛ አናት ላይ በሚዘገንን ሁናቴ ሰውና ሰው ይተላለቃል። ሕይወት ይጠፋፋል።

ሙሔ ይህንን ሁሉ ላንድ አፍታ ሲያይ፥ ከቆሬ ድረስ ያመጣውን ዓላማ ዘንግቶ ሌላ ሰቀቀን፥ ሌላ ንዴት ያዘው። ራሱ የዋለበት የማይጨው እልቂት ይገባዋል። ቀለሙ ከቀለማችን የማይመሳሰል ባዕድ ባሕር አቋርጦ ሊገዛን ቢመጣ ነው። ግን ሹም ለምን ተሻርኩ ብሎ የማያርስ፥ የማይቆፍር፥ የማያርም፥ የማያጭድ እህል ማስጫን ለምን ቀረብኝ ብሎ፥ አንዱ የሌላውን ንብረት ካልዘረፍኩ ብሎ ወገን፥ ከወገኑ እንዲህ መተላለቅ አለበት? የአንድ እናት ልጆች እንዲህ መጨካከን አለባቸው? ወሎ ካሁን ቀደም ያየው ሞት ያየው እልቂት አይበቃውም? ድፍን ወሎ ያልተቆፈረ ያልተከደነ ክፍት

መቃብር መሆን አለበት? ሰው ጨካኝ አውሬ ነው የሚል ሐሳብ እየመጣበት ጉሮሮውን ሲቃ እየተናነቀው ዓይኑን ክድን አደረገ። ማየት አሠቀቀት።

«የለም፥ ሰው በተፈጥሮው ጨካኝ አይደለም። ጨካኝ የሚያደርገው ሥርዓቱ አስተዳደሩ ነው። ትክክለኛ ሥርዓትና አስተዳደር በሰው ልጆች መካከል ፍቅርና ሰላም እንዲነግሥ ያደርጋል» ሲሉ እነታረቀኝ የተናገሩት ትዝ አለው።

በሰው ልጆች መካከል ፍቅርና ሰላም እንዲነግሥ የሚያደርግ ሥርዓትና አስተዳደር ምን ዓይነት ይሆን? አስተማሪዎቹ ራሳቸው ሳያዩት ሳይደርሱበት አለፉ። ለጋ ሕይወታቸው በአዲሱ፥ ሥርዓት እልቂት በሚሉት ጥላቻና ጭካኔ ተቀነጠሰች። ይህ እልቂት መቆም አለበት።

ክንዱን ማንሣት ያቃተው ይመስል መጥረቢያውን አንዘላዝሎ ይዞ በቦዘ አእምሮ ወደ አፈናው ውጊያ አመራ። ብቻውን ያንን ትንቅንቅ ሊገላገል። ብቻውን ባርኮና አውግዞ ሰላም ሊያነግሥ።

ሰውየው በአለባበሱ ከሽፍቶቹ ወገን መሆኑ ግልጽ ነው። የሚተኰሰው ግን በሁሉም ላይ ነበር። ጥርሱን አግጥጦ ዓይኑን ጨፍኖ፥ የሚንዘፈዘፍ እጁ እንዳሰኘው አፈሙዙን ግራና ቀኝ እያወዛወዘ ጥይት ያዘንማል፤ ሞት ይዘራል፤ ሕይወት ያጭዳል.....

ሙሔ ለቅጽበት ቀጥ ብሎ ቆሞ። አንድ ጊዜ እንደ ቅጠል ወደሚረግፈው ሰው፥ ሌላ ጊዜ ሞት ወደሚተፋው መትረየስ ዓይኑን አመላለሰ።

ሰውየው ከዚህ ቀደም ጦር ሜዳ ውሎ የማያውቅ የመጨረሻው ፈሪ መሆን አለበት፤ ፍርሃት ብቻ ነው። እንደዚህ የሚያደርግ። ፍርሃት ጭካኔን ይወልዳል። የመጨረሻው ፈሪ የመጨረሻው ጨካኝ ነው። ፍርሃቱን ለመወጣት ዓለምን ከማጥፋት አይመለስም። አዎ፥ ጭካኔን ለማጥፋት ፍርሃትንም ማጥፋት ያስፈልጋል። ሙሔ መላ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ መጥረቢያውን በሁለት እጁ ወደ ላይ አንሥቶ ሞት ወደሚዘራው ፍርሃት ተፈተለከ።

ሙሔ መጥረቢያውን ከፍ አድርጎ ይዞ ከሰውየው ትከሻ በላይ ሲያንዣብብ፥ ሰውየው ውቃቢው የነገረው ይመስል፥ ድንገት ቀና ብሎ ዓይኑን ሲገልጥ አንድ ሆነ። ከአሁን ቀደም ያየው መልክ ነው? መጥረቢያ የያዘ እጁን ወደ ላይ እንደ ዘረጋ ሙሔ ባለበት ያደረቀው ግን የሰውየው መልክ ትወሳ አልነበረም። የዓይኑ ፍጥጫ እንጂ። በክፉ ቀን ያረዳት የላሙ የቦቂትን ጭንቅላት ሕፃናት ልጆች ከድንጋይ ላይ አስቀምጠውት አፍጥጠው እንዳያቸው ዓይኖች ዓይነት.....እያየ የማያይ፥ ሳያይ የሚያይ የሚመስል ከድንጋጤና ከፍርሃት ሁሉ በላይ የሆነ ፍጥጫ....ሕይወት ከሞት ጋር በገሃድ ሲጋተር ብቻ የሚፈጠር ፍጥጫ። የሕይወትና የሞት ጣውንትነት ፍጥጫ።

ሙሔ መልሶ በሞት ፍጥጫ ላይ አፈጠጠበት። መጥረቢያ የያዘ እጁን ወደ ላይ እንደ ዘረጋ አንድ ነገር ከቆመበት አነጠረው። መጥረቢያ ጨብጦ የተዘረጋው እጁ ወደ ታች ነዘረ። የሚፈልጥ እንጨት የመሰለ ድምፅ ተሰማው። ርጥብት ነገር ተረጨ።

ሁሉ ነገር ባዶ ጭለማ ሆነ.....

ካፊያ ጣለ። ሕይወት ከሌለው ገና መርጋት የጀመረ ደም በዝናም ውኃ እተበጠበጠ፥ እየቀጠነ፥ ደማቅ ቅላቱን እየለወጠ ከአፈር ጋር ተቀላቀለ። ከመሆነኛ ሆድ እየሠረገ ገባ።

ጆቢራዎች እየተጠራሩ እየተሰበሰቡ ማንዣበብ ጀመሩ።….

## ፪

የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤተ ሰብ በጥቂት ወራት ውስጥ በጣም ተለውጦ ነበር። ሰው ኑሮውን ይመስላል እንዲሉ አዲሱ ነገር አዳዲስ ሁናቴ አስተማራቸው፣ አስለማመዳቸው። መሶብ ቤት ከከፈቱ ወዲህ በገረድና በአሽከር ላይ መደንፋታቸውን ለትልቅ ለትንሹ ዱላ ማንሣታቸውን ትተውታል። «ደሞ ከርቸሌ ያስገባኝ!» ይላሉ ብቻቸውን። ይህም ሆኖ አሽከርና ገረድ አልቀመጥላቸው ካለ ቆይቷል። የገጠር መሬት የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ ከወጣ ወዲህ ፊታቸውን ያጠቆሩበት ሠራተኛ ሁሉ እየጣላቸው መሄድ ነው። አንዳንዷም «እንደ ትናንቱ መስሎት እንዴ? የፊውዳል ዘመን አክትሟል» ስትል ልክ - ልካቸውን ትነግራቸዋለች። እንደ ወትሮው እንደ ልባቸው መሳደብ ይከጅላታል፣ መግረፍ ይቃጣቸዋል። በሌሎች መሰሎቻቸው ላይ የደረሰው በቁጥጥር ሥር መዋሉ፥ ከዚያም አልፎ የፍየል ወጠጤው ሽለላና አብዮታዊ እርምጃው ከፊታቸው ድንቅ አድርገው ለጊዜው ይታገሡታል። መኝታ ክፍላቸው ውስጥ ብቻቸውን ሲሆኑ ፊንቅኋቸው ይወጣል። ስቅስቅ ብለው ያለቅሳሉ። ከሰው ጋር ሲወያዩ ደግሞ «ብቻዬን መሆኔ ነው። ሴት መሆኔ ነው እንጂ ደጃዝማች ቢኖሩ እንዲህ የማንም መጫወቻ እሆን ነበር?» ይላሉ። መልሰው ደግሞ «ኧረ እንኳን ፈጣሪ ይህንን ከብዙ ዓመታት በፊት የሞቱ ባላቸውን የሚያነሡት ለአፍ ልማድ ያህል እንጂ ከልባቸው ትዝ ብለዋቸው አይደለም። ሕይወት ያለው ትዝታቸው ከሕሊናቸው ሰሌዳ ከደበዘዘ ቆይቶአል። ከግድግዳው ላይ የተሰቀለው ፎቶግራፍ ባያስታውሳቸው ኖሮ መልካቸው ስንኳ ምን እንደሚመስል ጨርሰው በረሱት ነበር። የሟች ባላቸውን ስም እያነሡ ከንፈራቸውን ይምጠጡ እንጂ ልባቸው የሚያስበው ደግሞ ስለ ማናዬ ደኅንነት ነበር። ማናዬ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ተመልሰው «ይህንን ምናምንቴ» ሁሉ ልክ የሚያስገባትን ቀን በጕጕት ቢጠባበቁም «እኔው ነኝ ወትውቼ የሰደድኩት። ምናለ ከዚሁ ከእኛው ጋር ሰው እንደሆነው ይሆን ነበር» እያሉ መጸጸታቸው ደግሞ አልቀረም።

የሠራተኛውን ችግር እየቆዩ ዘዴ አገኙለት። ከአገር ቤት ሁለት ዘመዶቻቸውን አስመጡና ባዕድ ሠራተኛ መቅጠሩን ተዉት። ባንድ በኩል ከገረድ ጋር እኩል አፍ መካፈት ያስመረራቸው ሲሆን፥ በሌላ በኩል ግን ለጥንቃቄው ሲሉ ነው። እንኳ ባዕድ ሠራተኛ ዘመድ ስንኳ ዛሬ ጊዜ በጥርጣሬ መታየት አለበት። ከዚህ ቤት አድኃሪያን እየተሰበሰቡ ይዶልታሉ ብሎ ቢያሲዛቸውስ?

ሁለቱ ዘመዶቻቸው፥ ራሣቸውና ዘለቃ ሆነው የመሶብ ቤቱን ሥራ ተያይዘውታል። አንድ ባላገር ዘመዳቸውን ዘበኝነት አቁመዋል።

ከግቢው በር ላይ «የሀገር ምግብ ቤት» የሚል ጽሑፍ ከመሶብ ሥዕል ጋር ተለጥፎበታል። ግን የፈለገ ሁሉ እንደ ልቡ ገብቶ የሚበላበትና የሚጠጣበት አይደለም። የማይፈልግ ወይም ያልታወቀ ደንበኛ ድንገት ገብቶ «ምግብ አለ?» ብሎ የጠየቀ እንደሆነ የሚሰጠው መልስ «አልቋል» የሚል ነው።

«ቢራስ?»

«እሱም የለም።»

«ለስላሳ መጠጥ?»

«ገና አልመጣልንም።»

«ታዲያ ምን አላችሁ?»

«ለጊዜው ምንም!» ትላለች እንዴት፥ መመለስ እንዳለበት የተነገረችው ዘመድ - ሠራተኛ። እንዲያውም ብዙ ጊዜ የውጭውን በር ተዘግቶ የታወቁ ደንበኞች ሲያንኳኵ እየተከፈተላቸው ነው የሚገቡት። ውስጡም ከአንድ መሥሪያ ቤት ምንም ያህል የተለየ አይደለም። ለስሙ ያህል ብቻ ባንኮ ቢጤ ከአንድ ጥግ አለ። ከእርሱ ጀርባ ከመደርደሪያው ላይ ጥቂት ጠርሙሶችና ብርጭቆች ተደርድረዋል። ሁለት የመጠጥ ቤት ጠረጴዛዎች ከተመሣሣይ ወንበሮቻቸው ጋር በሁለት አግጣጫ አሉ። የተቀረው ግን የመኖሪያ ቤት ሳሎን ነው።

በፊት መኝታ ቤት የነበሩት ሁለት ክፍሎች እንደዚሁ አንዳንድ ሙሉ ሳሎን አለባቸው። የቀድሞ ከፍተኛ መኰንኖች ከሥራ የተወገዱ ወይም ጡረታ የወጡ የቀድሞ ሹማምንት ከገጠር መሬትና የከተማ ቤት የተወረሰባቸው የትናት ሀብታሞች፥ እየተገናኙ ውስኪ እስቀድተው ወሬ የሚለዋወጡበት፥ መልእክት የሚቀባበሉበት የጀርመንንና የኦምዱርማንን ራዲዮ የሚያዳምጡት፥ በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ውስጥ ነው። ወሬ - ምሥጢር - መልእክት.....

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል «የሀገር ምግብ ቤት» የከፈቱት በወይዘሮ ሽዋዬ አነሣሽነትና አማካይነት ነበር።

ማናዬ ለመሸፈት ሲነሣ በገቡለት ቃል መሠረት ወይዘሮ ሽዋዬ ለወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንደ እናት ያህል የሚስቡ ሆኑ። እህል በጆንያ፥ ቅባት በቆርቆሮ ቅመማ፥ ቅመም ሳይቀር በሠራተኛ ይልኩላቸዋል። ወይም በመኪና አስጭነው ይመጣሉ።

«ዘርፉ የሚቸግርሽ ነገር ካለ ንገሪኝ አትደብቂኝ፤ የእኔ ያንቺ ነው፥ ያንቺ የኔ ነው» ይላሉ።

«ኧረ ምንም ችግር የለ። ሞቶ ተርፎ!» ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ይመልሳሉ። ግን የገንዘብ ነገር ውስጥ ውስጡን የተሰማቸው ሂዶ ነበር። ያ ሁሉ የእህልና የቡና ቤት መሬት ተወርሶባቸው ሀብታቸው የማይጐድል የመሰለው ወይዘሮ ሽዋዬ ነበሩ። ድግሱ ተጋባዡ፥ ስብሰባው፥ የገጠር መሬት አዋጅ ከመታወጁ በፊት እንደነበረው ቀጠለ።

በሐምሌ ወር ላይ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ ሲወጣ፥ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የፍል ውኃ መሬታቸውን በደህና ዋጋ ሸጠው የገንዘብ ችግራቸውን ፋይል ባንድ ጊዜ ለመዝጋት የነበራቸው ተስፋ ለጊዜው ተቋረጠባቸው። ጨርሶ ግን ተስፋ አልቆረጡም።

እጃችንን አጣጥፈን ማስረከብ። አይደረግም! ለጊዜው እነሱ እንደ ፈለጉ አንድ ሌላ ቤት ለንግድ ሥራ ይፈቅዳል ተብሏል። ቀደም ብዬ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም መስከረም ወር ሽጩላታለሁ ብዬ ልፈርምልና ለምን አንዱን አትወስጂም ሲሉ በቁጣ መልክ ጠየቁ። «እኔም አንዱን ትልቁን ላስቀር ነው።»

«ከምን አባቴ አምጥቼ ልከፍልሽ?»

«ነግደሽ ሠርተሽ ባገኘሽ ጊዜ።»

«እንግዲህ በስምሽ ዕድሜዬ ምኑን ነገድኩት ብለሽ?»

«በስምሽ ይዘውሽ ቆዩ! የሚሆነውን ምን ይታወቃል?»

«ከሆነማ እንዳልሽ» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል። ቤት በነፃ ሲገኝ እንዴት እምቢ ይባላል።

አፈጻጸሙን ወይዘሮ ሽዋዬ በሚያውቁበት መንገድ አቀላጠፉት። በመጀመሪያ ቤት የሚመዘግቡት ሲሰማሩ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የትርፍ ቤት ቅጽ እንዲሞሉ ተደረገ። ቀጥሎ ሻጭ፥ ገዢና ሦስት እማኞች የፈረሙበት የሽያጭ ውል አንድ ዓመት ሙሉ በሣጥን ውስጥ የኖረ እንዲመስል ተደርጎ ተሰናዳና ቤቱ ለሚገኝበት ቀበሌ ጽሕፈት ቤት ገባ። ለተጨማሪ ማረጋገጫ ሦስት ሰዎች ቀርበው መሰከሩ። ጠቅላላው ሰነድ ከቀበሌው ጽሕፈት ቤት መሽኛ ጋር ወደ ሥራና ቤት ሚኒስቴር ተላለፈ።

ለሽያጭ የመረጡትን ቤት ተከራይቶ የነበረው የውጭ አገር ዜጋ ከኢትዮጵያ በመውጣቱ ለአንድ ወር ያህል ተዘግቶ የቆየ ባዶ በመሆኑና ወይዘሮ ሽዋዬም ከቀበሌው ስሕፈት ቤት አንሥቶ በየክፍሉ ጉዳያቸውን የሚገፉላቸው ሥውር ሰው ስለነበራቸው አንዳንድ፥ ችግር አላጋጠማቸውም። ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ምን የመሰለ ቪላ ቤት ተረከቡ። ወይዘሮ ሽዋዬ አሁንም የዕቃ መግዣ ገንዘብ በብድር ስም ሰጥተዋቸው መስከረም ሳይጠባ የሀገር ምግብ ቤት ተከፈተ።

በጥቂት ቀናት ውስጥ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል «የሀገር ምግብ ቤት» «እኛው ናቸው» የሚሏቸው ሰዎች የሚገናኙበት የወይዘሮ ሽዋዬ ቤት ቅርንጫፍ አከል መናኸሪያ ሆነ።

በጥቅምት መባቻ ሰሞን አንድ ቀን ምሽት የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ልዩ ደንበኞች፥ አቶ ተጫነ ኰሎኔል፥ ደመላሽ ፊታውራሪ ወርቃለማሁና ነጋድራስ አገኘሁ በትንሹ የሳሎን ክፍል ውስጥ ተሰብስበዋል። ከመካከላቸው ውስኪ በጠርሙስ ተሹሞአል። ውስጥ ተሰብስበዋል። ዘለቃ ከቴፕ ሪኮርደሩ አጠገብ ተቀምጣ የቴፕ ክር መራረጠችና አንዱን ስታጒርሰው «እምቧ በይ ላሚቱ» የሚለው ዘፈን አስተጋባ። ይህች ዘፈን በመሶብ ቤትና በታክሲ አካባቢ የሰሞኑ ወረት ሆናለች። ደግመው ደጋግመው እንዳልሰሟት ያህል ሁሉም ከቅኝቱ ጋር ራሳቸውን ማወዛወዝ ጀመሩ።

«እሜቴ ኧረ ይምጡና ይቀመጡ እባክዎ!» አላቸው ተጫን፥ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በማድ ቤቱ በር በኩል ሲገቡ።

«እደርሳለሁ። ዘለቃዬ ኧረ እሱን ሙዚቃ ዝቅ አርጊው!» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተመልሰው፥ ወደ ማድ ቤት እየወጡ። ለሰዎቹ ጥብስ ቢጤ እያዘጋጁ ነበር።

«ጠጡ እንጂ!» አለ ተጫን ብርጭቆአቸውን እየሞላ። ለሰሞኑኡ አስደሳች ወሬ ጠርሙስ ውስኪ የከፈተው እርሱ ነበር። ሻሽመኔ አጠገብ ሃያ ጋሻ መሬት የተወረሰ ቢሆንም ያረባቸው የነበሩትን ከአምስት መቶ የሚበልጡ ከብቶች አሽሽቶ በድብቅ በመሸጥ ብዙ ገንዘብ ስለ ያዘ አዘውትሮ የሚጋብዝ እርሱ ነው።

«ማስተጣት ያስጠጣል» ኰሎኔል ደመላሽ ውስኪውን በሰፊው ተጐነጭው። «ግን እኔ ያልገባኝም ጀርመን ራዲዮና ቢ.ቢ.ሲ. ራዲዮ ወልዲያ ተያዘ ሲል መኪና እንዴት ከደሴ ሊመጣ ቻለ ነው?»

«መንገድ አለመዘጋታቸው ደግ አረጉ ባይ ነኝ። ለምን ሕዝብ ይቸገር!» ሲል ተጫን መለሰ፥ ከውስኪው ጋር ፊቱ በደስታና በተስፋ እየፈካ።

ትንሽ የጥርጣሬ መልክ የሚታይባቸው ፊታውራሪ ወርቃለማሁ ብቻ ናቸው። ታስረው ከተፈቱ ወዲህ የተሰበረ ቅስማቸው በሚገባ አላገገመላቸውም። «እኔ የምፈራው ሁሉም ነገር ወሬ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ነው» አሉ ልባቸውን ለዘፈኑ ሰጥተው።

«ምኑ?» ነጋድራስ አስገኘሁ ኰስተር ብሎ ጠየቃቸው።

«እነዚያ መጣን መጣን ይላሉ። እነዚህ እየበረቱ ይሄዳሉ። በመካከሉ....» ፊታውራሪ ወርቃለማሁ ንግግራቸውን አቋርጠው ተውት።

«ምኑን ነው የበረቱት። ይችን ከተማዋን የሙጥኝ ስላሉ ነው? ስሜነህ እንደላከው መልክት ከሆነ ጐጃምን በሙሉ አስገብሯል» ሲል ነጋድራስ አገኘሁ መለሰ።

«የሚባለው እውነት ከሆነ፥ አሜሪካ መሣሪያ ቢሰጥ እንጂ ራሱ መጥቶ የሚዋጋ ይመስልሃል?»

«ባይመጣስ?» ኰሎኔል ደመላሽ በንቀት ከንፈሩን መጠጠ። «መሣሪያው ከተገኘ አሁን የሚንጫጫ ሁሉ ምን መሰላችሁ? ባንዴ ነው የሚበታተነው። አይተውነው የለ በየካቲት! ወዲያው እርጭ! ምን አለው ብላችሁ ነው የሳሙና አረፋ!» ኮሎኔል ደመላሽ ውስኪ በተጐነጨ መጠን ድፍረቱ እየገነነ ይሄዳል። በጣም ሞቅታ ሲሰማውማ መላ ኢትዮጵያን ባንድ አፍታ ከቁጥጥሩ ሥር የሚያደርጋት ይመስለዋል።

«ብቻ!» ሲሉ ፊታውራሪ ወርቃለማሁን አቋረጣቸው።

«ፊታውራሪ እርስዎ ደግሞ ብቻ...ብቻ....እንዲያው ማለት እያበዙ ሄዱ! ሰልበው ነው የለቀቁዎት ልበል?» ደመላሽ ዓይኑን አጕረጠረጠ።

«እኔ ወርቃለማሁ! ማንን ፈርቼ!»

«ታዲያስ?»

ፊታውራሪ መልስ ሳይሰጡ ውስኪ ተጐነጩ።

በዚህ ጊዜ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል መሶብ አሲዘው ገቡና ብርጭቆ የተቀመጠበትን ጠረጴዛ ወደ ጐን ሆኖ መሶቡ በሰዎቹ መካከል ተሠየመ።

«ለመሆኑ ሰውየሽ ዛሬ ይት ጠፋ?» ሲል ተጫን ዘለቃን ድንገት ጠየቃት፥ የመሶቡ መምጣት ያስታወሰው ይመስል። ተጫን «ሰውየሽ» ያለው ከጥቂት ወራት ወዲህ ዘለቃ ወዳጅነት የያዘችውንና አዘውትሮ በመካከላቸው የሚገኘውን ሰው ነበር። ተጫን በአንድ በኩል እንደ ዘመድ ሊያያት ቢሞክርም በልቡ ስለሚከጅላት እንደ መቅናት ይቃጣዋል። ስለዚህም አነጋገሩ የማናናቅ ቅላጼ ነበረበት። ዘለቃ በበኩልዋ ግን አዲሱን ወዳጅዋን እንደ ብርጭቆ በጥንቃቄ ይዛዋለች።

የዘለቃ አዲሱ ወዳጅ በሌለበት «ትልቁ ዓሣ» እያለች ትጠራው እንደ ነእብረው እንደ ፊተኛው ወዳጅዋ አድብታ ያጠመደችው «መለስተኛ ትልቅ ዓሣ» ነበር።

ውስኪ እንደ ውኃ የሚያስቀዳው የፊተኛው ወዳጅዋ ከገጠር አዋጅ ማግሥት ቅጣቱን ተከናንቦ ድራሹ ሲጠፋ፥ የፍቅር ኀዘን ባይሰማትም፥ በዚያ አካባቢ ሰው መያዝ እንደሚያስፈልገውና እንደሚጠቅም ተገንዝባ ነበር።

የሚጠመድ በመቃኘት ላይ እንዳለች፥ አንድ ቀን አለቃዋን የሚፈልግ ሰው ቴሌፎን ደወለ።

«ለጊዜው የሉም።»

«የት ሄደ? በአስቸኳይ ይፈለጋል?» ደግ የሾመውን ሥራ አስኪያጅ አንተ የሚል እንደዚያኛው ትልቅ ዓሣ መሆን አለበት።

«ለጊዜው አላወኩም። ግን ከየት ነበር? መልዕክት ልቀበል?» ድምፅዋን እንድ እንድፍ ጥጥ አለሰለሰችው። እንደ ወላላ አጣፈጠች። በጆሮ የሚያንሾካሹክ የፍቅር ቁልምጫ ቃና ሰጠችው።

«ከመረጃ ክፍሉ።»

«ውይ?» ድምፅዋን እንደ ማሲንቆ ቅኝት ስልም አረገችው።

«ምነው?»

«ምንም።»

«ታዲያ ምን አስደንገጠሽ?»

«ማ? እኔ? ምን አስደነገጠኝ?» በቀጭኑ ከትከት ብላ ሳቀች። «ብቻ ከእንደዚኢህ ያለ ከፍተኛ ቦታ ቴሌፎን ስቀበል የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለሆነ፥ ትንሽ እንዲያው አለ አይደል?»

«ግሩም ትሑት ጸሐፊ ነሽ።»

«መቼም ኢትዮጵያ እንድትቀድም የተቻለኝን እሞክራለሁ።» አነጋገሩ ከየት እንደ መጣላት አልታወቃትም።

«እሱ ነው የሚፈልገው። ደግሞም ጥሩ ድምፅ አለሽ።»

«አመሰግናለሁ።»

«በቴሌፎኑ ሽቦ በኩል ሌላም ጥሩ ነገር ይታየኛል።»

«ምን ደሞ?» በእጁ የዳሰሳት ያህል የመሽኮርመም ድምፅ አሰማች።

«የለበሽው ቀሚስ ግሩም አረንጓዴ ከፈይ ነው። ደግሞ ልገምት፥ ልገምት ጫማሽ....ጫማሽ -»

«ለጥቂት ተሳስተዋል። ግን ከመስቀያው ነው።» ድፍረቷ ራሷንም አስደነቃት።

«የመስቀያው ጥሩነት ልብሱ ሲወርድ ነው የሚታየው።»

«ውይ! ቀልደኛ ተጫዋች ነዎት።» ጥቂት አቅማማችና በመዳፈር ለጠቅ አድርጋ፥ «ታድያ እኮ አውራጅ ያስፈልገዋል» አለች።

«እሱስ ልክ ነሽ።»

ሁለቱም ተሳሳቁ። የመጀመሪያውን ቁም ነገር ረስተው ለብዙ ደቂቃ ተቀላለ። ተጨዋወቱ። ተዋወቁ። በቀጠሮ መገናኘቱ ቀላል ነእብር።

ይህ አዲሱ ደንበኛዋ፥ እስከ አሁን ድረስ ከፍተኛ ጉዳይ ገና ያልፈጸመላት ቢሆንም ለክፉም፥ ለደጉም፥ በመጠባበቂያነት ይዛዋለች። ከዚህም በቀር፥ ዘለቃን ለብቻዋም ሆነ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል መሶብ ቤት ለሚገናኙ ሰዎች በግቢ አካባቢና በአገሪቱ ተፈጠረ የተባለውን ነገር ሁሉ ይዘከዝክላቸዋል። ሆን ብሎ ምሥጢር ለማውጣትና ለማካፈል ሳይሆን በነገሩ ሁሉ መካከል ራሱ የሚጫወተውን ሚና ከፍ አድርጎ ለማሳየት ብቻ ነው።

«እፍፍፍፍ!» ሲል በረጅሙ ይተነፍሳል - ላቡን የሚጠርግ ይመስል በመዳፉ ፊቱን እየዳበሰ።

«ምን ሆንክ?»

«እኔኮ ግራ የገባኝ አንድ ነፍሴን ከስንቱ ልሆንና ስንቱን ላደርግ እንደምችል ነው።»

«ምን ተፈጠረ?» ጥይቄው አንደ ዋዛ ነው።

መጠጥ ይጋብዛል። የራሱን አሥር እጥፍ ጨምሮ ከሌሎች፥ የሰማውን ራሱ እንደ ሠራው አድርጎ ያወራላቸዋል። «እነማን ናቸው ብላችሁ እንዳትጠይቁኝ። ምሥጢር ነው» ይላሉ በመጨረሻ።

ራሱ በፈቃዱ የሚቀባጥረው በላይ እነርሱም አጥብቀው አይጠይቁትም። እንዳይጠረጠሩ። ምንም ቢሆን የዚያው አካባቢ ሰው ነው። ማመን አይቻልም። ምሥጢር የሚያወራላቸው አውቆ እነሱን ወጥመድ ለማስገባት እንደሆነስ? በበኩላቸው ግን አነጋገሩን እያደነቁ፥ በውስኪ እያሟሟቁ፥ ብዙ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃ ያገኙበታል። የተገኘው መረጃ በአገር ውስጥም በውጭም አገርም ላሉት ዋና ዋናዎቹ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። የስዎች ስምም ሆነ የጐደለው ሊላ ነገር ሁሉ የሚሟላበት የተለያየ ምንጭ ደግሞ አለ።

በውጭም አገር ራዲዮ በተባራሪም ከስሙት ወሬ ጋር በደርግ አካባቢ ምን እንዳለ ለማወቅ ያም ምሽት በታም ፈልገውት ነበር።

«እኔ ምልሽ፥ ዛሬ ሰውየሽ የት ጠፋ?» ሲል ተጫነ ዘለቃን እንደ ገና ጠየቃት።

«እ!» አለች ዘለቃ ከሐሳብ እንደ ነቃች፥ «ዛሬ መንቀሳቀስ አልችልም፤ በሥራ ተጠምጃለሁ ብሎ ደውሎ ነበር።»

«ያው መከረኛ ስብሰባ ይሆናላ!» ሲል ተጫነ ለጠቅ አደረገ።

«ምን ተገኝቶ ይሆን ደሞ?» ሲል ፊታውራሪ ወርቃለማሁ በተለይ ማንንም ሳይሆን በደፈናው ጠየቁ።

«ስብሰባ ካለ» ኰሎኔል ደመላሽ አንገቱን ወደ ጣሪያው አንጋጥጦ የሚያስብ መስለ። «ምናልባት ከወሎና ከቤጌምድር ሁናቴ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ማወቅ አይከፋም ነበር።»

«እስቲ ራዲዮ ክፈቱ። ሁለት ሰዓት ሊሆን ነው። ያወራው ይሆናል» አሉ ነጋድራስ አገኘሁ።

«ኤዲያ! ቢሆንስ ተሰበሰቡ ተበተኑ እንጂ ምክንያቱን መች ይናገራል።»

ዘለቃ ወደ ራዲዮው አመራች።

«እባክሽ ተዪው!» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል።

«ምናልባት ብንሰማው። መግለጫም ይኖር ይሆናል» አሉ ፊታውራሪ እያመነቱ።

«እርስዎ ደሞ የፍየል ወጠጤ ቢዘፈንብዎ - ቢዘፈንብቆ አይሰለችዎትም?» አሳቸው ተጫን በማሽሟጠጥ።

«አንተስ ከሰለቸህ እንደ ወንዶቹ ወጣ አትልም ነበር።»

«ከዚሁ እየሠራሁ ነው።»

«እስቲ አትጨቃጨቁ» አለ ደመላሽ በእልቅልፍ አኳኋን፥ «ግዴለም እንስማው። ጆሯችንን አያቆሽሸው። ማንኛውንም ነገር ማወቁ አይከፋም።

«አሁን የምሽቱን ዋና ዋና ዜናዎች እናሰማችኋለን» ሲል የራዲዮ ዜና አንባቢው ጀመረ። የሀገር ውስጥና የውጭ አገር ዜናዎችን ሲያሰማ እምብዛም ጆሮአቸውን አልሰጡትም። «አሁን ዘግይቶ የደደረሰን ዜና!» ሲል ሁሉም ጆሮአቸውን አቀኑ። «በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለውን ለውጥ ለማደናቀፍ በወሎ ክፍለ ሀገር በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወረ ፀጥጣ ሲነሣና የውንብድና ተግባር ሲፈፅም የነበረ ፊታውራሪ በላይ ዘለለውና ግብረ አበሮቹ ባለፈው እሑድ ከኩታ - በር ወረዳ በገበሬ ማኅበር አባላትና በፀጥታ አስከባሪዎች ተደምስስዋል።» መብረቅ እንደመታው ሁሉም ክው አሉ።

«ሊሆን አይችልም» ሲል ተጫነ ጮኸ።

«እስቲ ዝም በል ይጨርስ!» ኮሎኔል ደመላሽ ተቆጣ።

«ከክፍለ ሀገሩ አስተዳደር እንደተገለጸው በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ሹመቱን መከታ በማድረግ ሕዝቡን ሲበዘብዝብና መሬት ሲነጥቅ የኖረው በላይ ዘለለው የገጠር መሬት የሕዝብ ያደረገው አዋጅ እንደ ወጣ ከግብረ አበሮቹ ጋር በርሃ በመግባት፥ የወሎን ክፍለ ሀገር ሕዝብ ሲዘርፍ ሲያሠቃይ እንደ ነበረ ታውቋል።» ሳይታወቅባቸው ሁሉም ውስኪያቸውን እያነሡ ከነበሉት። «ከበላይ ዘለለው ጋር ከተደመሰሱት ግብረ አበሮቹ መካከል ቀድሞ የአገር አገዛዝ ይባል የነበረው የመሬት ይዞታ ኃላፊ ሆኖ በሕዝብ እንባ ሲቀልድ የኖረው ማናዬ ሽዋሉል የተባለው ወንበዴው» ብሎ ራዲዮኑ ሳይጨርስ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ውጋት ከሁለት እንደ ሰነጠቀው «እእህ!» ብለው እንደ ማጓራት ቃጣቸው።

«ምነው?»

«ምን ሆኑ?»

ሰዎቹ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከማናዬ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አያውቁም ነበር።

በመደንገጥና በመገረም ሁሉም ዓይናቸውን ጉልጉለው እንደ መነሣት አሉ። ዘለቃ ከመቅጽበት ደርሳ ሁለት እጅዋ ዞሮ የማይሞላውን ትከሻቸውን እንደማቀፍ በማድረግ ኃይለኛ ትንታ አለባት» አለች። ተደጋግፈው ወደ ሁለተኛው ሳሎን ወስደው አሳረፉዋቸው። «ግዴለም ሂዱ ትንሽ አረፍ ካለች ይሻላታል» አለቻቸው ዘለቃ።

«ምንድን ነው ያለው ራዲዮው ዘለቃ?› ሲሉ ጠየቁ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሰዎቹ ከወጡ በኋላ።

«ምንስ ቢል ያለፈው አለፈ። የፈሰሰ ውኃ እንግዲህ አይታፈስ።»

«እኔ ነኝ፤ እኔው ነኝ ለዚህ ያበቃሁት» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በማቃሰት።

«ምን አረግሽ አንቺ?»

«እኔ ባልወተውት፥ እስቲ እንደ ሰዎቹ ወንድ ይውጣህ ብዬ እኔ ባላስጨንቀው፣ እነ አይዞህ ባልለው እሱማ መች ከጅሎት ነበር። የሄደውስ ቢሆን እየቀፈፈው አልነበር?» እያሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አቃሰቱ።

«ከዚህ ቢቆይ ኖሮስ፥ እንደ ጥጃ አሥር ጊዜ መቀፍደዱ ይቀርለት ነበር? አንድ ፊቱን ይሻለዋል። »

«እሱንማ ብዬ ነበር። ግናስ፥ ግናስ፥ እኔ ቁም ስቅል ባሳየሁት እንዲያ እንደቀፈፈው ሂዶ የትም ተደፍቶ ይቅር? ደፊህን ይድፋው!» ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አልጋቸውን ያሞቀላቸው፥ ገላቸውን ያዋዛላቸው ትዝታው መጣባቸውና ተንሰቀሰቁ።

«እህ! ምን እያልሽ ነው። ሰው ምን ይልሻል?» ስትል ዘለቃ ገሠፀቻቸው።

«እውነትሽን ነው ልጄ» አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በንፍረቃቸው መካከል፥ «ደረት ጥሎ ለማልቀስ ኀዘን፥ ለመቀመጥ የማያመች ነው። ምኔ ሞተብኝ ብዬ? እንዲያው በሆዴ እህህ! እያልኩ መቻል ነው እንጂ።» ወዲኢያው ቀጠል አድርገው ከንፈራቸውን እንደ መንከስ አሉና «ብቻ ግዴለም። ደምህ ደመ - ከልብ ሆኖ ቢቀር እኔ ዘርፈሽዋል አይደለሁም» ሲሉ ዛቱ።

በሌላ ክፍል ሦስቱን ሰዎች በድንጋጤ ከአቀረቀሩበት የቀሰቀሳቸው ደመላሽ ነበር።

«ምነው መብረቅ የመታችሁ መሰላችሁ?»

«ከመብረቅም መብረቅ! መርዶ ነው እንጂ። በራዲዮ በደብዳቤ ያንን ያክል የተፎከረበት ይኸው ሆኖ ቅረ ማለት ነው?» ፊታውራሪ ወርቃለማሁ በአዘኔታ ራሳቸውን ነቀነቁ።

«ይኸ ይኸ ነው የሚያበሽቀኝ!» ሲል ደመላሽ በተራ ተመለከታቸው።

«ምኑ?» ሲሉ ፊታውራሪ ጠየቁ፥ ፈራ ተባ እያሉ።

«የሁላችሁም ነገር!» ሲል ደመላሽ አቋርጦ ተወው።

«አዎ! የቻልነውን ያህል መቼም ገንዘብ ያስፈልጋል ሲባል እንሰጣለን። ውጤቱ ግን እንደዚህ ከሆነ በእውነቱ ዋጋ የለውም» በማለት ነጋድራስ አገኘሁ ለጠቅ አደረጉ።

«አሁንም ልክ አደላችሁም። እናንተው እንደ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተደናግታችሁ በቀላሉ መፈታታችሁ ደግሞ ይብሳል። አንደኛ የሰማነው የእነርሱ ራዲዮ ያለውን ነው። እነ በላይ ዘለለው ቢሸነፉስ ምን ያስደንቃል። የጦር ልምድ የላቸው በዚህ ላይ የሥፍራ አመራረጥ ስሕተት ተደርጓል። ወሎ የሚያመች አልነበረም።»

«ሌላው ክፍለ ሀገር ቢሆን እኮ እስከዚህም አላቀፈንም» አሉ ፊታውራሪ ወርቃለማሁ።

«ቢሆንም ቢሆንም» ሲል ለጠቀ ኮሎኔል፥ ደመላሽ።

«ወሎ ግን እንዳልኩት፥ እውነቱን ለመናገር አልጋ ወራሽም ቢሆን ለክፉ ቀን ይሆነኛል ብለው በሚገባ አልያዙትም ነበር። የውጭ ገንዘብ መለመኛ መሆኑን ባያውቁም፥ በኃይለኛ ፕሮፓጋንዳም ሊሰማ ይችላል። ይህንን ይህንን ሁሉ ሳይ ነው እየበሸቅሁ፥ አዲስ አበባ ሆኜ ከምሠራው ይልቅ ወደ ጫካ ገብቼ ላዋጋ፥ ወይም እንዲያው ከኢትዮጵያ ድንበር ወጥቼ በብሰባቸው ላይ እየተገኘሁ በሚገባ ላስረዳቸው የሚል ሐሳብ የሚመጣብኝ።» ኮሎኔል ደመላሽ ንግግሩን ሲጨርስ ውስኪውን በሰፊው ተጉነጨለት።

ጠርሙስ ውስኪውን ያወረደው ተጫን ከሌሎች ድፍረት ተሰማው። «ይህ - ያ ሆነ ተባለ። አንተም ይህ ቢሆን፥ ያ ቢደርግ አልክ። ጥሩ። ግን እንደ ዘመኑ አነጋገር የጉዳዩ መደምደሚያ ምንድን ነው? ወይስ እንዲሁ ዝም ብለን ማየት መጠበቅ ነው?»

«ገና ነው፤ በጊዜው ይደመደማል።»

«እስከ መቼ? እኛ እኮ አለቅን።»

«ባሕታውያኑ አምስት ሰዓት ይገዛል ነው የሚሉት አሉ» ሲሉ ፍታውራሪ ወርቃለማሁ ተናገሩ።

«ገና አራት ዓመት! ምኑን ተረፍነው?»

«ይኸው። አንዱ የሚያበሽቅም ይኸው ነው። በቀላሉ ነገር ካልሆነልን ወዲያው እንፍረከረካለን። እነርሱ እንዳሉት የራት ግብዣ ካልሆነ፥ አለመሆኑን እኛም እናሳያችዋለን። ወይስ ሌላ ምርጫ አለ?» ደመላሽ ሦስቱንም በየተራ ተመለከታቸው።

«እሱማ ነው!»

«ሲሆን ሲሆን ነገ የሚሆነው አይታወቅም!»

የመበረታቻ መልሱን ተቀባብለሉት።

በማግስቱ ሁለት ዜናዎች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ወጡ። ከአማኑኤል ሆስፒታል አካባቢ የተገኘው አንደኛ ዜና፥ በወደቀው መንግሥት ጊዜ ብዙ ሰዎች የአእምሮ መታወክ የሚደርስባቸው፥ በማኅበራዊ ኑሮ መመሳቀል መሆኑን ገልጾ አሁን፥ በተሻሻለ ሕክምና የብዙዎቹ የአእምሮ ጤንነት በመሻሻል ላይ እንደሚገኝና ከተሻለ ሥርዓትም መስፈን የተነሣ የአእምሮ መታወክ እንደሚቀንስ

ያመለክታል። ሁለተኛ ዜና በአራት ኪሎ አጠገብ ከሚገኘው ጅምር ሕንፃ ከአራተኛ ፎቅ ላይ ውድቆ ስለ ተፈጠፈጠ ወጣት ነው። ዜናው ቦጋለ ዘለቀ የተባለው ይህ ወጣት፥ ከዘመቻ የቀረ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ መሆኑን ይጠቁማል። ከኪሱ ውስጥ ታረቀኝ ለተባለ ጓደኛው የጻፈው ደብዳቤ መገኘቱን ታረቀኝ፥ በወሎ ክፍለ ሀገር ዘምቶ በወንበዴዎች የተገደለ ታጋይ ወጣት መሆኑን፥ ቦጋለ ዘቀም ሕይወቱ ተርፎ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል በሕክምና ላይ መገኘቱንና የአደጋው ሁናቴም በመጣራት ላይ መሆኑን ይገልጻል።

## ፫

«አውጡኝ አውጡኝ እባካችሁ» አለ ሙሔ እያቃሰተ። ከተኛበት የጠፍር አልጋ ዙሪያ፥ ካሣሁን፥ ዘይኔ ያይኔ አበባ ከበውታል።

የሙሔ ትንፋሽ እንደ ጋለበ ፈረስ እየገፋ ይወጣል። ካሣሁን ግንባሩን በመዳፉ ዳስሶ ትንሽ አሰበ። «አባዬ የት ነው የምትወጣው?» ሲል አልጋ ልብሱን በእጁ እየደባበሰ ጠየአ።

«አውታኝ ነው የምልህ!» ሙሔ እየቃሰተ ከአንገቱ በላይ ቀና ለማለት ሞከረ። መልሶ ወደቀ። እያቃሰተ ተነፈሰ። «ልጄ ካሣሁን ፈቃዴን፥ ፈጽምልኝ። አየር ልይ። ሰማይ ልይ። መሬት ልይ። ታፍኜ አልሙት።»

«ሞትን ምን አመጣው? ወትሮውንም ቢሆን ሐኪም ቤት አልቆይም ብለህ ሳትድን መምጣት አልነበረብህም። አሁንም ሐኪም ቤት ብንሄድ ነው የሚሻለው። አዝማቾቹ አሉ። ከለመን መኪና ያመጡልናል። ስለዚህ ሄጄ ልጠይቃቸው።»

«በከንቱ ሰውን አታስቸግሩ። እኔ እንደ ሆነ ተመልሼ ሐኪም ቤት የምሔድበት ምህኛት የለም» አለ ሙሔ እያቃሰተ። «የዚህ የዚህ በፊቱንስ መች እመጣ ነበር?»

ሙሔ ወደ ቤቱ ካልወሰዳችሁኝ ብሎ ያስቸገረው ሆስፒታል ሳምንት ያህል እንደ ተኛ ነበር። በመሆንኛ ተራራ ላይ በጥይት ከተመታ በኋላ፥ ነፍሱን ያወቀው ደሴ ሐኪም ቤት ተኝቶ በሁለተኛ ቀን ነበር። ሐኪሞች የተቻላቸውን ያህል ሕክምና ቢያደርጉለትም የሕመም ሥቃዩ በመሻል ፈንታ እየባሰበት ሄደ። ፋታ የማይሰጥ ሥቃይ። ጀርባ የማያላውስ ቀስፎ የሚይዝ ሥቃይ። በጥይት የተመታበትን ቦታ ሲረሳ ከንቱ ልፋት መሆኑ ተሰማው። ሆስፒታል በተኛ በአምስተኛ ቀን ሐኪሙን ጠየቀው። «አዬ ሐኪም። እኔ በማይጨውም በአምስቱ ዓመት አርበኝነት ብዙ ጦር ሜዳ ላይ ውያለሁ። ሰው ሲሞት ቆስሎ ሲድን አይቻለሁ። የእኔ ዓይነት ቊስለኛ ግን አይድንም። የጀርባ አጥንት አከርካሪውን የተመታ። በከንቱ ነው የምትደክሙት።»

«አይዞዎት ይድናሉ» አለ ዶክተሩ፥ ነገሩን ያቃለለ በመምሰል።

«የለም በእግዚአብሔር ይዝዎታለሁ እውነቱን ይንገሩኝ።»

«ይድናሉ አልኩዎት!»

«አየ ሐኪም! ሞትን የምፈራና የምደንግጥ መስሎት ነው። አይጨክኑ። እኔ ከሞት ጋር ነው የኖርኩት። በሞት መካከል። መቃብር የተፋኝ ስለሆነ ሞትን እንግዲህ የምፈራ አይደለሁም። ስለዚህ ቊርጡን ይንገሩኝ። እንዳሰኘኝ ደስ እንዳለኝ አኳኋን እንድሞት። በእግዜር ይገፎታለሁ ይንገሩኝ።»

ሐኪሙ በሐሳብ ተጨነቀ። በሙሔ ሁናቴም ተደነቀ።

«ለምን ማወቅ ገለጉ?»

«የነገርኩዎት። ባሰኘኝ አኳኋን ሞትን እንድቀበለው።»

ሐኪሙ በሐሳብ ጠጉሩን አከከና፥ «የእኛ ሐኪሞች ዓላማ በተቻለ መጠን ሕመምተኛ እንዲድን መጣር ነው። እስከ መጨረሻው መታገል ነው። እርስዎም የመዳን ትንሽ ተስፋ ሊኖርዎት ይችላል። እንዳሉት አከርካሪ አጥንቱ የተሰበረ ቊስለኛ ማዳን እንደ ተአምር የሚቈጠር ነገር ነው። ምናልባት ቢድኑም ከወገብዎ በታች ሰውነትዎ አይሠራም።»

«ሽባ እሆናለሁ ማለትዎ ነው? ሰው እየተሸከመ ጓሮ የሚያወጣኝ ወይም ከተጋደምኩበት ከሽንቴና ከዓይነ ምድሬ ጋር የምለወስ ሽባ ሆኜ እቀራለሁ ማለት ነው። ከመሞት በምን ይሻላል? ኧረ እንዲያው ሞት ይመረጣል!»

ከዚህ በኋላ በምንም ዓይነት ሆስፒታል አልቆይም፥ አልታከምም ብሎ የሆስፒታሉን ሠራተኛ ሁሉ ስላልጨነቀ በአውቶሞቢል ቤቱ ድረስ አምጥተው አስተኙት። የሥቃይ ማስታገሻ ኪኒን ተውለት።

ሥቃዩ በበረታበት ቊጥር ኪኒዒኑን እየዋጠ መንፈሱ ተረጋግቶ፥ «አይዞአችሁ። ምንም አልሆን። ደህና ነኝ። ኧረ እሱ ምስጋና ይግባው» እያለ የተገላብጦሽ እነዘይኔን ሲያጽናና ሰንብቶ ነበር። ከአንዴም ሁለቴ ሕፃኑን ለማየት ያለውን ጕጕት ገልጾላቸው ነበር።

ሙሒሀ እያቃሰተ ዓይኑን ክድን አድርጎ ፈገግታ አሳየ። «እኔኮ አልሞትም። አልጣሽ ዘንዳ ነው የምሄደው። እናታችሁ ዘንዳ። ታዲያ ደስ ብሎኝ ለመሄድ ነው የምፈልገው። መንገዱን እያየሁ። ኧረ ወጡኝ! አውጡኝ ፈቃዴን የምትፈጽሙ ከሆነ።»

ከቤት ውስጥ ያሉት ሁሉ እርስ በእርሳቸው ተያዩና ሳይነጋገሩ በሐሳብ እንደ ተሰማው ሁሉ፥ ሙሔ የተኛበትን አልጋ በአራቱ ማዕዘን አንሥተው ማንቀሳቀስ ሲጀምሩ ሙሔ ተወራጨ። «አውጡኝ አልኳችሁ እንጂ ከነ አልጋው ተሸከሙኝ አልኳችሁ? አልጋ አልፈልግም።»

«ታዲያ እንዴት ነው ኮ?» ሲል ካሣሁን በመጨነቅ ጠየቀ።

«መሬቱ ላይ ነው ማረፍ የምፈልገው። ንጣፍ ካለ አድርጉልኝ። ከዛፍ ሥር። ምንድን ነው ችግሩ? አልጣሽም መሬት ውስጥ ነው ያለችው። እኔ ስንኳ ክብር ማዕረግ አግኝቼ ነው። ካሣሁን አውጡኝ እኮ ነው የምላችሁ። ነፋስ ይምታኝ። አገር ልይ፤ መሬት ይንካኝ!»

ከግራሩ ዛፍ ሥር ጕዝጓዝ ነስንሰው ጀንዲ አንጥፈው በዚያ ላይ ጨርቅ ደርበው አስተኙት። ተጋድሞ ትንሽ እንደ ቆየ። «ካሣዬ እስቲ ቀና አርገኝ። ስተኛማ አንድያውን እተኛለሁ» ሲል እያቃሰተ ተናገረ። ጀርባውን ከግራሩ ግንድ አስደገፈው ሁለቱ ሴቶች ከጐንና ከጐን ተቀመጡ።

ሙሔ ሰመመን እንደ ያዘው አንድ ጊዜ ዓይኖቹን እየከደነ፥ ሌላ ጊዜ እየገለጠ አካባቢውን በሙሉ ያስተውላል። ይቃኛል። ይማትራል። በምዕራብ በኩል ያዘቀዘቀችው ጀንበር አገር ምድሩን በሚያጥበረብር ጨረር አልብሳዋለች። ዝናም የቋጠሩ አጥቢያ ደመናዎች በመካከል እየገቡ ሰፋፊ ጥላቸውን እየዘረጉ ያልፋሉ። ቀድሞ የተዘራውን አፍርቶ ወይባ በመሰለበት፥ ዘግይቶ፥ የታሰረው አሽቶ ገና አረንጓዴ በሆነበት ማሳ ላይ አንድ ጊዜ ፍንትው ሌላ ጊዜ ደብዘዝ የሚለው የፀሐይ ብርሃን ሲለዋወጥበት ዓይን የሚያፈዝዝ ልብ የሚመስጥ ልዩ ኅብረ ቀልም መልክ ይሰጠዋል። የሠዓሊ ብሩሽ የነደፈው ሥዕል ይመስላል። በዚህ ላይ በዝናም እርግዝና የወረዛ አየር፥ የሕይወት መዓዛ አለው። ሙሔ ለረጅሙ ጊዜ አካባቢውን የራሱንና የጐረቤቶቹን ማሳ ያለበትን ማዶውን ከተመለከተና እያጠረ በሚሄደው ትንፋሹ የወረዛውን አየር ከሳበ በኋላ ዓይኑን፥ ወደ ካሣሁን ወደ ዘይኔና ወደ ያይኔ አበባ መለሰ። አይቶ እንደማይጠግባቸው ሁሉ ዓይኖቹን አንከራተተባቸው። በልቡ ፍቅር፥ በዓይኑ ስስት ዳበሳቸው።

«ለመሆኑ ሰዎች ሁሉ የት ሄዱ? አይዋ ከበደስ? ሌሎችስ? እንደዚህ ነው የምሸኘው? ጥራቸው ይሰናበቱኝ።»

«አባባ ለምን እንዲህ ትሆናለህ? ምንም አትሆንም። ትድናለህ! ወትሮውንም ሐኪም ቤት ብትቆይ ኖሮ እስከ አሁን ይሻልህ ነበር።» ዘይኔ ስትንሰቀሰቅ፥ ሳትወራጭ እንባዋ እንዲህ ይወርድ ጀመር። ጨፉ ላይ እንደሚንጣለለው የቦርከና ወንዝ በእርጋታ፥ ጥልቀት።

«ይልቅ አንቺ ምን እያልሽ ነው?» የሙሔ አነጋገር የተግሣፅ ሳይሆን የማባበል ነበር። «ያንን ሁሉ አልፈን፥ የአሁኑ ደግሞ የሚያዘፍን እንጂ የሚያስለቅስ ነው? እናትሽን እንዴት እንደቀበርናት ትዝ ይልሽ የለ?»

ሙሔን አንድ ነገር ጉሮሮውን ተናነቀው። «እንደ ከብት ልጆቻችንን የትም እየጣልን አልነበር እንደ ከብት የተበተነው? ዋጋና ክብር ያጣነው? ሕፃኑን ወንድማችሁን የሆነውን ይሁን እሱ ባወጣ ያውጣው ብዬ አይደል መንገድ ላይ ባዳ ዘንድ የጣልኩት። ግን እግዜር ይስጣቸው ደህና ይዘውታል። ከተያያችሁና ከተጠያየቃችሁ ይበቃል። አንዴ በእግዜር ፊት ሰጥቻችዋለሁ። ታዲያ ያንን ሁሉ አልፈን አሁን እናልቅስ? አይገባም። እናንተ እያላችሁ - እናንተ ካላችሁ፥ እኔ አልሞትም። አልሞትኩም። ዘር ተቀብላ መልሳ ሕይወት ሰጭ እህል እንደምታፈራ መሬት እናንተን አፍርቻለሁ። ሕይወቴ በሕይወታችሁ ይተካል። የወለደ አይሞትም። ያርፋል እንጂ። እርግጥ የልጄን ልጅ በዓይኔ ባየው ደስ ባለኝ» አለ ሙሔ፥ በደከመ ፈገግታ ወደ ዘይኔ እየተመለከተ። «እስካሁን ፈቃዱ ስላልሆነ አልማርረውም። እሱ ባለ ጊዜ ይሆናል።»

ካሣሁን ይህንን ሲሰማ ሰውነቱን ውርር አደረገው። ዘይኒኤ ልጅ እንድትወልድ ፍሬ ልሰጣት የማችል መሆኔን ልንገረው? የሚል ሐሳብ ውልብ አለበት። ዳሩ በጭንቀቱ ላይ ኀዘን መጨመሩ ምን ይረባል? ቢሞትም ከነ ተስፋው መሞቱ ይሻለዋል፥ አለ በልቡ።

ጀንበሯ በቆዳ ዳገት መጥለቅ ስትጀምር በእርሻ ሥራ የዋሉት የመንደሩ ሰዎች ሁሉ መምጣታት ጀመሩ። እንደ ቀድሞው፥ ጥጃ እናቷን፥ ወይፈን ጊደሯን፥ ኮርማ፥ መሲናዋን አለሌ ባዝራዋን፥ የሚጠሩበት ጩኸት አይሰማም። እንደ ቀድሞው ከብት ውጭ ሲግጥ አያመሽም። የሰው አስከሬንና የከብት ሬሣ በገፍ የለመደው ተኩላና ጅብ እየጠበቀትም አልተቻለም። ዓይን በዓይን መንጠቅ ይቃጣዋል። ይህም ሁሉ ሆኖ ሰው አልተከፋም። አንዱ በዶማ ሌላው በመኰትኰቻ የባሰበት በቆላፋ እንጨት እየኳተነ፥ ያለው ከሌለው እያቀናጀ አንዱ ለሁሉም፥ ሁሉም ለአንዱ በየተራ በሥራ እየተሠማራ ውሎ ሲመለስ

ደስ እያለው ዘማቾች እንደ ነገሩት ኅብረቱን፥ አንድነቱ መተሳሰቡን በልዩ ልዩ ዜማ ይገልጻል። ችግር ያጠወለገው ፊት ስንኳ ልዩ የፈገግታ ለዛ ማሳየት ጀምሯል።

ከበደ፥ ቢልልኝና አሮጊቷ ሥራ ውለው ወደ መንደር ሲመለሱ ግራ፣ በመጋባትና በመደነቅ በዛፍ ሥር በሙሔ ዙሪያ ተሰበሰቡ። «አብዳችኋል ልጆች? ቊስሉ ነፋስ ይገባው የለም? ወይስ በአንድ ቀን ዳነ ልትሉኝ ነው?» ሲል ከበደ ጠየቀ።

«እሱው ነው ካላወጣችሁኝ ብሎ ያስቸገረ» ስትል ዘይኔ መለሰች፥ እንባዋን እየጠራረገች። ለአንድ አፍታ ሁሉም ዝም አሉ።

«ምን እንደ ጉድ ታዩኛላችሁ?» ሲል ሙሔ ጠየቀ፥ ሁሉም በየተራ እየቃኘ።

«ያልተለመደ ነገር አመጣሁባችሁ? አዎ፥ ሰው ከሞት ጋር ጣዕር ስገጥም፥ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል። እኔኢ ግን ልዝናና፥ ነፋስ ይምታኝ ነው የምለው። ታዲያ ጣዕር እኮ የሚያስጨንቀው አልሞትም ብሎ ለሚታገለው ነው። የደረሰ ቀኑን አልቀበልም ሲል። እኔ ግን ለየትኛው ዕድሜዬ ነው ከቀነ ቀጠሮዬ ጋር የምሟገተው። ክፉውንም ደጉንም አይቼዋለሁ። ትዝ ይልሃል አይዋ ከበደ፥ ከዚህ ዛፍ ሥር ተቀምጠን፥ ወቶሞቢል ወደዚህ ሲመጣ የተመለከትን እንደሆነ እኒያ መናጢ ሲትዮ መጡ እያልን እንዴት እንሳቀቅና መግቢያ ቀዳዳው ይጠፋን እንደነበር? አሁን ግን አሥር ወቶሞቢል ቢንጋጋ ሥጋትም የለብን። የፈሰሰው ደሜ፥ ለተረፉት ልጆቼ የጉልተኛ የትክለኛ፥ የጭቃ ሹም፥ የምስለኔ ዓይን ሳይገላምጣቸው፥ ጉስጉሻው ሳይበበር ውድማቸው ሳይመዘበር ከብታቸው ሳይነዳ ያለ ሥጋት እንዲኖሩ ካበቃቸው እኔ፥ አልሞትኩም ባይ ነኝ። እርግጥ አሁን ከብትም እህልም የላቸውም። ግን ጤንነቱን ከሰጣቸው ላባቸውን ካንጠፈጠፉ ያገኙታል። መሬታችን ለጋስ ናት። ላቡን ለሰጣት፥ እጥፍ ድርብ አድርጋ ነው የምትከፍለው። ስለዚህ ነው ደስ እያለኝ ወደ አልጣሽ ዘንድ የምሄደው። እናንተን ወንድሞቼንም የምለምነው መቃብሬን ከጐንዋ እንድታደርጉልኝ ነው።»

አነጋገሩ ልባቸውን ሲነካው የቀብር ነገር በማንሣቱ ደግሞ ሁሉም እንባ እየተናነቃቸው ዓይናቸውን በጨርቃቸው መጠራረግ ያዙ። ዘይኔ ተንፈቀፈቀች፤ ካሣሁን ጥርሱን አፋጨ፤ ከበደ አገጩን በመዳፉ ደግፎ በጠሊቅ የትካዜ ባሕር ውስጥ ሰመጠ። እንደ ሰመመን ጭልጥ አድርጎ የሚወስድ ትካዜ።

«ምን ሆናችሁ እናንተ ሰዎች። ደስ ብሎኝ እንድሄድ አትፈቅዱም፥ ወይስ የእኔን ሆድ ለማባባት ነው?» ሙሔ በደከመ አንደበቱ ኰስተር ብሎ ለመናገር ሞከረ።

«ምንም አትሆንኮ አባዬ» አለች ዘይኔ በልቅሶ፥ ሲቃዋ መካከል።

«አዬ ልጄ! እናትሽ ስትጠራኝ ይታወቀኛል። ደስ እያለኝ ነው እሷ ዘንድ የምሄደው። እናንተን ወንድሞቼን» ሙሔ ወደ ጉረቤቶቹ ዘወር እያለ፥ «የምጠይቃችሁ ሌላ ነገር ቢኖር እነዚህን ልጆቼን እንደ ልጆቻችሁ አድርጋችሁ እንድትታዩልኝ ነው። አንተም አይዋ ከበደ የአደራ ልጄን በአደራ ሰጥቼሃለሁና በሚገባ ያዛት። ይኸው በጓደኞችህ ፊት ነው አደራዬን የሰጠሁህ።»

«ኧረ ግዴለም ለሱ» አለ ከበደ፥ በአንጀቱ ከውስጥ እየተለዋወሰበት።

«ከዚህ በተረፈ ምን የምነገራችሁ ነገር አለ?» ሙሔ ዓይኑን ከደን አድርጎ ጥቂት አሰበ። «ሰው የለፋበትን መዝረፍ የለመዱ እነዚያ መናጢዎች መቼም አይተኙምና ላባችሁ ለሚፈስበት መሬ፥ ለክብራችሁ ዝንጉ እንዳትሆኑ። ለካሣሁንም የምሰጥህ ምክር ይኸው ነው። ዘር ካልተረፍክልኝ ግዴለኝም። ለክብርህ ለነጣነትህ ስትል። ከዚያ ወራዳ ኑሮ የከፋ ሞት የለምና። ስለይህም ነው እንደኔ ላለው አይለቀስለትም የምለው።»

ወንዶቹ የሚያደርጉት ሳይታወቃቸው በመስማማት አንገታቸውን ነቀነቁ።

«እንግዲያውስ» አለ ሙሔ ካሣሁንን በፈገግታ እየተመለከተ። ዱሮ ክራር መጫወት ትወድ ነበር። እስቲ አንጐራጕር።

«አሁን ክራር የት አለኝ አባዬ?» ሲል ካሣሁን መለሰ፤ ስሜቱ ግራ ተጋብቶበት።

«ወቸው ጉድ፥ ወሎም ክራርና ማሲንቆ ይጣ?» ሙሔ እንደገና ትካዜ የገባው መሰለ።

«የአይዋ ደሴ ክራርኮ ነበረች።» ከበደ ሲናገር አልታወቀውም።

«አዬ አይዋ ደሴ! ይህንን ጊዜ ቢያዩት ስንኳ ምን ነበረበት?» ሙሔ ከንፈሩን መጠጠ። «ካለች አምጣት። ባለ ቤት የላት እንግዲህ» አለ ሙሔ ቀጥሎ።

ከበእ አሁንም ምን እንደሚሠራ ሳይታወቀው እንደታዛዥ አሽከር እየተቻኰለ ተዘግቶ ወደ ከረመው የአይዋ ደሴ ቤት ሄዶ ጢስ የጠጣች ክራር ይዞ ተመለሰ።

ካሣሁን ጆሮውን ደቅኖ በማዳመት በባቲ ቃኝና ቀስ ብሎን ያንጐራጕር ጀመር።

ኧረ ገለሌ ኧረ ገለሌ፥

ኧረ ተው ገለል ኧረ ተው ገለል፣

መለቃለቂያው ደም ራጨቱ፥

ገለሌ ምሳው ፋጨት ራቱ፥

በርክና ማዶ ከሆነ ቤቱ፥

ይብላኝ ለናቱ።

ተው ሳበው ሳበው ሳበው መሸብኝ፥

የጆቢራ ራት ግብር አለብኝ።

ኧረ ተው በለው ፈጥነህ ተራመድ፥

ተደበላልቋል ወዳጅ ከዘመድ፥

ተደበላልቋል ወዳጅ ከዘመድ።

እሰዬ ጀግናው ደጋግመህ በለው፥

ፈሪን ይግረመው::

ሰንጋው ምን ይበል ጋላቢ ሲያጣ፥

ጦሩ ምን ይበል ወርዋሪ ሲያጣ፥

አትስጡት ለሰው ጀግና እስኪመጣ::

እሰዬ ጀግናው ደጋግመህ በለው፥

ፈሪ ይግረመው::

ደሞ ገለል፣ ደሞ ገለሌ፥

ያያቶችህ ስም ደሞ እንዳይጠፋ፥

ያባቶችህ ስም ደሞ እንዳይጠፋ፥

ዋርካ ፈረስህ ስሙ እንዳይጠፋ፥

ፈጥነህ ግጠመው አትቊረጥ ተስፋ::

«እንዲያ በል! እንዲያ በል፥ እፎይ! ደስ ብሎኝ ልሙት!» አለ ሙሔ ያለ - የሌለ የእስትንፋስ ኃይሉን አጠራቅሞ:: ዋርካ ዱሮ ዱሮ፥ ማይጨው የዘመተበት ፈረሱ ነበር:: ፈረስ ብሎ ዝም ነበርና ከማይጨው የእሳት አፈና አውጥቶ ኮረም ሲደርስ ከሥሩ ተመትቶ ሲወድቅ አርበኝነት የገባው ግላሱን ብቻ ይዞ ነበር:: ዋርካ የማስረሻ እናት የሕግ ሚስቱ ከባንዳ ጋር ኰብልላ መሄድዋን ከአጣልሽ ጋር መገናኘቱ ያስታውሰዋል:: ከዚያ በኋላማ ያደለበውን ሰንጋ የአልጋ ወራሽ ባለሟል ሲነዳበት፥ ምስለኔና ጉልተኛ ሙክቱንና አላባውን ሲወስድበት ስንኳ የፈረስ ጌታ ለመሆን ቀርቶ ወደል አህያ ሊያተርፍ አልቻለም:: በከፋውም በተደሰተም ቊርጥ ዋርካ ፈረሱን ማውሳት አንድ ዓይነት ጽናት፥ አንድ ዓይነት ኵራት፥ አንድ ዓይነት አለኝታ ለቀድሞ ትዝታው ሲሰጠው ቆይቷል:: ካሣሁን ይህንን የተገነዘበው በዳገታማ ሚካኤል ዘይኔን ተድሮ ገና በጫጉላ ቤት በነበረበት ጊዜ ነው:: እንደ ዋዛ አንድ ጊዜ የሚዜውን ክራር አንሥቶ ሲጫወት::

ካሣሁን እንጕርጕሮውን ገታ አድርጎ ክራሩን ወደ አምባሰል ሲቃኝ በዚያ ፈዝዘው የነበሩት ሰዎች ሁሉ እንደ መባነን ትንሽ ነቃ አሉ:: ከአንድ ልዩ የሕልም ዓለም ውስጥ የወጡ መሰላቸው::

«ኧረ ምን እየሠራን ነው? አሁን የውጭ ሰው ቢመጣ ምን ይለናል? በእርግጥ የሚያደርጉ ነገር በሕልም ስንኳ የማይደርስ እብደት ዓይነት መሆኑ ይሰማቸዋል:: አሁን ማ - ይሙት የሚያጣጥር ቊስለኛ ውጭ አጋድሞ፥ ልቅሶ አይሉት ዘፈን፥ ዙሪያ ከቦ በክራር ማንጕርጕር እብደት እንጂ ምን ይባላል:: ግን ሊያቆሙ ደግሞ አልቻሉም:: እንደ አዚም እንደ ምትሃት በአንድ ኃይል ተይዘዋል:: ምስማር እንደ ሚስብ መግነጢስ በልዩ ሥውር ኃይል ተጠምደዋል:: ከክራሩ እንጕርጕሮ ጋር የሙሔን ሁናቴ ባስተዋሉ መጠን የያዛቸው አዚም እየባሰባቸው ሄደ:: በሕመም ሲሠቃይ የሰነበተው ሙሔ አሁን ፊት ልዩ ፍካት ይታይበታል:: የመርካት የመደሰት ስሜት ይነበብበታል:: ሌላው ቀርቶ ገርጥቶ የነበረው

ደሙ የተመለሰ ይመስላል። ዓይኖቹን ከደን አድርጎ እንጉርጉሮውን ሲያዳምጥ ከንፈሮቹ በፈገግታ ገለጥ ይላሉ። ጠቅላላ ገጽታው በሞት ጣዕር ላይ ሳይሆን መልካም፥ ሕይወት በማገጣጠም ላይ የሚገኝ ሰው ዓይነት ነው።

ካሣሁን እንጉርጉሮውን በአምባሰል ቅኝት ቀጠለ

አያ በለው በለው፥ አያ በለው በለው፥

አይቼ ልደስት፥ ስታንከባልለው።

ኸረ በለው፥ ኸረ በለው፥

ኸረ በለው፥ አትለውም ወይ፥

እወዳለሁ ጀግና ዘወትር ገዳይ።

ሸህ ገድሎ የሚገባ በአንድ ቀን ጀንበር፥

ኸረ ጕራው ኸረ ጕራው፥

እወዳለሁ ጀግና የማይነብር።

ኸረ ጕራው ኸረ ጕራው።

ጦም ውሎ ጦም አድሮ እየተጋደለ፥

ላገሩ ጀግና ነው፥ ተገን የተባለ።

ጕራው፥ ጕራው፥ ጕራው።

ከጀግና ሰው በቀር በየጕራው ገዳይ፥

ከኔ ጋር አይውልም፥ የመንደር አውደልዳይ።

ጕራው፥ ጕራው፥ ጕራው።

«ግን ከዚህ ላይ ቁሞ - ነገሩ ሸህ ከመግደሉ ላይ አይደለም» አለ ሙሔ በተዳከመ አንደበት። «እኔ መሆነኛ ተራራ ላይ የተገለጸልኝን እውነት እናንተም ልጆችና ወንድሞች በልባችሁ ልትይዙት ይገባል። እርግጥ ጀግና ይገድላል። ግን ፈሪኢ ደግሞ የበለጠውን ሕይወት ያጠፋል። ጀግና አዛኝ ነው። ጀግና ማለት ርኅሩኅ ነው። መግደልም ቢኖርበት ሕይወት ማጥፋት ደስ የማይለው ነው። ስለዚህ ለክብራችሁ ስትሉ፥ ለነጣነታችሁ ስትሉ ብትሞቱም ግድ የለኝም ስል፤ ሳይነኳችሁም አትንኩ። በጕልበታችሁ ተማምናችሁም ሌሎችን ለማጥቃት አትመኙ። ሕይወት ለማጥፋት አትጣደፉ። ፈሪ ብቻ ነው የሚጣደፍ። ከፍርሃቱ ያመለጠ እየመሰለው። ፈሪ ብቻ ነው ጨካኝ። በጨለማ የሚያየው ጉቶ ሁሉ የሚባላ አውሬ እየመሰለው። አዎ፥ ሸህ የገደለ ጀግና ነው። ጠላቱ እሱን ጨርሶ የማያጠፋው ከሆነ፤ የሀገሩ ነፃነት የማያሳጣበት ከሆነ፤ ጕድቶ የማይጕዳው መሆኑ ካወቀ ሸህ ሕይወት፥ ያዳነም ጀግና ነው።

የሚጐዳውንና የማይጐዳውን የማያይ ፈሪ ብቻ ነው። መሆነኛ ተራራ ላይ ያየሁት እልቂት ይህንን እውነት አሳየኝ። እና፥ የፍርሃት ጭካኔን ከጀግንነት አትቊጠሩት።» አድክሞት በስሱ ተነፈሰ።

ጊዜው መምሸቱ፥ አየሩ መለወጡ የታወቃቸው፥ ዝናም መጣል ሲጀምር ነበር። «ኧረ እንግባ!» አለ ከበደ፥ ተሸክመው ለማስገባት ወንዶቹ ወደ ሙሔ እየቀረቡ።

«ዝናም ውስጥ። ብርድ ለቊስልኮ መጥፎ ነው።»

«ጠል ነው። ተጠምቄበት ልሂድ። ከዚህ ሌላ አላስቸግራችሁም።»

ዙሪያውን ቆመው ጥቂት ቆዩ። ዝናሙ እየበረታ ሄደ። ጨረቃዋ በዳመና ተሸፍና ለዓይን ይዞ ስለ ነበር፥ ሙሔን በዳንሳ አንሥተው ወደ ቤት ይዘውት ገቡ። አሁን አልገባም ብሎ የመቃወም ድምፅ አላሳማም።

በእሳት ብርሃን ወደ አልጋው ሲያዛውሩት ሁሉም ክው አሉ። ዓይኖቹ ተከድነው አስደሳች፥ ሕልም እንደሚያይ ከንፈሮቹ ገርበብ እንዳሉ ናቸው። አንድያውን አሸልቧል።

«ዋይ! ዋይ! አባዬ!» ስትል ዘይኔ ጮኸች። ከፍ አድርጋ ይዛው የነበረውን የሚነድ እንቸት ወደ ምድጃው እየወረወረች።

«አይዞሽ! አይዞሽ! ግንኮ የሚያስለቅስ ሞት አልሞተም» አለ ካሣሁን፥ ትከሻዋን አቀፍ አድርጎ።

ማዕበል ፪፥ የአብዮት መባቻ ተፈጸመ።

ማዕበል ፫፥ የአብዮት ማግሥት ይቀጥላል።

ማዕበል ፬፥ የአብዮት ዋዜማ አንብበዋል?

Amharic Books t.me/amharicbookss